ዘነበ ወላ

ልጅነት

ልቦለድ
2000 ዓ.ም

የመጀመሪያ ሕትመት መጋቢት 2000 ዓ.ም
የሁለተኛው ሕትመት ሰኔ 2000 ዓ.ም

© ዘነበ ወላ ወጋ

ኢሜል Zenebewola @ Yahoo.com.
የመ.ሣ.ቁ 25360 ኮድ 1000 አዲስ አበባ

ሙሉ የባለቤትነት መብቱ የተጠበቀ ሆኖ በጽሑፍ ከደራሲው በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር፣ ይህን መጽሐፍ እንደገና ማሳተም፣ መቅዳት ወይም ሙተርጎም አይቻልም።

ያለ ደራሲው የጽሑፍ ፈቃድ ወይም የቅጂና ተዛማጅ መብትን ከደነገገው አዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ ምንም አይነት ክፍል መልሶ ማሳተም፣ መቅዳት ወይም በሌላ በማንኛው ዓይነት ዘዴ ማባዛት፣ ማሠራጨት አይፈቀድም።

ከዚህ የሕትመት ውጤት ጋር በተያያዘ በባለቤቱ (ደራሲው) እና በሕግ ያልተፈቀደ ተግባር የሚፈጸም ማንኛውም ሰው በደራሲው (ባለቤቱ) ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ኃላፊ ነው።

የሽፋን ስዕል፦ ነገደ ኃይሌ
የሽፋን ዲዛይን መስከረም ጉሳዬ

ከመድፍ ቀረሽ ሰላምታ ጋር!!!

ለአባቴ (*ሁዱጋ) አቶ ወላ ወጋ
ለእናቴ (*ኤሲቪሬ) ወ/ሮ ወርቅነሽ ባላ
ለዶ/ር ተወልደብርሐን ገብረአዝዚአብሔር
ለዶ/ር ሙሴ ኃይሉ
ለአቶ አሰፋ ጉሣዬ
ለአቶ ወልደገብርኤል አባተ
ለተማሪ አባይነህ ድርጌ
ለዶ/ር አብርሐም ፈለቀ
ለአቶ ሽመልስ አራርሶ

...ሰንቱን አሰታውሼ እችለዋለሁ? ይህንን ሰል እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልጠቀስኳቸው ወዳጆቼ ሁሉ በልቤ እየብሰ ለሰልኳቸው ነው። ወዳጆቼ በሕይወት ያሉም፣ ያለፉም ናቸው። ላለፉት የላሊበላን ፅድቅ፣ በሕይወት ላሉት የማቱሳላን ዕድሜ ይስጥልኝ፤ እየልኩ ይህችን ስንኖራት 'ፉት ቢሏት ሞልጥ' ያለችብኝን ልጅነት፤ ስጽፋት ግን ዓመታት የፈጀችብኝን ትንሽ መጽሐፍ መታሰቢያ ትሆናቸው ዘንድ ሳበረክት ከመድፍ ቀረሽ ሰላምታ ጋር ነው።

ዘነበ ወላ
ከልኤቱ፣ እሥራ ምዕት ጉዘአችን ላይ ተብረከተ
(ቂርቆስ) አዲስ አበባ

---

*ሁዱጋ፣ ቢጋሞ የማዕረግ ስም።
*ኤሲቪሬ፣ በጋሞ የአክብሮት መጠሪያ።

ዕድሜ ከእንጀራ ይሰጥልኝ!!!

ይህችን ልጅነት ሰል ርዕስ የሰጠኋትን መጽሐፌን በርካታ ወዳጅ ቼን፣ ባልንጀሮቼን አሰነብቢያቸዋለሁ። ሁሉም ጊዜያቸውን ሰውተው የሰጡኝ አስተያየት ገንቢ ነው። ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ። በተለይም ፈጠራዬን ከጥንስሱ ጀምሮ ያውቂ የነበረው ጋሽ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ስዘናጋና መጻፉን ችላ ስለው በተደጋጋሚ በማስታወስ፣ አንድ ምዕራፍ እንዳነበለትም በመጠየቅ አትግቶኛል። ራሱ ጋሼ ስብሐት «የአገራችን ዝሬዎች አርሻን ለወይፈን ለማስተማር የሚጠምዱት ልምድ ካለው በሬ ጋር ነው» ያለኝ አባባል በዚህች ትንሽ መጽሐፍ ላይ እውነት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የአርትኦት ሥራውንም አግዝኖል።

ባለቤቴና የልጆቼ እናት ወይዘሮ ፀሐይ በላቸው ፀሐፌ በመሆን ለሰጠችው ግልጋሎት ከፍተኛው ምሥጋናዬ ይደረሳት።

ኮምፒዩተራቸውን እንድሠራብት በመስጠት ለተባበሩኝ ጓደኞቼ ለአቶ ጥምቀት አለማማውና ለአቶ እስክንድር ኃይሉ ላደረጉልኝ እገዛ ልባዊ ምሥጋናዬን እያቀረብኩ፣ ቸርነታቸውን ስመዝነው ለእንዲህ አይነቶቹስ አምላክ ከበረከቱ አብዝቶ በሰጣቸው አሰኝቶኛል።

ጋሼ ስብሐት ሲጽፍ «እኔ ቤቴ የምለውን ዓይጥ አገሬ ትለዋለች» ይላል። ለእኔ የአገሬ ድንበር የሚጀምረው ከቤቴ ነው። የቤቴ ጌታ (አከራዬ) አቶ ተስፋዬ እሸቱ ከመላው ቤተሰቡ ጋር ለሰጠኝ ሰላም ከምሥ ጋናዬ ድርሻ አለው። ከእነዚህ ወዳጆቼ መካከል አንዱ ቢጓደል አትጠራ ጠሩ። ይህችን ሙከራ አናደትም ነበር። ይህንን መጽሐፍ አንብባችሁ ከወደዳችሁት ላቅ ያለውን ምሥጋና ለቡድን አባሎቼ አቅርቡልኝ። የጐደለ ካለም ተወቃሹ እኔ ነኝ።

ሁለት ሺህ ዓመተ ምህረታችንን እያከበርን ነው። ለአገራችንም ሆነ ለምድራችን ሰላም የበኩላቸውን ለማድረግ ያጣሩትን ሁሉ ሳስባቸው በፍቅር ነው። ለሁሉም እሱ አይመረመሬው የሃሳባቸውን እንዲከውኑና በአገራችን ሥልጣኔ ላይ የበኩላቸውን እንዲያዋጡ ጤና፣ ዕድሜና እንጀራ ይስጥልኝ።

ዘነበ ወላ
ጥር 2000 ዓ.ም
ቂርቆስ አዲስ አበባ

ማውጫ

ተ.ቁ		ገጽ
1.	ፈጣሪና ፍጡር	7
2.	ሀሁ	18
3.	ወደ ሐኪም ቤት	26
4.	ወላጅ አንደ ሐኪም	32
5.	ባልና ሚስት	42
6.	ከሀሁ እስከ ወንጌል	46
7.	ጅሮ ቆራጭ	54
8.	ቤት ለአንባዳ	64
9.	ይህች ምራቅ ሳትደርቅ	73
10.	ሰኖ	78
11.	ዓይነጥላዎቻችን	84
12.	መጣና ጌታችን ላመት ከብራችን	101
13.	ወደ ሙቪ	106
14.	ተራኪው	111
15.	የልደት ስጦታ	118
16.	ሌባና ፖሊስ	127
17.	ዕንቁጣጣሽ	134
18.	«በሶውን ልብ»	143
19.	መጫወቻ ፍሊጋ	145
20.	ትንቢት	152
21.	ይዋጣላቸው	155
22.	ሽቀላ	161
23.	ክርስትና አባት	173
24.	ዕርቀ ሰላም ቢወርድ	179
25.	ካምቦሎጆ የማይዝ ተመልካቾች	183
26.	ዘለአለማዊነት	188
27.	ቢንዝል በአገራችን አገኘን	198
28.	አድባር	203
29.	ኪስ አበደች	210
30.	አባባ ጀንሆይ	216
31.	ድንቡተኛው ክለብ	218
32.	የታሰረው ጋኔን	224
33.	ፋኖ ተሰማራ	239
34.	ምትሀተ መስኩት	243
35.	ንባብን በተበብ	248
36.	ምሥጢር	252
37.	መውሊድ	258
38	የቴያትር ሀሁ	267
39.	ውዝዋዜ	270
40.	ምሕረት	274
41.	ፍተሻ	278
42.	ጥናት	282
43.	ኩረጃ	294

መግቢያ

ኧረ ልጆች! ልጆች! እንጫወት በጣም
ከእንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም
ልጅነቴ! ልጅነቴ! ማርና ወተቴ

***

ልጅህን በሚሔድበት መንገድ ምራው በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።

መጽሐፈ ምሣሌ 11:16

***

ዕውቀትን ከአንቀልባ እስከ መቃብር ዘመን ፈልጓት።

ነብዩ መሐመድ (ሰ.አ.ወ)

***

ልጅህን በቀን አንዴ ግረፈው። አንተ ምን እንዳጠፋ ባታውቅም እሱ ያስታውሰዋል።

የቻይናዎች አባባል

***

«የክዙር ስው ጣዕመ መዓዛ እስከ ዓለምዳርቻ ይደርሳል»

ገድለ ክርስቶስ ሰምራ

***

«ሕፃናትን በእጆቻችን ልናቅፋቸው ባንችል በልባችን እንቀፋቸው»

ሪደርስ ዳይጀስት

***

«ለንዑሃን ሁሉም ነገር ንፁህ ነው»

የአረቦች ምሣሌ

***

ልጆቻችሁ በእናንተ በኩል መጡ እንጂ ከእናንተ አልመጡም።

ካህሊል ጊብራል

***

«ተረት ተረት»
«የላም በረት»
ሆድህ ይተርተር በብረት»

እማዬ

***

ልጆቻችንን ዓይናቸውን ገልጸው እንዲያልሙ እናስተምራቸው

ስሙን የዘነጋሁት ወሐፊ

***

እንቡሼ ገላ የአብሽ ገለባ
ሜዳ ነው ብዬ ገደል ስገባ
ገደል ገብቼ ልወጣ ስል
ጅቡ መጣብኝ ከቂጤ ሥር...

ፈጣሪና ፍጡር

አያቴ አንጥረኛ፣ አባቴ ሸማኔ
ወንድሞቼ ቀጥቃጭ፣ አዝማሪ ነኝ እኔ
ቤተሰቤ ሁሉ የእጅ ሙያ አላቸው
ለእናት አገራችን የሚያኮሩ ናቸው
ድምፃዊ ታምራት ሞላ።
ግጥምና ዜማ -ቶማስ አበበ።

ፋንጋይ ብላችሁ ልትጠሩኝ ትችላላችሁ። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመኳቸው ሰዎች አባትና እናቴን ነበር። የአባቴ ቁመናና መልክ አሁንም ትውስ ይለኛል። ዜራሞ ኢንቻ ጠይም፣ አጭርና ወፍራም ነበር። አዘውትሮ የሚለብሰው ሹራብና ቁምጣ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ ስንደል ጫማ ይጫማ ነበር።

በሰንበት ቀናት ነጭ በነጭ ተፈሪ ቅድ ጠባብ ሱሬውን ይታጠቅና ከላይ ረጅም ቀሚስና ሹራብ ለብሶ በላዩ ላይ ሳሪያን ኩቴን ይደርብበታል። ነጭ በነጭ ወይም አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ነጠላ ከላይ ይከናነባል። ጥቁር ወይም ነጭ ጫማውን ይጫማል። ስድስት ባትሪ ጎራሽ ሬዲዮም ነበረን። ይህንን ሬዲዮናችንን ዳንቴል ያለብስና እንግቶት እስከ መጨረሻው ከፍቶት ይንሸራሸራል። እኔንም የክት ልብሴን አልብሶኝ በሚንሸራሸርበት ሁሉ ያስከትለኝ ነበር። ሬዲዮናችን ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ እያንባረቀ ዕቁብ ወደሚጥልበት አጎራባች ቤት ተያይዘን እንሄዳለን። ብዙም ሳንቆይ ሬዲዮናችን የዕለቱን ዜና እወጃ መጀመሩን ያበስረናል።

«እንደምን ዋላችሁ ዜና እናሰማለን። ዜናውን ምሰሰማችሁ አሳምነው ገብረወልድ» ነኝ ሲል ጋዜጠኛው ጆሮ ገብ በሆነ ድምፅ የታዳሚውን ቀልብ ይገዛል።

ከዕቁብተኞቹ፣ እንዳንዶቹ፣ «ዛሬር ይመስጣን» በማለት ለሬዲዮና ችን እጅ እየነሱ ምላሽ ይሰጣሉ። ሁሉም ታዳሚዎች ዜናውን ለማድመጥ በእድናቆት ያቆበቁባሉ።

«በቅድሚያ ርዕሰ ዜናዎቹን እናሰማለን። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በግብፅ፣ በሶቪየት ኅብረት፣ በቼኮዝላቫኪያ፣ በዜልጅግ፣ በፈረንሣይ፣ በፖርቱጋልና በዩጎዝላቪያ ያደርጉት የነበረውን አፈቤላዊ ጉብኝት አጠናቀው ትናንት እኩለ ሌሊት ላይ መናገሻ ከተማቸው ገብተዋል» ሲል ቀደም ብሎ በጫጫታ ተሞልቶ የነበረው ቤት ዐጥ ረጭ ይላል። ዕቁብተኛው ሁሉ ጆሮ የሆነ ይመስል ቀልባቸው በሬዲዮኑ መልዕክት ይገዛል። ዳኛው ብር ከዕቁብተኛው እየተቀበለ መቁጠሩን አቁመዋል። ፀሐፊው ብዕሩን እንደቀሰረ ያደምጣል። የዕቁብተኛው አስተናጋጅ እማማ ብርሌ የጠላ ማንቆርቆሪያቸውን እንደያዙ በሣሎኑና በጓዳው መካከል ባለው በር ቀጥ ብለው ቆመው ያደምጣሉ።

ጋዜጠኛው የዕለቱን ዜናዎች ርዕሰ ጉዳይ ካሳወቀ በኋላ ትንተ ናውን በሰፊው ተያያዘው። ሁሉም እወጃው ቀልባቸውን ስቦት ሬዲዮኑ

የሚያስተላልፈውን ዜና በትኩረት ይከታተላሉ። ወገም ከያለበት አይፈ ልቅም፣ የሰላምታ ልውውጥም የለም፣ ብርጭቆ እንኳ አይንኳኳም፣ የዜና እወጃው በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እስኪደርስ ለአድማጭ ሁሉ የሕይወት ምንጭ መረጃው ሆነ።

አዲስ አበባ፡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተፈጥሮ አደጋ ለተጉዱ የፓኪስታን ዜጐች ሰባት ሺ ፓውንደዲዕርዳታ ላኩ።...

ኒውደልሂ፣ በሕንድ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ የደቡብ ራጅስታን ገዛት የ620 መንደር ነዋሪዎች ሕዝብሥበችጋር የሚሰቃይ መሆኑን የደረሰን ሪፖርት አመለከተ።

ጋዜጠኛው የዕለቱን ዜና በሚያስገመግም ድምፁ አንቆርቁሮ ሲያበቃና «በሰላም ዋሉ» ሲል፣ «አሜን እናንተም በሰላም ዋሉ» ብለው ታዳሚዎቹ ምላሹን ለሬዲዮኑ ይሰጡታል።

«ሰባት ሺ ባውንድ አስር አስር ብሩ አንድ ሁለት ተብሎ ሰባት ሺ ባውንድ ሞልቶ ነው የተላከው?» አባቴ በጣም ግር ብሎት ጠየቀ።

«ቢሆንስ ምን ችግር አለው? አገራችን ማሩን፣ ውተቱን ታፈልቃለች ከዚያ ላይ ቆንጥሮ መላክ ነው» አሉ የዕቁቡ ዳኛ።

«አቶ ዜራሞ፣ ፓውንድ አንጂ፣ ባውንድ አኮ አይደለም ያለው አሳምነው። ፓውንድ የእንግሊዝ ገንዘብ ነው። አንዱ ፓውንድ ወደ እኛ ገንዘብ ቢመነዘር በትንሹ 5 ብር ሊሆን ይችላል» አለ የዕቁቡ ፀሐፊ በአዋቂ መንፈስ።

«ኃይሉ፣ አሱስ ቢኖር አይደል? ብቻ አግዚአብሔር ከዚህ መዓት ይጠብቀን» አለ አባቴ።

«ምን ይመጣል? አገራችን ለምለም ነች። ሰላም አለን። አንሠራለን። ታለም መንግሥታት ጋር በልማት አንወዳደራለን። ፓኪስታንና ሕንድ ግን ሰላም የላቸውም በጦርነት ይፋጀሉ። ሳርፋም፣ ችጋሩም ይጨክንባቸዋል» አለ ፀሐፊው በርግጠኝነት።

«ኃይሉ፣ እህል ሰንል አንድ ነገር ትዝ አለኝ። በቀደም በቾ ነበርኩ» አሉ ዳኛው ከአፋ ነጥቀው። «እህሉ ጥንቡን ጥሏል። የሚሸምተውም የለም። ምን የመሰለ ማኛ ጤፍ አንድ ኩንታል በአሥር ብር ሸመትኩ። መኪና አራት ሽልንግ አስከፍሎኝ አዲስ አበባ ይገፍ ገባሁ።»

«ይኸውልዎት፣ እዚህ ጥንቡን ጣለ የሚሉት እህል እዚያ የለማየ ለማያት ያህል የራቀ ነው» አለ ፀሐፊው።

«እግዚኦ! እዚህ አገራችን የሚበላው የጠፋ እህል እዚያ ተራቡ ማለት ነው?»

«አመብርሃን!»

«አንተ ከየት አገኘኸው ይህንን ወሬ?»

ወደ ሬዲዮኑ ጣቱን ጠቆመ።

ይህን ጊዜ ስለ ሬዲዮ አሠራርና አፈጣጠር ሁሉም የመሰ ለውንና የሰማውን መሰንዘር ይጀምራል። በመጨረሻ የሚደርሱበት ጭብጥ «አባ ጠቅል ምን ይሰነዋል? ትልቁን ጋንጩር አቡነ ጴጥሮስ ሃውልትጋ አስሮ ውሎውን ያስለፈልፈዋል» ይላሉ።

አንዱ ከጓላው ቆመጥ ይዘው ያሳደዱት የሚመስል ጋዜጠኛ በሬዲዮ ማውራት ጀመረ። ቤቱ ውስጥ ዕቁብተኛው አንደገና ሠጥ አለ።

«... *ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ሙሉ የሥልጣኔ ዕድገት በማብሰር የሰሞኑን አፈሴሊያዊ ጉብኝት ልክመ ልክቶ ለመላው ሕዝባቸው ያደረጉትን ታሪካዊ ንግግር አሁን እናሰማለን።*»

አባባ ጃንሆይ መናገር ጀመሩ።

«*የምንወድሆና የምትወደን ሕዝባችን ሆይ፣ በተደረገልን የወዳጅነት ጥሪ መሠረት ያደረግነውን ረጅም የጉብኝት ጉዞ ፈፅመን በለሁል እግዚ አብሔር ቸርነት በምንናፍቀውና በሚናፍቀን ሕዝባችን መካከል ተመልሰን በመገኘታችን እጅግ ከፍ ያለ ደስታ ተሰምቶናል።*»

ትልልቆቹ ሰዎች ፈገግ ብለው፣ ሙሉ ትኩረታቸው በአባባ ጃንሆይ ንግግር ተይዟል። አባባ በቀስ ሲጋራ ሲለኩሱ ቀልቤ ተሳበ። አንዲም ሳይሰቡለት አመዱ አየረዘመ እየረዘመ ሄደ። አሳቸው ሙሉ በሙሉ ጆሮ ሆነዋል። አባባ ጃንሆይ አሁንም እየተናገሩ ነው።

«*ከዚህ ቀደም... ካደረግናቸው ጉብኝቶች በተመለሰንበት ጊዜ የተ ደረገልንን መልካም የወዳጅነት አቀባበልና ያሳደረብንንም ሰሜት ገልጠ ንላችሁ ነበር። በአሁኑ ጉዟችን ከዝገኘናቸው አገሮች መንግሥታት መሪ ዎችና ከሕዝቦቻቸውም የተደረገልን አስደናቂ አቀባበልና የተገለጠልን እውነ ተኛ የወዳጅነት ሰሜት ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር ስለሆነ የደስታችንን ሰሜት ልናካፍላችሁ ወደድን።...*

የአባባ በቀስ ሲጋራ ልትከስም ቁራጭዋ ላይ ስቀር ጣታቸውን ቅጥል አደረገቻቸው። ልክ ጉንዳን እንደነከሳቸው ሁሉ ከጣታቸው ወደ መሬት ጥለዋት በጫማቸው አወደሟት። አባባ ጃንሆይ አሁንም እየተናገሩ ነው።

«...*ምድረ ግብፅን ከረገጥንበት ጊዜ አንስቶ በየሔድንበት ሥፍራ ሁሉ ከመንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ከሕዝቡ የተደረገልን ከፍ ያለ አቀባበልና የተገለጠልንም ከልብ የሆነ የወዳጅነት አስተያየት ከፍ ያለ የደስታ ሰሜት አሳድሮብናል።*»

እስካሁን አብሮን የነበረ አንድ የኮሌጅ ተማሪ ምንም ሳይል ምንቅር ብሎ ወጥቶ ሄደ። አባቱና የዕቁቡ አድምተኞች በመገረም አንዴ ቀና ብለው አይተውት እንደገና ጆሮአቸውንና ቀልባቸውን ወደ ሬዲዮኑ መለሱ። አባባ በቀለም ሌላ ግስላ ለኩ።

«...*እንደምታውቁት ግብፅና ኢትዮጵያ ያላቸው ግንኙነት በመቶ ሳይሆን በብዙ ሺህ ዘመናት የሚቆጠር ነው። የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች የቅርብ ጎረቤቶች ከመሆናቸውም በላይ፣ ከአንድ ወንዝ ውሃ የሚጠጡና ተመሳሳይ ባህል ያላቸው ሲሆኑ ብዙ የሚያስተሳስሯቸው ግንኙነቶች አሉ።...*»

እማማ ብርሌ የቀዱትን ሻይ ለዕቁቡ ፀሐፊ ቀስ ብለው አቀበሉት። በዝግታ ተቀበላቸው። በግንኪያ ስኳር እየሰፊረ ሻዩ ውስጥ ይጨምራል። አፈን የሚማፍጥ ምራቅ ሞላው። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ማንኪያ ስኳር ጨመረ። «አሁን ፉት ሲለው በጣም ይጣፍጠዋል» አልኩና በሆዴ አሰብኩ። እሱ ግን እያግሰለ ጃንሆይ ወደሚያወሩለት

አባቴ ከፊደል በፊት የራሱን የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንድለይ ያደረገኝ በበለጠን ጥበብ ነበር። አንድ ቀን ሸማ እየሠራ ከአገሩ ልጅ ጋር ሲጨዋወቱ ቆይተው ይነጎባበታሉ። አባቴ እዚያው በተቀመጠበት ያልቋጨው ጉዳይ ስለነበረው «ጎንጀባ ሃያ! ሃያ!» አለ።

«ዜራሞ ሃያ! ቁጥር ነው?»

«አይደለም! አይደለም! ፉንጋዬ? ዛሬ የዘሮችህን ቋንቋ የምትጠ ይቅበት ዕድሜ ላይ ደረስክ። ጥፋ ነው። ተመስገን። አንተም አታላ ግጥብንም እኛም አንላቀቅም። አንድ ላይ የምንግባባበት ቋንቋ ይኖረ ናል» አለና የዘር ግንዘሬን፣ የምንጅላት፣ የቅንጅላቴን ቋንቋ ማስተ ማሩን ጀመረ።

«ሃያ ፉንጌ።»
«ምንድን ነው?»
«ና እያልኩህ።»
ተጠጋሁት።
«ባ!» አለኝ በአጭ አንድርቅ አያመላከተኝ።
«ምን ማለት ነው?»
«ሂድ እያልኩህ ነው።»
ራቅኩት።
«አታ።»
ዘም ብዬ የእጁን ጥቆማ በማየት ተቀመጥኩኝ።

«ትክክል! ተቀመጥ እያልኩህ ነበር» አለና የመምህርነቱ ውጤት ስላረካው ፍንድቅ አለ።

በየዕለቱ የሚያስተምረኝን ቃላት ገጣጥሜ በደንብ መናገርና ማድመጡን እየቻልኩበት ሔድኩ። አናቴም በአስተማሪነቱ ትሳተ ፋለች። በዚህም ጥረታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ቋንቋው እየተዋሃደኝ መጣ። በዚህ መልክ ከቤተሰቤ ጋር በዘሮቻችን በጋሞ ቋንቋ መነጋገር ተሳካልኝ።

አባቴ ለልጅ ተረት ማውራት አያውቅበትም። ጨዋታን ጨዋታ ሲያመጣው ተረቱን አዕምሮው ለወጉ ብሚለማማው መልኩ ያፈልቅ ለታል። የተረትን ያህል በሚጥም መልክ ስለራሱ መራርና አስደሳች ሕይወት መተረክ ግን አላምሮ ይችልበታል። በዚህ የማሳደግ ዘዴው ነበር ገና በልጅነቴ አባቴን በደንብ ያወቅኩት።

በአባቴ የሽመና ሥራ አመቺነት ብዙውን ጊዜ የምናሳልፈው አብረን ነበር። ዛሬ ይህን የሕይወቴን ምዕራፍ ስተርክላችሁ፣ በዚያኔው የልጅነት ሕይወቴ በርካታ ወጎችን አየተጨዋወትን፣ ከሥራ ነፃ ስንሆ ንም እየተሳፋን በፍቅር አብረን ማሳለፋችንን በደንብ አስታውስዋለሁ።

አባቴ ትንሽ ጠጅ የቀማመስ እንደሆነ ባሕርዩ ይለወጣል። የኢጣሊያን ጊዜ ቂሙን ይቆስቁስና ከእናቴ ጋር ንትርክ ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ቆንጆ ምሽግ ከሆነችው አልጋዬ ላይ እወጣና አደፍጣለሁ። ለእኔ በማይዝነኝ ሃሳብ ቲነታርከው ምሽቱ ሲገፋ ተኳርፈው ወደ መኝታቸው ያዘግማሉ።

ሕይወት አንዳንዴ መራር እንደምትሆን እየገባኝ የመጣው በዚያው በጨቅላነት ዕድሜዬ ነበር። ንትርካቸው ከፍቶ ድምፃቸው እውጪ ከዘለቀ በቅርብ ያሉ ጎረቤቶቻችን፣ (በአብዛኛው የክርስትና አባቴ አባባ ኃይሌ) ይመጡና እርቀ ሰላም እንዲወርድ ያደርጋሉ።

በወቅቱ ያ ሕይወታችን አብዛኛውን ጊዜ ጨዋታ ቢመስለኝም፣ አሁን ሳስበው ለኔ የምርምር የማወቅና የመጠበብ ጊዜም ነበር። ያለፈውን ቀን ንትርክ ትንሽዋ ልቤ አትረሳውም። አባቴ ግን ረስቶት በሚቀጥለው ቀን ከወገቡ በላይ ራቁቱን ይሆንና አልጋ ላይ በደረቱ ተኝቶ «ጀርባዬን እከክኝ» ይለኛል። በዚህ ወቅት የአስተካከክ ስልቴ ይለወጣል። አባቴ «አምን! እሱጋ!» ሲለኝ፣ ያልበላው ጎኑ ላይ አከዋለሁ።

«አሁን ምንድነው ያልኩህ?» ይለኛል ቢጋሞ ቋንቋ፣ በግማሽ ጎኑ ቀና እንደማለት እየከጀለው። «ለእናትህ አግዘህ ነው? እረፍ!» ይለ ኛል። አባቴ «ጋሼ! አንተን አያገባህም። በእኔና በእሷ መካከል አትግባ» ብሎ ገስጾኝ ተመልሶ ይጋደማል። «ጋሼ» ሲለኝ ሁሌም በማላዥ ስሜት ነው። እኔ ግን ያገባኛል በሚል ስሜት፣ የበላሁ የጠጣሁትን ያክል ጀርባውን ቡጥጥ አደርገዋለሁ።

«ዋይ!» ብሎ ዘሎ ይነሳል።

እኔም ተፈናጥሬ ከአልጋው እመሬት እወርዳለሁ።

«ብታርፍ ይሻልሃል! እከክልኝ አልኩህ እንጂ ማን እንደ ድመት ቧጭረኝ አለህ?»

ብዙ ተለማምጠኝና አግባብቶኝ እንታረቃለን። ጨዋታ እንጀ ምራለን።

«ዜራሞ፣ እኔ፣ አንተና እማዬ እንዴት ተገናኘን?»

«በጣም የሚገርም ነው» ጥያቄዬ ቀልቡን ይስበዋል።

«እኔ ለምን የአባባ ጃንሆይ ልጅ አልሆንኩም?»

በመገረምና በመደነቅ ፈገግ ይላል። «ባሎቴ ትሰሚዋለሽ ልጅሽ የሚጠይቀኝን?»

እማዬ ጓዳ የዕለት ሥራዋን እያከናወነች ነው። ትኩረቷ ሥራው ላይ በመሆኑ መልስ አልሰጠችንም። አባቴ ወደ እኔ መለስ ብሎ በፈገግታ እያስተዋለኝ «ጋሼ፣ ይሄ የእኔም የጃንሆይም ጉዳይ አይደ ለም። ሁሉን የሚያከናውነው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህንን አሁን የምንግርህን ጨዋታ ጤናህ ተስተካክሎ መማር ስትጀምርና ነፍስ ለታውቅ ትምህርትህ ውስጥ ታግኘው ይሆናል። እኔ ግን ስንሞት እኔ እናትህና አንተ የተገናኘነው እንዲህ ይመስለኛል...» በጥንቃቄ፣ ዝግ ባለ አንደበትና በውብ የአተራረክ ዘዴ ወጉን ይቀጥላል።

እኔም በፀጥታ አደምጠዋለሁ።

«እግዚአብሔር በወርቅ ዙፋኑ ላይ ተቀምጧል። እናንተ ሕፃናቱ ደግሞ እርሱ እግር ስር ተደርድራችሁ ተቀምጣችኋል። ከዚያም እግዚአብሔር በስማችሁ እየጠራ፣ 'ፉንጋይ አንተ ዜራሞና ባሎቴ'ጋ ሂድ!' ሲልህ ወደ እኛ ትመጣለህ። 'መኮንን አንተ ደግሞ ጃንሆይ'ጋ

ሂድ!' ይላል እግዚአብሔር። ጓደኞችህን ቀጢሳውንም፣ ሲሳይንም፣ መኩዬንም እንዲሁ ወላጅ እንድንሆናችሁ ያደለናል። በዚህ አይነት ሁኔታ ነው የተገኘኘነው። አንዱን መሪ፣ ሌላውን ተመሪ የሚያደርገው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሁላችንም ግን እሱ ፊት እኩል ነን። ገዢ ተገዢ የለም። ሁላችንም የእሱ ፍጡራን ነን» እያለ ከእኩያው ጋር እንደሚያወጋ ሁሉ ትንታኔውን ይጨምርበታል።

እናቴ የእግር ውሃ አመቃ ዐሳህን አድርጋ ሰጠችን። አባቴም ቀና ብሎ አያወጋኝ ለመታጠብ እግሩን ሳህኑ ውስጥ ጨመረ። «ዋይ! ምነው ባሎቴ? ዶሮ ነኝ እንዴ? በይ ቀዝቃዛ ውሃ በርዢልኝ።»

እየሳቀች በረዘችለት።

የእኔን እግር መጀመሪያ አጠበ። የራሱን እየታጠበም «ይኸው ልህ የኔ ጎረምሳ በዚህ ሁኔታ ነው የተቀመቅነው።»

«ዜራሞ፣ አቤት! ብዙ ነገር ታውቃለህ። ስንት ዓመትህ ነው?»

«ጋሼ፣ አውነቱን ልንገርህ? እናትህ ታሳቂ ነች።» አለኝ ፈጣሪዬ እንደ እግዚአብሔር ዕድሜ አልባ ሆነብኝ።

እናቴ ባሎቴ ጋጋ ትባላለች። እማዬን እምዬ ማርያም ፊቷ ላይ በርካታ ቦታዎች ላይ ስማታለች። ጠይም፣ አሞር፣ ቀጭን ሆና በሥራ ላይ አንደ ጉንዳን ኃያል ፍጥረት ነች። በርካታ ሥራዎች አሏት። እንጀራ ትጋግራለች፣ ጠላ ትጠምቃለች፣ አረቄም ታውጣለች። ሌሊት ከእንቅልፏ ተነስታ ቀኑን ሙሉ እንደሸማኔ መወርወሪያ ከወዲያ ወዲህ ቱር- ቱር ስትል ጀምበር ትጠልቃለች። አንዳንዴ ዕኩለ ሌሊት ላይ ነው የዕለት ተግባሯን የምታጠናቅቀው።

ነፍስ አውቄ እናቴን ሳስተውላት ሁሌም የማውቃት አንዲህ ስትባትል ነበር። ሞልቶላት ተዝናናች ቢባል የአሥር ሣንቲም ቡና ገዝታ አፍልታ፣ ጉረቤቶቻችንን ጠርቼላት፣ ቤት ያፈራው ቁርስ ቀርቦ፣ አብራቸው ታድማ አንድ ሰኒ ቡና በጠጣች ጊዜ ነው። ይህ ለሷ ከፍተኛ የመዝናኛ ዓለም ነበር። ቡና እየጠጣችም የምትፈትለው ጥጥ ወይም የምታዳውረው ልቃቂት ከእጇ አይጠፋም። ሕይወት ለእሷ ምንጊዜም ሥራ ነው።

አንዱ ሕፃን ድንገት ቢጮህ «ፉንጋይ!»

«እኔ አይደለሁም ቀጢሳውና ሴምላል ተጣልተው ነው» ስላት፣ ክንጇ ላይ ተለቅልቆ የደረቀ ሊጥ በደህንኛው እጇ አያስለቀቀች ብቅ ብላ «ምን ያጣላችኋል? አንተ ሴምላል አታርፉም!?»

ሴምላል፣ ቀጢሳው የሷጨረውን ፊቱን እያሻሸ፣ ንፍጡን አሁንም አሁንም ሽቅብ እየሳበ ያጉረመርማል።

«ንፍጥህን ችምጋለህ? እንፍ! በልና አውጣው። አይዞህ ይተካ ልሃል» ብላ ሴምላልን ገስጣው ወደ ቀጢሳው ዞራ «አንት ድባኖ! የም ታሸንፈኝ እንዳይመስልህ ብታርፍ ይሻልሃል!»

ቀጢሳው ብዙ ምስራፍ እንደሮጠ ሁሉ ቁና ቁና እየተነፈሰ ሴምላል ላይ እንዳፈጠጠ ነበር። ሁላችንንም ተቆጥታን፣ ተስማምተን

አንድንጨዋወት አስጠንቅቃን፣ ስታበቃ፣ ከቋት ጠብ የማይለውን ሕይወታን ፊር ለማስያዝ በጥድፊያ ወደ ኩሽና ትገባለች።

እናቴ የፈለገውን ያህል ትኩረቷ ሥራ ላይ ቢሆን፣ ሁሌም እኔ በእሷ ዕይታ ውስጥ ነኝ። «እግርህን ስብስብ ወሸላህ እየታየ ነው። ኧረ አፍህን ደግሞ እንዴት እንዴት ነው የምታደርገው?» ብላ ገስጣኝ ጓዳ ትገባለች። እንዲህ ከወዲያ ወዲህ ቱር ቱር እያለች እንዴት እንደ ምታየኝ እየገረመኝ ሳለ ወዲያው ደግሞ አንድ ነውር የምትለውን ነገር አደርጋለሁ። እንዴት እንዳየችኝ አይገባኝም። እኔ ሳያት ጀርባዋን ስጥታኖለች። ዞራ ሳታየኝ «አንተ ልጅ የሚነግሩህን አትሰማም እንዴ? ዋ! ዛሬ' ብታርፍ ይሻልሃል!» ብላ አስፈራርታኝና አስጠንቅቃኝ ሥራ ዋን ትቀጥላለች።

እናቴ ሲሞላላትና ፉታ ስታገኝ ለልጅ ተረት ማውራቱን አሳምራ ታውቅበታለች። ወጋችን ወደ መራሩ ጉዳይ ካነጣጠረ «ይህ የልጅ ጉዳይ አይደለም» ብላ ትዘጋውና ጣፋጩንና ዕድሜ ልክ ውስጤ የሚቀረውን ሌላ ታሪክ ትዘራብኛለች።

«አንድ ጊዜ አባትህ ጥርሱን አመመው። የጥርስ ሕመም እኔ አላውቅም። እሱ ግን ሕመሙ በዘሬ አለ ነው የሚለው። አያትህንም እንደሚያማቸው አጫውቶኛል። አንዴ ታዲያ እኔም ሥራ በዝቶብኝ ሳልከተለው ቀረሁና፣ በጣም እየተሰቃየ አስነቅላለሁ ብሎ ወደ ልዑል መኮንን ሆስፒታል ሄደ። ኡዲያ! የእኔ ሥራ! ሸማኔው ወንዝ ጥርግ አድርጎ እየወሰደው 'አዬ ይሄኔ ቤቴ ብሆን ኖሮ አንዴ እወረውር ነበር' ይላል። እኔም የዚህ ሸማኔ ቢጤ ነኝ፣ በዚሁ ሥራዬ ምክንያት የዚያን ዕለት ዓለሜን ላላይ ቀረሁ።

«ልንገርህ ነው። በሽታው ጠናበትና ሆስፒታሉ አካባቢ እንደ ደረሰ ሜዳው ላይ ተኛ። እዚያ ወድቆ *አባከና የሚለው አጣ። ያኔ እንደ አሁኑ ሆስፒታሉ አጥር አልነበረውም። አባትህ የተኛው ልክ ዋናው መንገድ ዳር ላይ ነው። አንድ ሰው መጣና ከተኛበት ቀስቀ ሰው። እየተሰቃየ ቀና ብሎ ቢያይ አጠገቡ ጃንሆይ ቆመዋል።»

«አባባ ጃንሆይ?!» ተገርሜ ጮኽኩኝ።

«አዎን ጃንሆይ ራሳቸው። ሕመሙ ድራሹ እልም አይልም? አይዞህ አሉና አሁንም የሆነውን ጠየቁት። ጥርሱን አሞት እንደተኛ ነገራቸው።

«ጃንሆይም አብረዋቸው ላሉት ሐኪሞች ዞር አሉና 'አክሙት እንጂ እገሌ' ብለው ትእዛዝ ሰጡ። በጥድፊያ ተንከባክበው፣ በብስክ ሊሊት ወስደው አከሙት።

«በብስክሊሊት አሳፍረው?» ጓጓሁ።

«አዎን በብስክሊሊት። ብስክሌት ብልህ እናንተ ከነከበደ ጋር የምትጫወቱበት አይነት አይደለም። የትልቅ ሰው አለ፣ ተጋድመው በት የሚነዳ። ወስደው አከሙና ሲለቁት፣ የእናቴ ልጅ፣ ጥርስ ሲያም

---

* አባከና፣ በኦሮሚኛ የዚህ ጊታ ማለት ነው።

አሳር ነው የሚያሳየው:: ከተነቀለም ፈውሱ ፈጣን ነው:: እንደ ልጅነቱ እየሟረቀ መቀቶ ሁላችንንም ደስ አሰኘን...»

«ወይኔ! እኔም በኖርኩ:: ብስክሊቷን አብሬው እነዳት ነበር:: ያኔ ግን እግዜር ወደ እናንተ እንድመጣ ገና አልላከኝም ማለት ነው?»

ግር አላት::

እንዲት እንደተገናኘን አባቴ ያጫወቸኝን በአጭሩ አወጋኋት::

«አይደለም:: አባትህ ደሞ ነገር ፈበላሽል:: እኔ እንደማስታውሰው እንዲት መሰለህ? እጣኑ ቂርቆስ ብዙ ሕፃናት ሰብስቦ በሦስት ሰሙኒ፣ በብር፣ በሦስት ሽልንግ ይሸጣል:: እኔ አየሁህና ደስ አልከኝ:: የዚያኔ ነው ፋንጋይ ያልኩህ:: ስጠራህ ደስ ብሎህ መጣህና አቀፍከኝ:: እኔም እጣኑ ቂርቆስ የጠየቀኝን አምስት ሽልንግ ከፈልኩና ገዛሁህ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእኛ ልጅ ሆንክ::»

«እጣኑ ቂርቆስም ሆነ እግዚአብሔር አንድ እኮ ናቸው::»

«አዎን ሁለቱም አንድ ናቸው» አለቺኝ በእርግጠኝነት፣ ወይም ወጉን ለማሳጠር::

እማዬ መዋሸት ነውር እንደሆነ ደጋግማ የምታስጠነቅቀኝን ያክል፣ ለበጉ ሲሆን እንዴት ማበል አንዳለብኝ የምታስጠናኝ ጊዜም ነበር:: ይሁን እንጂ ሁሌም ጠንካራ እውነተኝነቷ ስለሚገዘፍ እኔም በአብዛኛው የምከተለው ይህንኑ ባሕርይዋን ነበር::

ቤተሰቦቼ 'የአንድነት' እድር አባል ናቸው:: አንድ ቀን እማዬ ወርሐዊ መዋጮውን ሄዳ መክፈል አልቻለችም:: አባቴም ሰሥራ ከወጣበት አልተመለሰም:: አድርቶኛው የሚሰበሰብበት ቦታ ቅርብ ስለነበር እኔን ላከችኝ::

«ብሩን ጭብጥ አድርገህ ያዝ፣ ዘራሞ ኢንቻ ሲሉ አቤት በል:: ካርዱን ስጣቸው:: ስለ አባትህ ሲጠይቁህ ሽማ ለደንበኞቹ ሊያደርስ ጠዋት ነው የወጣው በል:: እናትህን ካሉህ ትናንትና አክስቴን አሞዋት ከሄደችበት አልተመለሰችም በላቸው::»

«እሺ::»

«ስትመለስ እንጭቻ ጋግሬ እጠብቅሃለሁ:: በል ብርርር ብለህ ሂድ!»

የእድሩን መዋጮ ከፍዬ ተመለስኩ::

«ከፈልክ?»

«አዎን::»

«ታዲያ ምነው አኮረፍክ?»

«ምንም::»

በዚህ መካከል *አደይ ዝማም ወደ ቤታችን እየሳቁ ገቡ:: እን ዳዩኝ«አይ ፋንጋይ! እድርተኛውን ሁሉ በሳቅ ሆዳችንን አፈረሰው::»

«በምን ምክንያት?» አለች አማዬ፣ ትንሽ ፈገግ ብላ አደይ ዝማምን እያየች::

---

*እደይ፣ እናት፣ እማዬ፣ እማማ ለማለት በትግርኛ የሚጠቀሙበት ቃል::

«ዘራሞ ኢንቻ ሲባል አቤት አለ:: አባቴን ሲጠየቅ ሽማ ሊያደርስ ከሄደበት አልተመለሰም አለ:: እናትህስ? ሲሉት አትናገር ብላኛለች እንጂ እቤት ውስጥ አረቄ እያወጣች ነው::»

«አንት!» ብላ አፈጠጠችብኝ፣ ዓይናጅ ግን አይቆጡም::

«አንቺ ነሽ» አልኳት::

«እኔ ምን አልኩኝ?»

«አትዋሽ እያልሽ ሁልጊዜ ትቆጫለሽ፣ ሰባቂ እያልሽ ትማ ቻለሽ:: አሁን ደግሞ ብዋሽ...»

ከትከት ብላ ስቃ በብሩህ ዓይናጅ ቁልቁል አየችኝና «አይ ፋንጋይ! እሰዘ ልብ ይስጥህ:: በል ሂድና ትንሿ ነርጓዳ ሳሀን ውስጥ ያስቀመጥኩልህ እንጭቻ አለ፣ ውስድና ብላ» ብላኝ በቅርቡ የፈፀምኩ ትን ሌላ የቂልነት ድርጊት ለአደይ ዝማም ልታወራላቸው ስትጀምር፣ አደይ ዝማም አቋርጠዋት የራሳቸውን ልጅ የኑይቶምን ቂልነት ለእማዬ ያጫውቷት ጀመር "እትዬ ባሉቴ የእኔም ጉድ ያው እንደ ፋንጋይ እኮ ነው! በቀደም ዕለት ከትምህርት ቤት ሲመጣ ምሳውን ጓዳ አስገብቼ ደብቄ ያስቀመጥኩለትን እሰጠዋለሁ አልበላም" አለ::

"ለምን?"

"አንቺ ከዘመዶችሽ ጋር በጉመን እየበላሽ ለእኔ በአይብ ትሰጪኛለሽ?"

ሁለቱም ከልብ የኮረኮሯቸውን ያህል ሳቁ::

ካለፉት ሳምንታት በአንደኛው ቀን አባቴም ሆነ እናቴ ቤት ውስጥ አልነበሩም:: እኔ ከምጫወትበት መጥቼ የምበላው እፈልጋለሁ:: መሶቡንም፣ ድስቱንም ስከፍተው አንድ አይነት ምግብ አገኘሁ:: እማዬ በዚህ ሰዓት ያለችው ጉልት ነው:: በልጅ እግሬ ሮጬ ጉልት ደረስኩ:: ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አፋፍ ላይ ቆሜ «እማዬ! እማዬ!»

«ወይ! ወይ!» አለቺኝ መደቧ ላይ እንደተቀመጠች:: ገበያተኛው ይተራመሳል::

«ድስቱ ውስጥ ያለውን ነው የምበላው፣ ወይንስ መሶቡ ውስጥ ያለውን?»

«የመሶቡን እንዳትነካ ያባትህ ነው:: ድስቱ ውስጥ ያለውን ብላ!!»

ገበያተኛው በሳቅ አውካካ:: እኔም ፊቴን ወደ ጉዳዬ መለስኩ:: በሶምሶማ ሩጫ ወደ ቤቴ ስሄድ ቲቲ ውሻዬ ቀደመችኝ:: በፍጥነት አስከነዳችኝ:: እቤት ስንደርስ በሩ ተከፍቷል:: አባቴም መሶቡ አጠገብ የተቀመጠለትን ምግብ በሳህን ይዞ ቆሟል:: ልክ እንዳየኝ «ፋንጋዬ ደንስ!» ሲለኝ ጆሮዬ ተከፈተ:: ለካ ሬዲዮናችን እየዘፈነች ነበር!

አዮቴ ለንጥረኛ፣ አባቴ ሸማኔ
ወንድሞቼ ቀጥቃጭ፣ አገሮሪ ነኝ እኔ
ቤተሰቤ ሁሉ የእጅ ሙያ አላቸው
ለእናት አገራችን የሚያኮሩ ናቸው::...

ሀሁ

ኧረ ልጆች ልጆች፣ እንጫወት በጣም
ከእንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም
ልጅነቴ! ልጅነቴ ማርና ወተቴ፡

'እንጫወት በጣም' በልጅነት ከምንዘምራቸው መዝሙሮች መካከል አንዱ ነበር። ማን እንደደረሰው አላውቅም። ማን እንዳስ ጠናን አሁን ትውስ አይለኝም። ማንም ሰው ሳያሳየን፣ አርስ በራስ እየተማማርን፣ ወይም ፈጥረን አልያም ከአካባቢያችን ልጆች ተምረን፣ እንደዚሁም ከድሮ ልጆች ወደ ዘንድሮ ልጆች ተላልፈው የምንጫወታቸው በርካታ የጨዋታ አይነቶች እንደነበሩን አሁንም አስታውሳለሁ። ትዝ ከሚሉኝ መካከል ሌባና ፖሊስ፣ የእጅ ቦምብ፣ አሌቡም፣ ሹሌ፣ ሰኞ ማክሰኞ፣ ዕቃ ዕቃ፣ ብይ፣ ጠጠር፣ ... እና ሌሎችም ነበሩ።

ቁስ ትምህርት ቤት በተመዘገብኩበት በመጀመሪያው ዕለት ከጥቂት ሰዓታት በኋላ መማር በጣም ጠላሁ። ትዝ ይለኛል አባቴ ትምህርት ቤት እንዲያስገባኝ የጠየኩት እኔው ነበርኩ። እሱ ግን "ቆይ ፉንጋይ እስኪሻልህ ትንሽ ታገስ" ሲል በምክር መልክ ሐሳቤን ተቃውሞ ነበር።

"እምቢ ተሽሎኛል! እንዴ! እነነቢጥ፣ እነመኩዬ ቀጫጫ ውኃ ትምህርት ቤት ገብተዋል" ስል የመማር ጉጉቴን ገለጽ ኩለት። እንዳልኩትም እነ መኩዬ ቀጫጫው፣ እነ ኃይሉ ዶሮ ኖራ በተቀባ ግድግዳ ላይ በከሰል ፊደላቱን እየጻፉ "ይቺ 'ሠ' ነች፣ ስትገለበጥ 'በ' ትሆናለች" እየተባባሉ ሲጨዋወቱና በልጅ መንፈስ ሲመራመሩ አየኋቸው። የማላውቀው ችሎታ እንዳላቸው ገባኝ። ይህንን እውቀት የገበዩት ከቁስ ትምህርት ቤታቸው እንደሆነ ተገነዘብኩ። ሲሳይ ጉቢጥ 'ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር' ብሎ ፃፈና ፍክ ብሎ አነበበው። መንፈሳዊ ቅናት በአእምሮዬ ተፀነሰ።

ከአባቴ ጋር ስንመካከር ትሰማ የነበረችው እናቴ "እንዴ! እንተ ምን ችገረህ?" አለችው። "እማራለሁ ካለ አስገባው። ለእኔም አረፍት ነው። አንድ ውሪ በጮኽ ቁጥር ነፍስና ሥጋዬ እየተ ለያዬ ተቸግሬያለሁ።"

"እሄሄ ይች ውሸት አሉ አንባዬ አዳል። አሁን የልጅሽን አመል አጥተሽው ነው? እኔ ምን ችገረኝ የዛሬን ሽልንግ ከፍዬ አስመዘግበዋለሁ። ነገ ግን እንቢ አልማርም ካለ አንቺው አዳሽን ትችያለሽ።"

"ግዴለም። እንዴ! አንኳን ሽልንግ አንድ ብርም ቢሆን ለልጄ አከፍልለታለሁ" አለችና ሃሳቧን እንደተቀበላት ገምታ የሰርክ ልብሴን ታወልቅልኝ ጀመር። አፈርማ ቀለም ካኪ ኮትና

ቁምጣ የከት ልብሴን አለበሰችኝ። በጣም ደስ ስላለኝ ስታለብሰኝ እቁነጠነጣለሁ። አርፌ ልብሴን እንድቀይር ተገስጠኛለች። ግሰጣዋን ችላ ብዬ አንዴ እቅፍ አድርጌ ሳምኳት። በማሾፍ ጠቀሰችኝ። አባቴ ቆሞ ፈገግ ብሎ ያየኛል። የባቄላ እሹቅ በደንብ ዘግና በኪሴ ጨመረችልኝ። ቦት ጫማዬን አደረኩ።

ሁለቱ የት ትምህርት ቤት ብዛባ የተሻለ እውቀት እንደ ምገበይ ይነጋገሩ ጀመር። በዚያን ወቅት በአካባቢያችን አራት የቄስ ትምህርት ቤቶች እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። እንደኛው በቂርቆስ ደብር ውስጥ፣ ሁለተኛው ብረት ጋራጅ፣ ሌላው በአቅራቢያችን የኔታ ተከለወልድ የሚያስተምሩበት ሲሆን፣ አራ ተኛው ራቅ ያለውና ምድር ባቡር ኩባንያ ያለው ነበር።

ብዙዎች አብሮ አደጎቼ የሚማሩት ቂርቆስ ደብር ውስጥ ነበር። የተወሰኑት ብረት ጋራጅ ሲማሩ፣ ቦቻራ አባቱ ምድር ባቡር ስለሚሠሩ እዚያ አስገቡት። ለቁጥር የማያመች ቢሆንባ ቸው ብረት ጋራጅ አካባቢ አስቀየሩት።

እኔም ብረት ጋራጅ አካባቢ ያለው እንደሚስማማኝ ተማም ነው እዚያ እንድማር ወላጆቼ ወሰኑ። እንደምክንያት ያቀረቡት ከብዙዎቹ የሰፈር ልጆች ጋር ኩተማርኩ ከትምህርቴ ይልቅ ጨዋ ታው ቀልቤን ይስርቀኝና ሰነፍ እንዳልሆን፣ የሚሻለው ብዙ የማ ውቃቸው ልጆች የሌሉበት ብመዘገብ እምነታቸው ስለነበር ይመስ ለኛል። እኔ ደግሞ የትኛውም አካባቢ ብገባና ብማር ግድ አልነ በረኝም። ፍላጎቴ መማር ነውና ሁሉም ነገር ቀስ በቀስ የሰመረ መሰለ።

እናቴ ከጆሮግንዷ ሥር አራት ፍራንክ አውጥታ ስጠ ችኝ። ሻሽዋ ዝርዝር ፍራንክ ማስቀመጫ የምስጢር ኪሷ ነበር። በፍራንኩም ሮጬ ከጀግል ሱቅ ፊደል ገዝቼ እንድመጣ ላከ ችኝ። መንገድ ላይ ሳሀሉ መቃን አገኘሁትና ትምህርት ቤት ልገባ መሆኑን ነገርኩት። ቀጭን ረጅም ስሰሆነ መቃ ቅፅል ሰሙ ነው። ደስ ብሎት ወደ ትምህርት ቤት መሄዱን ትቶ አጅቦኝ ሱቅ ሔደን ፊደል አብረን ገዛን። እግረመንገዱንም "ፉንጋይ እኛ ትምህርት ቤት ተመዝገብ አብረን እናጠናለን" አለና ተለማመ ጠኝ። ባይለኝም ወላጆቼ የመረጡት ትምህርት ቤት እሱም የሚማርበት ነው።

አባቴ ቀኝ እጁን ይዞኝ በግራ እጁ ፊደሌን አንግቤ ሳሀሉ መቃ እጅቦኝ እውቀት ወደምገበይበት፣ የጥበብ አዝመራ ወደ ፈካበት፣ ማይምነትና አላዋቂነት ወደሚጠፋበት እምባ አመራን።

በዚህ መንገድ ስሔድ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። ከእኛ መንደር ምንም የተለየ አዲስ ነገር አላየሁበትም። አባቴ "ፉንጋዬ መንገዱን ልብ አድርገህ እይ ስትመለስ እንዳይጠፋህ። ግን ተወው እስከምትለምደው እኔ ራሴ ቀትር ላይ እየመጣሁ እቀበልሃለሁ።"

"እኔ እኮ አውቀዋለሁ፣ አባባ ዜራሞ" አለ ሳህሉ። በቀኝ እጁ በርጩማውን በግራ እጁ ፊደሉን ይዞ፣ በላስቲክ ኮዳ ውሃውን ሞልቶ በአንገቱ ላይ አንጠልጥሏል።

"አዛ ለካ አንተም አለህ። ልክ ነህ ሳህሉ እንዳትለያዩ።"

"እሺ።"

"ጎን ለጎን እንቀመጣለን?" እኔ ጠየቅሁ።

"እኔ እኮ አቡጊዳ ነኝ።"

ግር አለኝ።

"ምን ማለት ነው?" አባቴ ጠየቀው።

"ፉንጋይ አሁን የሚማረው ሀሁ ነው። እኔ ግን አቡጊዳ ስለሆንኩ የምቀመጠው ሌላ ቦታ ነው።"

"የቱ ይበልጣል?"

"አቡጊዳ ነዋ!"

"ጎሽ የኔ ልጅ በርታ። በወራት ቀደም ስላልክ ነው የተሸጋገርከው?"

"አዎን። በቀደም ለታ ነው ከሀሁ ወደ ሀ-ግእዝ ሁ -ካኢ፣ ከዛ ሀ-ግእዝ ለ-ግዕዝ፣ ከዛ አቡጊዳ የተዘዋወርኩት።

ተናደደኩ። "ድሮ አስገባኝ ስልህ እምቢ ብለኸኝ አስበ ለጥከኝ" አልኩ፣ ማልቀስ እየቃጣኝ።

"አዬ ጋሼ የትናንት የትናንት ወዲያውን ትተህ ዛሬም በሆ ነልህ። አሁን አንተ ልትማር?" አለና ከራሱ ጋር ተሳሳቀ። እኔ ራሴን ከማውቀው በላይ ያውቀኛል።

አነስተኛ ጅረት እንደተሻገርን ትምህርት ቤቱ አካባቢ መድረሳችንን የሕፃናቱ ጫጫታ አበሰረን። ወደ ግቢው ስንዘልቅ ተማሪዎቹ በአንዲት አነስተኛ ዛኒጋባ ውስጥ ተሰባስበው በዜማ ፊደል ይቆጥራሉ። አርፍደው የመጡትን ተማሪዎች የኔታ ከዛኒ ጋባዋ ውጪ ባለ መስክ ላይ ሲቀው ነው የደረስነው።

አንዳንዶቹ ተንበርክከዋል። አንድ ሁለቱ በእግራቸው ሥር እጅ በጆሮ ይዘዋል። የኔታ የተንበረከኩትን እያስነሱ እጃቸውን በአለንጋ እየገረፉ ወደ መማሪያው ከፍል ያስገቡአቸዋል።

መቃ በርጩማውን፣ ፊደሉንና የውሃ ኮዳውን በሚቀመጥበት ቦታ አነሮ ተመለሰና ተንበረከከ። እኔም ተከተልኩትና ተንበረከኩ። እሱ በሹክሹክታ "ፉንጋይ፣ አንተኮ አርፋጅ አይደለህም። እኔ የተንበረከኩት አርፍጄ ነው።"

"አዬ ጋሼ ግና መቼ ምን አይተህ ነው ለመንበርከክ የቸኮልከው? አይዞህ ትደርስበታለህ!" እያለ አባቴ አንቀርቅቦ አነሳኝና ከጎኑ አቆመኝ። ፊደሌ ከእጄ አምልጦ ወደቀ። አንስቼው ቀና ስል ከዬኔታ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጥን።

ጠባብ ግንባር፣ ፊንጣማ ወጋ ወጋ ያደረገው ጠይም ፊት፣ ጉንጮቻው ደግሞ ጉንዳን እንደወረረው ሁሉ በጸጉ ተሸፍኗል። ትልቅ የቁስ ጥምጣም አናታቸው ላይ ከምረዋል። ዐሐይ

ብትወጣም ጋቢያቸውን እንደተከናነቡ ናቸው። ቦላሌ ሱሬ ታጥቀዋል። ባዶ እግራቸውን ናቸው። ኮስታራነታቸው ለልጅ ልብ ይከብዳል። ጥቋቁር ዓይኖቻቸውን ሳስተዋለ ስቀው የሚያውቁ አይመስሉም።

"እንደምን አደሩ አባ!" አለ አባቴ እጅ እየነሳቸው።

"ዛሔር ይመስገን" ብለው አፀፋውን መለሱ። አለንጋ ቸውን አጥፈው የጣ እጃቸውን ችብ ችብ እያደረጉ ቀረቡን።

"ልጁን እንዲያስተምሩልኝ ይገፍው መጥቻለሁ።"

"ማለፊያ እናስተምረዋለን" አሉና ቁልቁል እያዩኝ "አንተ ማሙሽ ስምህ ማን ይባላል?" አሉኝ። ጥቋቁር ዓይናቸው ሳይረግቡ ያስተውሉኛል።

"ፉንጋይ ዜራሞ።"

"ምን?"

"የቤት ስሙ ነው ፉንጋዬ የምንለው። ትክክለኛ ስሙ ተስፋዬ ነው" አለ አባቴ። "ስናቆላምጠው የኔ ፉንጋ፣ ፉንጌ እያልነው ተሰመደና ትክክለኛ ስሙ መስሎት ነው ለእርሶ መናገሩ" አለ አባቴ በትህትና።

"ሁሉም ሕፃን ባይሆን አብዛኛው የቤት ስም ይኖረዋል። ተስፋዬ ግን ማለፊያ ስያሜ ነው። ስንት ዓመትህ ነው?" ብሰው ጠየቁኝ።

"ሰባት"

አባቴ ሳቀብኝ እጁን ሞብጥ አደረኩት፣ አልሞላሁም ብለው እንዳያስወጡኝ ስለፈራሁ። እሱ ግን ችላ ብሎኝ "አይሞላውም" አላቸው።

"መቸ አጣሁት?" አሉና እኔን "በል ሂድና እዚያ ከልጆች ጋር ሆነህ ተማር" አሉኝ።

የአባቴን እጅ ለቅቄ በናፍቀነት ከልጆች ጋር ተቀላቀልኩ። ሕፃናቱ ፊደል መቁጠራቸውን ትተው ካልተለመደ ዓለም እንደ መጣ ልዩ ፍጥረት ፍጥጥ ብለው አዩኝ። አንደኛው ተጠጋልኝና ከአጠገቡ አስቀመጠኝ።

"ፉንጌ" አለኝ ሳህሉ መቃ።

ዞሬ አየሁትና "ልምጣ?"

"እባው ሆነህ ነው የምትማረው" አለኝ መቃ በለሆሳስ።

"እሺ!" ብዬው ወደ አባቴና የኔታ ዞርኩኝ። የሚነጋገሩት አይሰማም። አባቴ ኪሱ ገብቶ ገንዘብ አውጥቶ ሳንቲሙን ቆጠረና ሲከፍል አየሁት። ዞሮ አየኝ። ተያየን። በዓይን ተሰነባበትን።

"ሳስተምርህ?" አለኝ አጠገቤ ያለው ልጅ። ስሙ አሰፋ እንደሆነ እየነገረኝ።

"እሺ" አልኩና ፊደሌን አስተካከልኩ።

"ገልብጠኸዋል!" አለና አስተካከለልኝ። ከያዘው ሣር መዞ አንዷ ፊደል ላይ ጠቁሞ "ሀ" አለኝ።

"ሀ" አልኩ።።
"ሁ" አለኝ አጠገቧ ያለችውን ፊደል።።
"ሁ" አልኩ።።
"ሂ" አለኝ የተማሪ አስተማሪዬ፣
"ሂ"
"ሃ"
"ሃ እንደገና?" ስል ጠየኩኟ።
"አዎን።። ይኼም ሃ ነው የሚባለው" አለኝ።።
ቀና ብዬ አየሁት።። ዓይኖቹ በርበሬ መስለዋል "ዓይንህን አሞሃል?" አልኩት ትምህርቱን ችላ ብዬ።።
"አዎን አሁን የወሬ ስዓት አይደለም።። የትምህርት ነው።። እንማር አለበለዛ አለቃችን ይገርፍሃል።።"
አካባቢውን ቃኘሁ።። ሁሉም ልጆች ፊደላቱን ለመለየት እየተጣጣሩ ነበር።። የመምህሬን ዓይን ተከትዬ ሳስተውል አንድ ልጅ ላይ አፍጧል።። ልጁ እኔ ላይ አፍጧል።። አስተያየቱ እልቅ ናውን ያመለክታል።።
"ሂ" አለኝ አስተማሪዬ ዓይኑን ከአለቃችን ላይ ነቅሎ።።
"ሂ" ስል መለስኩ።።
"ሀ"
"ሀ"
"ሆ"
"ሆ"
አስተማሪዬ እየጠቆመኝ፣ መልካቸውን ለመለየት እየሞከርኩ እስከ ፕ ዘለቅን።።
እንደገና "ሀ" ሲል፡
"ቆይ ደክሞኛል" አልኩና ከኪሴ አሹቅ አውጥቼ ቃምኩ።።
"ስጠኝ!"
ዘግኜ ሰጠሁት።።
ያ አፍጦ ሲያየኝ የነበረው ልጅ ቱር ብሎ መጣና "ለኔም ስጠኝ" ብሎ እጁን ዘረጋ።። አጠያየቁ የመለመን ሳይሆን፣ የማዘዝ ያክል ነበር።።
"ለምን እስጥሃለሁ? አልሰጥም!"
ፊደል አስቆጣሪዬ ነውር ነገር እንዳልሠራ ምክሩን ሲለግሰኝ "ስጠው! አለቃችን እኮ ነው!" ብሎ በሕይወቴ ከመጀመሪያው አለቃዬ ጋር አስተዋወቀኝ።።
"አለቃችን ቢሆንስ?" ስል ግር ብሎኝ ጠየቅኩ።።
"ብትስጠው ግን ይሻልሃል! ዋ!" አለና ከሰጠሁት አሹቅ እየቃመ፣ አለበለዛ እምቢ ካልከው ይገርፍሃል።።"
"ለምን ይገርፈኛል?" አሁንም ግር እንዳለኝ ጠየኩ።። እስከ ዛሬ እኔን የመግረፍ መብት ያላቸው እናትና አባቴ ብቻ ነበሩ።። አልፎ አልፎ እማማ ረታሽም ይገርፉኛል።። የለፈራችን ትልልቅ

ሰዎች ግን ጥፋት ካጠፋሁ ይቆጡኛል እንጂ ገርፈውኝ አያውቁም።። ይህ አይነቱ ቅጣት የሚደርስብኝ አጥፍቼ ስገኝ ነበር።። ቆለሜን አልሰጥም በማለቴ የምገረፍበት ምክንያት ግን አልገባህ አለኝ።።
"አለቃችን ሰለሆነ" አለና ልጁ እጁ ላይ የቀረችውን ርጋፊ ሰጠው።።
አለቃው በፍጥነት ቃማትና፣ እጁን ወደ እኔ ዘረጋ።። እኔ በበኩሌ በእምቢታዬ እንደፀናሁ ነው።።
መቃ ቱር ብሎ መጣና "ሩንጋይ፣ ይኸውልህ፣ ቂጣም ሆነ ቆሎ ከቤትህ ካመጣህ ለአለቃችን ትንሽ፣ ትንሽ መስጠት አለ ብህ።። አለበለዛ ሰበብ ፈልጎ ይገርፍሃል።። ትንሽ ስጠው" ብሎ የአብሮ አደግ ምክሩን ለግሶኝ ለራሱም እንደሰጠው እጁን ዘረጋልኝ።።
ዘግኜ ሰጠሁት።።
መቃ በነዚያ ዘርዛራ ጥርሶቹ አሹቁን እየከካ፣ ከድርሻው ለጌታቸው አለቃችን ገበረ።።
"በቃ ተወው! በኋላ ግን ይቆጭሃል" አለና ጌታቸው በነብር አየኝ በል አፍጠጠኝ፣ መቃ የሰጠውን አሹቅ ቃመ።። ከዚያ አንጃ ግራንጃችንን ሲያደምጡ ወደነበሩት ሕፃናት ዞረና "በሉ ተማሩ" አለ በአዛዥ ድምፅ።።
አስተማሪዬ ትዕዛዙን ሲተበል "ሀ!"
"ቆይ ትንሽ እንረፍ!"
"እረ! አሁን የአረፍት ሰዓት አይደለም።። ሀ" አለኝና "ለጌታቸው አሹቅ ከልክለኸው አሁን ይሄን ሰበብ አድርጎ ይመታሃል" አለኝ፣ አረፍትህንማ በትንሽ አሹቅ ንፍገት ገደልካት በሚል ትዝብት እያስተዋለኝ።።
ይሔ የጀመርኩት የትምህርት ቤታችን ደንብ ግራ አጋባኝ።። ጌታቸው እማዬ የለጠችኝን አሹቁን በእጅ አዙር ተቀብሎ እየከካ በጥላቻ ዓይን ያስተውለኛል።። "አትማሩም?!" ብሎ ጮኸ።።
"ሀ" አለ አስተማሪዬ።።
ዝም ብዬ አሹቁን መቃም ቀጠልኩ።።
ጌታቸው ቱር ብሎ ተጠጋና በክርኩም ቆጠኝ።።
ፌዝኽቴን ለቀቅኩት።።
የኔታ ዳዊት የሚማሩ ልጆች መካከል ሆነው "ምንድነው?"
"ይኼ ጌታቸው ይማታል!" አልኩ በልቅሶ ዜማ።።
"ውሸቱን ነው የኔታ ተማር ስለው ከኪሴ አሹቅ አውጥቶ ይቅማል።። አሰፋ ምስክሬ ነው።። እውነቴን አይደለም አሰፋ?!" ብሎ ጌታቸው አስተማሪዬ ላይ አፈጠጠበት።።
"ልክ ነው የኔታ!" አለ አሰፋ ረጃጅም ቅልጥሞቹን ዘርግቶ እንደመቆም እያለ።።

"አንተ ማነው ስምህ? አርፈህ ተማር ጥሬም ካለህ እረፍት ላይ ትደርስበታለህ"

ተረጋግተን መማር ልንጀምር ስንል፣ እከክ መላ አካላቱን የወረረው አንድ ቀጫጫ ልጅ በቀኝ እጁ ግራውን እያከከ "ስጠኝ?" ብሎ እከካም ግራ እጁን ዘረጋልኝ። አካሉ ይቀፋል፣ አለማመኑ ያሳዝናል። ቆንጥሬ ሰጠሁት።

"ሀ" አለ መምህሬ፣

"ሀ" አልኩ ባኮረፈ ድምፅ። አንዴ መቃም አምሮኛል፣ ይህ መብቴ ግን በአለቃችን ሥልጣን ታግዷል።

"ሄ" ጋ ስንደርስ፣

መቃ በፍጥነት አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠና "ፉንጋይ የምመ ክርህን ብትለማ ይሻልሃል። ለጌታቸው ትንሽ አሹቅ ስጠው" አለኝ። ቀና ብዬ ሳይ ጌታቸው መቃ ወንበር ላይ ተቀምጠ ያፌ ጥብኛል።

"አልሰጥም"

"አይ! ሰበብ ፈልጎ ይገርፍሃል፣ ያንበረክክሃል፣ በኩርኩም ይቆጋሃል። የኔታ ደግሞ የሚሰሙት እሱን ብቻ ነው። እኛም ፈርተን ጥፋተኛ መሆንህን አንመሰክራለን" አለኝና አሹቅ እንድ ሰጠው እጁን ዘረጋ።

በእንቢተኝነቴ ትከሻዬን ሰበቅሁ። ለመቃ ግን ትንሽ ዘግኜ ሰጠሁት። ተቀበለኝና እኩል ለእኩል አካፍሎ ለጌታቸው ገበረ። የተቀረውን ለነዚያ ዘርዛራ ትንንሽ ጥርሶቹ አቀበለና ከካቸው። አቆረጣጠሙ በአፌ ምራቅ እንዲሞላ አደረገኝ። ሳይጣደፍና ሳይ ፈራ ቦታው ተመልሶ ተቀምጦ ፊደሉን አነሳ።

ጌታቸው በጣም በሽቆ መቃ የሰጠውን ጥሬ እየቃመ፣ አጠገቡ ያኖረውን አርጩሜ አንስቶ አንዴ ሾጥ አደረገኝ።

ጮኽኩ።

"ምንድነው?" የኔታ ቀና ሳይሉ ጠየቁ።

"ይህ አዲሱ ልጅ በደንብ አይማርም" እያለ ጌታቸው ለየኔታ እየተናገረ፣ በአኳኋኑ ገና አሳርህን አሳይሃለሁ በሚል ዛቻ አፈጠጠብኝ።

"እረ አንተ ልጅ ተው ተማር!" ብለው ገሰጡኝ።

ከግቢው ውጪ ከፍተኛ የጩኽት ድምፅ ተሰማ። በሩ ተበርግዶ ተከፈተ። ቦቸራን እናቱ እማማ አሰለፈች በገመድ ጠፍረውት እየጎተቱት ገቡ። ደንብሮ እንዳይፈረጥጥ ታላቅ እህቱ ገነት ትልቅ አርጩሜ ይዛ ከኋላ ተከትላለች።

እማማ አሰለፈች አርር ድብን እያሉ "ይኸው የኔታ፣ ይዘነው መጥተናል። ይህ ዱር ቤቱ የሆነ ልጅ!" አሉ።

የኔታ ከበርጩማቸው ላይ ፍየል እንዳየ ነብር እመር ብለው ተነሱና "እህ! አንተ የዱር ድመት፣ በመጨረሻ ተገናኘን?"

ዘንቦ እንዳባራ ሁሉ የተማሪዎቹ ጩኽት ፀጥ ረጭ አለ። ዓይኖቻቸው ተነልጉለው ወጥተው ቦቸራ ላይ አፍጠዋል። እኔና አሹቁንም ረሱን። የቦቸራ ጩኽት አየሩን ሞላው። ለማፈትለክ ይታገላል። ለጋ ጉልበቱ በሦስት ሰዎች ተጠምዶ ሊቋቋም አልቻለም። ንፍጡ፣ እንባውና ላቡ ፊቱን አርጥበውታል።

"ወይኔ አ! አ! አ! አንቺ ነሽ ያስያዥሺኝ አ!" ብሎ እህቱ ላይ አፈጠጠ።

"ፐ! ዱርዬው ተያዘ!" አለ ጌታቸው።

"ዱርዬ አልከው? የሰፈሬ ልጅ ነው እንግረዋለሁ!" አልኩ እየተቆጨሁ።

"ተይ አንቺ ቀጫጫ! ብታርፊ ይሻልሻል፣ አለበለዛ እጨ ፈልቅሻለሁ። ደሞ ለዱርዬነቱ ምን ምስክር ያስፈልገዋል? ትም ህርት ቤት እዪዳለሁ እያለ ካምቦሎጆ አይደለም የሚውለው? ዛሬም እንደተለመደው ፓስቴውን እየበላ ሲሽሎከሎክ ተያዘ። ተው ትንሽ አሹቅ ስጠኝ!?"

ትከሻዬን በእምቢታ ሰበቅኩ።

ቦቸራ አሁንም የድረሱልኝ ድምፁን ያሰማል። አካላቱ በአሷራ ተለውሷል። ለማምለጥ ሲጣጣር ባልተሳካ ትግሉ ሰውነቱ ተላልጧል።

የኔታ ክንብንባቸውን አውልቀው ወንበራቸው ላይ አስቀ መጡ። አለንጋቸውን እንስተው "እሺ የእኛ የዱር ድመት፣ የት ከረምክ?" ብለው ቃጡና ባለ ኃይላቸው በአለንጋቸው ዠለጡት።

እረታውን አቀለጠው። ተሰፋ ሳይቆርጥ አሁንም ለማ ምለጥ ይታገላል። እናቱና እህቱ ሳያላውሱ ይዘውታል። እማማ አሰለፈች "የኔታ እግር እግሩን! አዎን እሱጋ! አይ፣ ከፍ አሉ። እያዩ፣ ሰበብ ይሆንዎታል! አዎን አሁንም ዝቅ! ዝቅ" ይላሉ ሆዳ ቸው እየተሸበረ፣ ውጫዊ አካላቸው የተደሰተ እየመሰለ።

ከእኛ ጋር የምትማረው ታናሽ እህቱ ሂሩት ይህ ሁሉ ግርፊያ በወንድሟ ላይ ሲወርድ ስታይ ሳይነኪት ማልቀስ ጀመረች።

እኔ በማየውና መኖር በጀመርኩት አዲሰ ሥርዓት ላይ ጥላቻ አደረብኝ። ሽንቴ ወጠረኝ። በግርግሩ መካከል እንዴት ማምለጥ እንዳለብኝ አብሰለሰልኩ። ቦቸራ ተሰማ ተይዞ ባይመጣ የዱኔታን አለንጋ የምቀምስበት ወቅት ደርሶ እንደነበር አስታ ወስኩ።

የሚመለከተውን ጭፍግ ሕይወት መቋቋም የተሳነው አንዱ ሕፃን ፊሱን ጡጥ! አደረጋት። ሌሎቹ ዞረው አዩትና ሳቁበት። ጭንቁን ያረገበው ሕፃን አጠገቡ ወዳለው ልጅ እየጠቆመ "እኔ አይደለሁም እሱ ነው የፈሳው" ሲል ተከራከረ። ቢሆንም በእፍ ረት ከአፍ የወደቀ ጥሬ አክሏል።

ቦቸራ ተጠልፎ ወደቀ። በተዘረረበት፣ በላዩ ላይ የሚወርደውን አለንጋ ለመቋቋምና ለመመከት እየሞከረ "የኔታ፣ ሁለተኛ አይለምደኝም! ሁለተኛ!..." ተማፀነ።

የታነቀ እውነቱን ይናገራል፣ ነገርግን የሚያምነው የለም እንዲሉ፣ የኔታ በአፀፋው አላኸኩበት። "አሄሄ! እንተዋወቃለንኮ ቦቸራ! እባብ ለእባብ አሉ... ሁሌም አንተ ወጥመድ ውስጥ ስትገባ ማምለጫ ጥበብህ ሁለተኛ አይለመደኝም ነች!" ብለው የበሉ የጠጡትን ያህል ገረፉት። በአሰነዛዘራቸው የእማማ አሰለፈችን ምክር ልብ ያሉ አይመስልም። ጥምጥማቸው ወልቆ መሬት ተንከባለለ። የተላጠ ድንች የሚመስለው መላጣ አናታቸው እርቃኑን ቀረ።

በዚህ ወቅት የሁሉም ትኩረት ቦቸራ ላይ መሆኑን አየሁና ሹልክ ብዬ ወጣሁ።

ወደ ሐኪም ቤት

"ልጅቻችሁ በእናንተ በኩል መሐ እንጂ ከእናንተ አልወጣም"

- ካህሊል ጊብራል

ወደ ሰፈሬ ለመመለስ መንገዱ ምንም አላሳሳተኝም። ጠዋት አባቴ እንዳልሳሳት ባሳሰበኝ መሠረት ምልክት ባደረኳቸው ነገሮች መሪነት ሠፈሬ ተመለስኩ። አበራ ወፍጮ ቤት አካባቢ ስደርስ ትምህርት ቤት ያልገቡትን የሰፈሬን ልጆች ከርቀት አየ ኋቸው።

ቀጪሳውና ሴምላል የጭቃ ብይ ሲጫወቱ፣ ቁልጭና ባሪቾ ቆመው ይመለከቱዋቸዋል። እኔ እያለከለኩ አጠገባቸው ስደርስ ጨዋታቸውን አቁመው እንደ ልዩ ፍጥረት አፍጥጠው አዩኝ።

"ተማሪ ቤት ገብተህ አልነበረም?" አለኝ ቀጪሳው በመደነቅ እያስተዋለኝ።

"ወጣሁ!" አልኩ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ። ከኋላዬ ማንም እንዳልተከተለኝ ዞሬ መንገዱን አየቃኘሁ።

"መቼ?"

"ድሮ።"

ሁሉም ሳቁ።

ሴምላል የተንጠለጠለ ንፍጡን ከአፍንጫው ላይ በእጅ ጌው እየጠረገ "ጠዋት እኮ ድሮ አይደለም። ተማሪ ቤት የገባኸው ዛሬ ጠዋት ነው። የወጣኸውም ዛሬ ነው" ብሎ አረመኝ።

"ለምን ወጣህ?" ብሎ ቁልጭ በጓጓ ስሜት ብልጣብልጥ ዓይኑን ሳያረግብ ጠየቀኝ።

"ይጋረፋሉ። በቸራን በገመድ ጠልፈው ሲገርፉት ሳይ ፈርቼ ሮጬ ወጣሁ" አልኳቸው፣ አኳኋኑ አሁን እንደሆነ ሁሉ እየዘገነነኝ።

"ቦቸራ ተያዘ?!" አለ ባሪቾ ደንግጦ።

"እምን ተያዘ። የኔታ ጠልፈው ጥለውት በጣም ገረፉት። ሲገርፉት ጥምጥማቸው ተፈቶ ወደቀ። ደግሞ መላጣ ናቸው፣ የተላጠ ድንች ይመስላል። ሲገርፉት... ሲገርፉት... እሱ ደግሞ ሲጮኽ ሲጮኽ እማማ አሰለፈች ቆመው ሲያስገርፉት... ጎሽ የኔታ ትንሽ ዝቅ... እያሉ ሲያስደበድቡት" አልኩና ልክ እሳቸው እንደሚጋረፉት አይነት አስር አስር ጊዜ መሬት ላይ ቃጣሁ።

"ሄደን በአጥር ቀዳዳ ሲገርፉት እንይ?!" አለ ቀጪሳው።

"መንገዱን ማን ያውቀዋል?" አለ ባሪቾ።

"ቆንጌ አሳየን?" አለ ሴምላል።

"እኔ? እምቢ!" አልኩና ወደ ቤቴ አፈገፈግኩ።

"ተወው! እኔ አውቀዋለሁ እንሂድ" አለ ቀጪሳው። የጭቃ ብዩን ለመሰብሰብ እንኳን ጊዜ ሳይኖረው ወደ ቄስ ትምህርት ቤቱ አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ። ሌሎቹ ተከተሉት።

እየፈራሁ እየቸርኩ፣ ለወላጆቼ ምን አይነት ምክንያት ባቀርብ እንደምታመን እያብሰለሰልኩ ወደ ቤቴ ማዝገም ጀመርኩ። እናቴ የቡና አተላ ልትደፋ ወጥታ ከርቀት አየችኝ። እሱ ነው? እሱ አይደለም በሚል ስሜት እያጣራች ነው። እኔ ቀስ እያልኩ እግሬን እየጎተትኩ ወደፊት እንቁቀቃለሁ። እኔ መሆኔን ለየች። መደነቅም መገረምም በገጽዋ ላይ ይነበብ ጀመር። አተላውን በፍጥነት ደፍታ በቆመችበት፣

"ዜራሞ" ስትል አባቴን ተጣራች።

"ወይ!" ቤት ውስጥ ሆኖ መለሰላት።

"ና... ጉዳችንን እይ!" መሳቅ ጀመረች።

ከሸማኔ ጉርጓድ ውስጥ ባዶ እግሩን ቁር ብሎ ወጥቶ እንዳየኝ በሃፍረት ፈገግታ ፊዙ ቀረ።

"አላውቅልህም! እኔ እንጃ! መጥፎ ትምህርት ቤት ነው ያስገባሽኝ። ይጋረፋሉ" አልኩ እየተጠጋሁት።

"ገና ከመግባትህ ምን አጥፍተህ አቀመሱህ?" አለና አፈፍ አድርጎ ተሸክሞኝ ወደ ቤት ገባን። እያወረደኝ "እንዴ! ቂጥህን ምን አረጠበው?" አለና ቂጤን አዙሮ አየው።

"ሽንቴን ለቆት ነዋ! አፈር በሆንኩ! ምን አድርገህ ነው ይህንን ያህል ያሸበሩህ?!" አለችና አካላቴን ደባብሳኝ፣ በሽንት የረጠበ ልብሴን ማውለቅ ጀመረች። ቦት ጫማዬም በሽንት ተሞልቷል።

"ይጋረፋሉ።"

"ምን አጥፍተህ?" አባቴ ጠየቀኝ።

"ምንም አላረኩም። አለቀችን አሹቅ ስጠኝ አለኝ። እምቢ አልኩኝ። አሁንም ለመነኝ። እምቢ አልኩኝ። ከዚያ በኩርኩም ጭንቅላቴን ኳ! አደረገኝ"

"በሽታ ይምታው! ጉዕ መሆኑ እኮ ነው" አለች እማዬ ሕመሜ እየተሰማት። "ታዲያ እንዴት ትምህርት ቤቱን ጥለህ ወጣህ? ሽንትህን እስክ መሸናት ያደረቁህ ጭንቅ ይሄው ነው?!" አለች ለራሷ ያህል።

"እሱ ብቻ አይደለም። ቦቸራን ይዘው፣ ጠልፈው ጥለው በጉማሬ ሲደበድቡት አየሁና ፈርቼ ቀስ ብዬ ሮጬ ወጣሁ።"

"ወይ ጉድ" አለ አባቴ። "ቦቸራስ ይገባዋል። ይሄ አውደ ልዳይ! ትምህርቱን ትቶ ውሎና አዳሩ ካምቦሎጆ ሆኗል። በይ ልብሱን ቀይሪለትና ለየኔታ ነግሬ..." ብሎ አባቴ የመፍትሔ ሃሳብ ሊያቀርብ ሲል፣

"እምቢ! ሁለተኛ እዚያ ትምህርት ቤት አልገባም!" ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ።

እማዬ አቅፍ አድርጋ ይዛኝ "ተወው" አለች። "መማር ካልፈለገ አታስገድደው። በዱላ ከብት እንጂ ሰው ይታገዳል? ገና ከአሁኑ ብቅ ሲል በዱላ ከጀመሩት ደነዝና ፈሪ ሆኖ ነው የሚቀረው። ስንቱ ሕፃን ነው ከማለዳው ትምህርቱን እየጠላ የቀረው?!"

"ምን ችግርኝ? እኔ እንደሆን አንዴ ሽልንጌን ከፍዬ እንዳማር ሞክሬያለሁ። ከዚህ በኋላ ከዕዳው ነፃ ነኝ" አለና ወደ አርቡ ሄደ።

"ግዴለህም። እኔ ባሎቴ! እንኳን ለአብራኬ ክፋይ ለሌላ ውም አውቅበታለሁ። የቆንጋይን ጉዳይ ለእኔ ተወው" አለችውና ወደእኔ ዞራ "ቆንጋይ፣ የማይጋረፉበት ቦታ ብወስድህ እትማርም?"

"እማራለሁ!"

ስድስት ሰዓት ላይ መቃ ፈደሌን ይዘልኝ መጣ። ከእነሱ ትምህርት ቤት መውጣቴን ስነግረው በጣም አዘነ። እንዳልወጣ ሲለማመጠኝም "ቆንጋዬ፣ ዝም ብለህ ነው የፈራኸው። ለአለቃ ችን የዚያን ጊዜ ትንሽ አሹቅ ብትሰጠው ምንም አይነካህም ነበር። እኔም ሀሁን ቶሎ ቶሎ አስጠናሃለሁ። ወዲያው ሀ-ግእዝ፣ ሁ-ካኢብ ትገባለህ። ከዚያም ሀማዕገ፣ ለማዕገ ትደርሳለህ። በመ ሁ-ካኢብ ትገባለህ። ከዚያም ሀማዕገ፣ ለማዕገ ትደርሳለህ። በመ ቀጠል አቡጊዳ እንደገባህ እኩል እንሆናለን። ጎን ለጎን እንቀ መጣለን። ብስክሌት አስነዳሃለሁ።" አባቴ አባባ ወልደሥላሴ ፈረ ንጅ ቤት ስለሚሠሩ ብዙ የፈረንጅ መጫወቻ ቤታቸው አላ ቸው። አብረን ነው የምንጫወትባቸው።

"እንቢ! አልፈልግም!" ጮኩኝና "ከፈለክ እዚህ አስጠናኝና ሌላ ትምህርት ቤት አብረን እንግባ።"

መቃ ሌላ ትምህርት ቤት የመግባቱን ሃሳብ አልጠላም ነበር፣ እናቱ እማማ አመለወርቅ እሺ አይሉትም። በማስጠናቱ ተስማምቶ ከአቡጊዳ ያልዘለለ እውቀቱን ያካፍለኝ ጀመር።

በመማማሩ ሒደት የፊደላቱን ብዛት ለመለየት የሚደረ ገው ጥረት አሰልቺና አታካች እየሆነብኝ ሄደ። በድግግሞሽ ከፊደላቱ ጋር መተዋወቄ ግን እየጨመረ መጣ። የመቃ መምህ ርነት በጣም ተስማምቶኛል። ሲደክመኝ "እንረፍ" ስለው አይቃወ መኝም። እሱም ወዲያው "እሺ" ይልና ካረፍን በኋላ የልጅ አስተዋይነቱን እንድመለከት ይጋብዘኛል።

"ፋንጋይ እይ 'ጨ' ሦስት ቀለበቶች አሏት።"

"አዎን! ይህችኛዋ ደግሞ ሸፋፋ ነች አልኩት።

"አዎን 'ፖ' እቺስ ቶ? እጆቿን ዘርግታለች።"

"እቺስ የተጠቀለለችው?"

"አዎን 'ወ' ነች!"

"ይህችኛዋስ እግሮቿን ቀጥ አድርጋ ቆማ እጆቿን ወደ ሰማይ ሰቅላለች" አልኩት 'ዘን እያሳየሁት።

"ልክ ነህ" አለኝና መቃ ጨዋታ ቀየረ። "ነገ ከበደን ልንጠ ይቀው ሐኪም ቤት እንሄዳለን። አንተም ከእኛ ጋር ለምን አትሄድም?"

ከበደ ወልደሥላሴ ታላቅ ወንድሙ ነው። አሞት ደጃች ባልቻ ሆስፒታል መተኛቱን ሰሞኑን ቡና እየተጠጣ ወላጆቻችን ሲያወሩ ሰምቻለሁ።"መሐድ እፈልጋለሁ። ቆይ እማዬን ልጠይ ቃት" አልኩና ፊቴን ወደ ጓዳ መልሼ "እማዬ፣ ነገ ሐኪም ቤት ሔደን ከበደን እንጠይቀው?"

"አይ! መጠየቅ እንኳን ነበረብን። ዳሩ ይሞላልኛል ብለህ ነው?" አለችኝ። ሊጥ እያቦካች ነው።

ፈጥኜ ሄጄ ባንነበሰችበት አቀፍኳት። ሐኪም ቤት ይዛኝ ሄዳ እንድታሳየኝ እየሳምኳት አለማመጣት ጀመር።

"አቤት ያንተ ነገር!" አለችና ካንነበሰችበት ቀና ብላ እየ ችኝ። እጇ ላይ ሊጡ በወፍራሙ ተመርጓል።" አንድ ነገር ሰማህ 'ውለዱ! ሱራ ባንገት!' ነው። ምን ይሻልሃል? እሺ ሥራ ክሌለኝ እንሄዳለን።"

"ውይ በናትሽ እሺ በይኝ!"

አቅማማችና "እሺ!"

መቃ አብሮኝ ቢሰማትም ፈቃደኝነቷን አበሰርኩት። በጣም ቸኮሰተ። ጠጋ ብሎልኝ አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀምጠን እንደ ፉና ያስተምረኝ ጀመር። ከህ አስከ ፕ" ቆጠርን።

መቃ ፈደሉን ቁጭ አድርጎ የሐኪም ቤት ልምዱን አጫው ቹኝ። በሚቀጥለው ቀንም ሆስፒታል ስንሄድ መቃ እንደነገረኝ ወንድምየው የተኛው ፎቅ ላይ ነበር። ኮፍሉ ውስጥ ለንግሳ ከበደ አንዲት ንውህ አልጋ ላይ ተኝቷል። ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ፍራፍ

ሬዎች በወረቀት ከረጢት፣ አረንቻታው በጠርሙስና በብልቃጥ መድኃኒት ራስጌው ባለች አነስተኛ ኮመዲኖ ተደርድረዋል።

ከበደ ከፍራፍሬዎቹ ለእኔና ለመቃ እንዲሰጡን እናቴን አስታወሰ። ከየአይነቱ ተሰጠን። እስከምንጠግብ በላን። አንዳንድ አረንቻታ ተደገመን። እየጣፈጠን ጠጣን። ፎቅ ላይ ቆመን በማደ ሰዎች ሲያልፉና ሲጮሀ ሙ፣ መኪናዎች ከወዲያ ወዲህ ሲተላለፉ አስተዋልን። ይህ ሁሉ አደናቆቴን ከፍ አደረገው። ምቾቱም ማረከኝና ከበደን ሌጋ ብዬ "መርፌ ይወጉሃል?" አልኩት። በዚያን ሰሞን እኔም ጉሮሮዬን አሞኝ አስር አለቃ ወልዴ መውጊያ መርፌአቸውን እማዬ በትንሽ ድስት እየቀቀለችላቸው አክመውኛል። በዚህም «እጄ መድኃኒት ነው!» ትልልቅ ሰዎች ሲሏቸው ሰምቻለሁ።

"ተወግቼ አላውቅም። የምጠጣው መድኃኒትና የምውጠው ኪኒን ብቻ ነው" አለኝ ፈገግ ብሎ።

"ትምህርት ቤትህ ትሄዳለህ?"

"ካልዳንኩ እንዴት ትምህርት ቤት እሄዳለሁ?"

"ሐኪሞቹስ አይቆጡህም?"

"ለምን ይቆጡኛል? አይቆጡኝም። ቶሎ እንድድንላቸው ግን ያክሙኛል?"

"እንዳንተ አሞኝ እኔም እዚህ ብተኛ ደስ ይለኝ ነበር።"

ከበደ በጣም ሳቀ።

እማማ አመለወርቅ ልጃቸው ከታመመ ወዲህ እንዲህ ስቆ አይተውት ስለማያውቁ ተገርመው "ምን ተገኘ?" ሲሉ እሳቸውም ፈገግ ብለው ጠየቁት።

እኔ ያልኩትን ነገራቸው።

አዋቂዎቹ በሙሉ ሳቁ።

"አይ የልጅ ነገር" እያሉ ከሌላ ገጠመኛቸው ጋር አዛምደው መጨዋወቱን ቀጠሉ። እኔም ምኞቴን በልቤ ይዤ እዚያው በዚያው ረስቼ ከእኩያ ጓደኛዬ ጋር ጨዋታ ጀመርኩ።

በሚቀጥለው ቀን እማዬ አተር ክክ በሰሌን ላይ አስጥታ የሰፈር ልጆች እንዳይዘግኑ፣ ዶሮዎች እየጫሩ እንዳይበትኑት እጠብቃለሁ። "በደንብ ከጠበቅክ የማደርግልህን እኔ ነኝ የማውቀው" ስላለችኝ የሰፈር ልጆችን አንዴ እንኳ አላዘግን ብያ ቸዋለሁ።

ቀጢላው እየኮመከኝ፣ እየተለማመጠኝ ሊዘግን ሲል፣ ከእን ቅልፉ እንደባነነ ሁሉ ከሳቁ ውስጥ ነቅቼ "ተው!" ስል ተቆ ጣሁት።

"እምቢ ካለ በግድ እንዘግናለን" አለች መኩዬ ቀጫ ጫው። ደፋር ነች።

"እማዬ!" አልኩ ክኩን እያስተዋልኩ።

መኩዬ እሳት እንደነካት ሁሉ እጇን በፍጥነት ሰብስባ እግሬ አውጪኝ አለች።

"ምንድነው?" አለች ማድቤት እንዳለች።

"ይህቺ መኩዬ በግድ ልትዘግን ነው።"

"አንት ቀጫጫ፣ አታርፍም? ዋ! የመጣሁ እንደሆን ፈስዘን ነው የማስጨርስዘ" አለች እዚያው ማዕድቤት ውስጥ እያለች።

መኩዬና ቀጢላው እንደ ወፍ በረሩ። በሃምሳ አለቃ ታደሰ ቤት ግድግዳ ተከልለው ግማሽ ቄንቅላታቸው እየታየኝና ዓይኖ ቻቸውን እያቁለጨለጩ ይለማመጡኛል።

"ብታርፉ ይሻላችኋል። ይኼ ክክ እኮ የእማኑ ቂርቆስ የሰለት ክክ ነው" አልኳቸው ጮክ ብዬ፣ የእማማ በለው ገጠ ብልሃት ትዝ እያለኝ። እማዬ ማድቤት ውስጥ ሥራዋን እየሠራች የምለውን ሰምታ ስትስቅ ትሰማኛለች።

እማማ በለጡ የሽሮ ክክ ፀሐይ ላይ ካሰጡ እሳቸው ሳያዩ እኛ ዘግነን እንደምንቅም ያውቃሉ። ስለዚህ ክካቸውን ሲያሰጡ የምንጫወተውንም ልጆች ሆነ በየቤታችን ያለነውንም በሙሉ ጠር ተው ይሰበስቡናል። ሳቂታ ናቸው። ሲቆጡም እየሳቁ ነው። በጎ ጣጣነታቸው ትልልቅ ሰዎች በለጡ ገጠ ይሏቸዋል። ልጆች ግን እማማ ብልጧ ነው የምንላቸው። ወደ ክካቸው እያሳዩን "ተመልከቱ ይህ ክክ የእማኑ ቂርቆስን ጠበል ጠዲቅ የማደርግበት የሰለት ክክ ነው። አሁን እኔ አስጥቼው ሳላየው ዘግኖ የበላ ልጅ ወዮለት። እኔ ባላየው እማኑ ቂርቆስ ስለሚያየው ተቆጥቶ ሆዱን አሳብጦ ፊስ በፊስ አድርጎ ነው የሚገለው። ስለዚህ እንዳት ቀሰፉና እኛንም ከፍተኛ ሃዘን ላይ እንዳትጥሉን፣ አደራ እንዳ ትዘግኑ። ላልሰሙት የሰፈር ልጆች ሁሉ ንገሯቸው" ይሉና ትንሽ ትንሽ ክክኩ ቆንጥረው ይሰጡናል። መኩዬ ቀጫጫው ፊርቆ ሲያፈገፍግ "አይዞህ አሁን ብላ። እኔ ስለሆንኩ ቆንጥሬ የሰጠ ኋችሁ እማኑ ቂርቆስ ምንም አይልም" ይሉን ነበር።

ልጆች ሳለን ትልልቅ ሰዎች የመክሩንን እንሰማለን፣ የሚነ ግሩንን ሁሉ እንደ ሕግ እናከብረዋለን። ይዘችኛዋ የእማማ በለጡ የሥነ ልቡና ትእዛዛቸው በትንሿ ሕሊናችን ውስጥ ገዝፋ የምትፈጸም ኃያል ሕግ ነች። ከማያሳድገን ከእማኑ ቅዱስ ቂርቆስ ጋር በክክ ሌብነት መጣላት ስለማንፈልግ ትእዛዘዋን በፍጥነት እንፈጽማታለን።

መኩዬ ቀጫጫው ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ላይ ዱምቡሎ አገኘችና አንስታ ፓስቴ በላችበት። እማኑ ቂርቆስ ስላያት ሆደን አሳመመው። በጣም አስቀመጣት። ለረጂም ጊዜ ታመመች። ሞተች ሲባል፣ ብዙ መድኃኒት ጠጥታ ዳነች። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ቀጫጫ ሆነች። በስሟ ላይ ቀጫጫው የሚለው ቅጥል ተጨመረባት። ለእንቁ ጣጣሽ አበባ ሰጥታ ፍራንክ ስታገኝ ከቂርቆስ ላይ የሰረቀችውን ዱምቡሎ ለደብሩ ከፈለች። አሁንም የእማዬን ክክ ካልዘገንኩ ብላ

የምታስቸግረው መኩዬ ቀጫጫው 'ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም' እንዲሉ ሆኖ እግሯን ሰብሰብ አደረገች።

"ጎሽ የእኔ አስተዋይ! ልክ ነህ። ይህንን የስለት ክኬን ትነኩና ወየውላችሁ" አለች እማዬ ከማድቤቱ ብቅ ብላ።

ከልጆቹ ጋር መፋጠው ጋብ አለ። የአባባ መሹ ዶሮ ግን በማን አለብኝነት ግዙፍ አካሏን እያንጎማለለ፣ አካባቢውን እየ ቃኘ፣ ሚሰቶቹንም በኩራት እየጠራ ወደ ተሰጣው ክክ ተራ መደ።

"እሽ!ሽ!ሽ!" አልኩት።

በዶሮኛ አቀራራ። እኔን እሰከነመፈጠሬም ችላ ብሎ ከኬሻው ላይ ተፈናጥራ የወደቀች አንድ ክክ አነሳና ላይበላት መልሶ መሬት ጥሎ ሚሰቶቹን ጋበዘ። ተንደርድረው ወደ እሱ እየሮጡ መጡ። አንደኛዋ ቄብ ዶሮ ጥሬዋን ለቀም አደረገቻት። ወላጇ ዶሮ ቄቧን አባረረቻት። አውራው ወደ ክኩ ማዕድ ተራመደ።

"እሽ! ሽ! ሽ!"

አቀራራ።

ተናድጄ ባዶ እጄን ልገጥመው ተንደረደርኩ።

አውራ ዶሮው እግሩን አንፈራጠ ጠበቀኝ።

"እሽ! እሽ! ሽ! ሽ!" ብዬ በእጄ እየቃጣሁ ገሰጥሁት።

ሽቅብ ዘሎ ከንፈሬን ነከሰኝ። ድብን የሚያደርግ ቁንጥጫ ያክል ተሰማኝ። ትንሽ ቆይቶ ደም ከከንፈሬ ላይ ይፈስ ጀመር። ተደናግጬ ጨኸቴን ለቀቅኩ። እናቴ ከተፍ አለች። ጉዳዩን እያጣራች የመጀመሪያ ዕርዳታ እንዲደረግልኝ የምጣድ ማሰሻ መጣ። እኔ ግን በዜማ "ቶሎ ወደ ሐኪም ቤት ውሰዱኝ!" እያልኩ አሪታዬን አስነካሁት።

ወላጅ እንደ ሐኪም

"የሰው ልጆች ሁለት ነገሮችን ሰናጣ ይቆጨናል።
አንዱ ልጅነትን ሲሆን፣ ሌላው ጤናችንን ነው"
-የአረብኛ ምሣሌ

የአባባ መሹ ዶሮ ባደረሰብኝ የመንቆር ጥቃት ለጥቂት ቀናት ቁስለኛ ሆንኩኝ። ዶሮውም የማጎበረሰባችንን ሕግ የማይከ ተል አመፀኛ በመሆኑ ታረደ። እንድበቀለው አባባ መሹ ምሳ ጋበዙኝ። ጎረቤት ሄጀ ምግብ የመመገብ ልማድ ስላልነበረኝ ግብ ዣቸውን አልተቀበልኩትም።

በልጅነቴ ወቅት በጣም ሕመምተኛ ነበርኩ። ከአንዱ ሕመም ሰድን ሰንበትበት ብሎ ሌላኛው ይከተላል። በዚህም ሳቢያ ወላጆቼ ያልተሳሉት ታቦት፣ ያላማከሩት የመድኃኒት አዋቂ፣ ያልበጠሱት ቅጠልና ያልማሱት ስር እንዳልነበረ በደንብ አስታ ውሳለሁ።

ነፍሰ ከማወቄ በፊት ሞተ ተብዬ 'ጉድጓዴ ተምሶ ልጤ ተርሶ' አበቃለት ሲባል እንደገና ሕይወት እዘራለሁ። ቀኬው፣ ችፌው፣ የሆድ ሕመሙ ይፈራረቅብኛል።

ጤናዬ በተለያዩ ጊዜያት ቢከዳኝም ልጅነት ሰለነበር እያነ ክስኩም ሆነ ሻል ሲለኝ እየተንፏቀቅኩ ከጓደኞቼ ጋር እጫወ ታለሁ። ለቃዬን ሰለሚያሰረሳኝ መጫወቱን እወደዋለሁ። ወላጆ ቼም ጨዋታው ከሕመሙ ፋታ እንደሚሰጠኝ ሰለሚገባቸው በቅርብ ርቀት እየተቆጣጠሩ እንድሳተፍ ያደርጉኛል።

ከዕለታት በአንዱ ቀን እሽቅድምድም መጫወት ጀመ ርን። ከእማማ ጎደቴ ጠጅ ቤት ሮጦ የአባባ ዘውዴን ግቢ ነክቶ መምጣት ነበር ርቀቱ። መኩዬ ቀጫጫው ከፊቴ ትሮጣለች። እንደ ወፍ እየበረረች ነበር። እኔም እኩተሳታለሁ፣ ጥሩ ጤንነት እየተሰማኝ። መኩዬን እንቅፋት ቡድስ እደረጋትና መሬት ተዘረ ረች። የአውራ ጣትዋ ጥፍር ንቅል አለ። በወደቀችበት አራት ፍራንክ መሬት አየች።

"ባትጋሩኝ... በትኩሰ... እንጀራ... በመርፌ ቀዳዳ!" አለች ሕመሙ በሠራ አካላቷ እየተሠራጨ። ሕመምዋን ዋጥ አድርጋ ደሰታ ፍንድቅ ባለ ስሜት። ዓይኖቿ ግን እንባ አቅረዋል። እሷም እንደ እኔ ሰበበኛ ነች።

በልጅነታችን ፍራንክ ወይም ሌላ ጠቃሚ ዕቃ ያገኘ ሕፃን "ባትጋሩኝ! በትኩሰ እንጀራ በመርፌ ቀዳዳ!" ቀድሞ ካለ ማንም ሳይከፍለኝ ብሎ አያሰገድደውም። ለፍጥነትም ሲባል አላጥሮ "ባትጌ" ማለት ይቻላል።

"በናትህ ፉንጌ እግሬ ላይ ሽንትህን ሸናልኝ" ብላኝ መኩዬ የመጀመሪያ ዕርዳታ እንድለማሳት ተማፀነችኝ። እግሯን እንፈራጣ ተቀምጣለች። አራት ፍራንኩን ባታገኝ ኖሮ በጩኸት ምድር ሰማዩን ታደባልቀው ነበር። አሁን ባለፀጋ በመሆንዋ የጥፍ ሯን መነቀል ችላ አለችው። እኔም ወሸላዬን አወጣሁና አውራ ጣትዋ ላይ ሸናሁላት።

"ኡህ! ኡ! ሲያቃጥል!" አለች ላቅም ልቅሶም በተቀላ ቀለበት ድምፅ።

በደንብ ሸናሁባት። የአውራ ጣትዋ ደም ታጠበና ጮማ የመሰለ ነጭ ሥጋ ወጣ። ቁራጭ ጨርቅ ከወደቀበት አንሰተን አውራ ጣቷን ጠቀለልንላት። በረባሶዋን አሰተካክላ አደረገች። በዚህ መልክ የመጀመሪያ ዕርዳታው ሕክምና ተጠናቀቀ።

የእኔም ሆነ የአብሮ እደጎቼ ሐኪሞች በአብዛኛው ወላጆ ቻችን ነበሩ። አንዳንዴ ሕክምናቸውም ፍቱን መድኃኒት ይሆ ናል። በተወሰነ ደረጃ ግን መፍትሔ ይጠፋል። በዚህ ጊዜ ነበር ጣር ላይ ሆነን ወደ ሐኪም ቤት የምንወሰደው።

"ተማሪ ትምህርቱን እንዲገልጽለት ቡና መጠጣት የለበ ትም" የሚሉት ወላጆቻችን ራሳችንን ስንታመም አቦል ቡና በስኒ ይቀዱና ስኳር ጨምረውበት ጠኖ አዳም ነክረው ይሰጡናል።

ሆዳችንን ሲያመን 'ድንገተኛ' እንድናኝከ ያደርጉናል። መጋኛ ሲመታን በሲኒ ከበር ደፍ ላይ በቢላ ተፈቅፍቆ፣ ትንሽ አመድ፣ በላዩ ላይ ውሃ፣ ጨው ወይም ስኳር ይጨምሩበትና በጥ ብጠው "ጅው አድርገው ይሻልሃል!" ይሉናል። እንታዘዛለን። ጤንነታችን ብዙም ሳይቆይ ይመለሳል። ጉንፋን ሲይዘን ባህር ዛፍ ይቀቅሉና ያጥኑናል።

አንድ ዕለት ሆዴን ቆረጠኝ። እማዬ ሆዴን ዳበሰችውና በጣቷ ወጋ ወጋ አድርጋ መረመረቺኝ "ቆይ ነገ ጠዋት መድ ኃኒት እሰጥሃለሁ። ጠዋት፣ ጠዋት ነው የሚዋጠው" አለቺኝ። ጠዋት እንደተነሳሁ መድኃኒቱን እንድትሰጠኝ አስታወስኳት። ቁርሴን በሶ እየሰጠችኝ፣ "ይህንን ብላ አሁን መድኃኒቱን እዘጋ ጅልሃለሁ" አለቺኝ። ሳሕኑን ተቀብዬአት የተጨበጠውን በሶ መግ መጥ ጀመርኩ። በጣም መረረኝ። "እማዬ ይመራል!"

"ዝም ብለህ ብላ። ሞርስ አድርገው መድኃኒቱን ቀጥፍ አሰጥሃለሁ። ሻይ ደግሞ ስለሚፈላልህ የሚመረው ይጣፍጣል።"

ሻይ እኛ ቤት ብርቅ መጠጥ ነው። ተናፍቆ ስለሚጠጣ፣ ሻይ እንደልቤ ለመጠጣት እንዲያስችለኝ በሶውን ከነመምረሩ አጣድፌው ጀመረ።

አባቴ ፈገግ ብሎ አስተዋለኝ 'ሲያርስ የዋለ ማረሻ ፣ግርግዳ ላይ ተሰቅሎ፣ ቤት የዋለው ማንኪያ ገንፎ ውስጥ ጥልቅ አለ' አለና በጋሞኛ ተረተብኝ። "ኧረ! ቀስ በል ያንቅሃል! በልኩ ብት ጎርሰው ምን አለበት?"

እማዬ በጆሮግንድዋና በሻሽዋ መካከል ባሳት ምስጢር ኪስ ውስጥ ሚንቲም እንዳለ ፈተሸች። አሳገኝችም። "ዜራሞ እስኪ ለፉንጋይ ሻይ ቅጠልና ስኳር መግባ ስድስት ፍራንክ ስጠኝ?"

"እንዴ! ይሄ ቤት የአረብ ቤት ነው እንዴ!? የምን ሻይ ነው?" አሳት። እሱም በሶ እየበላ ነበር።

"ተወው ባክህ እኔ ለልጄ ሆድ አላንስም" አለችና ወደእኔ ዞር ብላ "ሞርስ አድርገህ ጠብቀኝ። እኔ ደግሞ ወሬ ሳላይ አፍ ታም ሳልቆይ ከተፍ እላለሁ" አለቺኝና ራስጌ ካለው መሃረብዋ ፍራንክ ወስዳ ወደ ሱቅ በረረች። እኔ ደግሞ እሷ ሳትመለስ በሶ ውን ለመጨረስ ዋጥ፣ ዋጥ ማድረጌን ቀጠልኩ።

"ኧረ! ጋሼ እንዳያንቅህ" አለ አባቴ። አበላሌ አላማረ ውም። "አሁን የጎረስከውን ሁለቴ ልትጎርሰው ትችል ነበር" ጆሮ ዳባ ልበስ ብዬ 'ወጠቅሁ'። እማዬ ስትመጣ በሶውን ጨርሼ ውሃ እየጠጣሁ ነበር። "ጎሽ የእኔ ፉንጋ!" አለቺኝ ሰሃኑን እየተቀ በለቺኝ።

ቤታችን በዚያን ወቅት የሻይ ማንቆርቆሪያ አልነበረም። ትንሿን የወጥ መቀነሻና ማሞቂያ ድስት ምድጃው ላይ ጣደች። በዚህች ድስት የሚፈላ ሻይ ቃናው ወጥ ወጥ ይላል። ይሁን እንጂ ያው ሻይ ስለሆነ ተሻምተን እንጠጣዋለን። በሻይ መጠ ጣቱ ምንጊዜም ቅድሚያ የሚሰጠኝ ለእኔ ነበር።

እማዬ ሻይቅጠሉን በፈላው ውሃ ውስጥ እየጨመረች "እንዴት ነው፣ ይጣፍጣል አይደል?"

"ይመራል።"

"ግዴለህም፣ ሆድህ ሲድን መጣፈጡን ትረዳለህ" ብላ ብርጭቆ ለማምጣት ወደ ጓዳ ገባች።

አብሰለሰልኩ። የእማዬ ባሕርይ ሁሌም እንዳስገረመኝ ነው። ሁሌም በአስተሳሰብ እልፍ እርምጃ ትቀድመኛለች። እንዲህ አይነት መራር ምግብ ሰጥታኝ "ይጣፍጣል!" ብላ ቀምሳ ትባርከልኛለች።

"እንዴ? ይህንን ምኑ ይጣፍጣል ትይኛለሽ እንጀራው እኮ ሻግቷል!" ብዬ ሙግት እገጥማለሁ።

"ዝም በል! ይሄ ምኑ ሻገተ? አሳየህም ወጡ ውስጥ ቅቤ ዛቅ አድርጌ ስጨምርበት?" ብላ ደህና ጉርሻ ጠቅልላ ትጎርስና "ልጄ የድሃ ልጅ ያገኘውን በልቶ ነው የሚያድገው" ስትለኝ መሻማት እጀምራለሁ። ቅቤ የገባበት ወጥ በጣም እንደምወድ በደንብ ታውቃለች።

ጣት የሚያስቆረጥም ወጥ የሠራች ዕለት ለእኔና ለአባቴ እያቀረበችልን "ብሉ እስኪ እንደነገሩ ቢሠራም" ትላለች።

እኔ ደግሞ ቶሎ ቶሎ እየጎረስኩ "እማዬ ይሄ ወጥሽ እኮ በጣም ይጣፍጣል። ለምን እንደነገሩ ነው የተሠራው ትያለሽ?" ስላት፣

የሰበጣ ሳቅ እየሳቀች "እሺ የእኔ ውሻ፣ አንተም ወጥ ታውቃለህ?!" ብላኝ ፈገግ ትላለች። እስተያየቷም እኔን እኔ ከማውቀው በላይ እሷ እንደምታውቀኝ ብልህ ዓይናችዋ አብጠር ጥረው ያሳዩኛል።

ሻዩን መቅዳት ጀመረች።

"ባሎቴ" አባቴ ተጣራ።

"አቤት።"

"በሞቴ ይሄ ብርድ አንጀቴ ውስጥ ገብቶ አንሰፈሰፈኝ። ለእኔም በክብር ዘበኛው ብርጭቆዬ አንድ ቅጅልኝ" አለ አባቴ፣

እናትና ልጅ ተሳሳቅንበት። እሱም አብሮን ሳቀ ዕለቱ ፀሐያማ ነው።

ለእኔ ስኳሩን በዛ አድርጋ፣ ለእሱም በሚወደው ብርጭቆ ቀዳችና ሰጠችን። "እኔ ለቡና እንጂ ለሻይ ግድ የለኝም" ብላን "ቶሎ ቶሎ ጠጣ፣ አሁን ሆድህን ያሽልሃል።"

ከሰዓት በኋላ... ስሞክር አንድ ያልለመድኩት አካል ከሰውነቴ ውስጥ ሲወጣ አየሁና በድንጋጤ "እማዬ" ብዬ ተጣራሁ።

ከተፍ አለች።

ቁልቁል ከአካሌ ውስጥ የሚወጣውን ነገር አሳየኋት።

"አይዞህ፣ የኮሶ ትል ከሆድህ ውስጥ እየወጣ ነው" ብላ አረጋጋችኝ።

"በበላሁት ቁርስ ውስጥ የኮሶ መድኃኒት ጨምረሽ ነበር?"

"ቂል አትሁን። እያየኸው? የታባቱ!! ይሄ ነበር ሆድህን የቆረጠህ። ከዚህ በኋላ ሥጋ ሳይበስል አትብላ።"

"እሺ" ብልም ሲያምረኝ ግን አትጨክንብኝም።

አንድ ሰሞን ደግሞ ሆዴ ተነፋቶ ከሌላው አካላቴ ሁሉ ገዘፍ መታየት ጀመረ። ምን ማድረግ እንደሚገባት እማዬ ጎረቤቱን ማማከር ጀመረች። በዚህ ወቅት የአባቴ የሸማ ደንበኛ የሆኑት እማማ ድንቡሉ ድንገት ደረሱና "ለምን አንድ ሲኒ ቤንዚን አታጠጭውም። የኔን ልጅ ዘሩን ባለፈው ሣምንት እንደው ሆዱ ከበሮ ቢያክል አንድ ሲኒ ቤንዚን አጠጥቼው ዳነ። ጥርግርግ አድርጎ ወስፋቱን አወጣለት" አሏት።

እማዬም የእማማ ድንቡሉን ምክር ሰምታ ተግባራዊ አደረገች። ትገ ይለኛል፣ የዚያን ዕለትም በምወደው ሻይ ተስፋ ተደልዬ አንድ ስኒ ቤንዚን ጠጣሁ። ሻይውም ተፈላልጎኝ። ይሁን እንጂ የቤንዚኑ ጠረን ሙሉ በሙሉ የሻዩን ጣዕም አጠፋብኝ። የዚያን ዕለት ቀኑን ሙሉ መኪና ሆኜ ዋልኩኝ። እያንዳንዱ የምሰማው ድምፅ ሁሉ የሞተር እንደነበር አስታውሳለሁ። ስራ መድ እንገዳገዳለሁ። የሚገርመው፣ ተፈላጊው ፈውስ በዚህ መድኃኒት ተገኝቶ የሆዴ እብጠት ቀነሰ።

በሕፃንነቴ የስለት ልጅ ይመስል በጣም ሰበበኛ ነበርኩ። አሁን እንደዋህ የምተርከው ያ የስቃይ ወቅት ሰቤተሰቦቼ መፈጠሬ ያሳዝናቸው፣ ይፀፅታቸው እንደነበር አስታውሳለሁ። ገና ነፍስ በማላውቅበት በ1950ዎቹ በአገራችን ክፉ ረሃብ ተከሰቶ ነበር። 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ' እንዲሉ፣ እንደ እኔ ከገቅ ተኛው ማኅበረሰብ ውስጥ ለተፈጠሩ ሕፃናት ጊዜው የሰቆቃ ሆኖ ነበር።

ነፍስ ካወኩ በኋላ እማዬ ስለዚህ ወቅት ረሃብ ስትተርክልኝ "ልትሞትብኝ ነበር። የዚያን ጊዜ ነው ስምህ ፋንጋዬ የተባለው። እንዲሁ ፍገዝ ብለህ ዓይንህን ብቻ ታስለመልማለህ። ቅርት አልክ። ጊዜው ክፉ ነበር። ረሃብ ድፍን ኢትዮጵያን መታት። ከታኅሣሥ ግርግር በኋላ በአገራችን ችግር ነገሠ። ጊዜው የሩዝ

ጊዜ ይባላል። ጃንሆይ ቢጨንቃቸው ሩዝ ከውጪ አገር አስመጡ። እሱንም ፍራንክ እንደልብ ያለው ነው የሚሸምተው። ቸግሮህ ወረቅም፣ ጨርቅም ግዛኝ ብትል ማንም አይሸምት። ዕቃ ንብረት ሁሉ ጥንቡን ጥሏል። በጊዜው እፍኝ ጥሬ ይበልጣል። እንደ እኔ አይነቱ ድሃ ገንዘብ ከዬት ያመጣል? ዓይኔ እያየ ልጅ አይሞትም ብዬ፣ አባቴራን ሰፈር ቡላ የሚባል የአገራችን ሰው ወጌሻ አለ። መድኃኒት አዋቂ ነው። የልጆች ግግ ይነቅላል፣ የተቀጨ ካለ ያሻል፣ ውልቃትም ካለ ያስገባል። እጁ መድኃኒት ነው። አንድ እግሩ ሰላሳ ነው። ሰው ኖሮት አምስትም፣ አስርም ብር ቢከፍል ይቀበላል። መልስ የለም። እንደ እኔ አይነት ድሃ ከመጣበትም በነፃ ያክማል። 'ልጄን አድንልኝ' ልለው ይገደህ ስሄድ 'አንቺ ባሰ-ቴ' ሲሉኝ ሰማሁ። ዘወር ብል እትዬ ዘነቦች መኮንን ናቸው። እናቴ የአገር እናት ቤታቸው ሁሌም ሙሉ ነው። ነፍሳቸውን አምላክ ይማረው አሁን አርፈዋል። አቤት አልኳቸው።

'ወዴት እየሄድሽ ነው?'

"ልጄን አሞብኝ ቡላ ጋ መድኃኒት ፍለጋ እየሄድኩ ነው።"

'ነይ እኔጋ መድኃኒት አለ እሰጥሻለሁ ግቢ።'

"ጨንቆኛል። እትዬ መላ አያጡም ብዬ እሺ አል ኳቸው።'

'አንድ እንጀራ በሰሃን አመጡ። ያኔ እንጀራ ብርቅ ነው። እንኳን ሊበሉት ሊያዩት ይናፍቃል። አይ ማጣት! የት አባቴ! የተቻለውና ከርስቱ የሚያስቈጭን ካልሆነ፣ ማንኛውም ድሃ ቤት እንጀራ አይደለም፣ ጭብጥ ጥሬ አይገኝም። በርበሬ ድልህ ዛቅ አድርገው ሰጡኝ። አንቲን ከእዝሌ አውርጄ ታቅፌሃለሁ። ጠረጴዛ ላይ አኖሩልኝና።

'ብይ' አሉኝ።

"እርቦኛል! አይ ሞት! ጨካኝ ነው። አሁን እትዬ ይሙቱ?" ትንሽ ስትቆጭ ቆይታ ትረካዋን ቀጠለች።

"እየተንሰፈሰፍኩ በላሁ። አበላሌ እህል ዓይቼ የማላውቅ ይመስላል። መቼም በክፉ ጊዜ ማን ማንን ይታዘባል? ውሃ ሰጡኝ፣ ግጥም አድርጌ ጠጣሁ። ቡና አፈሉ። አምሮኛል። የቡና ሱስም አለብኝ። ስለ ክፉው ጊዜ እያነሳን ደጉን ጊዜ እንዲ ያመጣው እየተጨዋወትን ጠጣንና ተነሳሁ። ቡላጋ ለመሄድ። መድኃኒቱን? አልኳቸው አንቲን መልሼ እያዘልኩ!"

'መድኃኒቱን?! መድኃኒቱንማ አንቺ ውጠሻል። ከእህል በላይ ምን መድኃኒት አለ? ይልቅ ቁጭ በይና አጥቢው። አሁን ይድንልሻል' አሉኝ እየሳቁ። ችግሬ ገብቶዋቸዋል። ቀይ ቆንጆ ናቸው። ታውቃቸዋለህ? ...እንዳሉኝ ከእዝሌ አውርጄሀ ጡቴን አውጥቼ አንረስትሁ። ተስገብግበህ ጠባህ። ለካ ሬሃቡ ጡቴ ወተት ማፍለቅ እንዳይችል ከልክሎታል። ጡቴን ጠባህ ጠባህና ዓይንህን

ገለጥከ። ተመስገን አልኩኝ። እንዲህ አይነት የክፉ ቀን እናት ናቸው እትዬ ዘነበች። እውነትም ተእህል በላይ ምን አይነት መድኃኒት አለ?"

ነፍስ ካወኩ በኋላ በጣም እሰቃይበት የነበረው ሕመም ችፌ ነበር። አንዳንዴ የአንድ እግሬን መዳፍ ሲወረው፣ በሌላ ጊዜ ሁለቱንም እግሬን ያመኝ ነበር፤ ቁስሉ በእግሬ ላይ ችፍፍ ብሎ ከመነፋረቁም በላይ በጣም ይሸኝና ያሳክከኝ ነበር።

መንደርተኛው ባትሪ ድጋጋይ ተቀዋቅሎ ከውስጡ የሚወጣውን ካርቦን እግሬ ላይ እንድትደመድምልኝ እማዬን መከሯት። የጨነቃት እማዬ መፍትሔ ያገኘችኝ መስሏት ምክራቸውን ተግባራዊ አደረገች። በተደመደመልኝ ጥቂት ደቂቃ ውስጥ የሚያሳብድ ሕመም ይሰማኛል። ማልቀስ ስጀምር "ገም በል፣ እየመ ዘመዘልህ ነው" ብለው ከጎረቤቶቻችን አንዷ ያፅናኑኛል። እማዬ ቶሎ ውሃ ታፈላና በሙቅ ውሃና በሳሙና ታጥብልኛለች። 'እከክን የሰጠ አምላክ ማከኪያን አይነፍግም' እንዲሉ፣ ሳከው ነፍሴ ጥቂት እፎይታ ታገኛለች። እፎክት እፎክትና አካሌ ይዝላል። አልጋዬ ላይ ተኝቼ ውጪ ውጪውን ሳይ እማዬ ተከዝ ብላ አጠገቤ እንደተቀመጠች አባ ዘለቀ "እንደምንዋላችሁ" እያሉ ገቡ።

አባንም የስፈር ልጆች ሁሉ እንወዳቸዋለን። "ልጆችና አረቄ እወዳለሁ። ሁለቱም ያሞቁኛል" ይሉናል።

ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም፣ ስለ ልጅዋ ኢያሱስ፣ ስለ ቅዱሳኑ፣ መላእክቱና ሰማዕታቱ የተረትን ያህል በሚጥም ቋንቋ ያጫውቱናል። አንዳንዴ በጨዋታው መካከል ወራቱ ያፈራውን እሸት ይገዙልናል። ሽምብራም ሆነ ባቄላ እሸት ሲደርስ አሁንም የማስታውሰው የኔታን ነው። ትልቅ ሰርያን ኮታቸው ኪስ ውስጥ "ኃይለ ራጉዔል አንዱን እጅህን ስደድ" አሉኝ እጄ ደርሶ ኮክ ጨበጠ። አኔን የሚጠሩኝ በክርስትና ስሜ ነው።

"ዛሄር ይመስገን!" አለች እማዬ፣ ተነስታ መስቀላቸውን ለመሳለም እየተዘጋጀች።

"እመት ባለሙቴ፣ ኃይለ ራጉኤል እንዴት ነው?" መስቀል አሳልመዋት "ደህና ናችሁ?" እያሉ ወደ ቤት ዘለቁ።

"እኔ እንጃለት" መለሰች እማዬ። የሚቀመጡበትን አግዳሚ እያመላከተች።

"አይዝምት፣ ሞትም ሕይወትም በእሱ እጅ ነው። አባ ገብረማርያም የሚባሉ የበቁ መነኩሴ እዚህ አራዳ ጊዮርጊስ ደብር ውስጥ ይኖሩ ነበር" ብለው ጨዋታ ጀመሩ። ከፊት ለፊቴ ባለው አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። እንደተለመደው ቤቱን ጠበል ረጭተው ስለሚሄዱ እማዬ በትልቅ ጣሳ ውሃ ቀድታ አመጣ

ችላቸውና "እሺ" አለች። ጨዋታቸው የተረት ያክል ለልጅ በሚ ጥም መልኩ ስለሚተርኩት ስሰማቸው ደስ ይለኛል።

"አንድ ቀን ጌታችን በሕልማቸው መጣና 'ገብረ ማርያም!' አላቸው።

"አቤት አሉ" አባ ጌታችን፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አውቀዋል።

"በል ተነስና ድፍን ኢትዮጵያን እየዞርክ ባርክ። ከሰሜን እስክ ደቡብ፤ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ እየባረካት እንድትጓዝ መርጬሃለሁ።"

"እንደ ፍቃድህ ይሁን" አሉ አባ። "ወጣትነታቸው ተመለሰ! አንድ ዘንግ ሲደክማቸው እንዲመረኮዙት፣ አንዲት ቢበሏት ቢበሏት የማታልቅ ጭብጦና አንድ ቅል ውሃ ጅው አርገው ቢጠጡት መልሶ የሚሞላ ሰጣቸው። ለሱ ምን ይሳነዋል? ቅሌን ጨር ቄን ሳይሉ ጉዞ ጀመሩ። ልክ መሃል አራዳ ሲደርሱ አምባ ጓሮ ተነስቷል። የአራዳ ልጆች እየተፋጁ ነበር። አንዱ ለሌላው ሰብቆ የወረወራት ጦር በአየር ላይ እየተወነጨፈች ስትመጣ አባ አስተዋሉና 'ጌታ ሆይ ተልዕኮዬን እስክምጨርስ ይዘንን መዓት ከእኔ ላይ ነለል አድርግልኝ" አሉት።

"ጦርዋ በአየር ላይ ቁጥ አንድትል አደረጋት።"

"ማን?" እማዬ የቡና ሲኒ እያቀራረበች ነው። እንደ ፊልም ትዕይንት ወለል አድርጎ የሚያሳይ ትረካቸው ሕመሜን አስረሳኝ። አካላቴ ሙሉ በሙሉ ጆሮ ሆነ።

"ባለቤቱ ነዋ! አይመረመሬ!"

"እዝጊዎ ለእሱ ምን ይሳነዋል!" አለች እማዬ ሰረቅ አድርጋ ስታየኝ መዝለፍለፌ ቀርቶ ነቃ ብያለሁ።

"አባ አልፈው ሄዱ ያለውን ትውልድ፣ መጪውንም ትውልድ ባረኩት። ያለፈው ምህረት እንዲያገኝ እየተማፀኑ ድፍን ኢትዮጵያን የተፈጥሮ ፀጋዋን እንዲባርክ፣ ትውልዱም በአግባቡ እንዲጠቀምበትና ብርሃናማውን መንገድ እንዲጓዘው አባ ለመ ኑለት። ልመናቸውም ተሰማ።

"ዞረው አዲስ አበባ ተመልሰው ልክ አራዳ ጊዮርጊስ ደብር እንደደረሱ 'ተመስገን! ላንተ ምን ይሳንሃል? ከዚህ በኋላስ ውሰ ደኝ!' እንዳሉ፣ ያቺ ጉዞአቸውን ሲጀምሩ ከአራዳ ልጆች የተወረወረች ጦር ከቆመችበት ተነስታ በደረታቸው ተቀበቀበች!።"

"ሞቱ?" አልኩ ሳላስበው።

"አዎን አረፉ። እሳቸው የበቁ ስለሆኑ የተወረወረባቸውን ጦር አዩት። እኛ ግን ባናየውም ከእናታችን ማኅፀን ተከፍለን ከወጣንበት ቀን ጀምሮ የተወረወረብን ጦር እየተከተለን ነው። ስለሆነም፣ ልጆችን በአግባቡ ማሳደግ፣ ሲታመሙ ማስታመም እንጂ፣ አብሬው ፍግም ካላልኩ ማለቱ ተገቢም አይደለም። ጭንቀትዎን የተረዱት አቶ ዜራሞ ልከውኝ ነው የመጣሁት!" አሉና ጨዋታቸውን ደመደሙ።

"እውነቶትን ነው። አንዱን በትንታ፣ አንዱን በጥይት፣ ሌላውን በስቅላት የሚቀጣው ራሱ ነው። እኒስ ምን ላርግ የፈጠረውን በወጉ እስኪወስድ? የወላድ አንጀት አይደል? አልችል ቢለኝ ነው" አስቻቸው።

አባ ሥርዓተ ፀሎታቸውን አድርሰው ቤቱን ፀበል ረጭተው ለእኔ ብርቱኳን ስጥተውኝ ሄዱ። አባቴ በዚህ ጊዜ መጥቶ ነበር። መንደርተኛው ተሰባስቦ የባጥ የቆጡን እያወራ ቡናው ተጠጣ። በችፈ ሕመሜም ለምን ያህል ጊዜ እንደተሰቃየሁ አሁን ትውስ ባይለኝም ምንም አይነት ሕክምና ሳይደረግልኝ ዳነ።

ብዙም ሳልቆይ ክትፎ ሜዳ ኪስ ስጫወት ወድቄ በግራ እጄ ላይ ውልቃት ደረሰብኝ። የዚያን ዕለት ማለዳ እማዬ አንድ ቦታ ስትልከኝ እንቢ ብያት ተበሳጭታ ረግማኝ ነበር። ምላስዋ ጥቁር ስለሆነ ብዙም ሳይቆይ ደረሰብኝ። ሌላው የስቃይ ምዕራፍ ተከሰተ። እጄን አንከርፍፌ ወደ ቤት ስገባ እናቴ አይታኝ "ውይ በሞትኩት! ምን ሆነህ ነው?"

"አንቺ ረግመሽኝ!" አልኩ በልቅሶ ዙማ።

"እሰይ! እንኳን! ማን አባክ የማዝህን እንቢ በል አለህ?!" አለችኝ። በአስተያየትዋ ላይ ግን ይህ እርካታ አይታይም።

አባቴ ፎኸ "ስመሆኑ ምን ስታደርግ ይሆን? ስብራት ይሆን ወይስ ውልቃት?!" ብሎ በጥያቄ ያጣድፈኝ ጀመር።

"ስጫወት ነው!" አልኩት በስቃይ።

ጎይቶም አሻር ውልቃቱ እንዴት እንደደረሰ ለአባቴ አስረዳው። ሲናገር ጥፋተኝነት ይታይበታል። እኔ ግን ተጋጭተን ስወድቅ ግራ እጄ እንደተሰበረ አውቃለሁ።

ከገጠር የመጣው ባላገሩ ዘመዳችን አቶ ቡሳ ወጌሻነት እንደሚሞክር ተናግሮ፣ ጠዋት፣ ጠዋት ቅቤ እየቀረበለት ያሰቃየኝ ጀመር። ማንም ጩኸቴን ሊሰማኝ ዝንፉ አልነበረም። ከአሁን አሁን ይድናል እያሉ ዝም እንድል እያበረታቱኝ ማሸቱን ቀጠለ። ከዕለት ወደ ዕለት ስቃዩ እየበዛ እብጠቱም ከፍ እያለ ሄደ። ይህ ባላገር ዘመዳችን ወሩ አገሩ የሚሄድበትን ቀን ናፈቅሁ። እንደ ምኞቴ ሳይሆን ሕይወት ያዘጋጀችልኝን ሲአል ሲያላየኝ ሰነበተ።

አልጋዬ አጠገብ እማዬ ምግብ አዘጋጅታ አብረን እንድ ንበላ አቀረበችልን። በዚህ ወቅት ወላጄቼ ሥጋ የምንበላ ከሆነ ለስላሳውን፣ ዳሩ ከሆነ የቡጡን ከፊቴ እያስቀመጠልኝ የማዕድን ሥርዓት ያስተምሩኛል። ከአባቴ፣ ወይም ከእናቴ ፊት ከቀረስኩ እጄን "ቲ!" ያደርጉኝና "ከፊትህ ብላ!" ይሉኛል። ይህንን ደንብ ካወኩት ቆይቷል። ይህ ባላገር ወጌሻዬ ከፊቴ ሲቆርስ በደህኛው እጄ "ቲ" አደረኩትና "ከፊትህ ብላ" አልኩት። አባቴም እናቴም አፍረው ተሸማቀቁ። እኔም ቂሜን ተወጣሁ።

ስምን ያህል ጊዜያት ግራ እጄን አንከርፍፈ እንደቆየሁ አሁን አላስታውስም። በተባረከ አንድ ዕለት እዚያው ክትፎ ሜዳ ግራ እጄን አንከርፍፈ ከንደኛዊ ጋ ብዬ እጫወታለሁ። አንድ ሽማግሌ ሰውዬ በሜዳው አቋርጠው ሲያልፉ አዩኝና "ና! ማሙሽ!"

ጨዋታውን ትቼ ተጠጋኋቸው። በርከክ ብለው ሹራቤን ገልጠው አስተዋሉኝ። ሌላ ሰው እንዳይነካኝ እከላከል የነበርኩት ልጅ ስለኝህ አዛውንት ዝም ብዬ ታዘዝኳቸው። ጥቂት ከመረቃቸው በኋላ እንትፍ እንትፍ አሉብኝና "የማን ልጅ ነህ?"

"የዘራሞ ኢንቻ።"

"የሽማኔው!?"

"አዎን!"

"ጠዋት አናትህ ይዝህ እኒ ቤት ና፣ እዚያ ማዶ አጥር ግቢው ይታይሃል። ፈረንጁ ወፍሮ ቤት ፊት ለፊት?"

"አዎን!"

"ያ ግቢ የኔ ቤት ነው። አይዞህ አድንሃለሁ። በጠዋት ነው የምትመጡት እሺ?" አሉኝ።

ለምን እንደሆነ ባላውቅም ልቤ መቶ በመቶ አምኗቸዋል። ጠዋት ከእናቴ ጋር ሄድን። በጥቂት ደቂቃ ውስጥ በእጄ ላይ ተአምር ሠሩ። ውልቃቱ ገላ። በረጅሙ ተነፈስኩ። ካለፉት ሳምንታት ስቃዬ አዛውንቱ ለዘለአለሙ ገላገሉኝ።

"ስንት ነው የምከፍለው?" ጠየቀች እናቴ፣

"ሁለት ሽልንግ።"

"ምነው አንድ ሽልንግ አይደለም እንዴ?"

"ከፊያ" አልኳት።

ከፈለች።

አዛውንቱም እየሳቁ "ደኽውለታ! ጉዳተኛው ጥቅሙን አውቆ ዳነን!" ብለው ሁለት ሽልንጋቸውን ተቀበሉ።

ባልና ሚስት

"...እረ ይሻልሻል ይሻልሻል፣
አበበ ቢቂላ ያገባሻል፣
ጥላሁን ገሠሠ ይደርሻል
- ልጆች ሆነን ከዘፈንነው

እናቴ ላይ -አንድ ትልቅ ጠባሳ አለ። እማማ ማሚቴ ናቸው ድሮ የፈነከቱኝ። አሁን ድንገት ይህንን ጠባሳ ስነካው በትዝታ ፈረስ ወደኋላ ሸምጥ ጋለብኩ።

ከጓደኞቼ ጋር ዕቃ ዕቃ እንጫወት ነበር። ይህ ጨዋታ ሴቶችንም ይጨምራል። እኔን ባል፣ መቅደስን ሙሽራ አደረጉ። የእናቷ የእማማ ማሚቴ ላሽ አናቷ ላይ እንደ ቬሎ በክር ሸብ ተደርጎ ቁልቁል ተለቆ አጊጣለች። አበባም ታቅፋለች። በእኔ ቁምጣ ላይ ምንም አይነት ለውጥ አልተደረገበትም። በግራ ትከሻዬ ላይ ያለው ውልቅ ውልቅ እያለ ያስቸግረኝ የነበረው ማንነቻ ከቀኙ ማንነቻዬ ጋር በልጥ ወደ ኋላ ታሰረ።

እኔና መቅደስ ጎን ለጎን ተቀምጠን እጆቻችን ተቆላልፈዋል። ሚዜዎቻችን በግራም በቀኝም ከአጠገባችን ተቀምጠዋል። አበረ ሻቃ የቆርቆሮ ከበሮውን እየደለቀ "ሙሽርዬ ሙሽር አበባ፣ ይዘህ በጊዜ ግባ!" እያለ ያዜማል። የከበሮ አመ ታቱም ሰምሮለታል።

"ኃይለሥላሴ ይሙት! የማታጨበጭቡ ከሆነ ከዚህ እናባ ርራችኋለን!" እያለ ሲሳይ ጉቢጥ ሕፃናቱን ያስጠነቅቃል። "ኃይሉ ዶሮ አታጨበጭብም?!"

ይጥና በዚያ ጆሮ በሚቧጥጥ ድምፁ አዝማቹን ካላወርድኩ ብሎ ከዜማው ጋር ግብግብ ገጥሟል። የድምፁ አወራረድ ባይስምርለትም ፍንደቃው ከልክ በላይ ሆኖ "ሙሽርዬ..." እያለ ሲያላዝን፣ አብነት ባሪያው በእወራረዱ ተበሳጭቶ በካልቾ ሊጋና ዝም አሰኘው።

ይጥና ሲነጫነጭ ባሪያው ፈገግ ብሎ በእናቲት አናንጫ ውን እያላበው "ምሳው እስከሚዘጋጅ አሁን ሽርሽር ሄደው ይምጡ" አለና እየተሽኮረመመ ሃሳብ አቀረበ።

ኃይሉ ዶሮ ከሽቦ የሠራትን የሙሽራ መኪና እያጠማዘዘ የኋሊት ሄደና ሙሽሮቹን ሊጭንን አዘጋጀ። ጡሩንባም የሞተር ድምፅም እያስማ አጃቢዎች ገለል ብለው መንገድ እንዲለቁለት ያስጠነቅቃል። የተበጠሰ ማንነቻው እንዳይጠልፈው አስር ጊዜ እየመለሰ ወደ ኪሱ ይከታል።

ውሮም ሌላ የሽቦ መኪና ይዞ በአጃቢነት ተሰልፏል። ቀጢሳው በከረሜላ ወረቀት የጠቀለለውን ጠጠር ለከበቡን ታዳ ሚዎች በተነላቸው። ጭብጨባው ጦፈ፣ ዘፈኑም ደመቀ፣ አልል ታው ቀለጠ። በደንቡ መሠረት የኃይሉ ዶሮን ሹራብ ይዤ ከኋላ ተሳፈርኩ። ከጎኔ እጇን ከእጄ ያቆላለፈችው መቅደስ ተሳፍ ራለች።

ሚዜዎቻችን በውሮ መኪና ተሳፈሩ። መስፍን ፑሉቶ እንደ የተሸነቆረ ጣሳ እንደ ካሜራ ዓይኑ ላይ እየደገነ "ገለል በሉ!" እያለ ሙሽሮቹን በተለያየ አቅጣጫ ፎቶ ያነሳናል።

በአጠገባችን ለጉዳያቸው የሚያልፉና የሚያገድሙ ትላልቅ ሰዎች ጭልጥ አድርጎ ከወሰዳቸው ሃሳብ ባነው ለደቂቃም ቢሆን ወደ ገሃዱ ዓለም በመመለስ "ምን ተገኘ?" ብለው ይጠይቃሉ። አንድም ቀን ሲስቁ ዓይቻቸው የማላውቀው አባባ ጥላሁን እንኳ ፈገግ ብለው "ያሳድጋችሁ! ለወግ ለማዕረግ ያብቃችሁ" ሲሉ ሰማኋቸው።

እማዬ ወደ ገበያ ስትሄድ "እነማን ናቸው ሙሽሮቹ?" ብላ ጠየቀች። እኔ መሆኔን እንዳየች" ውይ የእኔው ፉንጋዬ ነው እንዴ ሙሽራው? ቱ! ቱ! ከዓይን ያውጣችሁ"ብላ መርቃን፣ "ታዲያ ወዴት ነው የምትሄዱት?!"

ሲሳይ ጎቢጥ "ሽርሽር!" አለና መለሰላት።

"እንዳትርቁ"! ብላ ፈገግ ብላ አስተዋለችን።

በኃይሉ ዶሮ ሾፌርነት ወደፊት ተጓዝን። እየተጨፈረ ጉዞው እሰከ አበራ ወፍጮ ቤት ቀጠለና መኪናውን ተጠምዞ ወደነበርንበት ቦታ መለሰን።

ጨዋታው እንደቀጠለ ነው። ለምሳ የሰንሰል ቅጠል ቀርቦ ልን፣ በቆርኪ መጠጥ ታደለን። ደስ እያለን ተበላና ተጠጣ። እንደገና ዘፈን ተጀመረ። ሚዜዎቻችን ተነስተው እስከስታውን አስነኩት።

በዚህ መካከል የመቅደስ ታላቅ እህት ልጃገረዷ መዓዛ መጣችና "በቃ ደከሚቸዋል። አሁን ትንሽ መተኛት አለባቸው" አለች።

ሙሽሮቹ እየተጨፈረልን ከበረንዳው ላይ ተነስተን እኛ መቅደስ ቤት ገባን። መዓዛ አመቻችታልን ታጣፊ አልጋዋ ላይ ጋደም አልን። ይህን ጊዜ የመቅደስ እናት የእማማ ማሚቴ ድምፅ ከውጪ ተሰማ። መአዛ እየሳቀች ከቤቱ ውስጥ ወጣች። እማማ ማሚቴ መቅደስ ከጎን ተንተርሳ ጋደም እንዳለች አዩን። ከው ብለው ቀሩ። ዘንቢላቸውን በቁማቸው ለቀቁት። እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው"አንተ ቆሮቆንዳ ፉንጋ! ለመሆኑ ምን አስበህ ነው ልጄን አቅፈህ የተጋደምከው? አንት ምናምንቴ!" ብለው ቁንጮዬን ጨምድደው ሽቅብ ሳቡኝ። እንደ ድመት እየጮህኩ ተንጠለጠልኩ። "መልስልኝ እንጂ! ገና እንብርትህ ሳይደርቅ!? ምን ልታረጋት ነበር?!" ብለው መዳብ ቀለበት

ባጠለቀ ባታቸው በኩርኩም ቆጥኝ። ፍንቸር አልኩና በሳሎኑ ወለል ላይ ተዘረርኩ። ኩርኩሙ ከአናቴ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ። በጩኸቴ ሰማይ ምድሩን አናወጥኩት። መቅደስ ግር ብሏት በተሸበረ ስሜት ተጋደማ ታያቸዋለች።

"ተነሽ! እንቺ ምናምንቴ! የምናምንቴ ልጅ! ለቂንቂኑ ትደርሽበታለሽ። የዘር አይለቅ..." አሉና በጥፊ ሲመቷት ፍንቸር ብላ መሬት ወደቀች።

ከደስታ ወደ ሃዘንና ወደ እንዲህ አይነቱ ሽብር ለመሸጋገር ከደቂቃዎች በላይ አልፈጀም። በቁጣ የሚንጨረጨሩት እማማ ማሚቴ ከአናቴ ደማ ፊን ብሎ ሊወጣ አይተው ጩኸታቸውን አቀለጡት።

ንረቤት እየተጯጯሐ ደረሰ "ምነው? ምን ተፈጠረ?"

"ልጁን ገደልኩት!" አሉና አፊፍ አርገው አንስተው እቅፍ አድርገውኝ ቆሙ። ተነባብረው በሩን ያጨናነቁ ጭንቅላቶች፡ ከብዙ ዓይኖች ጋር ብቅ ብለው ይታዩኛል።

ቀጠሳው ሮጦ ሄዶ ከኑልት ለምትመለሰው እማዬ መፊ ንኩቴን አረዳት። ፊትለክ ብላ ግርግሩ መካከል ደረሰች። ከእማማ ማሚቴ አጅ ላይ ቀልባኝ የመጀመሪያ እርዳታ ይሰጠኝ ጀመር።

የምጣድ ማሰሻ ካለበት ተፈልጎ መጣ። ጭንቅላቴ ተተ ኮሰ። ደሙ ቆመ። ወደ እኛ ቤት በሸክም ሄድኩ። አረንቻታ ተገላልኝ። አልጋዬ ላይ ጋደም ካልኩ በኋላ እናቴ ሁኔታውን አጣራች። ጥፋተኛ እኔ ሆኜ ተገኘሁ። በድርጊቴ በጣም ደን ግጣና አፍራ "አንተ! እንኳን ያቀመሰህ! ባሰጌ!"

እኔ ግን ጥፋቴ ምን እንደሆን አልገባኝም። ከአካኋናቸው እንደተረዳሁት የሚያስቅ፣ የሚያሳፍርና የሚያስደስት ነገር አለበት።

"ጉድ በሉ! ፉንጋይ መቅደስን አበላሽቲት ነበር" ይላል አንዱ።

"የዘንድሮ ልጆች አያደርጉም አይባልም!" ይመልሳል ሌላው በጣም እየተገረመ።

"የምር እኮ ነው። ልክ መርፌና ክር እንደሆኑ ወይዘሮ ማሚቴ ጉድሽን እደ ያላቸው እናት ከች አሉ!"

"አበስኩ ገበርኩ!"

"በቁማቸው ዘንቢላቸውን ለቀው አጠገባቸው ባለ ዘንዘና አናቱን አሉት።"

"አይ ጨክነብት። አሁን እሱ ቢገናኛት ምን እንዳያመጣ ነው? ግና አንድ ፍሬ እኮ ነው። ያው 'ልብ እንቅርት ይመኛል' አይደል? የሱም ወሸላ...!" ወፋፍራም ሳቅ አካባቢውን አናጋው።

የጨከነችብኝ ዓለምነሽ ነበረች። "እትዬ ባሎቴ ግደሉት! **በቶ ይገደል!" እያለች** ወተወተቻት። ጆሮዋ ስለማይሰማ ስትናገር

ጮክ ብላ ነው። እኔንም ጠቋሚ ጣቷን እየወዘወዘች "አይቀር ልህም ትገደላለህ!"

እማዬም "እሺ" ለማለት በምልክት ቋንቋ መለሰችላት።

ፊርቼ እማዬን ቀና ብዬ ሳያት፣ ሰብሰብ አድርጋ አቀፈችኝ።

ብዙዎቹ ጎረቤቶቻችን ግን ጥፋቴን ሰምተው "ወይ ጉድ! ፉንጋይ ይዘንን አደረገ?!" ብለው ይገረማሉ እንጂ፣ ሲሳይ ነቢጥ ወይም መኩዬ ቀጫጫው ፍራንክ ሰርቀው ጋስቴ በልተው የተገረፉ ዕለት የሚቆጡትን ቁጣ በገጽታቸው ላይ አላየሁባቸውም።

አባቴ ለፍርድም ሰቅጣትም ችኩል ነበር። እናቴ ግን በፍትሕ አበያየን ረገድ ከአባቴ ትልቃለች። ጉዳዮቹን አንድ በአንድ ካጣራች በኋላ ነው ወደ ብይን የምትሄደው። በዚህም መሠረት አባቴ'ጋ የሚያሰቀጣ ወንጀል እናቴ'ጋ ምሕረት ያስገኛል።

"ፉንጋይ!" አለችኝ ሰፊርተኛው ወደየቤቱ ከሄደ በኋላ። "እንዳትደብቀኝ። ማነው እንዲህ አይነት ባለኒ ነገር እንድታ ደርግ ያሳየህ?" ሁሌም አውነቱን ለማናገር ታላቅ ኃይል ያላቸው ዓይኖቿ የሥራ አካላቴን እየመረመሩት ነበር።

ከዕቃ ዕቃ ጨዋታችን ዝርዝር ልጅምር ስል አቋረጠችኝና "ተቃቅፋችሁ መተኛቱን ነው ያልኩት!" አለቺኝ በንዴለ ታል።

"መዓዛ ነች። መጀመሪያ መቅደስን ታጣፊ አልጋቸው ላይ አስተኛቻት። ከዚያም እኔን ታቅፋ ከአጠገቧ አስተኛችኝ። ከዚያ ሳማት!" አለቺኝ። ጉንጭዋ ላይ ሳምኳት። "አፏ ላይ ሳማት" አለቺኝ።

"እጣኑ ቂርቆስ የሥራዋን ይስጣት!" ይዘች ምናምንቴ" አለች እማዬ ለራሷ ያህል።

እኔ ቀጠልኩ "ከዚያ ወሸላዬን ሳብ ሳብ አደረጎችው ቁም ጣዬን አውልቃ" ስል እማዬ ሳቋን ለቀቀችው። ሳቅዋ ድሮ የማውቀው አይነት የደስታ መግለጫ ሳይሆን የምሬት ነበር።

"ቱ! ቱ! አበስኩ ገበርኩ! እስኪ ራሷ ቂን! ቂን እያለች ጎረምሳ ማንጋጋቱ አንሷት ሕፃናቱን ብልግና ታስተምራቸው?" አለች ወደ ጣራው እንዳንጋጠጠች። ማስረዳቷን ቀጠልኩ "ከዚያም ወሸላዬ..." ጠቋሚ ጣቴን ቀጥ አድርጌ አሳየኋት።

እሷም "በቃህ!" ብላ ገስጣኝ ማብሰልሰል ጀመረች። እማዬ ምርመራዋን እንዳጠናቀቀች ስለገባኝ ዝም አልኩኝ።

አባቴ የሸማ ገበየ ፍለጋ ከሄደበት አልተመለሰም። እሱ ከመጣ የተፈነከትከብት ጉዳይ እንደገና መጣራት ይጀምራል። የአባቴን ባሕርይ ጠንቅቃ የምታውቀው እናቴ ቀድማው ራቴን አብልታ አስተኛችኝ።

የድሮ ሰዎች በጣም ይከባበሩ እንደነበር አስታውሳለሁ። በልጅ ጉዳይ መቀያየም ቢፈጠርም በልጁ ፊት አይነጋገሩም። አጥፊውን፣ ወይም ተበዳዩን ልጅ ገለል አድርገው እውነተኛው

ጉዳይ ላይ ይወያያሉ። በሽምጋይ አማካኝነት የችግሩን ምንጭ ይመረምራሉ። ይቅር ለእግዜር ተባብለው፣ እንደ ጥንቱ ተዋደ ውና ተፋቅረው መኖር ይጀምራሉ። እኔንም የዚያኔ "ደግ አደረጉ! ቢመቱህም እናትህ ናቸው!" እማዬ ትበለኝ እንጂ፣ ችግሩን በበነጋው እንደሚመረምሩት ገምቻለሁ።

ያ ጣፋጭና መራራ ትዝታዬ ግማሽ ምዕተ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ዓመት ነው የቀረው። ይሁን እንጂ የባልና ሚስት ጨዋታ ትናንት የተከናወነ ያህል አሁንም ጎልቶ እንዲታየኝ የአማማ ማሚቴ የመዳብ ቀለበት ማጥቱን አናቴ ላይ አኑሯል።

ከሀሁ እስከ ወንጌል

"ልጅነቴ እንደ ሻንት ተውኔት (ሜሎድራማ) ነበር።
እየተሰደበ 'እየተገረፉ' መማር መቼም ለእኔ ሜሎ ድራማ ነው"
ዜራር ደፓርድየፖ (ፈረንሣዊ የሲኒማ ተዋናይ)

እነሆ ትምህርት ቤት ገብቼ እንደገና የመማሬ ጉዳይ የግድ ሆነ። ግዴታውን የፈጠረውም እኔ በተከታታይ ስሞን የሠራኋቸው መጥፎ ተግባሮችና ያጋጠሙኝ አደጋዎች ነበሩ። አንደኛው በመዓዛ ገፋፊነት ከመቅደስ ጋር 'ባለጌ ሥራ' ለመሥራት መስማማቴ ሲሆን፣ ሌላው ከኃይሉ ዶሮ ጋር ተጣልተን ፊታችንን በኃይል ተሞነጫጨርን። እንዲሁም የተሰጣ እህል ሰጠብቅ 'እሽሽ አትበለኝ የሹም ዶሮ ነኝ' ያለው የአናጢው የአባባ መሹ ዶሮ ከንፈሬን በመንከሱ የደረሰብኝ የመቁሰል አደጋና ሌሎች ችግሮች ተደራርበው ቄስ ትምህርት ቤት የመግባቴን ጉዳይ አፈጠነው።

ወላጆቼ በትንሽ በትልቁ ጉዳይ መደናገጡ ተደራርቦባቸዋል። በየቀኑ ከሚከሰት ነፍስን ከሥጋ የሚለይ ችግር ለመገላገል እኔን ቄስ ትምህርት ቤት ማስገባት መፍትሔ እንደሆነ ወላጆቼ ከጎረቤቶቻችን ጋር መክረዋል። እኔም ጥፋቴን ስለተቀበልኩ ቄስ ትምህርት ቤት መግባቴ ጥሩ እንደሚሆን ገመትኩ። ዝግጅቴ እንደቀድሞው በፍጥነት ተከናወነ። በቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው ቄስ ትምህርት ቤት ሊያስመዘግበኝ ይዞኝ የሄደው አሁንም አባቴ ነበር።

ይህንን የሕይወቴን ምዕራፍ ለመቃኘት በቅርቡ ወደ ለማዕቱ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ዘልቄ ነበር። ቤተ

ክርስቲያኑ በአሁኑ ዝቤ ታድሷል። ምዕመናን ፀሎት የሚያደርሱበት ቦታ በጥሩ ሁኔታ ተገንብቷል። ቤተመቅደሱ ከሙታን አምባ በግንብ አጥር ተለይቷል። ድሮ ችግኝ የነበሩት ተክሎች ዛሬ ዕድሜ የጠገቡ ዛፎች ሆነዋል።

በልጅነቴ አንድ ተማሪ ፊደል እየቆጠረ የቀበር ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም ያስተውላል። ጉልት የሚገቡየዩ ሰዎች በቅርብ ርቀት ይታያሉ፣ ጫጫታቸውም ይሰማል። አቃቢቶች ከመቃብር ቤታቸው ወጥተው ፍርፋሪያቸውን ካቡ ላይ ሲያሰጡ ይስተዋላሉ።

ፊደል የምንቆጥረው በደወል ቤቱ ውስጥ ሲሆን፣ ፀሐይ ሙሉ ለሙሉ ወጥታ መለብለብ ስትጀምር በርፊጨማችንን ይዘን ጥላ ወዳጠላበት አቅጣጫ እንድንዞር የኔታ ያዙናል። ለየኔታችን ፀሐይ ሰዓታቸውም ጭምር ነበረች። ለዕረፍት የሚለቁንም ሆነ፣ ለምሳ ወደየቤታችን የምንሄደው በፀሐይ ጥላ አለካካቸው ነበር። በሃሳብ ሲመሰጡ ወይም ሲቆዝሙ አለታችን ያስታውሳቸዋል።

የፊደል ዘር ለመለየት በምንጣጣርበት ወቅት ትኩረታችንን የሚሰቡ በርካታ ጉዳዮች ይከሰታሉ። ለቀብር ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚገቡ ለቀስተኞች ሲጯጯሁ ትምህርታችንን አቁመን አለታቀሳቸውን እናስተውል ነበር። ወይም አንዲት ለዕ ለት ውሎዋ የምትሯሯጥ አይጥ ከካቡ ስር ትወጣና አፍጣ ታየ ናስች። አንዱ ሐዋን እንዳያት "አይጥ!" ብሎ ይጮኻል። ወደ አፈጠጠበት አቅጣጫ እናያለን። ቀልባችን ሁሉ ዓይጧ ላይ አርፎ ፀጥ እንላለን። በማንጎላጀት ላይ የነበሩት የኔታም ጫጫታው ጋብ ሲል ይነቃሉ። "ተማሩ!" ብለው አለንጋቸውን ሲሰነዝሩ ጫፉ ያረፈበት ልጅ የተመታ አካሉን እያሻሸ ማልቀስ ሲጀምር እንደገና መንጫጫታችንን እንቀጥላለን።

ብዙም ሳልሰነባብት ሀሁን አጠናቅቄ ሀ- ግእዝ ሁ -ካኢብ መማር ጀመርኩ። ይሁን እንጂ በዘመኑ ትምህርቱን የምንማርበት ስልት በልጅ አቅም የሚሸከሙት ባለመሆኑ ታከተኝ። ልጅን አባብሎና አግባብቶ በጨዋታ መልክ የሚገበይ ትምህርት ባለመሆኑ ጠላሁት። ልክ ወላጆቻችን በዘያው በልጅነት ጊዜ ጭናቸው ላይ አስቀምጠውን አፍንጫችንን ሰንገው አብሽ፣ ወይም ወተት አልያም መድኃኒት እንደሚግቱን ሁሉ፣ ሁሉም ነገር የሚካሄደው በግድ በመጋት ነበር። በዚህ ወቅት ምንም የልጅን ፍላጎት በመከተል የሚካሄድ ነገር አልነበረም። በዚህ ምክንያት ከአባቴ ጋር ነጋ ጠባ መጨቃጨቅ ጀመርን። እናቴ መማሩ እንደሚጠቅመኝ ለማሳመን ትውተውተኛለች። ዕድሜ ልኬን እንዲያሸንፈኝ የተፈጠረው አባቴ ግን በኃይል ያስገድደኛል። ይሁን እንጂ የእናቴ ፍቅርም ሆነ የአባቴ ኃይል ትምህርቴን እንድወድ አላደረጉኝም። 'ፊደስን ወደ ወንዝ መውሰድ ይቻላል፡ ውሃ እንዲ ጠጣ ማድረግ ግን አይቻልም' እንዲሉ፡ የተለያዩ ስበብ አስባቦችን እየፈጠርኩ ከትምህርት ቤት እቀራለሁ። ቅዳሜና

አሁድ ጤናማ የነበርኩት ልጅ፣ ስሟርቅ፣ ስስቅ ወላጆቼን አስደስት የነበርኩት ሕፃን፣ ለኛ እታመማለሁ። ከትምህርት ቤት ስቀር አፍታም ሳልቆይ እድናለሁ። በዚህ ወላጆቼ አዝነው "አይነጥላ ይኖርበት ይሆን?" ተባብለው መወያየታቸውን አስታውሳለሁ።

ለኛ ማለዳ ከእንቅልፌ ብነቃም፣ ትምህርት ቤት ላለመሄድ ፀጥ አልና አደፍጣለሁ። ይህንን ባሕርዬን አሳምራ የምታውቀው እማዬ "ፉንጋይ ተነስ ስድስት ሰዓት ሆኖዋል!" ትለኛለች። ከንብ ንቤን ሳልገልጥ በቲቃውሞ አጉተመትማለሁ። በዚህ ጊዜ "ዜራሞ!" ብላ ትጣራለች።

እንደኳስ ነጥሬ ከአልጋዬ ላይ እወርድና ቁምጣዬን መታጠቅ እጀምራለሁ። አባቴ የተጠራበትን ጉዳይ ቀድሞውኑም ስለ ሚያውቀው "ወይ!" ሳይል ከሸማኔ ጉድጓዱ ሲወጣና ፊቴ ሲደርስ አንድ ይሆናል። እንፋጠጣለን። ፊቴን ተጣጥቤ፣ የጠዋት ፀሐይ ሳልሞቅ ቁርሴን እንደ ነገሩ ቀማምሼ ጉዞ እጀምራለሁ። አባቴ አርፌሜ ይዞ ይከተለኛል።

ፊደሌን፣ በርፌማዬንና ውሃና አሹቅ የተሞላበት ጠር ሙሴን ይዤ መጓዝ ስጀምር ማተቴምተምና ቀስ እያልኩ ማል ቀለ እጀምራለሁ። አባቴም አርፌማውን አንድ ሁለቴ ያሳርፍ ብኛል። ያን ጊዜ ጨዝቴን አቀልጠዋለሁ።

አባቴም በተራው ማነብነቡን ይጀምራል። እኔ ግን ምን እንደማል አይገባኝም። "ሒድና ተማር። አሁን ምን የሚያስ ለቅስ ችግር አለብህ?! እንደእኔ ገጠር ብትወለድ ኖሮ ከንንህ ታገኛት ነበር። አይ አለማወቅ! ጋሼ፣ ወደድክም ጠላህም፣ እኔ በሕይወት እስካለሁ በግድህ ትማራታለህ!"

ፎክ ብዬ አለቅሳለሁ።

አንጀቴ አያረረ አሁንም አንድ ሁለቴ ያሳርፍብኛል። ፍጥነቴን እጨምራለሁ። በማይማሩት አብሮ አደጎቼ በጣም እቀ ናለሁ። ውሮ ደስ ባለው ቀን ነው ወደ ትምህርት ቤት የሚ ሄደው። አባቱ ወታደር ስለሆኑ አጋዴን ፀምተዋል። እናቱ እማማ ወርቅውሃ ደግ ስለሆኑ አይቆጡትም።

ሴምላል የትምህርት ቤት ደጅ ረግሞ የሚያውቅ አይመ ስለኝም። ንፍጡን ሽቅብ እየማገ የዓይን አር ባልደፈነው አንድ ዓይኑ አፍጠብናል። ፊቱ ላይ ዝንብ እያደነ፣ የጠዋት ፀሐዩን እየሞቀ በመገረም እኔና አባቴን ይመለከተናል። ሊታጠብበት ያወጣው ውሃ የሞላ መወዘቻ ከፊቱ ተቀምጧል። በፀሐይ ለብ እስኪልለት እየጠበቀ ነው።

ቀጢሳው እንደኔው በጠዋት ተነስቶ "አልማርም! ቁርሴን!" እያለ ይጮኻል። መንደርተኛውም "ኡኡ! ደሞ ነጋለት ይሄ ፊደል ተራራው" እያሉ ያላግጡብታል። ምንጊዜም ቁርሱን ከበላ በኋላ ነው ፊቱን የሚታጠበው። አባቱ አባባ በየነ በመስክ ሥራ

ብዙ ጊዜ ከቤተሰቡ ይለያል፣ እናቱ በመንደርተኛው ግፊት ትንሽ ያስገድዱትና ይተውታል። ጠንክረው ጫን ካሉት ድንጋይ አንስቶ እስከመወራወር ይደርሳል። ለእሱ መድኃኒቱ አባቱ ነበሩ። አባቱን ሲያይ የሚገባበት ነው የሚጠፋው። እንደ አጋ ጣሚ አባቱ አዲስ አበባ ከሰነባበቱ ትምህርት ቤት የምንቀረውን ልጆች ሁሉ እየቀሰቀሰ "ትምህርት ቤት እንሂድ!" የሚለን እሱ ነበር።

አባቴ "አይ አለማወቅ! ወደ ብርሃን ሲሉት፣ ጨለማን ይመኛል። የማትረባ! ፈጠን በል! እኔ እንዳንተ አልሞላልኝም። የምጣደፍበት ጉዳይ አለ" ብሎ አርምጃ እንድጨምር አንዴ ሾጥ ያደርገኛል።

አባቴ የሚለው ብርሃንና ጨለማ አይገባኝም። ትምህርት ቤት የማይሄዱት ጓደኞቼ የጠዋት ፀሐይ እየሞቁ እያየኋቸው ነው፣ እኔ ግን ጥላ ውስጥ ተቀምጬ እንድማር እየተገደድኩ ነው እያልኩ በሆዴ ይህንን እንቆቅልሽ ለመፍታት እሞክራለሁ።

አንድ ቀን በአባቴ ልምጭ ታጅቤ ወደ ቁሰ ትምህርት ቤት ሰሐድ መንገድ ላይ ቀለም ቀቢው አባባ ታደሰ አገኙን። መሰላል ተሸክመዋል። በኮሮጆ ቢጤ ምሳቸውንና ቀለም መቀቢያ ሙራዎ ቻቸውን አንግበው እየተጣደፉ "ምንድነው ዜራሞ?" አሉና ጠየ ቁት ቆም ብለው።

"አልማርም እያለ...!" አሳቸው።

መብረቅ ድንገት እንደወረደበት ደንግጠው "ፉንጌ፣ በሬ ሆነህ መቅረት ትፈልጋለህ?!" ብለው ጠይቀውኝ መልሴን ሳይሰሙ "አወይ! ልጅነቱ የምትመለስ በሆነና አባቴ እንዲህ እየገረፈ ተማሪ ቤት በወሰደኝ! አይ የልጅ ነገር ሆኖ ነው። ዜራሞ። ግረፈው! ግረፈው! የአሁኑ ዱላህ ሬት አይደለም ማር ነው!" በማለት ለሕመምተኛ መድኃኒት እንደሚያዝ ሐኪም አባባ ታደሰ ዱላ አዘውልኝ በጥድፊያ ወደ ጉዳያቸው ተጓዙ።

አባቴ ምክራቸውን ሰምቶ በአዲስ ኃይል እያባረረኝ፣ እኔ ቱስ ቱስ እያልኩኝ፣ አላፊ አግዳሚው ግማሹ እየተፀየፈኝ፣ አሰተዋዩ እያዘነልኝ ቅዱስ ቁርቆስ ደብር ደረስን።

የኔታም በአለንጋቸው ቸቀበሉኝ። የእሳቸው ከረር ያለ በመሆኑ በቁሜ በርፌማዬንና ሙርሙሴን ለቀቅኩና አለንጋው ያረፈበትን አካሌን ማሸት ጀመርኩ። አባቴም ሕመሜ ተሰም ቶት ሰቅጠጥ አለ። የኔታም አዩትና "አይዞት አቶ ዜራሞ፣ ዱላ የማይበጀው ለሽክላ ብቻ ነው" አሉት።

በዚህ አስታክከው የኔታ ከአባቴ ጋር ትንሽ ያወጋሉ። ስለ ዓይነ ጥላ ያነሳባቸዋል። "አይደለም ሲለግም ነው። ሰፈር ማውደ ልደሉን ለምዶ ነው!" ብለው አባቴን ያፅናኑታል።

አባቴ በፍቅር ዓይን ሰረቅ አርጎ ያየኛል። እኔም በንዴት በበነ ዓይን አፈጥበታለሁ። እሱም አርፌሜዋን ጥሎ ወደ ዕለት ተግባሩ ይዘልቃል። በዚያን ወቅት በየዕለቱ እየተመዘዘ የምገረ

ፍባቸው ልምጮች ቢጠራቀሙ ኖሮ አንድ ምጣድ አስሞተው ቡሃቃ ሙሉ ሊጥ ያስጋግሩ ነበር ብዬ እገምታለሁ።።

የኔታም ያረፈደውን ቀጥተው "ተግሩ" ሲሉ ያዙናል።። ህሁ የሚማረው ከሚያስተምረው ጋር ተጣምሮ ይቆጥራል።። ሀ -ግእዝ ሁ -ካኢብ...፣ አቦጊዳ፣ መልዕክተ፣ ወንጌልና ዳዊት በየብጤው በመሆን ፊደላቱን መቁጠር ይያያዛል።።

በቁስ ትምህርት ቤት ሕይወቴ እኔና አብሮ አደጎቼን የሚ ያስደስተን ቀን እምዬ ማርያም በ21 የምትነግሥበት ዕለት ነበር።። በዓሉ እንደነገ ሊሆን በዋዜማው "ልጆች ነገ የእመቤታችን ንግሷ ነው።። ስለዚህ ትምህርታችሁን እንድትገልጽላችሁ፣ ፀበል ፀዲቋን እናደርሳለን" ሲሉ የኔታ በሚቀጥለው ጠዋት አራት ፍራንክ ከወላ ጆቻችን ተቀብለን እንድንመጣ ይነግሩናል።። የሁላችንም ቤተሰ ቦች ያለምንም ጥያቄ ይሰጡናል።።

በ21 ጠዋት ማንም ሳይቀሰቅሰኝ እነቃለሁ።። አራት ፍራ ንኪን ከአባቴ ወይም ከእናቴ ተቀብዬ ጭብጥ አድርጌ እይ ዛታለሁ።። እጄ ውስጥ ማንቲሚ ያልባታል።። ከሰፈሬ ልጆች ጋር ተጠራርተን ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን።። ቤታቸው ቅርብ የሆነ ልጆች የሻይ ማንቆርቆሪያ እና ሣህን ያመጣሉ።። ገበያው እዚያው በመሆኑ የሚፈለገው በፍጥነት ይሸመታል።። ሻዩ ይፈ ላል፣ ዳቦው ይባረክና እንቋደሳለን።። በዚህ ዕለት እጅ በጆሮ የለም፣ መንበርከክ የለም፣ እጅህን ዘርጋ የለም፣ ቂጥህን እዙር የለም።። በአጠቃላይ ግርፊያ የለም።። በነፃነት ስንጨዋወት ውለን በጊዜ ወደ ቤታችን እንመለሳለን።።

ሌሎቹ አስደናቂና አስደሳች ዕለታት ደግሞ በፍልሰታ ፆም ሰሞን ይመጣሉ።። እኔ አስራ ሰድስቷንም ቀን እቆርብ ነበር።። በዚያን ሰሞን የየኔታ አለንጋም ሆነ የቤተሰብ ቁጣ ይቀራል።። አንድ ነገር አጥፍቼ አባቴ ቢቆጣ እንኳ "ተወው! ቆርባል" ስትል እናቴ ትከለክለዋለች።። እሱም የቃጣውን እጅ ሰብሰብ ያደ ርጋል።።

ረስቼው ቁርሴን የበላሁ ዕለትም ቢሆን እቆርባለሁ።። የኔታ አራት ሰዓት ላይ የምንቆርበውን እንድንሄድ ሲፈቅዱልን "ቁር ሳችሁን በልታችሁ የምትቆርቡ ካላችሁ ትቀሰፋላችሁ" ሲሉ እየሰ ማሁ ለቁርባን እወጣለሁ።።

ከዚህ መለስተኛ እስር ቤት ማምለጫ ለለሚሆነኝ በጣም ብፈራና ብጠራጠርም ቆርቤ መቀሰፉን ትንሿ ሕሊናዬ የመረ ጠችው ይመስለኛል።። ይሁን እንጂ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ተሰልፌ ሥጋ ወደሙን ልቀበል ስል ልቤ መሸበር ይጀ ምራል።። "እግዚአብሔርዬ እባክህን አትግደለኝ!" እያልኩ በየደ ቂሳውስቱ በአፌ የሚሰጡኝን ተሰጥኦ እቀበላለሁ።።

ወደቤት ስሄድ አፌን ሸፍኜ፣ ከልጆች ጋር ሳልላፋና እር ጥበት ሳይነካኝ እውላለሁ።። የምጫወተውም በእርጋታ ነበር።።

ጀምበር እንደ ጠለቀች ቤት ገብቼ ራቴን በልቼ እግሬን ሳልታ ጠብ ባገኘሁት ቡትቶ ጠረግ ጠረግ አደርግና እተኛለሁ።። በቆረ ብኩ ማግሥት ድብን ካለ እንቅልፍ ላይ ነቅቼ ራሴን በሕይወት ሳገኘው እግዚአብሔር እንደማረኝ አምናለሁ።። "ዛሬም እቆር ባለሁ!"

"እሽ እንዳልክ!"

"ቁርሴን ሰጪኛ።።"

"እንደሱማ ነውር ነው ትቀሰፋለህ!"

"ትናንትና የኔታም እንደ አንቺ ብለውኝ ነበር።። እኔ ግን አለሁ!" ስላት እናቴ በኃይል ትስቃለች።። በሳቅዋ መካከል መረታ ትዋን እመለከታለሁ።። ወደ ጓዳ ይዛኝ ገብታ ቁርሴን ትሰጠኛ ለች።። "ልጆች ገብተው እንዳያዩኝ ጠብቂልኝ" ስልም ዘብ እንድ ትቆምልኝ አዛታለሁ።። ተመግቤ እንዳጠናቀቅኩ፣

"አንተስ ማንም አይችልህ የምትገርም ፍጥረት!" እያለች ነጠላ አጣጥፋ ታከናንበኛለች።። ያለምንም ሸኚ ከአብሮ አደጎቼ ጋር ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን።።

አስደሳችና ተወዳጅ ዕለታት ምንጊዜም ቢሆን አጭር ናቸው፣ ቶሎ ያልፋሉ።። እንደገና ከፊደል ጋር ትንቅንቅ እንጀ ምራለን።። ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የሚቀፈኝን ያህል ማታ ወደ ቤቴ መመለስ ያስደስተኝ ነበር።። ልክ የምንለቀቅበት ደወል ሲደወል ክጓደኞቼ ሁሉ ቀድሜ ከቤተክርስቲያን ግቢ በሩጫ እወጣና "አንደኛ!" ማለት ያስደስተኛል።። ይሁን እንጂ አንዳንድ ቀን በርፌሜዬን ወይም ጠርሙሴን ረስቼ ወደ ቤት እመለስ ነበር።።

የዕለቱ ትምህርት ሁልጊዜ የሚጠናቀቀው ሕይወቴን በሙሉ በሕሊናዬ ተቀርፆ በቀረው "አባታችን ሆይ!" ፀሎት ነበር።። ከዚያም በወር አንዴ የምታሳርፈንን እመቤታችን ድንግል ማርያምን ተማፅነን፣ ማሳረጊያችን "በሰይጣን ጉሮሮ አጥንት ይቀ ርቀር፣ በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር" ብለን ሩጫችንን እና ስነካዋለን።።

በእንዲህ አይነት ስሜት ውስጥ እያለሁ ከአባቴ ጋር መንገድ ላይ ከተገናኘን "ምነው ጧዋትም እንዲህ እየሳቅህ ስትሄድ ባይህ!" ይልና ሊያግዘኝ በርጨሜዬን ወይም ጠርሙሴን ይቀበ ለኛል።። ሣቁ ተጋብቶበትም አብሮኝ እየሳቀ በፍቅር እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ቤታችን እንሄዳለን።።

አብረውኝ ቁስ ትምህርት ቤት የተማሩትን ልጆች ጥቂቶ ቹን እስታውሳለሁ።። ጃምቦና ሲራክ ቁንጮ ደግሞ በተለየ ገጠመ ኛቸው ምን ጊዜም አልረሳቸውም።።

ጃምቦ ከስቶኪንግ የተሠራ ትልቅ የጨርቅ ኳስ ነበረው።። ሁሌም በአረፍት ሰዓት ምትሮሽ ስንጫወት እሱ በረኛ ሆኖ እኔ እለጋለሁ።። የእሱ የበረኛነት ፍቅር ተጋብቶብኝ እኔም በቅጡ እለማመድ ነበር።። ቤታቸው ከትምህርት ቤታችን አጠገብ ስለነበር

በእረፍት ሰዓት ውሃ ለመጠጣት ወደ ቤቱ ሲሄድ ያስከትለኝና እናቱ ከአሹቁም ከቂጣውም ብለውን ወደ ትምህርት ቤታችን ቶሎ እንመለሳለን። እሱ በዚህ ዕድሜውም ኃይለኛ ጡት የመጥ ባት ሱስ ነበረበት። ይህን አመሉን ዘወትር ስለማይበት "ቀንጋይ! ለማንም እንዳትናገርብኝ በእናትህ!" እያለ ምስጢሩን እንድ ደብቅለት ይማፀነኛል።

"እሺ" አለዋለሁ ከልቤ፣ ቆለፌን እየቃምኩ።

እናቱ እንደማፈር እየቃጣቸው "አሁን በስተእርጅና ቢቀ ርብህስ?" ይላሉ እንደምክር።

"አሳቅልሽም አንቺ ደግሞ!" ይልና ጡቱን ይንርሳል።

ይሄንን ልማድ አባትየው በግድ እንዲያቆም አደረጉ። በዚህ ምክንያት ጃምቦ ሐዘንተኛ ሆነ። ፊዘዝ ማለትም ጀማመ ረው። ጨርቅ ኳሷንም ትምህርት ቤት ይዞ መምጣት ተወ። ትምህርት የመቀበል ቅልጥፍናውም ቀነሰ። የሚገርመው፣ እናት የው የአባትየውን ሕግ ቢያከብሩም ጡታቸው እያጋተ አስቸገ ራቸው። ልጃቸውም በጣም ስለሚያሳዝናቸው በድብቅ ቶሎ ያጠ ቡታል። ቢሆንም እንደድሮው እንደልቡ ባለመሆኑ ሐዘንተኝነቱ እንደቀጠለ ነበር።

አንድ ቀን አባቱ እቤት ውስጥ ልብሳቸውን ይተኩሳሉ። እናቱ ውጪ ተቀምጠው እህል ያበጥራሉ። ጃምቦ ደጅ ቁጭ ብሎ ያንጎራጉራል።

"ተው ቻለው ሆዴ፣ ተው ቻለው ሆዴ

ሲያልፍ ለሚያልፍ ቀን ምነው መናደዴ..." እንጉርጉሮው የአባቱን ቀልብ ሳበ። ብቅ ብለው ቢያዩ ጃምቦ ነው። በጣም ተገርመውና ከልብ አዝነው "በይ ስጪው ጉድ እኮ ነው፣ 'ሲያልፍ ለሚያልፍ ቀን ምነው መናደዴ' ብሎ አንጎራጎረብኝ" አሉ ተደንቀው።

"አንተ፣ ምን ብለህ ዘፈንክ?"

"የአያሌው መስፍን አዲስ ዘፈን ነው። በሬዲዮ ነው የሰማሁት።"

"ምን እንዳልክ ንብቶሃል?"

እንደ እስክስታ ወራጅ ትከሻውን እየለበቀ ቆዘመ።

"ተነሺ ስጪው እንጂ ምን አፍጠሽ ታይኛለሽ? ተሰቃለች እንዴ ደግሞ?! ጥርስሽን ያርግፈው እቴ!"

እናቱ ደስ ብሎአቸው እቤት አስገብተው አጠቡት። እሱም ትምህርት ቤት መጥቶ ደስታውን አበሰረኝ። ባሕርዩም እንደ ድሮዋ ተመለሰች፣ ፊቱ በደስታ አምሮ የጨርቅ ኳሷን ይዟት ነበር የመጣው።

ቁንጮ ደግሞ ምን ጊዜም ቢሆን ከአፉ ላይ እንደ ፒፖ የሚያንጠለጥለው ጡጦ ነበረው። በሕይወቱ ጡጦ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ቁንጮ ሲጠባ ነበር። የእኔ አስተዳደግ በእናቴ ጡት

ስለነበር የጡጦውን ጥቅም የነገሩኝ ጓደኞቼ ናቸው። ይጣፍጥ እንደሆን ለማወቅ እንዲያቀምሰኝ ለመንኩት። እሱ ግን እያጉተ መተመ ሸሸኝ። ቁንጮ እዚህ እንዲውል ተፈልጎ ቂስ ትምህርት ቤት መጣ እንጂ ከኛ በጣም ትንሽ ስለነበር ካልፈለገ አይማ ርም። የኔታም አይናገሩትም። አንድ ቀን አድፍጬ ጠበኩትና ጡጦውን ነጥቄ በፍጥነት መጥባት ጀመርኩ። ቁንጮ መሬት ድብ ብሎ እየተንፈራፈረ ጩኸቱን አቀለጠው።

አወቀ ዱዱ "ወይኔ! ጡጦውን ነጠቀው!" ሲል ጮኸ።

እኔ ስጠባ፣ ቁንጮ ሲንፈራፈር የኔታ ተክለወልድ ፊት ለፊት አይተውኝ ኖሮ እጅ ከፍንጅ ተያዝኩኝ። የጡጦውን ወተት በቅጡ ሳላጣጥም በዚህ ጥፋቴ ክፉኛ ተገረፍኩኝ።

በግድ የምጋተውን የቂስ ትምህርት 'ቀስ በቀስ ሰንቂላል በእግሩ ይሔዳል' እንደሚባለው ከዘው እስከ መልሰክተ ዮሐንስ ዘለቅኩ። ወንጌልንም ሦስቴ ደገምኩ። በዚህ ወቅት ከአብር አደጎቹ መካከል እነ ኃይሉ ዶሮ፣ አበረ ሻኖ፣ ሲሳይ ጎቢጥ፣ መኩዬ ቀጫጫው ዘመናዊ ትምህርት ቤት መማባት ጀምረዋል።

ከወንጌል ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መማባት እንደሚቻል ከእናቴ ጋር መከርኩ። እሷም ጠዋት ጠዋት ወደ ቂስ ትምህርት ቤት ስሄድ ማሳዘኔ ስልችቷት ስለነበር በትምህርት ቤቱ መለወጥ የፀባይ መሻሻል ይታይበታል ብላ ተስፋ በማድረግ በሃሳቤ ተስማማች። አባቴም ዘወትር አርፊቅሜ ይዞ እኔን ማሳደዱ ታክቶት ስለነበር ሳያንገራግር "እንዲ! ከመዘባበት ምን ትገረኝ፣ ለማስመገቢያ የሚሆን ገንዘብ ዛሬ የለኝም እንጂ" አለ።

"እኔ እከፍላለሁ!" አለች እማዬ። ዘልዬ እቅፍ አድርጌ ሳምኳት። "ኢዲያ! ፈሳም! ትምህርትህን ጠበቅ አርገህ ይዘህ መጀመሪያ እስኪ ሰወብን!"

አባባሷ አልገባኝም። ለውጡ ግን አስደስቶኛል። ወዲያ ውኑ ቅድመ ዝግጅቴን ጀመርኩ። ስሙኒ ስጥታኝ ፀጉሬን ተማሪ ቁርጥ ተስተካክልኩ። ቁንጮዬንም ለዘለዓለሙ ተሰናበትኳት። በወቅቱ የአራተኛ ክፍል ተማሪ የነበረው ከበደ ደብተሬ ላይ አንድ ማሳሰቢያ ጻፈልኝ። 'ይህ ደብተር የተማሪ ተስፋዬ ዜራሞ ደብተር ነው። ማንም እንዳይነካ። የነካ አርባ ጅራፍ ይገረ ፋል።' ቆጥሬ አንብቤው ተገቢው ማስጠንቀቂያ በተገቢው ቦታ ላይ በመስፈሩ ተደሰትኩኝ።

በዚህ አኳኋን የቂስ ትምህርቴን "ዋዝድሮው" አድርጌ ዳዊት ሳልደግም ከሳቴ ብርሃን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዜሮ ክፍል ገባሁ።

ጆሮ ቆራጭ

"ልጅን በሚሔድበት መንገድ ምራው፣
በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።
መጽሐፈ ምሣሌ ምዕራፍ 11:16

የአባባ ጃንሆይ የልደት ቀን ነገ በመላ አገሪቱ ስለሚከበር፣ በዋዜማው አዲስ አበባ በልዩ ልዩ ትዕይንት ደምቃለች። አውራ ጎዳናዎችዋ የወታደራዊ ማርሽ ባንዶች ዜማ ያስተጋባሉ።

እኔና ሲሳይ ጎቢጥ ከጓደኞቻችን ጋር ድብብቆሽ ስንጫወት "ነገ እኮ በዓል ነው። ዛሬ ወደ መስቀል አደባባይ ብንሄድ ሙዚቃ ስንሰማ ውለን መምጣት እንችላለን" አለኝ።

"እረ?! ማን ሂዱ አሳችሁ ተብለን ብንገረፍስ? ቀጤ ሳውና ቁልሟ ገና ሳይነኳቸው ነው እሚለፈልፉት!"

"እኔና አንተ ብቻ እኮ ነን እምንሄደው። ልክ ቀጤሳው ኩኩሉ ሲል ተደብቀን በጨነቀ ሱቅ አድርገን፣ የቂርቆስን አደባባይ አቋርጠን ወደ አስጢፋኖስ ሸው እንበል። ደግሞኮ እዚያ የክቡር ዘበኛ (ክ.ዘ) ሙዚቃ ከሆነ አበበ ቢቂላ ሊመጣ ይችላል። አበበ ቢቂላን ማየት አትፈልግም?..."

በጣም ጓጓሁና ተስማማሁ።

ቀጤሳው "ኩኩሉ!"

"አልነጋም" እያልን እኛ እምንደበቅ መስለን ባሰብነው አቅጣጫ እጥፍ አልን። ኃይሉ ዶሮ እንቅልፍ ባልጠገበ እቅል እየተንገዳገደ ሊደበቅ ወደራሳቸው ግቢ ገባ። ሌሎቹ በየስርቻው መወታተፉን ያዙ።

እኔና ጎቢጥ እየሮጥን መሺለኪያን እጥፍ ካልን በኋላ ትንሩ ሻችንን ለመዋጥ ቆምን። መስቀል አደባባይ ስንደርስ ልክ ጉቢጥ እንዳለው የማርሽ ባንድ ሙዚቃ ይጫወታል። በደስታ እየፈነደቅን ተመልካቾች መካከል ተቀላቀልን። እንዳስብነው የክብር ዘበኛ ሙዚቀኛ ቡድን ነው።

የባንዱ አባላት በባለቡሽ ባርኔጣቸው ላይ የአንበሳ ጎፈር ከምረዋል፣ በገበርዲን ሱፍ ዩኒፎርማቸው አጊጠዋል። በጥቁር ሱሪያቸው ላይ ባለቀይ ጨርቅ ቁልቁል እስከ ቁርጭምጭሚ ታቸው በመስመር ተስፍቷል። በትከሻቸው ላይ ደግሞ የአንበሳ ጎፈር ዘንፈል ብሎ ይታያል። የተወለወለ ቀይ ቡት የቆዳ ጫማ ተጫምተዋል።

በርካታ ባዕመ ዜማዎች ካሰሙን በኋላ ፈታቸውን ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስታዲየም መልሰው ወደፊት መራመድ ጀመሩ። እኔና ጎቢጥ እንዳንጠፋፋ እጅ ለእጅ ተያይዘን ተከተልናቸው።

"እ! ወደ ፒያሳ እየሔድን ነው።"

"አንተ እንዳንጠፋ?!"

"አንተ ደሞ *ቡካቲያም ነህ!"

"እረ *ቦክቼ እኮ አይደለም። እንዳንጠፋ ስጠነቀቅ ነው።"

ትከሻዬን አቅፎ እየደባበሰኝ "ምን መሰለሽ ፉንጋዬ፣ እኔ ሁሉንም መንገድ አውቀዋለሁ። አሁን በፒያሳ እንሂድና በአራት ኪሎ አድርገን በቤተመንግሥት በኩል አልፈን እዚህ እስጢፋኖስ እንመጣለን። ምንም አትፍራ። ደግሞ ሱቆቹ ውስጥ ቆንጆ ቆንጆ መጫወቻዎች አሉ፣ እናያቸዋለን። ምናለ በለኝ አበበ ቢቂላን ደግሞ ፒያሳ እናገኘዋለን"

ግማሽ አምሮት፣ ግማሽ ፍርሃት ይሰማኛል። እጁን ጭብጥ አድርጌ ይዤው በዕቅዱ ተስማማሁ። ከካምቦሎጆ በኋላ ያለው መንገድ ለኔ አዲስ ነው። ጎቢጥን እጠይቀው ጀመር። "እሺ ይሔ ሠፈር ማን ይባላል?"

"ይኸው እያየኸው! ጋንዲ ሆስፒታል እያለ ወደ እዚያጋ ደግሞ ስንሄድ ሲኒማ ቤት አለ። ወደላይ የሚወስደው መንገድ ቸርችል ጐዳና ይባላል። ወደ ፒያሳ የሚያደርሰው መንገድ እሱ ነው። ምንም አትፍራ እኔ መንገዱን በደንብ አውቀዋለሁ። ከአባቴ ጋር ቤላ ሆስፒታል ሄጄ መምጣቴን አልነገርኩህም? አባቴ ደግሞ ክ.ዘ አይደል? ሁሉንም መንገድ አንድ በአንድ እያሳየኝ እየተንሸራሸርን ነው የሔድንበት። ብዙ ጊዜ ተመላልሼበታ ለሁ። ከኔ ጋር ከሆንክ አትጠፋም። ሙዚቀኞቹ ፒያሳ ላይ መጫወታቸውን እንኳ ቢያቆሙ እኔ መልሼህ ወደ ሠፈራችን እን መጣለን።"

"ጎቢጥ፣ ከእማዬና ከአባዬ ጋር ብዙ ጊዜ መርካቶ መሄዴን ታውቃለህ አይደል? እኔም ከሠፈራችን እስከ መርካቶ ያለውን መንገድ በደንብ አውቀዋለሁ" አልኩት። እኔ ግን መርካቶን ባየሁት ቁጥር ሁሌም አዲስ ስለሚሆንብኝ ትክክለኛ ምስሉን በዚ ያን ጊዜ ሀሊናዬ መገምገሙ አይይዝልኝም።

"ልክ ነህ መርካቶን በደንብ ታውቀዋለህ" አለኝ፣ እኔ እን ዳመንኩት እያመነኝ።

በቸርችል ጎዳና አቋርጠን ወደፊት ጉዞአችንን አቀናን። የመዘቀዋቹ የፊት መሪ ዘንጉን ሽቅብ እያነሰ መልሶ እየቀለበ እንደገናም እንዳልፈለጋት፣ እርሷ ግን እንደፈለገችው ከአየር ላይ ስትመለስ መልሶ እየቀለባት በአንገቱ ላይ እያሸከረከራት በቄንጥ ይራመዳል። ተከትለናቸው ፒያሳ ገባን።

በርካታ ሕፃናት ከሠፈራችን ተነስተን በሙዚቀኞቹ መሪነት እስከ ዓለም ዳር በሚያደርስ ጉልበት መጓዙን ቀጠልን። አሁን ረሃብ የለም፣ መድከም የለም፣ ይቆጡኛል እጠፋለሁ ብሎ መስጋት የለም። የራሳችንን ነፃነት ቡተግባር አውጀን በደስታ

ቡካቲያም፡ ፈሪ።
በክቼ፡ ፈርቼ።

እየፈነጠዝን ዜናውን በትኩሱ ለመጨለፍ እንደቋመጠ ጋዜጠኛ ከፌትም ከኋላም እየቀደምን ከጥበቡ ማዕድ እንቋደሳለን፡፡ በጣም ደስ የሚሉ ብዙ መዝሙሮች በጎብረት እየተዘመሩ ፒያሳን አቋርጠን እንድ ትልቅ ሃውልት ያለበት ሰፊ አደባባይ ደረስን፡፡

"ይኼ ምንድነው?"

"የምኒልክ ሃውልት፡፡"

"ማናቸው ምኒልክ?"

"የአባባ ጃንሆይ አባት፡፡" አለኝ ሲሳይ ጉቢጥ በእር ግጠኝነት፡፡

ይህንን ስንባባል የፖሊስ ሠራዊት ማርሽ ባንድ ደረሰ፡፡ ሁለቱም ባንዶች ከአደባባዩ ማዶና ማዶ ቆመው ለጥቂት ደቂ ቃዎች የሙዚቃ ኖታቸውን ከቀያየሩ በኋላ በጎብረት አስደሳች ዜማ ያፈልቁ ጀመር፡፡

ከመስፍን ሐረር ጐዳናም ሆነ ከደጎል አደባባይ ወይም ከሌላ እቅጣጫ የሚመጡ እንደ ሴቼንቶ፣ የቤትም ሆነ የንግድ መኪና እንዳያልፍ ትራፊክ ፖሊስ መንገዱን ዘግቷል፡፡

"ረጅም ዕድሜ ለጣሀዩ ንጉሣችን!" አሉ አንድ እዛውንት፣ የሚወርድ ዕንባቸውን እያበሱ፡፡

የጎብረት ዝማሬው ሲያበቃ ሙዚቀኞቹ ኖታቸውን ቀያ የሩ፡፡ ከ.ዘ. ወደ አራት ኪሎ አቅጣጫ ሊጓዝ፣ ፖሊስ ቸርችል ጎዳናን ቁልቁል ተያያዘው፡፡

በዚህ መካከል እኔና ሲሳይ ጎቢጥ ተጠፋፋን፡፡ ምንም እልጨነቀችም፡፡ ነፍሴ በዚህ ሰዓት እምትናገረው በሙዚቃ ቋንቋ ስለነበር፣ የጀመርኩትን ማዕድ ለመቀዠል ክቡር ዘበኛን ተከትዬ ሄድኩ፡፡ ባንዱ አንድ አካባቢ እንደደረሰ እንድ ሁለት ዜማ ካለማ በኋላ አሣረገ፡፡ ማዘ በሚባል በጣም ትልቅ መኪና መጫን ጀመሩ፡፡

"ይሔ ሰፊር ማን ይባላል?"

"ስድስት ኪሎ፡፡"

"ቂርቆስ በየት በኩል ነው መንገዱ?"

"ኡ! አንተ ጠፍተሃላ? እኔ አላውቀውም፡፡"

ይህን ጊዜ ነበር የባነንኩት፡፡ ለካ ጠፍቻለሁ! በዙሪያዬ የነ በሩትን በመቶዎች እሚቆጠሩ ሕፃናት ቃኘሁ፡፡ አንድም የሰፊሬ ልጅ የለም፡፡ ፍርሐት ወረረኝ፡፡ ልጆቹ ሁሉ በየአቅጣጫው ሲበ ተኑ፣ ብቻዬን ቀርቼ ሲመሸና ጅቡ ሲበላኝ ታየኝ፡፡ ጀንበር ማዘ ቅዘቅ ጀምራለች፡፡ ማልቀስ ጀመርኩ፡፡ መንገደኛው ምን እንደ ሆንኩ ይጠይቀኛል፡፡

"ጠፋሁ!"

"ለፊርህ የት ነው?"

"ቂርቆስ!"

"ኡ! ቂርቆስ?! ዛሬ ጅቡ በላኝ አትልም?" ይልና ጥሎኝ በራሱ ሃሳብ ተወጥሮ ወደ ጐዳዩ ቱር ይላል፡፡

አንድ አንካሳ ዓይነ ሞጭሚጫ ሰውዬ ጠጋ አለኝና «ምን ሆነህ ነው? ይሄኔ ጠፍተህ ይሆናል ከውካዋ!..." እያለ በስድብ አጣደፈኝ፡፡

ዝም አልኩት፡፡

"አይሃሂ መቆጣትህ ነው አንት ምናምንቴ?! ስንተኛ ክፍል ነህ?"

አልመለስኩለትም፡፡ ጠጅ ጠጅ ከሚሸተው ትንፋሹ ለመ ሸሽ ትንሽ ራቅ አልኩኝ፡፡

"ምንድነው? ምን ሆነህ ነው የኔ ፉንጋ?" ከኋላዬ ሩህሩህ የሴት ድምፅ ተሰማኝ፡፡

ለማንም መልስ ላይሰጥ የቆረጠው ልቤ እኝህን ባለለማያዊ ሻሽ ሴትዮ ሳይ ልቤ ቷ ብሎ ተከፈተ፡፡ በቅፅል ስሜ ስለጠሩኝ የሚያውቁኝ መስለኝ

"ጠፋሁ!" አልኳቸው በልቅሶ ዜማ፡፡

ደረታቸውን ደጋግመው ደቁና "እዬ እናትህ! እች እምዬ ይሄኔ ምን ውጣት ይሆን?!" አሉና ከያዙት የተጠበሰ በቆሎ እሸት ሰጡኝ፡፡

'ብልጥ ልጅ የሰጡትን እየበላ ያለቅሳል' እንዲሉ፣ እሸቱ ረሃቤን ስለቀሰቀሰው የልቅሶ ዜማዬን ሳልስት በቆሎውን እየፈሰ ፈልኩ መቃም ጀመርኩ፡፡

"ዝም በል! በቆሎዬን እየበላ ያለቅሳል እንዴ? ምንም አትሆንም አይዞህ፡፡ እኔ እናትህ እያለሁ? ዝም በል" ፊገግ ብለው አካባቢያችንን ቃኙ፡፡

አንድ ሰውዬ በአጠገባችን ሊያልፉ ፈጭ "ጨና ይስ ጥልኝ?" አሏቸው፡፡

"እግዜሃር ይመስገን ምነው በደህና?"

"አረ እኔስ ምንም አልቸገረኝ፡፡ ይሄ ልጅ ጠፋሁ ብሎ ቢያለቅስ፣ እርሶ ወደታች ስለሚሄዱ፣ እዬዱበት ድረስ ይዘውት ሄደው ለሌላ ሰው አደራ ብለው እንዲሸጡት ነው እማስቸግሮት፡፡ እኔ ይዤው እንዳልሄድ እዚህ ሆኗል ልግባ ነው" አሏቸው፡፡

ለውዬው "ለፊርህ የት ነው?" አሉኝ፡፡

"ቂርቆስ!"

"አቤት! ከዚያ እዚህ ምን አመጣህ? አይ የልጅ ነገር! ይብላኝላት ለናትህ! ቀጣፊ! ይሄኔ ወሳጆችህ ሳያውቁ ነው ተደ ብቀህ የወጣኸው?"

"ሲሳይ ጎቢጥ ነው እንዲድ ያለኝ፡፡"

"ማን ነው ሲሳይ ጎቢጥ?" አሉና ሴትዮዋ ትንሽ ፊገግ ብለው፣ ሳልነግራቸው ለሰውዬው አደራ ሰጥተውኝ ሄዱ፡፡

"እሺ ጀግናው ተከተለኝ" አሉኝ ሰውየው፡፡

በረጃጅም ቅልጥማቸው አንዱ እሚራመዱትን እኔ እሳቸው ላይ ለመድረስ በሶምሶማ ሩጫ መከተል ነበረብኝ። በተረት የምስማቸው ጆሮ ቆራጩ ስውዬ ትውስ አሉኝ። ቀና ብዬ ለውየውን አየኋቸው። ፊታቸው እንደ ቁመታቸው ረጅም ነው። ትልቅ ጠባሳም አለባቸው። አናታቸው ላይ ጎፈር የሌለው ባለ ቡሽ ባርኔጣ አድርገዋል። ባለፈሮ ጫማቸው አስፋልቱ ላይ ያለውን አሸዋ እየከካ ያደቀዋል።

"ምን ታየኛለህ?" ብለው ቁልቁል ሲያፈጡብኝ ጨነቀኝ።

"እማትረቡ! ቢነግሯችሁ ቢዘክሯችሁ አይገባችሁ ባለ ጌዎች!"

ሌሎችን የሚሰድቡ ይመስላል፣ ግን ከኔ ጋር ናቸው።

"እኔም አለሁበት?"

"እንደኛው አንተው ነህ!"

ተፋጠጥን። የምለው አጣሁ።

"የኔ ሰፈር እኮ እርሶ ሰፈር አይደለም። የኔ ሰፈር ቂርቆስ ነው።"

"የትም ይሁን፣ ከወላጆቹ ፈቃድ የሚወጣ ልጅ አይረባም። ጆሮውን መቆረጥ አለበት!" ሲሉ ጆሮዬ ላይ ድምፃቸው አስተጋባ።

በጣም ፈራሁ። ለማምለጥ ፈትለክ ስል አደናቀፈኝና ወደ ፊቴ ተደፋሁ። ግንባሬ ከአስፓልቱ ጋር ተጋጨ። ህመሙ የሠራ አካላቴን ሲያናውጠውና ጩኸቴን ሰለቀው አንድ ሆነ።

ከጩኸቴ በላይ "ሽንብራው ፈሰሰ!" የሚል ድምፅ ከበስ ተጎላዬ አስተጋባ። ጆሮ ቆራጩ በሁለት እርምጃ ደርሰው ብብትና ብብቴን ይዘው አነሱኝ። ፀጥ ብዬ ዙሪያዬን ተመለከትኩ። የፈሰሰ ሽንብራ የለም። ስወድቅ በደረሰብኝ ጉዳት ህመሙ በዝቶብኝ ስለነበር ማልቀሴን ጀመርኩ።

"እንዴ! እንዴት ወንድ ልጅ ሆነህ ታለቅሳለህ?!" አሉኝ ጆሮ ቆራጩ ቁልቁል እያዩኝ። ዓይና�ቸው ይስቃሉ እንጂ አልታዘቡኝም።

ወዲያውኑ ፀጥ አልኩኝ "ወንድ ልጅ ለካ አያለቅስም?" እያልኩ በሆዴ።

"እርቦሃል ማለት ነው። ወንድ ልጅ ቶሎ እንባው የሚመጣው ሲርበው ነው። ና!" አሉኝና በቀኝ እጃቸው ግራ እጄን ይዘውኝ ዳቦ ቤት ገቡ።

ሁሌ እንደማደርገው በቃኝ አላልኩም። ሆዴ የዳቦ ነገር ሲነሳበት ይሞረሙረኝ ጀምሯል።

ባለአራት ፍራንክ ትልቅ ዳቦ ገዙና ሰጡኝ። ተቀብዬ አጣድፌው ጀመር። እኔ ማዕድ ላይ ስለሆንኩ ጆሮ ቆራጩ ዝም ብለውኝ ስንሔድ አንድ ትልቅ ሃውልትጋ ደረስን።

አንዲት በአለባበሷ ጎስቆል ያለች ወጣት ወደ ታች አቅጣጫ ስትሄድ "ጤና ይስጥልኝ የእኔ እህት!" አሏት ጆሮ ቆራጩ።

"ዛሬር ይመስገን!።"

"ወዴት ነው እምትሄጂው?"

"ምነው በደህና ጠየቁኝ?"

"ይሄ ልጅ ሰፈሩ ጠፍቶበት ነው። እኔ ከስድስት ኪሎ እዚህ ድረስ ይዤው መጣሁ። ወደታች እምትዘልቂ ከሆነ አብሮሽ ሄዶ ከዚያ ለሌላ ሰው አደራ ብለሽ ወደ ቂርቆስ እንድ ትሸኝልኝ ነው መንገድሽን የጠየኩት።"

"እኔ እስጢፋኖስ ድረስ ነው እምሄደው።"

ቀና አልኩና "እስጢፋኖስ ከደረስኩማ ሰፈሬን አውቀዋ ለሁ!" አልኩ ዳቦዬን እያላመጥኩ።

"ዝም በል! ከውካዋ! ጆሮውን መቆረጥ አምሮታል መሰለኝ" ሲሉ፣ በፍርሃት ተሸብሬ እንደገና ማልቀስ ጀመርኩ።

"እሪ ዝም በል! አታላዝንብን። የምታኝከውን ዋጥ! ወንድ ልጅ እያላመጠ አያለቅስም" ሲሉኝ ዝም አልኩ። ያላመጥኩትን ዋጥኩና ሌላ ገመጥኩ።

"እንት ቀጣፊ፣ አዋቂ ጨዋታ መካከል አትግባ" ብለው ገሰጡኝና ሴትዮዋን "እስጢፋኖስ ድረስ ከወሰድሽው በኋላ ለሌላ ሰው አደራ ብለሽ ወደ ቂርቆስ ሰደጂልኝ።"

"ካገኘሁ እሺ።"

"ታገኛለሽ እንጂ። ወይም ለገሀር ድረስ እሚወስደው ካገኘ ድልድዩን ተሻግሮ ይሄዳል።"

እኔ በሆዴ "ካምቦሎጆ ከደረስኩ በኩባንያ አድርጌ በዲቼል በር ቂርቆስ መሄድ እችላለሁ" አልኩ።

"እሺ!" አለችና ሴትዮዋ በቀጭንና በሻካራ እጇ ግራ እጄን ያዘችኝ።

በድጋሚ "እደራ!" አሏትና ጆሮ ቆራጩ እኔን ቁልቁል እየገረመሙኝ "እንት ቀጣፊ ወየውልህ ሁለተኛ ትጠፋና እንተን አያድርገኝ! ድጋሚ ከተገናኘን ሁለቱንም ጆሮህን ነው የምቆርጠው!" ድምፃቸው ውስጥ ግን ከፊት አያስተጋባም።

በዚያ የልጅነቴ ወቅት እንዲህ ለልጅ ጥቅራቸውን እንጂ ፊታቸውን በፍፁም ከማይስጡ ትልቅ ሰዎች ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች ፊት ለፊት ተገናኝቻለሁ። እነሱ ለእኔ እውነተኛዎቹ የመጨረው ትውልድ ወላጆች ነበሩ።

ጆሮ ቆራጩን ከተሰናበትን በኋላ፣ ፍርሃቴ ሁሉ ለቀቀኝ። ሴትዮዋ በዚያው ሻካራ እጇ ጥርቅም አድርጋ እንደ ያዘችኝ መሔድ ስንጀምር ቀና ብዬ አየኋትና «ይኼ ምንድነው?» ዞሬ ሃውልቱን እየተመለከትኩ።

«እ?!» አለችኝ በመደነቅ ስሜት ቁልቁል እያየችኝ «የኛ ቁሪስት! ትጠይቃለህ ደግሞ፣ ይኼ ሃውልት አራት ኪሎ ይባላል

አያልኩ ለአንተ ሳስረዳ አዚሁ ተገሽፌልህ ልደር?!» እጄን ሳብ አድርጋ ቁልቁል መራመድ ጀመረች።

በዚያ ትርምስ አንድም ቃል ሳትተነፍስ በሕዝቡ መካከል እየተሽለኮለከን አለፍን። ዳቦዬን ጨረስኩ። ውሃ ጠማኝ። በምንሄድበት መንገድ አንዱ ግቢ ውስጥ የቧንቧ ውሃ ድምፅ ሺ ሲል ሰማሁ።

"ውሃ ልጠጣ?!" አልኳትና ከእጇ አምልጬ አጠገባችን ባለው ግቢ ዘው ብዬ ገባሁ። "ምን አይነት ቢራቢሮ ፍጥረት ነው?..." እያለች ተከተለችኝ። ከሟንቧው አጠገብ ውሃ ሲቀዳ ያገኘሁት እኩያዬ የሚሆን ልጅ በመሆኑ ውሃ እንዲያጠጣኝ ጠየኩት። እሷም ደርሳብኝ ለመነችልኝ። ልጁ በጣሳ ከባልዲው ጠልቆ ሰጠኝ። ጠጥቼ እንደጨረስኩ እጄን ጥብቅ አድርጋ ይዛኝ ተመ ልሰን ወደ መንገዱ ወጣን።

ከፊት ለፊታችን ባለው ትልቁ ግቢ በር ግራና ቀኝ ላይ ቀጥ ብለው የቆሙትን የክቡር ዘበኛ ወታደሮች አየሁና "ይሄ የማን ቤት ነው?"

"የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው። ታላቁ ቤተ መንግሥት ይባላል።"

"ውይ! የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው? በናትሽ! በናትሽ! ሄደን እንጨብጣቸው?!"

ከትከት ብላ ሳቀች። 'የደላው ሙቅ ያኝካል' ጃንሆይ እን ዳንተ ሥራ ፈት መሰሉህ? በል ልጄ እኔ እንዳንተ አልደላ ኝም። ፈጠን ፈጠን ብለህ ተራመድ። ለመሆኑ ምን ልታደርግ ከቂርቆስ እዚህ ድረስ መጣህ?"

"ውይ! ግን ተይው!!"

"ለምን?"

ቅንድቤን በጣቴ ጠቆምኳት።

"ቅንድብህ ምን ሆነ?"

"እ! እማላቅ መሰለሽ? እማማ ረታሽ ነግረውኛል ኮ።"

"ምን ነገሩህ እማማ ረታሽ?"

"ጃንሆይ ካገኙኝ ለቀሪጥ..."

ሳቅዋን መቆጣጠር አልቻለችም። "እንደው ለመሆኑ ምን ልታደርግ ነው ከዚያ እዚህ ድረስ የመጣኸው?" አለችና በእደፈ ነጠላዋ ዕንባ ያቀረሩ ዓይኖችዋን አባበሰች።

ምንም ሳልፈራት ስለ አጠፋፌ እውነተኛውን ምክንያት ነገ ርኳትና "እኔኮ ሙዚቀኛቹ ከተማዋን ዞረው ተመልሰው እተነ ሱበት ቦታ ላይ ሲበታተኑ ሰፈሬ መመለስ አያቅተኝም ብዬ ነው። ሲሳይ ኅቢጥን ግን ሳገኘው አለቀውም።"

"ማነው ደሞ ሲሳይ ኅቢጥ? እቤት ስትገባ አባትህ ትንሽ ሳያቀምሱህ አይቀሩም።"

"ኅቢጥ ካታጠረ እገረፋለሁ፣ ካላታጠረ ግን ማንም ስላላየኝ አልገረፍም።"

"በል ዝም በል!" አለችኝና በራሷ ሃሳብ ጭልጥ አለች። አረማመዷ ፈጣን ባለመሆኑ ለጉዞዬ ብዙም አላስቸገረኝም። ውሃ በብዛት ስለጠጣሁ ሆዴ ውስጥ ሲንቦጫጭ ይሰማኛል። መኪና ዎቹ በአጠገባችን ሽው እያሉ ሲያልፉ አንዲት ሃሳብ መጣ ችልኝ። በመኪና የመጓዝ ልምዴን ላካፍላት ፈለኩ። "አባቴ መርካቶ ለባለ ሴሼንቶ ስሙኒ ከፍሎ ጭኑ ላይ አስቀምጦኝ ብዙ ጊዜ ወስዶኛል። ታዲያ ሴሺንቶ ውስጥ ሆኜ ሰው ሁሉ ወደ ኋላው ነው የሚሔደው። አሁን እኮ መኪናው በአጠገባችን ሲያልፍ እኛ ወደኋላ እየሮጥን ነው መኪና ውስጥ ላሉት ሰዎች የምንታያቸው።"

ከትከት ብላ ሳቀች። ነጠላዋን ተከናንባ በሳቅ በሚያበሩ ዓይኖቿ እያየችኝ "አንተ እዚህ ትፈላሰፋለህ። እናትህ ግን ይሄኔ..." አለችና በረጅሙ ተንፍሳ ጉዞዋን ቀጠለች።

እኔ ግን ወሬዬን ቀጠልኩ። "ደግሞ ኮ ሰው ብቻ መሰለሽ ወደኋላ እሚሄደው? ሜዳውም፣ ቤቱም፣ ዛፉም፣..." ስል እንድ ውሻ ባጠገቤ አለፈ። "ውሻውም ጭምር ነው" ስላት ዳግመኛ ሳቋ አሸነፋት።

"እንተ ነል ጥርስ! አፍህን ዝጋ" አለችኝ።

"ጥርሴኮ ተሰብሮ አይደለም!"

"ታዲያ ምን ሆነህ ነው?" ጨዋታዬን ወዳዋለች።

"ሰባት ዓመት ስለሞላኝ ነው የተነቀለው።"

"እንዴት ተነቀለ?"

"በጣም ሲነቃነቅ እማዬ በክር ካሰረችው በኋላ፣ አባበለችኝ አባበለችኝና ሳብ አደረጎችው" አልኩና፣ ጥርሴን እንደ ምነቅል ሁሉ ስወራጭ እጄ ከእጇ አፈተለከ። መልሳ አልያዘችኝም።

"የተነቀለውን ጥርስህን የት አደረከው?"

እኩል እየተራመድን አንጋጥጬ አሳየኋትና "ለወፌቱ ሰጠ ኋት። የርሷን እንድትሰጠኝ" አልኩና በመዝሙር፣

ወፌ! ወፌ! ያኔን ጥርስ ሳንቺ!

ያንቺን ጥርስ ለኔ ብዬ ጣራ ላይ ወረወርኩት አሁን ይበ ቅልልኛል።"

"መቼ ነው የተነቀለው?"

"ድሮ! እንዲበቅልልኝ ጠዋት ጠዋት በአመድ እየታሸ ልኝ ነው።"

"ወሬኛ ቢጤ ነህ፣ ስምህ ማነው?"

"ተስፋዬ ዜራሞ።"

"ዜራሞ ደግሞ የምን ስም ነው?"

"የአባቴ።"

"እናትህስ ግን ይባላሉ?"

"ባሎቴ ጋጋ"

"እንዴ'! አንተ አውቅሃለሁ። ስምህ ፉንጌ አይደለም?"
"ተቀይሯላ! አሁን እኮ አንደኛ ክፍል ነኝ"
"እናትህ ጉልት እንጀራ ይሸጣሉ አይደል?!"
"አዎን።"
"ከቦኖ ውሃው አጠገብ አይደለም መደባቸው?"
"አዎን። ከርሷ አጠገብ እማማ ብርሌ ናቸው እሚቀ መጡት። ከዚያ በኋላ እማማ ሹሸ..."
"ዝም በል! ተዋውቀናል" አንት ዙረታም ቆይ ዋጋህን ታገኛታለህ" አለችኝና ሳቅ ጨዋታውን አቁመን በፍጥነት መራ መድ ጀመርን።
መናፈሻው አካባቢ ስንደርስ በራሷ ሃሳብ ተመስጣ ቆመች። መንገድ የጠፋት መሰለኝና ልረዳት ፈለኩ። "መንገዱ ጠፋብሽ እንዴ? ቆይ በእንዴ አሳይሻለሁ" አልኩና ምራቁን ግራ እጇ ላይ ተፋሁ። በቀኝ እጇ ምራቁን በካራቴ ስመታ፣ ምራቁ አብዛኛው ወደ መናፈሻው ተረጨ፣ ወዲያው ወደላይ ቀና ብዬ አየኋትና "በዚህጋ እንሂድ።"
በሙዚቃዊ ሳቅዋ አስተጋባ። በዚያው ሻካራ እጅዋ ክንዴን ይዛኝ "በእንዲህ አይነት ጨዋታ መንገድ ይፈለጋል? የጠፋ ፅቃ ነው እንጂ።"
"እረ? መንገድም ይፈለጋል!" አልኳትና አንዱን የወደቀ ቆርኪ በእግሬ በለኛ ማክለኛ ጨዋታ ስልት መታሁት።
"በምራቅ መንገድ ማወቅ ከቻልክ ለምን ቅድም ከስድስት ኪሎ ወደ ቂርቆስ ለመመለስ አልተጠቀምክበትም?"
"ቅድም እኮ ደንግጬ ነበር። ባልደነግጥ ኖሮ በምራቁ ምልክት እሄድ እሄድና ሰፈሬ ግብት እላለሁ!" በፈጣን ድምፅ ነቃ ብዬ መለስኩላት። በራስ መተማመኔ እየጨመረ ነበር።
በፈገግታ እያየችኝ "መልስ አታጣም መቸስ" አለቺኝ። በምራቁ አቅጣጫ መሪነት በጠቆምኳት መንገድ ቁልቁል ይዛኝ ተጓዘች። ሁለት የክቡር ዘበኛ ወታደሮች ግራና ቀኝ ጠብመንጃዎ ቻቸውን ይዘው ቀጥ ብለው የቆሙበት በር ላይ ደረስን። «ይኼም የአባባ ጃንሆይ ቤት ነው?» ጠየኳት መሪዬን።
«አንተ ቆቅ ነህ!» ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥትን ታውቀዋለህ?» ጠየቀችኝ።
«አዎን!» አልኳት፣ ግን ውሸቴን ነው።
የአዋቂነት መንፈስ በሥራ አካላቴ ናኘ። እስጢፋኖስ አካባቢ ደረስን።
"ከዚህ በኋላ ባቡር መንገዱን ከተሻገርኩኝ ሰፈሬ መድረስ እችላለሁ"
"አሁንማ ቤትህ ካላደረስከህ አልመለስም ሆ! የትዬ ባሎቴ ውለታ!" አለች ግማሽ ለራሷ እያጉተመተመች።

"እረ! መጥፋቴን ነግረሽ ልታስገርፈኝ" ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ።
"ዝም በል! አሁን እኔ ባላደርስህ ሊቀርልህ ኖሯል? አታይም፣ መሽቷል እኮ!" ማልቀስ መጀመሬን አይታ "በቃ አትነፋረቅብኝ መሺለኪያን እንዳላስፍኩህ ብቻህን ትሄዳለህ።"
እንዳስችውም መሺለኪያን እንዳለፍን ቆማ እያየችኝ እኔ በልጅ እግር በሶምሶማ ሩጫ ወደ ሠፈሬ ሄድኩ። ጨለሚል ግን ጨረቃ መሉ ብርሃንዋን ፈንጥቃለች። ትከተለኛለች። ስሮጥም ከጎን ከጎኔ እያበራችልኝ ሠፈር ደረስኩ። ጨረቃ ሁሌም ማታ ማታ እኔን መከተል ትወዳለች።
ሦስት ልጆች በዕድቱ ጠፍተን፣ የተገኘው ሲሳይ ጎቢጥ ብቻ ነው። ኃይሉ ዶሮ የደረሰበት አይታወቅም።
ቀጢሳው የኔን መምጣት በርቀት ሲያይ ለቤተሰቦቼ ለመና ገር ወደእኛ ቤት ሮጠ። መኩዬ ቀጫጫው በፍጥነት እኔጋ መጥታ ስለ ሠፈራችን የዕለት ሁኔታ መረጃ ሰጥታኝ የት እንዳ መሸሁ ጠየቀችኝ። መልስ ሳልሰጣት ከእኛ ቤት ጎረቤቱ ሁሉ ተግተልትሎ ወጣ። አባቴ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ሊፈጀኝ ሲል፣ አባባ አጋፋሪ በከዘራቸው ሳብ አድርገው አበረዱት።
ወደኔ ዞረው "ፉንጋይ፣ የት ውለህ መጣህ?" አሉኝ በለ ዘብታ።
እውነቱን ነገርኳቸው።
"ኃይሉንስ አይተኸዋል?" ሲሉኝ የዶሮ እናት እማማ ሸጊቱ የሰማይ ስባሪ እሚያክል ቁመናቸውን እያንዣበቡብኝ በዕንባ የደፈ ረሰ ዓይናቸውን እያቁለጨለጩ መልሴን ይጠብቃሉ።
"ኃይሉ እኮ ከእኔ ጋር አልሄደም!" አልኩ።
እማማ ሸጊቱ "ወይኔ ልጄን! ይሄኔ ዓይኑን አውጥተው መለመኛ አድርገውታል! ወይኔ! ወይኔ" ሲሉ ኡኡታቸውን አቀ ለጡት። ማታ የዶሮ ወጥ እየሠራሁ ካልበላሁ አልተኛም ብሎ ሌሊቱን ቁጭ ብሎ አጋመሰ። እሷንም ሳይቀምስ እንቅልፍ እሸነፈው! ወይኔ ልጄ! እንደዚያ እንዳማረው ድፍት ብሎ ይሆ ናል! ኡ! ኡ!"
"ጠዋት አብራችሁ አልነበራችሁም?" አባባ አጋፋሪ ደግ መው ጠየቁኝ።
"ጠዋትማ አብረን ነበርን፥ እኔና ሲሳይ ጠፍተን ስንሄድ ቀጢሳው ኩኩሉ እያለ ነበር። እኔና ሲሳይ የምንደበቅ መስለን ስንጠፋ ኃይሉ ወደ ግቢያቸው ገባ። እርሱኮ ኩኩሉ ስንጫወት ብዙ ጊዜ እሚደበቀው እቴነሽ አልጋ ስር ነው፣ እዚያ አይታ ችሁታል?"
ታላቅ እህቱ እቴነሽ በሩጫ ወደ ቤታቸው በረረች። ጎረቤቱም ተከተላት። እኛ እነኃይሉ ግቢ በር ላይ ስንደርስ እቴነሽ እየሳቀች ወጥታ "አልጋ ስር ተኝቷል!" ብላ አበሰረችን።

በኃይሉ ዶሮ ባልተጠበቀው መንገድ መገኘት ነገሩ ሁሉ ወደሳቅ ተለወጠ። የኔ ጥፋተኝነትም በዚያው ተረሳች።

ቤት ለእንግዳ

"ተረት ተረት"
"የላም በረት?"
"ሆደህ ይተርተር ለብረት"
እማዬ!

በቤታችን ውስጥ አልፎ አልፎ እንግዳ ይበዛል። አንዳን ዴም የተማከሩ ይመስል የአባቴና የእናቴ ዘመዶች ከየጠቅላይ ግዛቱ ይመጣሉ።እንግዳ ሲመጣ ደግሞ አባቴና እናቴ ቤት ያፈራውን ለማቀራረብ ጉድ ጉድ ይላሉ። የእንግዶቹ መምጣት ደስታንም ጎዘንንም የሚያስከትል ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለዘመናት የማይረሳ ትዝታ ትተው የሚሄዱ ናቸው።

በአንድ የበጋው ወር መገባደጃ ላይ ሳርያን ኮትና ተፈሪ ቅድ ሉሪ የለበሰና ቦት ጫማ ያደረገ ባላገር ቤታችን መጣ። ለአባቴ የሩቅ ዘመዱ ነበር። ዛሬ በምናቤ ስስለው እጭር፣ በጋያ ጢስ የበለዙ ጥርሶች፣ የደፈረሱ ዓይኖችና የተሸበሸበ ግንባር ያለው የቀይ ዳማ ነው። እነዚያ ድፍርስ ዓይኖቹ ደግሞ ንቁዎችና ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ የሚያስተውሉ ናቸው። ከፍተኛ የትምባሆ ሱስ ስላለበት በላይ በላዩ ግስላ ሲጋራውን ያጤሳል። ሲጋራውን ገንዘብ ከኪሱ አውጥቶ አይገዛም። ቤተ ዘመዱ ይሸ ምትለታል፣ አንድ ቀን የሚገዛበት ፍራንክ ቢያጣ እማዬ እንድ ትሸምትለት ጠየቃት።

እማዬም ፈገግ ብላ "ምነው ቅድም ቱማ ውሃ ጠጣበት ብሎ አንድ ብር አልስጠህም?!" አለችና ጥያቄውን በጥያቄ መሰ ለችለት።

በምፀት ሳቀና "ብር ተመንዝሮ ሲጃራ ይገዛል? ብር ግብር ይከፈላል እንጂ!"

እማዬ የኮረኮሯትን ያህል ሳቀች። ሰውዬውም በእናቴ የብር ውሎን አለማወቅ ሳቀባት። ይህን አስቂኝ አጋጣሚ አባቴ ከገበያ እንደተመለስ አጫወተችው። አባቴም ስቆ አንድ ፓኬት ግስላ በስድስት ፍራንክ ገዛለት። በቤተሰባችን አስደናቂ አጋጣሚ በተነሳ ቁጥር ይህ ገጠመኝ ሰዛው ሳይነጥፍ ሁሌ እንደ አዲስ ያስቃቸዋል።

ከዓመታት በኋላ *ፍቅር እስከ መቃብር* ውስጥ "ባላገር የሚበላው ቢያጣ የሚገብረው አያጣም" የምትሰዋን አባባል ሳነብ ተራዬን እኔም ሳቅሁ።

እንግዳን መቀበልና መሸኘቱን ወላጆቼ ቢወዱትም እኔ ግን ደስ አይለኝም። በእንዲህ አይነት ዕለት ተቃውሞዬን ለእናቴ ብቻ በሚገባ ቋንቋ አልባ ድርጊት እገልጻለሁ። ጉንጩን እነፋና ትከሻዬን እንደ እስክስታ ወራጅ አሰብቃለሁ። እሷ ደግሞ "ተው አንተ ልጅ" በማለት ታሰጠነቅቀኛለች። በቆምኩበት አንደጨፋሪ አሰበቃለሁ፣ ከተቀመጥኩም እግሬን አንፈራግጣለሁ።

"እሂሂ! ብታርፍ ይሻልሃል!"

በተቃውሞዬ እፀናለሁ።

"እንተ ልጅ!" ብላ ማማሰያዋን ስትቃጣ ዞር ብዬ አመ ሰጥኩ። አባቴ ንትርካችን አልገባውም። ግር እንዳለው እንግ ዳውን ይቅርታ ጠይቆ ወደ እናቴ ዞረና "ምን አድርጊ ነው የሚልሽ?"

"ተወው! ተጫወቱ። እኔና እሱ እንተዋወቃለን" ብላ ወደ እኔ ዞራ "አንተን አያድርገኝ የተያዝክ እንደሆን!"

ከእንግዶቹ አንደኛው በጋሞ ቋንቋ "ምን ፈልጎ ነው?" ሲል ጠየቃት። 'ምንም!' በሚል ስሜት ትከሻዬን ሰበቅኩ። አኳኋኔ ግር እንዳለው በመለኪያ የተቀዳለትን ካቲካላ ብድግ አድርጎ ፉት አለና ሞጭሟጫ ዓይኖቹን አስለመለመ። አባቴም "ተዋቸው እነርሱ ይተዋወቃሉ" አላቸውና ወጋቸውን ቀጠሉ።

እናቴ ዝንጉርጉር ሻሽዋን አጠበቀችና "እግርህን ሳትታ ጠብ ነው ራትህን የበላኸው?" ብላ መልሴን ሳትጠብቅ ብብትና ብብቴን በእጆቿ ይዛ አነሳቺኝና ትልቁ አልጋ ላይ ቁጭ አደረ ገችኝ። ከዚያም ሰብ ባለ ውሃ እግሬን እየፈተገች "የትም አሏራ ስታቦን ውለህ ምን ምን እንደምትሸት ባወከው? ፈሳም! ያንተን እግር ማጠብ..."

"ወይኔ ቁስሌን!" አልኩና ጮኽኩኝ።

"ዝም በል!" አሰና አባቴ ዘሎ መጥቶ አፈጠጠብኝ።

ሕመሜን ዋጥኩ።

"ጋሼ ስታርስልኝ ስትኮቴኩትልኝ ነው እንቅፋቱ የመ ታህ? ቀጣፊ! እዚህ እኛ የምንጨነቀው ሳንተው የወደፊት ኑሮ የተቃና እንዲሆንልህ ነው። ትሰማለህ? የአያት የቅድመ አያት መሬታችንን በነፍጠኞች እየተነጠቅን ነው" አለኝ በኃይለ ቃል።

አልገባኝም። የእግሬን ሕመም ቻል አድርጌ ጨዋታቸ ውን ሰማድመጥ ሞከርኩ። እማዬም ያለምንም ከልካይ እግሬን እንደልጊ መፈተጉን ቀጠለች። አመመኝ ብዬ ብቃወም የሚከተ ለውን ስለማውቅ ህመሙን ቻልኩት።

እማዬ ብዙውን ጊዜ እግሬን የምታጥበኝ ሌላ የሚያጣድፍ ጉዳይ ሳይኖራት ነው። ፋታ ካላት አጠገቤ ቁጭ ብላ ስታጠብ እያስተዋለች "ቁርጭምጭሚትህጋ እሸው! የጣቶችህ መሀልና

መህሉን! ኧረ አንተ ልጅ ውሃ አትፍራ!" እየነገረችኝ፣ እንደ ተባልኩት ካልፈጸምኩ ትበሳጭና "የማትረባ! እግሩን መታጠብ የማይወድ ወንድ ልጅ ጠረኑ ምን ምን እንደሚል ባወቅህ? ስታድግ ጉድህ የሚፈላው ያንተ!..."

በዚያን ወቅት የእኔ ማደግና የእግሬን አለመታጠብ ያሳ ቸው ዝምድና አይገባኝም። እንዲህ በተናደደች ወቅት ብጠይ ቃት አትመልስልኝም፣ ብትመልስልኝም ቋንቋዋ ይጠጥርብኛል።

በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ ስለምጠላ፣ ታዝዤ ስታጠብ ጭን ቶት ይይዘኛል። አጠገቤ ሰው ከሌሰ እግሬን መታጠብ ሳይሆን የመቀባት ያህል እግሬን በውሃ አንቦጫርቅና እነሳለሁ። በዚህም ምክንያት ሁልጊዜም እግሮቼ ሬንጅ የተቀቡ ይመስላሉ። አስገ ዳጅ ኃይል ከተፈጠረ ፊቴን አጨማድድና ዓይኔን ጨፍኜ "እትት ት!" እያልኩ አንድ እግሬን ወደ ሳህኑ እሰዳለሁ። እማዬም "ውሃ ዘርህን አልጨረሰ! ዘርማንዘሩን የፈጀበት እንኳን እንዲህ አይጨነቅም!"

እግሬን እየፈተገችኝ ከአባቴ ጋር ባሳነሮቹ የሚያወሩትን ለመስማት ሞከርኩ። ወሬው ለእኔ በፍፁም የሚገባኝ አይደለም። አንዳቸውንም አያስቃቸውም። አንዱ ሲያወጋ ሌላው በትዕግሥ ትና በአትኩሮት ያደምጠዋል። የሚጠቀሙባቸውም ቃላት ለልጅ አይገቡም። ንጉሥ ነገሥት፣ ጭቃ ሹም፣ ምስለኔ፣ አገረ ገዢ የሚባሉት ቃላት በወጋቸው መካከል ተደጋግመው የሚነሱ ነበሩ።

እማዬ እግሬን በጨርቅ አደራርቃልኝ አልጋው ላይ ተመ ቻችቼ ጋደም አልኩኝ። ፊቴን ወደ እንግዶቹና አባቴ መልሼ እለማቸዋለሁ። ዓይነ ሞጭሚጭው እንግዳ "እንዴት የአያት የቅ ድመ አያቶቻችንን መሬት በጭሰኝነት እንመራለን። ሰው በገዛ አገሩ ጭሰኛ ይሆናል?!" ሲል አማረረ።

እማዬ አንዳንዴ አርጥብ እንጨት ምድጃው ውስጥ ከታ አልነድ ሲላት በጭስ ትታፈናለች። እነዚህም ሰዎች በአገራቸው በገዛ መሬታቸው ላይ በጭስ የሚያፍናቸው አለ ማለት ነው? ብዬ ሳስብ አባቴ ቀበል ያደርግና "ንጉሥ ነገሥቱ ናቸው ጉድ ያደረጉን። ባለመብት መሆናችንን አስፈላጊውን ማስረጃ ሁሉ አቅ ርበን ፍርድ አንድናገኝ ስንወተውት፣ ጉዳዩን ባላባቶች በጉቦና በምልጃ አስቀድመው ይዘውት በጭሰኝነት ተሰጠን" ብሎ በቁጭት የደም ሥሩ ተግተረተረ።

ሌላኛው እንግዳ ጭቅጭት የጠገበ ቡልኮውን ገልጦ ቀኝ እጁን ዘረጋና መለኪያዋን አንስቶና ከካቲካላው ፉት ብሎ "ጃንሆይ ምን አደረጉ? እኛን ያስቸገረን አፈንጉሥ ደባልቄ ነው። ንጉሡ ይግባኛችንን በዙፋን ችሎት ተራ በተራ አይተው ፍርድ ሊሰጡን ሲሉ ያ የአርን ዝንብ ጥልቅ አለና! ግርማዊ ጃንሆይ፣ ይህ ጉዳይ ለፍርድ የተሟላ አይደለም። ስለዚህ ግርማዊነትዎ ሌላ ቀጠሮ እንዲሰጠን ቢያዙ አላቸው። የተፈጸመውም ጉዳይ

በይደር ተላለፈ። እንግዲህ በዳግም የዛሬዋ ዕለት ላይ ለመድረስ እኛም አርጅተናል። የልጅ ልጆቻችን ቢፈፅሙት እንጂ እኔስ የምታደለው አይመስለኝም" ብሎ ተከዘ አለና "አምላክ ፊቴን መልሶልን ቢሆን ኖሮማ አፈንጉሥ ደባልቄ ይህንን የነገር መርዙን አይረጭብንም። ጃንሆይም ይዳኙን ነበር!" አለና ፀጥ አለ።

"ጃንሆይ ተነስተው ቆመው ነበር?" ሲል አባቴ በጥድፊያ ጠየቀ።

"በደንብ" አለ ዓይነ ሞጭሚጭው ሰውዬ በእርግጠኝነት።

ጃንሆይን ብዙ ጊዜ አይቻቸዋለሁ። እንደ ድመት ሁሌም ንፁህ፣ ንቁ፣ አጭርና ቀይ ናቸው። "ለምንድነው አባባ ጃንሆይ የሚቆሙት?" ስል በጥድፊያ እማዬን ጠየኋት።

እሷም "እንዲህ አይነት የአዋቂ ጨዋታ ለልጅ አይገባውም" አሰኝኝ። የዕለት ሥራዋን እያጠናቀቀች በመሆንዋ ከጨዋታው ለመቀላቀል እንዝርቷን እያነሳች።

በእርግጥ እንዳለችው አልገባኝም። ነገር ግን በግድ በመሬ ታቸው ላይ በጭስ የሚታፈኑበት ሁኔታ እንደተፈጠረባቸው ሰም ቻለሁ። እማዬ እኔን ከማጫወት ይልቅ ወደ እንግዶቹ በመሄዷ ቀንቻለሁ። በተቃውሞ ተወራጨሁ። ውዲያው ገባት። አጠገቤ መጥታ ቁጭ አለችና "ነገርህ ሁሉ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ነው?" ብላ ልብሴን እያወላለቀችልኝ ታጫውተኝ ጀመር። "ይኸ ውልህ እኔና አባትህ ትንንሽ ልጆች እያለን ፋሽስት ጣሊያን አገራችንን ወሮ ነበር። በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ለዓለም መንግሥታት አቤቱታቸውን ሲያሰሙ ውጪ አገር ሄዱ። እንደሚባለው በዚያ የሰዳት አገር እያሉ ተሳሉ። እግዚአብሔር ለአሸናፊነት አብቅ ቷቸው ለአገራችን መሬት ካበቃቸው ለሕዝባቸው ፍርድ ሲሰጡ ቆመው ለመዳኘት መሳላቸው ይነገራል። አምላክም ልመናቸውን ሰማቸው። አምስት የመከራ ዘመንም አለፈ። በድል አድራጊነት አዲስ አበባ እንደገቡ በሰለታቸው መሠረት ሰሞኑን የአባትህን አገር ሰዎች በመሬት ጉዳይ ሲሟገቱ ሲፈርዱላቸው ነበር የቆሙት።"

"ታዲያ ቆመው ፈረዱላቸው?"

"ምን ይፈርዱላቸዋል እንደሰማኸው በይደር ታለፈ።"

ትንሿ ልቤ ጃንሆይን ተቀየመቻቸው። "መቆማቸው ካል ቀረ ምን አለበት ቢፈርዱላቸው?"

"ትሰማኛለህ፣ የኔ ፉንጋ! ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ነበር..." ብላ ምሽቱን ከእኔ ጋር እንደምታሳልፍ አበሰ ረችኝ። አካሳቴ ሁሉ ጆሮ ሆኖ ፀጥ አልኩ።

"ተረት ተረት!" አስታራቂው ቃል ከአንደበቷ ይሰማል።

"የላም በረት..." እመልሳለሁ።

"ሆድህ ይተርተር በብረት" ብላ ትኮረኩረኛለች። ፍንድቅ ብዬ አስቃለሁ። ቂመኝነቴ፣ አልታዘዝም ባይነቴ፣ ማመፁን ይረሳና በላቅ ጠበል ተጠምቄ ሌላ ልጅ እሆናለሁ።

"እረ እዚህ ቁም ነገር ጨዋታ ላይ ነን!" አባቴ ተቆጣ።

"እሺ ተጫወቱ" እማዬ ዝቅ ባለድምፅ መልሳ ለኔ ደግሞ በሹክሹክታ ያህል "አንድ ሰውዬ ነበረ..." ብላ ስትጀምር ትመስ ጠኛለች። ጠይም ገጽዋ የተቆላ ቡና ይመስላል። ንቁ ዓይኖ ችዋን ቦዘዝ አድርጋ እያስተዋለችኝ ብዙም ወጣትነት ያልራቀው አካልዋ ዘና ይላል።

አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ኮስተር ብላ አናቴን እየደ ባበለች፣ ወይም ነጠላዋን እየቋጨች፣ አለበለዚያም እየፈተለች ትረካዋን ትጀምራለች። እማዬ ሁሌም ሁለት ሰው ነች። እያ ወጋች የምትሠራው ከእጇ አይጠፋም። ሥራ የምትፈታው ወደ እኩለ ሌሊት አካባቢ የዕለት ሥራዋን አጠናቅቃ ከሁላችንም መጨረሻ ጉንዋን ለማሳረፍ ወደ አልጋዋ ለመተኛት በምት መጣበት ወቅት ብቻ ነው።

በእንዲህ አይነቱ የተረት ሰዓት የምደሰተው እኔ ብቻ ሳል ሆን እማዬም ጭምር ነበረች። ሳጫውታት፣ ሳደምጣት ደስ ይላ ትና "ሳሽ ፉንጋዬ እየደረስክልኝ ነው" ትልና ለራሷ ያክል በስ ሆላስ "አምላክ የተባረከ ልጅ ባደረገህ ብቻ" ብላ ታጉተመ ትግለች።

የሕይወቷን ክፍተት እኔ እንድሞላላት አምላክ ስለላከላት ደስ ይላታል። ደስታዋ ያለአንዳች ቃል፣ በድርጊትዋ ስለሚገባኝ ፍቅራችን ጥልቅና ጥብቅ ነበር።

ብርድ ልብሱን ተከናንቤ፣ ጭንቅላቴን ብቅ አድርጌ በተ ረቱ ውስጥ የሚፈጠረውን ሰውዬ በዓይነ ሕሊናዬ እሥለዋለሁ። ትዝ እንደማለኝ በዚያ አይጠገቤ በሆነ የልጅነት ወቅት ያለ ምንም ግርዶሽና ዓይነጥላ በርካታ ተረቶችን ሰምቻለሁ። አንዳን ዶቹ አሳዛኝ ሲሆኑ፣ የተቀሩት አጨራረሳቸው አስቂኝ፣ አልያም አስፈሪ ይሆኑብኛል።

በተረቱ ውስጥ የሚከሰተው ባሕርይ የተራበ፣ የተጠማ፣ አያሌ ምዕራፎች የተጓዘ የመንግሥት መልእክተኛ ወይም አንድ የራሱ የሆነ ተልእኮ ያለው ሰው ይሆናል። ሁሌም ሰውዬው ሲታየኝ ሽመልና ስንቅ ይዞ ነበር።

እማዬ ተረቶች ውስጥ ሰውም፣ የዱርና የቤት እንስሳትም አሉበት። የጠጣን ብልጥነት፣ የዝንጀሮን ቂልነት፣ የአሀያን ቻይ ነት፣ የአንበሳን ኃያልነት፣ የነብርን ቁጡነት፣ የዔሊን ቀርፋፋነት ታሳየኛለች።

እኔ አልጋዬን ለእንግዶቹ ስቅቁ አላስተኛም ብዬ እንደ ማምፀው፣ አሀያስ ለምን ሰዎችን እምቢ ብሎ ጫካ ውስጥ አይኖርም? ዝንጀሮስ ለምን ብልጥ አይሆንም?... እያልኩ ፅንፍ

አልባ ጥያቄዎችን አነሳለሁ። እናቴም ሳትታክት ልታስረዳኝ ትሞክራለች። ከዕውቀቷ በላይ ሲሆን፣ "ይህ የእግዚአብሔር ፋንታ ነው" ብላ ምላሹን ለፈጣሪ ትተወዋለች።

የአያ ጅቦን ተረት በሰማሁ ምሽት በጣም እፈራለሁ። በዙሪያዬ ያለ ማንኛውም ነገር በፍጥነት ጅብ ሆኖ ይበላኝ ይመ ስል ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ አስተውላለሁ። ስተኛም ብርድ ልብሴን በጭንቅላቴና በአግሬ ወጥሬ እከናነባለሁ። ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ ለመተኛት እሞክራለሁ። እንቅልፍ በዓይኔ ሳይዞር ብዙ እቆያለሁ። ፍርሐቴ በጣም ከአየለ ክንብንቤን ሳልገልጥ እማዬን እጣራለሁ። "ምን ሆንክ?" ትለኛለች በውስጤ የዘራችውን ፍር ሃት ረስታው።

"ፈራሁ!"

"ና! እኛጋ።"

"መብራቱን አብሪዋ!"

"ምን አስፈራህ? ና አይዞህ!" ብላኝ ማብሪያና ማጥፊ ያውን ግርግዳው ላይ በዳበሳ ስትፈልግ ንቁ ጆሮዎቼ ይሰማሉ።

አባቴ በቁጣ "ባይበራስ አትመጣም?" ይለኛል። በሠራ አካ ላቴ የነገሠውን ፍርሃት ሳይረዳ፣ ጉዳዩን ቢያውቅም በአዋቂ ልብ ግድ የለው። ሁልጊዜ በብልሃት ሳይሆን በግድ ይህንን ዓለም እንድደፍር ያስገድደኛል።

ማብሪያና ማጥፊያው ቀጭ ሲል አምፖሉ ተግ ብሎ አስፈሪውን ጨለማ ያባርረዋል። ቤቱ ውስጥ ምንም እንደሌለ ብርሃኑ ቢያበስረኝም፣ እንደፈራሁ ወደ ወላጆቼ አልጋ ራቁቴን እሮጣለሁ። አባቴ ቀልቦ መካከላቸው ያስተኛኛል።

አያ ጅቦ መካከል የሚተኛን ሰው እንደሚበላ ቢተረክል ኝም፣ አባቴን የሚያሸንፍ ጅብ እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ። በሁለቱ ሙቀት አካሌ እየቀለጠ ፍርሃቴም ገስል እያለ ሲሄድ እን ቅልፍ ይወስደኛል። ጠዋት ስነቃ እኔነቴን በግርግዳው ጥግ አገኘዋለሁ።

"እማዬ ማታ መሐል አልነበረም እንዴ የተኛሁት?"

"ነው እንዴ?" በማለት አቋግሳብኝ ተነስቼ ፊቴን እንድ ታጠብ ታዘኛለች። ልብሴን ለባብሼ በመወዘቻ ውሃዬን ይገር ያንን ማታ የሰማሁትን አስፈሪ ጅተረት ለጓደኞቼ ላወራላቸው እወጣለሁ።

የቴያትር ጥበብ በዞረበት ዝር ያላለችው ይህች የእኔ ገነት ጥበቡን ለእኔ አእምሮ መጥና የተውኔት ስልት ባለው ውበት የማቅረብ ችሎታ ነበራት።

አያ ጅቦን መምሰል ስትፈልግ አንዲት ቡትቶ ታነሳና ተከናንባ በጅብኛ ቋንቋ "እመት ጠጢት፣ እመት ጠጢት፣ እባ ክሽን የእኔ እመቤት ነገ አልቢ የምመልስልሽ አንድ አንኮላ ወተት አበድሪኝ ይላታል፤ እቤቷ ሄዶ።"

ከጅብ ባሕርይ ወጥታ እማዬ ትሆንና "ውሸቱን ነው ሊበላት ፈልጎ ነው። ልክ አያ ዝንጀሮን አታሉ እንደበላው። ጠጢትንም አታሉ ሊበላት" ትለኛለች በጣም በለሆሳስ ድምፅ። ጥንቃቄዋ አያ ጅቦ እንዳይሰማት የፈራች ትመስላለች። እኔም ፀጥታውን ሳላደፈርስ በጥቅሻ ገባኝ እላታለሁ።

የጠጢትን ባሕርይ ተላብሳ በቀጭን ድምፅ "ለመሆኑ አንተ ማነህ?" ትለዋለች።

"አያ ዝንጀሮ ነኝ" ይላታል።

"ምነው ድምፅህ አያ ዝንጀሮን አልመስል አለኝ? ደግሞ አያ ዝንጀሮ ከሆንክ አካላትህን እንዲህ ምን አገማው?" ትለዋለች። እማዬ ወደራሷ ባሕርይ ተመልሳ አፍንጫዋን ቆንና "አያ ጅቦ ግማታም ነው።"

አፍንጫዬን እይዛለሁ።

"አያ ጅቦ ተናዶ ሊያንቃት ይወረወራል። ጠጢትም በብል ሃት ታመልጠዋለች።"

"እሺ" እላለሁ የዛሬውን ገፀባሕርይ ፍፃሜ ለማወቅ።

"አንድ ሰውዬ ከዕለታት አንድ ቀን ሲሔድ፣ ሲሔድ፣... ሩቅ አገር ደረሰ። የገበሬ ቤት ሲያገኝ 'ቤቶች!' ብሎ ተጣራ።

የቤቱ ጌታም "ደጆች!" ብሎ ይመልሳል።

የቤቶችና የደጆች ቃላት ትርጉም ይጠፋብኛል። ይሁን እንጂ በኋላ ትዝ ካለኝ ልጠይቃት እያሰብኩ ተረቱን ሳላቋርጥ መስማት እቀጥላለሁ።

"የመሸብኝ የእግዜር እንግዳ ነኝ። የዛሬን ምሽት አሳድራችሁኝ ከጅብ መበላት ታስጥሉኝ ዘንድ እማፀናለሁ" ሲል ይለምናል። ባለቤቱም 'ቤት የእግዜር ነው ግቡ' ብሎ ያስገባውና ለሚሰቱ እንግዳ መምጣቱን ተናግሮ ጥሩ ራት እንዲዘጋጅ ነገራት። የእንግዳውን እግር ልጆቹ በሞቀ ውሃ እንዲያጥቡ አዘዛቸው። ራት እስኪቀርብ እንግዳውን ያጫውተው ጀመር። መንገደኛውም እሳት እየሞቀ ከየት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ ለቤቱ ጌታ ያጫውተው ጀመር።

"አዋቂዎቹ ሰዎች በሞቀ ጨዋታ ላይ እያሉ የግቢው በር ተንኳኳ። የቤቱ ጌታም ፈጠን ብሎ ወጥቶ 'ማነው?' በማለት ይጠይቃል። ከውጪ የቆመውም የሩቅ አገር መንገደኛ መሆኑን ገልጾ እንዲያሳድሩት ይለምናል። የቤቱ ጌታም ደስ ብሎት ይግቡ ጌታዬ፣ ቤት የእግዜር ነው!" ሲል በትህትና መለሰ።

"በዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ የገባው እንግዳው የተባባሉትን ሰምቶ ስለነበር፣ ብትሩን አንስቶ አዲሱን እንግዳ አላስገባውም ብሎ ተቆጣ።

"ለምን?"

"ቆይ ዝም ብለህ አድምጥ" ብላኝ ተረቱን ቀጠለች። "የቤቱ ጌታ በዚህ ተገርሞ 'ለምን አታስገባውም?' ይህ ቤት የእኔም

ያንተም አይደለም፣ የእግዜር ነው' አለው። የመጀመሪያውም እንግዳ 'እኔ የመንግሥት ምስጢር ይዤ የምጓዝ ሰው ነኝ። ይህ ሰው ቀደም ብሎ ከቀን ጀምሮ ሲከታተለኝ ነበር። በተለይ ጭው ያለ በረሃው ውስጥ ስንገባ ከአሁን አሁን ደፋኝ እያልኩ ነፍሰና ሥጋዬ እየተለያየ ነው አዚህ የደረስኩት፣ አምላክ ይመስገን' ብሎ አንጋጠ እግዜርን ወደ ሰማይ እያየ አመሰገነና 'ስለዚህ ይህ ሌባ ሌሊት አርዶኝ የመንግሥት ምስጢር ቢዘረፍ ትልቅ ጉዳት ይደርሳል። በዚያ ላይ ደሜ ደመ ከልብ ሆኖ ይቀራል። መዘዙ ለእናንተም ይተርፋልና ይህንን ሰውዬ እዚህ ቤት አላስገባም' ሲል ተከራከረ። የቤቱ ጌታም 'ግድ የለህም፣ እኔ እጠብቅሃለሁና እባክህን ቤት ለእንግዳ ብለን እንቀበለው፣ እያለ በገዛ ቤቱ ለመነው። እየማለና እየተገዘተ ምንም አይነት አደጋ እንግዳው እንደማያደርስ ሊያሳምነው ውተወተ። እንግዳው ግን ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ችክ አለ።"

"ኡ! በጣም ክፉ ሰው ነው! እማኑ ቂርቆስ ደግሞ ታያለሽ ይፈርድበታል።"

"እውነትክን ነው። ክፉዎች ላይ እማኑ ቂርቆስም፣ ጌታችን መድኃኒታችንም..."ከአፍዋ ነጥቄያት "እምዬ ማርያምም!"

"አዎን፣ ቅዱሳኑ ሁሉ እንዲህ አይነት መጥፎ ሰዎች ላይ ይፈርዱባቸዋል።"

በእንዲህ አይነቱ ትረካ ወቅት ችግሩ በተከሰተበት ቦታ እንዳለች ሁሉ በኃይል ተመስጣ በመንፈሷ ትበራለች። ተረትዋ እንደ እውነተኛ ታሪክ ስለሚሆንብኝ መንፈሴ አብሯት ይከን ፉል። "ከዚያስ?" አልኳት የቅዱሳኑን ፍርድ እየናፈቅኩ።

ከዚያ ባለቤትየው እንደነገርኩህ ጥሩ ሰው ስለሆነ፣ በኋላ የመጣውን እንግዳ ይቅርታ ለምኖት ጎረቤት ወስዶ እንዲያድር አደረገው። ለመጀመሪያው እንግዳም ማለፊያ እራት ቀርቦለት በላ ጠጣ።

"እሺ።"

"ከዚያማ ባለቤቱ የሚተኛበት መደብ ላይ ቁርበት አንጥፎ ቡሉኮ ደርቦለት የመጀመሪያውን እንግዳ አስተኛው። ማለዳ ወፍ ጭጭጭ! ሲል እንግዳው ተነሳና የጠዋት ቡናውን ጠጥቶ ቁርሱን በልቶ፣ የቤቱን ጌታ ለመስተንግዶውም፣ ሕይወቱንም ስላተረፈለት አመስግኖ ተሰናብቶ ቄዙ ጀመረ። ሲሔድ... ሲሔድ... ውሎ አመሻሽ ላይ ዳማኛ ከአንዱ ባላገር ቤት ለምኖ ማደር ሊኖርበት ሆነ። በአቅራቢያው ወደሚገኝ የገበሬ ቤትም ተጠጋና አሳድሩኝ አለ።

"ገበሬውም ልክ እንደትናንትናው ሰው ተቀብሎና አክብሮቱን ለመግለጽ ሙክቱን አርዶ አበላው። በሞቀ ውሃ እግሩንም በልጆቹ አሳጥቦ ይጨዋወቱ ጀመረ። ብዙ ተጨዋወቱ። ምሽቱም ሲጋመስ ገበሬው ወደ መደቡ ለመኝታ እየሄደ እንግዳውን 'ለመ ሆኑ ወዳጄ፣ ትናንትና ማታ አደርክበት ቤት አላስገባም ብለህ

ሽመል መዘህ ያባረርከውን እንግዳ አሁን ብታየው ታውቀዋለህ?' ሲል ያልታሰበና ከጨዋታቸው ውጪ የሆነ ጥያቄ ጠየቀው።።

"እንግዳው ክው! አለ።። ገበሬውም ወደ መኝታው እያዘገመ 'ትናንት አላስገባም ብለህ ያባረርከኝ ሰው እኔ ነኝ።። ሰመሆኑ ወዳጄ! ምን በደልኩህ? የትለ እንተዋወቃሰን? አልያስ ለዚህ በል ተነው ነገ ዓይነምድር ለሚሆን አህል እንዳልካፈልህ ብለህ ነው?...' ብሎ ቢጠይቀው፣ እንግዳው በተግባሩ በጣም አዘነ።። ፀፀቱ ስላሸበረው ተወርውሮ ገበሬው እግር ላይ ድፍት አለና እያለቀሰ ይቅርታ ጠየቀው ይባላል።።

"አየሽ አጣኑ ቂርቆስ ሲፈርድበት!" አልኳት በጣም ተገርሜ።።

"ታዲያስ! ለዚያውም አፍታም ሳይቆይ።። ቢሞት ይሻለው ነበር።።"

"ውነትሽ ነው ድብን ባለ!"

አንዲህ አይነት ስብዕናን የሚቀርፁ ተረቶች በሰማሁ ወቅት እኔም ጨዋ፣ ትሁት፣ ሰዎችን አፍቃሪ ሰመሆን እጥራለሁ።። እዚያው በዚያው ባሕርዬ ተለውጠ መንቀሹቀዥኜን ተወት አደር ግና ረጋ ለማለት እሞክራለሁ።። የትረካው ባሕርያት በሕሊናዬ ውስጥ የራሳቸውን ማኅተም ያኖሩብኛል።። በቆይታ ተፈጥሮ ወደ ለገሰችኝ ባሕርይ የምመለስ ቢሆንም በጊዜው አስተዋይና አመዛዛኝ ሆኜ እታያለሁ።።

"የባላገር ሰዎች ሁሉም ጥሩዎች ናቸው!" አልና ቤታችን እንግዳ ሆነው የመጡትን ሰዎች በርህራሄ ዓይን አያቸዋለሁ።።

"የአገር ቤት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ልጆቻቸውም በጣም ጥሩ የተባረኩ ናቸው።። የትላልቅ ሰዎችን እግር ያጥባሉ።። ሲልኩዋ ቸው ይታዘዛሉ።። ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይሠራሉ።። አናም የእኔ ፉንጋ..." ብላ እየደባበሰችኝ "አንተም አድገህ ሰው እንድትሆን ፀጋው ከተለገሰህ እግርህ የሚደርስበት ቦታ አይታወቅም።። ሰው የሚወለድበትን እንጂ የሚሄድበትንና የሚሞትበትን አያውቀ ውም።። የሰው ልጅ እጣው ሁለት አይነት ነው።። ተጉዞ ሄዶ እን ግዳ ይሆናል፤ ወይም እንግዳ ይቀበላል።። ስለዚህ ተጓዡም ተቀባዩም ሰዎች ቅን ከሆኑ፣ ኑሮዋቸው ጥሩና መልካም ይሆ ናል።። አንተም ኑሮህ የሰመረ ሆኖ ሁሉም ነገር እንዲባረክልህ ጥሩ ልጅ ሁን።። ደግ ሁን" እያሰኝ፣ በሕይወት ተሞክሮ የበሰለ ምክሯን በቅጡ እንደሚገባው እኩያዋ ታወራልኛለች።።

የምትለው ሁሉ ባይገባኝም፣ ጥሩ ልጅ መሆን እንደሚኖ ርብኝ እረዳለሁ።። ጥሩ ልጅ ከሆንኩ እግዚአብሔር ያሳድገኛል፣ ትምህርቴንም ይገልጽልኛል፣... አካሌ እየዛሰ ሄደ፣ ድብን ያለ እንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ አለ።።

ይህች ምራቅ ሳትደርቅ

"ና! የእኔ ፉንጋ! አረብ ቤት ትሄድና የአራት ፍራንክ ዘይት፣ የሁለት ፍራንክ ጨው፣ አራት ፍራንክ መልስ አስው።። እንካ ስሙኒውን።። ስትመለስ የማደርግልህን አታውቅም! ብርር በል! ቱፍ! (ምራቃቸውን እየተፉ) ይህች ምራቅ ሳትደርቅ ከተፍ በል!" አሉ እማማ ረታሽ።።

"እሺ።።"

"ቆይ አትንከውከው፣ ምንድነው ግዛ ያልኩህ?"

"የአራት ፍራንክ ዘይት፣ የአራት ፍራንክ ስኳር!"

"ይሽው! አላልኩም።። ይሄ ልበቢስ! ስኳር መቃምዋ ሱስ ሆናብሃለች ማለት ነው? ልብ በልና አድምጠኝ...!" ብለው ያር ሙኛል።። ከአፋቸው ነጥቄ "የአራት ፍራንክ ጨው።።"

"እሪ እኔ አልውጣኝም! የአራት ፍራንክ ጨው ምን ላደርግበት ነው? ድግስ የለብኝ!" ብለው እማማ ረታሽ አረሙኝ።።

እኔና አብሮ አደጎቼ በሰፈራችን ውስጥ ትላልቅ ሰዎችን አረብ ቤት በመላላክ አገልግሎት መስጠቱ አንዱ የውዴታ ግዴ ታችን ነበር።። ጎረቤቶቻችን ከእናታችን ማኅፀን ስንወጣ ሁሉ የዓይን ምስክር ናቸው።። እንደ አሳዳጊዎቻችን ስለሚቆጠሩም ክቤ ታችን ውጪ ሁሉም ትላልቅ ሰዎች በእኛ ሕይወትና ደህንነት ላይ የወላጆቻችንን ያህል የመወሰን መብት ነበራቸው።።

ተልከን ስንመለስ ልዩ ልዩ ጉርሻ ይሰጠን ነበር።። መላላኩ ከመደጋገሙ የተነሳ ጉርሻቸው ምን እንደሚሆን ከወዲሁ እናው ቀዋለን።። የአንዳንዱ ጉርሻ የሚናፈቅ ነበር።። እማማ አመለወርቅ ከጅሩ ዘመዶቻቸው በሚጭኑላቸው ጥቁር ስንዴ የሚጋግሩት ሙልሙል አሁንም ሳስበው ምራቄን እውጣለሁ።።

የኃይሉ ዶሮ እናት እማማ ሸጊቱ በውብ ቋንቋቸው ሲመር ቁን እዚያው፣ በዚያው አድገን እንዲታየን እያደረጉ አሹቁን በኪሳችን ያጭቁታል።። እማማ ሒለሚቱ አንጎሏ ከተላላኩንላቸው በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን የወሰዱብንን የጨርቅ ኳስ ይመል ሱልናል።።

በእኔና በእማዬ ብቻ የሚታወቅ የጋራ ምስጢር አለን።። ልትልከኝ ስትፈልግ ትጠራኝና መልዕክቱን ነግራኝ "ስትመለስ እማደርግልህን አታውቅም" ካለችኝ ስመለስ በጣም የሚጣፍጠኝን የቅንጭ ፍቅፋቂ እንደምትሰጠኝ አውቃለሁ።።

ከሁሉ በጣም የሚደብረኝ *ሃደ በቀሉጋ መላክን ነበር።። ቅቤ ነጋዴ ናቸው።። እማዬ ደንበኞቸው ነች።። አንዳንዴ ከእማዬ ጋር ገበያ ስሔድ የስሙኒ የራስ ቅቤ ትገዛቸውና እኔን መርቀውኝ

---

* ሃደ፣ በኦሮሚኛ እናት።።

ትንሽ ቅቤ ቆንጥረው ቁንጮዬ ላይ ይቀቡኛል። በላዩ ላይ የጉሎ ቅጠል ይለጥፉበታል። ከሃደ በቀሉ ጋር ፀጓችን በዚህ ነበር። ጓደኞቼ ካዩኝ "ቅቤያም!" እያሉ ይሰድቡኛል። በእንዲህ ያለ እጋጣሚ በጭንቅላቴ መሬት ቆሜ ቅቤውን ከአባራ ብደባልቀው ምርጫዬ ነው። ይሁን እንጂ ሃደ በቀሉ እንደመረቁኝ ሁሉ እንዳ ይረግሙኝ ስለምፈራ ንዴቴን ዋጥ አደርጋታለሁ።

በዚህ ወቅት እማዬ ቅቤ ስቀባ መናደዴ ይገባታል። አኳ ኋኔን ችላ ብላ ሁለቱ የቅቤን ፍቱንነት በአማርኛና ኦሮምኛ ጉራማይሌ ከሃደ በቀሉ ጋር ያወጋሉ። በተዘዋዋሪ ለኔም እየነ ገሩኝ ቢሆንም እኔ ግን አልሰማቸውም። ተሰነባብተው ወደ ሰፈራችን ስንሄድ ንትርኬን እጀምራለሁ። እሷም እርጋታ ባልተ ለየው ለሆሳስ ድምፅ "አይ የልጅ ነገር! አሁን ቅቤ ምን ጉዳት አለው? አናትህን ቀዝቀዝ ያደርግልሃል። ይህንን ከርዳዳ ፀጉርህን ያለሰልስልሃል። ግን እኔ ምን ችገረኝ አንተ ቀረብህ። እቤት ስን ደርስ አጥብሃለሁ" ስትለኝ እፎይታ ይሰማኛል።

አረብ ቤት ከሚልኩኝ ጎረቤቶቻችን አንዷ ደግሞ እማማ ረታሽ ናቸው። እማማ ረታሽ እኔ ከመወለዴ በፊት ከእናቴ ጋር የወጣትነት ጊዜያቸውን አብረው ስላሳለፉ በእኔ ላይ ከወላጆቼ በላይ ታላቅ ሥልጣን አላቸው። መሐን ስለነበሩም በጣም ይወ ዱኛል። ነፍስ ከማወቄ በፊት አዝለውኝ ከሰፈር ሰፈር ይዘዋወሩ እንደነበር እናቴ አጫውታኛለች። አንዳንዴ ለእናቴ ሳይነግሯት ይዘውኝ ስለሚሄዱ ለእናትና አባቴ የጠፋሁ ስለሚመስላቸው በዚህ ጊዜ ምድር ቁና ትሆንባቸዋለች። ከፍቅራቸው ብዛት የተነሳ በዚ ያን ወቅት ብርቅ የነበረውን ፎቶ እኔ ከእማማ ረታሽ ጋር ብዙ ጊዜ ተነስቻለሁ። ለእሳቸው የመውደድ መግለጫ የሆነው ይህ ድርጊታቸው እኔን በኃይል ይገዛኝ ነበር። እማማ ረታሽ ሲቆጡኝ ከፍርሃቴ ብዛትም አንዳንዴ ሽንቴን ጭርቅ አደርግ ነበር።

የእማማ ረታሽ ዓይኖች ተንልጉለው ሲያፈጡብኝ ልክ ቂር ቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተንጠልጥለው እንዳየኋቸው የቅዱሳን ሥዕሎች፣ ዓይን ብቻ ሆነው ይታዩኛል።

መልዕክቱን አስተካክለው ነግረውኝ ፈትለክ ብዬ ስሮጥ ከጀርባዬ ፈገግታቸው እንደሚከተለኝ ልቤ ይጠረጥራል። እማማ ረታሽ ሲቆጡ የማስፈራታቸውን ያህል፣ ሲስቁም በነፃነትና ከልብ ስለሆነ፣ እንደ አበባ ፈክተው ያምራሉ።

ድሮ ከቂርቆስ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት አንድ ትልቅ አረብ ቤት ነበር። አረቡ ከብ የእስላም ቆብ አናቱ ላይ አድርጎ ጫቱን በጉንጩ ወጥሮ፣ የዐመድ ጫፉ የረዘመውን ሲጋራ እሱ ላይ ለጥሞ፣ ሽርጡን እገልድሞ በሰፊው መደብሩ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ ገበያተኛውን ያስተናግዳል። እኛ ልጆች አረቡ የምርቃት ከረሜላ ስለማይሰጠን ከእርሱ መደብር መሸመት

እንወድም። ወላጆቻችንን ግን እየቀለደ ከሸቀጡም እየመረቀ ስለ ሚሸጥ መደብሩ ሁሌም በደንበኛ እንደተጨናነቀ ነበር።

ከማርገጃው ወረድ ብሎ የተከፈተች የጨነቀው ሱቅ ውስጥ የሚነግደው ሡልጣን ግን የእኛን የሕፃናቱን ልብ የሚስብ መስ ተንግዶ ነበረው። ብይ የሚያካክሉ የምርቃት ከረሜላ ይሰ ጠናል። ከረሜላው ቢያልቅ ስኳር እንዲመርቅልን እናደርገ ዋለን። የተላክነው ሁለት ልጆች ከሆንን ከረሜላዋን ቆርጭመን እንካፈላለን። ስኳራንም እንዲሁ። ሡልጣን በዚህ ብልሃቱ አማ ሉን በምንሸምተው ሸቀጥ ላይ ይሸቅበናል። አሸቃቀቡ ከልክ በላይ ከሆነ የሸመትነውን እንድንመልስ ወላጆቻችን ያስገድዱናል። በዚህ ወቅት ትልቅ ጭንቀት ይፈጠራል። ምክንያቱም የምርቃት ከረሜላዋ ተበልታለች። ይሁን እንጂ ሡልጣን በጥበቡ ሸቀጡን ያስተካክልና ግብይቱን የሰመረ ያደርገዋል።

የተላኩትን ሸቀጥ ሳላላስት ሸመትኩ። ስሙኒዋን ከፍዬ የአራት ፍራንኳን መልስ ለእጁ፣ ለአፈም ምርቃት ከረሜላዋን ተቀብዬ ወደ ሰፈር ተመለስኩ።

እማማ ረታሽ ቤት ልገባ ስል፣ እኛ ቤት ቁጭ ብለው ቡና እየጠጡ አዩኝና "ፉንጋይ፣ እዚህ ነኝ!" ብለው ጠሩኝ። የገዛ ሁትን የዘይት ብልቃጥ ተቀብለውኝ ከፍ አድርገው ዘይቷን እያዩ "ከየት ነው የገዛኸው? ከአረቡ ቤት ነው ወይስ ከሡልጣን ጋ?" ብለው የቅዱሳን ዓይኖቻቸውን ጎልጉለው አጉረጠረጡ።

በፍፁም እሳቸውን መዋሸት ስለማልችል፣ ደካማ በሆነች፣ ፍርሃት በተሞላባት ድምፅ "አዎን!" ስል፣

"አልመለስክልኝም እኮ! አንተ ምናምንቴ! የምርቃት ከረ ሜላ ለምደሃል ማለት ነው?" ብለው ሲያፈጡብኝ ሽንቴ ወጠረኝ።

ዳግመኛ የዘይት ብልቃጧን ከፍ አድርገው እገላብጠው እያዩ "አያችሁ እንዴት እንደሸቀበው? አሁን ይሄ የአራት ፍራንክ ዘይት ነው?! ገንዘብ መጫወቻ መስለሀ? በል ተንበርከክ!"

ተንበረከኩ። እኔ ስመጣ ተቋርጦ የነበረውን የደራ ወሬያቸ ውን ጀመሩ። እኔን እስከነመፈጠራም ረሱኝ።

"እሺ ገጠ፣ ምንድን ነበር ያልሽው?" አለ አባቴ፣ አርቡ ውስጥ ቁጭ ብሎ ድሩን እያፍቋታ።

"አንተ ወደል ዶርዜ! በአንተ አፍ ገጠ ልባል?" ጠየቁ እማማ በለሰ እየሳቁ።

"ኤዲያ! አንቺ ደግሞ፣ የቅድሙን ጨዋታ እንቋጨው እንጂ" ባለቤቷ አንድ ሳምንት ዝም ብሎ ቢተኛስ?" አሉ እማማ ረታሽ የዘይት ብልቃጣቸውን መሬት እያስቀመጡ።

እማማ በለሰ እየሳቁ "መቼስ ትዳር አይደል እችለዋ ለሁዋ! አለች ሴትዮዋ! አሉ።"

"ሁለተኛ ሳምንትም ባል ፀጥ ብሎ ቢያንኮራፋስ?" አሉ እማማ ረታሽ፣ ውብ ጠይም ገጽታቸው በፈገግታ ተሞልቶ።

"ስልጆቼ ስል እችለዋለኋ!" አለች፣ አሁንም እንደ መና ደድ እየቃጣት" አሉ እማማ በለጡ እየሳቁ።

"ሦስተኛ ሣምንትም ዝም ቢላትስ?"

"መጋዣ ነኝ እንዴ? እህል ብቻ እየበላሁ የምኖረው!? ወዳጅ እይዝበታለኋ! ብላ ቁግ አለች" ሲሉ እማማ በለጡ፣ ታዳሚው ሁሉ በሳቅ አውካካ።

እማዬ ቡና የጠጣችበትን ስኒ ባዶውን ለእማማ ወርቅነሽ ሰጠቻቸው። ወርቅነሽ ባለ ቀይ ሻሽ ጠይም ረጅም ሴትዮ ናቸው። ቡና ተጠጥቶ ካለቀ በኋላ እድምተኞቹ ስኒያቸውን ይለጧቸዋል። እሳቸውም የአተላውን አወራረድ በስኒው ላይ እያ ስተዋሉ መተንበይ ይችሉበታል። በዚህ ጊዜ ሁሉም በትኩረት ይከታተሏቸዋል። እሳቸው በሌሉ ጊዜ ትንበያቸው እንደሠራም እንዳልሠራም ትልልቅ ሰዎች ሲጨዋወቱ አዳምጫቸዋለሁ። አሁ ንም የእማዬን ስኒ አዩና "አንቺ ትፀንሻለሽ ሴትም ልጅ ትወል ጂያለሽ" አሏት።

አባቴም "እስኪ እንኪ ወርቅዬ፣ ሲኒው አስረጋዡንም ይና ገር ይሆን?" አለና ባዶ ሲኒውን ሲያቀብላቸው ቤተኛው እንደገና ሳቀ።

የተንበረከከብት መሬት ቆረቆረኝና ስንቀሳቀስ፣ ሚዛኔን ስቼ አጠገቤ ያለውን ሳፋ ስነካ ተንኳኳ። እማማ ረታሽ ወደእኔ ሲዞሩ ተፋጠጥን። ሳቃቸውን ዋጥ አድርገው ተከሳተሩ። "በል ተነስ! ሁለተኛ ከሠልጣን ሱቅ ትገዛና ወየውልህ! ለዛሬው ምሬ ሃለሁ።! ተነሳሁ። ከቤት ልወጣ ስል እማዬ አናቷን እየደባበሰች "ና ፉንጋይ፣ ሃደ በቀሉጋ ሔደህ..."

"ቅቤ!" ብዬ ሳላስበው በሽቄ በጣም ጮኽኩ።

"አንተ ወጠጤ! እከክከክ! ተጎረመሰ ማለት ነው?! በል ውጣና ልምጭ ይዘህልኝ ና!" አሉኝ እማማ ረታሽ። እየተነ ጫነጭኩ ስወጣ "ኧረ! ለመሆኑ ሰንት እንጀራ ብትበላ ነው እምዬን ቀና ብለህ የምታያት?!" ሲሉ ይሰማኛል።

አንዲት ቀጭን ልምጭ ይዤ ስገባ እማማ ረታሽ ዓይ ተውኝ ከትክት ብለው እየሳቁ "እንተ!? ይሄ ልጅ እንዴት ጠግቧል በቂርቆስ?! አሁን ይህች ለንቋሳ ምንህ ላይ ባሳርፍብህ ነው የምታምህ? በል ወፈር ያለውን መርጠህ አምጣ!"

አንዴ ቢያሳርፉብኝ ለዘለዓለሙ የሚሸኘኝን መቀርቀሪያ የሚያክል ቆመጥ ይዤ ገባሁ። እማማ ረታሽ ጭንቅላታቸውን ይዘው እየጮኹ "አንተን ገድዬ ከርቸሌ እንድማቅቅ ትፈልጋለህ እንዴ?" ብለው ሳቁብኝና "በል ለዛሬ ምሬሃለሁ። ሁለተኛ ስትላክ እምቢ ትልና ወየውልህ። በርበሬ እጥኜ ልከ አገባሃለሁ። በል ና! እግሬን ሳም! የእናትህንም ሳም!..." ያሉኝን እንዳደረኩ እርቀ ሰላም ወረደ።

"እንካ ለኔም የአራት ፍራንክ ሳሙና ግዛልኝ። መርፌም እስመርቅ፤ ልብ አርግ። አንቺም ስጪው" እሉና ስሙኒው ተሰጠኝ። ከመገረፍ በመዳኔ ደስ እያለኝ የተፏት ምራቅ ሳት ደርቅ ስመድረስ ወደ ሃደ በቀሉ መደብ በረርኩ።

እየሄድኩ አንድ ነገር ትውስ አለኝ። ባለ ሁለት ፍራንክ ሳሙና በዚያን ጊዜ ይሸጥ ነበር። በአራት ፍራንክ አንድ ሳሙና ገዝቼ መርፌ ከማስመረቅ፤ በአራቱ ፍራንክ ሁለት ሳሙና ብገዛ ሳቸው እንደሚሻል አሰብኩና ተመልሼ መጥቼ ለእማማ ረታሽ ነገርኳቸው። ጨዋታቸውን ቆም አድርገው በትኩረት ካደመጡኝ በኋላ "ጎሽ የእኔ ልባም! እንዲህ አስተዋይ እንድትሆን ነው የምፈ ልገው። ባለሁለት ፍራንኩን ሳሙና መግዛት ያልፈለኩት ለምን መሰለህ? ሽታው ደስ አይልም። ስለዚህ ብርርር ብለህ ያልኩህን ባለአራት ፍራንኩን ግዛልኝና ና!" አሉኝ።

በለመደ እግሬ ፈትለክ አልኩኝ።

ከጉልት ስመለስ ጎረቤቶቻችን ወደየቤታቸው ሄደዋል። እማዬ ብቻዋን ስኒዎቿን እያጣጠበች ነበር። አኩርፌ ቅቤዋን አጠገቧ መሬት ላይ ቁጭ አድርጌላት ልወጣ ስል "ፉንጋይ ና! ቁርስህን ልስጥህ!?"

ዝም አልኳትና ከቤት ሣሙናውን ላደርስ ወጣሁ።

"ምን ቸገረኝ "ለአኩራፊ ልጅ ምሳው ራቱ ነው" ስትል እሰማታለሁ።

ለምሳ ሳልመለስ ስጫወት ዋልኩ። መሸት እንዳለ ወደቤት ተመለስኩ። በቀዝቃዛ ውሃ ሳልፈራ እግሬን ታጠብኩ። አልጋዬ ላይ እንጣጥ ብዬ ወጣሁና ተንበርክኬ ልብሴን እወላለኩ።

"ራትህን ሳትበላ ልትተኛ?!" አለች እማዬ በመገረም።

ቁምጣዬን ሣጥኑ ላይ ጣልኩ። ሹራቤንም ደገምኩት። ብርድ ልብሱን ገልጬ ልተኛ ስል "ራትህንማ ሳትበላት እትተ ኛትም" አለች። ድምፅዋ የጭንቀት ነበር።

ዝም ብዬ ተከናነብኩ።

"ዋ! ረታሽን ነው የምጠራልህ!"

በፍጥነት ክንብንቤን ገለጥኩና አፈጠጥኩባት። በቆመች በት ቁልቁል እያየችኝ "ረታሽ!" ጮክ ብላ ተጣራች።

ዘልዬ ከአልጋዬ ወጣሁና "መጀመሪያ ቁርሴን ስጪኛ!" አልኳት። በንዴት እርር ድብን ብያለሁ። ረታሽን ስር በሰደደ ሁኔታ ጠላኋቸው።

እማዬ እየሳቀችብኝ ጋቢ ከሣጥኑ ላይ አንስታ አለበ ሰችኝ። ጓዳ ገብታ እንጀራውን በሳህን ላይ ቆልላ፣ ብዙ ወጥ አውጥታበት አመጣችልኝ።

"መጀመሪያ ቁርሴን ብዬሻለሁ?"

"ኤድያ! አትበሳበስብኝ! እኔ ቁርስ፣ ምሳ፣ ራት እያልኩ ስመድብ አልውልም። የቻልከውን ያህል ብላ!" አለችና ጠረጴዛው ላይ ሳህኑን አስቀመጠች። እንዝርቷን ይዛ ፈንጠር ብላ ተቀምጣ

ሰረቅ አርጋ ታየኛለች። እኔም እየተነጫነጭኩ ጠመ ልጓሜን መፍታት ጀመርኩ።

ሰኞ

"ልጆቻችንን ዓይናቸውን ገልጸው እንዲያልሙ እናስተምራቸው"
ስሙን የዘነጋሁት ጸሐፊ

በልጅነቴ ሰኞ በጣም የምጠላው ቀን ነበር። በአሁኑ የጉል ምስና ዕድሜዬ ላይ ሆኜ "ለምን?" ብዬ ራሴን ስጠይቀው አያሌ ምክንያቶች በሃሳቤ ይመጡብኛል።

ለተማሪ ቅዳሜና እሁድ የእረፍት ቀናት ቢሆኑም፤ ነገር ግን በውስጠ ታዋቂ የሥራ ቀናት ናቸው። ጀምሬ ያላጠናቀቅኩት ወይም ከነጭራሹ ያልሠራሁት የቤት ሥራ፣ ያልታጠበው የትምህርት ቤት የደንብ ልብስና ሸራ ጫማዬ፣ ያልተከረከመው ፀጉሬ፣ ያልተቆረጠው ጥፍሬ፣ በወጉ ሳይጠናቀቁ የእረፍት ቀናቱ ካለፉ ጭንቀት፣ መሸበርና በራስ አለመተማመን ያሳድሩብኛል።

እርብ ከስዓት በኋላ በትምህርት ቤታችን በድራማ፣ በመጻሕፍት ንባብ፣ በክርክርና በልዩ ልዩ ጥበባት የሚያዝናኑን መምህራኖቻችን ዕለቱን ፋሲካ ያደርጉልናል። ሰኞ ዕለት ግን እንደ ባለዛር ተቀይረው ሥነ ሥርዓት፣ ሞራልና ሕግ ይሆናሉ። ተግባራቸው ትእዛዝ መስጠትና ደንብን ማስፈጸም ብቻ ይሆናል።

እግዬን ከእንዲህ አይነቱ ሰጋት እንድትገላግለኝ በጊዜ ልብሴን እንድታጥብልኝ ከወዲሁ አስታውሳታለሁ። በበቆሎ ቆሮ ቆንዳ ሸራ ጫማዬን ፍትግ አድርጌ አጥባለሁ። እሁድ ማታ አካላቴን እታጠባለሁ። ጥፍሬንም አከረክማለሁ። ይሁን እንጂ ሁሌ አይሞላልኝም። የቤት ሥራዬን አልሠራሁም። በተጨማሪ ሰኞ ጠዋት የለዘዘውን ልብሴን ለብሼ ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ቅዝቃዜው ጥርሴን ማንገጫገጭ ይጀምረኛል። ቁርሴም ቅዝቃዜውን የሚያብሰው ይሆናል። የዚያን ዕለት ፀሐይም ዘግይታ የምትወጣ ይመስለኛል።

ወደ ትምህርት ቤት ስሔድ ታቦት እንደተሸከመ ቄስ አረማመዴ አዝጋሚ ይሆናል። የቤት ሥራ ሠርቶ የመጣ የክፍሌ ልጅ ካጋጠመኝ ለምኜው በፍጥነት ስገለብጥ የልብሴን ቅዝቃዜም እረሳለሁ። በወሩ መጀመሪያ ላይ ከሆነ "ቲቸር ጥበበ የወር ደሞዝ አምጡ" ብለዋል ስል አባቴ ገንዘብ ከሌለው አስቀድሜ ባለመናገሬ እየተቆጣ የዚያን ዕለት እንድቀር ያዘኛል። በዚህ ጊዜ

'እልል በቅምጤ' እልና ደስታዬን ዋጥ አድርጌ ዕለቱን በነፃነት ሰጫወት እውላለሁ። ይሁን እንጂ ይህ ብልሃቴ ብዙ ጊዜ ይክሸፋል። ቤተሰቦቼ የትምህርት ቤቱን ደንብ አለምረው ስለሚ ያውቁት ቀደም ብለው የደንቡን አድርሰው "እኔ ትናንት መንገድ ላይ ቲቸር ጥበበን አግኝቼአቸው የወር ደሞዛቸውን ከፍያቸዋለሁ። ካርኒውን አስታውሰህ አጽፊህ ና!" አባቴ ሲለኝ እጪዬ ዱብ ይልና በልቤ እያነባሁ የዔሊ ጉዞዬን እያያዘዋለሁ።

ተዘጋጅተው የመጡት ተማሪዎች በዕለቱ ተርብ ሆነው ይታያሉ። ተዝናንተው ይጨዋወታሉ። አንዳንዶቹ ያወጋሉ፣ ይክራከራሉ፣ ቁመታቸውን ይለካካሉ። ዓለሙ ሰማይ ልብሱን እንዳያቆሽሽበት አየተጠነቀቀ በክራ ይጫወታል። (ዓይኖቹ ሰማያዊ ስለሆኑ ነው፤ ዓለሙ ሰማይ የምንለው) መክዬ ቀጫጫው በሰባራ ምላጭ ጥፍሯን ትከረክማለች። ሻቃ የገነፈለ እስክርቢቶውን የተበጣጠሰ ቀለም እንዲሰባሰብ ከቀፎው አውጥቶ ይንጠዋል። በቅጥር ግቢው ጥጋጥግ ፀጉሩን የሚደመድመው፣ የተጨማደደ ልብሱን እየላበ የሚዘረጋጋው ይስተዋላል።

ሁለት ሰዓት ላይ ደወል ይደወላል። በየክፍላችን እንሰለፋለን። ከእኛ ፊት ለፊት፣ ከፍ ባለ ቦታ ላይ የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር ቲቸር ጥበበ ይቆማሉ። ሌሎቹ መምህራኖች በእኛና በርዕሰ መምህራችን መካከል ባለ ክፍት ቦታ ላይ ፊታቸውን ወደእኛ መልሰው በመደዳ በአሳርፍ ይቆማሉ። ሁሉም በአለባበሳቸው ንፁህ ናቸው፣ ጫማዎቻቸው ያንፀባርቃሉ፣ ፀጉራቸውን ተከርክመዋል፣ ጢማቸውን ተላጭተዋል።

በእኛና በመምህራኖቻችን መካከል ቆሞ የሚያዝን ተማሪ አዝገመጋሚ በሆነ ድምፅ "ሰልፈኛ!" ሲል ነቃ እንላለን። በድጋሚ "ሰልፈኛ! ተጠንቀቅ" ብሎ ያዘናል። መምህራኑም ሆኑ ደቀ መዛሙርቱ በተጠንቀቅ እንቆማለን።

"ከንዳ!"

ከፊታችን ባለው የክፍል ጓደኛችን ትከሻ ላይ ቀኝ እጃችንን በመዘርጋት እንከነዳለን። ከፊታችን የቆሙት የክፍል አለቆቻችን የሰልፉ መስመር ሳይጣመም ቀጥ ብሎ መዘርጋቱን በጭን ቅላታችን ውሃ ልክነት ያስተካክላሉ። መስመር ያዛነፈውን ተማሪ ሰም እየጠሩ እንዲስተካከል ያዙታል።

አለቆቹ በቃልና በድርጊት የሚሳተፉበትን ሥራ እንዳጠና ቀቁ ፊታቸውን አዙረው በተጠንቀቅ ይቆማሉ። ይሄኔ ያ የባታ ሊዮን አዛዥ "አውርድ!" ይላል። ቀኝ እጃችንን ከጓደኛችን ትከሻ ላይ እናወርድና በአሳርፍ እንቆማለን።

በዚህ ወቅት ሁለት የተመረጡ የሰድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሰልፈኛው መካከል ወጥተው በወታደራዊ አረማመድ ወደ ርዕሰ መምህራችን ቢሮ ይገባሉ።

"ሰልፈኛ ተጠንቀቅ!" ይላል አዛዦችን።

የእግሮች ገጥመው መቆም ድምፅ ይሰማል። ከቲቸር ጥበበ ቢሮ ተማሪዎቹ ሲመጡ አንደኛው ሰንደቅ አላማችንን በክንዱ ላይ ታቅፎ፣ ወደ ፊት ይራመዳል። ሌላኛው እየመራው ምሰሶው አጠገብ እንደደረሱ አንደኛው ተማሪ ባንዲራዋን በጥን ቃቄ ነጥሎ በትከሻው ላይ ያኖራል። የባንዲራዋን ሁለት ጫፍ ከመስቀያው ሲባጎ ጋር በመተጋገዝ ያሥሩታል። ከዚያ በኋላ ዕለቱ የተባረከ እንዲሆን "አባታችን ሆይ" እንፀልያለን።

"አሜን!" ብለን እንዳሳረግን፣

"ተጠንቀቅ!" የሚለው የአዛዣችን አዝጣምጋሚ ድምፅ ያስተጋባል።

"አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት!" ሲል፣ በድጋሚ ያዘናል።

ደሙን ያፈሰሰ፣ ልቡ የነደደ
በአርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ
ንጉሡን አገሩን ክብሩን የወደደ
ነፃነቱን ይዘ መልካም ተራመደ።
ሰንደቅ ዓላማችን ክብራችን ውዴቱ
ያኮራሻል ንጉሠ ነገሥቱ!...

አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራችን በምሰሶው ላይ በዝግታ ሽቅብ ትሔዳለች። ሁላችንም በዓይናችን እስከ ጫፍ እንከተላ ታለን። ለምን እንደሆነ ሳላውቅ አንዳች ንዝረት በሠራ አካላቴ ተሞ እንባዬ ይመጣል።

አዛዣችን "አሳርፍ!" ሲል አሳረፍን። ባንዲራዋን የሰቀሉት ተማሪዎች ሲባጉውን ምሰሶው ላይ አስረው እንደጨረሱ እንደ አወጣጣቸው ወደ ተነሱበት ሰልፍ ተቀላቀሉ።

የሣምንቱን ዜና ያጠናቀረው ተማሪ ከሰልፈኛው መካከል ወጥቶ ሪፖርት ወደሚያደርግበት መድረክ ሄደ። ጋዜጠኞችን ገላዬ ቱባ በዛፍ ፍሬ ከስልነት የተተኮሰ ሰሪያን ኮቴን ከቦላሌ ጋር ለብሷል። የተወለወለ ጫማ አድርጎ በቄንጠኛና በራስ መተ ማመን ስሜት ተራምዶ መድረኩ ላይ ወጣ። ከኪሱ አጣጥፎ ያስቀመጣትን ወረቀት አወጣና እየዘረጋጋ ርዕሰ ዜናውን ማንበብ ጀመረ። ለደንቡ ያህል ወረቀት ያዘ እንጂ የዜናዎቹን ዝርዝር በቃሉ የሚያውቀው ይመስላል። የዘመኑ ኮከብ ጋዜጠኛ የአሳምነው ገብረወልድ ተፅዕኖ ባለበት ስልት መዝለቅ ጀመረ።

"እንደምን አደራችሁ። ዜና እናሰማለን። ዜናውን የማነብ ላችሁ ተማሪ ገላዬ ቱማ ነኝ..." ብሎ ምንም አይነት መሸበርና መር በትበት ሳይታይበት ኮራ ባለ አንደበት "ሚማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በታላቁ ቤተመንግሥት የአሜሪካንን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ሔነሪ ኪሰንጀርን ተቀብለው አነጋገሩ።...

"ታዋቂው የማራቶን ጀግና ሻምበል አበበ ቢቂላ በእንግሊዝ አገር በተደረገው የማራቶን ውድድር አሸንፎ የወርቅ መዳሊያ ተሸላሚ ሆነ..." በማለት ርዕሰ ዜናዎቹን ካሰማን በኋላ ወደ ዝርዝር ጉዳዮቹ ይዘን ዘለቀ።

ገላዬ አገር አቀፍና ዓለምአቀፍ ዜናዎችን ብቻ አልነበረም የሚያበስረን። እንደ አስፈላጊነቱ አልፎ አልፎ የሚገጥሙት የት ምህርት ቤታችንን ዜናዎች በማከል በቅርብ መረጃ ትኩረታች ንን የመሳብ የራሱ የሆነ ስልት ነበረው። ትምህርት ቤታችን ከጥበበ ዝቢያ፣ ከፈለገ ዮርዳኖስ፣ ወይም ከጎብረ ብሔር ትም ህርት ቤቶች ጋር ያደረገው የስፖርት ውድድርን እንደ ስለሞን ተሰማ እየተቸ ይዘግባል። ዘገባው በአጨዋወታቸው ጥሩ እንቅ ስቃሴ ያደረጉትን ሲያሰደስት፣ በደካማነታቸው የሚያፍሩትን ቅር ያሰኛቸው ነበር። በጨዋታው ላይ ያልተገኙት ደግሞ ዘገባውን ሙሉ በሙሉ ይወዱለታል።

ዜናዎቹ በሽንት ቤት አጠቃቀም፣ በክፍላችን ንፅህና በመ ጠጥ ውሃ ብክነት ላይ ሁሉ ያተኩራል። እንደ አስፈላጊነቱ ትም ህርት ቤቱ በወር ያወጣውን ወጪ ከደረሰኝ ላይ ተመልክቶ ስለ ሚዘግብ የርዕሰ ጉዳዩን ክብደት ያሳየናል።

አንዳንዴም ገላዬ በግሉ ሲያነብ ያጋጠመውን ለየት ያለ የአገራችንን ታሪክ በማንበብ ያስገርመን ነበር። አንድ ጊዜ 'ከታሪክ ማኅደር' አሰና ብዙዎቻችን ሕይወታችንን ሙሉ የማን ረሳውን ታሪክ አነበበልን።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በክረ ምቱ በዘነበው ኃይለኛ ዝናብ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባት ሀገረ እንግሊዝ የገንዘብ ዕርዳታ ላኩ። ይህም ዕርዳታ በሌጋሲዮኑ በኩል ቀጥሎ ካለው ደብዳቤ ጋር ተልኳል።

ለክቡር ሜዩሪከናቪናልዲስትሬስ
ሉንዶን፣

...ሁልጊዜ በምናሰባት ለምለምና ወብ በሆነች አገርዎ ላይ ለደረሰው ጥፋት መጠነኛ የገንዘብ ዕርዳታ መጠየቅዎን ስለሰማን፣ የገንዘቡ ቁጥር ምንም ከፍ ያለ ባይሆንም፣ የኛንና የሕዝባችንን ወዳ ጅነት ስመግለጽ ያህል አንድ ሺ ፓውንድ በሌጋሲዮናችን በኩል ልከ ንልዎታል።

ብርሃንና ሰላም መጽሔት
1946 ዓ.ም

ገላዬ እንደ አንድ ብቁ ጋዜጠኛ ዜናውን ሙሉ ለማድረግ ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ የአነባበብ ስልቱ ታላቅ ጉልበቱ ነበር። በዚህም ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል። እኔም ስድስተኛ ክፍል ስደርስ የትምህርት ቤታችን ጋዜጠኛ የመሆን ታላቅ ምኞት አደረብኝ።

ገላዬ አዝናኝና አስተማሪ ዜናዎቹን አንብቦ እንዳጠናቀቀ ለአስጨናቂው የንፅህና ፍተሻ አብሮን ይሆናል። መምህሮቻችን በተመደቡበት ክፍል በቅደም ተከተል የንፅህና ፍተሻ ይጀምራሉ። መምህራኖቻችን ሁሉም ነጭ ማህረብ በእጃቸው ይይዛሉ። የመጀመሪያው ተፈታሽ አስቃችን ነው። መምህራችን ፊቱ መጥተው ሲቆሙ አንድ እርምጃ ወደፊት በመራመድ 360 ዲግሪ ዞረው እንዲፈትሹት ትርፍ ቦታ ይተውላቸዋል።

መምህሩም ጠቅላላ ንፅህናውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በጥንቃቄ እየቃኙት በመሀረባቸው ማጅራቱን አሸት ያደር ጉታል። ከዚያም መሀረባቸውን ያስተውላሉ። ፀጉሩን እንደ አስፈላጊነቱ እየዳበሱ "እጅህን ዘርጋ!" ካሉ እስካሁን ባዩት ረክተዋል ማለት ነው። አለቃችንም ጥፍሮቹን ያሳያቸዋል። በወጉ ካልተከረከሙ ነገር ተበላሸ ማለት ነው። በአንደኛ ደረጃ ስሙን በጥፋተኞች ማስታወሻ ላይ እንዲጽፍ ይታዘዛል።

የፈለገንን ያህል ብንዘጋጅም መሸበርና መርበትበታችን የማይቀር ነው። ከፊት ስፈቴ አበረ ሻቃ ቀጥ ብሎ ቆሞ ለእኔ ብቻ በሚሰማ ለሆሳስ ድምፅ "ተስፍሽ፣ ፀጉሬ ከጓላዬ አድጓል?"

"ትንሽ!" ስል መለስኩ በጥንቃቄ።

"ወይኔ! ይሄ ገብጋባ ፀጉር አስተካካይ ስሙኒዬን በልቶ እንዲህ ይከረክመኛል? ሊያስገርፈኝ!! አባቴ ይሙት ትናንትና እኮ ነው የተከረከምኩት" ይለኛል፣ እኔ ምሕረት የማወርድለት ይመስል።

ከጓላዬ ዓለሙ ሰማይ አባቱ አስጠብበው ያሰፉለትን የወታደር የደንብ ልብስ ቁልቁል እያስተዋለ "አልተተኮሰም እንጂ ንፁህ ነው" ሲለኝ በፈጣን ስልት ዞሬ አለባበሱን አይቼ ወደ እሱ ጋደል ብዬ "የተተኮሰ ይመስላል።"

"ማታ እጥፍጥፍ አድርጌው መደቤ ላይ አስተካክዬ አንጥፌው ከላይ ካሊም አለበስኩትና በጥንቃቄ ተኝቼበት አደርኩ።"

አስተዋይነቱ አስገረመኝ። ይህች አጋጣሚ አንድ አሪፍ እውቀት የገበየሁባት ዕለት ሆነች። ነፍስ አውቄ የራሴ ካውያ እስከሚኖረኝ ጊዜ ድረስ በዓለሙ ጥበብ ለአያሌ ዓመታት ልብሴ ላይ እየተጋደምኩ አተኩስ ነበር።

"ዓሊሽ፣ እናቴ ትሙት አሪፍ ነሽ!" አልኩት በፍጥነት ዞሬ እያየሁት። ሰማያዊ ዓይኖቹ ተስለመለሙ። ይሁን እንጂ አሁንም ፍርሃት ይታይበታል። "ወይኔ ሽንቴ መጣ!" አለኝ በዝግታ።

መምህራችን ፍተሻቸውን እያቀላጠፉ እኛ አካባቢ ተቃርበዋል። በጣም ያደገ ፀጉር ሲያጋጥማቸው "አፍሮ የቅማል ማሰሮ!" ይሉና በመቀስ ይመደምዱታል። ተማሪውም እንደ ጅብራ ተገትሮ ፀጥ ብሎ የመጣለትን ምድመዳ በፀጋ ይቀበላል። ማንገራገር የሚባል ባህል በደማችን ውስጥ የለም። መምህራኖቻችን የሚያደርጉት ሁሉ ለእኛ የሚበጅ መሆኑን አሳምረን

ስለምናውቅ እርምጃቸውን ሁሉ የምንቀበለው እንደ ቅዱስ መጻሕፍት ቃል ነው።

ልጃገረዶቹ ብዙዎቹ ንቁዎች ቢሆኑም የታወቁ ዝርክርኮችም ነበሩ። ኑኑሽ አገር ሰላም ብላ ያሠረችውን ሻሽ ለመደበቅ ስትጣጣር ይደረስባታል። ሸዋፀሐይ ትንሽዋ ጥፍርዋ ላይ የተቀባችውን ቀለም ለማስለቀቅ ትፈቀፍቃለች። ከቤቷ ስትነሳ የተጨማደደውን ቀሚስ ለብሳ የመጣችው አለምነሽ የጓደኞቿን ንፅህና አይታ በፍርሃት ተጨንቃ እየሳበች ትዘረጋጋለች። ዘምዘም ንፁህና የተተኮሰ ዩኒፎርሟን ለብሳ፣ አናቷን የተከናነበችውን ሂጃብ እንደ ረግን አንገቷ ላይ ሸብ አድርጋ በኩራት ቆማለች።

ሲሳይ ጎቢጥ በዓለሙ ሰማይ ላይ ተንጠራርቶ ጎሸመኝ። ዞሬ ሳየው ከአጥሩ ውጪ አመለከተኝ። ሴምላልና ቀጢሳው ከአጥሩ ውጪ ቆመው በመደነቅ አፍጠው ይመለከቱናል። ሁለቱም ትምህርት አይማሩም። ቀናሁባቸው። በቆመብት በምልክት ያወሩን ጀመር።

"ቆሼ ለቀማ መሄዳችን ነው" አለን ቀጢሳው።

ሴምላል ንፍጡን ሽቅብ ሳብ አደረገና ጭቅቅታም አካላቱን ፎከቶ ደሀና ሁኑ እያለን በድንገት አንድ ቦታ ላይ አፍጠቀረ። የቀጢሳውም ብልጣብልጥ ዓይኖች ተከተሰው አፈጠጡ። ረጃጅም ቅልጥሞቹ እንደማፈግፈግ የኋሊት ተሰበቀ። ሊወረወር ነው።

ወደ አፈጠጡበት ቦታ ስመለከት የቲቸር ጥበበ ዓይኖች እፍጠውባቸዋል። አንድ እግራቸው አንካሳ ነው። በደሀናው እግራቸው እየተወረወሩ ብቅ ጥልቅ እያሉ እኔና ሲሳይ ጎቢጥ አካባቢ በጥቂት እርምጃ ደረሱና "ማነው ከአሁኖቹ ዱርዬ ልጆች ጋር ሲጠቃቀስ የነበረው?"

ዓለሙ ሰማይ ተርበተበተ። ሁሌም ሳያጠፋ፣ ከጥፋተኛ ጎን በመገኘቱ ብቻ ይሸበራል።

ሁሴን ጂቦ "የእነሱ ሰፈር ልጆች ናቸው" አላቸው ሳይጠይቁት። የትምህርት ቤታችን ጉልኪፐር ነው። ቦማያገባውም ነገር ይወረወራል።

"ማነው?" አሉ በአስገምጋሚ ድምፅ ደገሙና ቲቸር ጥበበ።

ፀጥ አልን።

"ብታርፉ ይሻላል!" ብለውን ወደነቀጢሳው አካባቢ ቢመለከቱ ድራሻቸው ጠፍቷል።

ፈታኙን ቀን ሰኞን እንዲህ አሰፍነው። ወደ ክፍል ገባን። ቲቸር እስኪመጡ አለቃችን ስም መጥራት ጀመረ። ብዙዎቻችን ተራ ቁጥራችንን የስማችንን ያህል ስለስመድነው "15!" ሲል፣

"የስ ሰር!" አልኩ።

የቤት ሥራ ያልሠሩ ልጆች ይህችን አጭር ጊዜ በፍጥነት ይጠቀሙባታል። አንዳንድ ቅን ልጆች በማንበብ አለ በለዛም በራሳቸው ፈጣን አጻጻፍ ይገለብጡላቸዋል። ጥቂቶቹ እንደ ወላጅ "ቅዳሜና አሁድ የት ነበርክ?" ብለው ይቆጣሉ። በዚህ አይነት ጥድፊያና ንትርክ መካከል መምህራችን ቲቸር አባብያ ይገባሉ። ጫጫታው ረጭ ይላል።

ሁላችንም እንነሳለን።

"ጉድ ሞርኒንግ ስቱደንትስ!"

"ጉድ ሞርኒንግ ቲቸር!"

"ሲት ዳውን!" ይሉና እንዲ ወደ እኛ እንዲ ወደ ጥቁር ሰሌዳው ይመለከታሉ። "ባለፈው ሳምንት የቤት ሥራ ሰጥቻች ኣለሁ?!" ሲሉ የክፍላችንን ጎበዝ ተማሪ እያዩ ይጠይቃሉ።

"እንዲ?! የቤት ሥራ ተሰጥቶን ነበር እንዲ?!" ሲል መኩዬ ቀጫጫው የክፍሉ ተማሪ ሁሉ በሳቅ ያውካካል። በእንዲህ አይ ነቱ ክስተት የሰኞ ጭፍግ ዕለት ዓይናችንን ገልጠን እንድናልም በሚያደርግ ትዕይንት ይጀምራል...

አይነጥላዎቻችን

እንቡሼ ገላ የአብሽ ገለባ
ሜዳ ነው ብዬ ገደል ልገባ
ገደል ገብቼ ልወጣ ሰል
ድቡ መጣብኝ ከቁጤ ሰር
ከቁጤ ሥር....!

ታዳጊ ልጃገረዶች እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደ እንዝርት ይሾራሉ። የከበብናቸው ሕፃናት በማጨብጨብ ጨዋታውን እናደ ምቃሰን። ልጃገረዶቹ ቡፍ ብሎ በአየር በሚነፋው ቀሚሳቸው እርቃኑን በሚሆነው ጭናቸው ስርሲኒማ ሰማየት ውሮና ሲሳይ ጎቢጥ እየሳቁ መሬት አድፍጠው ሽቅብ አፍጠዋል።

ጉብሎቹ በጨዋታው ተመስጠው፤ በእግራቸው አፈራውን እያቦነኑ፤ በመንፈሳቸው ሰማየ ሰማያት ገብተዋል። አንዷ ሌላዋን ፈገግ ብለው እያስተዋሉ፤ አልያም ዓይኖቻቸውን ገርበብ አድ ርገው በአለ በሌለ ኃይላቸው ሁሉ ይሽከረከራሉ።

"ወይኔ! ሲኒማ በነፃ!" አለና ሲሳይ ጎቢጥ በጉንጩ መሬት ነክቶ ሽቅብ እያስተዋለ ጮኸ።

"አምን በናትህ እኔም አየሁት!" አለና ውሮም ጮኸ።

"ኧረ እኔኮ ቡታንቲ አድርጌያለሁ! ባለጌ!" አለች ብርቱካን ድንገት ጨዋታውን አቁማ።

"ያንቺንም የብርሃኔንም አይተንባችኋል። ኃይለሥላሴ ይሙት! አይቼባችኋለሁ!" አለ ጎቢጥ። "ውሮ አላየህም?"

"በደንብ አይቻለሁ" ሲል ውሮ፣ ብርቱካን ፊቷን በእጅዋ ከልላ ማልቀስ ጀመረች።

በዚህ ወቅት እማማ ረታሽ ከቤታቸው ብቅ አሉ። ቱግ ብሰው "እዚህ እየተበላቀጣችሁ ብቅሌ ላይ አቧራ ታቦናላችሁ? ምናምንቴ ሁላ! ጥፉ ከዚህ!" ብሰው ገሰጡን። ጨዋታው ፈረሰ፣ ሕፃናቱም ተበታተንን።

"እቃዬ ገላ! እቃዬ ገላ!" አለች ጩኔ በአየር ስትንሳፈፍ አይታት፣ እየተከተለቻት። የኛም ትኩረት ወደዚህች ተወዳጅ በራሪ ዞረ።

"እንች መንቃራ ምንቅርቅር! አትመናቀሪብኝ! ቶሎ ወደ ቤት!" አሉና እማማ ረታሽ ጮኹባት፣ መፍካት የጀመረችው አበባ ከሰመች። ሮጣ ወደ ቤቷ ገባች።

"ሁላችሁም ወደየቤታችሁ!" እኛ ላይም ጮኹ።

"እንቺ ሴት ልጅ እንዲህ ነው የሚቀመጠው? እግርሽን ሰብሰብ! ኧረ አፍሽንም ገርበብ አርጊ! አ! ብላ እኮ ነው ወሬ የም ታየው፣ ወሬ በአፍ ይገባ ይመስል፣ ደሞ ዓይኗን እንዴት እንዲት ነው የምታቅለበልበው?!..." እማማ ረታሽ ሴት ጓደኞ ቻችን ላይ የሚወርዱባቸው ግለጣዎች ናቸው።

ገና ከማለዳው በሴት ልጆች ላይ ቁጥጥሩ በጣም ይጠ ብቃል። ነፃነት የሚኖራቸው በየቤታቸው ጓዳ ብቻ ነው። በአደ ባባይ ማንንም ቀና ብሰው እንዳያዩ ተደርገው ነው የሚቀረፁት፣ ስለዚህ አሁን ወንዶቹ ወደ ሌላ ጨዋታ ስንሄድ ሴቶቹ አብሮ አደጎቻችን ወደየቤታቸው ቱር...ቱር ብሰው ገቡ።

አንዷ ደፈር ብላ ገሳጭዋን "ታዲያ የት እንጫወት?" ብላ ብትጠይቅ፣

"እከክክ! ለዚህም ተበቃ? የእከሌ ልጅ መልስ ሰጠችኝ እኮ! ኧረ ሰምች ጉድ በሉ! ምን አለ ኧናቷ ብታ ስገርማት?!"

በዘመኑ የተጣሉብን አያሌ ግርዶሾች እንደ ጥላችን ይከ ተሉን ነበር። የፊጠራ ሃሳቦች በምናባችን ቢመጡም በአበሻዊው ወግ አጥባቂነት ብዙዎቹ ከጅምሩ ጫጭተው ከውስጣችን እንዲ ጠፉ ይደረግ ነበር። ትውስ እንደሚለኝ በቆርኪ ቁማር ተጫ ውተንም ሆነ፣ ከየቡና ቤቱ ደጅ ለቅመን ሲጠራቀም፣ የጀበና ማስቀመጫ የሚሆን ማቶት ብዙዎቻችን ለቤተሰባችን ሠርተናል። ይህም በዋዛ የሚከወን አልነበረም።

"አንተ እጅህን እንዳትቀጠቅጠው።"

"ኧረ ሚስማሩ እጅህን ይወጋሃል።"

የማቶቱ በረክት የደረሳቸው የአንዳችን እናት "እትዬ፣ ይተ ዋቸው ማቶት እየሠሩ ነው" ሲሉዋቸው ተቆጭዋ መለስ ይላሉ።

በእንዲህ መልኩ ግርዶሻችንን እየጣስን ራሳችንን ለመሆን ዘመኑ እስካለፈ ድረስ ጥረናል። ዱላውንም እርግማኑንም እየቻ ልንና በልጅ ልብ እየረሳን።

እኔ ወደ ኃይሉ ዶሮ ቤት አካባቢ መሔድ አዘወትር ነበር። ውሮ፣ ሻቃ፣ እና ቀጢሳውም ይመጣሉ። ኃይሉ ዶሮ የሥዕል ዝንባሌ ነበረው። ሲፈልግ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጎጆ ቤት መሣል ይችላል። እሱ እያሳየን እኛም ለመሥራት እንሞክር ነበር። እኔ የሚለጠኝ የቃል ትምህርት ከተግባር ጋር ታግዞ ሲገለጽልኝ በቀላሉ ይገባኛል። ሥዕሉን መሣል ስጀምር ግን ጠረ ጴዛው ሦስት አግር ይኖረውና አራተኛውን የምስልበት ቦታ ይጠ በኛል። ወንበሩም በትክክል የቆመ አይሆንም። ኃይሉ ካስተማ ረኝ በአሁኑ ዕድሜዬም በውስጤ የቀረው አሳማኝና ጎጆ ቤትን መሳል ብቻ ነው።

ኃይሉ ዶሮም ጓደኞችን ብቻ ሳይሆን ትእግስት ያለው የሥዕል መምህራችንም ነበር። የራሱን ደብተር እየቀደደና እየሰ ጠን እንድንሥል ደጋግሞ ያሳየናል። እኛም ደስ እያለን እንሞክ ራለን። ለራሱም የተሻለ መክራ የሚያደርግበት የሥዕል መማሪያ መጽሐፍ ነበረችው። አባቱ አባባ ቱሉ ናቸው የገዙለት። ኃይሉ ዶሮ እያሳየን በተመስጠ እንሥላለን። አንድ ቀን እንዲህ በመማግር ላይ እያለን እናቱ እማማ ሸጊቱ ወደቤት ሲገቡ በግዙፉ አካላቸው በሩ ላይ ቆመው ብርሃኑን ከለሉንና "ጉድ! ጉድ! ታያላችሁ እነዚህ ውጫጮች የሚሠሩትን። ለካ እንዲህ እየተሞነጫጨረበት ነው ደብተሩ በላምንት በላምንት አስቀ የሚባ ለው! ግርማ ዝም ብለህ ታያለህ?" ብለው ለዶሮ ታላቅ ወንድም ቀኝ እጃቸውን ሰጡት።

ሁሌም ጉዳዩን ሳያጣራ እርምጃ በመውሰድ ፈጣን የሆነው ጎረምሳው ግርማ ቱሉ የሥዕል መማሪያ መጽሐፉን ነጥቆን፣ በሰባ ተኛ ክፍል እንግሊዘኛው ሙልጭ አድርጎ እየሰደበን፣ በካልቾ እየለጋ ከቤት አስወጣን።

በሥዕል ጥበብ ዓይነጥላችንን የመግፈፍ ጥረቱም እዚህ ላይ ቆመ። የዶሮ ችሎታም ክፍ ሳይል ቀረ።

"ከዛሬ ጀምሮ በደብተራችሁ ላይ ትሞነጫጭሩና ነፍሰ-ሥጋችሁን እለያየዋለሁ!"እያሉእማማ ሸጊቱም አይነ ጥላ ሆኑብን።

'ልጅ አባቱን ይበልጣል' ይባላል። በዚያን ወቅት በጥበብ ረቂቅ ምስጢር በመንፈስ ከታላላቆቹ ኢትዮጵያውያን ሠዓሊዎች አገኘሁ እንግዳ፣ አሰፈለገ ሰላም፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ እና ከሌሎችም ጋር በምናባችን እያወጋን እንደሆን ማን ያውቃል 'የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፣ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ'

ይበሉን እንጂ ያበሰልነውን ጥሬ በሚያደርጉብን አዋቂ ሰዎች ላይ ሳናቁም ወደ ሌላ አይነት ጨዋታ እንሰማራለን።

የክረምት ወቅት ይመስለኛል። ዘንቦ እንዳባራ በደመና ግላጭ ፀሐይ ብቅ አለች። ትንሽ ቆይታ በፀሐይዋ ብርሃን ውስጥ ካፈያ ጀመረ። "ውይ ልጆች ይሔኔ እኮ ጅብ ወልዳለች" አለ ጉቢጥ አንጋጦ እያየ።

"ክርስትና ለእኔ" አለ ቀጢሳው።

በጣም ሳቅን።

ዝናብ እንጭባራ ጭቃ እያቦካን መጫወት ጀመርን። ጨዋ ታው በቆይታ እንደ ምርጫችን ይቀየራል። ቅርፃ ቅርፅ መሥ ራት ጀመርን ጠረጴዛ፣ ጀበና፣ ስኒ፣ ጎጆ ቤት፣ ሰው። ሁላች ንም በየራሳችን ፈጠራ ተመስጠናል። በዚህ መካከል ውሮ "የሠራ ሁትን ሰው እዩ" አለና ቀልባችንን ሳበው።

በአጠገባችን አልፋ የምትሄደው መዓዛ ሥራችንን አይታ "የውሮ ሰው ከሁላችሁም ይበልጣል። ሽንት መሽኛ ግን የለውም" አለች።

"እሱንማ በጣም ትልቅ ሠርቼ አሳያሻለሁ" ብሎ ውሮ ጭቃ አነሳና በትልቁ ማድበልበሉን ጀመረ። አንድ ቀን የሠራ ችኝ ተንኮል አሁን ትውስ አለኝ። እምቢ እንዲላት በጥቅሻ ስነግረው አየችኝና በኩርኩም ቆጋችኝ! እኔም እየጮኽኩ "ምን አደረኩሽ? ተይ አንቺ ልጅ! በናትሽ! በጉልበትሽ አምላክ!" እያ ልኩ ሳለቅስ አባባ አጋፋሪ ሰሙን።

አባባ አጋፋሪ አንድ ዓይና ናቸው። ለአንድ ዓይናቸው ሲሉ ዓለምን ሁሉ ይፈራሉ። መዓዛ ስለመታችኝ ይቆጧታል ብዬ ስጠብቅ፣ አሳቸው ግን ራሳቸው ጥቃት እንደደረሰባቸው ሁሉ "ጉድ! ጉድ! እንዲያው የት ብንሄድ ነው በሰላም የምንኖረው?" ሲሉ ጠየቁ። ግር አለን። የባሰ ምን ተፈጠረ? በሚል ስሜት መጮኼን አቆምኩ።

በአጠገባችን ሲያልፉ የነበሩት አባባ ተሰማ ተገርመው "ምን ተፈጠረ፣ አጋፋሪ?" አሉ።

"እነዚህ ልጆች አንድ የሚላቸው አጡኮ፣ የጎንት አባት። አታዩም? ይሄ የሚያድበለብሉት እኮ ሰው ለመምታት ነው። የሰው ዓይን ቢያፈሱስ?"

"አጋፋሪ፣ ያንተ ዓይን ሁሌንም የሚያሳይህ አድቦልቡሉ ነው? ልጆቹ ለራሳቸው መጫወቻ ዕቃ እየሠሩ ቢጫወቱ ምን አለበት?" አሉ እማማ በለሙ ገጠ። ጫጫታውን በርቀት ሆነው እየተከታተሉ ነበር።

"ወቸው ጉድ! አንቺ ገጣጣ፣ ሰድበሽ ለሰዳቢ ስጭኛ! ይሄ ድብልብል አይደለም?!" ብለው በዚያችው አንድ ዓይናቸው አባባ አጋፋሪ አፈጠጡ።

ግንንም የማይፈሩት እማማ በለሙ ፈገግታ ከፊታቸው ሳይጠፋ "ተው! ተው! አጋፋሪ። 'አንድ ዓይና ባፈር አይጫወ

ትም' ሆኖብህ እንጂ እነሱ ማንም ላይ ሊወረውሩት አይደለም የሚያድበለብሉት። እንዲህ የምትሰጋ ከሆነ ወትሮውንም እግርህን ሰብስብ አታረግም?" አሉዋቸው።

"እንች ግማሟ! ምን ሳደርግ ነው ዓይኔ የጠፋው?"

"ስትሄድ ነዋ... የማላውቅ መስለህ አንት ሴት አውል!" ተቆጡ።

"እረ! በሕግ ይቺን ሴት ያዙልኝ። ስሜን እያጠፋችው ነው።"

"ምን ስም አለህና? እንደ ወንዶች ኮንጎ ወይስ ኮሪያ ዘምተህ ነው የታወርከው? ንብሩኝ ባይ!"

"ልብ አርጉልኝ!"

"ምን ነካሽ ገዐ!" አለ አባቴ።

"አጋፋሪ! ልጅ አልይ አለ!፣ መድረሻ አሳጣቸው።"

"ልብ አርጉልኝ! ያንቺ ልጆች እዚህ ውስጥ አሉ?"

"ባይኖሩስ? እነዚህም ልጆቼ ናቸው!"

ንትርኩ ከሮ በሰፈርተኛው ሃይ! ሃይ! ባይነት በረደ። ጉዳዩ ሲጣራ የፀቡ ምክንያት በእኛ ላይ አነጣጠረ። "እረ እኛ ልንማታበት አይደለም..." ብለው ኃይሉ ዶሮ ስለጨዋታው ሲያስረዳ "ዝም ብል አንት ቀጣሪ አንተስ አታሸንፈኝም!" ብለው አባባ አጋፋሪ በክህደት ቂጡን ዠሰጡት።

የውሮ እናት እማማ ወርቅሃሃ "አሁንስ አንተ ልጅ፣ ምን ባደርግህ ይሻላል?" ብለው ውሮን ጆሮውን ስቀም አድርገው ጭኑ ስር እጃቸውን ሰደው በቁንጥጫ እየመዘለጉት፣ እየጎተቱ ወደ ቤታቸው ይዘውት ሄዱ።

ትንሽ ትልቁ ቢኃስጠን የጥፋተኝነት ሰሜት ተሰማን። የሠራነውን ቅርፃ ቅርፅ ከልባችንም ውስጥ ደፈጠጥነው። አሁን ማን ያውቃል? በሥነ- ጥበብ ሠረገላ ከአክሱምና ከላሊበላ ቀራፅያን ጋር በምናብ ተገናኝተን እንደሁ? ወይም ድንበር በማይገድበው፣ ፅንፍ አልባ በሆነው የሰው ልጆች ምናብ ተንሳፈን ከነሚካኤል አንጀሎና ክሊዮናርዶ ዳቪንቺ ጋር በመንፈስ ተገናኝተን እንጠበብ እንደሆነስ?

የእኔንና የአብሮ አደጎቼን የልጅነት ጊዜ ሳሰላስል አያሌ ርዕሰ ጉዳዮች ትውስ ይሉኛል። አንዳንዴ ትልልቅ ሰዎች ነሽጥ አድርጓቸው ክእኛ ጋር መጫዋወት ይፈልጉና፣ የተለያዩ ጥያቄ ዎችን ይጠይቁናል። ከነዚህም መካከል በይበልጥ ትውስ የሚለኝ "ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ?" ሲሉኝ የምመልሰው አልነበረኝም። እንደሚመስለኝ "ስታድግ" ሲሉኝ ማደጌን አላምንም ነበር። በዚያን ወቅት እኔም ልጅ፣ ወላጆቼም ሕይወታቸውን በሙሉ እናትና አባቴ ሆነው እንደሚኖሩ ነበር የማምነው።

አሁን ሳየው እምነቴ ትክክል ነበር። ስምን? ማኅበረሰብ በሂይማኖቱ፣ በሥነልቡና፣ በባህሉና በወጉ እሰረኛ ሆኖ ልጆቹን በጥበብ፣ በፈጠራ ነፃ ሆነው እንዲያድጉ አይፈቅድም። የማሰብ ነፃነቱ የተጋረደ ነው። ከዚህም የተነሳ ምናቡ ነፃ ያልሆነው ልጅ መንፈሱ ጫጭቶ ዝንባሌው ወይም ተሰጥኦው ምን እንደሆነም ሳያውቅ ያድጋል። ማኅበረሰባችን በግርዶሽ የልጅ ዓይነጥላ ሆኖ ሳለ "ሲያድግ እንዲህ ይሆናል..." ብሎ መጠበቁ ከንቱ ሕልም ነው። ባዶ ራዕይ ነው።

ልጅ ራዕይ እንዲኖረውና ዓይኑን ገልፆ እንዲያልም ነፃ ሆኖ ማደግ ይኖርበታል። ልጅ ለአደጋ እንዳይጋለጥ መጠበቅ፣ እሳት እንዳይፈጀው መከላከል፣ ክፉና ደጉን እንዲለይ በወዳጅነት ቀርቦ ማዋየት ሲገባቸው ሁሉም የኅብረተሰቡ አካሎች በጠላት የተወረረ መንደር ውስጥ እንዳለ ወታደር ልጅን ማስጨነቅ ይቀላቸዋል። ጠይቆ ከመረዳት በፊት መቅጣት፣ በትንሽ በትልቁ እየገሰጡ በራስ የመተማመን ሰሜቱን መናድ ባዘል አድርገውት እንደነበር መናገር እወዳለሁ።

ከሺ አንድ የሆኑ እንደ እማማ በለጠ ገጠ አይነት ወላጆች ግን የወደፊቱ ፈጣሪዎች ጋሻ ሆነው ሲመክቱ ላይ ኅይደግስ አይጣላም' እንድል ያደርገኛል።

ፀሐይዋ በእኛ ጨዋታ መፍረስ ያኮረፈች ይመስል በደመና ተጋረደች። ሰማይ አጉተመተመ። ብዙም ሳይቆይ አህያ የማይ ችለው ዝናብ ይዘንብ ጀመረ። ሁላችንም ወደ የቤታችን ተበታ ተንን። እናቴ ጉልት ሄዳለች። አባቴም ሠርቶ የቆረጠውን ሸማ ሊያደርስ ወደ ደንበኞቹ ሄዷል። ቤታችን ሰለተቆለፈ የክርስትና አባቴ ቤት በረንዳ ላይ ተጠለልኩ። ውሻዬ ቲቲ መጥታ እላዬ ላይ ለመጠምጠም እየሞከረች ትልሰኝ ጀመር።

በዚያን ወቅት አንድ ሕፃን "እናቴን ዝናብ እንዳይ መታት!" ብሎ ጆሮውን ጥርቅም አድርጎ ከያዘ እናቱ ከገናቡ መደብደብ ያድናታል ብለን እናምን ነበር። እኔም የዝናቡን አወራረድ እያየሁ፣

"እማይይይዬ
ቶሎ ነይልኝ!
ወተቱን ባህያ!
ዳቦውን በጉያ..." እያልኩ መዘመር ጀመርኩ።

አብሮኝ የነበረው ቀጪሳው "ፉንጌ፣ እናትህ ጉልት ናቸው? ዝናብ እንዳይመታቸው ከፈለክ ጆሮህን ክድን ክፍት አታድ ርገው። በደንብ ጫን ብለህ ያዘው። ክድን ክፍት ካደረክ እናት ሀን ዝናብ አልፎ አልፎ ይመታቸዋል።"

ሺ... እያለ የሚወርደውን ዝናብ ለመስማት ጆሮዬን ደጋ ግሜ ክድን ክፍት አደርግ ነበር። እማዬን ዝናብ ምንም እን ዳይመታት ጆሮዬን ጥርቅም አድርጌ ያዝኩ።

ከረዢም ቆይታ በኋላ ዝናቡ አባራ። እናቴም አባቴም ከሄዱበት መጡ። እማዬን በደንብ ዞሬ እየኋትና "ዝናብ መታሽ?"

"ለምን ጠየከኝ?" አለች እንጀራ ልትሸጥበት ገበያ ይዛ የሄደችውን እንቅብ ጓዳ እያስቀመጠች።

"አልመታሽም አይደለ?" ጠየቅኩ።

"አዎን አልመታኝም!"

ደስ አለኝ። ዝናቡ ለምን እንዳልመታት ምስጢሩን ነገር ኳት። ፈገግ ብላ በብልሀ ዓይኖችዋ ልብ ብላ እያስተዋለችኝ "ጎሽ የኔ አሳቢ! ሁልቀን ዝናብ ሲመጣ ቶሎ ብለህ ተጠለልና ባለሁበት ዝናብ እንዳይመታኝ ጆሮህን ጥርቅም አርገህ ይዘህ ጠብቀኝ" አለችና ገዝታ ያመጣችልኝን አንባሻ ግማሹን ቆርሳ ሰጠችኝ። የአዋቂነት ስሜት እየተሰማኝ ተቀብዬአት መግመጥ ጀመርኩ። ለውሻዬም ትንሽ ሰጠኋት። እየበላሁ ከውጪ ልጆች ሲንጫጩ ሰማሁ። ልወጣ ስል "እህል ይዘህ?" አለችኝ እማዬ። በቤተሰባችን ልማድ የተሰጠኝን ምግብ በልቼ ካልጨረስኩ ከቤት ይዞ መውጣት ክልክል ነበር። በፍጥነት ጨረገድኩት። ውሃ ከአንሰራ ውስጥ ቀድቼ ጠጣሁና በጥድፊያ ወጣሁ።

በንቢጥ አመራር ሰጪነት ልጆች በጭቃ ቦዩ ላይ ግድብ እየሠሩ ነበር። ተቀላቀልኳቸው። ግድቡ በጎርፍ ሞልቶ እንዳይ ፈርስ ውሮ በጣቱ በስቶት በቅጠል አሸንዳ ሠራለት። በእንዲህ አይነት የጨዋታ ወቅት ሁሉም ነገር የሚካሄደው በጥድፊያ ነው። ግድቡ ተሠርቶ ተጠናቀቀ።

የወረቀት መርከብ ሠራን። በየራሳችን ላይ ልዩ ምልክት አድርገን መርከቦቻችንን ማወዳደር ጀመርን። በእንዲህ አይነት ጨዋታ መውደቅ መነሳት ያለ ነው። በውሃ ውስጥ መንቦጫረቁ አይቀሬ ነው። ጭቃ በጭቃም እንሆናለን። አንዳንዶቻችን በዚህ ጊዜ በጣም በስብሰን ውሃ ውስጥ የገባች አይጥ እንመስላለን። ቅዝቃዜው አንጀታችን ውስጥ ገብቶ ቢያንሰፈሰፈንም፣ ጥርሳ ችንን እያንጫገጭን ስሜታችን ሳይቀዘቅዝ እንውዳደራለን።

በተለይ የወረቀት መርከባችን ከቀደመችልን የረገጥንበትን ሳናውቅ እየተከተልናት፣ እያፏጨንና እየጮኽን እናበረታታለን። ትሰማን ይመስል ደስታችን ወሰን አልባ ይሆናል። የአሸናፊነት ስሜታችን ያይላል። ለልጅ፣ ውስጣዊው ደስታ እንጂ ውጫዊ ውብቱ አያስጨንቀውም። ወደ ውጪ በማየት የበለፀጉት ትላልቅ ሰዎች ግን ወደ ውስጥ የሚያዩን ዓይናችንን በቁንጥጫና በኩር ኩም አሳውረው ወደ ደጅ የማየት ሕመማቸውን ያጋቡብናል። በግድም በውድም እንለምደውና ስናድግ የእነሱው ግልባጭ እንሆናለን።

በእንዲህ አይነት አፀብ ድንቅ ደስታ ላይ እያለሁ ጆሮዬ ለቀም ተደርጎ ተይዞ በቁንጥጫ ሲለመዘገ ደነገጥኩ። ዞሬ ሳይ እናቴ ነች "እንተ ቀኪያም! ማታ እንደ ዶኪ ስትንፈቀፈቅ ቁጭ

አድርገህ ታሳድረኛለህ! አሁን ግን ባንተ ቤት መርከበኛ ሆነሃል። ድንቄም መርከበኛ! በል ግባ!" አለችና ጆሮዬን ለቃ በኩርኩም ጭንቅላቴን ቆጋችኝ።

"ወይኔ ቁስሌን! ወይኔ ቁስሌን!" እያልኩ እናቴን እየዳበ ስኩኝ ሮጬ ቤት ገባሁ።

"ዝም በል! ጋሼ! ኮንጎ ወይስ ኮርያ ዘምተህ ነው የቆሰል ከው?!" አለና አባቴ ተቆጣኝ። ትንፋሼን ዋጥ አደረኩኝ።

ጓደኞቼም በፍጥነት ተበታትነዋል። ግድቡም ፈረሰ። ጎር ፉም ፏ! ብሎ አካባቢውን አጥለቀለቀው። ይህም አዋቂዎቹ ከሚ ጋርዱብን ከዓይነ ጥላዎቻችን አንዱ ገጽታ ነበር። ማን ያው ቃል? በጥበብ ፈጣን ጀልባ ቀዝፈን ከኖህ መርከብ ምስጢር ሕይወት ሹክ ብላንስ እንደሆን? ወይም ከካሌብ፣ ከቫስኮ ደጋማ፣ ከማርኮ ፖሎ... እኩል ለመቅዘፍ የሚያበቃንን አውቀት በጨቅ ላው ሕይወታችን ጀምረን እንደነበር?

በዚያ ትናንት እንደተከወነ ሁሉ ዛሬ ቁልጭ ብሎ በሚ ታየኝ የሕይወቴ ምዕራፍ እንዲህ አይነት ጥፋት አጥፍቼ ሰያዝ የምመከረው ምክር "ለምን አርፈህ አትቀመጥም? አታየውም የመምሬ በቀለን ልጅ አርፎ ቁጭ ብሎ ደብተሩን ነው የሚያ ጠናው! ለምን አንተም ደብተርህን አታጠናም! "እባላለሁ።

ዝም ብዬ ለመቀመጥ ስሞክር ደግሞ "ምን የሚያስተክዝ ነገር ተፈጠረ? ጋሼ አይዞህ ልጆችህ እንደሆን በዕድላቸው ያድ ጋሉ" ብሎ አባቴ ቁዘማዬን ያግዳል።

በኋለኛው ሕይወቴ እንደተገነዘብኩት በማኅበረሰባችን ውስጥ ተከዝ ብሎ ማውጠንጠንና ማብሰልሰልም የተከለከለ ነው። ጎጂ ሐሳብን ከማውጠንጠን አኳያ ስለሚገነዘቡት ነው። በዚህ ስልት ውጫዊው ገዝር ውስጣዊ ዓይናችን ታውሮ እናድጋለን። ይሁን እንጂ ጥቂት፣ በጣም ጥቂት ዕድለኞች ይህንን አይነጥላ ገፍፈን በመውጣት ዝንባሌያችንን እንከተላለን። በዚህ ወቅት ያ በልማዳዊው እምነት ተተብትቦ ድሮው ላይ የቆመ የማኅበረሰብ ክፍል በመደነቅ "ከየት አመጣችው? ከወዴት ተማረው..." በማለት ሲያወጋ አጀብ ሲል ይደመጣል። እኛ ሕፃናት እያንዳንዱ ልጅ እንደ ተሰጥኦው ቢለያይም የራሱ ፀጋ እንዳለው ማሳየት የጀመ ርነው ገና ከማለዳው ነበር። ነገር ግን ጠልቆ የሚያስተውለን ዓይንና ልብ ማኅበረሰቡ ውስጥ አልነበረም።

በልጅነቴ ደጋግሞ ሲወራ ሰምቼ ውስጤ ታትሞ የቀረ የኅብረተሰብ እምነት አለ። ወላጆች ስለልጆቻቸው በኩራት ሲናገሩ ሴቷን "ምንም አታውቅም! ጨዋ አንገተ ሰባራ ልጅ ነች፣ በአፍዋም ጨው አይሟሟ!" ወንዱን "ማንንም ቀና ብሎ የማያይ ትሁት ሽቁጥቁጥ ልጅ ነው። አሁንማ አደገ።"

ከረምቱ አልተገባደደም። ፀሐይ አልፎ አልፎ ብቅ ብት ልም ቆይታ በደመና ትረታለች። እንቅስቃሴውም ግርዶሹም

እንደቀጠለ ነው። ነፋሱ ዝግ ብሎ ይነፍሳል፣ ደመናው መበተን ጀመረ። አንጋጠ ሲያይ የነበረው ኃይሉ ዶሮ "ልጆች እዩ!" አለና ደመናው ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርፅ እየሠራ ነበር። ተፈጥሮ የምትጠ በበውን እያየን እንጠቋቆማለን።

"ዘንዶውን አያችሁት ልጆች!" አለ ሲሳይ ጎቢጥ፣ ቅርፁን በእጁ እያመለከተን።

ዘንዶው እየተሳበ ሲሄድ ይታየናል። የጉሙ ባዘቶ ተገምሶ ሲታይ "ወይኔ አፉን ከፈተ!" ብሎ ውሮ ጮኸ። "ተመልከቱ እንጂ፣ ምላሱን አወጣ!"

በቆይታ አናቷን የተከናነበች የሴት መልክ ተከሰተ፣ ልብ ብለን ስንመለከተው የእምዬ ማርያምን ምስል መሰለ። ልጇን ታቅፋዋለች። በአናታቸው ላይ ቀስተ ደመና ከአፅናፍ አፅናፍ ተሰመረ። በመደነቅ ጩኸታችን በኃይል ጨመረ።

ተፈጥሮ ስትሥል እኛ እያስተዋልን ስንተነትን ጥቂት ቆየን። "አትሄዱም ከዚህ?! የምን መአት ነው የምትጠሩት!" አሉ የተረፈ ገልጆ አባት ልጃቸውን በጥፊ ጭው አድርገውበት። "ሂዱ ከዚህ! ምን ያሚርታሉ?" ብለው ገሰጡን፣ ጠጅ ጠጥተው ሞቅ ብሏቸዋል።

ተበታተንን።

በኋላ እንደተገነዘብኩት አዋቂዎች ዓይነተላዎቻችን መሆና ቸውን እነሱም የሚያውቁት አይመስለኝም። በእነሱ ቤት የተ ቀጣ፣ ሥርዓትን አሳምሮ የሚያውቅ ትውልድ እያላደጉ ነው። ይህን ምንም ሳያዘጋጁለት በዕድሉ የሚያድግ ትውልድ፣ በበኋ ለኛው ዘመኔ ከልባቸው "ተተኪውና አገር ተረካቢው ትውልድ!" ሲሉትም ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ።

በደመናው የሥዕል ጥበብ ተገርመን ሳናበቃ "አንበጣ ና ቡና ጠጣ!" የሚል ጩኸት ሰማን። ቂም በማይዘው ልባችን ቁጣውን ሁሉ ረስተን ወደ አንበጣው አደን ሄድን። አደኑ የልጅን አካል የሚፈትን እንቅስቃሴ አለበት። መዝለል፣ መሮጥ መያዝ፣ ማስተዋል... ኮትን እንደመረብ ተጠቅሞ ማፈን።

አንበጣዋ ሜዳ ለሜዳ የምታሯሩጠንን ያህል፣ መንደሩ ውስጥ ትጥለች። ጎቢጥ አንዷን እንበጣ ሲያሳድድ ከእማማ አስሚቱ በር ጋር ተጋጨ። እማማ አለሚቱ ትልልቅ ሰዎች እንጎሏ ነው የሚሏቸው። ሰላም ናቸው ሲሏቸው ያኮርፋሉ፣ አኩርፈዋል ሲሏቸው ይሰቃሉ። በዚህ ነው ቅፅል ስም የወጣላቸው።

ጎቢጥ በርግጎ የእማማ አስሚቱን በር እያየ «እንዴ ሞቱ እንዴ ለምንድነው ከቤት ወጥተው ያልረገሙን?» ሲል ጠየቀ።

«ሞተች!» ሳህሉ መቃ ደንግጦ የክርስትና እናቱን ደህንነት ጠየ ቀን። እርግጠኛ ለመሆን በበሩ ቀዳዳ ለማየት ሞከረ። ምንም

እይታይም። በመስኩት ሲያጮልቅ በኑሮ ልብስ የተጠቀለለ የእማማ አለሚቱ እካል አልጋ ላይ ተዘርሯል። የጓዳው መብራት በርቷል።

«እዎ ሞታለች እናቴ። በሯን ሳትከፍተው ሦስት ቀን እንደሆነ እንማዬ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። ወይኔ እናቴ!!» አለና መቃ ጨኸቱን አቀለጠው።

የሞት ወሬ ክንፍ አለው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ወሬው መንደሩን አዳረሰው። ጆሮዋን የሚያማት አለምነሽ ጆሮም ደርሶ «ወይኔ እናቴ ደጓ እጉራሼ!» እያለች ጩኸትዋን አስነካችው። መንደሩ በለቅሶ ተደበላለቀ።

ሽማግሌዎች የሚያለቅሱትን ዝም ለማሰኘት እየሞከሩ፣ በሩን ለመክፈት ተጣጣሩ። በሩ ጥርቅም ተደርጉ ተዘግቷል። የመስኩቱን መቀርቀሪያ ሲሞክሩ በቀላሉ ተከፈተ። የእማማ አለሚቱ ሬሳ አልጋቸው ላይ ተዘርሮ ታየን። ጨኸቱ እንደገና ተባባሰ። እዚያም እዚህም ዋይታ ሆነ።

መቃ በመስኩት ዘሎ ገብቶ በሩን ከፈተው። ለው ግር ብሎ ሲገባ ሲል እማማ አመለወርቅ «ነበዘ 'ግርግር ለሌባ ያመቻል' የሴትየዋ ንብረት እንዳይባክን ሁላችንም ወደ ቤት ውስጥ እንግባም። እንድ ለው ገብቶ መሞታቸውን ያረጋግጣል። ከዚያ ተዘጋጅተን ማልቀስ እንጀምራለን።»

እማማ አመለወርቅ ወደ ውስጥ ገቡተው ጓዳ አልጋ ላይ የተዘረረውን የእማማ አለሚቱን አስከሬን ዳሰሱት። ከው ብለው ሲደነግጡ ይታዩናል። «ኧረ ዝም በሉ አላረቆም እካላቸው ሙቅ ነው።» ብለው አብስረውን «እትዬ! አንቱ እትዬ አለሚቱ!» እያሉ ተጣሩ።

ይህን ጊዜ የዕድራችን ዳኛ አባባ አርአያ፣ እባ ዘለቀ፣ ደርሰዋል። አባባ ገብሬ ጡሩምባውን ለመንፋት አቆብቁበዋል። አባባ አርአያ «እንዳትነፋ!» እሷቸው የአባባ ገብሬን ሁኔታ አይተው።

«ኧረ አሉ!» አሉ እማማ እመለወርቅ በጣም ደንግጠው።

ተዘርግቶ የሚታየው የእማማ አለሚቱ እስከሬን ተንቀሳቀሰ። ሁላችንም ተደናገጥን። እንደተጠቀለሉ ቀና አሉ። የተጠቀለሉበትን ነጭ ጨርቅ ፈቱት። በመስኩትም በበርም ተጨናንቀን እፍጥጠን እናያቸዋለን።

«ለምን እንዲህ አደረጉ እትዬ?» ጠየቁ እማማ አመለወርቅ።

«ብሞት ማን እንደሚጄልቅስልኝና እንደማያለቅስልኝ ለማወቅ ነው።»

«ድንቅ ምርምር ነው። አበሻ ከሳቁ ይልቅ ለቅሶውን ነው የሚወድ፣ ታዲያ እንደጀመሩት ለቅሶውን ባይነፍጉት ጥሩ ነበር» አለ ግርማ ቢጨ ተንጠራርቶ እያያቸው።

«ምን ማለትህ ነው ግርማ?» አባባ አርአያ ኮስተር ብለው ጠየቁት።

«እዚህ የመጣሁት ለራሴ ለቅሶቅ ብዬ ስማልቀስ ነው። ከምለቅበት ይልቅ የማለቅስበት ዕልፍ ነው። ለቅሶዬን ግን እማማ አለሚቱ ነጠቁኝ። ልብ አሳላችሁም ይሆናል እንጂ አለምነሽ

የምታለቅሰው ለራሷ ነበር:: አጉራሼ አይደለም ስትል የነበረው?» አለ ግርማ::

«በስመአብ በል ልጂ» አሉ አባ ዘለቀ በጣም ተከዘው::

«በስመአብ አልልም አባቴ! እመት አለሚቱ ከሕይወታቸው ይልቅ ሞታቸው ነው ዕርባና ያለው:: ሩቅ ሳይሔዱ ከነዚህ ልጆች ነጥቀው ጠረጴዛቸው ስር የሰበሰቡት የጨርቅ ኳስ መሳት እዩት:: ይህን እንደ ጥፋ ጠረጴዛቸው ላይ ያስቀመጡትን የላስቲክ ኳስ ለልጆቹ የወረወረላቸው አንድ ፈረንጅ ነው:: ፈረንጁንም ይዤው እዚህ ስፈር የመጣሁት እኔ ነኝ:: ይሔ ቱሪስት ይሔን 'ጌቶ' ሰፈራችንን ሊጉበኝ ሲመጣ ሕፃናቱ መጫወቻ እንደሌላቸው አይቶ ኳስ ይዞ ስለነበር እንዲጫወቱባት ቢወረውርላቸው እላቸው አጅ ገብታ እንደ ቅርስ ተሞሽራ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጣለች» አለ ግርማ በኃይለ ቃል::

«ኡ..ሁ..ሁ.. አመድ በዱቄት ይስቃል?» አሉ እማማ ዓለሚቱ እንደ እስክስታ ወራጅ እንገታቸውን እየሰበቁ::

«ማነው አመድ እኔ የፈታውራሪ በላቸው ልጅ?» ሲል ግርማ አቅራራ::

«ማነው አባትህትን ፈትአውራሪ ያደረጋቸው? ስማቸውስ በላቸው ነው?» መስሱ እማማ ዓለሚቱ::

ነገሩ በጣም ተባባሰ:: ሽማግሌዎች ነገር ስማብረድ ሃይ ሃይ ማለት ጀመሩ:: ግርማ የመነታረክ ስሜቱን ላያበርድ ወደ እኛ ዞር አለና «ፋስት ያራዳ ልጅ በዚህ ጊዜ ነው ኳሷን የሚቦክመው» ብሎ እባንኖን ወደ እማማ አለሚቱ እፍጠ «አስቲ አባቶቻችንን እንቆጣ ጠር? እያቴ ደጃዝማች ድንበሩ ዘለቀ የእጤ ምኒልክ የወርቅ ልምጭ አቅራቢ ነበሩ::»

ሰዉ ሳቅ በሳቅ ሆነ:: ግርማ እብሮ እየሳቀ «አባቴም በቤተ መንግሥት ባለሟልነቱ ለጃንሆይ ሰሚኒስትሩና ሰመኳንንቱ መቅጫ የወርቅ ልምጭ አቅራቢ ነበር:: የእርሰስ ባስቤት አሥር አለቃ ናቸው ሃምሳ አለቃ?!...» ብሎ ግርማ ቀልዱን ወደ ዘሰፋ ስለቀየረው እማማ አለሚቱ ተቆጥተው «እንተ በሙት ባሰቤት ታላግጣለህ?!» ብለው እግራቸው ስር ያለውን ዘነዘና አፈፍ አድርገው ወደ በሩ ተንደረደሩ:: ግርማም እንደምርጥ ሥልጡን ቦክሰኛ መክቶ የኋላ አፈገፈገ:: ሽማ ሚሌዎቹ እማማ አለሚቱን ያዟቸው:: በዚህ ጊዜ መኩዬ ቀጫጫው ቀልጥፋ ቤቱ ውስጥ ገብታ ውብዋን ኳስ መንትፋ ተሰወረች:: ግርማ ኳሷን መቦጫጭቅን ካየ በኋላ ነገር እንዲበርድ በተረጋጋ ስሜት መናገር ጀመረ:: እማማ አለሚቱም ይቅርታ እንዲያደርጉለት እግራቸው ላይ ወደቀ:: ግርማ እንዲህ ባለውለታችንም ቢሆን ጠጁን ጥግብ ብሎ አያቅራራ ሲመጣ ካገኘነው እንለክፈዋለን::

አማማ አለሚቱ ከሞት ተነሱ ተበሉ ወሬው መንደሩን አዳረሰው:: ቤተኛው ወደ ውስጥ ገብቶ ያዕናናቸው ጀመር:: ጨዋታው ተጀመረ ቡናውም ተፈላ:: እማማ አለሚቱ ግን ያስቀስላቸውን እያመሰገኑ ያላስቀስላቸውን እየወቀሱ ነበር::

ሌላ ጊዜ አላንዶ ለመጫወት ስፋ ያለ ባለአራት ማዕዘን ወረቀት በረጃጅም የሣር አውታር እንሠራለን:: ክበስተኋላው ላይ እንደ ጭራ የተቀጣጠለ ወረቀት እንቀጥልበታለን:: አውታሩ መሃል ላይ ረጅም ክር ይታሰርና በነፋሻማ ወቅት በአየር ላይ ቀስ በቀስ ሲለቁት ወደ ሰማይ ሲውለበለብ ስናየው በጣም ማራኪ ነበር:: አላንዶው አልፎ አልፎ ዝቅ ብለው ከሚበሩ አሞራዎች ጋር የሚጋጭ ይመስላል:: አንዳንድ ጊዜ ግን የንፋስ ግፊት በማጣት ወደ ምድር ይወርድና በኤሌክትሪክ ገመድ ላይ ይጠ መጠማል:: በዚህ ወቅት የሚደርስብን ስድብና እርግማን አይነሳ!!

"ምናምንቴዎች ኮረንቲው ኮንታክት አድርጉ ጋንጪር ደማችሁን ምጥጥ ቢያደርገው ጉዳችሁ በፈላ ነበር!! ምን አለ እነ ዚህን ልጆች አርፈው እንዲቀመጡ አንድ የሚላቸው ቢኖር?"

ወላጆቻችን ይህንን ጨዋታ የጃፓን ሕፃናት ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት ይጫወቱት እንደነበር አውቀው ቢሆን ኖሮ እንኳ ግድ አይኖራቸውም ነበር:: በአንደኛው ጆሮአቸው ሰም ተው በሌላኛው አፍሰውት አርፈን ተቀምጠን አለማሰብን አንድን ማር ሁልጊዜም በትጋት ያስገድዱናል::

በዚያን ወቅት በሰፈራችንም ሆነ በትምህርት ቤታችን ውስጥ የስልክ አገልግሎት አልጀመረም:: እኛ ግን ሁለት የክ ብሪት ፓኮዎችን የሚያገናኝ ረጅም ክር አስረን ስልክ ሠርተን ማዶ ለማዶ ሆነን እናወራለን::

"ሃሎ! በዱምቡሉህ ፓስቲ ገዝተን ብንበላበት ምን አለ በት?" አለችኝ መኩዬ ቀጫጫ ከማዶ ቆማ ፋናስ ድፏን እያሳ የችኝ::

"ኧረ? እኝ በይ!"

"ዶሮ ብታልም ጥሬዋን:: እናንት ምናምንቴዎች! ምን ድነው የምትባባሉት?"ጠየቁ እማማ ሸጊቱ እማድቤት ሥራ እየሠሩ::

"ምን መስለሽ እማዬ?" አለ ኃይሉ ዶሮ::

"ሂድ! ፈሳም! ስምጀችኋለሁ:: ደሀና ነገር አታወሩም? ድጋሚ ይህንን የዱርዬ ሥራችሁን ካንሾካሾካችሁ ክራችሁን ብጥ ስጥሱን አውጥቼ ነው የማባርራችሁ"

ምን እናውራ? ተፋጠጥን:: አንድ ሃሳብ መጣልኝ "ሃሎ! ኳስ ጨዋታ እንሂድ?"

"እናንተ ልጆች፣ ዙረት ልትሄዱ? ዛሬ ብታርፉ ይሻ ላችኋል!"

"እናጥና?" አለችኝ መኩዬ::

"እሄሄ!! ይሄማ ቢሆንላችሁ ወግ ነበር:: ማን ያውደል ድል? ማን ያንፏቅቅ? ፎቃቃ ሁሉ!" አልለቀቁንም እማማ

ሸጊቱ። ትንሽዬዋን ሣይንሣዊ ምርምራችንን በሳንሱር መቀሳቸው እየቆራረጡ እዚያ ላይ አመከኑብን።

የልጅ አእምሮ ንፁህ ነው። ይሁን እንጂ ቤተሰቦቻችንና ማኅበረሰባችን በየበኩላቸው በባሕርያችን ላይ የራሳቸውን ከንቱነት አያነፁብን ሰብዕናችን መጉደፍ የጀመረው በዚያው በጨቅላነታ ችን ጊዜ ነበር።

የአንዳችን አናት የወሬ ሱሰኛ ይሆናል። ጎረቤትም አሳፈ አግዳሚም በክፉ ያነሳኛል ብለው ሁሌም እንደ ጠረጠሩ ነው። ስለዚህ ልጃቸውን ይጠሩትና "በል ና ቀስ ብለህ የምትጫወት መስለህ እነ እገሊት ምን እንደሚሉ ስማና ና!" ብለው ይልኩታል። ሰብቀኝነት ገና ከማለዳው በእንዲህ መልኩ በሰብዕ ናው ላይ ተዘርቶ ያድጋል።

"አፈር ያስበላችሁ! የአናንተ እጅ በሶ ጨብጧል? ሳትፈ ነክተው የመጣህ እንደሆነ እዚህች ቤት እንጀራ እትቀምሳትም። ሞቼ ነው ቆሜ እንዳንተ አይነቱን አጋሰስ የምቀልበው" የተባሉ በዚያው በጨቅላነት ዕድሜ የሂትለር መንፈስ ይጠናወታቸውና እንደ ነብር ደም የጠማቸው ሆነው ወደ ገሃዱ ዓለም ይቀላ ቀላሉ።

የአንዳንድ ወላጆቻችንን ቅድስና ሳስብ ግን የኅብረተሰባች ንንም አስተዋይነት አዘሀጋ ማንሳቱ ግድ ነው። አንድ ያልተለ መደ ወሬ ሳንጠየቅ መተርተር ስንጀምር አፋችን በጥፊ ይጮ ላል። "ሁለተኛ እንዲህ አይነት ወሬ ታመጡና ወየውላችሁ ዕጣኑ ቂርቆስ አይለመነኝ በርበሬ አዋጄ ነው ፈሳችሁን የማስጨር ሳችሁ። ገና ብቅ ከማለት የምን ወሬ ነው?!" ሲሉን፣ በዕለቱ ያስ ደንግጠን እንጂ ከዓመታት በኋላ ስናስተውለው ታላቅ ፍስሐ የሆነ፣ ዓይነጥላችንን የገፈፈ ፀጋ ኖሯል።

አስተዋይነት ብቻ ሳይሆን ፍቅርም የሚዘራብን ጊዜ ነበር። "ና የኔ ፉንጋ አደኑ አደደል እንዴ? ይሄ ደግሞ ማነው? አቤት ጊዜ እንዴት ይሮጣል!? ይሄ እውነት ውሮ ነው? አሁን ስሙን ማን አላችሁት? አዎን ገነነ ሸጋ ስም ነው። ና ሳመኛ" ይባልና በፍቅር የምንዋኝበት፣ አብረን የምናወጋበት ሁኔታ ይፈጠራል።

"እስኪ ሬዲዮኑን ክፈቱት። ፉንጋይ፣ ና ደንስልኝ" እባላ ለሁ። "ተስፋዬ ነው ስሙ? እውነትም ተስፋዬ።"

መደነስ እጀምራለሁ።

እንዳለመታደል ሆኖ ሬዲዮኑ ዜና ማውራት ይጀምራል። *"እንደምን ዋላችሁ? ዜናውን የማሰማችሁ ታደሰ ሙሉነህ ነኝ"*

"ቆይ ጥላሁን ገሠሠ መዝፈን ሲጀምር ነው የምትደንስ ልኝ። ቁም አሁን ወሬውን ይጨርሳል። አይ ባሎቴ፣ ይሄ ቂልሽ ወሬና ዘፈንም አይለይ?"

ሬዲዮኑ ርዕሰ ዜናዎችን ማተት ጀመረ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሜክሲኮ የሚያደርጉትን ይፋ ጉብኝት መጀመራቸ ውን ሮይተርስ የዜና ወኪል ገለጸ።"

ትልልቆቹ ሰዎች እስከ መፈጠራችን ረሱን። ወሬያቸው ሁሉ ስለ አባባ ጃንሆይ ሆነ። ሬዲዮኑ ዜናዎችን እንደጨረሰ፣ ሞቅ ያለ ሙዚቃ ጀመረ። በቆምኩበት መውረግረግ ጀመርኩ። ውሮ አብሮኝ ይደንስ ጀመረ። የአዋቂዎቹ ትኩረት ወደ እኛ ዞረ።

የእኔና ውሮ አካል ገና መጋጋል ሲጀምር መኩዬ ቀጫ ጫው ልቀላቀል ልተው በምትልበት የማመንታት ስሜት ውስጥ እንዳለች ከሙዚቃው በላይ እንድ ድምፅ ጎላና "የጥሩ ዕቃ ሥም ፊሊፕስ!" ብሎ ደመደመ።

"ይሄ ዘፈን እኮ አይደለም። ቆዩ..." አሉ በፍቅር የቀረቡ ባልቴት። አቆምን።

ነሸጥ ያደረጋት መኩዬ ቀጫጫው ገፋችኝ። ቀብ አድርጌ እነኳት። ይሄኔ ባልቴቷ ገላጋይነት ገቡ። "እረ አትጣሉ። ምን የሚያጣላ ነገር አለ? ጨዋታው እንደሁ ለሁሉም ይበቃል። መጣ ላት ክልክል ነው። መምታትም መመታትም አይቻልም። በሉ ተስማምታችሁ ተጫወቱ?" ብለው በማለዳ መስማማትን የዘሩብን ነበሩ። ይዘ አይነቱ ደግና የማስተዋል መንፈስ ስጓሰኛው ሕይወ ታችን ታላቅ ስንቅ ሆነን።

"እንት አቦሬ አፍ ምናምንቴ! ያንተም ሆነ የእሳ አፍ አር! አር! ይላል። ሁለተኛ አንድ ነገር ትንፍሽ እንዳትሉ!" የተባሉት አብሮ አደጎቻችን በዚያው የጨቅላነት ዕድሜ ቅስመ ሰባራ፣ በራሳቸው የማይተማመኑ፣ ፈሪዎችና ድንጉጦች ሆነው ማደጋቸው ግን ሳይዘነጋ።

'በሠርቶ አፍራሹ' ፈቃድ አንድ ጥበብ ተከስተልን። በዚ ያም ፈጠራ የማሰብ መብታችንን የከለከለንን ኅብረተሰብ መቅ ጣትና ማሸበር ጀመርን። በቀበሌው ሲሳይ ገቢዮ መሪነት በጥይት ቀለሀ ውስጥ እርሳስ እናቀልጣለን። እርሳሱን ከቀልሃው ጋር እዋህደን በሚስማር እናጎደጉደዋለን። በውጪ በኩል በቀልሃው ቂጥ ስር በክርክሩ ላይ ክር እናሥራለን። በሌላኛው ጫፍ ላይ ሚስማር ይታሠራል። ፍራንክ ካለን በዱምቡሎ አንድ ፓኬት ክብሪት እንገዛለን። ካለበለዚያም ከየቤተሰቦቻችን ክብሪት እንመ ነትፋለን። የተወሰነ የክብሪት ሰልፈር በቀልሃው ውስጥ እንፈረ ፍራለን። በጥንቃቄ ሚስማሩ ከቀልሃው ጋር ተዋህዶ ከድንጋይ ወይም ከግንብ ጋር ሲላተም አሸባሪ የፈንጂ ድምፅ ያወጣል። መንደርተኛው አሉታውን ያቀልጠዋል። ሕፃናቱ በአመፁ ልባችን ረክቶ በርካታ ክብሪቶች እንደገና ቀልሃው ውስጥ ጨምረን እንዲ ያንባርቅ እናደርጋለን። የሲኦል ድምፅ መንደሩን ያናውጠዋል።

የእካባቢው ነዋሪ ጎብረተሰብ አቤቱታውን ለየቤተሰቦቻችን ያሰማል።

አንድ ዕለት አንድ ባላገር አህያውን እያነዳ ከገበያ ይመለ ሳል። እግግ ውድነሽ ከቦኖ ውሃ በእንሥራ ውሃ ሞልተው ወደ ቤታቸው ይመጣሉ። አንደኛው ግንነቱን የግንናገረው ጓደኛችን ትልቅ ቃሪያ ለሁለት ሰበረና ጉግጁን አህያው ቂጥ ውስጥ ወተ ፈበት። አህያው በረገገ። እያናፋ አመር ብሎ ሲዘል የእግግ ውድነሽን እንሥራ ጀርባቸው ላይ ለጋው። እንሥራው እንደ መድፍ ፈነዳና ውሃው ምድሩን አራሰው። በዚህና መሰል ተግባ ራችንም የሰፈራችን ማኅበረሰብና የታዳጊ ወጣቶች ቅራኔ በጣም እየሠፋ መጣ። ልባችን ለማንም ለምንም የማይመስስ እየሆነ ሔደ።

"ለመኪና ይዳርጋችሁ" አሉ እግግ ውድነሽ አንጀታቸው አሮ።

"ዳር ዳሩን እንሄዳለን" እንዳያውቁን በቀጭን ድምፅ።

"በአጭሩ ያስቀራችሁ!"

"ጠረጴዛ ላይ እንቆግለን"

እርስ በራስ ምስጢራችንን እንጠባበቃለን። ከእኛ መሐል ያጋፈጠ ልጅ ከመካከላችን ይገለላል። ይህ ቂም እስከሚረሳ አብ ሮን እንዳይጫወት ይታገዳል። የሆያሆዬ ሰሞንም ከሆነ አብሮን አይጨፍርም። ይህን ያልተጻፈ ሕጋችንን ሁላችንም እሰምረን ስለምናውቅ ምስጢር እንጠብቃለን።

"እናንት ፈሳሞች! አትጠፉም ከዚህ?! ነብር እየኝ በሉ! እንተ ዶጅ ዝም ብለህ ታየኛለህ? ቀኝ እጂን ሰጥቼሃለሁ እንድ አንዲ በጥፊ በልና ከዚህ አጥፋልኝ" ብለው እግግ በለጡ ገለ ገሰጡን። ብትን አልን። ዶጅ ትእዛዛቸውን መፈጸሙን ላያዩ ተመልሰው ወደቤት ገቡ።

ጨዋታችን እያመረረ፣ በሌሎች ሰዎች ውስጣዊና ውጫዊ ስቃይ የመሳቅ ጠባያችን ሳናውቀው ውስጣችን እያደገ መጣ። አሁንም ጨዋታችንን ቀይረን መፈንጠዙን እንደቀጠልን ነው።

እንዲት ቀይ ሻሽ ያሠረች፣ የሻግ ቀሚስ የለበሰች፣ ያደፈ ነጠላ የተከናነበችና ኮንጎ ጫማ ያደረገች ሴት መጣች። መሬት የወደቀችውን መሐረብ ድንገት አየቻትና ቀና ብላ ግራ ቀኙን ተገላመጠች። ጎንበስ ብላ መሐረቧን ልታነሳ ጥቂት ሲቀራት ከሯን ሳብ አደረግናት። ትዕይንቱ እኛን በጣም ሲያስቀን፣ ድርጊቱ የተፈጸመባት ምስኪን ግን ደንግጣና አፍራ የእርግማኑን መዓት እያወረደችብን ወደ ጉዳይዋ ሄደች።

ቁራጭ ብር ስናገኝ ያደፈች መሐረብ ፈልገን ውስጧ ሶልዲ ጨምረን እንቋጥራታለን። የብሯ ቁራጭ ብቅ ብላ ትታያ ለች። መሐረቧን በክር አስረን፣ መንገድ ዳር እናስቀምጣታለን።

ክሯ እንዳትታይ ጭቃ እንቀባታለን። ከዚያ ከሯን ተርትረን፣ እኛም ተደብቀን አላፊ አግዳሚውን በጥንቃቄ እናስተውላለን።

ሌላ ጊዜ ደሞ ኪሳችንን መንገድ ላይ ጥለናታል። እኛ ፈንጠር ብለን እንጫወታለን። አንድ ሲቆፍር ወይም ሲገነባ የዋለ ሠራተኛ እገልግሉን አንግቦ ከማዶ ሲመጣ እየነው። በረባሶ ጫማ አድርጓል።

"ምታልን ጋሼ! ምታልን!"

የበላ የጠጣውን ያህል ኪሳችንን ለጋት። "ወይኔ እግሬን!" ብሎ ቅንጥስ ሲል በሳቅ እውካን። በፈነዳ ኪስ ውስጥ እንዳች የሚያክል ድንጋይ ከተንበት ነበር።

አንድ ቅዳሜ ቀን ጎደቴ ጠጅ ቤት በራፍ አጠገብ የሰፈር ልጆች ተሰብስበን እንጫወታለን። ሽምብራ እሸት ስንጠረጥር ቆይተን ባሪኾ ወደ አባባ ዘውዴ ግቢ እቅጣጫ ሄደና "ኩሊ! ኩሊ!" ብሎ ተጣራ።

የሚያሸክማቸውን ይጠብቁ የነበሩ ሠራተኞች በሶምሶማ ሩጫ ባሪኾ ጋ ደረሱ።

"የትልበት ሥራ ነው! ጌኖ መውቀጥ ትችላላችሁ?"

"በደንብ! ስንት ሰው ነው የምትፈልገው?"

"ለእምስታችሁም ይበቃል።"

"እሺ አንችላለን።"

"በሉ ተከተሉኝ" ብሎ በሶምሶማ ሩጫ እያንጋጋቸው ሲመጡ አይተን በሳቅ እውካን። ባሪኾም በነኃይሉ ዶሮ ሰፈር አድርጎ በጨነቀው ሱቅ ዞሮ በጀግል ሱቅ በኩል አድርጎ መልሶ ሰፈር ይዞአቸው መጣ። ሁሉም አኩል መሮጥ ስላልቻሉ ወደኋላ የቀሩም ነበሩ። ባሪኾም ልክ እኛ እካባቢ ሲደርስ ፍጥነቱን ጨመረና በሃምሳ አለቃ ታደሰ ቤት በጓሮ በር ገብቶ ተሰወረ።

ኩሊዎቹ እንዳላገጠባቸው አውቀው በቁጣ ሰፈሩን ቀውጢ እደረጉት። እኛ ግን ትንንሽ ብንሆንም እንደ አዳኝ ውሻ በእ ድማ ስለምናጠቃ ሊደፍሩን አልቻሉም። እየሳቅንባቸው፣ ኩሊዎቹ እየተራገሙ ወደ መጡበት ሄዱ።

ይህንን ልብ ብለው ያስተዋሉት እግግ በለጡ ብልጧ ክትክት ብለው ስቀው "ተመስገን በሉ ሰዎች! ልጆቻችን እዚህ ደረሱልን። የዘራነውንም ማጨድ ጀመርን!" አሉ ፉከ ብለው።

በልጅነታችን ሳንከለከል የምንጫወተው በቡድን ተከፋ ፍለን ወታደር ሆነን በምንዋጋበት ወቅት ነበር። የኢትዮጵያና የጣሊያን ወታደሮች ሆነን እንገጥማለን።

የከሰል ማንደጃ ቅዳጅ ወይም የተሸነቆረ ታኒካ ታንቡር አድርገን የበረኪና ላስቲክ በሲጋራ ወረቀት ጠቅልለን በማጌጥ ጥሩንባ እንሠራለን። በረጃጅም ካኪ ወረቀት የወታደር መለዮ ሠርተን እናደርጋለን።

ከዚያም ወታደራዊ ሙዚቃ እያሰማን የሠልፍ ትዕይንት ለመንደርተኛው እናሳያለን። ሰፈርተኛው ያደንቅልናል። በዚህ ወቅት የፊት መሪ ለመሆን ፉክክር ይጀመራል። ሲሳይ ጎቢጥ ያባቱን የክብር ዘበኛ መለዮ ያደርግና ቀጠን ያለች ዘንግ ይዞ ፊት መሪ ልሁን ይላል። እኛ ደግሞ "ጎባጣ ስለሆንክ ሰልፋችንን ታበላሻለህ!"

"ቀጥ አላለሁ!" ይልና ጎቢጥ ደረቱን ነፍቶ ቀጥ ለማለት ይሰጠጣል። ትንሽ ቆይቶ ይዘነጋውና ይጎብጣል።

አብነት ባሪያው የፊት መሪያችን ይሆናል። ሲሳይ ጎቢጥ መለዮውን ሲከለክለው፣ አብነት ብትሯን ተረክቦ ፊት መሪያችን ይሆናል። አየተሽኮረመመ ብትሯን ማሽከርከር ይጀምራል። የሠፈራችን ጡረተኞች ወታደራዊ ትዝታቸው እየተቀሰቀሰ ፈገግ ብለው "ረጋ በል!" ሲሉት አብነት ባሪያው የኋላ እርምጃ ተራምዶ ፍጥነቱን ከእኛ ጋር ያስተካክላል...

ሰልፉ ወደ ጦርነት ጨዋታ ይቀየራል። የኢትዮጵያና የጣሊያን ወታደር ሆነን እንከፋፈላለን። ብዙ ጊዜ የጣሊያን ወታደር መሆን የሚፈልግ ልጅ የለም። ይሁንና ጨዋታው መካ ሄድ ስላለበት "ከዘውድ ከንፈር" ተብሎ በፍራንክ ዕጣ ይወጣል። የቡድን አባቶች የኢትዮጵያና የጣሊያን ወታደር መሪ ሆነው ይመደባሉ። የተቀረነው ጭፍሮች ተሟድነን ዕድል በመራችን ቡድን ውስጥ እንመደባለን።

የመገዳደል ጨዋታው ይጀመራል። የበዓል ሰሞን ከሆነ ጠመንጃችን ከኳባ የተሠራ ይሆናል። የጥይት ድምፅ እንዲኖረው ኮባውን አልፈን አልፈን እንቀርፈውና የጠላት ወታደር ስናይ እንተኩስና እንዘርረዋለን። ከበዓል ውጪ ከሆነ ማንኛውም ቆመጥ እንደ ጠብመንጃ ያገለግላል። ከአካባቢው ጋር ለመመሳሰል ጭንቅላታችን ላይ የዛፍ ዝንጣፊ እናሥራለን።

ከዚህ በኋላ በተመደብንበት አገር ምሽግ ይዘን መታኮስ ነው። በተደበቀበት ሆኖ ቀድሞ ያየ ልጅ ጠላቱን ሕፃን "አገኘሁህ! አንት ፋሺስት!" ይልና ይተኩሳል። የተመታውም ልክ በጥይት እንደተገደለ ሁሉ ይዘረራል። በዚህ ጨዋታ አንዳንድ አዋቂዎችም ይሳተፋሉ።

ትዝ ይለኛል፣ ባሻ ሐረሩ ከዘራቸውን ደገፍ ብለው "በለው! ይሄ ሰላቶ እንዳያመልጥህ!" እያሉ ለኢትዮጵያ ወታደር ድጋፋቸውን ይገልጻሉ።

የሃምሳ አለቃ ታደሰ ፍንድቅ ብለው እየተንከተከቱ አሳዳጁን "ወንዱ! ደረሰበት!" ሲሉ ያደንቃሉ። (በዚህ አጋጣሚ አዋቂዎቹ እውነተኛውን ትዝታቸውን ይጫወታሉ)

የጦርነት ጨዋታው አድካሚ ነበር። ቁጭ ብድግ ማለቱ፣ መሸሹ፣ ማሳደዱ፣ አልሞ መምታትና መንከባለሉ ታክለብት ሙሉ ወታደራዊ ጥንካሬው እንዲኖረን ሰለምንጥር ፈታኝ ነበር። ይህን

ጨዋታ በደንብ እንድንጫወት አይነጥላዎቻችን ፈቀዱልን። ከልብ ተጫወትነው፣ እስከ እውነቱ!!

መጣና ጌታችን ላመት ግብራችን

ሆያ ሆዬ!
ሆ!
የኔ ጌታ!
ሆ!
ጌታ ነው ጌታ!
ሆ!
ጌታ ጠንበለል!
ሆ!
ዝናቡ መጣ!
ሆ!
ወዴት ልጠለል! ...

ሰኔ ሠላሳ ካለፈ በኋላ የፈተና ውጤታችንን እንዳወቅን ትምህርት ቤታችን ይዘጋል። ሐምሌ ተጠናቆ ታላቅ ፍስሐ ይዘልን የሚመጣው ወር ነሐሴ ነበር። ነሐሴ 13 ቀን ቡሄ ነው። ቀደም ብለን እንዘጋጃለን። ጅራፍ በስፈራችን እዚህም እዚያም ይጮሃል። ትልልቅ ሰዎች የትም ሆነው "ኡ! ይጨህባችሁ!..." እያሉ ሲያማርሩ ይሰማሉ። እኛ ግን ትንሽ ራቅ ብለን አካባቢውን በጅራፍ ጩኸት እናደበላልቀዋለን።

ቡድናችን ከዓመት ወደ ዓመት ይለዋወጣል። ቁጥራችን አንዳንዴ ይበዛል፣ አልያም ያንሳል። ዘንድሮ እኔ፣ ጎቢጥ፣ መኩዬ ቀጫጫው፣ ሴምላል፣ ቀጠሳው፣ ሻቃ፣ ይጥና፣ ፑሉቶ፣ ዶሮ፣ ውሮና ሳይቶም አሻሮ የአንድ ቡድን አባል ለመሆን ወሰንን። ዓለምነህንና ወንድሙን ደምስን አናስገባም አልናቸው። ሁለቱ በጉልበት ከእኛ ስለሚበልጡ ዓይን በዓይን ያጭበረብሩናል። ስለምንፈራቸው በዓይናችን ያየነውን ስሙኒ ዲናሬ ነው ሲሉን ማመኑ ለደህንነታችን ይበጃል። አምና የአማማ አመለወርቅ ትልቅ ሙል ሙል የት እንዳገቡት ሳይታወቅ ጠፋ። በዚህ ምክንያት ዘንድሮ ከእነርሱ ጋር ላለመጨፈር ወሰንን።

ዓለምነህና ደምስ በአስተዳደጋቸው እንደ እኛ በጥብቅ ቁጥጥር ታፍነው ሳይሆን ያደጉት ልቅ ሆነው ነበር። እኛ አጥፍታችንል ተብለን የምንገረፍበትን ጉዳይ እነሱ አባታቸው ተከራክረውላቸው ነፃ ያደርጓቸዋል።

አንዴ ደምስ እኔን "ገብር!" አለኝ። በጉልበት የሚበልጠውን ልጅ የሚያሸንፈውን ልጅ ማስገበር እንደ ደንብ ነበር

የምንቆጥረው:: ስለዚህ ደምስ ስለሚያሸንፈኝ ቆሉም፣ ቂጣም እግዬ ስትሰጠኝ እያመጣሁ እንድገብር አዘዘኝ:: ሆያ ሆዬ ሲመጣ ፍራንክ የምገብርበት ጊዜ ደረሰ:: እኔ ግን እምቢ አልኩት:: በዚህ አመፀኝነቴ መግቢያ መውጫ አሳጣኝ:: ሰፈር ውስጥ መጫወትም ሆነ ካምቦሎጆ አካባቢ ዙረት እንዳልሄድ አገደኝ:: እኔ ግን እየተደበቅሁ ሰፈር ውስጥም እጫወታለሁ ዙረትም እሄዳለሁ:: ድንገት ካየሁት እንደ ወፍ ቱር ብዬ እሸወራለሁ:: ፀያፍ ስድብ እየሰደበኝ፣ ሲያገኘኝ ደሜን እንደሚጠጣ ይዝትብኛል::

መሸሸጉ ሁሌም አይሞላምና አንዴ ከካምቦሎጆ ስመለስ መንገድ ላይ ተፋጠጥን:: ከአራተኛ ክፍለጦር ፊት ለፊት ነው የተገናኘነው:: ወደኋላ ብመለስ ሮጦ ይደርስብኛል:: አስጥሉኝ ብዬ የጮኽኝ የምለው ትልቅ ሰው በእካባቢው አጣሁ:: ፈተለክ አልኩኝና ባቡር መንገዱን እቋረጥኩኝ:: ደምስ ያገኘውን ድን ጋይ አንስቶ ወረወረ:: እኔን ስቶ የመኪና መስታወት መታ:: ባለመኪናው ደምስን አሳድደው ያዙትና ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት:: በልጅነት ዘመኔ ደምስ የመጀመሪያው አሸናፊ ሲሆን እየሁ::

አባቴ ግን "እንዴት እኔ እያለሁ ልጄን?" ብለው ፎከሩ:: ከላሹንም አሳሪውንም በጆሮ ገብ ድምፃቸው እያቅራሩ አስፈራሩአቸው:: ሰዎቹ ይቅርታ ጠይቀው ደምስን ለቀቁላቸው:: ይህ ድርጊት ከመሰረቱ ሲጠና ጉዳዩ እኔ ላይ አነጣጠረ:: ቤተሰቦቻችንም በጉዳዩ መክረው ሁለተኛ እንዳይደርስብኝ ታገደ:: እኔም ሸክም የወረደልኝን ያህል አፍይ አልኩኝ:: ይህ ቂም ስላለብኝ የእኛ የሆያሆዬ ቡድን አባል እንዳይሆን የመጨረሻውን ጥረት አደረኩ:: የቡድናችን አባሎችም ድጋፋቸውን ሰጡኝ::

ወንድማማቾቹ የቡድናችንን አባሎች በተናጠል እየጠሩ ያታልሉን ጀመር:: እኔ በእቢታዬ ፀናሁ:: ውሮ ግን ለሆያሆዬ እክፍላለሁ ብሎ ከዓለምነህ ሰሙኒ ተበድሮ ብይ ተጫውቶ ተበልቷል:: ስለዚህ ስሙኒውን እንደሚምረው ሲነግረው ደስ ብሎት እንድናስገባቸው ይለማመጠን ጀመር:: በዚህ ተናደን ውሮንም ከቡድናችን አሰወጣነው:: በጣም አዝኖ እያለቀስ ለእናቱ ለእግማ ወርቅውሃ ሄዶ ነገራቸው::

ከእነ ኃይሉ ዶሮ ጋር ጓሮ ጥላው ሰር ቁጭ ብለን ስንመ ካከር እግማ ወርቅውሃ ድንገት ከተፍ አሉ:: "እናንተ! እንዴት ብትጠግቡ ነው ልጄን ሆያሆዬ ከእኛ ጋር አትጨፍርም ያላችሁት?!" አሉና አፈጠጡብን:: 'ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመትም አይቆዩ!' ፈሳም ሁሉ! በሉ አስገቡት!" ብለው ውሳኔያቸውን አሳወቁን::

"እኛ ውሮን እምቢ አላልነውም:: እሱ ግን እነ ዓለምነህን አስገቢው እያለ ያስቸግረናል:: እንቢ ያልነው ለዚያ ነው" አለ ቀጢሳው::

"ውሮ እንደዛ ብለሃል?" ጠየቁ እናቱ::

"አምን!"

"አንተው ነሃ ጥፋተኛው! እነሱ እኮ ትላልቅ ልጆች ናቸው ያጭበረብሯችኋል:: አንተ ከእኩዮችህ ጋር አርፈህ ተጫወት" መግባባታችንን ሲያዩ ጥቂት ምክር ቢጤ ለግሰውን ጥለውን ሄዱ::

እነዓለምነህ በተናጠል በመደራደር አልሆን ሲላቸው ወደ ማስፈራራቱ ሄዱ:: በዚህ ጥቂት ተሸበርን:: ጎቢጥ እንድ ሃሳብ ትውስ አለችውና እንደመፍትሔ ለቡድናችን አቀረበ:: "ለቦቾራና ለዶጅ ገማጣው ለየአንዳንዳቸው ዲናሬ ዲናሬ ብንሰጣቸው ያስፈራሩልናል:: እንንገራቸው!"

ግለፈያ መፍትሔ ሆነ:: ሁሉቱም የመንደራችን ጉልበተኞች "ባትከፍሉንም እንዳይመቷችሁ እናስጠነቅቃቸዋለን" አሉን:: ፍራንኩን ግን አይምሩንም::

ከባድ ሸክም የወረደልን ያህል እፎይ አልን:: አንደኛው ገንዘብ ያዥ፣ ሌላኛው ዳቦ ተሸካሚ በመሆን ያጭበረብሩን የነበሩትን ወንድማማቾች በኃያላኑ ኃይል ገታናቸው:: ሆኖም ግን ሆያሆዬ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ራሳችንን እንድንጠብቅ መከርን:: ለደህንነታችን ሲባል ከመንደራችን አለመራቁ እንደሚበጀን ተመካከርን::

ለችቦ መሥሪያ የሚሆነንን ከሴ መቁረጡን ተውነው:: ለምን? ከሴ ቆረጣ ስንሔድ ሁላችንንም ጫካ ሙስጥ ይዘው በላማ ሊገርፉን ወንድማማቾቹ መወሰናቸውን ደረስንበት:: ችቦ በዱምቡሉ ገዝተን ለማብራት ተመካከርንና ከውጥመዳቸው አመለጥን::

በእቅዳችን መሠረት ሞፈራውን ከእያንዳንዳችን ቤተሰብ እንጀምራለን:: እነሱም በደስታ ተቀበለውን ርቀን እንዳንሄድ መክረውን የቻሉትን ይሸልሙናል:: ፍራንክም ዳቦም አንድ ላይ የሚሰጡ ቤቶችም ነበሩ::

ወደ ጎረቤቶቻችንና ወደ መንደራችን ሰዎች ቤት ስንዘልቅ ማጣትና ማግኘትን እናስተውል ነበር:: አንዳንዶቹ ውስጣቸው በማጣት ጠቁሮ፣ እኛ እየጨፈርን ስንመጣ ፈገግ ብለው ይቀበሉናል:: ሌሎቹ ደግሞ መጪዉን ጊዜ በደስታና በተስፋ ለመቀበል/ ወስነው ፈካ ብለው ያስተናግዱናል:: እጃቸው ቢያጥር እንኳ ለቡና ብለው ያስቀመጧትን እርጋፊ ሣንቲም ይሰጡናል::

የታመሙ ወይም ሥራ ፈት የሆኑ ትልልቅ ሰዎች ቤት ጎራ ብለን ጨፍረን በደስታ እድምቀን እንወጣለን:: ከልጆቻቸው መረጃ ቀድሞ ስለሚደርሰን ዳቦም/ ሆነ ፍራንክ ከዚያ ቤተሰብ አንጠብቅም:: የእነዚህ ችግረኛ ቤተሰብ ምርቃት አሁንም ትውስ ይለኛል:: "እግዜር ያሳድጋችሁ! አሱ ወሮታውን ይክፈላችሁ! ከዓመት ወደ ዓመት አብረን እንድንሸጋገር፣ የደስታችሁ ተካፋይ ልታደርጉኝ መጣችሁ? እኔን ለወግ ለማዕረግ እንዳበቃችሁኝ እሱ አይመረመሬው እናንተን አግኝቶ ከማጣት ያድናችሁ!"

ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ ክፉ ቀን የሚሉትን አሳል ፈው፣ የተሻለ ሕይወት በበጎለኛው ጊዜ ይኖራሉ። በዚህ ወቅት እኔም ሆንኩኝ አብሮ አደጎቼ ጎርምሰናል። ያኔ ቤታቸው ሂደን ሆያሆዬ የጨፈርንላቸውን ከውለታ ቆጥረው ሰወላጆቻችን ማጫወ ታቸውን አስታውሳለሁ።

ስንጨፍር በደንብ ግጥም ማውረድ በማይችል ልጅ ስህተት ቅር የተሰኘ ቤተሰብ ከእኛ ውትወታ የሚገላገልበት ወቅትም ነበር።

"ሆያ ሆዬ ጉዴ ብሯን ብሯን ይላል ሆዴ!" ሲልና እኛ ስንቀበል፣

"ኧረ! ብሯን ብሯን አለ ሆድህ!?" ይላሉ።

"ሆያሆዬ ና! ና! ልምጣ ወይ ወደ ማታ!"

"አሁን ገና አወቃችሁልኝ! አምን፣ ወደ ማታ ኑ!" ይሉናል።

ባላገር ያደጉ ያህል የግጥም አወራረዱን አሳምረው የሚያ ውቁበት ጓደኞችም ነበሩኝ።

"ሆያ ሆዬ!

"ሆ!"

"ሆይ የኔ እመቤት!"

"ሆ!"

"የፈተለችው!"

"ሆ!"

"የሸረሪት ድር!"

"ሆ"

"አስመሰለችው!"

"ሆ!"

"ሸማኔ ጠፍቶ!"

"ሆ!"

"ማርያም ሠራችው!"

"ሆ!"

"ለዚያች ለማርያም!"

"ሆ!"

"እዘኑላት!"

"ሆ!"

"ዓመት ከመንፈቅ"

"ሆ"

"አለቀላት!"

"ሆ!"

"ሆያሆዬ ናና! በሰፈው ጎዳና!"

እንዲህ አይነቱ መወድስ እስከ አንድ ብር ያሸልመን ነበር።

ውሻ ካለበት ግቢ ገብቶ መጨፈር ራሱን የቻለ አሣር ነበር። አንዳንዶቹ ቤተሰቦች ድምፃችንን ከውጪ ሲሰሙ ውሻ ቸውን ፈትተው ይለቁታል። እኛ ግን ቀድመን መረጃ ስለሚ ሆረን ብንደነግጥም ራሳችንን መከላከል እንችላለን።

እንዲህ እንዲህ እያለ አስደሳቹ ቀን እንደማንኛውም ዕለት ጊዜን ቆጥሮ ያልፋል። ገንዘባችንን እንከፋፈላለን። ለእያንዳ ንዳችን ለሽልንግ ዱምቡሎ የጐደለው ይደርሰናል። የተሰጠንን ዛቦ ለለማኞች ስንሸጠው ሰሲኒማ መግቢያችን በደንብ ሸቅለን ትርፍ ገንዘብ የምናገኝበት ሁኔታ ይፈጠራል። ቡድናችንን በጥንካሬው እንዲቀ ጥል ሳገዙን ልጆችም የውላችንን እናደርሳለን።

ሁላችንም ሽልንግ ሽልንግ ኖረን። ነገ ሲኒማ የምንገባበት ቀን ይሆናል። የዚያን ዕለት ሌሲቱ ረጅም ነው፣ ቶሎ አይነ ጋም።

በዚያ የለጋነት ዕድሜ ገንዘብ ይዞ መገኘት በወላጆቻችን ስለሚያስቀጣ የደረሰን ዲናሬ ዲናሬ እንደሆነ አስረድተን ለቡና ማፍያ እንዲሆናቸው ለእናቶቻችን እንስጣቸዋለን። የአንዳንዶቻችን ወላጆች ከፈቀዱልን ፓስቴ እንገምጥበታለን። ሽልንጋችንን ግን ዙሪያዋ ቦታዎች እንደብቃለን። እኔ በቁምጣ ስሪዬ ወገብ ላይ ያለውን ድርብ ጨርቅ ቀድጄ ምስጢር ኪስ ስለሠራሁ እዚያ ውስጥ ደበቅኩት። መሰለ ዲዲ አባባ ዘውዴ ግቢ ሠንሠለ ውስጥ ጉድ ጓድ ቆፍሮ ፍራንኩን ቀብሮ ለምልክት እሳዩ ላይ አሩን አራ በት። ሲምላል ሽንቱን በጊዜ ሸንቶ ወሸላው ሽለፈት ውስጥ ከትቶ በክር ሸብ አድርጎት አደረ። ቀጪላው ፍራንኩን የት እንደሚደብቅ እስካሁን አላወቅኩም። መኩዬ ቀጫጫዋ ግን ወንድምዋ ኪሷን ፈትሾ እንዳይሰርቃት በመስጋት ለሚፈራት ልጅ ደብቅልኝ ብላ አደራ ትሰጠ ዋለች... የዚያን ዕለት ለደንቡ ያህል ሁላችንም ቤታችን ገብተን እንጋደማለን እንጂ እንቅልፍ በዓይናችን ሳይዞር ይነጋልናል።

ወደ "ሙቪ"

"ሲኒማ ትልቅ ጥበብ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ዕውቀት ልትገበይበት ትችላለህ። ያወቀበት ይጠበብበታል"
ስብሐት ገብረእግዚአብሔር

ነህ ሲቀድ ወፎች ሲዘምሩ ለመስማት ስንናፍቅ ያደርነው ልጆች ሲነጋጋ እንቅልፍ ሊጥለን ይችላል። ቀጢሳው ከሁላችንም ንቁ ስለነበር በማለዳ ተነስቶ በፉጨት ይቀሰቅሰን ጀመር "ፊፍቲ ፊፍቲ' ብሰን ርዕስ በለጠነው ፊልም ውስጥ እንዳደመጥነው አይነት ፉጨት ያሰማል። መንደርተኛው ሳያውቅም መልዕክቱ ለእያንዳንዳችን እንቅልፍ ላልጣለን የሰፈር ልጆች ይደርሰናል።

ከአልጋዬ ላይ ነጥሬ ተነሳሁ። ቁምጣዬን ታጠቅኩ። ሹራ ቤን ለብሼ በረባሶዬን አጠለኩ። "ወዴት ነው?" አለች እማዬ። በማለዳ ተነስታ የዕለት ሥራዋን ጀምራለች።

"ራስ ብሩ ሜዳ ሄደን ስፖርት ልንሠራ።"

"ቁርስህን ሳትበላ?"

"በቃኝ!"

ቀልባችን አረፈበት ሲኒማ ቤት እስከምደርስ በፍፁም በመ ንፈሴ የማይመጣ ነገር ቢኖር ምግብ ነው። አሰብነው ሲኒማ ቤት ደርሰን ለመግባት ስንወሰን ሁለት ፓስቴ የምገዛበት ትርፍ ዲናሬ አለች።

ቀጢሳው ቆፈን ያቆረፈዳቸው እጆቹን ለማሞቅ ሹራቡን ጎትቶ እንደ ጓንት እጆቹን አልብሶ በአራቱም አቅጣጫ እየተ ዘዋወረ ያፏጫል። ከእኔ ቤት እቅጣጫ ፑሱቶ፣ አብነት ባሪ ያው፣ ተረፈ ገልጆ መጡ።

በሌላው በኩል ኃይሉ ዶሮ፣ ሴምላል፣ ባረኾ፣ ውሮ፣ ሲሳይ ጎቢጥ... በረባሶአቸውን እያጠለቁ ማንገቻቸውን ወይም ቀበቶአቸውን እያጠባበቁ ብቅ ብቅ አሉ። ማናችንም እንቅልፍ አልጠገብንም። እንጨናበሰለን።

"አንድያሞ!" አስ ቀጢሳው።

ተክተልነው።

ለማስመሰያ እንዲሆነን የጨርቅ ኳስ ይዘናል። በከረጢቱ ውስጥ የተያዘው ግን ሙልሙል ዳቦ ነበር። ወሬው እንደልብ ነው። መንገድ መሪያችን አብነት ባሪያው ትንሽ ከሁላችንም ከፍ ስለሚል የትራፊክ ደንቡን ሁሉ አሳምሮ ስለሚያውቅ የእሱን መመሪያ እናከብራለን። በአቋራጭ መንገድ ይዞን ስለሄደ በሚከ ሲከ አደባባይ አሸርግን፣ በአምስተኛ ሥ'ሊስ ጣቢያ በኩል ሽቅብ

ወጥተን በፔፕሲኮላ ፋብሪካ ጉራንጉሩን ሽቅብ እቋርጠን ሲኒማ አዲስ ክተማ ደረስን። ሬክላሞቹን አየን።

በዚያን ጊዜ ወሬ የሚበዛበትን ፊልም ማየት አንወድም ነበር። ምንጊዜም የሚማርከን ድርጊት ነበር። ወይም በእኛ ቋንቋ 'ክትክት' ያለበት ፊልም መሆን አለበት። ስለዚህ የአዲስ ክተማን ሬክላሞች አይተን ለመምረጥ እንዲመቸን ወደ ሲኒማ ራስ አዘ ገምን። ብዙውን ጊዜ የእኛን ፍላጐት የሚያሟሉልን ሲኒማ ራስና ሲኒማ አዲስ ክተማ ናቸው። አሪፍ ክትክት ያለበት የቴክስ ፊልም፣ አሪፍ ግላድያተር፣ አሪፍ ዲቴክቲቭና የሕንድ ፊልም ያቀርቡልናል። ወረፋ አስጠባቂ ዘበኞቹም ይመስሙናል፣ ሽጉጥ የላቸውም እንጂ አለባበላቸው፣ ኬፕ እደራረጋቸው፣ አኳኋናቸው፣ አነጋገራቸው በጠቅላላው እንደ ሲኒማ አክተሮች ነበር።

ብዙውን ጊዜ ሬክላሙ አካባቢ በረንዳ አዳሪ ልጆች አይ ጠፉም። ሳንጠይቃቸው ጠጋ ይሉንና ሲኒማ ልንገባ መምጣታ ችንን ጠይቀውን ካረጋገጡ በኋላ ስለፊልሙ ጥራትና ብቃት ለእኛ ባዕድም፣ ግልፅም በሆነ ቋንቋ ይተርኩልናል። ከሲኒማ ራስ ጋር ምንም አይነት ስምምነት ሳይኖራቸው በነፃ ማስታወቂያ ይሠሩለታል። አክተሮቹን በተደጋጋሚ ፊልሞች ስላዩዋቸው የቤተዘመድን ያህል ያውቋቸዋል። አንዳንዴም ሲጠሩዋቸው ራሳ ቸው ባወጡላቸው ሰያሜ ነው። ትክክለኛ ስማቸውን አያውቁ ትም። ባያውቁትም እኛ ይህንን እንደ ጉድለት አንቆጥረውም።

"ይሄ ችስታው ነው። ይሄኛው ፈርናንዶ ሳንቾ፣ ማማ ሚያ! ማየት ማለት ይሄኛውን ፊልም ነው! አቤት ሲሸዋ ወዱ! ከትክት ደግሞ እንደልብ!" ይልና እንደኛው ትረካውን ይጀ ምራል። ጭቅቅት የወረሰውን አናቱን ፎክቶ ሲቀጥል "ይሄኛው 'ማዘር ኢንዲያ' ላይ የተጫወተው ራጂሽ ካፑር ነው። እዚህ ላይ ከሂማማሲን ጋር ይጫወታል። እ! ዘፈናቸው ልብ ያጠፋል!" እንደማንራጎር ይቃጣዋል። ድምፁ ሌላ ትልቅ ሰው ሆዱ ውስጥ ተቀምጠ የሚዘፍን ይመስላል።

አካላቸው ውሃ በዘረበት ዞሮ አያውቅም። ፀጉራቸው በጭቅቅት ተፈታትሎ ድብዳብ ሆኗል። ዓይኖቻቸው ድፍርስ ናቸው። ጥርሳቸው በሲጋራ ጢስ በልሟል። ድምፃቸውም እንደዕድ ሜያቸው ሳይሆን በጣም ጐርናና ነው።

"እዚህ ብትገቡ ጥሩ ነው። እኔ ዲናሬ ጎደሰኝ እንጂ የሚ ሞላልኝ ባገኝ እደግመው ነበር። እናቴ ትሙት እሪፍ ፊልም ነው! እስኪ በናታችሁ ከቻላችሁ ዲናሬ፣ ከሌላችሁ ድንቡሎም ቢሆን ሙሉልኝ?!"

እኔ ገንዘብ እንደልቤ ኖሮኝ የሰጠሁበት ጊዜ ትውስ አይ ለኝም። 'እጀ ወርቅ' ጓደኞቼ ቁልጭ፣ ወይም ባሪኾ ምንም ሳይመለሳቸው እስከ ክርክ ይሞሉላቸዋል። በየቀኑ ሬክላም ተመ ልክቶ ሲኒማ የሚገባ አዲስ ልጅ በመጣ ቁጥር እየቀፈፉ ከአንድ

ብር በላይ ይሸቅላሉ። ይህ የማስተዋወቅ ሥራቸው መጥዳደሪ ያቸውም ነበር።

አድፋሙ ልጅ ትረካውን ይቀጥላል። "ሦስተኛው ፊልም የሚወድ ልጅ ቢያየው በጣም የሚያስደስተው ነው። 'ውመንስ ግላዲያተር' ነው ርዕሱ። ወንዶችና ሴቶች ግላዲያተሮች ይጣሉና ወንዶቹም ሌላ ሰፈር ሴቶቹም ሌላ ሰፈር መኖር ይጀምራሉ። ትንሽ ቆይቶ ወንዶቹ እየሸወዱ ሽል እያሉ ሴቶቹን ማፈን ይጀምራሉ። በዚህ ምክንያት ሴቶቹ ተናደው የወንዶቹን ሰፈር ድምጥ ማጡን ለማጥፋት ይዘምታሉ።

"ሴቶቹ?!"

"ታዲያስ! ግላዲያተር እኮ ናቸው። አክተሯ በጫማ ጥፊ የወንዶቹን አለቃ ስትለጋው ጉንጩ ላይ የጫማዋ ቁጥር ይታተማል። አቤት ክትክታቸው! ወንዶቹን ድምጥማጣቸውን ያጠፏቸዋል። የተማረኩትን ወንዶች ሴቶቹ ሲከፋፈሉአቸው፤ ስታርዋ ሁስት ደስ ደስ የሚሉ ወንድ ወጣቶችን በግራና በቀኝ ወገብ ወገባቸውን አቅፋ ስትሄድ፤ እነሱ ሲፈራገጡ 'ዘ ኢንድ' ይላል።"

ጓጓሁ። 'እዚህ እንግባ' ማለት ግን አልችልም። ምክንያቱም በሕጋችን መሰረት ሁሉንም ሲኒማ ቤቶች ዞረን ሬክላሞቹን ማየት አለብን።

አንዲህ አይነት አጓጊ ፊልም የወጣ ዕለት ዱርዬ ልጆች 'ፎርጅድ' ትኬት የሚሸጡበት ዕለት ይሆናል። ረጂም ሰልፍ ኖሮ ግፊያ በሚበዛበት ወቅት 'ሠርግና ምላሽ' ይሆንላቸዋል። አቅመ ደካማ ልጅ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ሲያዩት ጠጋ ብለው "ትኬት ትገዛለህ?" ይሉታል። ልጁም አረፉ ፊልም ሳያየው እንዳያመልጠው በመጓጓት "አዎን!" ይልና በሽልንግ ይገዛቸዋል።

'ሃቲ ሚሪ ሳቲ' የተባለው ተወዳጁ የሕንድ ፊልም ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚታይ በሬዲዮ ይለፈፋል። ይህንን ልፈፋ የእኛ ሰፈር ልጅ ስዩም ሞራ ይሰማል። ሞራ የዚያን ዕለት ሚኒስትሪ ይፈተናል። ሲያስበው በፈተናው ምክንያት ይህ ፊልም ሳያየው ሲያመለጠው ነው።

"በሚቀጥለው ዓመት ሚኒስትሪ እፈተናለሁ" አለ በዚያ ጎርናና ድምፁ። ቅፅል ስሙም ሞራ የሆነው በዚህ ድምፁ ነው። ጉሮሮውን ሞራ ደፍኖታል ብለን እናምናለን።

ውሳኔውን አክብሮ ሃቲ ሚሪ ሳቲን ሊመለከት ሲኒማ ራስ ተገኘ። ትኬት ለመግዛት ግፊያው ከአቅሙ በላይ ሆነበት። ፈንጠር ብሎ በቆመበት አንድ ልጅ መጣና፤

"ትኬት ትገዛለህ?"

"አዎን። ስንት ነው?"

*"ቼላ"

---

*ቼላ፣ ሃምላ ሚንቲም።

ከፈለ። የገዛውን ትኬት በር ላይ ለትኬት ቆራጩ አሳይቶ ሊገባ ሲል ተያዘ፤ ሲጣራ ትኬቱ የሐሰት ነው። ሞራ በዚያ ሙት ቀስቃሽ ድምፁ አላጓራም። የቀረቀራትን ሽልንግ አውጥቶ ሌላ ትኬት ተጋፍቶ ገዛና "ወይኔ! ፋራ ብሆን ይቆጨኝ ነበር!" አለ በዚያ ጉርናና ድምፁ።

በዚያን ወቅት ከጎብረተሰባችንና ከሰፈር ልጆች የውግዘት መዓት ወረደበት። አናቱ እማማ ዘመናይ የፊጢኝ አስረው፤ በርበሬ አጥነው ዘወገራ ፈሱን አስጨረሱት።

ስዩም ሞራ ጉርምስና ሲጀግምረን ታሞ ሞተ። ይህንን መርዶ የሰማሁ ዕለት በዚህች አጭር ዕድሜው ቶሎ ተሸቀዳድሞ ሃቲሜሪ ሳቲን ዓይቶ ማለፉ አስገረመኝ።

ይህች የምንኖርባት ዓለም እንደ ሆቴል ቤት ብንመስላት፤ ባለሆቴሉ አንድዬ ነው። ያሰኘንን አዘን ልባችን የፈቀደውን ከውነን እንደሰታለን። በመጨረሻም ሒሳብ ስንል (ባንልም ጭምር) አስተናጋጁ መላክ ሞት ፀአዳ ልብሱን ተጉናፅፎ ነጭ ጓንቱን አጥልቆ በትሪ የያዘውን ደረሰኝ ያሳየናል። ደረሰኝዋም "እባክዎትን ሕይወትዎትን ይክፈሉ" ትላለች። ሞራም በዚህች አጭር ዕድሜው ያሰኘውን አድርጉ ሕይወቱን ደስ ሳሰኘው ጉዳዩ ማዋሉን ሳስብ አበጀ ያልኩት አሁን ነው።

ከዚህ ከሞራ አሳዛኝ ገጠመኝ በኋላ የቂርቆስ ልጆች የንበዝ አለቃ መርጠን ወደ ሲኒማ ቤት የምንጓዝ በመሆናችን አንታለልም። አለቃችን አብነት ባራያው ረጋ ያለና ንቁ ነው። እሱ ካላዘዘን በምንም ተአምር ሽልንጋችንን *አንሸለቀቅም። የሌሎቹን ሲኒማ ቤቶች ሬክላም ሳናይ በአሻሻጮቹ መረጃ ሰጪነት ብቻ አንወስንም። ስለዚህ ወደ ፒያሳ ጉዞ ጀመርን።

ሲኒማ ዓድዋ ብዙ ጊዜ ለእኛ የሚስማማን ፊልሞችን ያወጣ ነበር። ፕሮጀክተራቸው ግን አሮጌ በመሆኑ ፊልሙ ብዙ ጊዜ እየተቆራረጠ ነው የሚታየው። ዝናብ ከዘነበ አዳራሹ በጉርፍ ስለሚሞላ እግርን ሽቅብ አንስቶ መከታተል የግድ ነው። በዚህና በሌሎች ችግሮች ዓድዋ ምርጫችን ባይሆንም ምን አይነት ፊልም እንዳወጡ ለማወቅ ሬክላሞቹን እናያለን።

የግላዲያተር ፊልም ሬክላም ቀልባችንን ሳበው። ስታሩ ደረቱን ነፍቶ አቀበት ላይ ቆሞ ይስተዋላል። የትክለ ሰውነቱ የተስተካከለ ሆኖ መታየት የልጅን ብቻ ሳይሆን የአዋቂንም ዓይን ይማርካል።

"ይህንን ሬክላም ከፈለጋችሁ *መቦከም ይቻላል። ግን የት እንሰቅለዋለን?" አለ ተረፈ ገልጆ።

አንዳንዶቻችን ሬክላሙን ወደነው፤ መስረቁን ከጃጅሉን

---

*መቦከም፣ መስረቅ።

*አንሸለቀቅም፣ አናወጣም፣ አንከፍልም።

ነበር። ሌሎቻችን መስቀያውን አላሰብነውም። ገልጆ ግን አስከ ጥግ ድረስ ማስቡ አስደነቀን። 'ከየት አመጣችሁት?' የሚለውን የወላጆቻችንን መስቀለኛ ጥያቄ መመለስ አንችልም። ስለዚህ በብ ልሁ ጓደኞችን አስታዋሽነት እጃችንንም ልባችንንም ሰበሰብን።

እዚያው ሲኒማ ዓድዋ ደጅ ላይ ቆመን ሬክላሞቹን ለን መለክት ድንገት አንድ ጎረምሳ አየሁ። መኩዬ ቀጫጭዋን ጎሸም አደረኩና ጠቆምኳት። በለመጀ እግሯ ፈትለክ አለች።

በዚያው በልጅነት ወቅት አንዱ ሲኒማ ቤት ገብተን ከምንቀመጥበት ሌላ ትርፍ ወንበር እንይዝና በስሙኒ በስሙኒ እንሸጠዋለን። ዕድሜ ለልጅነት፣ ገዢ ከመጣ የምንቀመጥበትንም ወንበር በክርክ እንሸጠዋለን። በዚህ መልኩ ንግዱ የቀናው ልጅ በስሙኒ ሦስት ፊልም አየ ማለት ነው። እንዳስብነው ራስ ሲኒማ ስንደርስ የመጀመሪያዎቹ ተሰላፊዎች ሆንን። የባጥ የቆጡን ስናወራ ለሳቱ ደርሶ ትኬት መቆረጥ ጀመረ።

አንዳንድ ወንበር ይዘን መደዳውን ተቀመጥን። ከእኔ አጠ ገብ ዳር ላይ መኩዬ ቀጫጯው አለች። ብዙ ሰው ገብቶ አዳራሹ ሞልቷል። እዚህም፣ እዚያም ግስላው፣ ኒያላው፣ ጉራዛው...ሲጋራ ተለኮሰ። አዳራሹ በጢስ መታፈን ጀመረ። ፊልሙ ከመጀመሩ በፊት አንዱ ጎረምሳ መጣና መኩዬን "ወንበርሽን ሽጪ ልኝ?!" አላት።

"እሺ *ከርክ" አለችው።

ምስጢር ኪሱ የሚገባ መስለና እሷ ተነስታ ስትቆም ገፍት ሯት ቁጭ አለ። ደነጥኩኝ። አጠገቤ ያሉት የሰፈር ልጆች ተን ጫጩ። ጎረምሳው "ፀጥ በሉ! አለበለዛ እያንዳንድሽን አጪፈል ቅሻለሁ።"

ፀጥ አልን። መኩዬን ሳያት ደሟ እየተንተከተከ ነው። አንድ ነገር እንደምታደርግ ገመትኩ። ፊልሙ ጀመረ። አሪፍ ክትክት ነበረበት። መኩዬን እየተቆጣጠርኩ ፊልሜንም አያለሁ። ፓስቴዋን እየበላች፣ እሷም ቆማ እያየች ነው።

መኩዬን ፈንግሎ የተቀመጠው ጎረምሳ ደረቱን ገልብጦ ተንጋሎ ፊልሙን ይመለከታል። አንዳንድ ሰዎች ለስላሳ መጠ ጣት ጀምረዋል። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ጠርሙስ መሬት ሲን ከባለል ተሰማኝ። መኩዬ ጎንበስ ብላ ስታነሳ አየኋት።

የመጀመሪያው ዲክቴቲቭ ፊልም አለቀ። ሁለተኛው በሕንድ ኮሚኩ አክተር 'ማህሙዲ' ቀልድ ታጅቦ በዘፈን ደምቆ ዕልባቱ ላይ ደረሰ። ሦስተኛው ቴክስ ፊልም በመታየት ላይ እያለ ፀብ ተጀመረ። ትዕይንቱ የሁላችንንም ትኩረት አጥብቆ ያዘው።

---

*ከርክ፡ ሃያ አምስት ሳንቲም።

ከአጠገቤ "ክሽ!" የሚል የጠርሙስ ድምፅ ተሰማኝ። ዞሬ ላይ መኩዬ ጎረምሳውን ፈንክታው ቀድማ ባጠናችው መንገድ ከሲኒማ ቤቱ በርራ ወጣች። ጎረምሳውን ሳየው በጣም ደንግ ጧል። አልደማም። ተደነባብሮ ተኩተሳት። እኔም ከነበርኩበት ተንስቼ ቦታ ቀይሬ ሁለቱንም ትዕይንት መከታተል ጀመርኩ።

ብዙ ሰው የእነ መኩዬን ትርምስ ልብ አላለውም። ገና የሚተረከው የአቡጀዲው ግርግር የቤቱን ትኩረት ጨምዶ ይዞት ነበር። ከዚያን ዕለት ወዲህ መኩዬና ይህ ጎረምሳ ሲኒማ ዓድዋ ድንገት ሲገናኙ ዛሬ የመጀመሪያው ነው። ቀድሞ አይቷት ቢሆን ኖሮ ይዞ ይጪፈልቃት ነበር።

መኩዬ ራቅ ብላ ሲኒማ ኢትዮጵያ አጠገብ ሁሉን መቆ ጣጠር በምትችልበት ኩፍተኛ ቦታ ቆማ ጠበቀችን። አጠገቧ እንደ ደረስኩ እንደ ወሮታዬ ሳልለምናት በኪሷ ከያዘችው ቆሎ ጨብጣ ሰጠችኝ። ተቀብያት እየቃምኩ ሬክላሞቹን ማየት ጀመርን። በወ ቅቱ ሲኒማ ኢትዮጵያና አምፒር የመግቢያ ዋጋው አንድ ብር ስለነበር ወደ እዚያ ጎራ ማለት አይከጃጅለንም። ሁሉን ማወቅ በሚፈልገው ዓይናችን ሬክላሞቹን ማየታችን ግን የማይቀር ነው። ስናድግ የሲኒማ ቤቱ ደንበኛ እንደምንሆን ወስነን ወደ አገር ፍቅር ቴአትር እናዘግማለን። ከዚህ በኋላ ከአራቱ ሲኒማ ቤቶች የትኛው የእኛን ፍላጎት እንዳሚላ እንወያያለን። ከሁሉም ሲኒማ ራስ ላቀ። 'ውመንስ ግላዲያተርን' ልናየው ነው። ደስ አለን። በተረፈን ሣንቲም ፓስቴያችንን እንኚላለን። በተጪማሪ የሆያ ሆዬ ሙልሙልም አለን። ፊታችንን ወደ ሲኒማ ራስ መልሰን መራመድ ጀመርን። ምን መንገዱ ቢረዝም እንሸነፍም። ለምን ዓለም ዳር አይሆንም! ወደ ሲኒማ ቤት ስንሄድ አይደክመንምም፣ አይርበንምም፣ ዕድሜ ለልጅነት!!

ተራኪው

"አንደበተ ርቱእና ጪዋታ አዋቂ ሰዎች
የዓለምን ምሬት ማጣፈጫ ቅመም ናቸው"
(ስሙ ያልታወቀ ደራሲ)

ሲኒማ ልንገባ ስንሄድ ተረፈ ገልጆ መርካቶም ሆነ ፒያሳ ድረስ አብሮን ይሄዳል፣ ሬክላም ያያል። የት እንደምንገባ ካረጋ ገጠ በኋላ ወደ ስፈር ይመለሳል። ፍራንክ እንደ ልብ ቢያገኝም

ሲኒማ አይገባም። አንዳንዴ ግን ስለ ሲኒማው ተጋኖ ሲወራ ነሸጥ ካደረገው ይገባና እንደኛው ይደሰታል።

በሌላ ጊዜ ግን ፍራንኩን ለአደይ ዝማም በቅድሚያ ይሰጣቸውና በቀን አንድ አምባሻ እየሰጡት ይመገባል። ከከፈላቸው በላይ ብዙ አምባሻ ይበላል። የአደይ ልጅ ጎይቶም "አሻሮ ጓደኛች ንም ቢሆን እንዲህ አይኔት ማጭበርበር በእናቱ ላይ ሲፈጸም ይናደዳል። አሻሮ ከእኛ ጋር ይሸቅላል። ድብ ድብ ይጫወታል። አሪፍ ዝማ ከዘጋ ሙቪ እንደልቡ ይገባል። በምንም ተአምር ከአደይ ላይ እንደማይበርቅ ይናገራል። እኔ ግን አላምነውም። ሙሉ በሙሉ ይበከ ግል እንዳልል አንዳንዴ ቸር ነገር ሲያደርግ አየዋለሁ። አንዴ ከዙረት ስንመለስ በጣም ራበን። አንድ አሮጊት ቆሎ ነጋዴ አግኝተን ሳህን ላይ ማሰፈር ጀመርን።

አሻሮ ይዤን ሲያይ በጣም እየጮኸ «አማማ! አማማ! መጀመሪያ ፍራንኩን ተቀበሏቸው! የያዙት ሶልዲ ነው!» ብሎ አጋለጠን። ብትን አልን። አሮጊቷም ከቁም እንቅልፋቸው ባንነው «በሉ ፍራንኩን መጀመሪያ ከፈሉኝ?» ብለው አጥፊው አጠገባቸው ያስቀመጡትን ጃንጥላ አንደ ብትር ቃጡብን።

ገልጆና ጐይቶም ይነታረካሉ። አደይ ዝማም በመሃል ገብ ተው ያስማሙዋቸዋል። "ጐይቶም ዝም በል፣ እኔ እሱ አው ቃለሁ። እየራበው ነው፣ እንጂ ገልጆ አታላይ አይደለም" ሲሉ ከልባቸው ይመሰክሩለታል።

ገልጆ ይህንን የአደይን ውለታ አይዘነጋም። አደይ ከወ ፍጮ ቤት ሲመለሱ ካገኛቸው አህሉን ቀበል አድርጎ ቤት ያደር ስላቸዋል። እንጨት ሲፈልጡ ካጋጠሙት መቶረቢያውን ተቀብሎ የልባቸውን ያደርስላቸዋል። ሲላላካቸውም ከተፎ ነው።

ገልጆ በአባት አልታደለም። በሠፈራችን አባቱን ማንም ሰው አይወዳቸውም። አባቴ እንኳ ስለገልጆ አባት ሲያነሳ "ይህ የአባት ውራጅ!" ይላቸዋል።

አባቱ ሞላላ ራስ፣ ዓይነ በርበሬ፣ አጭር ሰውዬ ናቸው። ሁለት አይነት ሥራ እንዳላቸው አዋቂ ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻ ለሁ። ቀን ቀን ዱዳ ሆነው አፋቸውን አጣመው ለሃጫቸውን እያ ዝረበረቡ መርካቶ ሲለምኑ ይውላሉ። ማታ ደግሞ እጀ ጠባብ፣ ካኪ ኮትና ሱሪያቸውን ለብሰው ማሲንቋቸውን እየገዘገዙ በየጠጅ ቤቱ ይዘፍናሉ።

የገልጆ ታናሽ እህት አብራቸው ስትኖር፣ እናታቸው እኔ ነፍስ ከማወቄ በፊት ጥለዋቸው ሄደዋል። 'የዕለት ጉርሳቸውንና የዓመት ልብሳቸውን' አባት አያስቡም። ሁለቱም ሕፃናት ለመን ደርተኞቻችን ተላልከው ነው የሚበሉትን የሚያገኙት። እነዚህ ልጆች ያገኙትን በልተው፣ ካጡም ያማቸውን ማታ ኩራዝ አልባ ቤታቸው ውስጥ ይገናኛሉ። በጨለማው ውስጥ ስለ ዕለት ውሎ ዋቸው እያወጉ አባታቸውን ይጠብቃሉ። ወሬያቸው ብዙ ጊዜ

ስለ ምግብ ነው። ትዝታቸው ውስጥ አያሌ ጊዜያት የሚያነሱት በጣም የጠገቡበትን ዕለት ነው።

የአባትየው ድምፅ ከርቀት ሲሰማ ጠላት የደረሰባቸውን ያህል ፀጥ ረጭ ይላሉ። እየተሸበሩ የአባታቸውን ስድብና ቀረ ርቶ ያደምጣሉ። አባትየው ልጆቻቸውን ሲተው መረን የለቀቀ ነበር። በዚህም የገልጆ እህት ጆሮዋ ደንቁሯል። ልጆቹ አባታቸ ውን እንደ ወላጅ መውደድ ሳይሆን እንደ ጠላት በጣም ነው የሚ ፈሩት።

ከጓደኞቼ መካከል በጣም የሚራበው ገልጆ ነበር። የተ ቀረነው ልጆች ቤተሰቦቻችን ከሚሰጡን ቆሎም ሆነ ቂጣ ደብተን እናመጣለታለን። አንድ ቀን ለምሳዬ ከተሰጠኝ እንጀራ ቆርሼ በወጥ ጠቅልዬ ኪሴ ስከት እማዬ አየችኝና "የት ልትወስደው ነው?" ብላ አፈጠጠችብኝ። እውነቱን ነገርኳት። በጣም አዘነ ገልጆን ጠራችውና እስኪጠግብ እንጀራ በወጥ አበላችው። በዚህ ድርጊቷ ተደሰቼ እማዬን ሳም አደረኳት።

"ዘርበል! ፈሳም!" ብላኝ የሚጠጣውን ውሃ ሰጠችው።

ለእኛ ከምግብ የማይቆጠረው የጠላ ቂጣም ሆነ አሻሮ ገልጆ ካገኘው ጮማው እንደነበር አስታውሳለሁ። ገልጆ በባሕርዩ በጣም ጨዋ ልጅ ነው። ይሁን እንጂ ረሃብ ካየበት መስረቅ ይኖርበታል። የተሰጣ የሽሮ ክክ ተዘግኖ ኩተገኘ "ገልጆ በዚህ አልፎ ነበር?!" ሲሉ ወላጆቻችን ይጠይቃሉ።

ለመንደርተኛው በመላላክ ፍጥነቱና በልብ አድርስነቱ አንደኛ የሆነው ገልጆ፣ የላኩት ሰው በምርቃት ብቻ ሊሸኙት ከሆነ አይስማማም። የሚበላ እህል እስኪሰጡት ከበራቸው ላይ አይጠፋም። ከሰጡት ለማናችንም ሳያካፍል ለብቻው ይበላል።

ከእርሱና ከቀጢሳው በቀር ማንኛችንም ያልደረስንበት ልዩ የአመጋገብ ጥበብም ነበረው። ይኸውም፣ በኪሱ ቆሎ አጭቆ፣ አንዴ እንኳን ሲቅም ሳናየው በተሟሟፊ ጨዋታ ውስጥ አያለን በልቶ ይጨርሰዋል። ብዙ ጊዜ የያዛትን ቆሎ የሚቅመው አብ ሮት የሚጫወት ልጅ ብይዋን ሊመታ ሲያነጣጥስ ወይም ሙም ቹን አስተካክሎ ሲያነጣጥር ነበር። ከመካከላችን አንዱ ቀልጣፋ አይቶት "ስጠኝ!" ብሎ እጁን ቢዘረጋ፣ ከምሽቱ 12 ሰዓትም ቢሆን "ምሳዬ ነው!" ብሎ ርጋፊዋን ይቅማታል።

ገልጆ ጥርሶቹ ጠንካራ ናቸው። በዓመት በዓል ሰሞን የዶሮ፣ የበግ ወይም የበሬ አጥንት ካገኘን አምጥተን እንሰ ጠዋለን። ሲቆረጣጥመው፣ ተሰባስበን እንሰማለን። ልክ እንደ ድንጋይ ወፍጮ አፉ ውስጥ አጥንቷን ሲከካት በሳቅ እናውካ ካለን። እሱም አብሮን ይስቃል።

ገልጆ ይሞታታል እንጂ ከሰፈራችን ውጪ ዙረት ስንሄድ ከፊት ከፊታችን አይጓዝም። ችግሩ ብዙ ጊዜ ባቱ ላይ የኮሶ ትል እያየን ስንጠቁመው እየተሳቀቀ በስንጥር ሹጡን ያራግ ፋታል።

ከማንኛችንም ጋር አይጣላም። ስንጣላ ስማንም ሳያግዝ ይገላገልና ተለማምጠን ያስታርቀናል። ከእኛ መካከል አንዱ ነገር ቢፈልገው እንኳ፣ እሱ እንዳጠፋ ሁሉ ተለማምጦ ነገሩን ያበር ደዋል። አንድ ቀን "ስምን ኃይሉ ዶሮ ሲሰድብህ ዝም አልከው? አታሸንፈውም እንዴ?!" ብዬ ጠይቄው "ከእናንተ ጋር መጣላት የለብኝም። ከእናንተ ጋር ከተጣላሁ ማን ያበላኛል?" ብሎኛል።

ጢቢጢቢ ስንጫወት፤ ጢቢጢቢዋን የምናሥርበት ክር ካጣን ከገልጆ ሹራብ ላይ አንዷን ክር መዘን እናስርና ጨዋታችን ይቀጥላል። ቅንነቱና ትህትናው ልንደ ባህር ጥልቅ ነበር። ገልጆ በአንጋፋ ዝግ ግስት ይህ ቅፅል ስም ይውጣለት እንጂ፣ በእስ ተሳሰብ ከሁላችንም ይልቃል። ከሌላ ሰፈር ልጆች ጋር በቡድን ስንደባደብ ገልጆን ግንም አይችለውም። እንደ ፊጋ በሬ ሁለት ሦስቱን ሲያንከረባብት ማየቱ ራሱን የቻለ ተአምር ነበር። ሲመ ክትም ሆነ ሲሰነዘር እንደ ልጅ ሳይሆን እንደሠለጠነ በክሰኛ ቀልጣፋ ነበር። ለዚህ ቅልጥፍና የረዳው ስፖርት አዘውታሪነቱ ይመስለኛል። በጂምናስቲክ እንቅስቃሴ ሁላችንንም ይበልጣል። በእጅ መሄድ፣ መገለባበጥ፣ በአግጭ መቆም በጣም አሪፍ ነው። በኳስ ጨዋታ ንበዝ በረኛ ሲሆን፣ ሲያድግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አንድ ቁጥር የሆነውን ጌታቸው ዱላን መብለጥ ትልቁ ህልሙ ነው።

ሩቅ አሳቢ ነው። አንድ ቀን ስለ ስፖርት ሞቅ ያለ ወሬ ይዘን ከካምቦሎጆ ስንመለስ ትከሻዬን ደገፍ ብሎኝ "ሩንጋይ፣ አሁን እያሰብኩ ያለውን ታውቃለህ? አባባ ጃንሆይን ማግኘት እፈልጋለሁ። እንዳገኘኋቸው የስፖርት ችሎታዬን አሳያቸዋለሁ። ከዚያም አይተውኝ ደስ ሲላቸው አባባ ጃንሆይ፣ አሳድጉኝ! እላቸዋለሁ!"

እኔም ነሸጥ አደረገኝና አምሮቴን ገለጥኩለት። "ሳድግ ምን ግድረግ እንደማስብ ታውቃለህ? ወርቄ ሻይ ቤት እባባና አንድ ቅርጫት ሙሉ ፓስቴና አንድ ማንቆርቆሪያ ሙሉ ሻይ አስቀርቤ ስብቻዬ ብልት ጥጥት አደርጋለሁ።"

በጣም ሳቀ።

ሲኒማ ገብተን በመጣን ማግሥት ማታ ያየነው ታሪክ በአ ንደበተ ርቱዕ ጓደኞቻችን ይተረካል። ሲኒማውን የማየት ዕድል ያልደረሳቸው ልጆች በምናባቸው እየሣሉ ሲደሰቱ፤ ያዩትን የመ ድገም ያክል ያዝናናቸዋል። በትረካው ውስጥ የተሳሳተ ቦታም ካስ ጣልቃ ገብተው ያርማሉ።

ሁሌም 'ድድ' የምናሰጣው በጎደቴ ጠጅ ቤት ውሃ ልክ ላይ ነበር። ተመልካቾች ድንጋዩ ላይ ስንቀመጥ፤ ተራኪው ግን ቆሞ የአክተሮቹን እንቅስቃሴ፣ የድብድቡን ስልት፤ ሽጥጥ አመዛዘኑን፣

በግከል ያወጋናል። የሕንድ ፊልም ከሆነ ዘፈኑ ከነ እንቅስቃሴው ይቀርብልናል።

ፊልሙ ውስጥ ክርክር ከተነሳ ተራኪው በራሱ ፈረንጅኛ ያወራልናል። እኛም ይህ በእንግሊዞች መዝገበ ቃላት ላይ የሌለ ቋንቋ ይገባናል። ጣሊያንኛውም፣ ሕንድኛውም እንዲሁ።

ተራኪው ሲነግረን የሳተውና ልናውቀው የሚገባ ነገር ካለ ሴምላል ንፍጡን ሽቅብ ስቦ ያርመዋል። ተራኪው ቀጢሳውም በፍጥነት እርምቱን ሲቀበል "አምን! አክተሩ ሽል አለና ግቢሽው! ግቢሽው! አድርጎ ሲተኩስ...!" ብሎ በወሽመጥ የገባችለትን ታሪክ ይቀጥላታል። ከፊልሙ በስተጀርባ የሚደመጠውን ሙዚቃ አስፈ ሪውንም፣ አደገኛውንም፣ ፀጥታ የተሞላበትን እንቅስቃሴ ይታከል በታል። በዚህ አተራረክ ተራኪው በሙዚቃ አጅቦ ሩጫውንም ግልቢያውንም ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል።

በሲኒማ ቤት ውስጥ ተመልካቹ ለስላሳም፣ ሳንዲዊችም ገዝቶ እየተዝናና ፊልሙን እንደሚያይ፣ ሁሉ በመንደራችን የሲ ኒማ ትረካ ወቅትም የምንዝናናባቸው ልዩ ልዩ ሱሶች ነበሩ። ጉር ምስናው የጀግመራቸው ትንባሆ ያጤሳሉ። እነ አብነት ባሪያው፣ ባሪቾ፣ አመደ፣ ቦቸራና፣ ዶጅ ገማጣው አራምባ ይሰባሉ።

እኔ ሳድግ ታዋቂ ስፖርተኛ መሆን ስለምፈልግ ሲጋራ አልጠ ጣም። አራምባ መሳቡን አልፎ አልፎ እሳተፋለሁ። አራምባ የምናዘ ጋጀው ከቢንዝል ነው። ሱሱ ያለበት ልጅ ሁልቀን መሳብ ስለሚያ ስፈልገው ንፁህ ቁርጥራጭ ጨርቆች በላስቲክ ጠቅልሎ በኪሱ ይይዛል። እንደ ጂፕ አይነት መኪናዎች የቤንዝል ክዳናቸው በቀላሉ የሚከፈቱ ስለሆነ ከእዝህ ተሽከርካሪዎች ጨርቆቹን በቤንዝል ይነክራል። ጨር ቁም እንዳይነፍስበት በላስቲክ ይጠቀለላል። መሳብ በሚፈለግበት ጊዜ አንዷን ጨርቅ ነጥሎ በማውጣት በሁለት እጆቹ መዳፎች አፍኖ በአፉ የቤንዝሉን ጠረን ወደ ሆዱ ይስባል። አንዳንዴ በሾፈሮች ተይዞ ወገራም አለ። አራምባ ሲስቡት ዛና የማድረግ ስሜት ይፈጥራል። ከልክ በላይ ከሳቡት በጣም ያስከራል። ከቤተሰቦቻቸው ተጣልተው በረንዳ ለሚያድሩ ልጆች ጥሩ የብርድ ልብስ ነው። በሆድ ውስጥ የሚገኝ ተህዋስያንን በተለይ ወስፋትን በፍጥነት ያጠፋል። አራምባ ከፍተኛ የምግብ ፍላጉትን ይከፍታል። በዚህ ምክንያት ሱሱ ያለባቸው ጓደኞቼ ሁሉ በጣም ሆዳም ናቸው።

በአራፍ ጨዋታ መሳከል እያለን ከምንቅመው አሹቅ አንዷ ጥሬ ከአጃቸው ብትወድቅ ወሬው ተቋርጦ ጥሬዋ ትፈለጋለች። ያገኛት ለቀም አድርጉ ወደ አፉ ይወረውራታል።

የፈልሙ ርዕስ፣ ደራሲው፣ አዘጋጁ ለእኛ ምናችንም አይደ ሉም። እንዲህ አይነት ባለሙያዎች መኖራቸውንም በዚያን ወቅት አናውቅም። ጉዳያችን ከአከተሩ ጋር ነው። ስሙን ብና ውቀው ማለፊያ፣ ባናውቀው ራሳችን ስም እናወጣለታለን። በተደ ጋጋሚ ሲኒማ ስለምንገባ በዘመናችን የነበሩትን አክተሮች ከሞላ ጎደል እናውቃቸዋለን።

የዛሬው ተራኪያችን ተረፈ ገልጆ ነው። ፊልሙን አላ የውም። ሙሉውን ታሪክ ቀን ከቀጪሳው አድምጦ ስለነበር ፊል ሙን ያየውን ያክል መተረክ ይችልበታል።

"አክተሩ ጆንዌይ ነው። ከአንዲት ትንሽ ከተማ ቤተሰቡን ተሰናብቶ ወደ በረሃው መጋለብ ጀመረ- ደራራም!... ደራራም!..." ከሲኒማው ጀርባ የሚሰማ ሙዚቃ መሆኑ ነው።

ተመልካቾቹ ዘና ብለን እንስቃለን፣ ገልጆ ይቀጥላል "በጉ ዞው ላይ አክተሩ ውሃ ጠማው። ኦካባቢውን ሲመለከት ዛፍ ቢጤ አየ። እዚያ አጠገብ ምንጭ አይጠፋም ብሎ ተጠግቶ ሲያይ እንደ ገመተው ሆነ። ከፈረሱ ላይ ዱብ ብሎ በእፍኙ እየቀዳ ይጠጣ ጀመር። ጠላቶቹ ሊያፍኑት አድፍጠዋል።"

"ተበላህ! ተባላህ!" ተመልካቾቹ ተንጫጫን።

"ሽጉጡን መዞ ጠላቶቹን ግቢሽው! ሊያደርጋቸው ፋታ አላገኘም።" ሽጉጥ እንደያዘ ሁሉ ገልጆ እጁን ፊት ለፊት ደገነና "ተረባረቡበት። በቦክስ አናፈጡት። በመጨረሻ ሽጉጡንና ፈረሱን ነጥቀው በረሃው ላይ ጥለውት ሄዱ።"

"ጠላቶቹ ከተማ ደርሰው እየበሉና እየጠጡ በሙዚቃ ይደ ሰታሉ፣ ይደንሳሉ። አሪፍ አሪፍ ሴቶች ረጅም ቀሚሳቸውን በእ ጃቸው ሰብሰብ አድርገው በኃይል እየሳቁ አብረዋቸው ይጨ ፍራሉ።

ሁለት ወንዶች ጠረጴዛው ላይ ክርናቸውን ተክለው መዳፍ ለመዳፍ በኃይል መገፍተር ግብግብ ገጥመዋል። በግራና በቀኝ የበራ ሻማ ቆሞ፣ ያሸነፈው ተጋጣሚውን የእጁን እይበሉባህን በእሳቱ ቅጥል ያደርገዋል። በመጠጥ ደንበኛን ሙሉ ቢኖ መጨ ረስ አለመጨረስ የሚወዳደሩም አሉ... በዚህ መሃል የሴቦቹ አለቃ ትከሻውን መታ መታ ይደረጋል። አገር ሰላም ብሎ ዞር ሲል አገጩ በቦክስ ይነረታል። እንደኪስ ወደ ላይ ተለግቶ መሬት ይዘረራል። መቺው ጆንዌይ ነው።"

ጭብጨባውም ፉጨቱም ልክ እንደ ሲኒማ ቤቱ ይቀል ጣል።

"ጆንዌይ ቴክሱ በሽጉጥ ጠላቶቹን ይቆላቸው ጀመረ። ምድር ቁና ሆነች። ተንጫጩ ያ ሁሉ ጭፈራ ወደ ኡኡታና ጩኸት ተለወጠ። ጆንዌይ ማንም አያመልጠውም፣ ሀሏንም ቅልጥም ቅልጥሚን፣ ጭንቅል ጭንቅሏን እያለ ዋጋዋን ሰጣት።"

አሁንም ጭብጨባው፣ ፉጨቱ ቀጠለ።

"ጆንዌይ ጨርሷቸው ሽጉጡን ሽክርክር አድርጉ ወደ ሰገ ባው ይመልሳል።" አለና ገልጆ ደረቱን ነፍቶ እጆቹን መዳፍ በሰ ፊው ከፍቶ አስተዋለን። "አንድ በማጣጣር ላይ ያለ ጠላቱ ከወ ደቀበት በርሜል ስር እንደምንም ተጎትቶ ተነሳ። በእጁ መዋ ረቢያ ይዟል!...

"ተበላህ! ተበላህ!" ተመልካቾች ጮኸን።

"ሰምቷችኋል!! ድንገት ዞር አለና ሽጉጡን ላዋ አድርጎ ግቢሽው! አደረገው።"

"ወይኔ! ቹላ ከፍዬ ሲኒማ ቤት ከማይ ለገልጆ ክርክ ከፍዬ ባዳምጠው ይሻለኝ ነበር። እንካ ዲናሬ" አለና ቁልጭ ወረ ወረለት።

ገልጆ ቀለባትና "ቴንዮ!" ብሎ አምባሻውን ሊገዛ ወደ አደይ ዝማም ቤት በሶምሶማ ሩጫ ተንቀሳቀሰ። (ሲኒማውን ስናይ ቆይተን Tempo ብሎ ሲፃፍ መብራት ይበራል፣ እረፍት ነው። ይህንን ገልጆ በደንብ ያውቃል)

"ኖ! ኖ! አታቁም። አውራልን። ከጨረስክ በኋላ ወርቁ ሻይ ቤት ወስጂ '*አቦሲታ' እጋብዝሃለሁ!" አለው ቁልጭ።

ገልጆ ተመለሰ። "ጆንዌይ ሲጋራውን አወጣና ከብሪቱን በጠላቱ መላጣ ጭንቅላት ላይ ጭሮ ለኮሰ። ሲያፏጭ ፈረሱ ከች አለች! ዘሎ ጉብ! በፈጣን ሙዚቃ ታጅቦ ሽምጥ ሲጋልብ ይታ ያችሁ!

"አርሞኒካውን እየነፋ በረሃውን አቋርጦ ተራራና ተራራ መካከል ሲደርስ ሬድ ኢንዲያኖች ከበቡት። እሱ አስቀድሞ *ሾፎአቸዋል። በብልቅጤ ..." አለን ገልጆ፣ 'ብልቅጤ' በአይኑ ቂጥ ማየት መሆኑን ለመግለጽ በተቀደደ ሰሌን ኮፍያው እጮልቆ እያየን።

"ከፊት ለፊቱ ሽምጥ እየጋለቡ የሚመጡትን አንድ በአንድ ቀለባቸው። ጨኸታቸው ፀጥ አለ። ከፈረሱ ላይ ዱብ አለና ቸብ ሲያደርጋት ፈትለክ ብላ ከጦር ሜዳው ገለል አለች። ሽጉጡ እንደሆን ጥይት አያልቅበትም።"

በሳቅ ሆዳችን ፈረሰ።

"ጆንዌይ ማመን በሚያስቸግር ቅልጥፍና ተገለባብጦ፣ ከተ ራራ ተራራ ዘሎ፣ ገደሉን በሸርተቴ፣ ሃይቁን በዋና አቋርጦ፣ በኃይል ሲያፏጭ ፈረሱ ከች! ሰትል ጉብ ብሎባት ሲጋልብ ሙዚ ቃው ሲያጅበው ከሰማይ ጋር ከገጠመው መስክ ላይ ሲደርስ 'ዘ ኢንድ ሆነ!"

"አሆሆሆ!" ለገልጆ አድናቆት ጎረፈለት። አድናቆቱን በፍ ቅር ሲቀበሉ የነበሩት ዓይኖቹ አንድ ቦታ ላይ አፈጠጡ። ዞረን ስናይ፣ የመሸሻ ጊዜ ሳይኖረን ከጉደቴ ጠጅ ቤት ውስጥ የጠጅ አንቡላ ተደፋብን። ከምናብ ወደ ገሃዱ ዓለም በመመለስ ብትን አልን። ተመልሰን ግን እዚያው ነን። አሁን ወደ ሕንድ ፊልም... "ሻካር!"...

---

*አቦሲታ፣ በአሥራ አምስት ሣንቲም የሚሸጥ አንጀራ በወጥ።
*ሾፎአቸዋል፣ አይድቸዋል።

የልደት ስጦታ

ልጅህን በቀን አንዴ ግረፈው። አንተ ምን እንዳጠፋ ባታውቅም እሱ ያሰታውሰዋል።
የቻይና አባባል

ማርም ሬትም በነበረው ጓልጅነታችን ወቅት እኔም ሆንኩ አብሮ አደጎቼ ብዙ ጊዜ እንገረፍ ነበር። ተረፈ ገልጆ ግን አብሮ አደጐቹን ሁሉ በመወገር ያስቸነዳን ነበር። የወገራው አይነት የተሰያየ ነበር። አባቱ ጭካኔ የተሞላበት ቅጣትን ያውቁበታል። በርበሬ አጥነው ይወግሩታል። ይህ መአት የልብ አላደርስ ሲላ ቸው አሩን አርቶ እንዲበላት ያስገድዱታል። ገልጆ ቁርስ ምግው ራቱ ዱላ ነበር። አባቱ ማታ በአንዳች ምክንያት ሲወግሩት ሲያላዝን አምሽቶ ጠዋት ቅቤ የጠጣ ይመስል እያብለጨለጨና በራሱ ጭንቅ እየሳቀ እንዴት አድርጎ ከወገራው ራሱን እንደ ተከላከለ ይተርክልናል። ጭንቁን የሳቅ ሽማ አልብሶ ስለሚ ያወጋን መራሩን ሕይወቱን አስቂኝ ያደርገዋል።

«የሚገርም ነው። እኔ ደግሞ እጅ መንሻ እንዲሆነኝ የሲጋራ ቁሬ ስለቃችም ዋልኩ። ምን ቀረኝ፣ ካሊም፣ ከራቫን፣ ቫይስሮይን ጨምሮ ፊሊተር የሌላቸውን ቅጠለ ወርቅና ግሥላ ጭምር እንድ ፓኮ ሙሉ ከካምቦሎጆ ለቃቅሜለት ደጅ ቆሜ፣ እህቴን ፊርፍራ ጠቅላ እንድታቀርብለት ስጠራት የጠበቅኩት እሷን ሆኖ እሱ በሩን በረገደና እንደ ድመት ዘሎ እላዬ ላይ ጉብ አለና አንቆኝ እቤት ገባ። ከዛማ ምን ይጠየቃል ወገራውን ጀመረው» አለና ተረፈ ገልጆ ከልቡ ከትከት ብሎ እየሳቀ እሳቀን።

አባቴ ሲኒማ የሚወድ ልጁ ዱርዬ ይሆናል ብሎ ያም ናል። እኔ ደግሞ ሲኒማ ነፍሴ ነው። ሲኒማ ገብቼ ስመጣ ከቲነ ቃብኝ መወገሬ ላይታለም የተፈታ ነበር። በዚህም የሰፈራችን ሰዎች እኔና አባቴን መገላገሉ ሰልችቷቸው፣ ገና ድምፃችንን ከሩቅ ሲሰሙ "ኤጭ! ጀመሩ ደግሞ"! እያሉ ያማርራሉ።

አንዳንዴ ውስጤን ሳያጣራ ወገራውን ይጀምራል። ድንገት አንድ እንግዳ ሰው ደርሶ ይገላግለናል። ጉዳዩ ተጣርቶ የጥፋት ቀስት አባቴ ላይ ሲያነጣጥር፣ ይገርፍበት የነበረውን ቀበቶ እየታ ጠቀ "ጋሼ አሁን አንድ ሁለቴ አሳርፌብሃለሁ። ምንም አይደ ለም። ሌላ ቀን አጥፍተህ ስትገኝ ከማሳርፍብህ አንድ አስር ጅራፍ፣ አሁን ያሳረፍኩብህን ሦስት ብትር እቀንስልሃለሁ።!"

"እ! *መጀመሪያ ላታጣራ ስምንድነው የምትመታኝ?*"

"ከጥፋት ስለማትርቅ ነዋ! አምላክ አንተን አጥፊ እኔን ደግሞ እረኛህ አድርጎ አጣምሮናል። እኔስ ምን ላርግ? ፈርዶብኝ

ነው።መጥፎ ከብት ቢሆን ታርዶ ይበላል፣ ወይ ይሸጣል። እንደ አንተ አይነት መጥፎ ልጅ ግን ምን ይደረጋል?"

"ለምን ዛሬ ተመታሁ?" በኃይለ ቃል እጠይቃለሁ።

"አንተ! እኔ ላይ ነው የምትጮኸው!? ይሔ ራሱ ሊያስ ቀጣህ ይችላል። የቅድሙን ምህረቴን ሰርዤዋለሁ። በል ቶሎ ውሃ ቅዳና በብርጭቆ አምጣልኝ ጠምቶኛል!" ይጮኻል።

"እንሰራው ውስጥ ያለው ውሃ ክፍት ያደረ ነው"

"ገፈርሳን ማን ከደነው?!" ይጠይቀኛል በኃይለ ቃል። ያዘዘኝን ተግባራዊ አደርጋለሁ።

እኔም ሲኒማ ከመተው ሞቴን መርጫለሁ። አባቴም ሲኒማ በዞረበት ዳግም እንዳልዞር ስማድረግ በቀበቶ፣ በአርጩሜና በክ ርን እያፈራረቀ ይነርተኛል።

ፊረንጆች "ድልድዩን ስንደርስበት እንሻገረዋለን" እንዲሉ፣ እኔም ዛሬ ለወገራው እንደምደርስበት ተማምኜ ከጓደኞቼ ጋር እያወጋሁ ደስ ብሎኝ ወደ ሠፈር ጉዞ ጀመርን።

መርካቶ ውስጥ የሚተራመሰውን ሕዝብ አየሁና "ወይኔ ሽጉጥ በኖረኝ!" ስል በስሆሳስ ተናገርኩኝ።

ቀጪላው ሰምቶኛል።"ላጥ ታደርግና ግምሽው! ግምሽው! እያደረከ ታተራምሰዋለህ። ይታይህ ያን የተሸከመውን ሰውዬ ከአናቱ ላይ ቅርጫቷን ስትቦድሳት እንዴት እንደሚሮጥ!"

በጣም ሳቅን።

"ልክ ስታፏጭ ነጭዋ ፊረስህ ከች! ትላለች። እላይዋ ላይ ዘለህ ጉብ ብለህ በጭድ ተራ በኩል ወደ ሰፈራችን ቁርቆስ ሽው! ማማሚያ! ላንታ ግሪያ!"

አነጋገራችንም፣ አኳኋናችንም ተለውጧል። ምኞታችን እን ዳለች አክተሮቹን መሆን ነበር። በእንዲህ አይነት ስሜት ውስጥ ካለን ወሬው አያልቅም፣ አካላችንም አይዝልም። አይደክመ ንም። ሆዳችንን በልዩ ቀዶ ሕክምና ያወጡት ይመስል አይር በንም።

የካራቴው አክተር ዋንጊዩ፣ የቴክሱ ፊልም ኮከብ በርትራን ካስተር፣ ከሊንት ኢስትውድ የሕንዶቹ ራጂሽ ኩማር፣ ሐሚትሃብ፣ ሂማማሊን፣ ሌሎቹም የጓደኞቻችንን ያህል የምናው ቃቸው ናቸው። አሁን ደግሞ ሻካር ስለተባለው የህንድ ፊልም ወሬ ጀመርን።

በተክለሃይማኖት አርነን በልዑል መኮንን ሆስፒታል አቋር ጠን፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቴአትር አልፈን፣ ለገሀር ደረስን። አሁንም እየተከራከርንና ጮክ ብለን እያወራን ነው። ድልድዩን አለፍ እንዳልን "ያ ፉንጌ አይደለም? ባለቀዩ ሹራብ" ጮክ ብላ ስትናገር ገነትን ሰማኋት።

ከእኔ ጓላ መኩዩ ቀጫጫው፣ ሲሳይ ጎቢጥ፣ ቀጪላው፣ ሴምላል፣ ቦቸራ፣ ዶጅ ገማጣው፣ አብነት ባሪያው፣ ኃይሉ ዶሮ፣ ሻቃ፣ ይጥና... እየተግተለተሉ ነበር።

በዕለቱ ሰፈራችን በጠላት እንደተወረረ ፀጥ ብሏል። ሲኒማ ለማየት መሄዳችን ታውቋል። ይህንን ሁሉ ጥበብ ስናይ የዋልን ሕፃናት አንዱም ምትሃተ ጥበብ ሳይረዳን ታፍሰን ሃምሳ አለቃ አርአያ ቤት ለምርመራ ገባን። ተመስገን አልኩኝ። ወገራው በጎብረት ከሆነ ቀለል እንደሚልልኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

ብልሁና ሩህሩሁ አባባ አርአያ ምርመራውን ጀመሩ። ከመ ካከላችን በጣም ፈሪ የሆነውን ፍቀጢሳውን ጠሩት። እውነቷን መናዘዝ ጀመረ። ንፍጡና እንባው እየተዝረከረከ፣ አሰር አሰር ጊዜ እየማነለት፣ ወንጀል ወንጀላቸንን አከፋፈለን።

ጡረተኛው አባባ አጋፋሪ ሲኒማ የገባነውን ልጆች ቆጥ ረውን፣ በነፍስ ወከፍ ያጠፋነውን ሽልንግ ደመሩትና በሀይል ጮኸው "አምስት ብር እኮ ለእኔ የወር ቀለቤ ነው! 25 ኪሎ ጤፍ ወርቅ አድርጎ ይሸምትልኛል። ያውም የኩሊውን ወጪ ችሎ። ቆዳ መልስ በግ ልረድ ብል ተንቀባርሬ ፍሪዳውን የምጥ ልበትን ገንዘብ ነው ያጠፉት። ሃምሳ አለቃ፣ እነዚህን ፍጀቸው!"

አባባ አርአያ ፈገግ ብለው አጋፋሪን እየተመለከቱ "ረጋ በል አጋፋሪ! ለፍርድ አትቸኩል!" አሉና ወደ ቀጢሳው ዞረው ሲያዩት "ሲኒማ የገባነው ሆያሆዬ በጨፈርንበት ገንዘብ ነው። ሲኒማ ቤቶቹን ያሳየን አብነት ነው" አለና ታላቅ ወንድሙን አጋፈጠ።

የአብነት እናት እማማ ልኬለሽ ከጓላው ቆመው ለለነበር በጥፊ ልጃቸውን አጮሉት። አብነት ጮኸ፣ እያጉረመረመ ወንድሙ ላይ አፈ ጠጠ።

"ተዉ መማታት ክልክል ነው። የዱርዬው ልጅ ማንነት ሥረ መሠረቱ ከተጣራ በኋላ ጠባይ ማረሚያ እንልከዋለን። ከዱርዬ ልጅ ጋር እዚህ ማን ይዳረቅል? ዕድሜ ለተፈረ! ጠባይ ማረሚያ ገብቶ ረቂቅ ልጅ ሆኖ ይመጣል።" አሉ ሃምሳ አለቃ አርአያ የላይ የከንፈራቸውን ጢም እያፍተለተሉ። እንደገና ወደ ቀጢሳው ዞሩና በጥያቄ ያጣድፉት ጀመር። "ምን በልታችሁ ዋላችሁ?"

"ሆያሆዬ ጨፍረን ያገኘነውን ዳቦ።"

"ወይኔ ሙልሙሌ! ወይኔ ሙልሙሌ! ለእነዚህ ዱርዬ ዎች ነው ያንን ትልቅ ሙልሙሉ የሰጠኋቸው"! እማማ በለጡ ገጠ በንዴት ተናገሩ።

"ዝም በሉ!" ተቆጡ ሃምሳ አለቃ አርአያ። "የነገሩን ውል ለማጥፋት ነው የምትሽቀዳደሙት?!" ብለው ወደ ምርመራቸው ተመለሱ።

"ፉንጌ፣ ና!" አሉኝ አባባ አርአያ።

አባቴ እቤቱ ውስጥ አንዱ ጥግ ቆሟል። ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶታል። በጎብረት የሚደረገው ምርመራ ስላላረካው በግሉ ቤት መስዶ ሊመረምረኝ ጐረቤቶቻችንን ጠየቀ። አባባ

አርአያ አልፈቀዱለትም። አንዴ ጮኸና ላብ አድርጎኝ፣ ገላጋይ መሐላችን ከመግባቱ በፊት አንድ ሁለት ጊዜ ደህና አድርጎ ጀር ባዬን ደለቀው። እኔም የድረሱልኝ ጩኸት ሳሰማ እንደተለመ ደው ስላልሆነ መንደርተኛው ግር አለው። በጭንቅ ላይ የነበሩት አብሮ አደጐቼ የማንን የአጯጯህ ስልት እንደተጠቀምኩ ለለገባ ቸው ሳቁ። እንደ ዋንጊዩ ነበር። የጀግንነት ስሜት ተሰማኝ። ቀጢሳውን ገላመጥኩት።

"ተቃጠልኩ! ተቃጠልኩ! ምኑን ልጅ አለኝ እላለሁ?! ምኑን ዘር እፈራሁ እላለሁ?! አገር አሸባሪ ዱርዬ ወልጄ" አባቴ ለገላጋይ አስቸገሩ። እኔ ግን እንደ ልብ በተትረፈረፉ ገላጋዮች መካከል ስለነበርኩ ምንም አልፈራሁም።

የተሸበረው እንዲረጋጋ፣ የተቅለበለበውም እንዲያስተውል አባባ አርአያ ምክር ለገሱ። ልጆቹን መደብደብ ማደደብ እንጂ እርባና እንደሌለው ገልጸው፣ በጥፋተኝነታችን ይቅርታ እንድን ጠይቅና የወላጆቻችንን እግር እንድንስም ተደርጎ እርቀ ሰላም ወረደ።

ሁለተኛ በሲኒማ ቤት ደጃፍ ዝር አንልም ብለን ማልን። ይሁን እንጂ መሐላችንን ችላ ብለን በተናጠልና ከሚግባቡን ልጆች ጋር እየተሻረክን በስውር መዝናናቱን ተያያዝነው።

በልጅነቴ የመገረፍ ልምዴ በጣም እየዳበረ በመምጣቱ፣ በምገረፍበት ወቅት ምን አይነት ብልሃት ብጠቀም ከዱላው ውር ጅብኝ ራሴን ማዳን እንደምችል አሳምሬ አውቅ ነበር። ይሁን እንጂ አንዳንዴ ውጥኔ ከሽፎ ከማልወጣበት ወጥመድ ውስጥ እገባለሁ።

አንድ ጥፋት አጥፍቼ አባቴ ቀበቶውን መፍታት ሲጀምር እኔ እየጮኽኩ እወተውታለሁ። ይህ ውትወታዬ ትኩረቱን ስለሚ ያበላሽበት "መቼ ነካሁህ? ገና ሳላሳርፍብህ? እንዳሳረርከኝ ሳላሳ ርርህ!"

"ሁለተኛ አይለምደኝም! በጎብርኤል" እያልኩ በመለኮት የሚያልፍ መንደርተኛ አስተውሳለሁ።

አባቴ እያላጋጠብኝ "አሄሄ! ዛሬስ ተይዘሃል! የአባቴ አምላክ አይለመነኝ ልክ ሳላስገባህ አታመልጠኝም" ብሎ ሊያባር ፍብኝ ሲቃጣ፣ ቀበቶውን ለቀም አድርጌ ያዝኩና "ወይኔ ሊገ ድለኝ ነው!"

"ድብን በላት!" ነጥቆኝ አሳረፈብኝ "ዛሬስ ተገኝተሃል። ማንም ከእጄ አያወጣህም። ድብን እንዳደረከኝ እርር ድብን ሳላደረግህ!?" ብሎ ድጋሚ ሲቃጣ የክርስትና አባቴ አባባ ኃይሌ ከኋላ ቀበቶውን ለቀም አደረጉት። "ምንድነው?!" በጎርናና ድምፅ ጠየቁት። የተለኩሰ ግለላ ሲጋራቸውን በግራ እጃቸው ይዘዋል።

"ምን፣ ከእነዚህ ዱርዬ ልጆች ጋር አትግጠም ብለው እምቢ ብሎ" ብዙ ምዕራፍ እንደ ሮጠ ሁሉ ሜን ሜን እየተነፈሰ ወንጀሌን ይዘረዝራል።

"ኤድያ! አንተ ደግሞ! ትናንት አጥፍተው ተገርፈዋል። ከልጅ አትግጠም ብትለው እሺ ይልሃል? በል ተወው!" ብለው ገስጠውት ወደእኔ ዞረው፣ ደም የጎረሰ አይናቸውን አፍጥጠውብኝ እያዩኝ "ፉንጋ! የሚነገርህን አልሰማ ብለሃል? ዋ! ብታርፍ ይሻል ሃል።" በማለት ያስጠነቅቁኛል።

እንዳንዴ ገላጋይ ይጠፋል። አባቴ አንገቴን በጭኑና ጭኑ መካከል ይይዝና ቂጤን የበላ የጠጣውን ያህል ያሳርፍበታል።

እጁ እስከሚዝል ይነርተኛል። "ልክ ፖስቴ ስትበላ ደስ እንደሚልህ ሁን፣ ያኔ አያምህም" የሚለኝ የገልጆ ምክር ይኼን ጊዜ ዘጣም ጠቃሚ ነበር። በጣም ከፉሁኩኝ ስታዬን ቀለል ያደ ርገዋል። አንዳንድ ሩህሩህ ጎረቤትም ጩኸቴን ሰምተው በፍጥነት ይታደጉኛል። እንዲህ በጥድፊያ የሚካሄድ ፋታ አልባ ወገራ ውስጥ ብሆንም ከውጪ የሰዎችን ድምፅ ከሰማሁ አለያቸዋለሁ።

"እማማ በለጡ!" ትንፋሽ አጠረኝ።

"ምን ነካችሁ?" ይጠይቃሉ።

በሩ ተቀርቅሯል።

"አሄሄ! ዛሬስ ተገኝተሃል!"

"ወይኔ! ተቃጠልኩ!"

"ተቃጠል እንዳቃጠልከኝ!"

"ገደለኝ ኡ! ኡ! ኡ! ኡ!"

"እሰይ! አንጀቴ ቅቤ ጠጣ!።"

"ኡ! ኡ" በሕማ አምላክ!"

"ጉሽ! ጋሼ! ፖሊስ ጠራህ?" ብሎ በአዲስ ጉልበት የበትሩን መአት ማውረድ ይቀጥላል።

"ወይኔ ቆለጤን! ወይኔ ቆለጤን!" ፊቴ በላብና በንፍጥ ተለውሷል። እንዲያምነኝ በኃይል ተፈራገጥኩ።

አባቴ "ፀጥ በል! አሁን መቼ ነካሁህና ነው?" ብሎ ጮኸ ብኝ። ደንግጠ መጋረፉን አቆመ።

የመሸበር ገጽታ በፍፁም ሳያሳየኝ "እንኳን ቆለጥህ ለምን ነፍስህ አትፈርጥም!?" ብሎ ቀበቶውን አልጋ ላይ ጣለ። በጭኖቹ ያነቀኝን አንገቴን ለቆ "እግርህን ክፈት!" አለ፣ ሕክምና ሊጀ ምር። "ፀጥ በል! አሁን መቼ ነካሁህና ነው?"

"ዜራሞ፣ ክፈት ብዬሃለሁ!!" እማማ በለጡ በሩን የመስበር ያክል እየጮኑት ነው።

አባቴ "ፀጥ በል! ትንፋሽህን ዋጥ! አፍህን ያዝ! አትተ ንፍስ! ዋጥ! ትንፍሽ እንዳትል!" ሲለኝ፤

በቅልጥፍና ትእዛዙን ፈጸምኩ፣ ሳግ ግን አለቀቀኝም።

"አሄሄ! ይህቺ እልህ መጥፊያህ ነች። ትንፋሽህን ዋጥ ብዬሃለሁ!"

"ይሄ ጋንድያ ዶርዜ ልጁን ሊገለው ነው እንዴ? ክፈት ብዬሃለሁ፣ ዜራሞ!"

አባቴ በሩን ከፈተ። እናቴ ትንሽዋን እህቴን ታቅፋ እያባ በለቻት ወደ ጓዳው መተላለፊያ በር ላይ ኩርምት ብላ ተቀምጣ ታስተውለናለች። እንዲህ አይነቱ ስሜት የሚታይባት አላግባብ ስገረፍ ነው። አባቴን ላለመቃወም ያክል "እሱ ተው ሲሉት እይሰማ። እኔ ታዲያ ምን ላድርግ? ይበለው!" ትላለች። አጥፌ ሆኜ ከተገኘሁ ግን በቅርብ ርቀት ቆማ ወይም ተቀምጣ እያንዳንዷ የምታርፍብኝ ብትር የቱጋ መሆን እንዳለበት ታመክ ራለች። "በለው! የታባቱ! ተው እንደሱ አይደለም! ቂጥ ቂጡን! ተው ከፍ አልክ! ምን አይነት የጅል ቅጣት ነው?! ዓይኑን መትተኸው ነበር! ቂጡን እያልኩህ!"

በጥቆማዋ መሠረት "ወይኔ ዓይኔን!" ብዬ ጩኸቴን ሳቀል ጠው አባቴ መግረፉን ያቆምና ሁለቱም የመጀመሪያ ዕርዳታ ሰጪዬ እንዲሆን አደርጋለሁ።

የአባቴ አቀጣጥ ውርጅብኝ የበዛበት ቢሆንም ከእማዬ አነ ራረፍ ሺ ጊዜ እመርጠዋለሁ። እሷ ለመማታት በፍፁም አት ቸኩልም። "ተው!" እያለች ታስጠነቅቀኛለች። እጥፊነቴን ከቀ ጠልኩ እሁንም ዕርጋታ ሳይለያት በማስጠንቀቂያ ታልፈኛለች። አሻፈረኝ ካልኩ አስገራሚ በሆነ ቅልጥፍና ማማሰያዋን ሳብ አድ ርጋ ጣቶቿ ላይ፣ ወይም ቁርጭምጭሚቴ ላይ ቂ! ስታደርገኝ ነፍስና ሥጋዬ ይላቀቃሉ። ትንፋሼ አጥሮ በረጅሙ ስቤ ጩኸ ቴን በኃይል እለቀዋለሁ። ድጋሚ ሳታሳርፍብኝ ታላግጥብኛለች። እርር ድብን አድርጎኝ መሬት ላይ እንፈራገጣለሁ። በዚያ በማ ውቀው ፍጥነትዋ አንዴ ቂጤን ዝለጥ ስታደርገኝ መጮኼን አቁሜ መከላከል እጀምራለሁ።

አሰፈሪ በሆነ ግርማ "ተነስ! አትበሳበስ! ማን መሰልኩህ? እኔ ባሎቴ ነኝ እኮ!" ስትለኝ፣ ነጥሬ ቀጥ ብዬ እቆምና አመቺ የማልቀሻ ቦታ እፈልጋለሁ ...

...ዛሬ ስገረፍ ግን እሷ ከፍቷት ኩርምት እንዳለች ተቀ ምጣ ታያኛለች።

"ልትገለው ነው እንዴ!?" እያሉ እማማ በለጡ በሩን ከፍ ቶላቸው ገቡ።

አካላቴን እየደባበሱ ያባብሉኝ ጀመር።

"የታባቱ ይኼ ምናምንቴ! አቃጠለኝ! ተቃጠልኩልሽ በለጡ!" ብሎ አቤቱታውን አሰማና "ቆይ! የቀረኝ አንድ ነገር ነው። እንደ ተረፈ ገልጆ አርሀን ባላበላህ! እኔ ዜራሞ አይ ደለሁም!"

በፍርሀት ጮኹኩኝ።

"ፀጥ በል!" አለና አፈጠጠብኝ።

ትንፋሼን ዋጥኩኝ::
"ተወው በቃህ!" አሉ እማማ በስሙ::

...ተረፈ ገልጆ የደረሰበት መአት በሃሳቤ መጣ:: ገልጆ አንድ ቀን ረሃብ ከፉኛ ጠናበት:: ከሰፈራችን ልጆችም የሚሰጠው ጠፋ:: በዚህ መሃል ይጥና መጣና ዲናራ ሰጥቶት እንቁል ልጮ እያሰን ለመግመጥ ቅስቴ ከወርቄ ሻይ ቤት ገዝቶ እን ዲመጣ ገልጆን ላከው:: ከታርዉ ገልጆ በርሮ ሁሰቱን ፓስቴ ገዝቶ መጣ:: ይጥና "ለትል!" አለና ቆንጥሮ ጣለስት:: (በዚያ በልጅነታችን ዕድሜ አንድ ፓስቴ ሰብቻው መብላት የፈለገ ልጅ፣ አፍጠን የምናየውን ልጆች ዓይኖች ቅልውጥና መቀልበሻ "ለትል" ብሎ ቆንጥሮ ይጥልና የተቀረውን ያጨረግዳል:: ዝም ብሎ የበላ ግን ሆዱን ያመዋል ብለን እናምናለን::) ገልጆ ተወርውሮ ብጣቂዋን ፓስቴ ቀለባትና አፉ ውስጥ ወረወራት:: ይጥና ዓይናችን እያየ ዝም ብሎ መግመጥ ጀመረ:: ገልጆ ረሃቤን ቢያስታግስልኝ ብሎ እነ ዶሮ ጊቢ ውሃ ሊጠጣ ሄደ::

ይጥና ሰሁስተኛ ጊዜ ፓስቴውን ገመጠ:: ለአፉ አልከብድ አሰው:: ገርሞት ፓስቴውን ከፍቶ አየ:: ገልጆ እንቡጠቹን ከፓስ ቲዎቹ ውስጥ ፈልፍሎ በልቷቸዋል:: ነገር ግን በጥንቃቄ መልሶ ስሰገጠመው ፓስቴው ሲያዩት መሰንጠቁ አይታወቅም:: ይጥና እንደነቃ ደንግጦ ገልጆ ውሃ ጠጥቶ ሲመጣ ጮኸበት::

"አንተ ክላስኝ በኋላ ቆንጥረህ እንደማትሰጠኝ ሰለማውቅ የተላኩበትን ነው ዕምቡጡን አውጥቼ የበላሁት::" አለና ተረፈ ገልጆ አፈጠጠበት:: ይጥናም የጉልበቱን ልክ ያውቃልና አጉረምርሞ ዝም አለ:: የዚያን ዕለት መንደርተኛው ገልጆን ምንም ሳይል ከው ዋለ:: የተሰጣ ክክም አልነበረም:: በመንደራችን የሚገኙ ማድቤቶችን በፍጥነት አሰሳቸው:: የሚመነተፍ አልተገኘም::

ትዝ ሲለው አባቱ መሬት ቆፍረው ገንዘብ የሚቀብሩበት ጉድጓድ አለ:: ከዚያ ላይ ለረሃብ ማስታገሻ የሚሆነውን ያህል ገንዘብ ለመመንተፍ ወሰነ:: ጉድጓዷን ምሶ እጁን ሰደድ ሲያ ደርግ ድፍን 20 ብር አጁ ገባ:: መልሶ ሌላ ፈስገ:: አስር ብር አገኘ:: ጉርጓዷን በጥንቃቄ እንደነበረች ደፈናት::

የሰፈር ልጆችን በሙሉ አስከትሎን ወደ ወርቄ ሻይ ቤት ሄድን:: ሁለት እንጀራ በወጥ አንድ ላይ አስቀረበና በላ:: አንድ ሳህን ድንች፣ ሁለት ፓስቴ ጨመረበት:: አንድ በራድ ሻይ እዘ ዘና እስኪቀርብለት፣ አንድ ሲሮኮ አስከፍቶ ጠጣ:: አስገሳው:: በራዱ ሻይ እንደቀረበ አንድ ቡሽ ሰራሱ አስቀድቶ እኛንም ጋበዘን:: ስእሁቱ ሦስት ፓስቴ በቀጢሳው ላክላት:: ለሱም "እየጨረገድክ ሂድ!" ብሎ ሁለት ፓስቴ ገዛለት:: ቁጭ ብለን ለምናየው ሁለት ሁለት ፓስቴና ሻይ ጋበዘንና "ከዛሬ ጀምሮ ከአባቴ ጋር አልኖርም:: ካምቦሎጆ በረንዳ አዳሪ ሆኜ እኖራለሁ:: ትንሽ እንግሊዘኛ ብችል

ሰፈረንጆች እየተላላኩ አድጋለሁ:: ከዚያም ስፖርተኛ እሆናለሁ:: ዛሬ ፓስቴ እንደገዛሁላቸሁ ሰማንም እንዳትናገሩ" አለንና ገልጆ ከሻይ ቤቱ ስንወጣ ተሰነባብተን ወደ ካምቦሎጆ መንገድ ጀመረ:: እኛ ወደ ሠፈራችን ተመለስን::

ትንሽ እንደተራራቅን ተመልሶ "ከእናንተ ጋር ትንሽ አውርቼ ብሔድ ይሻለኛል፤ ሰፈራችን ሄደን ትንሽ እንጨዋወት:: ካምቦሎጆ ብኖርም ቀን ቀን እናንተጋ እየመጣሁ እጫወታለሁ:: እህቴንም እጠይቃታለሁ:: አባቴን ግን በቃ፤ ሁለተኛ ላገኘው አልፈልግም::" እያለን ሠፈራችን ደረስን::

አዘውትረን ድድ በምናሰጣበት በእማማ ጎደቴ ጠጅ ቤት በረንዳ ውሃ ልክ ላይ ተኮለኮልን:: የውሃ ልኩ ቀን ፀሐይ ሲመታው ስለሚውል ማታ ሲቀመጡበት ይሞቃል:: ቁልሞ፣ አመደ፣ ላሪቾ፣ አብነት፣... ተሰባሰብን በጠፈ ወሬያችን መሐል አንድ አይነት እሩምታ ከጠጅ ቤቱ ውስጥ ተሰማ:: ተደናግጠን ተነሳን:: አንዱ ገልጆን አንቆት መሬት ወድቋል:: ስናስተውል አባቱ ናቸው:: ተነስተው ገልጆን መሬት ስመሬት እየጎተቱ ወደ ቤታቸው ወሰዱት::

እቤት እንደገቡ ጠልፈው ጣሉት:: ከጣራው ማገር ጋር ቀድመው ባዘጋጁት ገመድ ጠፍረው እሥረው ቁልቁል ሰቀሉት:: እህቱ ሠናይት ከሰል እያቀጣጠለች ነበር:: አባትየው ታላቅ ተግ ባር እንዳከናወኑ ሁሉ ግዳያቸውን ቆመው ቁልቁል አዩትና ከት ከት ብለው ሳቁ:: ገልጆ የግልብጥ አባቱን ሽቅብ እያየ እንዲ ምሩት ይወተውታል:: ጉማሬ አንስተው ቅጣቱን ጀመሩ:: የገልጆ ሕመም ተጋብቶብን ጮኸን:: አባትየው ዞረው ሲያዩን በሩን የሕፃናት ጭንቅላት ሞልቶት አስተዋሉ::

"ዞር በሉ ከዚህ እናንት ሌቦች!" ብለው በአውሬ ድምፅ ገስጠውን በሩን ዘጉት:: በጭራሮ የተሠራ ይመስል በሩ ብዙ ቀዳዳ ነበረው:: በዚያ አንዳችን በሌላው ላይ ተደራርበን እናያለን:: ወከክ ባለው የከሰል ፍም ላይ በርበሬ ተጨመረበትና ገልጆን አጠኑት:: በኃይል እየሳለ ውተወተ:: አንድም የቀረው የቅዱሳን ስም አልነበረም::

"የወሰድከውን አንድ ባውንድ ምን አደረክበት?"
"እርቦኝ ወስጃለሁ!"
"ምን አደረክበት?"
"እርቦኝ ፓስቴ በላሁበት"
"ፓስቴ በላህበት?!"
"አዎን ፓስቴ በላሁብት!"
"በሁሉም ብር?"
"አይ! በሦስት ብር ብቻ::"
"የሶስት ብር ፓስቴ ጨረስክ?!" ድምፃቸው በድፍን ቂርቆስ አስተጋባ "ከነማን ጋር?"
"ለብቻዬ!"

ከስቀለበት አወረዱት። እዚያው ማጅራቱ ላይ ቆመው "አርህን እራ!" አሉ። እንዳሉት አደረገ። አይነ ምድሩ በኩሶ ትል ተጊጣለች። እንፋሎቱ አወዳቸው።

በርበሬ ዓይናቸውን እያጉረጠረጡ "አንሳና ብላት!"

ተግደረደረ። ጉማሬያቸውን ጀርባው ላይ እሳረሱበት። ጮኽ ተነሳ። አንቀው ቁልቁል ደፍተውት "አንሳና ብላ!"

"እሺ! እሺ! እበላለሁ!"

"አንሳና ብላት! አንትሥምናምንቱ! ብላት!"

ዓይነ ምድሩን አነሳ።

"ብላት!"

የእኛ ዓይን በንዴት ተጎልጉሎ ወጣ። አላስቻለንም። በኃይል እየጮኸን በሩን በድንጋይ መምታት ጀመርን።

"አትበላትም!?!" አሉና በጉማሬው ገረፉት። ዓይነ ምድሩን እንደጨበጠ ተንሰቀሰቀ።

"ብላት ብዬሃለሁ! ብላት!"

አባትየው ጩኸታችን ስላም ስለነሳቸው በሩን ከፈቱ። ብትን አልን። በሩ ተመልሶ ተዘጋ።

በዚህ መሐል አባባ አጋፋሪ መጡ። በቅዱሳን ስም መማፀን ጀመሩ። ለምላሻቸው ገልጆ አካል ላይ አለንጋ ሲያርፍ በኃይል ሲጮኽ ተሰማን። አባባ አጋፋሪ ልክ ራሳቸው አካል ላይ እንዳረፈ ሁሉ ስቅጥጥ ብሏቸው "ኧረ! በመብርሃን በወላዲቷ ይገር ሃለሁ! የተረፈ አባት፣ ተው ግፍ ነው!"

ክውስጥ "ጥፋ ከዚህ አንተ መላጣ!" አሉ የገልጆ አባት።

አጋፋሪ መለማመጣቸውን ትተው "ማንን ነው መላጣ ያልከው? አንተ ድጥ ራስ! ልመለጥም ልላጥም፣ እኔስ ለሀገሬ የሚገባኝን አከናውኜ እንጂ እንዳንተ ለሃጩን እያዝረበረብኩ..." ሲሉ በሩ ተበረገደ። ቀድሞ መቀርቀሪያ ብቅ ብሎ ታየ። መኳፎ ቀጫጫው እንደ ወፍ ቱር ብላ ጄዳ በቅርብ ካለው አባባ አጋፋሪ ቤት ገባችና ከስሩ ድቡልቡል ብረት ያለውን ከዘራቸውን ይዛ መጥታ አቀበለቻቸው። ቦቸራና ዶጅ ገማጣው ትልልቅ ድንጋይ አነሱ። የገልጆ አባት ዘው ብለው ከቤታቸው ሲወጡ የቦቸራ ድንጋይ ደረታቸው ላይ ነጠረ። አባባ አጋፋሪ የገልጆን አባት በከዘራቸው ሲገርልጡዋቸው ተዘረሩ። ገልጆ ዓይነምድሩን እንደ ጨበጠ ፈትለክ አለና ክሲኦሉ ወጣ። ዳግም ወደ እዚህ ቤት አልተመለሰም። እንደወሰነው ከካምቦሎጆ በረንዳ አዳሪዎች አንዱ ሆነ...

...ከሃሳቤ ተመለስኩ። የቆጠቆጠኝን ሰንበር እያስታመምኩ አማማ በለጡ "ፋንጋይ፣ ጥፋተኛ ነህ። አንተ ድውር ካላዳወርክ እሱ ሽማ ካልሠራ ምን ይበላል?" ብለው ወደ አባቴ ተመልሰው "አንተም ሥራን ቀስ በቀስ እንጂ በአንዴ ልመድ አትበለው። የልጅ መንፈስ መሆኑን አትርሳ!" አሉና አግባቡን።

ቀጣዮቹ ዕለታት ለእኔ የኩርፊያ ጊዜያት ናቸው። አባቴ ግን በባሕርዩው መኳረፍን አይወድም። እኔ ደግሞ ከጠላሁ ገለል ማለቱ ሰላም ይሰጠኛል። በዚህ ገለልተኝነቴ የተናደደው አባቴ አንድ ቀን ሞቅ ብሎት መጣ። ያለፈና እርቀ ሰላም የወረደበት፣ ይቅር ለእግዜሃር የተባባልንበትን ጉዳይ አንስቶ ነገር መፈለግ ጀመረ።

ይሄን ጊዜ እናቴ ከእኔ ጎን ቆመች። ፀቡን አክርሮት ሲገርፈኝ ሲል ጮክ ብላ "ተወው ባክህ! ዛሬ የተወለደበት ቀን ነው።" አለችው። ቀበቶውን እያጉረመረመ ታጠቀ። በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች ልጅ በተወለደበት ቀን ከተገረፈ ዓመቱን ሙሉ ያለቅሳል ብለው ስለሚያምኑ በልደታችን ቀን አንገርፍም።

ወላጆቼ እገረፍበት የነበረውን ምክንያት አሁን ቢጠየቁ አንዱንም አያስታውሱ ይሆናል። እኔ ግን ቻይናውያን እንዳሉት በየቀኑ የተገረፍኩበትን ምክንያት እነሆ! እንዲሁም ምርጧን የልደት ስጦታዬን እስካሁን አልረሳኋትም።

ሌባና ፖሊስ

እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ
ሰው ሁሉ የሚያውቀኝ
የምወደው ሰሺር ነው
ማነው የሚሰጠኝ?
ሰሙ እላችኋለሁ
ሰሙ እላችኋለሁ
ትምህርቴን እማራለሁ
ልጅ ሁሉ ያጠፋል
በአለንጋ ይገረፋል
አንዱ ሲለበልብ አንዱ ይጣፍጣል
ሁለቱም ያስፈልጋል ልጅንም ያሳድጋል

የሰፈሬ ልጆች እያዜሙ ሲጫወቱ ቤት ውስጥ ሆኜ ይሰማኛል። እኔ ባለፈው ስሞን ሦስት ስሙኒ ሠርቄ በመያዜ ክፉኛ ተገረፍኩ። በዚህ መዘዝም የአልጋ ቁራኛ ሆኛለሁ። ለዚህ ሁሉ ሥቃይ የዳረገኝ አብሮ አደጌ ባሪቾ ነበር። ባሪቾ 'እጀ ወርቅ' ነው። ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ ሲኒማ ልንገባ ራስ ቴያትር ሄድን። ትኬት የሚቆረጥበትን ሰዓት ስንጠባበቅ ባሪቾ በጆሮዬ "ተስፍሽ ልጋብዝሽ?"

"እሺ!"

አብረውን ከሰፈር ሲኒማ ለመግባት የመጡትን ጓደኞቻችንን 'ሽውደን' ባለሦስት ፎቅ ወደ ሆነው አንበሳ ሻይ ቤት ሄድን።

"ፉል በአራት ዳቦ!" አለ ባሪቾ፣ ሞባሸሩ እንደመጣ ወደ እኔ ዞረና "ሻይ ወይስ ቡና በወተት ይሻልሃል?"

ምርጫዬን ነገርኩት።

"ስማ፣ አንድ ቡና በወተትና አንድ ሻይ ጨምርበት" ብሎ አዘዘ። የተቀመጥነው መስኮቱ አጠገብ ስለነበር የጫት ተራው ትርምስ ከታች ይታየናል። ትኩሱ ፉል ከዳቦ ጋር ቀረበልን። እየተጨዋወትን ሻይና ወተታችንን ፉት እያልን ተመገብን።

ባሪቾ የመጨረሻውን የፉል ጥራጊ ጎረሰና "እንድገም?" አለኝ።

እንደጠገብኩ ነገርኩት። ቀደም ብዬ ከቤት ጎዝጉዤ ነበር የወጣሁት። አንዴ ተንጠራራና "በል እዚህ ቁጭ ብለህ ጠብቀኝ። እኔ ሽቃቅዬ ልምጣ..." ሲለኝ ዓይኖቼ ፈጠጡ።

"ፈራህ እንዴ? 'ቡካታም' አትሁን! *ሹፈኝ በመስኮት!" አለና ጥሎኝ ሽው አለ።

ጣፍጦኝ ፉት እለው የነበረው ቡና በወተት ሬት ሬት ብሎኝ መጠጣቱን ተውኩት። ቁልቁል በመውጫው በር ብቅ እስከሚል አፍጥጬ በመስኮት ስጠብቅ በጣም ቆየ። ግራ ገባኝ። የሻይ ቤቱን ሂሳብ ማስላስል ጀመርኩ። 85 ሣንቲም ዕዳ አለ ብኝ። ያለኝ ቼላ ብቻ ነበር። እርሱንም አሻሮ *ዲናሬ ሞልቶልኝ ነው እንጂ መጀመሪያ የነበረኝ 40 ሣንቲም ብቻ ነበር። ሂሳብ ለመክፈል 35 ሣንቲም ይጎድለኛል። ከየት አመጣለሁ? ተበላሁ!።

ከሃሳቤ ባንኜ ቁልቁል ሳይ ባሪቾ ብቅ አለ፤ ኪሱ ውስጥ አጣጥፎ የያዛትን ባርኔጣ አወጣና አደረገ። ወደ ሱቅ ተጠጋ። ከአንድ ሼህ ጋላ ቆሟል። እሳቸው ከባለሱቁ ጋር ይከራከራሉ። ባሪቾ ኮታቸውን ገልቦ የጋላ ኪሳቸውን በዝግታ ይበረብራል። ትንፋሼን ዋጥኩ። አንድ መላጣ ሰውዬ በጥድፊያ መጣና ከባለ ሱቁ ጋር ማውራት ጀመረ። ባሪቾ አንድ ጥቁር ቦርሳ ከሼሂው ኪስ አወጣና በሆዱና በሱሪው መካከል ቁልቁል ከተተ። አላባቢውን በፍጥነት ለቃኝ ማንም አላየውም። ወደ እኔ ዞር ሽቅብ አይቶኝ ጠቀሰኝና ወደ ሻይ ቤቱ መራመድ ጀመረ።

ፎቁን ወጥቶ እኔ ወደ ተቀመጥኩበት መጣ። ቦርሳውን አውጥቶ ከጠረጴዛው ስር መበርበር ጀመረ። ብዙ ብሮች አወጣ። ቦርሳውን እዚያው ጠረጴዛ ስር ጣለው። ባርኔጣውን አውልቆ አጣጥፎ ኪሱ ከተተ። ሒሳቡን ከፈለ። ሻይ ቤቱ ታችኛው

ሹፈኝ፡ ተመልከተኝ።
ዲናሬ፡ አስር ሣንቲም።

ወለል ስንደርስ ሱቁ አካባቢ የተሰረቁት ሰውዬ ሲጮኹ ሰዎችተሰብስበው ያዳምቃሉ። በትርምሱ መካከል በፍጥነት ወጥተን ታጠፍን።

በፍጥነት ሲኒማ ቤቱ ደረስን። ትኬት መቆረጥ ጀምሯል። ከጓደኞቻችን ጋር ተቀላቀልን። ፍርሃትና መደነቅ የሠራ አካላቴን ወሮታል። ባሪቾ ቀልጠፍ ብሎ ለሁለታችንም ትኬት ቆርጦ አንዷን ሰጠኝ።

ከማድነቅም በላይ ቀናሁበት። "ምነው እግዚአብሔር እኔንም እንደ ባሪቾ አራፍ ሌባ ቢያደርጎኝ? 'ሙቪ' እንደ ልቤ እገባ ነበር?!" የዚያን ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲኒማ ቤቱ ውስጥ ለስላሳ መጠጥ ጠጣሁ።

ሦስት ፊልሞች አይተን ብንወጣም አንዱንም አላስ ታውስም። የባሪቾ ድርጊት ግን አብሮኝ ወደ ቤቴ ዘለቀ። ውለ ታውን ሳልውል ሳላድር መክፈል እንዳለብኝ ወሰንኩ።

ገንዘብ የማገኝበት ምንም ዘዴ የለኝም። ቀላሉ መፍትሔ ከቤተሰቦቼ መስረቅ እንደሆነ ገባኝ። ብዙ ብዙ አብሰለሰልኩ። በቅርቡ ከባላገር የመጣችው ዘመዳችን ሙቀዴ ገንዘቧን የምታስቀምጥበትን ቦታ አውቃለሁ። ትራሱን ገለጥ ሳረገው መሐረቧ በሣንቲም ታጭቆ ተቋጥሯል። ሦስት ስሙኒ ወሰድኩ።

የዚያን ዕለት ችሰታ ስለነበር ባሪቾን ደረስኩላት። እግረ መንገዴንም የባሪቾን ውለታ ከፈልኩ፣ ራሴንም ከእኩያዬ እኩል አዋል ኩና ተደሰትኩ። ነገር ግን እቤት ስመጣ የጠበቀኝ አሣር ነበር። አባቴ ወደ ቤት እንደገባሁ ሊወግረኝ እንደ አንበሳ አግስቶ ተወረወረ። የከርስትና አባቴ መሀል ገብተው በአየር ላይ ቀልበው እነበረበት አስቀመጡት። ሙቀዴ በጋሞ ቋንቋ ኃጢአቴን ትለፈልፋለች።

"ጮጋ!" አሏት አባባ ኃይሌ በሚችሏት ጥቂት የጋሞ ቃል። "ዘም በይ!" ማለታቸው ነበር። በእርጋታ ምርመራቸውን ጀመሩ። "ፉንጋይ!"

"አቤት!"

"ሦስት ስሙኒ ጠፋባት!" ወደ ሙቀዴ እየጠቆሙኝ አረዱኝ።

"እኔ!..." ብዬ 'ዓይኔን ግንባር ያርገው!' ልል ስል፣ አባቴ ጮኽ ሊያንቀኝ ሲወረወር፤ በድጋሚ ቀልበውት ወደ ተነሳበት መለሱት። "ባንተ ቤት መቅጣትህ ነው። አሁን ነገር እያበላሸህ መሆኑን ልብ በል" አሉትና "አንተ!?" አሉኝ አፍጠው፤ "እውነቱን ካወጣህ ማንም አይነካህም። ብቻ እውነቷን አውጣ!" በዝግታ ከግስላ ሲጋራ ፓኮ ውስጥ አንዷን መዘው ለኮሱ። ሁለቴ በኃይል ማጉላት። በረጅሙ ተነፈሱ። ጢሱ ከአፋቸው እየተዝለገለገ እየ ወጣ ቤቱን ቢያጥነውም በጉሙ ውስጥ በድፍርስ ዓይኖቻቸው በጥን ቃቄ ያስተውሉኛል። ፊታቸው እንደተገተርኩ ሽንቴን ጭርቅ አደረኩት። ፀጥ ታው የዘለዓለምን ያህል ረዘመብኝ።

"ሦስቱን ስሙኒ ምን አደረከው?"

"አትመልስም?" አባቴ ጮኸብኝ።

"እኔ ግን አንተን ኮረንቲ ይዞህ ጮኬ አባባ ኃይሌ ባል ቦላውን ነቅለው አላዳንኩህም?!" አልኩት።

"ኮረንቲ ይዞኝ ያዳንከኝ ሌባ ለመሆን ነው እንዴ? አንተ ሌባ እንድትሆን አምላክ ከሞት ያተረፈኝ ከሆነ እኔ ሞቴን እመርጣለሁ" አለና ማልቀስ ጀመረ።

ትላልቅ ሰዎች ሲያወሩ እንደሰማሁት በኮረንቲው ውስጥ ያለው ጋኔን ደም ይመጣል። አባቴም የዚያን ዕለት ደሙን ጋኔን እንደመጠጠው ገባኝ። በዕለቱ ለጎረቤቶቻችን ሁሉ እኔ ዓብይ ዜና ሆኜ ዋልኩ። "ዜራሞን ተስፋዬ ከሞት አተረፈው!" ተብሎ ዝናዬ በድፍን ቂርቆስ ተናኘ። የሰማው ላልሰማው ሲያወራ የራሱን ሃሳብ ስለሚጨምርበት ከፍተኛ ግነት ተፈጠረ። ከአባባ ኃይሌ ቤት በርጩማ በፍጥነት አውጥቼ ላዩ ላይ በመቆም ባልቦላውን እንዳጠፋሁ ያወሩ ጀመር። የዚያን ዕለቱ ተአምረኛ ጀግና ዛሬ ጊዜ ከድቶኝ ሌባ ተብዬ ብይኔን እየተጠባበኩ ነው። ጀግና ሆኖ የሚገኘውን ማኅበራዊ ሞገስና ሌባ ተብሎ የሚመጣውም መዘዝ ከማለዳው ተገለጠልኝ።

"ዝም በል አንተ!" አሉትና አባቴን "ፋንጋይ፣ መልስልኝ እንጂ!" አሉኝ። ጠጅ ጠጅ የሚሸተው ትንፋሻቸው ከሲጋራው ጢስ ጋር ተዋህዶ ተነፈገኝ።

ሽንቴ ሞርቅ ብላ ቁምጣዬን አርሳ በሞኒ ላይ መንቆርቆር ጀምራለች። የነበረኝ ራሴን የምከላከልበት አቅም ከዳኝ። በልቅሶ ዜማ "ይሄ ባሪቾ..."

በጥፊ አጮሉኝ። ትንሿ ፊቴ ከትከሻዬ ጋር ተላትማ ተመለሰች። የሚያሰክር መጠጥ እንደጠጣሁ ሁሉ ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። የክበቡኝ ሰዎች ብዙ ሆነው ታዩኝ።

"ፍራንኩን ምን አደረከው ነው የምልህ?!" ግስላዋን ስምጥ ጠው መሬት አወደሚት።

"ፓስቴ..."

"በላችሁበት?" በጎልያድ ድምፅ።

"አ- አዎን!"

ከዚህ በኋላ የሆነውን የማስታውሰው በወገራው የማርያም ጠላት መሆኔን ብቻ ነው ... ከአንድ ቀን በኋላ ራሴን ታጣፊ አልጋዬ ላይ ተጋድሞ አገኘሁት። አካላቴ ክፉኛ ጎዳኋል። ከሕመሜ ሁሉ የከበደኝ ግን የቤተሰቤ ነቀፋ ነበር። ከዚህ ሁሉ ውርጅብኝ በኋላም የአባቴ የአጠቃቅ ስልት ክፉኛ የሚያምመኝ ነበር። እኛ ቤት ስሚገቡ ዘመዶቻችን ሁሉ ወንጀሌን ያወራላቸዋል።...

እናቴ ኮስተር ብላ አንዲት ቃል ደጋግማ ትናገር ነበር። "በዚህ ድህነት ላይ ሌብነት! እኔ ባሎቴ የምትረባኝ መስሎኝ ነው

ደፋ ቀና የምለው ልጁ። እኔ መቼ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አማረኝ? የማትረባ! ሌባ!" ብላኝ የምበላውን እንደውሻ ጥላልኝ ትሄዳለች። ፍቅሯን ያልነፈገችኝ ውሻዬ ቲቲ ብቻ ነበረች። ይሁን እንጂ ከሰው ልጅ ያጣሁትን ፍቅር ሙሉ በሙሉ ልት ሞላልኝ አልቻለችም።...

ውጪ የሚዘምሩት የሰፈር ልጆች ጨዋታ ቀይረዋል። "ሌባና ፖሊስ የሚጫወት! ሌባና ፖሊስ የሚጫወት!" በተጋደም ኩበት በመንፈሴ ተከተልኳቸው።

ከሰማይ የወረደ ያህል ኃይሉ ዶሮ ሊጠይቀኝ ከተፍ አለ። አባቴ ሌሎች ጓደኞቼ ሁሉ እንዳይጠይቁኝ ከልክለውቸዋል። ከዶሮ ቤተሰብ ጋር ግን በጣም ይዋደዳሉ። የከት ልብሱንና ጎንዝ ቡን የሚያስቀምጥበት ሳጥኑን በአደራ የሚያኖረው እነዶሮ ቤት ነው። በዚህ ቤተሰባዊ ወዳጅነት ዶሮ እንዳሰኘው እኛ ቤት መውጣት መግባት ይችላል።

በዚህ ሌብነቴ መዘዝ አባቴ ከባሪቾ አባት ጋር ተጣል ቷል። በሰፈራችን ልጆች አስተሳሰብ መስረቅ ነውር አልነበረም። በሌብነት ተይዞ መጋለጥ ግን ትልቅ ውርደት ነው። ወላጆቻችንን ከሌባው ልጅ ጋር ልጆቻቸው እንዳንገዋኘም በዓይነ ቁራኛ ስለሚከታተሉን ቅስማችን ይሰበራል። "የሰፈር ሰዎች ስለ እኔ ምን ይላሉ?"

"ያንተ መስረቅ ተረስቷል!"

ተገርሜ "እንዴት?" አልኩት ቀና ለማለት እየሞከርኩ።

"መኩዬ ቀጫጫዋ ትናንትና ሦስት ብር ሰርቃ ተያዘች።"

"ሦስት! ብር! ከማን ላይ?!"

"ከእናቷ ላይ። አንባሻ ሸጠው ከቀረቀሩበት ቦክሰች!"

"እንዴት?"

"እነዚያ የጠመንጃ ያዥ ሰፈር ልጆችን ታውቃቸዋለህ አይደል?"

"አዎን እነሁሴን ጂቦ ሰፈር!"

"አዎን! እነሱ ፍራንክ ካልገበርሽ በሰፈራችን ወደ ትም ህርት ቤትሽ አናሳልፍሽም አሏት፣ ኧረ እንዲያውም ወገሯት። ስለዚህ ከእናቷ ሦስት ብር ሠርቃ አንዱን ሰጠቻቸው። ሁለቱን ብር ሙቪ ገባችበት። ማታ ስትመለስ በወገራ ሲያጣድፏት ለፈለፈች። በገመድ አስረው አልጋ ስር አሳደሯት። አባ ዘለቀ ቤቱን ጠበል እንዲረጩላቸው ጠዋት ቀወሮ ነበራቸው። አባ መጡ። ቀጫጫዋ አልጋ ስር ተኝታ ትስላስት፣ ጉንፋን ይዟት ነበር። አባ ግር እንዳላቸው ዳዊታቸውን ይደግማሉ። አሁንም ስትሰል አባ እናቷን 'ምንድነው?' ብለው ጠየቁ። እናትየው የቀ ጫጫዋን ሌብነት ነገሯቸው። አባም 'በስማም ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ...' ብለው አማተቡና እናቷን ገዝተው አስፈቷት። ከዚያም መኩዬን መክረው ሁለተኛ እንዳትሰርቅ አስምለው ለቀቁዋት" ብሎ ድምፁን ዝቅ አድርጎ ነገረኝ።

አባቴ ድር ሊያደራ ወደ ወጪ ችካሎቹን ይዞ ወጣ። አድፍጠ ይጠብቅ የነበረው ሲሳይ ዝቺጥ ዘው ብሎ ገባ። የእኔን ደህንነት ሳይጠይቀኝ "ሰማችሁ?"

"ምኑን?!" አልነው እኔና ዶሮ በአንድነት።

"ሴምላል ያንን መኪና ሰፌ ደባላቸውን መነተፈው" ጉቢጥ ብሎ አስደነቀን። ሲሳይ ሲራመድ፣ ሲናገር፣ ሲያስብም ፈጣን ነው። ሲያወራም አንደበቱን ያዝ አያደርገውም። "መኪና ሰፈው ቀን ቀን ቡትቶ ልብስ ሲጥፉይውላል። ማታ የሸቀሰውን ከርከ፣ ዲናሬ፣ ዱንቡሉ ባንኩ ውስጥ ክቶ ሣጥኑን ይቆልፋል። ሴምላል ሁልቀን አድፍጠ ይጠብቃል። ዛሬ ጠዋት መኪና ሰፈው ሣጥኑን ከፍቶ የዘጋ መስሎት ሳይቆልፈው ሄደ። ሴምላል ከሣጥኑ ውስጥ ባንኩን አወጣና በሹራቡ ሸፍኖ ይዞ ወደ ውጪ ወጣ። ቀጢሳውን ደጅ አገኘው። ከእማማ *ጎደቴ ጠጅ ቤት ግርግዳ ላይ ኪሱን እየለጋ ብቻውን እየተጫወተ ነበር። ባንኩን አሳየው።"

"ከዚያስ?" አልኩ ቸኩዬ።

"ፏፏቴ ሄደው ባንኩን በድንጋይ ሰብረው ፍራንክ በኪ ሳቸው አጨቁ። የተረፈውን አሸዋ አልብሰውት ወደ ሲኒማ ራስ ደየሙ።"

"ሰውዬው አልነቃም?"

."ትንሽ ዘግይቶ ነቃ እንጂ! ሥራ ላይ ሆኖ ቅር ቅር ሲለው ቤት መጣ። ሣጥኑን ሲያይ ተከፍቷል። ባንኩ የለም። ጮኸ! ሰዎች ሲጠይቁት የተሠራውን ጉድ ተናገረ።

"ጥርጣሬው ሴምላል ላይ አረፈ። ቢፈለግ የውሃ ሽታ ሆነ። ሌሎች የሰፈር ልጆች ሁሉ ተሰብስበን ስንጠየቅ ሴምላል ከወሰደ ሲኒማ ራስ እንደሚገኝ ጠቆምን። እዋቂዎቹ በአምስቱም ሲኒማ ቤቶች እንዳንደ ሰው ዘብ እንዲቆም ተመዳድበው ሄዱ። አሁን መኪና ሰፈው ራሱ ፈይሳ ከሲኒማ ራስ ይዘዋቸው መጡ። ቢፈተሹ ኪሳቸው በፍራንክ ታጭቋል። ሃምሳ አለቃ እርአያ ቤት ገብተው ሲመረመሩ ያጡት ፍራንክ ሁለት ብር ብቻ ነው። የተ ቀረውን አስረክቡ። ዛሬ ታስረው እነዶሮ ቤት ያድሩና ነገ ባን ኩን የሰበሩበትን ቦታ ይመራሉ።" ይህን ነግሮን ሲያበቃ ጎቢጥ የሚቀጥለውን ትዕይንት ለመጨለፍ ፈትለክ አለ። ዶሮም ተከ ተለው።

እኔ ግን ለመውጣት አካሌም አይችልም፣ ቤተሰቤም እይ ፈቅድም፣ በተጋደምኩበት ሳብለለስል የሕፃናቱ ድምፅ ተሰማኝ። ጨዋታው ወደ ኩኩሉ ተሰውጧል።

"ኩኩሉ!" የፋንቲሽ ድምፅ ነው።

"አልነቃም" እቴቴ ትመልሳለች። በየስርቻው ለመደበቅ ሲሮጡ የምድር ድምድምታ ይሰማኛል። ልቤ ቆመ። እንደ ምንም በር ድረስ ሄጂ የጓደኞቼን መጨረሻ ለማየት ተነሳሁ። እማዬ ከማዕድቤት ስትመጣ አየችኝና "አርፈሀ ተኛ፣ ያንተ ቢጤ

*ጎደቴ፣ በወላይቲኛ እጌቴ ማለት ነው።

ዎች እየተገረፉ ነው" ብላኝ መወዘቻ ውስጥ ውሃ ሞልታ ወደ ግዕድ ቤት ተመለሰች። ተመልሼ ተጋደምኩ። እንዳሰችውም ፈሪው ቀጢሳው ሲጮህና "ሁለተኛ አይለምደንም!" እያለ ሲወ ተውት ይሰማኛል። ሴምላልም በጎርናና ድምፅ አጅቦታል። እር ጥበት የማያጣው አፍንጫው ሁሌም የሚንጠለጠለውን ንፍጡን ሽቅብ ሲምገው በሃሳቤ ታየኝ...

...ከዕለታት በኋላ ጤንነቴ ተስተካከለ፣ የሌብነት ታሪኬም ተረሳ። ከቤተሰቦቼም ጋር እንደ ድሮአችን በፍቅርና በሰላም መኖር ጀመርን። ይሁን እንጂ ፓስቴው ሱስ ሆኖብኝ አሳቻ ጊዜ እየጠበኩ ፍራንክ መመንተፌን አልተውኩም። አባቴ ልብ ባይ ልም እናቴ ግን ሁሌም በንቃት ትከታተለኛለች። እጅ ክፍንጅ ሰመያዝ የተሰያዩ ወጥመዶችን አዘጋጀች።

አንድ ቀን ከመርካቶ እህል ሸምታ እንደተመለሰች ሽክሟን አወረደችና መሐረሟን አልጋ ላይ ጣል አድርጋ ደጅ ወጣች። እኔ ግን የዚያን ዕለት አባቴ በጠጅ ሞት ብሎት ገብቶ ስለነበር ዲናሬዬን ሠርቄ ሁለት ፓስቴዬን በልቼለሁ። የምሴን እድ ርሻለሁ፣ ስለዚህ የእሷን ወጥመድ እንደጠገበ አይጥ እየገረመ ምኩ አለፍኩት።

ሌላ ቀን የጎመን ዘር በምታስቀምጥበት ጣሳ ውስጥ ስሙኒ አገኘሁ። እና አንስቼ ስሲጣት "ማን እኔ ያስቀመጥኩትን ንካ አለህ?" ብላ ገሰጠችኝ። በሚቀጥለው ቀን ግሰዳ ከራስጌዬ በፍራንክ የታጨቀ መሀረብዋን አገኘሁት። ፈታሁና እየሁት። ብዙ ስሙኒዎች ሌሎች ዝርዝር ፍራንኮች ናቸው!

ነፍሴ ለሁለት ተከፍላ ተነታረክች። አንደኛው ክፍል 'አንቷን ከርክ ወሰደህ ፓስቴ ብትበላባት ማንም አያውቅብህ አለኝ። ሌላኛው 'ውርድ ከራስህ!! ምለህ ተገዝተህ የተውከውን ሌብነት ልትመለስበት?' ሲል አስጠነቀቀኝ። እንዲሁ ሃሳቤ በውስጤ መውጠንጠኑን ቀጠለ። 'ብትምል ብትዝትስ ሌብነቱን እንደሆን አልተውከው። እናትህስ ይህን ሁሉ ፍራንክ ቆጥረው ይዘልቁታል ብለኸ ነው? እባክህን ከርኳን ቦክምና ነፍስህን ደስ አሰኖት። የትኩስ ፓስቴ ሽታ በአፍንጫዬ ሽው አለ። በፍጥነት ቁምጣዬን ታጠቅኩ። ሹራቤን ደርቤ፣ ስሙኒ ብድግ አድርጌ ወደ ወርቄ ሻይ ቤት ቁር አልኩኝ። ጉዳዩን በጥንቃቄ ፈፀምኩ። ከሻይ ቤቱ ስወጣ ከቀድ ሞው ጥንቃቄ ባልተናነሰ አንገቴን አስግጌ ግራ ቀኙን ዓይቼ ዋናው መንገድ ላይ ወጣሁ።

ረፋዱ ላይ ወደ ቤት ተመለስኩ። ከእማዬ ጋር ሳሉን ተገናኘን። ቁጭ ብላ ጠብቃኝ እንጂ በዚህ ሰዓት ቤት ውስጥ አትገኝም ነበር። "ከየት ነው የምትመጣው?!" አለችኝ።

አጠያየቋ ያስፈራል።

"ልጄወት ሄጂ!" አልኳት ዓይኖቿን እየሸሸሁ። ዓይኖቿ

ፍቅር ለመርጨት ኃያል ተፈጥሮ ያላቸውን ያህል፣ ጥላቻና ንቀት ሲረጩም መንፈስ ይሰብራሉ።

"እንካ ቁርስህን!"

"በቃኝ!" አልኳት ሳላስበው አመላለሴ ትክክል አለመሆኑ ወዲያውኑ ገባኝና ደነገጥኩ፡፡ እናቴ አምርራ የምትጠላው ውሸ ታምን ነው። በርካታ ጊዜያት ልዋሻት ስል ወዲያው ደርሳብኝ ተገቢውን ቅጣት አግኝቻለሁ፡ አሁንም ስለተያዝኩ አፈጠጠች ብኝ። የእኔ ዓይኖች መድረሻ ጠፋቸው።

አናቴን በኩርኩም መትታኝ "ሂድና ፊትህን በመስታወት እይ።"

እንዳሰችኝ አደረኩ። ከንፈሬ በዘይት ወዝቶ ያብረቀርቃል። ከፓስቴ ቤት እንደወጣሁ የከንፈሬን ወዝ በእፈር አብሼ ማጥፋት ነበረብኝ። አላደረኩትም። ፖሊሷ እናቴ ሌባ ልጇን እጅ ከፍንጅ ያዘችኝ።

"ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ አይለምደኝም!" አልኩና እያ ለቀስኩ እግሯ ላይ ተደፋሁ። አንስታ አቀፈችኝና እየተንሰቀሰቀች "እባክህን ልብ ግዛ!" አለችኝ።

እኔን የእናቴ ጥብቅ ቁጥጥር ወደ ጤናማው ማኅበረሰብ መለሰኝ። የቤተሰብ ቁጥጥር ላልቶለት በሌብነቱ የቀጠለበት ባሪኞ ግን በጉርምስና ሕይወት መጀመሪያ ላይ መርካቶ አካባቢ ሲሰርቅ ተይዞ ክፉኛ ተደበደበ። ለዕለታት ታሞ ሞተ። በሕይወቴ ለመ ጀመሪያ ጊዜ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኘሁለት ጓደኛዬም ባሪኞ ሆነ።

ዕንቁጣጣሽ

እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ
አዬ እቴ አበባዬ!
እቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ
አዬ እቴ አበባዬ!
ጥላኝ ሄደች በሐምሌ ጨለማ
አዬ እቴ አበባዬ!

ለዕንቁጣጣሽ ለሰፈራችን ስዎች የምሰጠውን አበባ ንድፍ በጥንቃቄ መገልበጥ ጀመርኩ።አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማቱን በጠበጥኩ። አንዱን ከሌላው ጋር በማዋሃድ የተለያዩ ቀለሞችን ፈጠርኩ። በሌላ ብልቃጥ በትንሹ እያደረኩ ሦስቱንም ቀለማት ሳዋህዳቸው ጠቆር ያለ ቀለም ሆነ።

ቀለማቱ እንዳይደፋብኝ ከትልቁ ሳጥን በስተጀርባ ባለው ክፍት ቦታ በእበት በተለቀለቀው ወለል ላይ ደረደርኳቸው። መሬት ተንበርክኬ ትልቁን ሳጥን አስደግፌ በሉህ ላይ እስላለሁ። ከቅዱሳን ምስሎች፣ ከአበባው፣ ከቅጠላ ቅጠሉ መልከ ላይ እያ የሁ ገለበጥኩ። በራስጌና ግርጌዎች ላይ "መልካም አዲስ ዓመት፣ እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላም ያሸጋገ ርዎት..." የሚሉ ምርቃቶችን ከጓደኞቼ እንዳየሁት አሠፈርኩ።

እንደ አስፈላጊነቱ ከጓደኞቼ ንድፍ እያየሁ እቀስማለሁ። ከአብሮ አደጎቼ መካከል ያለማንም ዕርዳታ ንድፎቹን አስቦ መሥ ራት እሚችል ኃይሉ ዶሮ ብቻ ነው። ዶሮ የሠራሁትን እቤቴ ወስጀ ሳሳየው መስተካከል ካለበት ያርማል። "ቂርቆስ እኮ ሕፃን ነው። ጎራዴ አይዝም። ቅዱስ ሚካኤል ነው ጎራዴ ያለው" ብሎ ሕፃኑን ቂርቆስን ይሥልና ለጓደኞቹ ያሳየናል። ይሁን እንጂ ኢየሱስና እጣኑ ቂርቆስ ይመሳሰሉብናል።

"እነዚህ እምዬ ማርያምንና ልጇን መሰሉ" ይላል ሲሳይ ጎቢጥ ባለ አንድዓይና መነፅሩን እያስተካከለ።

"ይምሰሉዋ! የሕፃኑ ቂርቆስ እናትም እንደምዬ ማርያም ልጇን ማቀፍ ትችላለች። ብትፈልግ እያት" አለና ግርግዳ ላይ ያለውን የቅዱሳንን ምስል ጠቆመ።

"የቂርቆስ እናት ማነው ስሟ?" ጎቢጥ ጠየቀ።

ዶሮ በተንበረከከበት "እማዬ!" ብሎ እማማ ሸጊቱን ጠራ ቸው። "ወይ!" አሉ፣ ማድቤት በር ደፉ ላይ ተቀምጠው ሽን ኩርት እየላጡ ነው።

"የሕፃኑ ቂርቆስ እናት ስም ማነው?"

"እየሉጣ።"

ወደ እኛ ቀና አሉና "ይገር ልውጣ።"

"እማማ ሸጊቱ እየሉጣ ነው ያሉት" አለና አበረ ሻቃ አረመው።

እርግቱን ሰምቶ ቀለም ብዙም ሳናባክን እምንጠቀምበትን ጥበብ ኃይሉ ዶሮ ሃሳብ ሰነዘረ። "ስንደዶ ላይ ትንሽ ጥጥ ትጠ መጥሙና መቀባት። ከዚያ ያኛው እስኪደርቅ ሌላውን በነከርነው እየቀባን ቀለማችንን መቆጠብ" ሲል፣

ጎቢጥ ካሱ ነጠቀውና አንዳይና መነፅሩን አውልቆ ልክ እንደ ትልቅ ሰው የመነፅሩን ፍሬም እየነከሰ "ይሄውላችሁ ልጆች እኔ ስቀባ በመጀመሪያ ቅጠል ቅጠሉን ነው። ከዚያ መልከ ብቻ መቀባት እጀምራለሁ።"

ሌሎች ጓደኞቻችንም የየራሳቸውን ልምድ ያካፍሉናል። አንዱ ሌላውን የማገዝ ባህላችን በጣም የዳበረ ነው። በዚህ ወቅት ወላጆቻችን ምንም አይነት ቁጣ አይሰነዝሩብንም።

እኔማ የተገላቢጦሽ በምሠራበት አካባቢ ወላጆቼ ዝር ካሉ እቆጣቸዋለሁ። ቀደም ብሎ አባቴ ድር እሚያደራበትን ብረት ከሣጥኑ ጓላ ያስቀምጥ ነበር። እኔ ቀለማቶቼን እዚያ ሳስቀምጥ

የብረቶቹ መቀመጫ ከአልጋ ሥር ሆነ። እሱ ዘንግቶ ችካሉን ፍለጋ ወደ ሣጥኑ ስር እጁን ክሰደደ እናቴ "ተው ዜራሞ፣ ፉንጋይ የአበባ ቀለሙን በጥብጠ ያስቀመጠው እዚያ ነው። እንዳትደፋበት" ስትለው "ታዲያ ችካሎቹን የት አስቀመጥሻቸው?" ይላታል።

ዕንቁጣጣሽ እየተቃረበ ሲመጣ አባቴን አንድ አንደበት እሚዘጋና አካልን ሽባ እሚያደርግ በሽታ አመመው። እኔ ስሠራ ዓይኑን እያቁለጨለጨ ያየኛል። እሚፈልገውን በምልክት ሲጠይቀኝ አቀርብለታለሁ። ስለ ሥራዎቼም አጫውተዋለሁ። ደስታውን በፈገግታው አያለሁ።

በእንዲህ አይነት ሰዓት ቀጢሳው ዘው ብሎ ቤታችን ገባና "ፉንጌ፣ ዶሯችን አረንጓዴ ቀለሜን ደፋብኝ" አለ እዝን ብሎ።

"ዶሮ ገዛችሁ?"

"አዎን ና ላሳይህ። ሲጮኽ ብታየው" የቀለሙን መደፋት ረሳው። እኛ ቤት ዶሮ ስላልተገዛ ጉጉቴን ቀሰቀሰው። ወደ እማዬ ዞሬ ሳይ "እኛ ዶሮ እምናርያው ለመስቀል ነው" አለች።

"ለምንድነው ታዲያ በድሮው ዕንቁጣጣሽ ዶሮ ገዝተን ያረድነው?"

"አይ የልጅ ነገር ዛሬ የዕለት ጉርሱም በአሣር ነው እሚገኘው። አታይም? አባትህም እኮ አልጋ ላይ ከዋለ ስንት ጊዜው ነው?" አንጋገሯ ልቤን ሰርስሮ ገባ።

ከቀጢሳው ጋር ሄጄ ዶሮአቸውን ማየቱን ተውኩት። እነ ኃይሉ ዶሮ ቤት በማ መገዛቱ ትውስ አለኝ። ዶሮ ሣር ሊያ ጭድለት ከነ ሻቃ ጋር ወደ መርእድ ሜዳ ሲሄዱ ነው እኔ ወደ ቤቴ የመጣሁት። ሁሉም ልጆች እቤታቸው የተገዛውን እየነገሩኝ በጣም ጓጓሁ።

"እኔኮ ግን የመጣሁት ማርገጃ ሄደን ቀለም እንድታጋዛኝ ነበር" አለ ቀጢሳው፣ ጭብጥ አድርጎ የያዛትን ፍራንክ እጁን ገልጾ አያሳየኝ። ሣንቲሚ ማላብ ጀምሮአታል።

ተያይዘን ወደ ማርገጃ ሄድን። ለሰፈራችን ልጆች ቀለምና ንድፍ እሚሸጥልን ጎሳዬ አበበ ነው። የቀለማቱን ውበትና ደማቅነት ለማሳየት በቦላሌ ሱሬው ጭኑ ላይ እንደ ባንዲራ ቀብቷቸዋል። ሽራ ጫማውን የጥምቀት በትር ይመስል በቀለማት አዝንርጉሯታል። ውበቷም ቆዳ ጫማ ያለንቃል። ሲራመድ በጣቶቹ መሬቱን እሚረግጠው እንደ ድመት በጥንቃቄ ነው። ሽራ ጫማውን ይነጥርባታል። አንጋገሩ የአክተሮቹን የነክሊንት ኢስትውድን ስልት በመከተል ቀልጠፍ ይላል። አማርኛውንና እንግሊዘኛውን ቀላቀሎ የሚያወራ አራዳ ልጅ ነው።

ቀለም ወይም ንድፍ ለመግዛት ወደ ማርገጃ ብቅ ያልን እንደሆነ ጎሣዬ መጀመሪያ በሰፊር ልጅነት ያግባባናል። "ጎሣዬ ይሸቅበናል፣ ከሌላ እንግዛ" ብለን አይተነው እንዳላየነው ሰንሆ

ንበት፣ በዚያ ምርጥ ቃል በሚያዘንበው ምላሱ የቀለሙን ጥራትና ውበት ያነበንባል።

በክላሰር ከያዘው ብዙ ንድፍ እየገላለጠ ስለእያንዳንዱ አበባ ስዕል ማብራሪያ ይሰጣል። "የቅዱስ ገብርኤል የጌታ መልእክተኛን፣ ወይስ የእመቤታችን የጭንቅ አማላጂን፣ ወይስ የሺ በክንፉ ሺ በአክናፉ የቅዱስ ሚካኤልን..." ጎሳዬ ሲናገር ወፍጮ ቤት ውስጥ እንዳለ ሰው ጮክ ብሎ ስለሆነ የኛን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የሚገኙትን ሕፃናት ሁሉ ቀልብ ይስባል።

"እኛ እምንፈልገው ቀለም ነው!" ሲለው ቀጢሳው።

"እሺ፣ ቀለም ሞልቶ! አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ...!" ቀልጣፋ ጣቶቹ የንድፍ መያዣ ክላሰሩን ዘግቶ ወደ ሰፊው ኪሱ ገብተው እጁን በመስደድ ቀለማቱን ማውጣት ጀምረዋል።

"አረንጓዴ!"

"እ! ፉንጋዬ ደንበኛዬ! ባለፈው የሸጥኩልሽ ቀለም አሪፍ አይደል?" እያለች ጎሣዬ ለቀጢሳው አረንጓዴ ቀለሙን ሰጥቶ አምስት ሣንቲሚን ተቀበለ። "በሉ ሂዱና አበባችሁን ቀቡ። እንቁጣጣሽ ደረሰ እኮ። ዛሬ ሩፋኤል ነው። በቃ ምን ቀረው? በሉ ቶሎ ሂዱ!..." አለንና ወደ ሌሎች ደንበኞቹ ዞረ።

ጎሣዬ የዕድሜ እኩያችን ሆኖ ብልጠቱ ከእኛ በላይ ነው። አንድ ክርክር ቢነሳ ሁሌም እሚጠናቀቀው በጎሳዬ ረቺነት ነው። (ለሚቀጥለው ዓመት እኔም ንድፍና ቀለም እነግዳለሁ ስል በሆዴ ወሰንኩ።)

"ዛሬ ከዘነበ እራቂታችንን እንጠመቃለን" አለኝ ቀጢሳው።

"አዎን" አልኩት። በውስጤ ግን ስመጠመቅ ፍላጎት አል ነበረኝም። ቀጢሳው ከፊቴ የውስጥ ስሜቴን ተረዳና "ለምን አትገረዝም?"

"ይሄ አባቴ ነዋ! አገሬ ወስጄሀ አያትህ መርቆህ ነው የማስ ገርዝህ እያለኝ ይሄው አደግኩ!"

"እንተ ብቻ አይደለህም። ገልጆም፣ ሴምላልም፣ ውሮም ወሸላሞች ናቸው" አለኝ ሊያፅናናኝ። እኔ ግን ለሩፋኤል ራቁቴን ከጓደኞቼ ጋር መጠመቅ ስለማፍር ከቤት አልወጣም። ውሮ ምንም ሳይመስለው፣ ሰዎች እያላገጡበትም እየሳቁበትም ተዝና ንቶ ይጠመቃል።

የሰፈራችን አየር በዕንቁጣጣሽ ሰሞን ደስ ያሰኛል። የኩበቱና የቅጠሉ ጢስ፣ የቅቤው፣ የቅመማ ቅመሙ ሽታ... አካባቢውን ያውደዋል።

እነዚያ የጥበበኝነታችን ቀናት ላይጠገቡ እንደጣሙን ዋዜማው ላይ እንደርሳለን። ማታ ሙቅ የጠጣ አዲስ ሸራ ልብሴን አጣዋፌ ሣጥን ላይ፣ ሸራ ጫማዬን እግርጌ አድርጌ፣ አበባቺን በክላሰር አስቀምጬ የነገው ፈሽታ እየታሰበኝ እተኛለሁ። እንቅልፍ ግን አይወስደኝም። ከንብቤን ሳልገልፅ "እማዬ! ነጋ?"

"አልነጋም። ገና ስድስት ሰዓት ነው!"
ትንሽ ቆይቼ "እማዬ!"
"አንተ ልጅ፣ ገና ስድስት ሰዓት ነው ስልህ!! ነገ የሚነጋ አይመስልህም?!"
በተጋደምኩበት አብሰለሰልሁ። ሲነጋ ቶሎ ብዬ አበቦቼን ለጎረቤቶቻችን እሰጣለሁ። ዘመዶቼ ቤት ቀለ ብዬ እሄዳለሁ እያ ልኩ ሳስብ ዶሮ ጮኸ።
"እማዬ!"
"ፉንጋይ ገና ነው፤ በደንብ ይንጋ። ደንቃራ እንዳትረግጥ በሌሊት አትሂድ።"
እንደገና ወደ ሃሳቤ አመለሳለሁ። በማገኘው ፍራንክ ስፖርት በልጅነት ለተባለው ቡድናችን የምለብሰውን ማሊያ እገዛ ለሁ። ከዚያም ባለ ብር ተስሙኒውን ኮፍያና መነፅር ያለውን መለዮ ገዝቼ በመስቀል አደባባይ ለንሽራሽር እዘንጥበታለሁ። ስሙኒ ለኪሴ አስቀርና የተቀረውን ለእማዬ እሰጣታለሁ...
"እምምም! እምምም!" የሚል ትልቅ ድምፅ በርቀት ተሰማን።
"ፉንጋይ፣ እየሰማህ ነው?" በጨለማው ውስጥ አባቴ አምጠ ጠየቀኝ።
"የምን ድምፅ ነው?"
"የባነት ሆቴል አንበሳ እያገሳ ነው" አለች እማዬ፤
"እምምም! እምምም!"
አንበሳ መሆኑን ስሰማ ድምፁ እልፍ አእላፍ ጊዜ ነላብኝ። ክንብንቤን ጠበቅ አደረኩ።
"ድው!"
"ፉንጋይ፣ ሊነጋ ነው። መድፍ መተኮስ ጀመረ" አለች እማዬ።
"ድው!"
"ሁለት!" መቁጠር ጀመርኩ።
"ስድስት ነው የተተኮሰው?" አለች።
"አምስት ነው።"
ተተኮሰ።
"አሁን ስድስት!"
ቆይቶ "ድው!"
"ሰባት!" አልን። እስከ ሃያ አንድ ድረስ አብረን ቆጠርን።
እማዬ የቅዱሳኑን ስም እየጠራች እግዚአብሔርን ስትማፀን ይሰማኛል። "አቤቱ ይህንን ሰው አንደበቱን ፈተሸው፣ አካሉን ፈውሰኸው ለክርሞው ለምሥጋና አብቃን! አቤቱ የሰላም፣ የፍቅር፣ የሥራ አገር አድርግልን...። አባታችን ሆይ፣ ደጉን አዘዝ ክፉውንም ያዝልን!..."

በእንዲህ አይነት ምሽት ከዘነበ እኔ አልጋዬ ውስጥ ተኝቼ እናደዳለሁ። ዝናቡ ፕሮግራሜን እያስተጓጉለብኝ ነው፤ ይሁን እንጂ በልጅ ልብ በጆሮና በልቤ ዝናቡ የሚፈጥረውን ሙዚቃ እያዳመጥኩ "እማዬን ዝናብ ሲዘንብ አልጋ ላይ ሆኖ መስማት ደስ ይላል" ስላት፣ ሃዘን ባዘለ ድምፅ "አይ የልጅ ነገር! ስታድግ ግን ልብህ ውጪ ዝናብ ሲመታው፣ አካልህ ብቻ ነው የሚጠለል" ትለኛለች።
"እንዴ! እማዬ፣ ልቤ እኔ ውስጥ አይደለም እንዴ ያለው? እንዴት ሳድግ ልቤ ከውስጤ ወጥቶ ይመታዋል?!"
"ለካ ካንተ ጋር ነው እማወራው። በል ዝም በል፣ ስታድግ ይገባሃል" ብላኝ ወደ ትካዜዋ ትመለሳለች።
የዚያን ዕለት ማታ እማዬ በወሎቷ በረንዳ እዳሪዎችን፣ አለሁ ባይ ያጡ የአልጋ ቁራኞችን... ሌሎችንም ታብባለች። መከራው ማየሉን ስታይ ግን እምላክን ታማርራለች። "ምነው ጌታዬ ፈጥረህ ትጫወ ትባቸዋለህ? ለወፎች ጉጆን፣ ለዱር አራዊት ጉሬን ሰጥተህ፣ በእም ላልህ ለፈጠርከው ስው ግን ምነው ጨከንክበት?" ... እያለች ከእዝአ ብሔር ጋር ታወራለች።
"ወፎች መንጫጫት ጀመሩ። ክንብንቤን ገልጬ ሳይ በበር ቀዳዳ ብርሃን ገብቶ ቤት ውስጥ መፈነጣጠቅ ጀምሯል።
"እማዬ!" አልኩ።
"አልነጋም! ፉንጋዬ!" ዐሎቷን አቋርጣ መለሰችልኝ።
"አንቺ በነውሮ ልታስቀድሚኝ ነው!" አልኩና ከአልጋዬ ላይ ዘልዬ ተነሳሁ። እርሷም ተነሳች። ልብሴን መለባበስ ጀመርኩ። ሸራ ጫማዬን ተጫማሁ።
"ፉንጋዬ!" ከውጪ ቀጪሳው ተጣራ።
"መጣሁ!" ያዘጋጀሁትን አበባ አነሳሁ።
እማዬ ከአልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ቀሚሷን እያጠለቀች "ይኸውልህ ፉንጋዬ፣ መንገድ ላይ ቆሻሻ ነገር ካጋጠመህ እንዳትረግጠው፤ ደንቃራ ነው ተጠንቀቅ። አበባ ሰጥተህ እምታገኘውን ፍራንክ ልጆች አታለው እንዳይወስዱብህ ቶሎ እኔጋ አምጣ፣ አጠራቅምልሃለሁ። ና ቆይ! ፊትህን ቅባት ልቀባህ" ብላኝ በዲናሬ ገዝታ ያስቀመጠችውን የአንበርሞታ ብልቃጥ አን ስታ ከፍታ በእጇ እየበሰች ፊቴን ቀባችኝ። የበሩን መቀርቀሪያ ከፈተችልኝና ሸኘችኝ።
ለሰፈራችን ሰዎች ቶሎ ቶሎ ሰጠሁ። እማማ አመለወርቅ እማማ በለጡ ብልጧ ስሙኒ ስሙኒ ሰጡኝ። አለሚቱ አንጎሏ "በጓላ ና!" አሉኝ። ካሳሁን ስሙኒ ሰጠኝ። ለወሰኔ እናት ስሰጣ ቸው። ባልና ሚስቱ ሳቁብኝና "ፉንጋዬ፣ አንድ ቤት እኮ እንድ አበባ ነው የሚሰጠው። የወሰኔ እናትና የኔን ፉንታ ነው አንድ ላይ ስሙኒ የሰጠሁህ" አለኝ ካሳሁን።

አፍሬ ስሸኮረመም የወሰኔ እናት እየሳቁ "አይዞህ ፉንጋይ፣ አምጣ:: እኔ ስሙኒ እሰጥሃለሁ" ብለውኝ መቀነታቸውን እየፈቱ "አድገህ ትምህርትህን ስትጨርስ ምንድነው የምትገዛልኝ?"

"ሬዲዮን::"

"አሂሂሂ ፉንጋይ!" እማይደርስ መስሎሃል? በል ቶሎ በል ጓደኞችህን ቅደማቸው" ብለው ስሙኒውን ሰጥተውኝ ወጣሁ::

ፍራንኮቼን ለእናቴ ሥወስጀ ስሰጣት "አሁን ያሰብክውን ለመግዛት ምንም ያህል አልቀረህም" አለችኝ::

ወደ ዘመዶቼ ቤት ሄድኩኝ:: ቱማ፣ ጫቦ፣ ጩቱሶ ሽልንግ ሽልንግ ሰጡኝ:: ዱማ አንድ ብር፣ አባባ በርታ ዲናሬ ሰጡኝ::..

እማማ ሽጊቱ በግዘፉ ቁመናቸው ቁልቁል እየገረመሙኝ "ፉንጋዬ መጣ:: ቱሶ፣ አንድ ነገር ስጠው!" አሱና ጓዳ ገብተው አንዳች እሚያክል ዳቦ ይዘው መጡ::

እዚህ ቤት፣ አይደለም በዓመት በዓል ቀን ባዘቦቱም ቀን የራበው "እስኪ ሽግዬን ሰላም ብያት ልምጣ" ብሶ በመግባት የሚበላና የሚጠጣበት ነው:: ሁሌም ጠረጴዛ ላይ ትሪው ሰፈድ ተከድኖ እንግዳ ይጠብቃል:: ሰው ሲመጣ ሰፈዱ ይነሳና፣ በቂ እንጀራ ተሌስበት ተጨምሮበት፣ ካለም ወጥ ወጥቶበት፣ ከሌለም ድልህ ተደርጎ እንግዳው የቻለውን ያህል ከበላ በኋላ ገበታው በሰፈድ ይከደናል:: ጠላም ካለ ይጠጣል:: ቢጠፋ ቢጠፋ ሽጊቱ ከማጀታቸው ቅራሪ አያጡም::

የሰፈር ልጆች አንድ ጥፋት ካጠፉን ጥፋተኞቹን ሰብስበው ገርፈውን መደምደሚያው መብላት ነው "እምቢ! በቃኝ" ማለት አይቻልም::

አባባ ቱሶ ስሙኒ ሲሰጡኝ ለራሴ ጉዳይ ደበቅኪት:: አበረ ሻቃ ከኋላዬ ሲመጣ ዳቦዬን ሰጥቼው ወጣሁ:: እማማ ሽጊቱ በእኔ ምትክ ሻቃን በማግኘታቸው ተገርመው "ይሄ አውደልዳይ ዳቦዬን ጥሎ ሄደ? ቆይ አንት ጋንደያ እዚህች ቤት ድጋሚ ትመጣታለህ!" ብለው ሲገስፁኝ ከኋላዬ ይሰማኛል:: አነጋገራቸው የጥላቻ ስሜት የለበትም::

የዘንድሮው ዕንቁጣጣሽ በጣም አስደሳች ነበር:: አበቦቼን ሁሉ ሰጥቼ ጨረስኩ:: ጉረቤቶቻችን ብዙ ሽልንጉች፣ ከርኩች፣ ዲና ሬዎች ሰጥተውኛል:: የፍራንኩ ብዛት ቁጥሩን አሳሳተኝ:: ያም ሆነ ይህ ብዙ ገንዘብ አግኝቻለሁ:: ያሰብኩትን ሁሉ እንደምገዛ እርግጠኛ ሆንኩኝ:: በዱምቡሉ አራት ከገዛሁት ደስታ ከረሜላ አንዷን ከመ ጠቅለያዋ ፈትቼ እየመጠጥኩ እማዬን ሂሳብ እንድናደርግ ጠየቅ ኩዋት::

"መለዮህንና ማሊያህን እሚገዛልህ አምስት ሽልንግ አለህ" አለችኝ:: ተደሰትኩ:: (ዳቦ ብላ ብሰው እማማ ሽጊቱ ባያስቀም ጡኝ ኖሮ ብዙ እሸቅል ነበር)

እቤት ቁጭ ብዬ እማዬ ጠበሳ የሰጠችኝን ሥጋ እየበላሁ የአንዳንዶቹ የነረቤቶቻችን ሁኔታ ትውስ አለኝ::

አንድ ዓይናው አባባ አጋፋሪ ዓይናቸውን አፍጠው አበባ ወቼን አንድ በአንድ እያዩ "ይሄ ማን መሆኑ ነው?"

"እመቤታችን ከጌታችን ጋር ነች!" አልኳቸው:: መሰዮአቸውን ሲያወልቁት ፀሐይ አርፎበት እማያውቀው መላጣ አናታቸው ነጭ ሆኖ ያብለጨልጫል::

"ይኼ ጌታችን መሆኑ ነው? ኧረ ልጅ ሳይሆን ትልቅ ሰው ነው እሚመስለው! አስተያየቱስ ቢሆን? ኤዲያ! ይሄ አላማረኝም:: ቀይርልኝ::"

ቅዱስ ሚካኤል ጎራዴውን መዞ ሣጥናኤልን ሲቀጣ እሚ ያሳየውን አበባ ሰጠኋቸው::

"ምነው ሰይፉን ጎራዴ አስመሰልከው?"

"ጎራዴና ሰይፍ ያው አይደሰም?"

"ዝም በል! ጎራዴና ሰይፍ አንድ ነው ይለኛል? 'ልጅ ስናትዋ ምጥ አስተማረች' እሺ ይሁንልህ፣ ደግሞስ ሸ. በክንፉ ሸ. ባክናፉ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል አንድ ብቻውን በሳጥና ኤል ላይ ዘምቶ ሳልከው? አይ የልጅ ነገር! እስኪ ሌላውን አሳየኝ::"

የቅዱስ ገብርኤልን ስሰጣቸው፣ አፍጠው ሲያዩት ዓይናቸው እንደዓሣ ዓይን ቅንድብ አልባ ሆነ:: ትንሽ ፊገግ ብለው "የም ሥራች ነጋረው ኃያሉ ቅዱስ ገብርኤል ምነው በእሳት ላይ መራመዱን፣ በሚንተገተግ እቶን ላይ ማዝገሙን ገደፍከው?" ብለው ሁሉም ሥዕሎች ላይ አቃቂር አውጥተው በገንቦ አበባ የተደረገ ገበትን ሥዕል መረጡ::

ራስጌያቸው ካስቀመጡት ዝርዝር ፍራንክ ከርክ አንስተው እየሰጡኝ "እደግ ልጄ! የሰለሞንን ጥበብ፣ የማቴሳላን ዕድሜ፣ የኢዮብን ትእግስት እርሱ አንድዬ ይስጥህ! እናትና አባትህን ሟሪና ቀባሪ ያድርግህ" ብለው መርቀውኝ "ያ አባትህ እንዴት አደረ?"

"አንበሳው ሲያገሳ እርሱ ነው የነገረኝ::"

"መናገር ጀመረ? ለርሱ ለአንድዬ ምን ይሳነዋል? አይዞህ እየተሻለው ነው" ብለውኝ ወጣሁ:: ስከርሞው ስአባባ አጋፋሪ አበባ እምሰጣቸው መጨረሻ ላይ ነው ብዬ እየዛትኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: እቤቴ ስገባ የሥጋ ጥብስ ሽታ አወደኝ::

"ሥጋ ክየት አመጣሽ?"

"ዕድሜ ላንተ! አንተነህ የገዛህልን::"

"አበባ ሰጥቼ ባመጣሁት ፍራንክ?"

"ታዲያ እግዚአብሔር ውለታህን ይክፈልህ። በአምስት ሽልንግ ግማሽ መደብ ከማርገኛ ገዝቼ መጣሁ። አሁን ደግሞ ቡና አፈላና ቤታችን ዓመት በዓል ዓመት በዓል ይሸታል።"

ኩራት ተሰማኝ። "ግን ከማሊያዬና ከመለዮዬ መግጥ ፍራንክ ላይ ወስድሽ?"

"በፍፁም! ክርሱማ አልነካብህም።"

ተደሰትኩ። ብር ከስኳኒውን ሰጥታኝ ከጉልት ሄጄ መለዮዬን ከነመነፅሩ እንድገዛ ጠየቅኳት።

"ያታልሉሃል" ብላ እምቢ አለችኝ።

በዚህ ስንጨቃጨቅ የክርስትና እናቴ እማማ ቦጋለች አንድ በዳንቴል የተሸፈነ ሳህን ይዘው ገቡና "ምንድነው?" ኮስተር ብለው ጠየቁኝ።

ነገርኳቸው።

"ስጪው፣ ጓደኞቹ ውጪ አሉ ያጋዙታል" ሲሉ ፈጥኜ ወጥቼ እኔ ያሰብኳትን ባለመነፅሩን ባርኔጣ ያደረገውን ሲሳይ ንቢጥን ጠራሁት። አንድ ዓይና መነፅሩን ዛሬ ቀይሮታል።

"ና! ባለመነፅር ከፍያህን ለማዬ ግባና አሳያት!"

"እሺ" አለና እየዘነጠ ከፊትከፊቴ ተራመደ። እናቴን በዚያ ፈጣን ምላሱ አሳመናትና ብር ከስኳኒውን ተቀብለን ወደ ጉልት ሄድን።

"የበግ ቆዳ ያለው?!" እየፎገሸ ይለፍፋል ነጋዴው።

"የዶሮ ቆዳ ያለው!" አብረውት ይጮኻሉ የሰፈር ልጆች። ነጋዴው ፀጥ ብሏቸው ሥራውን እየለፈፈ አለፈ።

ከገበያ ስንመለስ የሰፈር ልጆች እኛ ቤት አበባዬሆይ ይጨፍራሉ። አስናቀች በድርብ ጥርሷ እየሳቀች ክበሮ ትመታለች። መሠረት፣ ሰብለ፣ ፋንቲሽ፣ ወሐይ፣ አሰገደች፣ ሃዋ፣... እያጨበጨቡ ይቀበሏታል። የካፊያው ጭቃ ከቤት ቤት ሲዞሩ ጫማቸው ላይ ክፈፍ ሠርቷል። ሽራ ጫማ፣ ኮንጎ ጫማ፣ ባዶ እግር ይታየኛል። የአገር ባህል ልብስ፣ ሻማ፣ ሽንሽን ለብሰው ዘንጠዋል። እማዬ ስሙኒ ሰጠቻቸው።

"ክብረው ይቆዩን ክብረው
በዓመት ወንድ ልጅ ወልደው
ሠላሳ ጥጆች አስረው...
ክብረው ይቆዩን ክብረው"

በመነጥሬ ሳያቸው አረንጓዴ ይመስላሉ። ጎረቤታችን እማማ በለጡ ቤት እየጨፈሩ ሲሄዱ እኔ ወደ ጓደኞቼ ሄድኩኝ።

ቀጪሳው ፊኛ ይነፋል፣ ተረፈ ገልጆ ሆዱን እያባበሰ ስለ በላው ምግብ ደስ እያለው ያወራል፣ ንቢጥ መነፅሩን አስሬ እያስ

ተካክለ ሲያድግ ስፖርተኛ እንደሚሆን ያወራል፣ ሴምላል ከረሜላውን ቆርጥሞ ያካፍለዋል፣ ሻቃ ስለሚገዛው ባለብር ኳስ ይናገራል፣ ይጥና ትምህርት ቤት ሲገባ ስለሚገዛቸው ደብተሮች፣ እርሳስና ላጲስ ላውራ እያለ ይወተውታል፣...

...አለሚቱ አንጎሏ አበባዬን ተቀብለው ፍራንኬን ሳይስጡኝ ብዙ አመላለሱኝ። እንደዋዛ ጎራ እያልኩ በሌላ ጉዳይ በበራቸው የማልፍ እየመሰልኩ ታየኋቸው። እርሳቸው ግን እስከነመፈጠሬም የረሱኝ መሰሉ። በመጨረሻም እኔም የማለቃቸው፣ እሳቸው የማ ይሰጡኝ ሆነን እንደተፋጠጥን፣ ዕንቁጣጣሽ አለፈ።

በማግሥቱ በራቸው አጠገብ ከጓደኞቼ ጋር ስንጫወት ጠሩኝና ስሙኒ ሰጡኝ። ድካሜን፣ ቋንቋ አልባ ውትወታዬን ሁሉ ረሳሁት። ለነገ "ሙቪ" መግቢያ ቼላ ኖረኝ!!!

"በእውን ልብ"

"በህልሜ ቢራቢሮ ሆኜ እየበረርኩ ነበር፣
ሰነቃ ለካ ሰው ነኝ።
እንግዲህ እኔ ሰው ነኝ?
ወይስ ቢራቢሮ?"

ላኦትዙ

ሰሞኑን ተገረገዙኝ። ግርዛቱ የተካሄደው በድንገት ነበር። ትምህርት ቤት ውስጥ ልጃገረዶችና ወንድ ልጆች የምንጠቀምበት ሽንት ቤት አንድ ነው። ወረፋ ጠብቀን እንጠናቀቃለን።

ሽንቴን ስሸና ሁሌም በጥንቃቄ ነበር። ድንገት አንድ ቀን በሩን መለስ ሳላደርግ ስሸና ነገረኛዋና እንቅርታሚ ሚሚ አየችኝ። እየተሸማቀቅኩ ወጣሁ። ክፍል ገብተን አስተማሪ እስኪመጣ እንንጫጫለን። ብድግ አልኩና "ዝም በሉ እንጂ!" አልኩ።

ይሀን ጊዜ "ባንልስ፣ ወሸላ!" ሚሚ አለችኝ።

ከዚያ ያደረግኩትን በቅጡ አላስታውስም። ከፊቴ የነበረውን ዴስክ ዘልዬ ሚሚ ፊት ደረስኩኝ። በቦክስ አገጯዋን ነረትኳት! መሬት ተዘረረች። ደብተሬን ይዤ ከክፍል ሮጬ ወጥቼ እያለቀስኩ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ። ሚሚ እኔ ከጉዳቷት የባሰ ስድብዋ ቅስሜን ሰብሮታል። ማልቀሴን ሳላቆም ቤት ደረስኩኝ። በጊዜው አባቴ አገር ቤት ሄዷል። ለእናቴ የገጠመኝን ችግር ነገርኳት። አረጋግታኝ እንጎቻ ሰጠችኝ። ወዲያው ጉልት ሄዳ አንዲት ዶሮ በሦስት ሽልንግ ገዝታ መጣች። የማዘጋጃ ቤት የመ

ዝነብ ቤት ሹም የነበሩት አባባ ዶላሞ ደጋጋ የዓይን አባቴ ሆነው ተገረዝኩኝ::

ከዚህ በኋላማ ባገኘሁበት ሁሉ መሸናት ብርቅ ሆነብኝ:: ሽንቴ ቶሎ ቶሎ እንዲመጣ ውሃ በብዛት አጠጣለሁ:: ሽንቴም እንደመጣብኝ ግድግዳ ተደግፌ ፊቴን ወደ አላፊ አግዳሚው መልሼ እየሸናሁ፣ ወሸላ ማን እንደሆነ አሳያቸዋለሁ!!

አባቴ ከጋሞጎፋ መጥቶ ስለ ጉዳዩ ሲሰማ ደነገጠ:: ባህሉን በመጣሳችንም አዘነ:: ብዙ መሳቀቄን ስለሚያወቅ ጤናማ ግርዛት እንዲሆንልኝ ከአገሩ ሰዎች ጋር በባህሉ መሰረት የሚደረገውን ፈፀመ::

ብዙ ጊዜ ሽንቴን የምሸናው አባባ ዘውዴ ግቢ ጥግ በበቀለው ግራዋ ስር ነበር:: ከትምህርት ቤት ስመጣ ወይም አረብ ቤት ተልኬ ስመለስ፣ ልክ ግራዋው አጠገብ ስደርስ ሽንቴ ይመጣል፣ እሸናበታለሁ::

አሁንም ልክ እንደወትሮው ልሸና ስል "ተስፋዬ፣ መሺለ ኪያ አድርግና ሽና እኔ እሾልካለሁ" አለችኝ መኩዬ ቀጫጫው::

"እኔም!" አለ ውሮ::

"እሺ!" አልኩኝ:: የቁምጣዬን አንድ እግር ገልጬ እየ ሸናሁ ልክ ሊሾልኩ ሲሉ፣ የተገረዘውን ቁላዬን እሰብቅና ሽንቴን አላያቸው ላይ ለመልቀቅ በሆዴ አስቤያለሁ:: ውሮ ባይጠረጥረ ኝም መኩዬ በንቁ ዓይኖቿ እያስተዋለችኝ ነበር::

መሸናት ጀመርኩ:: ጭኔ በቁንጥጫ ደበነ:: "ምነው በስተ እርጅናህ ትሸናብናለህ?" በጨለማው ያባቴ ድምፅ ተሰማኝ::

ጋቢ ትከሻዬ ላይ ጥሎ "ውጣ! ውጪ ውጣና ሽና!" አለኝ::

"አልፈልግም! በአያ ጅቦ ልታስበላኝ!?"

"እንክት ያድርግህ!"

እማዬ መብራት አበራች:: ፍርሃቴ በግማሽ ለቀቀኝ:: አባቴ በሩን ከፍቶ፣ "ውጣ ብዬሃለሁ!" አለና ገፋኝ:: የኋሊት አፈ ገፈግኩ፣ አያ ጅቦ ሲጮህ ሰማሁት:: ወደ ጓዳ ላፈትልክ ስል አባቴ ለቀም አደረገኝ:: በሳቅም በንዴትም እያጉተመተመ ወደ ፊት ገፋኝ:: በእኛ ቤተሰብ ውስጥ እሁድ ማታ በጊዜ የመተኛት ልማድ ነበረ::

"ኡ! ኡ!" ጮህኩ::

አያ ጅቦም ጮኸ::

አባቴ ትቶኝ ወደ ውጪ ወጣና "ይኸው፣ እኔ ደጅ ነኝ:: ለምን ጅብ አይበላኝም?"

"ኧረ! እማላውቅ መሰለህ? አንተ ኮ ትልቅ ሰው ነህ::" ሳቁን ለቀቀው::

እማዬም ተነስታ የሸናህብትን ልብስ እያራገፈች ትስቃለች::

"ሂጂ! ጥርስሽ ይርገፍ! ምን አለ ራቱን እንደበላ ሸንቱን በጊዜ ብታሸኚው? በእሱ ሸንት እንድታጠብ የምታደርጊኝ አንቺ ነሽ!"

"እኔ ምን ላርግ? ሽና ስለው አልመጣብኝም ይላል:: ወይ አይነጥላ ይኖርበት ይሆን? እንዳመጣብን መቻል ነው::"

"እስከመቼ? ውጣ ጋሼ!"

ኮሽታ ሳላሰማ በጥንቃቄ እየተራመድኩ በሩ ደፍ ላይ ደረስኩ:: በግማሽ እንቅልፍ እዚያው ቆሜ መሸናት ጀመርኩኝ::

ከቤታችን ጓሮ ጅቡ ጮኸ:: ጆሮዬ አጥርቶ መስማት ጀመሯል:: ጅቡን ሳቅ ያፈነው የሰው ድምፅ አጅቦታል:: አንድ ተን ኮለኛ የሰፈር ልጅ ጓሮ እንዳለ ገዛኝ:: ዶጅ ገማጣው እየሳቀ ወጣ:: ወይኔ! ዛሬ የፈራሁትን ነገ ለጓደኞቻችን ነግሮ ያስቅብኛል!! እያልኩ በሆዴ እማዬ ወለዳ አስተኛችኝ...

..."ፉንጋይ! ፉንጌ! ኧረ ስድስት ሰዓት ሆኗል ተነሳ!" እማዬ ነች:: በእማዬ እምነት እንቅልፍ ድህነት ነው:: ሥራ ከሌላት በጊዜ መተኛት፣ በሌሊት መንቃት ፕሮግራሚ ነው:: ስለሆነም ልጇን በጊዜ አስተኝታ 'ተነሳ ስድስት ሰዓት ሆኖዋል!' ስትል፣ ምናባት ጊዜው ግን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ይሆናል::

መጫወቻ ፍለጋ

"ሕፃናትን በእጆቻችን ልናቅፋቸው ባንችል፣ በልባችን እንቀፋቸው"
ሪደር ዳይጀስት መጽሔት

የሠፈር ልጆች ቅዳሜ-ቅዳሜ መጫወቻ ፍለጋ ዙረት እፃሔድ ነበር:: ብዙውን ጊዜ ምርጫችን ፈረንጆች ቤት ጓሮ ማንጎዳጎድ ነበር:: ፈረንጆቹ ከቤታቸው አጥር ግቢ ውጪ ጉድጓድ ቆፍረው ቆሻሻውን እዚያ ይጥሉታል:: ዘበኞቻቸውም ጠቃሚ የሆነውን ዕቃ ይቃርማሉ:: በተቀረው ላይ እሳት ለኩሰው ይለቁበታል:: አንዳንዴ ከመቃጠሉ በፊት ደርሰን ደጋግ ዘበኞች ካጋጠሙን ደስ ያለንን ዕቃ እንወስዳለን:: ግን ብዙውን ጊዜ የሚያጋጥሙን እርጉም ዘበኞች ስለነበሩ ያባርሩናል:: ሸሽተን ከሌላ ቪላ ቤት ጓሮ ፍለጋችንን እናጧጡፋለን::

ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ብትንትኗ የወጣ አሻንጉሊት አገኘን:: ቀጪላው ከትከሻዋ እስከ ዳሌዋ ያለው የአሻንጉሊቷን አካል ሲያገኝ "ባትጋሩኝ! በትኩስ እንጀራ በመርፌ ቀዳዳ!" ብሎ ጮኸ::

አሻንጉሊቷ ጭንቅላት፣ እጅና እግር እንደሌላት ካስተዋለ በኋላ "በእናታችሁ ልጆች! የተቀረውን አካሏን ካገኛችሁት ትሰ ጡኛላችሁ?" የአሻንጉሊቷ ሙሉ አካል ከተገኘ ልብስ ሰፍተንላት ሁላችንም እንጫወትባታለን::" አለ ቀጢሳው እየተለማመጠን::

ብዙም ሳይቆይ ኃይሉ ዶሮ "ባትጌ!" አለና ጮኸ:: የአሻን ጉሊትዋን እጆች ሸቅብ እንደዋንጫ ሰቅሎ እያሳየን::

"ለቀጢሳው ስጠው" እያልን ሁላችንም ሰመነው::

ሰጠው::

"ዶሮ ደግ ልጅ ነው" አልን ሁላችንም፣ ቆሻሻውን ማገለ ባበሱን እየቀጠልን::

የቆሻሻው ትንፋግ አይነሳ! አዋቂን ሰው ከአገር ያስለቅ ቃል:: እኛ ግን መጫወቻው በልጠብን ያንን ከርፋት የልጅነት አፍንጫችን ችሎታል::

ከጥቅም ውጭ የሆኑ የሕክምና ዕቃዎች፣ የምግብ ማሸጊያ ፓኮዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ አርተፊሻል ፀጉር፣ የፀጉር ማስያዣ፣ ካር ቶኖች፣ ፊኛዎች አገኘን:: ፊኛውን እየተቀባበልን ነፋነውና ተጫ ወትንበት:: (በበኋለኛው የሕይወት ዘመኔ ፊኛ እያልን ስንነፋው የነበረው ኮንዶም እንደነበረ ተገንዝቤያለሁ::)

እዚያው ትንፋጉ ላይ ሆነን አስቂኝ ትዕይንት እየሠራን ያንን መራር ሕይወት እናጣፍጠው ነበር:: ቀጢሳው ግማሽ ጎኑ የተቃጠለውን አርተፊሻል ፀጉር አናቱ ላይ አድርጎ፣ የተሰበረ የፀጉር ጌጥ ሰክቶበት እንደ ፈረንጅ ኮረዳ እየተሽኮረመመ "ዊስ ዋይስ" ብሎ በራሱ እንግሊዘኛ ተናገረ::

ጎቢጥ ያንን አንድ ዓይኑ ላይ መስታወት የሌለውን መነ ፅሩን አደረገና አፉ ላይ የሲጋራ ቁራጭ ወትፎ እንደ ፈረንጅ ጎረምሳ ጎርነን ባለ ድምፅ "ዋት ኢዝ ዊስ ዋይ?" አለ በብረት ዘንግ ቆሻሻውን እየቆፈረ:: የአሻንጉሊትዋን እግሮች አገኘ:: ለቀ ጢሳው ሰጠው::

ቀጢሳው ቻርሊ ቻፕሊን ፊልም ላይ ባየነው ስልት በደስታ ተውረግርጎ ሹል አፉን አሞጠሞጠና ሲሳይ ጎቢጥን ሳመው::

ፍስጋችን ቀጠለ:: ውሮ አንድ ነገር ደብቆን ኪሱ ሊከት ሴምላል አየውና "ምን አገኘህ?" ሲል ጠየቀው:: ሁላችንም ካቀረ ቀርንበት ቀና አልን:: ውሮ ቁንጮውን እያከከ "ምንም አላ ገኘሁም!" አለ፣ ኪሱን ጨብጦ ላለማስፈተሽ እየሞከረ::

"እስኪ እናቴ ትሙት በልና ማል?!" ሲል ሴምላል ንፍጡን ሸቅብ እየሳበ ጠየቀው:: ውሮ መማሉን ፊራ:: በዚህ ምልልስ ወቅት መኩዬ ቀጫጫው እንደ እባብ ተሰባ ከውሮ ኋላ ደርሳ ከኪሱ በፍጥነት አንድ ነገር ስትስብ የአሻንጉሊቷ ጭንቅላት መሬት ዱብ አለ::

"ወይኔ አሻንጉሊቴን!" ሲል ውሮ ጩኸቱን አቀለጠው:: መኩዬ ቀጫጫው የአሻንጉሊቷን ጭንቅላት ከመሬት አንስታ እየ ደባበሰች ለቀጢሳው እንዲሰጠው ለመነችው::

ውሮ "እምቢ" አለ::

ሁላችንም ብንለምነው ችክ አለ:: እርሱም የራሱ አሻን ጉሊት እንዲኖረው፣ የተቀረውን አካል በሸቦና በጨርቅ ሠርቶ ሊጫወትበት መፈለጉን በልቅሶ ዜማ አወራን:: በዚህ ራስ ወዳ ድነቱ ሁላችንም አኮረፍነው:: መኩዬ ቀጫጫውም የአሻንጉሊ ቷን ጭንቅላት አፍንጫው ላይ ወረወረችለት::

ጀንበር ጠለቀች:: እኛም ያገኘነውን ኩተታ ኩተት ታቅፈን ወደ ሠፈራችን ጉዞ ጀመርን:: ውሮ ስላኮረፍነው በርቀት ይከ ተለናል:: ጥሰነው መሄድ ግን አንችልም:: እናቱ እማማ የወርቅውሃ "ልጄን የት ጥላችሁት መጣችሁ?" በማለት ሁላችንንም ስወላጆቻችን ከሰው ያስገርፉናል:: በዚህ ምክንያት ጉዟችን አዝ ጋሚ ሆነ:: ሻቃ ተናደደና ቶሎ እንዲከተለን ተቆጥቶ ተናገ ረው:: ውሮም ሲመልስ "እኔ መንገዱን አውቀዋለሁ:: ቀስ ብዬ እመጣለሁ::"

ቀጢሳው በጣም ተናዶ "እኛ ቶሎ ቶሎ እንሂድ:: ውሮን ተውት ይንቀራፈፍ:: ቀድሞን እንዲራመድ እኔ አደርገዋለሁ "አለ ንና፣ በጣም የምንወዳትን ፉጨቱን እያፏጨ በረጃጅም ቅል ጥሞቹ በፍጥነት መራመድ ጀመረ:: እኛም ሱጨቱን እያዳመጥን ተከተልነው::

አንዱን ፀጥተኛ የባለፀጋዎች ሰፈር አልፈን መታጠፊያው ላይ ስንደርስ፣ ቀጢሳው የአንዱን ሞጃ ቤት መጥሪያ ተጫነው:: በሩጫ ከአካባቢው ራቅን:: በርቀት ስናደምጥ "ወይኔ! እባባ እኔ አይደለሁም የደወልኩት!!" ብሎ ውሮ ይጮኻል::

ዘበኛው "አንት ነጫጭባ ጥፋ ከዚህ" ብሎ በመጮህ በድ ጋሚ ሲዝልጠው ተሰማን::

እኛም እየሳቅን ፍጥነታችንን ጨመርን::ውሮ እየሮጠ ደርሶብን "እንዳስገረፋችሁኝ እኔ ደግሞ ሰፈር ስንደርስ እያንዳን ድሽን ባላስወግርሽ ሞቻለሁ!" አለና እያላዘነ ቀደመን::

"የእኛን ቤት መጥሪያ ተጫንና እኔን አስገረፈኛ!" አለና ቀጢሳው አላገጠበት:: ውሮ በጣም ጮኸ ማልቀስ ጀመረ:: እኛም እብረነው ጮኸን:: በዚህ ወቅት አንደኛው የሀብታም ግቢ ተከፈተና "ይጩኸባችሁ እና! ምን አባታችሁ ታላዝናላችሁ፣ እናንት ገፊዎች!" ሲል በትር የያዘ ዘበኛ ተላደበ::

"ኧረ! እበት አባትክ ብላ!" ይዋና መለሰለት::

ዘበኛው ያባርረን ጀመር:: ሮጠን አመለጥነው:: የእር ግማኑን መአት ሲያወርድብን ከኋላ ይሰማናል:: ውሮ ማላዘኑን ትቶ በፍጥነት ከሁላችንም አይላል::

ረጅሙን መንገድ እንዲያሳጥርልን ከዘበኛ ጋር መላከፍ አንዱ ብልሃታችን ነበር። የቀረውን መንገድ ለመግፋትም ቀጢሳው ጨዋታ እንዲያመጣ ጎቢጥ ኮረኮረው።

"ቀጢሳው ስለትናንትና ማታዋ ወተት አውራልን?!" ቀጢሳው ጫሩን ከነገሩት ነገሯን የጥበብ ሽማ አልብሶዋት ይተርክልናል።

"እ! ወተት? የሚገርጅ እኮ ነው። እናቴ ትሙት! ወተቷን አሁንም ሳስባት ይገርመኛል!" አለ ቀጢሳው እንድናምነው መሐላውን እያስቀደመ። "እማዬ ማታ ልብ ሳትል ወተት በኩባያ ሰጠችኝ። ወይ ልጅ ነው ብላ ይሆናል። እኔ ግን እያማለሁ። ዝም ብዬ ተቀብዬ ተነነጨኋት። ትዝ ይለኛል ቀኑ አርብ ነው። የተነነጨሁትን አልውጠው ነገር ያሚን ያበላሽብኛል። እንዳ ልተፋው ወተት ነው። እኔ ደግሞ ወተት በጣም እወዳለሁ። ጉንጬ ውስጥ እንደያዝኩት ትኝት አልኩኝ። ጠዋት ስነሳ አፌ ውስጥ ወተቷ እርግት ብላለች! ዋጥ ሳደርጋት ልቤን አቀዘቀዘች!"

"ኡ ሌላ ነው! አሪፍ! እስቲ የድንቹን አውራላቸው" አልኩት።

"እ! ድንች! ድንችሽክን! በቀደም ዕለት በምሳ ሰዓት እቤት ስገባ እማዬ የለችም። በሸክላ ድስት ድንች ወጥ ተጥዶ በከሰል ምድጃ ላይ ይንተከተካል። ተክ! ተክ! ተክ! ተክ! ሲል አንድዋ ድንች ብቅ ብላ ሌላኛዋ ትሰጥማለች። አንዷን አውጥቼ ልብላ? ብዬ ጭልፋ ብፈልግ ብፈልግ አጣሁ። በስኒ ልጨልፍ ስል እጄን አቃጠለኝና አምልጦኝ ወጡ ውስጥ ሰመጠ። ወዲያው አንድ ብልሃት አሰብኩ። በመወዘቻ ቀዝቃዛ ውሃ ሞላ ሁና እጄን ነከርኩት። ከዚያም ተክ! ብላ ብቅ የምትለውን ድንች አቀልብና መወዘቻው ውስጥ እጥላታለሁ። አሁንም እጄን አቀ ዘቅዝና ሁለተኛዋን ድንች አወጣለሁ። አንደኛዋን እገምጣለሁ። አንዲህ እንዲህ ስል ድንቹን በሙሉ በሳሁትና ከቤት ወጣሁ። ትንሽ ቆይቼ ስመለስ እማዬ ወጡን እያማሰለች 'አሁን ከትፌ የጨመርኩት ድንች የት ገባ?!' ትላለች።

ሳቃችንን ለቀቅነው። "አንተ ደሞ የተልባውን ታሪክ ንገራቸው!" አልኩት ሲሳይ ጎቢጥን።

"የተልባዋ ታሪክማ የምትገርም ነች" አለ። "ሱስ ሆና ብኖለች። እማዬ አንድ ክዳን ያለው ጠርሙስ ውስጥ ተልባ ወቅጣ አስቀምጣለች። ወጣ ገባ እያልኩ አንድ ጭብጥ አቅማለሁ። እማዬ ማንን ትጠርጥር? ብታደፍጥም ልትይዘኝ አልቻለችም። የዕቃ ማስቀመጫ ቁምሳጥኑ በር ድሮ ነው የተነነጠለው። ግራ ገባት። እኔም እየሸወድኳት መቃሙን ቀጠል ኩበት። ትናንትና አድብቼ ሄጄ ሱሴን ለመወጣት የተልባ እቃውን ስክፍተው ሙልት ብሏል። እንደለመድኩት ዛቅኩና

ቃምኩ። ሳጣጥመው ሬት ሬት አለኝ። አላስቻለኝም። መሬት ተፋሁትና አፌን እየተጠመጠመጥኩ ስጮህ እማዬ ኩሽና ሆና 'አንተ አጋሰስ! አንተ ነህ ለካ ተልባዬን ቅመህ የጨረስከው? እኔም ሠራሁልህ። ዛሬ የቃምከው የጎመን ዘር ነው!'

ጨዋታው ወደ ፑሉቶ ላይ አነጣጠረ። ፑሉቶ የሚኖረው ከአያቶቹ ጋር በመሆኑ ከሌሎቻችን የበለጠ ነፃነት አለው። የሲኒማ መግቢያ ሲያጣ ከቤት ውስጥ ከሰል፣ ሽሮና በርበሬ ሠርቆ ይሸጣል። ሴት አያቱ በጣም ቢወዱትም የሸጠባቸውን ማገዶም ሆነ፣ እህል ዳግም እንዳይመነትፍ ለመደበቅ ብዙ ይደክማሉ። አንዴ የሲኒማ መግቢያ ሽልንግ ኖሮት የምሳ ስላጣ እኔን አማከረኝ። "እኛ ቤት የአተር ክከ አለ። አንተ በለበስከው የሰርያን ኮት በአንዱ ኪስ ለአንተ፣ በአንዱ ለእኔ ለምን መን ትፈን 'ሙቪ ያችንን' እያየን በክክ አንደበርም?" አለኝ።

ተስማማሁ።

ቤታቸው ጠባብና አንድ ክፍል ነች። በዕቃ መደርደሪያው ላይ በሰፈድ ተሞልቶ የተቀመጠውን ክክ እየዘነነ ኪሴ ይሞላልኛል። አንደኛው ሞልቶ ሁለተኛውን ኪሴን መሙላት ስንጀምር ትከሻዬን ከበደኝና ዘር ስል ወንድ አያትየው በተጠንቀቅ በር ላይ ቆመዋል። ዓይናቸው ፈጠ፣ ከዘራቸውን ቀና አድርገው በጥንቃቄ ያስተውሉናል። ቁርጭምጭሚት ቁርጭምጭሚታችንን እነካክተው ዶሮ ጠባቂ ሊያደርጉን ነው።

"መስፍን! ምንድነው የምትሠራው?" አሉና ሪንጌ ጮኹ። የፑሉቶ እያት አባባ ፊረጃ እንደ ቴክስ አሪፍ ኬፕ ሁልቀን ስለሚ ያደርጉ ሪንጌ እያልን ነው የምንጠራቸው። ፑሉቶም አያቱን አያቸውና አፈጠጠባቸው። እኔ ትንሽ ክክ የሞላሁበትን ጎኔን ወደ እማያዩበት አቅጣጫ አዙሬ ቆሜ ኪሴን ከደንኩ። ሪንጌ አሁንም እንደ 'ስታሮቹ' በተጠንቀቅ እንደቆሙ ነው።

ፑሉቶ በልቅሶ ዜማ "ልሙትልህ ማለት ነው?! በቃ ሙትት እልልሃለሁ" ሲል ሪንጎ ዱላቸውን ዝቅ አደረጉ። ይሄኔ ፈትለክ ብዬ ከቤታቸው ወጣሁ። ከዚያ በርቀት ስከታተል ብዙ አምረው ተነጋገሩና በፍቅሩ ለለተራቱ ያዩትን ሳይሆን. የሰሙትን አመኑለት።

"ፑሉቶ የአንጀራውስ ታሪክ?" አውራልን አልኩት።

"ኡ! ተስፉዬ በእናትህ እሱን ጉዴን እንዳታወራው!" አለኝ።

"ይወራ! ይወራ! ይወራ!" ተንጫጩ ሌሎቹ ልጆች።

መተረክ ጀመርኩ።

"በቀደም ዕለት እኛ ቤት አንዲት ልጅ እንጀራ ልትገዛ መጣች። እማዬ እንጀራውን ጉልት ልትሸጠው እንደወሰደችው ነገርኳት። ፑሉቶ ይህንን ስናወራ ሰማ። እናቱ እንጀራ ጋግረው በመሶብ እቤት አስገብተው ገበያ ሄደዋል። ወዲያው ልጅቱን

ጠራትና አስር እንጀራ በሽልንግ ሸጠላት። አንድ መረቀላት። ሽልንጉን ሸቀለና ወደ "ሙቪ" አብረን ሄድን።

"ልጅቱ እንጀራውን ቤቷ ይዛ ስትሄድ ቤተሰቦቿ እንዴት! ያለ ቆንጆ እንጀራ ነው እንዳያልቅ እንኪ አሁንም የሽልንግ ጨምረሽ ነይ፣ የገበያ ሳይሆን የቤት ይመስላል' ብለው ላኳት።

ልጅት ስትመጣ ፑሉቶ የስም። በምትኩ ሴት አያቱን አገኘችና "እንጀራ ሽጡልኝ"

"የምን እንጀራ?"

"የገበያ እንጀራ።"

"አረ እኔ እንጀራ አልሸጥም አትዬ! ባሎቴ ቤት ሂጂ!"

"እንዴ! ቅድም መጥቼ እኮ ከልጆት ላይ የሽልንግ እንጀራ ገዝቼ ሂጃለሁ!"

"አረ ባክሽ? ያ ወንበዴ ጉድ ሠርቶኛላ!" ብለው ሴት አያቱ ተነሰተው መሶባቸውን ሲከፍቱ አራት እንጀራ ብቻ ነበር መሶቡ ውስጥ የቀረቻቸው!" ስል ፑሉቶ በራሱ ጀብዱ አብሮን ሳቀ።

"እንዴ! ይኼ ብሽቅ በእኛ ታሪክ ይስቃል?! አትሳቅ ከእኛ ጋር። ተጣልተሃል! ፕ! ፕ! ብለንሃል!" አለና ቀጢሳው ውሮ ላይ አፈጠጠበት። ውሮም ደንግጦ ሳቁን አቋረጠ። ለካ ልብ ሳንለው አረግመዱን ከእኛ ጋር አስተካክሉ ወሬያችንን እየኮመኮመ ሲዝናና ነበር።

ሰፋፊዎቹ መንገዶች ጠበቡ። ቪላዎቹ ቤቶች ወደ ኋላ ቀሩ። ፀጥታው በጫጫታ ተተካ። ሠፈራችን ደረስን። ጎደቴ ጠጅ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጠን የዕለቱን ውሎ አብረውን ላል ነበሩ ለሰፈራችን ልጆች መተረክ ጀመርን። ጎቢጥ አንድ ዓይና መነፅሩን በቁንጥ እያስተካከለ እኔን አዳምጡኝ በሚል ስሜት ያወራል።

በዚሁ መካከል "ቀጢሳው!" ሲሉ እናቱ እግግ ልኪስሽ ጠሩት።

"አቤት!" አለና ኮተቱን አደራ ሰጥቶን ወደ ቤቱ ሄደ። ብዙም ሳይቆይ መጮኽ ጀመረ። በጣም ፊሪ ስለሆነ፣ እንኪን ዱላ አርፎበት ኖና ሲዝቱበት ያለፍን ያገደምንበትን መለፍለፍ እንደሚጀምር እርግጠኞች ነን። ውሮ አሳብቆብን ይሆናል ብለን ከመካከላችን ብንፈልገው ውሮ የለም። ስለዚህ ቀጢሳው እሚለውን ሰምተን ራሳችንን ለመከላከል በራቸው ላይ ተለጠፍን አዳመጥን። በበሩ ቀዳዳ ላይ ጨርቅ ስለጠቀጠቁበት ምንም አይታይም። ሻቃ በንዴት ፀጉሩን ነጨና "እናቱን! ውሮ ነው ያስፎገረው!" አለ።

ቀጢሳው ከውስጥ "ወይኔ! ወይኔ! ቁስሌን!" እያለ ይጮኻል። እናቱ ደግሞ "አንት ምናምንቴ! የትም እንደጋኔን ስትዞር ውለህ..." ይላሉ።

ግግሻችን ጎንበስ ብለን፣ ሌሎቻችን በሩ ላይ ጆሮአችንን ለጥፈን እያለን "እሰው በር ላይ ምን ትሠራላችሁ?!" ብለው እግግ ውቢት ሲጮኹብን በርግገን ተበታተንን።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ቀጢሳው ኮትና ቁምጣ ሱሪውን አውልቆ ያባቱን ትልቅ ሹራብ ለብሶ እየተንቀጠቀጠ መጣ። የሹራቡ እጅታ ከመርዘሙ የተነሳ እጁን ሙሉ ለሙሉ ሸፍኖት ተንጠልጥሏል። የአባቱን ትልቅ ነጠላ ጫማ አድርጓል። ሁላችንም ደንግጠን ስናየው ብልጣብልጥ ዓይኖቹን አቁለጨለጨና "ልጆች የተገረፍኩ መሰላችሁ እንዴ? ፅቃዬ የታለ?" አለና "ነገ ዓመት በዓል ስለሆነ እማዬ ገላዬን ስታጥበኝ እኮ ነው የጮህኩት።"

ሁላችንም በሳቅ አውካካን።

ውሮም ቀስ ባለ እርምጃ ከሄደበት መጥቶ መካከላችን ተቀላቀለ። ሁላችንም አኩርፈነዋል። መኩዬ ቀጫጭው "ቅድም ብት መጣ ኖሮ ያሰርገርከው አንተ ነህ ብለን ልንወግርህ ነበር!" አለችው።

አልገባውም።

"እኔኮ የአሻንጉሊቴን ራስ ለቀጢሳው ሰጥቼው አብረን እንድንጫወት ፈልጌለሁ" ሲል ቀጢሳው በዚያች ሹል አፉ ፈጣን በሆነ ስልት ጉንጩን ሳመና ደስታውን ገለጸለት። የአሻንጉሊቷን ራስ ተቀበለው። ውሮን ከዚያች በኋላ ማኩረፉን ተውነው። እንደ ድሮው ሽርካችን ሆነ።

ያ ሁሉ አልፎ፣ በጉርምስናችን ወቅት ቀጢሳው በአገራችን የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ከአንዱ ጎን ተሰልፎ ሞተ። ለእኔ ግን ሁልጊዜ በዓይነ ህሊናዬ ይታየኛል። ጭብጥ እግትሞላው ጭንቅላቱ፣ ብልጣ ብልጥ ትንንሽ ዓይኖቹ፣ አሬፍ የፉጨት ድምፅ እምታወጣውና ስትንርስ እንደ ፕላስቲክ እምትለጠጠው ሹል አፉ፣ ረጃጅምና ቀልጣፋ ቅልጥሞቹ አሁንም ይታዩኛል። ሁሌም ቀጢሳውን ባሰብኩት ቁጥር የሚታየኝ አካላቱን እናቱ ሲያጥቡት እሱ ሲጮኽ ነው።

ጎግ፣ ጎግው ላይ ብረት ምጣድ፣ ከዚያ ላይ በርጩግ፣ በርጩግው ላይ ቀጢሳው ራቁቱን ተቀምጦ ቆዳው እንደሚቀረደድ ሁሉ እየተንጣጣ እናቱ ሲፈትጉት ይቆይና አካላቱን ታጥቦ እንዳጠናቀቀ በቁንጥ ፈገግ ብሎ "ፉንጌ፣ ነገኮ ዓመት በዓል ነው። አካላትህን አትታጠብም?" ይለኛል።

አገራችን በልቧም ሆነ በእጅቿ ያላቀፈችው ቻውልድ እንዲህ ሆኖ ማለፉን ሳስብ ልቤ ይደማል።

---

* ማስርገር፣ ማሳጣት፣ማቃጠር።

ትንቢት

"ሥሌም ከምንወደው ነው የምንማረው"
ገተ

ልጅ ሆኜ ከሚናፍቁኝ ዓውደ ዓመቶች አንዱ መስቀል ነበር። አባባ ጃንሆይ፣ ፍሙሳፍንቱን፣ መኪንንቱን፣ ልዑሳኑን፣ ልዕልታቱን፣ ጳጳሳቱን፣ ኢጲስቆጶሳቱን እስከትሰው በግልጽ አውቶሞቢል ሆነው ለሕዝቡ ሸላምታቸውን እየሰጡ ወደ ተዘጋጀላቸው ሰገነት ወጥተው ዙፋናቸው ላይ ይቀመጣሉ። ሕዝቡ በእልልታና በጭብጨባ ምድሩን ሲያደበላልቀው እኔ አባቴን "እንኮይ አድር ገኝ" እለዋለሁ።

"እንዴ! ፉንጋይ፣ የለበስኩት ነጭ ልብስ ይቆሽሽብኛል!። ያለኸው ፊት ነው፣ ከዚህም ይታይሃል።"

"ሰዎቹ በፊቴ ወዲያና ወዲህ ሲያልፉ እየከለሉኝ እኮ ነው። ተሸከመኝ። ልብስህን የምታጥበው እማዬ አይደለችም?"

"አ ጋሼ! አንተን ማን ይችልሃል? እሺ ልሸከምህ።"

ሰዎቹን ቁልቁል ማየት እጀምራለሁ። ከፊት ለፊቴ ፈረሰኛ ፖሊሶች ከወዲህ ወዲያ እየተዘዋወሩ ሥርዓት ያስከብራሉ። እግረኛ ፖሊሶች በገመድ ከተከለለ አጥር ማዶ ሆነው ፀጥታውን ይቆጣጠራሉ። ፈረንጆች ፎቶግራፍ ያነሳሉ።

ለልፈኛው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት መትመም ይጀምራል። ይዘምራሉ።

አበባዬ
መስከረም ጠባዬ!
መስከረም ሲጠባ!...
ወዳገሬ ልግባ!

የምድር ጦር፣ የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይልና የክብር ዘበኛ ወታደሮች ችቦአቸውን ለኩሰው ዜማውን በጎብረት እያወጡና እየተቀበሉ በሰልፍ ይራመዳሉ። አባቴ እያንዳንዱ ሠልፈኛ በፊቴ ሲያልፍ እነማን እንደሆኑ ይነግረኛል።

መኩሪያ የሚባለው አንበሳ በአንድ ግልፅ መኪና ወለል ላይ ተጋድሞ በፊታችን አለፈ። አባባ ጃንሆይ ፊት ሲደርስ አገሳ። ሰዎቹ የተለያየ አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ።

"ይኼው አላልኩም? ጌታውን ያውቃል!"

"እውነትም ለያቸው!"

"እሳቸውን? እንስሳቱም አዕዋፉም ያውቋቸዋል።"

አባቴን"ዜራሞ፣እውነት አባባ ጃንሆይን መኩሪያ ያውቃቸዋል?" አልኩት በሹክሹክታ።

ግራ ቀኝ ተገላመጠና "አይመስለኝም፣ ፉንጋይ። አጠገባቸው ሲደርስ ወታደሩ ላይጎሸመው ይቀራል?" አለኝ. ትንሽ ፈገግ

ብሎ። 'ውሻ በበላበት ይጮኻል' ብቻ ላይሆን፣ አንበሳስ በበላበት እንደሚያገሳ ማን ያውቃል?

ጳጳሱ ደመራውን ይባርካሉ። ጃንሆይ ደመራውን ለመለኮስ ይነሳሉ። እልልታው ምድሩን ያደበላልቀዋል። ከዚህ በኋላ ሕዝቡ የሚጠብቀው ዳመራው ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ እንደሚወድቅ ማወቅ ነበር።

ትልልቅ ሰዎች ሲያወሩ እንደሰማሁት ደመራው ወደ ቀኝ ከወደቀ የፍስሐ የደስታና የፍቅር ዘመን ይመጣል። ወደ ግራ ከወደቀ የመከራ፣ የረሃብና የጦርነት ጊዜ ይሆናል። ይህንን ለማወቅ "ዜራሞ ዳመራው ወዴት ነው የወደቀው?" ስል ጠየኩት። እዝን ብሎ "በማዶ በኩል ወደ ቀኝ ነው የወደቀው" ብሎኝ ቀስ ብሎ ከትከሻው ላይ አወረደኝ።

ዘንድሮ አባቴ በጣም ታሞ አሁን ተሽሎት በግጣም ላይ ነው። በዚህ ምክንያት መስቀል አደባባይ መሔድ እየፈለኩ አልሔድኩም ነበር። ቅር እንዳለኝ ያስተዋለው ቱማ ባንጋ "ፉንጋይ ለምን መስቀል አደባባይ አንሄድም?" አለኝ፣ የልቤን አውቋል።

ቱማን እወደዋለሁ። በልጅነቴ አያሌ የጨዋታ አይነቶች ያሳየኝ፣ እንደ እኩያ ጓደኛው የሚያወጋኝ ሰው ነው። የእማዬ የእናቶ ዘመድ ሲሆን፣ ለእኔ ጥልቅ ፍቅር አለው። ሌሎቹ ትልልቅ ሰዎች ግን ተለዋዋጭ በሆነው ባሕርያቸው በጣም ያስፈሩኝ ነበር። ወላጆቼ ፊት በፍቅር ጎርፍ የሚያጥለቀልቁኝ ሰዎች፣ ብቻዬን ሲያገኙኝም የትናንት ፍቅራቸውን በማሰብ እኔ ፍንድቅ ብዬ ላያቸው እነሱ ፊታቸውን ጭንጊት አስመስለው ያልፉኛል። አልያም እስከ መፈጠሬ ይረሱኛል። አንዳንዶቹ ብቻቸውን ያወራሉ። ከራሳቸው ጋር የሚሳሳቁ ነበሩበት። አባቴም ከራሱ ጋር ሲሳሳቅ ብዙ ጊዜ አይቼው "አንተ፣ ብቻህን ትስቃለህ እንዴ?!"

"ሳቅሁ እንዴ?!" ይለኛል ቀልቡ ሁሉ ወደእኔ እየተመለሰ።

"በደንብ።"

"ጋሼ ትልቅ ሰው ስትሆን ትደርስበታለህ" እያሾፈ ይለኛል።

ዛሬም የደንቡን ለማድረስ ከቱማ ጋር መስቀል አደባባይ ደረስን። ከእሱ ጋር ስሆን ነፃነት ይሰማኛል። ቱማ ለትልልቅ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሕፃናትም አክብሮትን የሚሰጥ ድንቅ ሰው ነው። አሳስፈላጊ ነገር ስጠይቀው ሊገባኝና ሊያጓጓኝ በሚችል ጥበበ ይነግረኛል። "ፉንጋይ" ይለኛል ቱማ፤ "እኔ እንኮኮ አድርገኝ ካል ከኝ ምን ችገረኝ አደርግሃለሁ። እኔ ግን እንደሚመስለኝ ሲያድግ ከአበበ ቢቂላ የሚበልጥ ስፖርተኛ መሆን የሚፈልግ ልጅ በእግሩ ቢሔድ የበለጠ ጠንካራ ይሆናል።" እኔም አምነውና ከአፉ ነጥቄው "በቃ እንኮኮ አታድርገኝ" እለዋለሁ።...

ይህንን ስንጨዋወት የሰሙ አንድ ጡረታ የወጡ የክብር ዘበኛ አባል ጨዋታችን ሰቧቸው ከቱማ ጋር ወሬ ጀመሩ። ሙሉ ወታደራዊ ልብሳቸውን ለብሰዋል። ደረታቸው ላይ ሚዳሊያቸውን አንጠልጥለዋል።

በትረ መኮንናቸውን እጃቸው ላይ አያሽከረከሩ፥ "የዓለም ጋዜጦች ስለ አበበ ቢቂላ ሲያወሩ፥ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር ብዙ ሺ ሆነው ባህር ተሻግረው ዘመቱ። ያበቡትን ያህል ሳይቆዩ በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆች ድል ተመትተው ወጡ። አበበ ቢቂላ ግን ብቻውን ዘምቶ ድፍን ጣሊያንን በሰላም ጦርነት ድል መታ" ብለው ታል።

አልገባኝም። ቴማ በኋላ አስረዳሃለሁ በሚል ስሜት ጎሸም አደረገኝ። ፀጥ ብዬ ማዳመጥ ጀመርኩ።

"አሁን ምሥጋና ለፈጣሪያ ለፀሐዩ ንጉሣችን ይድረሳቸው። የተማሩት ልጆቻችን በዓለም ላይ ታላላቅ ሽልማትና ክብር ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ ወደ መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባ መጥተው ጃንሆይን እጅ ሲነሱ በሚያደርጉት ንግግር ውስጥ 'በንጉሠ ነገሥቴ መልካም ፈቃድ...' የምትባለውን አረፍተ ነገር ጨምረው ይናገራሉ። ደንብ ነው።

"አበበም ሮም አሎምፒክ አሸንፎ እንደመጣ 'በአለቆቼ ትብብርና በንጉሠ ነገሥቴ መልካም ፈቃድ...' ቢል ጃንሆይ አስቁመው ውት 'አንዲያው በአለቆቼ መልካም ትብብር ብለህ ትጠቅሳለህ እንጂ በትፈጠር ስለተቀባህ ነው' ብለው ታል።"

"እውነታቸውን ነው ጃንሆይ! ሲፈጠር ስለተቀባ ነው። ባይቀባማ እንዲህ ዓለም ሁሉ ከልብ የሚወደው ይሆናል?" አለና ቴማ "አበበ ቢቂላ ልጆችን በጣም ይወዳል አይደል?!"

"በደንብ! ታዳጊዎቹ ሁሉ ከእሱ የበለጡ እንዲሆኑ ጃንሜዳ ያሠለጥናቸዋል። ልጆችን ከአንጀቱ ነው የሚወዳቸው። የተነሳበትን አሳምሮ ስለሚያውቅ ልጆችን ከልቡ ያስተምራል። ይህንን ጉበዝ እንደ አበበ ጠንካራ እንዲሆን በትመክረው ነው እኮ ትዝ ብሎኝ ጨዋታችሁ መካከል የገባሁት" አሉ አዛውንቱ።

"ደግ አደረጉ። እኔ ደግሞ ስሞኑን ሲመቸን ከቡር ዘበኛ ካምፕ ወስጄ ከተማሪ ተሰፋዬ ዜራሞ ጋር አበበ ቢቂላን አስተዋውቃቸዋለሁ" ሲላቸው ቴማ በጣም ደስ አለኝ። በዚህ ምክንያት ዘንድሮ ዳመራው ወደ ቀኝ ይሁን ወደ ግራ መውደቁን አላጣራሁም። ከምወደው ታላቅ ስፖርተኛ ሕይወት የተማርኩትን ሰፈር ተመልሼ ለአብሮ አደጌቼ ለማውራት ቸኮልኩ።

ይዋጣላቸው

"ሕፃናትን ተዋቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና"
የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 19:13-14

መንግሥተ ሰማይን ላስብ የዮሴፍ ቤተክርስቲያን ጀርባን ነው የማስታውሰው። ተፈጥሮ ከነክብሯና ሞገሷ በዚያ የጨቅላ ነት ሕይወት ትታያለች። አረንጓዴው መስክ ዓደይ አበባ የፈ ካበት ነበር። ልዩ ልዩ እፀዋት ያብቡበታል። አጋምና ቀጋ እንደ ልብ ነው። ጉንዳኖች በጥንካሬ ይሠራሉ። የቢራቢሮዎቹ ጎብረ ቀለ ማት ቀልብን ይስባል። ንቦችም በትጋት ሲቀስሙ ይስተዋላሉ።

የሰፈር ልጆች እዚህ ገነት በሆነ ቦታ ላይ በሳምንት አንድ ቀን በመሔድ በገደላ ገደሉ ድብብቆሽ እንጫወታለን። የደፈርን ከወንዙ ዳር በመሰኖ ከሚለማው ካሮት ለመስረቅ እንሄዳለን። በንፁህ ወንዝ እንዋኛለን። የተደፋፈርንም ብዙ ጊዜ በዚህ ገሳጋይ ዝር በማይልበት ስፍራ እንደባደባለን።

ይህን ወንዝ የምንጠራው ፏፏቴ ብለን ነው። ከወንዙ በላስቲክ ከረጢት ዓሣ አጥምጄ ወደ ቤቴ በመውሰድ ለዕለታት በሴንኪሉ ውስጥ አኖርኩት። ለዓሣው የቧንቧ ውሃ እንደማይስማ ማው ጓደኞቼ ስለነገሩኝ ያለምንም መታከት በየሦስት ቀኑ ከወ ንዝ ውሃ፣ አልጌ እና ልዩ ልዩ እፀዋት በማምጣት መግ ቤዋለሁ።

በዚህ የምርምር ሀሁ ላይ ቤተሰቦቼ ጥሩ ተባባሪዎች ነበሩ። ጓደኞቼም ውሃ ከወንዝ በላስቲክ ቀድቶ በማምጣቱ አግ ዘውኛል። በየዕለቱ እንቅስቃሴውን በመከታተል እየተመካከርን የሴንኪሉው ዓለም እንዲስማማው ተጣጣርን። በአንድ አሳዛኝ ቀን ችግር ተፈጠረ። ቤተሰቦቼ ጠበል ጠዲቅ ኖሮባቸው ጎረቤቴን ይጠራሉ። ዳቦውም፣ ቆሎውም፣ ጠላውም ቀርቦ እየተጨዋወቱ ሲዝናኑ የማስረሻ እናት የሚጠጡበትን ብርጭቆ ለቅለቅ አድ ርገው አጠገባቸው በሚገኝ ሴንክሉ ላይ ልቅላቂውን አፈሰሱት። እማዬ "የማስረሻ እናት፣ አስገደሉን፣ እዚህ ውስጥ የፉንጋይ ዓሣ ነበር" ብላ ሳትረጋጋ እኔ ደረስኩ።

ጉዳዩን አጣራሁ። የዓሣውን ሁኔታ ተከታተልኩ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ዓሣው ተንፈራግጦ፣ በውሃው ላይ ተንሳፈፈ። ክፉኛ አለቀስኩኝ። የማስረሻ እናት በድርጊታቸው በጣም ማዘናቸውን አስታውሳለሁ። ዓሣዬም ብዙ ሰዓታት ሳይቆይ ሞተ። ከዚያ በኋላ ከወንዙ ውሰጥ ዓሣ ለማጥመድ በተደጋጋሚ ሞክሬያለሁ ግን አልሰመረልኝም።

የዋና ትምህርቴ ግን በጥሩ ሁኔታ እያደገ መጥቶ ውሃው ውስጥ መንሳፈፍ ቻልኩኝ። ከአብሮ አደጎቼ መካከል አንዳችንም የዋናን ሕግ አናውቅም። አንዱ ደፍሮ ከጀመረ ሌሎቻችን ያንን ደፋር እንደ ማለፊያ መምህር እንከተለዋለን። የሚለንን እያደረግን ከውሃውም እየጠጣን ልምምዳችንን እናጧጡፋለን። የእግራችን እንቅስቃሴ ውጤታማ ሲሆን፤ እጃችንን አከለን ጥልቀት አልባው አካባቢ መቅዘፍ እንጀምራለን። ሲደክመን ስንቆዝም ውሃው ወገባችን አካባቢ ቢደርስ ነው።

እግሮቻችን ከእጆቻችን ተዋህደው ዋናውን በቅጡ ያወቅን ሲመስለን ችሎታ አላቸው ብለን የምናምናቸውን ጓደኞቻችንን ጠርተን እንዲያዩንም እንዲያደንቁንም በማሰብ ከወንዙ ማዶ ለመሻገር እንዋኛለን። አንዳንዶቻችን ይህ የአካልም የአእምሮም ሥራ የሆነ ጥበብ ቀልጥፎ ሲገባን፣ ፈራ ተባ የሚሉት ዳር ላይ በማንበጫረቅ ብቻ በርካታ ጊዜያት ይፈጅባቸዋል።

ውሃን የሚፈሩ ልጆች ነበሩ። እነዚህኞቹ ከዳር ቆመው የሚዋኘው ልጅ ምን ማድረግ እንዳለበት አመራር ይሰጣሉ። "አዎን እግርህን! እንዲህ..." ይወራጫሉ። "እጅህን ደግሞ..." ይሉና አየሩን ይቀዝፉታል። አንዱ ተንኮለኛና ጉልበተኛ "ግባና አሳየው!" ብሎ ሲገፈትራቸው 'ከበሮ በለው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር' እንደሚሉት ይሆናል ድርጊታቸው።

በዚህ ጊዜ ችሎታው ያላቸው ልጆች ዘለው በመግባት ያወ ጧቸዋል። ይህ በድንገት ተገፍትሮ ለአደጋ የተጋለጠው ልጅ ጉልበት ካለው ከፍተኛ ፀብ ይፈጠራል። ገፍታሪውና ተገፍታሪው የሚደፋፈሩ ልጆች ከሆኑ መደባደባቸው የማይቀር ነበር።

በአንድ ልዩ ቀን ውሮ የምታምር የልጅን ልብ የምታማ ልል ሱፍ ኮትና ቦላሌ ሱሪ ለብሶ ወደ ፏፏቴ አብረን ሔድን። ሰፈር ውስጥ ይህንን ውብ አለባበሱን አድንቀንለታል። ውሮም ሕይወቴን በሙሉ እንዲህ አይነት ሱፍ ልብስ ሲለብስ የኖረ ይመስል አወለቀውና ጥሉልን ራቁቱን ወደ መዋኛው ወንዝ ሄደ። ከአኛ መካከል ቦላሌና ኮት በመልበስ ውሮ የመጀመሪያው ነበር። ለሌሎቻችን ብርቃችን በመሆኑ ሁላችንም ራቁታችንን ቆመን ወረፋው ደርሶን እስከምንለካው ተጣድፈናል።

መጀመሪያ ቀጪሳው ኮሚኩ ለበሰውና ወደ እኛ እያስተዋለ "ያምርብኛል?" ሲል ጠየቀን እንደ ትልቅ ወጣት እያቁጨ።

"በደንብ!" አልነው እንዲያወልቅ እያጣደፍነው።

"ከኋላዬስ" ይላል ይዘርና።

"አሪፍ ነው።"

"ቁጭ ብዬስ?"

"ደስ ትላለህ!"

"ወይኔ የኔ ብትሆን?!"

"በናትህ አውልቅ። ምን ያደርግልሃል? አንተ አትማር።"

"እረ! ባልማርስ ካምቦሎጆ ስሄድ አድርጌው አልሄድም? 'ሙቪ' ስገባ አልዘንጥበትም" አለና እዚያው በዚያው 'አክተር' መሆን አማረው። በሃሳቡ የፈጠረውን ሽጉጥ ከጎኑ ላይ ላጥ አድርጎ ደገኛና በእኛ አቅጣጫ ተኮሰ። ኃይሉ ዶሮ ለማስወለቅ እየታገለ ነው። በዚሁ መሐል ውሮ እያለቀሰ ሲመጣ አየውና። "ምን ሆንክ?" አለው ኮቱን እየለበሰ።

"እናንተ እዚህ ልብሴን ስትለካኩ እኔን ደራሽ ውሃ ወስዶኝ ነበር!" አለን ውሮ ያበጠ ግንባሩን እያሻሸ።

ወደ ወንዙ አየን። አፈሩን፣ ግንዱን፣ ቋጥኙን እያላጋ በፍጥነት ይወርዳል። ዓይናችን በድንጋጤ ፈጠ ቀረ። ከመካከላችን ወደ ማዶ ካሮት ለመስረቅ የተሻገረ ልጅ አሁን አለመኖሩን ታላላቆቻችን ዶጆ ገማጣውና ቦቸራ ተሰማ አስተዋሉ።

በመካከላችን ተረፈ ገልጆ የለም፣ ተደናገጥን። በካሮት ሌብነት ሁላችንም የተለያዩ ገጠመኞች አሉን። ዶጆ ገማጣው አንዴ በገበሬዎቹ ተይዞ መፈጠሩን እስከሚጠላ ተወግሯል። ራሱ በቀጠፈው ሳማ ለብልበው ለቀውታል። እኔም የሩንታዬን ቀምሻለሁ።

ካሮት መስረቅ ስንጀምር በደረታችን እየተሳብን ካሮቶቹ መደብ አካባቢ እንደርሳለን። በእጃችን መሬቱን ጫር ጫር ስናደርግ ያ ቁልቁል እንዲያድግ የተፈጠረ ተክል ብቅ ይላል። አፈሩን ጠረግ ጠረግ አድርገን በፍጥነት መግመጥ እንጀምራለን። አንገትን እያሰገጉ አካባቢውን መቃኘት የግድ ነው። ድንገት አንዱ ገበሬ አፋፍ ላይ ቆሞ ሊያየን ይችላል። ይህኔ እግሬ አውጭኝ እንላለን። ገበሬውም በመጮህ እማዶ ላለ ጓደኛው ማሳው ውስጥ "አይጠ ሞገጥ ገብቷል!" ሲል ያስጠነቅቃል።

የምንገኝበትን መደብ ይጠቁመዋል። ቆመጡን ይዞ የረገጠበትን ሳያውቅ ይንደረደራል። አንዳችን ሌላችንን መጠበቅ እንተውና በተለያዩ አቅጣጫዎች እንሮጣለን።

በዚህ ጊዜ ነበር እኔ ወጥመድ ውስጥ የገባሁት። አንደኛውን አቀበት ሮጬ ጨርሼ አመለጥኩ ስል፣ ከማዶ ያለው ለወዲህኛው ዘብ ይነግረዋል። ተመልሼ በሌላ አቅጣጫ ፈትለክ ብዬ አመለጥኩ ስል፣ በሌላ አቅጣጫ ያየኝ ላላየኝ ይጠቁማል። መግቢያ ጠፋኝ፣ ጉልበቴ ከዳኝ። ልቤ ልትፈነዳ ደረሰች። አንድ ጥሻ አገኘሁና ተወሸቅኩ። በደረቴ ተዘርሬ ልቤ ብትንፈራፈርም ትንፋሼን ዋጥ ለማድረግ ጣርኩ። ዓይኔን ገርበብ አድርጌአለሁ። ላቤ ይንቆረቆራል። በዚህ መሐል ጥሻው ተንኮሻኮሸ። ዓይኔን ስገልጥ አፍንጫዬ ስር ትልቅ የወታደር ጫማ ታየኝ። ቀስ ብዬ ሽቅብ ማየት ጀመርኩኝ። ረጅም ቅልጥም፣ ቁምጣ ሱሪ፣ ቀበቶ፣ ያደፈ ሹራብ። የተኮሳተረ ፊት ግንባሩን ቋጥሮ ቁልቁል ያስተውለኛል። በግራ እጁ ቆመጥ ይዟል።

"ተነስ!" ሲለኝ እንደኳስ ነጥሬ ተነሳሁ። ቁመቴ ሽንጡ አካባቢ አይደርስም። ማጅራቴን ጨምዶ እንዳንጠለጠለኝ ወንዝ ዳር ደረስን። የካሮት ኮረብታ መካከል ወረወረኝና "በል እያ ጠብክ አሱ ቅርጫት ውስጥ ጣል!"

ደስ ብሎኝ ሥራውን ጀመርኩ። ጀንበር እስክትጠልቅ የካሮት ተራራው እስኪጋመሰ የተሰጠኝን የሥራ ቅጣት በቅል ጥፍና አከናወንኩ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሳላስፈቅድ ትንንሾቹን ካሮቶች መግመጥ ጀመርኩ። የቁቆጣኝ አልነበረም። ጀንበር ስት ጠልቅ ዳግም ዝር ብል እንደሚገድሉኝ አስፈራርተው፣ ኬሴን በካሮት ሞልተው፣ ወንዙን አሻግረው መንገድ መርተው ሸኙኝ።

ይሀንን ውሎዬን ትናንት ማታ ለሰፈር ልጆች ሳወራ ተረፈ ገልጆ እየጎመጀ ነበር ያደመጠኝ። አሁን ደራሽ ውሃ ስላቆራረጠን ስጋቱ የጋራችን ሆነ። "ገልጆ!" እያልን መጣራት ጀመረን። ከወዲህ ያለው ጥሻው ተንኮሻሸ። ከጥሻው ውስጥ ገልጆ ወጣቱን እያጠባበቀ ብቅ አለ።

የተቀረነው ልብሳችንን ከየጣልንበት አንስተን ለበስን። ውሮ በመትረፉ ተደስተን ጨዋታውን አቋርጠን ወደ ሰፈራችን ለመመለስ ጉዞ ስንጀምር "ቆይ!" አለ ቦቸራ ተስማ።

ቆምን።

"ከእናንተ መካከል በጣም የተደፋፈራችሁ ልጆች ስላላችሁ ይዋጣላችሁ!"

"እሺ!" አለች መኩዬ ቀጫጭው።

ቀጢሳው ግልቀስ ጀመረ። "እኔ መደባደብ አልፈልግም። ማንም ሰበብ እንዳይሆንብኝ ነው የምፈልገው።"

"አንተና መኩዬ በጣም ተደፋፍራችኋል። ይዋጣላቸሁ" አለ ቦቸራ።

ቀጢሳው በረጃጅም ቅልጥሞቹ እንደ ድመት እመር ብሎ ዘልሎ መኩዬን እንዳትነቃነቅ እጆቿን ከወገቧ ጋር ጥፍር አድርጎ ያዛት። መኩዬ ልቧ የነብር ሆነ እንጂ አቅሟ የጥንቸል በመሆኑ ቀጢሳው አሳላውስ አላት። እንቅ አድርጎ ይዟት ይወተውታል። "እኔ ገመምተኛ ነኝ! በሽተኛ ስለሆንኩ ሰበብ እሆንብሻለሁ!"

"ምንም አላመመህም። ትናንትም ከትናንት ወዲያም ስት ዞር ነበር። አሁን ተደባደቡ ሲባል ፈርተህ ነው። ልቀቂኝ አፍ ንጫህን ነው የምስብረው" ትመልሳለች መኩዬ።

"ብታርፊ ይሻልሻል አንቺ ቀጫጭ! እንደ ትኋን ጭፍልቅ፣ እንደ ቅማል በጥፍርና በጥፍሬ መሐል አርጌ ቋ! አረግሽ ነበር፣ ግን እናትሽን እፈራቸዋለሁ።"

"እናቴ ምንም አትልህም! ይዋጣልን!" እያለች ለማምለጥ ትታገላለች። ግን የቀጢሳውን ከእግር ብረት በላይ የጠበቀን አያ ያዝ መበጠስ አልቻለችም። እኛ ከበን ቆመን በሳቅ እንንፈራ ፈራለን።

ቦቸራ እየሳቀ "ልቀቀውና በሕጉ መሠረት መሬት ተሰም ሮሳችሁ ተደባደቡ።"

ቀጢሳው በዚህ ጊዜ እንደታነቀ ሁሉ መኩዬን አጥብቆ ይዞ "በሕግ አምላክ! ወድቆ በተነሳው ባንዲራ!" አሰና እንደ ትልቅ ሰው ተማፀነ። ይህ ያልሰመድነው አለማመኑ የባሰውን አሳቀን። መኩዬም ሳቀች። ቀጢሳውም በአንድ እጁ አንገቷን አቅፎ ይዞ በሌላኛው ኮረኮራት፤ መኩዬ ቀጫጭዋ በኃይል ሳቀች።

"አንቺ ቀጫጭ! ሰበብ ትሆኝብኛለሽ ብዬ ነው የማርኩሽ። ብታርፊ ይሻላል?!" እያለ ቀጢሳው ይዝትባታል።

ጥሉ ወደ ቀልድ ተቀየረና ፀቡ ተረሳ። ቀጢሳው ፈሪነቱና ኮሚክ መሆኑ በጀው እንጂ ከመኩዬ ቀጫጭው ጋር የጀመሩት ፀብ በቀላሉ አይበርድም ነበር።

መኩዬን በመከባበር ስሜት ችላ ብዬአት ፈሪውን ቀጢሳውን አበሽቀው ጀመር። ይኼኔ ቀጢሳው ወደ ቦቸራ ቀረበና አንድ ነገር በጆሮው ነገረው። ቦቸራም "አ! ልክ ነህ ረስቼው ነው። ጃምቦና ፋንጌ ተደፋፍረዋል ይዋጣላቸው።"

እንዳለውም እኔና ጃምቦ በጣም ተደፋፍረናል። ሰኔ 30 እንገናኝ ተባብለን ተዛዝተናል። አጋጣሚው ፈቅዶ ትምህርት ቤት ከመዘጋቱ በፊት ይኸውና ፏፏቴ ተገናኘን። ቦቸራ የምን ደባደብበትን መስክ አዘጋጀልን። መሬቱ ላይ በቾክ አስምሮ የሁ ለታችንን መሬት ክልል ከፈለልን። ቀድሞ የደፈረ የቾኳን መስመር አልፎ የፀበኛውን መሬት ከረገጠ፤ መሬቱ የተረገጠበት ፍል ሚያውን መጀመር አለበት። እኔ በጣም ስለፈራሁ "እሱ እኮ ቁርሱን በልቷል" ስል መከላከያዬን ተናገርኩ፤ ቀጢሳው ላይ እያፈጠጥኩ።

"እናቴ ትሙት! እማምላክን! ብትፈልጉ ሆዴን ንኩት ምንም አልበላሁም!" አለና ጃምቦ ለመደባደብ ከልቡ ቆርጦ ጡንቻውን ማፍታታት ጀመረ። ሆዱን ገልጾ ለሚያደባድቡን ልጆች አሳየ።

ቀጢሳው የጃምቦን ሆድ ደባብሶ "ምንም አልበላም። ሆዱ ባዶ ነው" አለና "እስኪ አፍህን ክፈት" አለው። ጃምቦ ያለውን አደረገ። ቀጢሳው አፉ ውስጥ አስተዋለና "ማርያምን! ጥርሱ ላይ ምንም ፍራፍሪ የለም!" አለ።

የእኔ አባት ብደበደብም፣ ብደበድብም ይቆጣኛል፤ ይገር ፈኛል። በጓደኞቼ አካባቢ ፈርቼ ካፈገፈኩ "ፈሪ ፍርፋሪ! ምድጃ ቆፋሪ! ምድጃ ሲቆፍር አነቀው ነብር!" እያሉ ስለሚያበሽቁኝ በጣም ተጨነኩና "እሱኮ ጫማ አድርጓል በርግጫ ቢመታኝ እጎዳለሁ!"

"ፈርቶኝ ነው!" በረባሶዬን እንደሆነ አወልቀዋለሁ" አለና በረባሶውን አሽቀንጥሮ በባዶ እግሩ መሬት ላይ ዱብ ዱብ አለ።

"እ? የማላውቅህ መሰለህ? አንተ እኔን በጣም የደፈርከኝ እናትህ ስለማይቆጡህ ነው!!"

"ለምን አትቆጣኝም? ትቆጣኛለች። አንተ ግን ፈርተኸኝ ነው። ከዛሬ ጀምሮ ትገብራለህ" ሲለኝ ተናድጄ በጣም ጮኽ ኩኝ። እንደመሰለኝ አጪጪዜ የፍርሃት ነበር።

ጓደኞቼ ግን "አ! ፉንጋ ሠይጣኑ ተነሳበት! ዞር በሉ የጃምበ ደም እንዳይፈናጠርብን!" አሉና አሟሟቁኝ። ለካ አጪ ጪዜ አንደ ተጨነቀ ሕፃን ሷይሆን ለምዶብኝ እንደ ዋንጣዩ ነበር። መውጫ የለኝም። የመጨረሻ መከላከያዬን ተከሰኩኝ። "አንተ! ጉድህን እንዳላወጣብህ!"

"ምን ጉድ አለብኝ? ምንም ጉድ የለብኝም። የእናቴን ጡት መጥባት እንደሆን ድሮ ገና ነው ያቆምኩት" አለና ምስ ጢሩን ይፋ አድርጎ ለመደባደብ ቆርጠ መነሳቱን አረዳኝ።

ስደባደብ ያካበትኩት ልምድ ነበረኝ። ይኸውም አስቀድሜ እማታለሁ። ምቴ ከረር ያለ ከሆነና ብልት ቦታ ላይ ካረፈ ፀበ ኛዬ ይወድቃል። ባልተጻፈው ሕጋችን የወደቀን ልጅ መምታት ፈሪ ስለሚያሰኝ መንካት ክልክል ነው። የወደቀውም ልጅ ተሸና ፈነቱን ስለሚቀበል ድጋሚ መደፋፈሩ ይቀራል። ገላጋይ ባለበት ደፋር ለመምሰል መጣጣሩ ያዋጣል። እኔም አሁን ዕድሌን ለመ ሞከር ቆረጥኩኝ።

ጃምበ መሬቴን ለመርገጥ መስመር አልፎ እግሩን ሲቃጣ እንጣጥ አልኩና በቦክስ አገጩን አልኩት። እሱም ቦክሷን ጠግና ትከሻዬን ይዞ ቴስታ ሰነዘረ። ሳንነብስ ጭንቅላቶቻችን ተላተሙ። የኮርማ በጉች ልትሚያ ድምፅ ተሰማ ዞረብኝ። ጓደኞ ቻችን በቡድን ተለያይተው ለሚያግዙት ልጅ ክፍት ቦታ ይጠቁ ማሉ። "ፉንጌ፣ ሆድ ሆዱን በለው!" መክዬ ቀጫጫ ነች።

"በቦክስ! በቦክስ!" አበረ ሻቃ።

"ዳቦ ቤቱን!" ፑሉቶ ነው። ለማንም ሳያግዝ ክፍት ቦታ ሆድ አካባቢ መጠቆሙ ነበር።

ተፋላሚዎቹ ጉልበታችን ተመጣጣኝ ስለነበር መማታት ሳይሆን ተፈታተግን።

"ምንድነው? ለምን ሲጣሉ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ! ባለ ጌዎች! ልቀቅ!" የአልፎ ሂያጅ ካልቾ ቂጤ ላይ አረፈ።

ጃምቦንም በኩርኩም ቆጥት፣ ተላቀቅን። ሰውዬው ቦቸራን በእርግጫ ሊመቱት ሰነዘሩ። ተፈናጠረና አመለጠ። እኔና ጃምቦም ተለያይተን ማዶ ለማዶ ቆመን ቁና ቁና እንተ ነፍሳለን።

ሰውዬው "ኑ! ታረቁ!" አሉን።

ሁለታችንም ተግደረደርን።

"ማነህ? ና! ልምጭ አምጣልኝ። ቅዱስ ዮሴፍ አይለመነኝ ሁለታችሁንም ልባችሁ እስኪጠፋ ነው እምገርፋችሁ። ታረቁ ብያለሁ ታረቁ! አታመልጡኝም!" አፈጠጡብን።

አንዳንድ እርምጃ ተጠጋጋን።

"ተጨባበጡ!" አሉ ሰውዬው ጮክ ብለው።

ነቢጥ ጨፈቃ መቁረጥ ጀምሯል። እኛ ጀርባ ለጀርባ ተሰጣጥተን ተጠጋጋን። "ተጨባበጡ ብያችኋለሁ። አትሳሳሙም ማለት ነው?!"

ጃምበ ጀርባውን እንዳዞረ እጁን ዘረጋልኝ። ነቢጥ ጨፈ ቃውን አምጥቶ ለሰውዬው ሰጣቸው። ቅጠሎቹን መልምለው ልምጩን እያስተካከሉ "ፊት ለፊት እየተያያችሁ ተጨባበጡ" አሉ ጨፈቃውን እየቃጡብን። ዞሬ ፊት ለፊት እያየሁት ጨበ ጥኩት። እርሱም ጥብቅ አድርጎ በፍቅር እጁን ያዘው።

"ተሳሳሙ" አሉ ሰውዬው ጨፈቃውን እየጣሉ የሁለታ ችንንም ማጅራት ይዘው። ሁለታችንም እየተሸኮረመምን ሳቅን። በሰውዬው እጆች አቀራራቢነት ጉንጩን ሳምኩት። እሱም ንፍ ጡን ሽቅብ ሳበና ጉንጩን ሳመኝ።

ሰውዬው "ጎሽ! አትጣሉ። ጠብ ምን ይጠቅማል? እንዲህ መፋቀር እያለ! የምን ፀብ ነው? በሉ ተጫወቱ። እናንተስ ከሚ ጣሉ ለምን አታስታርቋቸውም?" አሉና ትዕይንቱን በዙሪያችን ቆመው የሚመለከቱትን ሕፃናት ገስፀው ወደ ቦቸራ ዞሩና "እንት መድረሻ ቢስ ምጥማጥ! ነብር አየኝ በል! አንተ ነህ እነዚህን ነብስ ያላወቁ ልጆች እምታደባድብ?! ብታርፍ ይሻልሃል!" ብለ ውት ሰውዬው እንድንጫወት አዘው፣ መጥረቢያቸውን አንስተው ወደ ደኑ ሄዱ።

ክርስቶስ በመንፈስ ሁሌም አብሮን በመሆኑ፣ አምረን ልንፋጅ ሰንል በአካል እንዲህ ሐዋርያውን ልኮ መንግሥተ ሰማ ያትን እንድንወረስ መልካሙን መንገድ ይመራን ነበር።

ሽቀላ

'የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው"
የአማርኛ ምሣሌ

በዕንቁጣጣሽ አበባ ሰጥተን፣ ሆያሆዬ ጨፍረን በምናገኘው ፍራንክ ሲኒማ መግባቱ በቂ አልሆን አለ። ስለዚህም እኔና ጓደኞቼ የተለያዩ የሥራ አይነቶች መፍጠር ጀመርን። ቂጠማ አሞዶ ለሴተኛ አዳሪዎች መሸጥ፣ ካምቦሎጆ አካባቢ መኪና መጠበቅ፣ ጋዜጣና የለስላሳ ጠርሙስ ከኪስ ተመልካቾች እግር ስር መንትፎ ለገበያ ማቅረብ፣ በቆሻሻ መጣያው አመድ ውስጥ

ሳይነድ የቀረ ከሰል፣ እና ሌሎች ጠቃሚ ቁሳቁስ መለቃቀምና ለሸማች ማቅረብ ጀመርን።

ቀጢሳውና ሴምላል ቋሚ 'ፈዳሚዎች' ነበሩ፣ ፈዳሚ ማለት በየሰፈሩ እየተዘዋወሩ ከአመድ ወስጥ ሳይነድ የቀረ ከሰል ይለቅ ማሉ። ጓሮ የተደፋ አመድ፣ የቆሻሻ መድፊያ ገንዳዎች የማዕድኑ ምንጮች ናቸው። በአንድ እጃቸው የላስቲክ ከረጢት በሌላኛው መቆስቆሻ ቀጭን ብረት ይይዙና ቆሻሻውን፣ አመዱን እያገለባ በጡ ከሰሉን ይፈልጋሉ። "ቢያንስ በቀን አንድ አንድ የላስቲክ ከረጢት ሙሉ ስለሚለቅሙ የሆዳቸውን ጥያቄ በየዕለቱ መልሰው የሲኒማ መግቢያቸውን ኮርተው ይችላሉ።

አንድ ሰሞን ያገኙት ሳይታወቅ ቀጢሳውና ሴምላል ሞኛ ሆኑ። የሲኒማም አይቸግራቸው፣ ፓስቴም እንደልባቸው ይበላሉ። የገንዘብ ምንጫቸው ግን በምስጢር የተያዘ ነው። ድሮ የምርቃት ከረሜላ ቆርጭሞ ለማካፈል የሚሰስተው ቀጢሳው ዛሬ ዱንቡሉ አውጥቶ ፓስቴ ገዛልኝ። ይህ ቁና ሙሉ ቆሎ ብቻውን ሲከካ አንድ ጭብጥ መስጠት የሚያስጨንቀው ቀጢሳው ምን እን ዲህ ደግ አደረገው? ይህንን ቸርነት ለመኩዬ ቀጫጫ ነገርኪት።

"ትናንትና ጉልት ጨው ሲሸጡ አይቻቸዋለሁ። በርካሽ ስለሚሸጡት ሰዎች ተሻምተው ነው የገዟቸው። ጨውን ከዬት እንደሚያመጡት ብናውቅ እኛም እንደእነሱ ሞኛ እንሆን ነበር" አለችኝ።

በምስጢር እከታተላቸው ጀመር። በኋላ እንደተረዳሁት እኔ ብቻ ሳልሆን የሰፈራችን ልጆች ሁሉ ትኩረታቸውን አሳረ ፉባቸው። ጥርጣሬያችን አድጎ 'የአንድ ሀብታም ጨው ነጋዴ መደብር ሰርስረው ገብተው ይሆን?' አልን። ግን ሌብነት ቢሆን አንዴ ሊሰምር ይችላል። ሁለት - ሦስቴ መሳካቱ ግን የማይ ታሰብ ነው።

ደግሞ ጨውን በምንም ተአምር ወደ መንደራችን ይዘው አይመጡም። መንደርተኛው 'ከየት አመጣችሁ?' ብሎ ቢጠይቅ ምላሽ ስለማይኖራቸው፤ ማንም ሳይደርስባቸው ላምንት ሞላ።

ብንላቸው፣ ብንሠራቸው ትንፍሽ አልል አሉ። ወደ ማስፈራራቱም ብንሄድ ምንም ፍንጭ አላገኘንም። በመጨረሻም መኩዬ ተናደደችና 'ነገ ሌሊት ተነስቼ እዚሀች አደፍጥና ተከትዬ ጉድ ባልሠራቸው ወንድ አይደለሁም" ብላ ዛተች።

ታደርገዋለች። እኔም መሰለሉን ልቤ ቢከጅልም እንቅልፉ እንደሚያሸንፈኝ አውቃለሁ። ቀጢሳውና ሴምላል ሌሊት ተነስተው አገር ሰላም ብለው የላስቲክ ከረጢታቸውን ይዘው ወደ ጨው ማዕድናቸው ጉዞ ጀመሩ። እየተጨዋወቱ ድንገት ገልመጥ ካሉ ቀጫጫዋ አንዴ ስልክ እንጨት ላይ፣ እንዴ ግንብ ላይ ትለ ጠፋለች። እንዲህ እያሉ ብዙ ተጓዙ። አሮጌ አውሮፕላን ማረ ፊያ ደረሱ። አንድ ጥሻ አግኝተው ቀጢሳው ወገቡን ሊያላላ

ቁጭ አለ። ሴምላልም ቁምጣውን አውልቆ ከአጠገቡ ተቀምጦ መጠናቀቅ ጀመረ።

"አንተ፣ የእናትህ ጡት እንዳይበጠስ ወደዚያ ጠጋ ብለህ እራ" አሰው ቀጢሳው።

ሴምላል ራቀና ተቀመጠ።

ይህን ጊዜ መኩዬ አካባቢውን ስትቃኝ አንድ የነጭ ድን ጋይ ከምር ያየች መሰላት። ልብ ስትል ጨው ነው። ቀድማቸው ሄዳ ቁልሉ ላይ ቁጭ አለች። ቢኖይል እጅጨችና «እናንተ ባለ ዶቅዶቁዎች ሞተር አጥፉ!»

ፈዳሚዎቹ በተቀመጡበት ከው አሉ። ቀጢሳው እግተበ። ሴሚላል ከድንጋጤው ብዛት ፈሉን በረጅሙ ለቀቀው። ሴምላል የሚለው ጠፋው። ቀጢሳው ግን በፈጣን ጭንቅላቱ አብሰለሰለና መኩዬ መሆኗን ሲያውቅ ድርድር ጀመረ። "ከአሁን በኋላ መኩዬ አንቺም ሽርካችን ነሽ። የምንሸቅለውን ፍራንከ ሁሉ እኩል እንካ ፈላለን። በቃ ማርያምን ከዛሬ ጀምሮ ሽርካችን ሆነሻል" አለና ትንሹን ጣቱን አቆላሞ እንድትሻረከው እጁን ዘረጋላት።

መኩዬ ቂመኛዋ "እምቢ!"

"ለምን?"

"በቀደም ለነፉንጋይ ፓስቴ ስትገዛ ለእኔ እምቢ አላል ከኝም? ለሙቪ ዲናሬ ጎሎኝ ሙላልኝ? ስልህ እኝ! በል አላ ልከኝም...?"

"አንቺ ደግሞ! ቂል አትሁኝ! ያ እኮ አልፏል። ከአሁን በኋላ ሽርክ እንሁን።"

"አልፈልግም። አሁን ሰፈር ሄጀ ፉንጋይን፣ ዶሮን፣ ውሮን፣ ጎቢጥን፣ ባረቾን፣... ጠርቼ ዛሬውኑ ጨውን አግዘን እን ጨርሰዋለን።"

"እንደዚያ ካደረግሽ በጣም ሞኝ ነሽ ማለት ነው። ሴምላል፣ በስሙኒ ፓስቴ ግዛና ና። እኔና እሷ ከረጢታችንን ጨው እየሞላን እንጠብቅሃለን" አለ ቀጢሳው። የፓስቴ ስም ሲጠራ ቀጫጫው ድል ተመታችና ምስጢረኛቸው ሆነች። የድሮ ሽርክቿን ሁሉ "ፕ!" አለችን።

ከላምንታት በኋላ ያ የማዕድን ምንጭ የሆነው ጨው አለ ቀና ምስጢሩን ይፋ አደረገችው። ለካ ነጋዴዎች ከጠቅላይ ግዛት ገዝተው የሰበሰቡዋቸውን ቆዳዎች ሳይበሰብስ እንዲቆይ በማጀያነት ተጠቅመው የጣሉት ጨው ነበር።

አበረ ሻቃና፣ ተስፋዬ ገበሉ የተዋጣላቸው መኪና ጠባ ቂዎች ናቸው። ካምቦሎጆ ትሪቡን አካባቢ ነው የሚጠብቁት። በዚያን ወቅት የታወቁ የእግር ኳስ ክለቦች ጨዋታ ካለባቸው፣ አለበለዚያም ዓለም አቀፍ ግጥሚያ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስታ ዲየም ከተካሄደ፣ ሻቃም ሆነ ገበሉ ኪሳቸው የፍራንክ ከረጢት ሆኖ ነው ወደቤታቸው የሚገቡት። ከሲኒማ አልፎ የትምህርት

ቤት ልብሳቸውን እስክ መሸመት ይደርሳሉ። ሻቃ 12ኛ ክፍል ትምህርቱን እስካጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ራሱን በራሱ እየረዳ ነው ያደገው።

ይህም ሥራ የራሱ የሆነ በርካታ ገጠመኝና ታሪክ አለው። አንዳንድ ባለመኪኖች በጣጮ ቆንቋና ስለሆኑ መኪናቸውን ቀኑን ሙሉ አስጠብቀው 'ዝርዝር የለኝም' ወይም 'ማን ጠብቁ አላችሁ?' ብለው ገስፀው ያባርራሉ። እንዲህ አይነቶቹ በሳምንቱ ተገቢውን ቅጣት ያገኛሉ። ትኩስ አር ይፈለግና በስሱ የመኪናቸው በር እጅታ ላይ ይቀባላቸዋል። ባለቤቶቹ ተመልሰው የመኪናውን በር ሲበረግዱ ያንን አይነምድር ይጨብጡታል። እኛ በቅርብ ተደብቀን በአኳኋናቸው እንስቃለን።

ፋራ የሆነው ባለመኪና ጦርነት ከገጠመን በሚቀጥለው ቀን ጉማውን እናስተነፍላለን። ጦርነቱን በማግባባት ካልፈታ የዝናብ መጥረጊያውን... ይመነተፋል።

አንድ ሰውዬ ነበር፤ ቀይ ቶዮታ መኪና አለችው። እኛን ያስጠብቀንና ሁልጊዜ ጥላ ፎቅ ይገባል። ማምሻውን ሲመለስ የሚሰጠን 10 ሣንቲም ነበር። ዝርዝር ፍራንክ ሲያጣ ድፍን ብር ይሰጠንና መልስ ይጠይቃል።አንድ ቀን ገበሉን "90 ሣንቲም መልስ አምጣ?" ብሎ ብር ይሰጠዋል።

"የያዝኩት 80 ሣንቲም ነው።"

ስማኒያ ሣንቲሙን መልስ ተቀብሎ ብሩን ለሁለት ቀደ ደው "በ10 ሣንቲሙ ፕላስተር አስለጥፍበት፤ ወይም ባንክ ሂድና አዲስ ብር ይሰጡሃል።"

ተነሳንበት! ቅጣቱን ለመጀመር የእሱን መኪና መጠበቅ አቆምን። ደስ ያለው ቦታ ገሽሯት ሲሄድ የዝናብ መጥረጊያውን፤ በመቀጠል የቤንዚን መክደኛውን ተመነተፉ። ቤንዚኑንም ሃራምባ ለሚሰቡ ልጆች ብፌ አደረግንለት። በዚህ አምርሮ በፖሊስ አስ ይዞ በልምጭ አስገረፈን። እኛም ለምናውቃቸው መስታወት መን ታፊዎች እሳልፈን ሰጠነው። በዚህም ጦርነት ድል ሲያደርገን ስላልቻለ ካምቦሎጆን እርም ብሎ ተወ።

አራዳ የሆነ ባለመኪና ግን ራሱን ያርምና ሽርክ ያደ ርገናል። ከእንዲህ አይነቶቹ ጋር ከመቀራረባችን የተነሳ በሰኔ ወር እካባቢ ሰርቲፊኬታችንን ጠይቀውን የምናሳያቸውና የሚሸል ሙንም ነበሩ።

መኪኖቹ 50 ይሁኑ 100 ከደንበኞቻቸው ከተረከቡ በኋላ ባለንብረቶቹ ካምቦሎጆ እስከሚገቡ ይጠብቃሉ። አሪፍ ጨዋታ ከሆነ ጠባቂዎቹ ገንዘብ ካላቸው *ከማን አንሼ ወይም *ሚስማር

ካምቦሎጆ፡ በተለምዶ አብያተም ከጥላ ፎቅ ፊት ለፊት ካታንጋ ሲባል፣ ከማን አንሼ ግራና ቀኝ ያለው መቀመጫ ነው፤ ምስማር ተራ በኪስ ሚዳው በሰሜንና በደቡብ በኩል ያለው ቦታ ነው።

ተራ አንድ ብር' ከፍለው ይገባሉ። ገንዘብ ከሌላቸው እንደ ጠጣ በካምቦሎጆው ምሰሶ ሽቅብ ወጥተው እጃቸውን ለተመልካች ብቅ ሲያደርጉ አንዱ ጎትቶ ያስገባቸዋል። መኪናዎቹን ከፍለው የመግ ባት አቅም ለሌላቸው ልጆች አደራ ይሰጣሉ።

ጨዋታው ሲጠናቀቅ 10 እና 15 ደቂቃ ሲቀረው ወደ ሥራቸው ተመልሰው የመኪናዎቹን ደህንነት እደራ ከሰጧቸው ልጆች በማረጋገጥ የደንበኞቻቸውን መምጣት ይጠባበቃሉ። በተ ለያዩ ቦታዎች ዘብ ካቆሟቸው ልጆች አንዱ "ሻቃ!" ብለው ሲጠሩት፤ ቱር ብሎ ይሄድና የሰጡትን ይቀበላል። "ገበሉ!" ብለው ሲጣሩ እሱም ፈተለክ ብሎ ይቀበላል። አበረ ሻቃና ተስፋዬ ገበሉ ለቀጠሯቸው ልጆች ወሮታቸውን ፓስቴ አልያም ሣንቲም ይከፍሏቸዋል።

እኔ የመኪናዎችን ስም መለየት አልችልም። ከጓደኞቼ እየጠየቅኩ ሁሌም አይነትና ስማቸውን ለማወቅ እጥራለሁ። "ገበሉ ይህቺ ማን ትባላለች?" እለዋለሁ፤ እንዲን መኪና እያ መለከትኩ።

"ቶዮታ ኮሎራ!" ይላል፤ በኩራት።

"ይህቺስ?"

"ታኖስ።"

"ያቺኛዋስ?"

"ሜርቼዲስ ቤንዝ..."

የመኪናዎቹ ታርጋ ቁጥር የተገዛበት ዋጋ ይመስለኝ ነበር። በዚያን ጊዜ አንዳችንም እውቀቱ ስላልነበረን ይህ እምነት ስረ ጂም ጊዜ እብሮኝ ኖሯል። ስለመኪና ላስብ የሚገርመኝ ትንንሽ መኪናዎች ትልልቆቹን ይቀድሟቸዋል። ሁሉንም ደግሞ ዶቅዶቂ በፍጥነትዋ ታስከነዳቸዋለች።

ገበሉ ሚጢጢ የእንግሲዘኛ ቋንቋ ችሎታ ነበረው። "ኖ ፋዘር፤ ኖ ማዘር!" እያለ ከፈረንጅ ጋር ሲያወራ ሰምቼዋለሁ። ከእውቀቱ እንዲያጋራኝ ጠይቄው ደስ ብሎት "ከወንድ ፈረንጅ ጋር ስታወራ 'ሰር' ነው የምትለው፤ ከሴት ፈረንጅ ጋር ካወራህ 'ማዳም' ወይም 'ሚስ' ትላለህ" ብሎ አስረድቶኛል።

የለገሃር ልጆች ካካምቦሎጆ ትኬት ገዝተው ስገቡያ በትርፍ ያቀርባሉ። የትኬቱ ዋጋ መርከስና መወደድ እንደ ጨዋታው እር ፍና ይወሰናል። ቀዝቀዝ ያለ ጨዋታ ያለ ቀን እምስት፤ አሥር፤ ሃያ አምስት ሣንቲምም ሲያተርፉ፤ በጣም አሪፍ ጨዋታ ያለ ዕለት የአንድ ብር ትኬት እስከ ሁለት ብር የሚ ሸጥበት ጊዜ አለ። ትኬት ገዝተው ስገቡያ የሚያቀርቡት ቦዲ ቢውልደሩ ቸርነት እና ወንድምአገኝ መርፌ ናቸው። ሽያጩ በቅልጥፍና ካልተካሄደ ለኪሳራ ስለሚዳርግ፤ እነዚህ ትኬት ነጋዴዎች የቸርቻሮ ሥራ የሚያከናውኑላቸው ሌሎች ትንንሽ ልጆችን ይቀጥራሉ። መነጠቅ ወይም መሠረቅ ቢኖር ተቀጣሪዎቹ ባለዕዳ ናቸው።

አንዴ የፍልውሃው ልጅ ሐሙራቢ አከፋፍሎ ለመሸጥ ከቸርነት ጢቦ ላይ አምስት ትኬት ተረከበ። ጨዋታው በጣም አሪፍ ስለነበር ትኬቱ በፍጥነት አለቀ። ሐሙራቢ አሥር ብሩን ይዞ ተሰወረ። ቸርነትም "እናቱ ሆድ ቢገባ እያመልጠኝም" እያለ አደባ። ዕለታት አለፉ። ሐሙራቢ ካምቦሎጆ መምጣቱን ተወው። ቸርነት ፍልውሃ እያዬደ ቢያደባም ሊይዘው አልቻለም።

ያን ጊዜ ሁላችንን ያማልለን የነበረው በብላሽ የሚታየው የጠር ኃይሎች ቀን ደረሰ። ሐሙራቢ ተደብቆ ካምቦሎጆ መጣ። ልክ አሁን ትንሽዋ ካምቦሎጆ የተሠራችበት ሜዳጋ ሲደርስ ቸርነት ሊይዘው ተወረወረ። ሐሙራቢ በጊዜ ስላየው ቀኝ ኋላ ዙሮ ወደ ሰፈሩ ሩጫ ጀመረ።

ኮቱም ቢል ቢል እያለች እንደሱፐር ማን ክንፍ ሆናለት እየበረረ የኢትዮጵያ ሆቴልን ፎቅ ዘሎ መከላከያ ሚኒስቴር ጣሪያ ላይ ዱብ አለ።

በመከላከያ ሚኒስቴር መስክ ላይ አንድ ጀነራል ቆመው ሽቅብ አንጋጠው እያዩ "ይኼ ሰው ነው ዝንጀሮ?" አሉ።

"ልጅ ነኝ!" አለና ከጣራው ሸር ብሎ እንደ ድመት ዘለለና በመዳፉና በእግሩ መሬት አርፎ "አድኑኝ ጀኔራል! ሊገለኝ ነው!"

"ማነው ገዳዩ?"

"ያው..." ወደ ቸርነት ጢቦ አመለከታቸው።

ቸርነት ዓይኑን ሳያረግብ አፍጠ ያያቸዋል።

"ና አንተ፣ ምን አርጎህ ነው የምትገለው?"

"ትኬት!" ሁለቱም እኩል ጮኹ።

«ፀጥታ!" ብለው ጀኔራሉ ተቆጡና "የሚዝም እኮ ነው። እን ዲህ እይነት አየር ወለድ ኢትዮጵያ ያለምንም ልምምድ እያፈራችልን እኛ ለማሠልጠን መከራችንን እናያለን" አሉ፣ ለራሳቸው ያህል። ከዚያም ወደ ልጆቹ እያስተዋሉ «ማነው ስምህ?»

«ሐሙራቢ።»

«ሐሙራቢ? ለመሆኑ የስምህን ትርጉም ታውቀዋለህ? ሐሙራቢ እኮ ሕግ ደንጋጊ እንጂ ፀሎኛ አይደለም። ያንተስ ስም ማነው?»

«ቸርነት።»

«ታዲያ ምን አጣላችሁ?» ብለው ችግሩን ከሥር ከመሠረቱ መረመሩ። ሁለቱም የየራሳቸውን እውነት ተናገሩ። ጀነራሉ «እቺን እውነት የምናወጣት በመሐሳ ነው። 'አምላክ አይለመነኝ፣ ከወላጆቼ ይነጥለኝ!' በሉና ማሉ።»

ቸርነት ማለ።

ሐሙራቢ ግን አፈገፈገ። በዚህም ጀኔራሉ ሐሙራቢን ይቅርታ እንዲለምን አድርገው 10 ብሩን ከፈሉለት ብሎ ያወራልን ገበሌ ነው።

«አንተ እይተሃል ፎቁን ዘሎ ሲበር?»

«እንክት!»

«አሰኪ እማምላክን በል?»

«እማምላክን!»

«እንዴ! ይኼንን ፎቅ እኮ እንኳን ሐሙራቢ አበበ ቢቂላ ራሱ ሊዘለው አይችልም።»

«ለምን እይዘልም? አንተ አቤን አይተኸው ስለማታውቅ ነው። አቤ አንድ ቀንስታ ካምቦሎጆ ሊለማመድ መጣ፣ በሮች ሁሉ ዝግ ሆኑበት። ከዚያም በቦርሳ የያዘውን ትጥቅ ለኛ አንድንጠብቅለት ሰጥቶን በካታንጋ በኩል እንጣጥ ብሎ ኳስ ሜዳው ላይ ዱብ አለ። ከዚያም በካምቦሎጆው ደረጃ ተመልሶ መጥቶ ትጥቁን እቀብለነው። ቀለበውና ልብሱን ቀይሮ ልምምዱን ጀመረ። እኛም በካምቦሎጆው ቀዳዳ እየነው።» አለኝ ገበሌ ደግሞ ደጋግሞ እየማለ።

ሁሌም የሚገርመን የሦስቱ ዳዊቶች ትኬት የሚነግዱበት ጥበብ ነው። አንድም ቀን ትኬት ለመግዛት ሲጋፉ አይቻቸው አላውቅም። ግን ሁልቀን ትኬቶች ይዘው ለተመልካቾች ሲሸጡ አያለሁ። አስተባባሪያቸው ዳዊት ምች ነው። ዳዊት ገንቦና ዳዊት ድድ አመራር ከምች እየተቀበሉ ያከናውናሉ። ትኬት የሚሸጡበትን ቦታ በየጊዜው ይቀያይራሉ። ከሦስቱ ውጪ ማን ንም በመካከላቸው አያስገቡም።

«ቱንጋይ ና!» አለኝ አንድ ቀን ዳዊት ምች።

ተጠጋሁት።

«ትኬት ከእኔ እየገዙ የሚገቡ ተመልካቾችን ተከትለህ ሔደህ በስላም መግባታቸውን ንገረኝ» አለኝ።

«እሺ» ብዬ ትእዛዙን ተቀበልኩ።

ማታ ወደ ሰፈር ስንመለስ አንጀት አርስ ጉርሻ እንደ ሚጠብቀኝ አውቃለሁ። እንዳለኝ በንቃት ትኬት ሸምተው የሚ ሔዱ ተመልካቾችን ተከትዬ በመሔድ በሰላም መግባታቸውን አስተውሳለሁ።

በር ላይ ሁሉም ነገር የሚከናወነው በጥድፊያ ነው። ትኬት ቆራጮች ምራቅ ለመዋጥ ጊዜ የላቸውም። የተመልካቹ ስልፍ በጣም ረጅም ስለሆነ፣ የጨዋታው መጀመሪያ ሰዓት ስለተቃረበ ጊዜ በካምቦሎጆ በር ላይ ያለልክ ትጣደፋለች። እነምች ትኬቶ ቻቸውን በሙሉ ሸጠው ጨረሱ። ባስቀሩት ትኬት ራሳቸውን ጋብዘው ሲገቡ እኔንም አዳበለኝ።

እኔ ብርቅ የሆነብኝን ጨዋታ ደስ ብሎኝ ማየት ጀመ ርኩ። ዳዊት ገንቦና ዳዊት ድድ በካምቦሎጆው ግራና ቀኝ አቅጣጫ ተስማርተው ተመልካቹን ኪሱ የቀረችውን ቁራጭ ትኬት እንዲሰጡአቸው ይለምናሉ። ስፖርት አፍቃሪው ሕዝብ በብዙ መልኩ ተባባሪ ነው። አንዳንዱ ጥያቄ ያበዛል። ይኼኔ ጠያቂውን ጥለው በመሔድ ወደሚቀጥለው ተመልካች በመጠጋት ቁራጪን ትኬት ይለምናሉ።

ዳዊት ምች ደግሞ ካምቦሎጆ መግቢያው በር ላይ ቆሞ የትኬት ቆራጩን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል። ትኬት ቆራጩ

ይቆርጥ ይቆርጥና እጁ በቁራጭ ትኬት ሲሞላ መሬት ይበት ነዋል። ዓይኑን ሳያረግብ በጥንቃቄ ሲጠብቅ የነበረው ምች ይሼኔ ከች ይልና ከመሬት አፍሶ ቁራጮቹን ትኬቶች ኪሱ ይከታል።

ገንቦና ድድ ከተመልካች ለምነው ያመጧቸውን የትኬት ቁርጥራጮች ለምች ያሰረክቡና መዝናናት ይጀምራሉ። አረንቻታ ይጠጣሉ፤ ሽምብራ በጨውም ቦነ ሽንኮራ እንደልባቸው ይበላሉ። የሸቀሉትን አብዛኛውን እጅ ምች ሲወስድ፤ ገንቦና ድድ ድርሻ ድርሻቸውን ያገኛሉ።

በዚያን ዕለት ዘብ ለቆምኩበት አብሬያቸው ተዝናንቼ እንድ ኮና ዳዊት ምች ሰጠኝ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀብታም ሆንኩ።

የዳዊት ምች እናት እማማ ዘርፌ የአባቴ የሸማ ደምበኛ ናቸው። ጋቢ፣ ነጠላና ቀሚስ አያሠሩ ለለባሽ ይሸጣሉ። በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ ድውር ሲያልቅ እንዳመጣ እማማ ዘርፌ ቤት እላ ካለሁ። በልጅ እግር ፈትለክ ብዬ እማማ ዘርፌ ቤት ስደርስ ማንም የለም። ግቢው ጭር ብሏል ወደውስጥ ዘለቅሁ። በረንዳውን አልፌ ገርበብ ያለውን የሣሎኑን በር አንኳኳሁ።

«ማነው?» አለኝ ዳዊት ምች።

«እኔ ነኝ» መለስኩ።

ገርበብ ያለውን በር ከፍቶ ምች ወደ እኔ መጣ። ከውስጥ ከጀርባው ባለው ጠረጴዛ ላይ የካምቦሎጆ መግቢያ ትኬቶች ተበታትነው ይታዩኛል። ምች ዓይኔ ያረፈበትን ቦታ ተከትሎ እስተዋለና በሩን መልሶ ዘግቶ የመጣሁበትን ጠየቀኝ። ቢያውቅም ነገርኩት። «እማዬ የለችም። እዚህ ጠብቃት» ብሎኝ ምች ወደ ውስጥ ገብቶ በሩን መልሶ ዘጋው።

ጥርጣሬዬን ግልጽ ለማድረግ ጠጋ አልኩና ዘበሩ ቀዳዳ ወደ ቤቱ ውስጥ አየሁ። መብራት አብርቶ በታላቅ ጥንቃቄ የትኬቶቹን ተመሳሳይ ቁጥር እያየ በሙጫ ያጣብቃቸዋል። የተጨማደደው ትኬት እንዲዘረጋጋ በመጽሔት ውስጥ ይከትና ይቀመጥበታል። ...

«ፉንጋይ ምንድነው የምታየው?» ከኋላዬ እማማ ዘርፌ ጠይቀው አስደነገጡኝ። ስደናበር በሩን ገፈተርኩት።
የዚያን ዕለት ምችም ሳየው እንደነበር ስለገባው ነው ማኖ ለማስነካት ዛሬ እንድ ኮና የሰጠኝ። ምስጢረኛቸውም ሆንኩ።

በዚያ ወቅት ብዙ ብር ይዞ ያየሁት ልጅ ዳዊት ምች ነበር። ነገር ግን ሁሌም ሐድራው አይጠፍላቸውም። አልፎ አልፎ ይነቃባቸዋል። እንዴ ዳዊት ድድ መታደራዊ ፖሊሲ ነቅቶበት በወገራ እሩን አብልተውታል። እንዲያም ሆኖ አንዱ ሌላውን አሳልፎ አይሰጥም።

የካምቦሎጆው አስተዳደር ሳይደርስባቸው ለበርካታ ጊዜያት በእንዲህ መልኩ መሸቀላቸውን አስታውሳለሁ። አልፎ አልፎ «ተመልካቾቻችን አንዳንድ አጭበርባሪዎች ሐሰተኛ ትኬት እያ

ዘጋጁ ለገበያ ስለሚያቀርቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ብታደርጉ» ተብሎ በድምፅ ማጉያ ሲለፈፍ የምች ብስጭት ትገ ይለኛል።

ከጨዋታ በፊት ይህ ልፈሩ ከተካሔደ ትኬት መሸጡን አቁሞ ከአካባቢው ይሰወራል። ካምቦሎጆ ውስጥ ገብቶ ጨዋታ ሊጀመር አካባቢ ከሆነ «ፉራዎች!» ይልና ምች ያላግጥባቸው ነበር።

ፑሉቶ፣ ውሮ፣ ዲዲ፣... ሣር አጭደው ለሴተኛ አዳሪዎች በዱንቡሎም በዲናሬም ይሸጣሉ። የሚያጭዱት በምላጭ ሆኖ ፍጥነታቸው ማጭድ የያዘ ሰው ያስንቃል። በድፍን አዲሳባ የት አካባቢ የደረሰ ሣር እንዳለ አሳምረው ያውቃሉ። ከሊሳቸው ሁለት- ሦስት ምላጭ አያጡም። ሣሩን ካጨዱ በኋላ የሚያሥሩበት ወፊቾ ደግሞ ከወገባቸው ላይ አይጠፋም።

የእነዚህ ጓደኞቼ ቀንደኛ ጠላቶች ዘበኞች ናቸው። በዚህ ምክንያት ልጆቼ ቀን ቀን ሣሩ የሚገኝበትን አካባቢ ይሰልሱና አጨዳውን የሚያካሂዱት በጨለማ ነበር። አንዳንዴ ተይዘው ቢወ ገሩም ብዙ ጊዜ ይቀናቸዋል።

ቁልጭ እና ባሪቾ 'እጀወርቅ' ናቸው። ባለመፈደማቸው፣ ሣር አጭደው ባለመሸጣቸው፣ መኪና ባለመጠበቃቸው፣ ጋዜጣ ባለመለቃቀማቸው ኩራት ይሰማቸዋል። አብነትና ደረጀ *አሸቃዮች ናቸው።

ቁልጭና ባሪቾ ሰዎች ካምቦሎጆ ትኬት ቆርጠው በሚገቡበት ሰዓት ሥራ ይበዛባቸዋል። በዚያ ውክቢያ መካከል አንድ የተዘናጋ ካጋጠማቸው ይመነትፋሉ። የተሰረቀው ሰው ኪሱን እየፈተሸ አላፊ አግዳሚውን በጥርጣሬ ዓይን እያየ ሌባውን ሲፈልግ መመልከት በጣም ያስቅ ነበር። የአንዳንዱ ተሰራቂ አጫጭሽ ያዘነውንም ልጅ ቢሆን ያልተሰመደ ስለሚሆን ሳይወድ በግድ ያስቀዋል።

ደረጀ መጽሐፍ የማንበብ ልምድ ነበረው። ጥሩ አንባቢና ተራኪ ነበር። ታላቅ እህቱ መስከረም ኮሌጅ ስለምትማር መጽሐፍ ገዝታ የማንበብ ልምድ ነበራት። መስከረም ሁላችንንም ፋይዳ የሌለን አድርጋ ትገምታለች፣ በጣም ትንቀናለች። ይሁን እንጂ እሷ ሳታውቅ ወንድሟ መጻሕፍቱን ሠርቆ አምጥቶ እና ነብና እነበረበት ይመልሰላታል።

ቁልጭና ባሪቾ ሸቃቅለው እስኪመጡ ካምቦሎጆ ሣሩ ላይ ጋደም ብለን አንድ የዘመኑ መጽሐፍ ይተረካል። በዚያ የንባብ ወቅት ማሞ ውድነህ፣ ብርሃኑ ዘሪሁን፣ በዓሉ ግርማ፣ እቤ ጉበኛ እና ሌሎችም ቀልባችንን የሳቡ ደራሲያን ናቸው። ከእነዚህ ደራሲያን

---

*አሸቃይ፡ የሌባ ተቀባይ።

መካከል የአንዱን ሥራ ባሪያውም ሆነ ደረጀ ሲተርኩልን ታሪኩ እንደፈልም ወለል ብሎ ይታየናል።

የገዙትን መጽሐፍ ገንዘብ በቸገራቸው ጊዜ ይሸጡታል። ከዚያ በፊት እኔ ቆሎ ተውሼ አነበዋለሁ። ሳነብ ዝግ ብዬ ነው፤ ስረሳም እንደዚሁ ነበር። አብነት ባሪያውም ሆነ ደረጀ ፈጣን አንባቢዎች ስለነበሩ ሲረሱም ፈጥነው ነው። በአንድ መጽሐፍ ጉዳይ ተከራክረው ካልተግባቡ ዳኝነት የሚጠሩት እኔን ነበር። ይህ አይነቱ ተፈላጊነቴ ይጥናን ያበሽቀዋል።

ይጥና ሪቼ የቦውሊንግ ኳስ ለማቀበል በወር 50 ብር ተቀጥሮ መሥራት ስለጀመረ የህብታም ስሜት የተጠናወተው ልጅ ሆኗል። እኔ መጽሐፍ አንጠልጥዬ ሲያየኝና ለእግኝነት እነ አብነት ባሪያውና ደረጀ ሲፈልጉኝ ያመው ጀመር። በትንሽ በት ልቁ "አንባቢው እዚህ ላይ ምን አስተያየት አለህ?" እያለ ያሳግ ጥብኛል። ሲኒማ አብረን ገብተን ቴንቦ ሲሆን "አንባቢው አንብብ እንጂ" እያለ ያበሽቀኛል።

ከሚገባ በላይ ብንደፋፈርም ከመዛዛት አላለፍንም። አን ዳንዴ እኔን የሚያጠቃበት መንገድ መረር ያለና በልጅ መንፈስ የማይታሰብ ሆኖ አገኘዋለሁ። አንድ ቀን ማታ አባቴ ሞቅ ብሎት መጣ። ሌሊቱን ሁሉ ሲጨቀጭቀኝ አደረ። መፈጠሬን የጠላሁበት ጊዜ ነበር።

በበነጋው ከሰፈር ልጆች ጋር ስለ አዳሬ ሳወጋ ሻቃ በመ ሐል ገባና "ትናንት ማታ እኮ ይጥና ከአባትህ ጋር ጎደቴ ጠጅ ቤት ቴሌቭዥን እያዩ ሁለት ብርሌ ጠጅ ገዝቶላቸው ስላንተ ሲያወራላቸው ነበር። እሱ ነው ያስጨቀጨቀህ" ብሎ አረዳኝ።

ከዕለታቱ በአንድ ቀን እኔና ይጥና ተግባብተን የምን መራመርበት ቀን ደረሰ። ከጳውሎስ ኞኞ አስደናቂ ታሪኮች በአን ደኛው ውስጥ አንድ ዱዳ ቦክሰኛ በጨዋታ ላይ እያለ ከተጋጣ ሚው በተሰነዘረበት ከባድ ቡጢ ምክንያት መናገር መጀመሩን አንብበን ተገረምን። እኔና ይጥና ይህንን አጋጣሚ በመገረም ብቻ ልናልፈው አልፈለግንም። የአባባ ይግም አህመድ የመጨ ረሻው ልጅ ዱዳ ነው። እናጫውተው ብለን ሪቼ ቦውሊንግ መጫወቻ የሕፃናት መዝናኛ ማዕከል ይዘነው ሄድን። ዥዋዥዌ በየተራ እየገፋነው በተደጋጋሚ በቡጢ አናቱን መታነው።

ልጁ ይጮኸና "በኃይል ግፉኝ" ይለናል በምልክት ቋንቋው። በጩኼ አናቱን እያፈራረቅን ብንነርተውም ሙከራችን ያሰብነውን ውጤት ሳያመጣ ወደ ቤታችን ተመለስን።

ቦቸራ፣ ዶጅና አመዶ የተዋጣላቸው ድብ ድብ ቁማር ተጫ ዋቾች ነበሩ። በተለይ አመዶ ፍራንኳን በዓይኑ ሳያይ፣ በእጁ ውስጥ እያሽከረከራት በሳፈር ትሁን በዘውድ አሳምሮ ያውቃ

ታል። እንቅልፉን ተኝቶም ቢሆን "ጉል! ማነው የሚያጠጣ?" ሳይል አይቀርም እያልን እንቀልድበታለን።

ክረምት ሲመጣ ሦስቱም ጉልት ውስጥ በቆሎ ጠባሽ ሆነው ይቀጠራሉ። አንድ በቆሎ ተጠብሶ ዱምቡሉ ይሸጣል። የብር ጠብሰው ቢሸጡ ደመወዝ ዲናሬ ይከፈላቸዋል። ማምሻቸውን ሆዳ ቸውን ችለው ከአንድ ብር እስከ ሁለት ብር በቀን ይሸቅላሉ።

ሸማች ማግኘት ላይ ከፍተኛ ችግር ነበረባቸው። የቀን ሠራተኞቹ ማምሻቸውን የበቆሎ ጥብስ ሊበሉ ይመጣሉ። ገበያው በጭቃ የሳቆጠ በመሆኑ አንዳንዶቹ ቁምጣ ሱሬ ለብሰው፣ ጋቢ ተከናንበውና ቦቲ ጫማ ተጫምተው ይመጣሉ።

አንደኛው በሳተኛ "እስኪ ጥብስ?" አለና ቦቸራን ጠየቀ። ጠብሶ ካከማቸው አንዷን አነሳና አሳየው።

ሰውዬው አንዷን የበቆሎ ፍሬ ፈልፍሎ ቀመሰና "ደረቅ ነው።" ደገመና ሌላውንም እንዲሁ ቀምሶ "አይ፣ እሸት እይደ ለም!" ብሎ ወደ ዶጅ ገማጣው መደብ ሲሄድ ቦቸራ አንድ ፍም አነሳና ሰውዬው ቦት ጫማ ውስጥ ጨመረበት።

ሰውዬው "ውይ! እማምዬ!" አለና ዘለለ። ወድቆ ቦቱን ሽቅብ ሲሰቅል ፍምዋ በቁምው ገብታ ቂጡን ለበለበችው። በፍጥነት ብድግ ቢል ተመልሳ ቦቱ ጫማ ውስጥ ገባች።

ተመልካች አስቂኝ ፊልም እንደሚያይ ይንከተከታል። ዶጅ ገማጣው አጠገቡ ያለውን አነስተኛ ደንበኛን ውሃ በፍጥነት አነሳና ቦቱ ጫማ ውስጥ ጨመረለት። ሰውዬው ከሲኦሉ ተገላ ገለ። ከፍተኛ ጦርነት ቢፈጠርም ቦቸራን ደፍሮ የሚመታ በመጥ ፋቱ ችግሩ በዚሁ አለፈ።

የሰፈር ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ከካምቦሎጆ ተጠባብቀን ነው ወደ ሰፈር የምንሄደው። አንዳንዴ እንደ ጉዳያችን አስ ፈላጊነት እንነጣጠላለን። ቁልጭና ባሪዥ ሞኝ ስለሆኑ በሰው ትከሻ በሽክም ነው ወደ ሰፈራቸው የሚሄዱት። አንዳንዴ ሽቀ ላው አልሰምር ሲላቸው ቀጪሳውና ሴምላል ትከሻቸውን ያከራ ያሉ። ባሪዥ ለቀጪሳው፣ ቁልጭ ደግሞ ለሴምላል ስሙኒ ስሙኒ ከፍለው እስከ ሰፈራችን በሽክም ይሄዳሉ። ባሪዥም ቁልጭም ቁንጥንጠች ናቸው። በልጆች ትከሻ ላይ ሆነው ልፍያ ያምራቸ ዋል። ወይም እግራቸውን እያወራጩ እንደ ሕንድ የፊልም ተዋ ናይ ይዘፍናሉ። በዚህ ጊዜ ሴምላል ሚዛኑን ለመጠበቅ እየተ ንገዳገደ "አንተ እናትክን! አርፈህ ተቀመጥ!" ብሎ ይቆጣል።

ቀጪሳው ባሪዥን ተሸክሞት ሲሮጥ፣ ቁልጭ ሴምላልን "ድረስበት! ዱምቡሉ አጨምርልሃለሁ!" ይለዋል።

ሴምላል ይሮጣል።

ቀጪሳው አጠገብ ደርሶ ቁልጭ፣ ባሪዥን ሊይዘው ሲን ጠራራ፣ ሴምላል ሚዛኑን ይስታል።

"ዋ! እግሬ መሬት ከረገጠ ዱምቡሉ እቀርጣለሁ!"

"እረ! ወንድ እናያለና! ቂርቆስን! ሰፈር እንድረስ" ይዝ ታል። ሴምላል፣ የተዝረከረከ ንፍጡ ሽቅብ አልሳብ ሲለው በኃ ኬቱ እጅጌ ይሞዥቀዋል።

"እሺ ሸንኮራ ልግዛ!" ቁልጭ ቁልቁል እያስተዋለ ሴምላልን ይጠይቀዋል።

መልስ ሳይሰጠው ቁደ ሸንኮራ ነጋዴው ይጠጋለታል። ባሪቾም ቀጢላውን አስፈቅዶ ሸንኮራ ይገዛሉ። ተሸካሚዎቹ የተሰ ጣቸውን ሸንኮራ ኪሳቸው ይከታሉ። አሸካሚዎቹ ግን በተቀ መጡበት ሸንኮራውን በጥርሳቸው እየሰነጠቁ መምጠጥ ይጀም ራሉ። ልጣጩን እርስ በራስ እየተወራወሩ ይማቱበታል። ይህ ሁኔታ ለተሸካሚው አሳር፤ ለተፈናጠጠው ደግሞ አዝናኝ ድርጊት ነበር...

...የለገሃር ድልድይ ወደ ማታ ሰው ይበዛበታል። ቢሆንም ተሸካሚዎቹ በስምምነታቸው መሠረት መሬት ሳይረግጡ ሰፈር መድረስ አለባቸው።

ባሪቾ የድልድዩን መደገፊያ ቱቦ አጋድሎ ይይዝና እንደ ሕንዱ አከተር ራሺካፑር መዝፈን ይጀምራል። ቁልጭም የላታ ማንግሽካርን ድምፅ አስመስሎ ይመልሳል።

ተሸካሚዎቹ ለመራመድ ሲሞክሩ አሸካሚዎቹ አጥብቀው በያዙት ቱቦ አማካኝነት አላንቀሳቅስ ይሏቸዋል። በዚህ ጊዜ ቀጢላው ተቆጥቶ "ስማ አናትክን! ክርኬን እንደሆን ቁጭ ታደር ጋታለህ። እግርህ መሬት ነካ አልነካ ግድ የለኝም። አርፈህ ተቀምጠህ ነው ሰፈር ላደርስህ የተስማማነው!"

"ወንድ! እግሬ መሬት ይንካና ታስከፍለኛለህ!"

ከብዙ ብዙ ድካም፣ ንትርክና ማስፈራራት በኋላ ሠፈር ይደርሳሉ። በዚህ ጊዜ ቀጢላውና ሴምላል ድካማቸውን ረስተው፣ ሸንኮራቸውን እየኮረሸሙ የጎደላቸውን ፍራንክ እንዴት ሞልተው ሊኒማ መግባት እንደሚችሉ ማሰብ ይጀምራሉ።

ክርስትና አባት

"እግዚአብሔር ድሆችን ይወዳቸዋል።
ለዚህ ነው አብዝቶ የፈጠራቸው"
አብርሃም ሊንከን

ቲቲ ውሻዬ በኩዳዴ ፆም ሰሞን የዓሣ አጥንት በልታ ጉሮሮዋ ላይ በመሰንቀሩ ትንሽ ታማ ሞተችብኝ። በጣም አዘን ኩኝ። ኃይሉ ዶሮ ሊያፅናናኝ ቤት መጣና "ለምን እኔና አንተ ርግብ አናረባም?" አለኝ።

"የእኛ ቤት መንገድ ዳር በመሆኑ አይመችም" ስለው "እኛ ግቢ ውስጥ እኮ ነው የምናረባው። ፍራንክ አዋጥተን ርግቦቹን እንገዛለን። ከዚያ ቤታቸውን ሠርተን እናኖራቸዋለን።"

ሁለት፣ ሁለት ብር አዋጥተን ወንድና ሴት የሆኑ አራት ርግቦች ከእንግዱ ላይ ገዛን። እንግዱ ከመንደራችን ወረድ ብሎ ከጨነቀው ሱቅ በታች ነው የሚኖረው። በርካታ ርግቦች አሉት። ርግብ ከሚያረቡ ሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት አለው። ወንጭፍና ትንንሽ ድብልብል ድንጋዮች በኪሱ ይይዛል። ቤቱ ተወልደው ያደጉ፣ እጁን በደንብ የለመዱ ርግቦች አሉት፣ በእነዚህ ርግቦች አማካኝነት ሌሎች ርግቦች ጠለፋ የሚያካሂድበት ጊዜም እለ። ይህን ለማድረግ ሌሊት ነው የሚነሳው። የቤት ርግቦቹን በሰሪያን ኮት ኪሱ ይይዝና አሰበው አካባቢ ሲደርስ ወደ ሰማይ ይለቃ ቸዋል። በአየር ላይ ይበርሩና ታች ሰው ግቢ ውስጥ ሌሎች ርግቦች ሲያዩ ያርፋሉ። ርግቦቹ ያረፉባቸው ሰዎች ይይዟቸዋል። ላባቸውን ይነቅሉታል። ለዕለታት እዚያው ይቆያሉ። ላባቸው እን ዳደገ አንድ ሁለት ርግቦችን አስከትለው ወደ ሰፈራችን ይመ ጣሉ።

እንግዱ አበበ እንዲህ አይነት ዝነኛ ርግቦች ስላሉት አንዱን ርግብ ወደ ሰማይ ለቅቆት ሲበር "ይመለሳል" ይላል በእር ግጠኝነት።

"ለማየት ያብቃህ አይመለስም" ይላል፤ አንዱ የሰፈር ልጅ።

"እንወራረድ።"

"በስሙኒ! በስሙኒ!"

"እሺ።"

ያስይዛሉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሲላ የተባለው ርግቡ በአያሌ ርግቦች ታጅቦ ከች ይላል! ሰፈራቸው በጭብጨባና በጩኸት ይደምቃል።

እንግዱ ርግቦቹን ከሸጠልን በኋላ ለሣምንታት የተረጋጋ ሕይወት ኖርን። ላባቸው የተነጨው ርግቦች መንቀሳቀስ ሲጀምሩ

አንዳንድ ስጋቶችን ፈጠሩብን። ከነኃይሉ ዶሮ ቤት ጓሮ ከእነ አደባይ ሰፈር አንድ ዱርዬ ድመት እየመጣ ቋሚ ጠላታችን ሆነ። እሱን ሌት ተቀን ስንጠብቅ፣ ብቅ ሲል በድንጋይም በዱላም ለመከላከል በምናደርገው ጥረት መንደሩን በጩኸት እናምሰ ዋለን። ትንሽ አሚቸው የተኙ አሮጊቶች እየተራገሙ ከየቤታቸው ይወጣሉ።

ድመት የገደለ እጄ ይንቀጠቀጣል የሚል እምነት ስለዘ ሩብን ዱርዬውን ድመት ከማባረር ፈቅ ያለ ድፍረት አልነ በረንም። ዱርዬው ድመት ግን ጨክኖ አንዱን ወንድ ርግብ በላ ብን። በዚህም ይሙት በቃ ፈርድንበት፣ ኃይሉ ዶሮ ጥሩ አላሚ ስለነበረ አነጣጥሮ የወረወራት ድንጋይ አንዱ ጆሮግንዱን ብትለው ዱርዬው ድመት ሲንደባለል በጣም ደስ ብሎኝ ጮኽኩኝ። ኃይሉ ዶሮም አብሮኝ ጮኸ "ወይኔ ፉንጋይ! እጄን እየው፣ መንቀጥቀጥ ጀመረ" አለኝ።

ሳይ እጁ ምንም አይንቀጠቀጥም። ዞር ስንል ድመቱ ተነ ስቶ ጥሻ ውስጥ ገብቷል።

"ይኼውልህ! ባለመሞቱ ነው እጄን ያንቀጠቀጠኝ የነበረው የተወኝ።"

አመንኩት።

ከዚህ ዱርዬ ድመት እንዲገላግለን እንግዱን አማከርነው። "ከርክ ከከፈላችሁኝ አናቱን ብዬ እገላግላችኋለሁ" አለና ተከዝ ብሎ "ግን ሌላ ብልሃት አለኝ። ድመቱ ለማዳ ነው ወይስ ዱርዬ?" ጠየቀን።

"እረ በጣም ዱርዬ ነው ማንንም አያስጠጋም" መለስኩ እኔ።

"ለማዳ ቢሆን ከሰፈራችሁ እንዲጠፋ ቀላል ብልሃት ነበረኝ። ዱርዬ ከሆነ ግን ስለማይያዝ መግደል ብቻ ነው ያለብን" አለ እንግዱ።

"ለማዳ ቢሆን ምን ታደርግ ነበር?" ዶሮ ጠየቀው "ለማዳ ቢሆን ኖሮ ትንሽ ቅቤ ትፈልጉና ይዛችሁት አፉን ዙሪያውን ትቀ ቡታላችሁ። አሷን እያሸተተ ሚያው እያለ ከሰፈሩ ይጠፋል። ብዙ ያስቸገሩኝን ድመቶች ያጠፋሁት በዚህ ዘዴ ነው" ብሎ አስደነቀን። ለወደፊቱም የመከላከያ ጥበቡን ዘረጋ።

"ለሆያሆዬ ጨፍረን እንከፍልሃለን። ግን ድመቱን ከገደልክ በኋላ እጅህን ቢያንቀጠቅጥህ እኛ የለንበትም" አለ ኃይሉ ዶሮ።

እንግዱ እየሳቀ "የምን እጅ መንቀጥቀጥ? የእኔ እጅ ነው የሚንቀጠቀጠው? ሰንትና ስንት ድመት ገድያለሁ። አንዷም እጄን አላንቀጠቀጠችውም።"

አላመነውም።

ርግቦቻችንን ቤታቸው ውስጥ ከተን ዘጋንባቸው። እንግዱ የዳዊት ወንጭፉን አነሳና ጎልያድ የሆነብንን ዱርዬ ድመት ሊገ

ላግለን ደፈጣ ያዝን። ሁሌም አዘጋጅቶ በኪሱ ከሚያስቀምጣቸው ጠጠሮች አንድ ሁለቱን መረጠ። ወንጭፉን በቅጡ መሥራቱን አረጋገጠ። ድመቱ ይመጣል ብለን ባመላከትነው አቅጣጫ ላይ ፀጥ ብለን ዓይናችንን ሳናረግብ ጠበቅነው።

ብዙም ሳንቆይ የጣራ መሏጠጥ ድምፅ ተሰማን። ኃይሉ ዶሮ ተንጠራርቶ አየና ለእንግዱ በጥቅሻ እየመጣ ነው አለው። ድመቱ ብቅ ሲል የዳዊት ጠጠር ተወነጭፉ ግንባሩን በጠረ ቀችው፣ በሁለት እግሩ ቆመ። ቁልቁል ከጣራው ሲወረወር በአናቱ መሬት ተተከለ። አንድ ሰቅጣጭ ድምፅ አሰማ። እየተ ንፈራፈረ ነው። መንደርተኛው ግልብጥ ብሎ ወጥቷል።

"ወይኔ ድመቱን ገደሉት" አለች አዳነች።

"አንቺ ወሬኛ!" አለና ኃይሉ ዶሮ አፈጠጠባት።

"ወይኔ ጉዳችሁ ፈላ! ማነው የገደለው? ገዳዩ እጁን ያን ቀጠቅጠዋል" አሉ አማማ ሽጊቱ።

እንግዱ በጥቅሻ ገለል እንድንል ነገረንና "በቃ ይሞታል። ከርኬን ግን ለሆያሆዬ ቁጭ ታደርጋላችሁ።"

ከዱርዬው ድመት ሞት በኋላ ለጥቂት ጊዜ በሰላም መኖር ጀመርን። ሁለቱ ርግቦቻችንም ዕንቁላል ጣሉ። እስከዛሬ የማናው ቀው ምስጢርም ተከሰተ። ርግቦች ምንጊዜም ሁለት ዕንቁላል ነው የሚጥሉት። ሁለቱም ይፈለፈላሉ። ሲያድጉም ባልና ሚስት የሚሆኑት እነዚህ ጫጩቶች ናቸው።

ከነኃይሉ ዶሮ ቤት በሦስትና በአራት መቶ ሜትር ርቀት ላይ የአባባ ተፈሪ ወፍጮ ቤት አለ። አባባ ተፈረ ግቢያቸው ውስጥ ያፈራውን ወይን ሲበሉ የመጡ ወፎችን አንድ ሁለቱን አስገድለው ለመቀጣጫ ወይኑ መካከል እንዳንጠለጠሉ ወሬ ሰን ሰማ፣ ስጋታችን በጣም ጨመረ። እርግጠኛ ለመሆን ሄደን በግቢው ቀዳዳ ተመልክተን የተንጠለጠሉ የወፎች ሬሳ ዓይተ ናል። ስለዚህ ርግቦቻችን ወደዚያ በረው በሌዱ ቁጥር በስጋት እንወጠራለን። በሰላም ሰፈራችን ሲመለሱ ትንፋሻችን መለስ ትላለች።

አንድ ቀን አባባ ተፈረ ግቢ ውስጥ ያለችው እትዬ ወይንሸት ሆያሆዬ እያስጨፈረችን ነው። አንዳች የሚያክል ሙል ሙል በቀኝ እጅዋ ሽቅብ ይዛ እያቁለጨለጨችን "በደንብ ጨፍሩ አለዚያ ይህ ሙልሙል አመለጣችሁ።"

እንደተባልነው በደንብ ጨፍረን እሷንና ቤተሰቦቿንም ከዓመት ዓመት እንዲያደርስ መርቀን ሙልሙሉን ተሸልመን ስንወጣ፣ ቤታቸው በረንዳ ላይ የቆሙት አባባ ተፈረ "ጉ ጨፍሩ!" አሉን።

ድሮ ልንጨፍር ወደ እሳቸው ቤት ስንሄድ በዘበኛም፣ በውሻም ነበር የሚያባርሩን። ባሬ ግን ማዜም ስንጀምር በእጃ ቸው ይዘውት የነበረውን ቆልማማ ፕላስቲክ መሰል ዕቃ ወደ ጆሮ

ግንዳቸውና አፋቸው አስጠግተው "በል አድምጥ!" ብለው ፕላስቲኩን ወደ እኛ አስጠጉት።

"ስልክ እኮ ነው" አለ ቀጪላው።

በኋላ ማንነቱን ያወኩት ልጃቸው አትክልት ከአሜሪካን ለዓመት በዓሉ ስልክ ደወለላቸው። አስጠርቶን የሚያስጨፍረን እሱ ነበር። ጨፍረን ስንጨርስ አሁንም በስልኩ አወሩ።

"አስር አስር ብር ስጣቸው?!" አባባ ተፈራ አንባረቁ። ድን ጋጤው አላቸውን ብቻ ሳይሆን እኛንም ነበር ያናወጠን። የእኔ ልብ ስትንፈራፈር ሹራቤን ቀዳ ልትወጣ ምንም አልቀራትም።

"አትቀልድ! አስር አስር ብር?!" አሉና ቆጠሩን።

ሰባት ነን።

አባባ ተፈራ ቤታቸው ከብት ያረባሉ። ወተታቸውን በከተማው ለሚገኙ ሆቴሎች የሚያድሉበት ፔጆ መኪና አላቸው። የመኪናቸውን ሞተር ካስነሱ በኋላ እስኪሚሚቅ ዘበኛቸውን ቁና አስይዘው ወደ መንገዱ ይልኩታል። ዘበኛው ከመንገዱ የጠርሙስ ስባሪ፣ ሚስማርና አጥንት እየለቃቀመ አስፓልቱ ድረስ ይዘልቃል። ተመልሶ የጥሬቱን ውጤት በቁና ሞልቶ ካላያቸው በኋላ ነው መኪናቸውን አስነስተው የሚሄዱት። በለቀማው ካልተደሰቱ እንደገና የሚልኩበት ጊዜ ነበር።

"ወቸ ጉድ! አያችሁልኝ? ይኼ ሁሉ ቅራቅንቦ እኮ መንገድ ላይ የተበተነው የመኪና ጎማ ስማፈንዳት ነው" ይላሉ አባባ ተፈራ በተስቀመው ቆሻሻ እየረኩ። ከእኛህ ሰውዬ እጅ ነው ልጃቸው በድምሩ ሰባ ብር እንድንቀበል ያዘዘልን። አላቸው ምናቸው ሞኝ ነው? አንድ አንድ ብር አደሉን። ስልጃቸው ግን "ያው እንዳልከው አደረኩልህ። እንደገና ይጨፍሩልህ?" አሉት።

እኛም በበኩላችን ቀኑን ሙሉ ጨፍረን የማናገኘውን አንድ አንድ ብር በአጭር ጊዜ በማግኘታችን ተደሰተናል።

ብዙ ጊዜ ሳያልፍ የተበላብንን ርግብ ስመተካት እንደገና ገንዘብ የሚያስፈልገን ምዕራፍ ላይ ደረስን። አንድ ርግብ ስመ ግዛት ምጥ ውስጥ ገባን። ወላጆቻችን ለልጅ ገንዘብ መስጠት ዱርዬ ያደርጋል ብለው ስለሚያምኑ በጭንቃችን ሊደርሱልን አልቻሉም።

ርግቦቹ ዕንቁላሎቹን በመፈራረቅ ነው የሚያቅፉት። ባሏ በዱርዬው ድመት የተበላባት ርግብ ከዕንቁላሎቹ ላይ ስለማትነሳ ስንዴም ሆነ ውሃ ጎጆዋ ድረስ እናቀርብላታለን። እንደነገሩ ስትቀ ማምስ እንደሰታለን። ዕንቁላሎቿን አቅፋ ስለምትውል ጭንቀታችን አየለ።

ከኃይሉ ዶሮ ጋር ፍራንክ የምናገኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር መከርን። ካምቦሎጆ አካባቢ የምንሸቅለው ጠርሙስና የጋዜጣ ጥርቅም የምንፈልገውን ያህል ገንዘብ ሊያስገኝልን አልቻለም።

ገንዘብ ይሰጠኛል ብዬ የማምነው ዳዊት ምኑ ስሞኑን ፖሊስ ቤታቸው ድረስ መጥቶ ከማጭበርበሪያ ተኬቶቹ ጋር እጅ ከፍንጅ ያዘው። ተባባሪዎቹ የሆኑት ዳንኤል ድድና ዳንኤል ገምቦ እንድ ላይ ጠባይ ማረሚያ ታስረዋል።

አንዳንድ ሥራ ለመሥራት ወሰንን። ከሴምላልና ከቀጪላው ጋር በመሆን ከለል 'መፈደም' ጀመርን። አሳዛኙ አጋጣሚ፣ በመጀመሪያው ዕለት ቆሜ አመዱን በስንጥር እየ ጫርኩኝ ከሰል ስለቃቅም አንድ ዘመዳችን አየኝ። ወደ ግል ጉዳዩ መሔዱን ትቶ በፍጥነት ወደ ቤታችን መጥቶ ለአባቴ ነገረው። ወገራ አቤቴ እንደሚጠብቀኝ ገብቶኛል። እንደ መታደል፣ አባቴ በዕለቱ ዕቁብ ወጥቶለት ስለነበር በከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ማረኝ። እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ ለማግኘት አሣራችንን የምናይበትን አንድ ብር ግን አልሰጠኝም። እኔ ከግርፊያው በማም ለጤ ተደሰትኩ እንጂ የአባቴ ንፍገት ቅር አላሰኘኝም።

ገንዘብ የምናገኝባቸው ዕንቁጣጣሽና ሆያሆዬ በጣም ራቁ። ባልታሰበ ቀን የኃይሉ ዶሮ ታላቅ ወንድም የግርማ ክርስትና አባት አባባ ባይላ መንገድ ላይ ዶሮን አግኝተውት ሁለት ብር ሰጡት። በዚህ ተአምር በደስታ ሰክሮ ሮጠ መጣና አበሰረኝ።

ኃይሉ ዶሮ በተረጋጋ መንፈስ አንዱን ብር ዘርዝሮ የስሙኒ ደስታ ከረሜላ ገዛ። ከወርቄ ሻይ ቤት የሃያ ሣንቲም አራት ፓስቴ ሸመትን። ቤታቸው ጓሮ መሸግን። ፓስቴና ደስታ ከረሜላውን እኩል አካፈለኝ።

"አንዱን ፓስቴ ሰንጥቀው።"

ያለኝን አደረኩ።

"ስንጥቁ ውስጥ ድፍን ከረሜላ ጨምር" አለኝ ዶሮ፣ ይህ የራሱ ፈጠራ የሆነ የፓስቴ አበላል ነው። ብር ስላገኘን ወንድ ርግብ መግዛቱን ጉዳይ መክረን ጨርሰናል።

"ግመጥ"

ከረሜላዋጋ ደርሰን ኮርሸም እስክምናደርግ ያሉት ገመጣ ወቼ አስጎምጂዎች ነበሩ። የዓለምን ፍስሐ ጭድ ላይ ተንጋለን እንደለታለን። እንዲሁ ሳቅ... ሳቅ... ፍንድቅ... ፍንድቅ እንላለን። እማማ ሸጊቱ ድንገት በግዙፍ ቁመናቸው ብርሃኑን ከለሉን። እኔና ዶሮ ቶሎ ብለን ፓስቴውን ሹራባችን ውስጥ ሸጎጥን። እሳቸው ግን "አላችሁ?" ብለው መኖራችንን ብቻ ተመልክተው ተመለሱ። ኃይሉ ዶሮ ግን ተሸበረ "ወይኔ አይታናለች ውሸቷን ነው፤ በኋላ ልትገርፈኝ ነው አሁን ዝም ያለችው! ግን አላየችኝም?" አለና ጠየቀኝ እርግጠኛ ለመሆን።

"አይተውናል።"

"ፓስቴ ስንበላ።"

"አይደለም፣ ጓሮ ቁጭ ብለን ስንጫወት።"

"እኔ ግን ፓስቴ ስንበላ ያየችን መሰለኝ።"

"እረ አላዩንም።"

"አይታናለች! በል! ቶሎ በል! የያዝከውን ፓስቴና ከረሜላ ሽንት ቤት እንጨምር::"

"ለምን?"

"አይታናለች!" አንባረቀ ዶሮ::

ጭንቀቱ ተጋብቶብኝ፣ ነገሩ አንጀቴን ቢበላኝም ያለኝን አደረኩ:: እሱም በሹራቡ ጠቅልሎ የያዛቸውን ፓስቴዎችና ሣን ቲሞች ከአንድ ብሩ ጋር ሽንቲ ቤት ውስጥ ጣላቸው::

ከኩሽናቸው ፊት ለፊት እንጨት ተፈልጦ ተከምሯል:: ኃይሉ እሮት ገብቶ ልብስ ደረበ፣ ሲገረፍ ቂጡን እንዳያመው:: እኔ በቅርብ ሁኔታውን እከታተላለሁ:: ወደ ኩሽና መጣና "እማዬ ለምን አትገርፊኝም?"

"ምን አጥፍተህ?"

"አሁን እኮ ፓስቴ ስበላ ያየሽኝ መስሎኝ::"

"ምን አለበት ብትበላ? ታያላችሁ የእኔን ጅል?" እማማ ሽጊቱ በመገረም ሳቁ::

"ኧረ! ስበላ ብታገኚኝ ምንም አትይኝም?"

"ምን እልሃለሁ? ካገኘህ እንክት አድርገው!"

ዶሮ አጓራና መሬት ዘፍ አለ:: ተንፈራፈረ:: "እኔ እኮ ያየሽኝ መስሎኝ፣ ከየት አመጣህ ብለሽ ትገርፊኛለሽ ብዬ፣ አባባ ባይሳ የሰጡኝን ሁለት ብር ዘርዝሬ ..."

"ሽንት ቤት ጨመርከው?"

"አዎን::"

"አወይ ልጄን! በል፣ ብርህ ካልወጣ አንድም ሰው ሽንት ቤት እንዳታሸና::"

"እሺ!"

በዚህ መካከል የዶሮ አባት ግንበኛው አባባ ቱሉ በራቂ ከሥራ ድክም ብሏቸው መጡ:: ጎርናና በሆነ ድምፃቸው "ምን ሆንክ አንተ?"

"አንተ ነህ! ክርስትና አባት ሰው አድርግልኝ ስልህ ቂርቆስ አንስቶሃል አያልከኝ፣ ትምህርትህን ይገልጽልሃል አያልከኝ፣ ያሳ ድግሃል አያልከኝ፣ እንደ ግርማ፣ እንደ እቴነሽ ሰው ክርስትና እንዲያነሳኝ ሳታረግ ሕፃኑ ቂርቆስ ክርስትና እንዲያነሳኝ አድርገህ ብራን አስጠፋህብኝ" እያለ ተንሰቀሰቀ::

አባባ ቱሉ ነገሩ አልገባቸውም፣ ሽንት ቤት መሄድም ፈልገዋል:: ኃይሉ ዶሮ ግን አሳባልፍ አላቸው:: ግራ ቢጋቡ እኔን ማብራሪያ ጠይቀውኝ ሁሉንም ጉዳይ በዝርዝር ነገርኳቸው:: አባባ ቱሉ ከትከት ብለው ስቀው "ብሩን አሁኑኑ እኔ እሰጥሃለሁ:: የክርስትና አባትም እሆንሃለሁ:: ስታድግ ግን አንድ ሺ ብር አድርገህ ልትከፍለኝ ትፈርማለህ::"

"እሺ" አለ ኃይሉ፣ የዳመነ ፊቱ ወዲያው ወገግ እያለ::

"በል አሳልፈኝ ሽንቴን ሽንቼ ልምጣና እንዋዋላለን" አሉና ሁለት ብር አውጥተው ሰጡት:: ገለል አለላቸው:: ተጠናቀው እንደመጡ ውሉ በታላቅ እህቱ በአቴነሽ ተጻፈ::

የብድር ሰምምነት

እኔ አባቴም የክርስትና አባቴም ከሆነው ከአቶ ቱሉ በራቁ በዕለተ ቂርቆስ ንግሥ ሁለት ብር ተበድራለሁ:: ይህን ብር አድጌ ትምህርቴን ጨርሼ ኮሌጅ በተሼ እንግሊዘኛ አንደውሃ አንደጠጣሁ አንድ ሺ ብር አድርጌ ልከፍል ተሰማምቼ ፈርሜአለሁ::

ኃይሉ ዶሮ ፈረመ::

"መስሎሃል የምለቅህ" አሉ አባባ ቱሉ ከምራቸው:: የውል ወረቀቱን አጣጥፈው እያሰቀመጡ::

በሕይወታችን ለመጀመሪያ ጊዜ ኃይሉ ዶሮ በተበዳሪነት፣ እኔም በአማኝነት ተገኝቼ ፊርማችንን ያኖርንበትን ማኅደር ከጉዳይ ም አልጣፍነውም:: ነገር ግን ርግቡን ከእነ እንግዱ ገዝተን የማርባት ጥረታችንን እንዴት እንደምንቀጥል እያውጠነጠንን ተጠቃቅሰን ከቤት ወጣን:: እግዚሃር አብዝቶ ከፈጠራቸው ድሆች መካከል እኔና ዶሮ እንዲህ ማሳያዎቹ ነን::

እርቀ ሰላም ሲወርድ

"በጥበብ ካልተያዘ ጀግንነት ሞኝነት ነው"
(ያልታወቀ ደራሲ)

ይኸው በገዛ ቤቴ ውስጥ የቁም እስረኛ ሆኛለሁ:: ውጪ ስንጫወት ይህቺ መኩዬ ቀጫጫ ደፈረችኝና በቦክስ አገጭዋን መታኋት፣ መሬቱ ላይ ፍንችር አለች:: እስከምትነሳ ከጠበቅኩ በድንጋይ እንደምትፈነክተኝ ስለማውቅ እግሬ አውጪኝ ብዬ ቤቴ ጥልቅ አልኩኝ:: እያለቀሰች በእልህ ቁና ቁና እየተነፈሰች ደረሰች ብኝ:: እናቴ "ምን ሆንክ?"

"ይኼ ፉንጌ ነገር ሳልፈልገው መታኝ!"

"ስንት እንጀራ ቢበላ ነው የሚመታህ? ይኼ ጋንድያ! ቆይ ይምጣ አሳየዋለሁ!"

"እቤት ውስጥ ገብቷል:: አልጋ ስር ወይም ጓዳ ይዩት እስኪ?!"

እማዬ ልትፈልገኝ ጓዳ ገባች።

ተዝናናሁ። መኩዬ "እማማ ባሎቴ የት እንዳስ ላሳዮት!" ስትል ተደናገጥኩ። እኔ የተደበቅኩት ከበሩ ኋላ ነበር። በበሩ ሰር እግሬ ብቅ ብሎ እንደሚታይ የገባኝ ወዲያው ነው። እግሬን ከመሰብሰቤ በፊት ግን መኩዬ በበረባሶ ጫማዋ የበላች የጠጣችውን ያህል በርግጫ ደቀደቀችኝ።

"ወይኔ ቁስሌን! ወጄኔ ቁሰሌን!" እያልኩ ከበሩ ጀርባ ወጥቼ ዘልዬ ሳሎን ወለሉ ላይ ተዘረርኩኝ። እማዬ ከጓዳ ሰት መለስ እየተንፈራፈርኩኝ ነበር።መኩዬ አንጀቷ ቅቤ ጠጥቶ፣ በግማሽ ሳቅ በግማሽ ልቅሶ ግዳይዋን ቁልቁል ተዘርሬ እየችኝ።

"ምን አገኘህ?!" አለች እማዬ ተደናግጣ።

"እግሬን... መኩዬ! በበረባሶ ጫማዋ...!" ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ አለ።

"ደግ አደረገ! እንኳን ዋጋህን የሰጠልኝ! መጀመሪያስ ለምን መታኸው?! ወንድ ነው። ብድሩን መለሰ።"

"ገና አለቅህም። ታየኛለህ!" ብላ ቀጫጫዋ ዛተች።

"ሂድ! አንተ ደግሞ ፈሳም! እኔ እየተቆጣሁት ትዝታለህ? በሉ ታረቁ!" ስትላት መኩዬ ፈትለክ ብላ ከቤታችን ወጣች።

እኔም በርግጫ የተገሸለጠ ቁስሌን ማስታመም ጀመርኩ።

"በል አርፈህ ተቀመጥ!" ብላኝ እማዬ ወደዕለት ሥራዋ ሄደች።

የመኩዬን ቂመኛ መሆን አሳምሬ ስለማውቀው ከቤቴ ላለ መውጣት ወሰንኩ። እንደመታደል፣ የዚያን ዕለት ቤተሰቦቼ ምንም አይነት መልእክት ስላላኩኝ አሸናፊ ሆኜ ዋልኩ።

የሰፈር ልጆችን አባብለው እንዲያሰወጡኝ መኩዬ ላከች ብኝ። "ሞኛችሁን ፈልጉ!" አልኳቸው። ቀጫጫዋ ግን የዋዛ አይ ደለችም። የድፍረቷ ድፍረት፣ አባቴ ቤት ውሰጥ ቁጭ ብሎ ሽማ እየሠራ እያለ በራችን ድረስ እየመጣች ትዝትብኛለች።

"ዜራሞ" ብዬ ሰጮኽ።

ፈትለክ ብላ በብርሃን ፍጥነት ከአካባቢው ትሰወራለች። ብዙም ሳትቆይ በመሰኮት ብቅ ብላ ትታየኛለች። አባቴ ግር አለው "ምን ሆነሃል?"

"ምንም!"

"በል ድውር ስለሚያስፈልገኝ አንድ ቁላ ማግ ቶሎ አዳ ውርልኝ።"

በደስታ ትእዛዙን ተቀብዬ ማዳወሬን ጀመርኩ። ውብ የሆነው ቅዳሜ በዚሁ አይነት ሁኔታ ለሽንትም ሳልወጣ አለ ፈልኝ።

እሁድ ወላጆቼ ከቤት ወጥተው ዕቁብም የመጠጣት፣ እድርም የመክፈል ተግባራቸውን የሚያከናውኑበት ዕለት ነው። ብቻ ዬን ስለምውል ደፈጣው መራር ይሆናል። የገመትኩት አል

ቀረም። ለማኝ ሳያራ በራችን ሲከፈት መኩዬ ደጃችን ላይ እየ ተንቆራጠጠች ነበር። እሁድ ጠዋትም ደፈጣው ቀጠለ። በሲሳይ ጎቢጥ አማካኝነት ለመደራደር ሞከርኩ። ቀጫጫዋ ሃሳቡን ውድቅ አደረገችው።

ካምቦሎጆ አሪፍ ጨዋታ ይካሄዳል። እኔና መኩዬ ብን ግባባ ኖሮ መኪና ከሚጠብቁ ጓደኞቻችን ጋር ተግባብተን ከሠራን ጥቂት የማይባል ሽቀላ እናከናውን ነበር። ተመልካቾች ለመቀ መጫነት የሚገለገሉበትን ጋዜጣ፣ እንደዋዛ ጣል የሚያደርጉትን የለሰላሳ ጠርሙስ መንትፈን ከሸቃቀልን በሚቀጥለው ቀን ኮርተን ሲኒማ የምንገባበት ገንዘብ ይኖረን ነበር። አሁን ግን በመጣላ ታችን ቡተለይ እኔ ቀረብኝ።

እኔም ሆንኩኝ አብሮ አደጎቼ በይፋ አንናገረው እንጂ ሁላችንም መኩዬ ቀጫጫዋን እንፈራታለን። የሷን ቂምና እልህ ማናችንም ችለን አንጋፈጠውም።

አንድ ቀን ከአብዲ ጋር ተጣላች። አብዲ ከባላገር የመጣ ልጅ ነበር። በሰላም ስንጨዋወት አብዲ «አስተማሪያችን ድርሰት ጻፉ ብለውን 'ጨውና ጥቅሙ' በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ጽፌ ለክፍል ጓደኞቼ አንብቤላቸው በጣም ተደነቀልኝ» ሲል አወራን።

ይሼኔ ይህች ሰላቢ ቀጫጫ ከትክት ብላ ስቃ "ጨውና ጢቅሙ!..." ብላ በአማርኛው አላገጠችበት። አብዲ እንደ ቮሊ ቮል ኳስ ቁልቁል ደብን አደረጋት። ጭቃው ላይ በአናቷ ተወተፈች። ስትነሳ ፈቷ ከጭቃው ገምሟል። በጣም ሳቅን። 'አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ!' ብሎ ይጥና አላገጠባት።

አቤት ዓይንዋ ያረገዘው ቂም! አላለቀሰችም። አልጮኸ ችም። ዝም ብላ እማማ ሸጊቱ ቤት ሄዳ ፊቷን ታጠበች። ስት መለስ አብዲ ረሰቷት ጭቃ ብይ ከኃይሉ ዶሮ ጋር እየተጫወተ ነበር። መኩዬ በነዚያ ወፍ እግሮቿ በራ መጥታ ቷ! አድርጋው በዚያው ፍጥነት ሮጣ ተሰወረች። አብዲ "ቆይ አገኝሻለሁ!" ብሎ ዛተ። በተጠበቀችበት ሳይሆን ባልታሰበው በጨነቀው ሱቅ በኩል መጥታ አደፈጠች። ኃይሉ ዶሮ እይቷታል። ሊያግዛት ስለፈለገ አብዲን በወሬ ወጥሮ ያዘው። አብዲ ጨዋታውን ሲከታተል ቱር ብላ መጥታ በጥፊ "ጭው!" አደረገችው። አብዲ ክው አለ። ከዘ ትሩ ይልቅ ድንጋጤው ጎድቶታል። በዚያው ስሜት የዕውር ድንብሩን ሊከተላት ሞከረ። ወፍን እንደወፍ ካልበረሩ እንዴት መያዝ ይቻ ላል? የእልህ ሳግ ተናነቀው።

ኃይሉ ዶሮ ወደ ጨዋታው እንዲመለስ አብዲን አረጋ ጋው። በልብስ ቁልፍ አሰይዘው ነው የሚጫወቱት። ትኩረቱን በሙሉ ይህች ሰላቢ ስላበላሸችበት ብዙ ቁልፍ ተበላ። ኃይሉ መበላቱን ተወት አርጎለት ሙሉ ትኩረቱን ጨዋታው ሲስበውና የቀጫጫዋ ድንገተኛ ብትር ሊወርድበት እንደ ሆነ። በዚህ ጊዜ አብዲ በጣም ተናዶ ማልቀስ ጀመረ። እኛን እንድናስታርቀው

ጠየቀን:: መኩዬ ተስማማች:: ምክንያቱም ተበቅላዋለች፣ በቅቷ ታል:: እኔን ግን እምቢ ስላለችኝ ቤቴን ምሽግ አደረኩ::

"ፋንጌ፣ ካምቦሎጆ ከእኛ ጋር አትሄድም?" አለኝ ኃይሉ ዶሮ ወደ ቤታችን ብቅ ብሎ::

"አልሄድም!" አልኩት:: "ቻው! ለነገ ሙቪና ለርግቦ ቻችን ቀለብ መግዣ ልሸቅል*ደይሜአለሁ!" አለኝ::

ወደ ካምቦሎጆ ሲሔዱ እየቋመጥኩ አያቸዋለሁ:: ዶሮ፣ መኩዬ ቀጫጫው፣ ሴምላል፣ ቀጠሳው፣... አበራ ወፍጮ ቤት አካባቢ ደርሰው ወደ ወርቁ ሻይ ቤት ታጠፉ:: በቂርቆስ ጓሮ አድርገው፣ በአራተኛ ከፍለ ጦር በኩል ሽቅብ ወጥተው፣ በመሺ ለኪያ ሄደው ካምቦሎጆ ይደርሳሉ:: ይኼኔ መኩዬ ተመልሳ መጥታ አበራ ወፍጮ ቤት መታጠፊያ ቆርቆሮው አጥር ላይ ተለ ጥፋ ይሆናል ብዬ ገመትኩና አፈጠጥኩኝ:: እንደገመትኩት ብቅ ብላ ታየችኝ:: ተመልሼ ወደ ቤት ገባሁ:: ዙተችብኝና ሄደች::

ባሪቾ ወደ ሰፈር ሲመለስ አየሁትና "ልጆቹስ?!" ስል ጠየኩት::

"ሄደዋል!"

እርግጠኛ ለመሆን መንገድ ላይ ወጣሁ:: መኩዬ ቀጫ ጫው ብቅ አላለችም:: በፍጥነት መንገድ ቀይሬ በጨነቀው ሰቅ አድርጌ ገበያውን አቋረጥኩና የባቡር ጣቢያውን ድልድይ ተሻግሬ ካምቦሎጆ ደረስኩ:: እዚህ አካባቢ ከተገናኘን መኩዬ እንደ ማለታት ታውቃለች:: ለማንኛውም ሰወር ያለና ማንም የሰፈር ልጅ የማይጠረጥረውን ቦታ መረጥኩ:: ዲናሬ አለኝ፣ ረፈድ ሲል እንዳይርበኝ የዱንቡሎ ሽምብር በጨው እበላለሁ:: ውሃ ሲጠማኝ የድንቡሎ ሽንኮራ ገዝቼ እመጥና ሽቀላዬን አከናውናለሁ::

በዚያ ዕድሜ አንድ ልጅ ብቻውን ያለሰፈሩ ከታየ በርከት ብለው የሚሄዱ ልጆች አስቁመው "ባብር!" ይሉታል:: የፊሯ ያለውን ሰጥቶ በካልቾም በጥፊም ከመመታት ይድናል:: የደፈረ ተጋትሮ ራሱን ይከላከላል::

ካምቦሎጆን የፍልውሃ ልጆች እንደግል ንብረታቸው ነው የሚያዩት:: ከቂርቆስ፣ ከሠንጋ ተራ፣ ከቄራ፣ ከለገሃር ሰፈሮች የምንመጣ ልጆችን በተናጠል ካገኙን አስፈራርተው ለማስገበር ይሞ ክራሉ:: አሁንም እኔ አጭሬ፣ ኮርማ፣ ሐሙራቢና እንጥል ብቻ ዬን ስላገኙኝ "ባብር!" አሉኝ::

"ወንድ ከሆናችሁ አንድ በአንድ ኑልኝ!" አልኳቸው፡ ደረ ቴን ነፍቼ::

"እንዴ! ወይኔ ብንሞት ይሻላል! እንዴት የቂርቆስ ልጅ የፍልውሃን ልጅ ይደፍራል!" ፎኸ አጭሬ:: ሽሮ የመሰለ ጥርሱን

*ደይሜአለሁ፡ ሔጃለሁ::

ነክሶ ለቡጢ ተዘጋጀ:: ሐሙራቢ አንድ ስንጥር አነሳና እቧራ ማው ሜዳ ላይ እያሰመረ "በሥነ ሥርዓቱ ተደባደቡ!" አለን:: እነ አጭሬ ቦቅቧቃ ስለሆኑ አንድ ላይ የማርያም ጠላት ሊያደርጉኝ ከበቡኝ::

ሐሙራቢ "*ቡካታሞች! ልከ አይደላችሁም! አንድ በአንድ ተደባደቡ::"

"ተዋቸው ይዋጣልን!" አልኩ::

የሌላ ልጅ ትከሻ ትከሻዬን ሲነካ ተሰማኝ:: ዞር ስል መኩዬ ቀጫጫዋ ነች:: ወደ ኮርማ ቦክስ ጨብጣ አፍጣ ታየ ዋለች:: እኔም አጭሬ ላይ አፈጠጥኩ::

በአየናቸው ብዙ ፊልሞች የአከተሩ ጓደኛ የፊለገውን ያህል ቢጣሉም ጓደኛው በጠላቶች ከተከበበ ያግዝለታል:: መኩዬም አሁን እንደዚያ ነው የደረሰችልኝ:: ቦክሱ ተጀመረ:: ባልታሰበ አጋጣሚ እነ ቦቾራና ዶጅ ገማጣው ስለመጡ የቂርቆስ ልጆች ተጨማሪ ኃይል ኖረን::

በዚህ ጊዜ የፍልውሃ ልጆች "ቆይ! ነገ የማናገኛችሁ አይም ሰላችሁ! እያንዳንድሽን አንድ በአንድ እናገኝሻለን!" እያሉ ሮጠው ሔዱ::

እኔና መኩዬም የዱምቡሎ ሽንብር በጨው፣ የዱምቡሎ ሽንኮራ ገዝሁና ከሁለቱም ግማሽ ግማሹን ተካፍለን በልተን ያለ ምንም ቃል ልውወጥ በመካከላችን ዕርቀ ሰላም እንዲወርድ አደረግን:: ብልጠት ካልታከለበት ጀግንነቱም በዚህ አጋጣሚ ተማርኩ::

*ቡካታሞች፡ ፈሪዎች::

ካምቦሎጆ የማይገቡ ተመልካቾች

"ብረር፣ ካልቾልክ ሩጥ፣
ከደከመህ ቀሰ እያልክ ተራመድ፣
ኩተሳህ ዳሆ"
ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስታዲየም የዓለም እቀፍም ሆነ የአገር ውስጥ ጨዋታዎች ሲካሄዱ የሰፈራችን ልጆች ከዚህ አካ ባቢ አንጠፉም:: ብዙዎቻችን ሞልቶልን አንድ ብር ከፍለን መግ

ባት አንችልም። ካምቦሎጆ አካባቢ እየተዘዋወርን ጨዋታውን እንከታተላለን።

ብዙ ጊዜ ሬዲዮ ያላቸው ሰዎች ወደ ካምቦሎጆ ይመጣሉ። መስኩ ላይ ተቀምጠው ሲያዳምጡ እኛ ዙሪያቸውን ከብበን እንሰማለን።

"ተመልካቾቻችን፣ ከዚህ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስታዲያም ጊዜያዊ ስቱዲዮአችን ጨዋታውን ማስተላለፍ እንጀምራለን። የኢትዮጵያ ቡድን አሰላለፍ፣ አንድ ጌታቸው ዱላ..." እያለ ጋዜጠኛው ሰለሞን ተስማ ተጫዋቾቹን ማስተዋወቅ ይጀምራል። በደስታ ፍንድቅ እያልን እናደምጣለን።

"የኢጣሊያ ቡድን አሰላለፍ..." ብሎ ተጫዋቾቹን አስተዋውቆ ከጨረሰ በኋላ ሁላችንንም ቀስፎ የሚይዝ ዜና በተለይ ለልጆቹ አበሰረን።

"እንደምታውቁት በቅርቡ ፔሌ የሚጫወትበት የሳንቶስ ቡድን ወደ አገራችን እንዲመጣ ጥረቱ ተጀምሮ ለተጨዋቾቹ ማስተናገጃ 70ሺ ብር ተወይቀናል። በዚህ ጉዳይ ቢጋዜጣና በሬዲዮ ስፖርቱን በማይደግፉና የስፖርቱ አፍቃሪ ሕዝብ ከፍተኛ ሙግት ውስጥ ገብተናል። የሳንቶስ ቡድን ቢመጣና ከአገራችን ተጫዋቾች ጋር ቢጋጠም ጠቀሜታው ጉልዘ እንደሆነ የሚሞግቱ ወገኖች አሉ። ይሀንኑ ጉዳይ አስመልክተው አቶ ይድነቃቸው ተሰማ የሚሉትን መግለጫ ምሽት ላይ እናስተላልፋለን። የእናንተን ስሜት ለማርካት የእግር ኳስ አድነት ወሳኝ ነውና ድጋፋችሁ አይለየን።"

ሕዝቡ በታላቅ ደስታውና በጭብጨባ፣ በፉጨትና በመጮኽ ድጋፉን ገለጸ። እኛም በደስታ ሣሩ ላይ ተንከባለልን። ትንሽ ቆይቶ ግን ሃሳብ ገባን። የመግቢያ ዋጋው የዚያን ዕለት አስተኛው አምስት ብር ይሆን ይሆናል። ይህን ያህል ገንዘብ አይደለም በእውን በህልማችንም አይመጣም። ተረፈ ገልጆ ጠቀስኝ። ተጠጋሁት "ፉንጋይ አይዘህ፣ እኔ ካምቦሎጆ ውስጥ የምነባበት አንድ መንገድ አለኝ። ለማንም እንዳትናገር። ቀኑ ሲደርስ አሳይሃለሁ አብረንም እንገባለን።"

"በናትህ! ለማንም አልናገርም፣ ለምን አሁን አታሳየኝም?"

"አሁንማ አልነግርህም። ግን እመነኝ እንገባለን። እኔ በማስበው መንገድ ከገባን ፔሌ የሊጋችን ኳስ እየቀለብን መልስን የምናቀብለው እኛ እንሆናለን።"

ገልጆ በጣም ብልጥ ልጅ ስለሆነ አመንኩት፣ ከሽምብራዬ አካፈልኩት።

አብዛኛውን ጊዜ ሸንኮራ ነጋዴ፣ ወይም ሽምብር በጨው ሻጭ አካባቢ እንገኛለን። የሸንኮራ ነጋዴው ጫፉን ቆርጦ ራቅ አድርጎ ሲወረውር ለመቅለብ እንሻማለን። ከሽምብራ ነጋዴው እጅ አንዲት ፍሬ ጠብ ብትልም ሽሚያው ያው ነው።

ካምቦሎጆ ውስጥ የሚሰሙ ጨኽቶች የድል፣ የቁጭት፣ የአድናቆት መሆናቸውን ውጪ ሆነን እናውቃለን። ያልተለመደ አይነት ድምፅ ሲሆንብን "ምንድነው!" ብለን ካምቦሎጆ ውስጥ የመግባት ዕድል የገጠማቸውን ልጆች አንጋጠን እያየን እንጠይቃለን።

"ዋ! አዋድ መሐመድ ለመንጌ የለጋለትን፣ መንጌ አክሮ መትቷት የኢጣሊያ አምስት ቁጥር ተደርቦ መልሶ በአርግጫ መንጌን ሊመታው ነበር" ሲለን፣

"ወይኔ መንጌ!" ብለን ሣሩ ላይ እንንከባለላለን።

በአንድ ወቅት የጋና ቡድን ወደ አገራችን መጥቶ እንደነገ ለመጫወት ዛሬ ሲለማመዱ የካምቦሎጆ በር ክፍት ስለነበር ገብተን አየናቸው። አያንዳንዳቸው አንድ አንድ ኳስ ይዘው ነው የሚለማመዱት። ይህ ትርዒት ማርኮን በማቀጥለው ቀን ከአባቶቻችን አንድ አንድ እግር ካልሲ ሠርቀን የራሳችንን የጨርቅ ኳስ ሰፋን። የአንዳንዶቻችን አባቶች ከዚያች ሌላ ካልሲ ስለሌላቸው አልጋ ላይ ሊውሉ ሆነ። ባባቶቻችን ካልሲ ኳስ የሠራነው ልጆች ተሰብስበን ተገረፍንና ኳሶቻችንን አስቀድደውን ካልሲዎቻቸውን መለስን።

... ጨዋታው ሊጠናቀቅ 15 ደቂቃ ሲቀረው የካምቦሎጆ በሮች በሙሉ ይከፈታሉ። መግቢያ በር ላይ ከፍተኛ ግፊያ ይፈጠራል። የተናደደውና የተደሰተው ተመልካች፣ ለመውጣት ተጣድፎዋል። ውጪ ሰዓቱ ደርሶ በር ሲከፈት ያችን የቀረችውን የሩብ ሰዓት ጨዋታ ገብቶ ለማየት የሚጠብቀው ችስታ ተመልካች ግፊያውን አጨናንቆት ፖሊስ በቆመጥ እየቃኘ በሩን ለማስከፈት ይሞክራል። አንዱ ሕፃን ተረግጦ ሲያለቅስ ይሰማል። በብዙ መከራና ስቃይ ወደ ውስጥ እንገባለን። ከጀርባችን በጣም ስለምንገፋ ከፊታችን ያለውን ወንፊት የሸቦ አጥር አጣብቆን ጭንቁንም ግፊያውንም ረስተን ተጨዋቾቹን እያስተዋልን ማንነታቸውን እናጣራለን። (ኳሷ ገና አልተሊጋችም)

"ያ! ማነው?"

"አዋድ መሐመድ።"

"አምስቱ?"

"አዎን።"

"ስምንቱ መንግሥቱ ወርቁ ነው?"

"አውቀኸዋል።"

"አለማየሁ ፊኛ የታል?"

"ቆይ አሳይሃለሁ።"

"አሥራ አንዱ የኢምባይሰራው የማነ አይደል?"

"አዎ"

"ፓቼ የታል?"

"ያውልህ ዘጠኝ ቁጥሩ::"
"ስድስቱ ማነው?"
"ተስፋዬ ወዲ ቀጭኔ"
"ሰባቱስ?
"መሐመድ ዓብደላ"

ተጨዋቾቹን አይቷን ሳንጠግባቸው ጌታቸው ዱላ ሊጋ:: እሱ የሰጋትን መንግሥቱ ወርቁ በደረቱ ተቀብሎ ለጀሚል ሰጠው:: አሰር ቁጥሩ ጀሜል አክሮ መታ:: የጣልያኑ በረኛ ጎረ ሳት:: ጨዋታው ለጥቂት ደቂቃ ተካሔደ:: የመሃል ዳኛው ፊሽካ ሲነፋ ጨዋታው ሁለት ለሁለት ተፈጸመ::

ደግሞ ሌላ ቀን በሌላ ጨዋታ እነዚያው ቡድኖች፣ ወይም ሌሎች ይገናኛሉ:: እኛም በዚያን ዕለት እዚያው ካምቦሎጆ እንገኛለን::

እኔ፣ ዶሮ፣ መኩዬ ቀጫጫው ሲኒማ መግቢያ ግንዘብ ለማግኘት አዲስ ሥራ ፈጥረናል:: በዚህ ጊዜ በጥድፊያ የምንዋ ከብበት ሰዓት ነው:: ጨዋታው እየተጠናቀቀ ሲመጣ ሕዝቡ ቆሞ የማየት ልምድ አለው:: ተቀምጠውበት የነበረውን ጋዜጣ በፍ ጥነት ከአንድ ጥግ ወደ ሌላው እያለፍን እንሰበሰባለን:: በዚያ መካከል የለስላሳ ጠርሙስ ካገኘን አንምረውም:: በጥድፊያው ወቅት ከተመልካች ጋር መጋጨት ይኖራል:: ተመልካቾች ሙሉ በሙሉ ትኩረታቸው ጨዋታው ላይ ስለሚሆን ሲጎሸሙ ዞር ብለው በኩርኩም ለኩፍ ያደርጉናል:: አንዳንዴም ይይዙንና "ምን ድነው ይሄ ያረገዝከው?" ይላል፣ በጋዜጣ የታጨቀ ሹራባችንን እያየ::

እኛ ከመመለሳችን በፊት አንደኛው "ተዋቸው የፓስቴ መብያቸውን እየሸቃቀሉ ነው!::" ይለዋል....

አንዳንዴ ከጓደኞቼ ጋር ውጥረት የበዛበት ጨዋታ ሲካሄድ እንጠፋፋለን:: ትዝ እንደሚለኝ የለገሃር ልጆች በዚህ እዲስ ሥራችን ላይ ብዙውን ጊዜ ትልቅ ባላንጣዎቻችን ነበሩ:: አንድ ቀን ብቻዬን ሹራቤ በጋዜጣ ተወጥሮ ወደ ሰፈር የምመለስበት ሁኔታ ተፈጠረ:: ዝናብ መጥቷል:: የግድ ጋዜጣዬ እንዳይበሰብስ በጊዜ ጉዞ ጀመርኩኝ:: የለገሃርን ድልድይ ተሻገርኩ:: ሜዳውን ማቋረጥ ስጀምር ሦስት የማውቃቸው የለገሃር ልጆች ጨዋታቸውን ትተው ተለያዩ:: መሀላቸው አስገቡኝ:: ሊያንቁኝ ቀኝ ጓላ ዞረው ወደ እኔ በፍጥነት ተወረወሩ:: ኦ! ኦ! ኦ! ብዬ እየጮህኩ ከፊቴ የመ ጣውን ኃይሉ ቁሬን በጥፊ 'በቁ' አደረኩት:: በርግጎ ዞር አለ:: ከጓላ በኃይል እያሳደዱኝ ሮጡ በደዊ ሻይ ቤት ዘው አልኩኝ:: ያባርሩኝ የነበሩት ታርዬ፣ ኃይሉ ቁሬና ስዩሜ ተከትለውኝ ሻይ ቤቱ ገቡ::

በደዊ "ምንድነው?" ሲል ጮኸባቸው፣ ጫቱን በጉንጩ ወጥሯል::

"...ሊነጥቁኝ ነው!" አልኩኝ ጋዜጠኞን ከሆዴ ጋር ጥብቅ አድርጌ ይዣ::

"ውጡ ከዚህ!!" በደዊ አላቸው:: ምንጊዜም የሚያዝው ለደንበኛው ነው::

"ቆይ እናገኝሃለን!" እያሉ ወጡ::

እኔ በፍጥነት ጋዜጣዎቹን የተቀዳደውንና ያልተቀዳደ ደውን ለብቻ ለብቻ ባንኪው ላይ ደረደርኩለት:: ሁለት የለስላሳ መጠጥ ጠርሙስ ጨመርኩ::

"አህ! ዛሬ ብዙ ሸቅለሃል! ሻይ እዘዝ" አለኝ በደዊ::

አራት ፓስቴ ከሻይ ጋር ቀረበልኝ::

ጋዜጣው ሽልንግ፣ ጠርሙሶቹ ሽልንግ በጠቅላላው አንድ ብር ሸቀልኩ:: ስሙኒ የተመገብኩበት ሲቆረጥ ሦስት ስሙኒ ደረ ሰኝ:: በቀበቶዬ መታጠቂያ ላይ ሰንጥቄ ባዘጋጀሁት ምስጢር ኪሴ ውስጥ ደበቅኩና ታጠኩ::

እንዴት እንደምወጣና የስዝርን ልጆች እንዴት እንደ ምሸውዳቸው ፓስቴዎቹን ከሻይ ጋር እያጣጣምኩ ማሰብ ጀመርኩ:: ቁጭ ብዬ ስቆዝም ዝናብ መዝነብ ጀመረ:: በጣም ደስ አለኝ:: እየሳሰ ሲሄድ በዶፉ ውስጥ ለማምለጥ እንደሚመቸኝ እርግጠኛ ነኝ::

ወዲያው በሩ አካባቢ ኃይለኛ የጓጓታ ድምፅ ተሰማ:: ቀና ስል መኩዬ ቀጫጫው ወሯ የገባ እርጥዝ መስላ ከተፍ አለች:: ኃይሉ ዶሮ ከኋላዋ ሲገባ በዝናብ የራሰው ሱጫ ፀጉሩ አናቱ ላይ ተለጥፎ፣ ዘርዛራ ጥርሱን ብልጭ እያደረገ ገባ:: ደስ አለኝ:: ባንኮኒው ላይ ጋዜጣውን ማደራጀት ጀመሩ:: ዘና አልኩና ድጋሚ አንድ ሻይ አዘዝኩ::

ዝናቡ መውረድ ጀምሯል:: አንገቴን መዘዝ አድርጌ በበሩ ስመለከት ኃይሉ ቁሬ ታዛው ስር ተጠልሎ አየኝና በዛቻ ጣቱን ወዘወዘብኝ:: ሦስት ጣቴን ሸቅብ ቀስሬ አሳየሁት::

እነ ዶሮ ተገቢያይተው እንደጨረሱ ውጪ መከበባችንን ነገ ርኳቸው:: "እሪ! እናታቸውን! የለገሀር ልጅ ደግሞ የቂርቆስን ልጅ ይደፍራል?!" አለች መኩዬ ቀጫጫው ፓስቴዋን እየ ነጨች::

ዶሮም "ዓይናቸውን ነው እምናጠፋው! ቢፈልጉ አንድ በአንድ፣ አለበለዚያም አንድ ላይ ይምጡ፣ እናናፍጣቸዋለን" አለና ጮርናቁውን ነጨ::

እኔም 'ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ' እንዲሉት፣ ከእንዱ ጋር ብተናነቅ እንደማሸንፍ እርግጠኛ ሆንኩኝ:: ዝናቡ እየባሰ ሄደ:: ሰማዩ በመብረቅ እየታረሰ ነው:: በፀጥታ ነገ እምናየውን ፊልም እያብሰለሰልን ከራሳችን ጋር ስናወራ፣ ከምንወዳቸው አክተሮች ጋር በሃላብ ስናወጋ ለረጅም ጊዜ ዘንቦ አባራ::

ከሻይ ቤቱ ስንወጣ ጨልሟል። አድብተን ስናስተውል ማንም የለም። የለገሀርና የቂርቆስ መለያ መንደር የሆነውን ዲተል በር በደፈጣ አቋርጠን ሰፈራችን በሰላም ደረስን።

በሕይወት ውስጥ ከቻልን መሮጥ፣ ካልሆነ መራመድ፣ ከመ ረረም መዳህን የተማርነው እንዲህ ነበር።

ዘለዓለማዊነት

"የከበረ ሰው ሣዕመ መዓዛ
እስከ ዓለም ዳርቻ ይደርሳል"
ገድለ ክርስቶስ ሰምራ

የአሸናፊ ፔሌ አባት አባባ ሐኑስ ታመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የታላቁ ታላቅ የሆነችው እህቱ አበበች ከመምህራን ተቋም ተመርቃ ቤተሰቡን የማስተዳደር ኃላፊነት ተረከበች። የተመደበች በት ትምህርት ቤት ከሰፈራችን በጣም ስለሚርቅ ቤት መቀየራ ቸው የግድ ሆነ። በዚህ ምክንያት አብሮ አደግ ጓደኞችን ፔሌ ከቂርቆስ ወደ ፈረንሣይ ሊጋሲዮን መሄድ በሁላችንም ላይ ብርቱ ሐዘን አሳደረ።ቀጢሳው ቆዝሞ "በቃ ፔሌ ከሄደች ቡድናችን መፍረሱ ነው?"

ፔሌ ሰምታው "እኔ ሁሌ ቅዳሜ ቅዳሜ እየመጣሁ እጫወ ታለሁ። ለምን ይፈርሳል!?"

"እንቺ እኮ የሌላ ሰፈር ተጫዋች ልትሆኚ ነው" አለ ዶሮ እየተቆጨ።

"ለምንድነው የሌላ ሰፈር ተጫዋች የምሆነው? እስከምሞት የሠፈሬ የቂርቆስ ተጨዋች መሆን ነው የምፈልገው!" አለች ፔሌ ከምር።

እንዲህ ስንጨቃጨቅ የሰሙን እማማ አመለወርቅ "እስኪ መለያየት ምን ምን እንደምትል ቅመሺት! ለማንኛውም አሸናፊ ዒርብ ማታ እየመጣ እኔ ቤት አድሮ ከእናንተ ጋር ሲጫወት ውሎ እሁድ ማታ ይሄዳል። አሁን ይኼ ብልሃት ጭንቀታችሁን አያቃልልላችሁም?!"

ተደሰትን። እኛም እምንችለውን እየተሸከምን ዕቃቸው መኪና ላይ ተጫነ። የመጨረሻዋን ዕስት አብረን ስናወራ አም ሽተን ከነከበደ ጋር እማማ አመለወርቅ ቤት አደረች።

ፔሌ በሌለችበት ተሰብስበን አንዷን ኪስ ሰፈሯ ወስዳ እን ድትለማመድባት ሰጠናት። "ለኔ ለብቻዬ እምለማመድበት ነው የምትሰጠኝ?" አለች እየተደሰተችና በፍቅራችን እየረካች።

"እውን፣ አንቺ አምበላችን ስለሆንሽ በጣም አሪፍ መሆን ይኖርብሻል። አሁን እምትሄጂበት ሰፈር ለብቻሽ ኪስ ያስፈል ግሻል" አልኳት።

"እሺ" አለችና ኪሱን ተቀብላ እሩቅ እሩቅ ማየት ጀመ ረች። ዓይኖቿ እንባ አቀረሩ። ፀጥታ በመካከላችን ነገሠ። ሳትሰ ናበተን ወደ አዲሱ ሰፈሯ ማዝገም ጀመረች። እኛም እንሸኘሽ ሳንላት ተከተልናት። ሲሳይ ነቢጥ ተክዞ አንዲት ጠጠር እየለጋ ይራመዳል። ኃይሉ ዶሮ የሸቦ መኪናውን ተሸክሞ ያዘግማል።

እስጢፋኖስ አካባቢ ስንደርስ ፔሌ ቆመችና "በሉ ተመ ለሱ። ከዚህ በኋላ ሳይመሽብኝ ቶሎ አዲሱ ሠፈሬ ለመድረስ መሮጥ አለብኝ። ቅዳሜ ጠዋት ከተወርዋሪ ኮከብ ጋር አይደለም ያለን ግጥሚያ?"

"ከክተት ባየር ጋር ነው" አለ ውሮ።

"ነው እንዴ? ከክተት ባየር ጋር?! እኔ ደግሞ ከተወርዋሪ ኮከብ ጋር የምንጋጠም መሰሎኝ ነበር ለማንኛውም ዒርብ ማታ መጥቼ ሰፈራችን አድራለሁ። እናንተም በጠዋት ነቅታችሁ ማሊያውን አውጥታችሁ ተዘጋጁ።"

"ማሊያውን እኮ እንድናጥበው ወስደነዋል" አልኳት።

"እንዴ! ዶሮ፣ ሰብስብና አንተጋ ይቀመጥ አላልኩህም ነበር?" አለች ፔሌ ትንሽ ቆጣ ብላ፣ ሌላ ጊዜ ቢሆን አንዴ በካ ልቾ ዝቃው ነበር እምትጠይቀው።

"እኔ ምን ላርግ? ይኼ ቀጢሳው፣ ነቢጥ፣ ሻቃ እላጠላብንም ሲሉኝ ተውኩት።"

"ውሸቱን ነው" አለ ቀጢሳው።

"በቃ አሁን አዳምጡኝ። ያላጠባችሁ አሁኑኑ ቤታችሁ እንደገባችሁ እጠቡ። ነገ በጠቅላላው ተሰብስቦ እነ ኃይሉ ዶሮ ቤት እንዲገባ። የእኔንም አስር ቁጥር ማሊያ ሰጥቼዋለሁ። ልጆች! በእናታችሁ እንዳትረሱ" ይህች ስትቆጣ አራስ ነብር አምትሆን ኃይለኛ ፍጥረት ዛሬ እላይዋ ላይ ፍቅር ነግሶ በልም ምጥ ተናገረች።

"በሉ ደህና እደሩ!" አለችና ኪስዋን አቅፋ በሶምሶማ ሩጫ የኢዮቤልዩን ቤተመንግሥት ዳገት ተያያዘችው። እኛ ፊታችንን ወደ ሰፈራችን መለስን። በዚህ መሃል ውሮ ወደ ፔሌ ዞረና "አሹዬ!"

መሮጧን አቁማ "ወይ!" ኪሳን እንዳቀፈች ጆሮዋን ቀሰ ረች። እኛም ውሮ ለምን እንደጠራት ለማወቅ ዞርንና ቆምን።

"የፈረንሣይ ሊጋሲዮን ልጆች ከደፈሩሽ ንገረን። ሄደን እንረግጥልሻለን። እናናፍጣቸዋለን!" አለ በልቅሶ ዜማ።

"እሺ!" አለች ስልል ባለ ድምፅ።

ውሮ ድምፅ አውጥቶ ማልቀስ ጀመረ። እኛ ግን እምና ስቅሰው በልባችን ውስጥ ነበር። ማንም ማንንም ሳያፅናና ወደ ሰፈራችን በካምቦሎጆ በኩል በፀጥታ መመለስ ጀመርን።

ከገደል ግቡ ጠጅ ቤት የሰፈራችን ሰው ግርማ ቢጬ እየዘፈነ ይወጣል። ተንኮለኛው ይጥና "ቢጬ የዱጥለስ አባት!" ሲል ስከፈው። ሁላችንም ሳመሸሽ ነቃ አልን።

"ማነው? ቢጬ!" አለ በአካባቢው የሚማታብት ድንጋይ እያ ማተረ። ማዘር ኢንዲያ ፊልም ላይ ፒቹ የሚባል ገፀ-ባህሪ አለ። በዚያ ቅፅል ስም የሰፈራችንን ሰው መጥራት ጀመርን። ፒቹ ስትቆ ላመጥም ቢጬ ሆነች።

"እንተ ነሃ ቢጬው!" አለ ባሪቾ እየሸሸ።

ግርማ አሪፍ የአራዳ ልጅ ነው። ብዙ ዓይነት ቋንቋዎችን መናገር ይችላል። ሥራው ፈረንጆችን አገራችንን ማስጐብኘት ነው። ጎይለኛ የጠጅ ሱስ አለበት። ማታ ጠጁን ጥግብ ብሎ እያቅራራ የሕንድ፣ የእንግሊዘኛና የአማርኛ ዘፈኖችን ጮክ ብሎ እየዘፈነ ወደ ሰፈር ይመጣል። እቤቱ ሊደርስ የመቶ ሜትር ርቀት ያህል ሲቀረው እናቱን "ማ" እያለ በሕንድ ስልት ይጣራል። እናቱ እየረገሙት በር ይከፍቱለታል።

ግርማ ቢጬ አንድ ድንጋይ አንስቶ "You son of a bitch!" አለና ያሳድደን ጀመር። ቀደም ብሎ በመለየት ቆዝማ ትጨነቅ የነበረች ነፍሳችን ከሥጋችን ተዋህዳ ራሳችንን ለመከላከል እግሬ አውጪኝ አልን።

ያነሳውን ድንጋይ እንዳይወረውር አንዳችን ስንከለል፣ ሌላው የቆመ መኪና ጋሻ ያደርግበታል። ደክሞት የጠጁ አንቡላ ፈልቶ ቁጭ ካለ፣ ከመካከላችን አንዱ ጠጋ ብሎ "ግርማ ቢጬ!"

"እናንት ገፊዎች፣ አላችሁ እንዴ?!!" ብሎ በአዲስ ጉልበት ያባርረናል።

እያሳደደን እኛም እየሸሸን የመሺለኪያን ድልድይን አለፍን። አዚያው አካባቢ አንድ ሰካራም ሰሌን ኮፈያ አድርጎ እየተንገዳገደ ሽንቱን ይሸናል።

ግርማ ቢጬ እንዳየው "እ!? ማንን ስመሸወድ ነው ሰሌን ኮፍያ አድርገህ እምትንገዳገድ? You! son of a bitch! አገኘሁህ!" አለና ሰውዬው መልስ ሳይሰጠው አንዴ ማጅራቱን አሰው። ሰውዬው ሽንቱ ላይ ተዘረረ።

"በናካውት! አንድ ጥለናል እሺ? ለካፊዎች!" አለ ወደእኛ ዞሮ። "እ! እ! ገደለው! ገደለው!" እያላገጠበት ይጥና ጮኸ።

"ጮክ እንዴ?" አለና ግርማ ድንጋዩን ወረወረ። በየስር ቻው አድፍጠን ውርወራውን አሳለፍን። በሁለት እጆቹ ጉልበቱን ተመርኩዞ ቀና ብሎ ያየናል። ቁና ቁና እየተነፈሰ ነው።

"ምነው ግርምሽ?" አለ ይጥና ደፈርም ፈራም እያለ ተጠ ጋው።

"እረ እናንተ ውሪዎች ተውኝ። አሁን እናንተ እምሽክ ብትሉ ኢትዮጵያ ምን ታጣለች? የእናንተም ሥጋ ሥጋ ሆኖ ምድራቱን ኮሶ ይታያት ይሆናል እኮ?"

በሳቅ አውካካን።

ግርምሽ ይጥናን በእጅ ጥቅሻ ጠራው። ተጠጋው። ተደግ ፍት በኃይል እየሳለ ቆየ። ቆመን እናስተውለዋለን። በተረብም በአሽሙርም ልክ ልካችንን እየነገረን ወደ ሰፈራችን እንደምንሄድ ሁላችንም ገብቶናል።

"እውነት እውነት እላችኋለሁ ማንኛችንም ብንሞት ኢትዮጵያ ምንም አታጣም፣ ምን አልባት እኔ ያን ዲቃላዬን አባት አልባ አደርገው ይሆናል። ስመሆኑ እየኖርን ነው?" ጠየቀ። ይህን ሃሳብ ሁላችንም ልንመልስ ከምንችለው በላይ ነው። እንደፈለገ ቢያወራ፣ ገባንም አልገባንም ግርማን ማድመጥ እንወዳለን።

"እመኑኝ እየኖርን አይደለም። ሕይወታችን እንዲለወጥ ሁላችንም መጣር መጋር አለብን። አሁን ያላችሁት 'በሮንግ ቄይ' ላይ ነው" በረጅሙ ሳስ። አሰነጠሰውና "የኔ መድኃኒዓለም እውነቱን አናገረኝ!" አለ በእሮጊት ድምፅ።

በጣም ሳቅን።

"ተመልከቱ ወንድሞቼ" በራሱ ድምፅ ግርማ ሃሳቡን መሰንዘር ጀመረ "አምቡላና ሲጋራ እንዲህ ያደርጋል። ልብ ያለው ካነኘው ሁሉ ይማራል። እግዚአብሔር መሬት ወርዶ ለፍጥረታት አይሰ ብክም። ልባም ብቻ አውቀቱን 'አንደር ስታንድ' አድርጎ አካ ሄዱን ያስተካክላል።"

ግርማ ቢጬ ከምክሩ ይልቅ የብዙዎቻችንን ቀልብ የሚ ስበው ሰምተን የማናውቃቸው የእንግሊዘኛ ቃላት ነበሩ። ባና ውቃቸውም ስንሰማቸው ደስ ይለናል። ሲሳይ ጎቢጥ አንዲት ዱል ዱም አርሳስና የተጣጠፈች ወረቀት ከኪሱ አወጣና 'አንደርስ ታንድን' በአማርኛ ፊደል ጻፈ።

"ሮንግ ቄይ!" ነበር ከልጅነቴ ጀምሮ የሄድኩት። 'ጋድ!' የእጁን ሰጠኝ። እኔም ልክ እንደ እናንተው የሲኒማ ሱሰኛ ነበርኩ። ስሲኒማ ፍራንክ አልሞላልህ ሲለኝ ምን እንደማደርግ ታውቃላችሁ? መቼም እምላክ ይቅር ይበለኝ። በረባሶ ጫማዬ ላይ ሬንጅ እቀባለሁ። በእጄ ጫማዬን እይዝና ባዶ እግሬን አዘግማ ለሁ። አንድ በደንብ የሸቀለ ለማኝ አጠገብ ስደርስ በረባሶዬን አጠልቃለሁ። ጠጋ እልና ሚዳ ላይ የተሰጡትን ሣንቲሞች በእር ግጫ ስመታቸው ሬንጁ ውስጥ ጥልቅ ይላሉ። ለማኙ ባንኖ እስክ ሚፈጭኝ እኔ አንድ ሁለት ሶስቴ ሣንቲሞቹ በሬንጁ እንዲጣበቁ እረግጣቸዋለሁ። ከዚያ ፈትለክ እልና ከአካባቢው እሰወራለሁ። አትጠራጠሩ አንዴ ረግጬ ቼላ፣ ከርክ፣ ከዚያም በላይ እሸቅ ላለሁ። ከዚህ በኋላ ነው ለማኞች የሸቀሉት ፍራንክ ጠርቀም

ሲል መልቀም የጀመሩት። ይህ ድርጊቴን አሁን ሳስበው 'ሮንግ ዌይ' ነው።"

ሲሳይ ጎቢጥ 'ሮንግ ዌይ' ብሎ ጻፈ። ሰራሱ ያህል በአማርኛ የጻፈውን ቃል እንዳይረሳው 'ሮንግ ዌይ' ሲል ግርማ ሰማውና "የተሳሳተ መንገድ ማለት ነው።"

"አልገባንም" አለ ይቄና። ደግሮት፣ እኛም ከበነው፣ አብ ረን አያዘገምን ነው።

"ብዙው ሰው ኑሮ የሚገባው ከወደቀ በኋላ ነው። እኔን ተውኝ። አርፋችሁ ትምህርታችሁን ተማሩ። አረፍ ከሆናችሁ አሁን ነው መንገዳችሁን የማስተካከያ ጊዜው። ዕድሉ አላችሁ። እውነት እላችኋለሁ 'ዛት ኢዝ ኢን ዩር ሃንድ!' አለና ያደፈ መሐረቡን አውጥቶ አፉን አበሰና መልሶ ኪሱ እየከተተ "መመልከት ያለባችሁ ሌባውን ሻካርን አይደለም። ሼክስፒርን ነው። ቴክሱን ጆንዌይን ሳይሆን ልብ ካላችሁ አነሽታይንን ነው። ዓለም እዚህ የደረሰችው በጥቂት አስተዋዮች ነው። የአቡጀዲ ግርግር ምንም አርባና የለውም።"

ሃሳቡ ረቀቅና መጠቅ እያለ ሄደ። ከጠራቸው ሰዎች ሼክ ስፒርንና ስታሮቹን ብቻ አናውቃለን።

"ሼክስፒርን አወቅከው? የከበደ ሚካኤል ሮማዮና ጁሊትን የተረጎመው ነው" አለኝ ጎቢጥ እርግጠኛ ሆኖ። ግርማ ቢጨ ሰምቶታል። የጎቢጥን አናት እየዳበሰ "አረፍ ነህ አሪፍም እንደ ምትሆን ያስታውቃል።"

"ሮሚዮ ሮሚዮ የልቤ ወለላ
እባክህ ስምህን ለውጠው በሌላ" ጎቢጥ ከግርማ አፍ ቀበል አርጎ አሳረገለት።

ሻካር በጣም የምንወደው የሕንድ ፊልም ነው። በልጅነቱ ሰርቆ ሲሮጥ ፊልሙ ይጀምራል። እየሮጠ ዞር ሲል ፊልሙ ውስጥ ያድጋል። ሻካር በጎብረተሰቡ በጣም የተጠላ ነው። አንድ ቀን መንደሩ በእሳት ተያያዘ። ሰው ሁሉ ሲድን አንዲት ሕፃን እሳቱ ቋያ መካከል ቆማ እንዲደርሱላት ስትጮህ ሻካር እሳቱ ውስጥ ዘሎ ገብቶ ሕፃንዋን ያድናታል። እሱ ግን በእሳቱ ይቃ ጠላል። ሕዝቡ ይቅር ብሎት ሕይወቱን ለማትረፍ ተሰብስበው ሲፀልዩ ፊልሙ ያልቃል። ይህንን ፊልም ያየን ዕለት 'እጀ ወርቁ' አብሮ አደጌ ባረቾ ጠጋ አለኝና "እኔም ሳድግ ቂርቆስን እሳት ሲያቃጥለው አድነውና ሰዎች ሁሉ የሚወዱኝ ልጅ እሆ ናለሁ" ብሎኛል።

"ግርማ ቢጨ!" አለ አበራ ጥይቴ ከወደዲተል በር አካባቢ ብቅ ብሎ ለከፈው። በለከፋ በሰፈራችን የታወቀ ነው።

ሁላችንም ሮጠንበት።

ደነገጠ።

"የማነህ ቀሽም? የጓደኞችህን 'ማይንድ' በቤት ሥራ ወጥ ረነዋል። 'ሮንግ ዌይ' መታረም አለበት።"

ቂርቆስ ጓሮ ደርሰናል።

"ኒውክሌር ቦምብን የፈለሰፈው ሣይንቲስት አልበርት አን ሽታይን ይባላል። ኒውክሌር ቦምብ ያላቸው አገሮች ስንት እንደ ሆኑ ታውቃላችሁ?"

ጎቢጥ እጁን አወጣ።

ግርማ እንዲናገር ፈቀደለት።

"አሜሪካ።"

"እ?!"

"መሰኮብ።"

"እ?!"

ጎቢጥ ተክዞ አብሰለሰለ።

"አሪፍ ነሽ፣ በርቺ። የተቀሩት ፍሬንችና ግሬት ብሪቴን ናቸው።"

"እሺ" አለው ይጥና፣ ግርማ በደንብ እንዲደገፈው እጁን ሳብ አድርጎ ማጅራቱን ወደ ብብቱ እያስጠጋ።

"መጀመሪያ ኒውክሌር ቦምቡን የፈለሰፈው አንሽታይን ነው። ሲፈለስፈው ለዓለም መጥፊያ እንዲሆን አልነበረም። ዓለም ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል እንድታገኝ ነበር። አንዳንድ ተንኮ ለኛ ወታደሮች ይህ ለጦር መሣሪያነት ቢውል ጥሩ ነው ብለው የአገራቸውን ፕሬዚዳንት አስፈቀዱ። እነሱ አገር ንጉሣቸው ፕሬ ዚዳንት ነው የሚባለው።"

"ፕሬዚዳንት" አለና ሲሳይ ጎቢጥ ጻፈ።

"ለወታደሮቹ ፕሬዚዳንቱ ፈቀዱላቸው። አሁን ይህ ኒውክሌር ቦምብ ቢፈነዳ ዓለም ትጠፋለች። በዚህ ታላቅ ስህተት የተሞላበት አስተሳሰብ አንሽታይን በጣም አዘነና ነጭ መሀረቡን አውጥቶ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ" አለና ግርማ በእቅፉ የተደገፈውን ይጥናን ለቅቆ ጎደቴ ጠጅ ቤት ውሃ ልክ ላይ ተቀመጠ። ሁላችንም እንደ ጫጩት ዙሪያውን ከበብነው።

"አንሽታይን አሁን በሕይወት አለ?" ሲሳይ ጎቢጥ ጠየቀ።

"በቅርቡ አረፈ። 'ኤም ስኩዌር ፕላስ ዋን' ብሎ ጻፈ። ማን አባቱ ይህቺን ምስጢር ይድረስባት?"

'ኤም ስኩዌር ፕላስ ዋን' ብሎ ሲሳይ ጎቢጥ ጻፈ። ለእኔ በሹክሹክታ "ታያለህ ይህቺን ሂሳብ ሠርቼ ቁጭ ባላደርጋት!"

"ኒውክሌር ቦምቡን ልትሠራ?"

"እንክት አብረን ከሠራነው በኋላ ለአባባ ጃንሆይ ነው መስደን የምንሰጣቸው።"

"የት እንሠራዋለን?"

"እነ ኃይሉ ጓሮ፣ ታውቃለህ ሂሳብ ጎበዝ ነኝ።"

"አዎ" አልኩ በለሆሳስ፣ የኔን የጊዜ ቤት ደካማነትና የአብሮ አደጌን ሊቀ ሊታውንትነት እያመንኩ፣"ግን ይቻላል?"

"ለምን አይቻልም? ይቻላል። እኛ እኮ ኢትዮጵያውያን ነን። ይሄ አገር እኮ የአባባ ጃንሆይና የአበበ ቢቂላ ነው። ስለዚህ የፈለግነውን መሥራት እንችላለን"

"እንደ አነሽታይን ዓለም ኮረንቲ እንደልቧ እንድታገኝ ነው ወይ የምትፈለስፈው?"

"በደንብ!"

አመንኩት። ሲሳይ ጉበኟ አያደርገውም አልልም። የራሱን የጨርቅ ኳስ ስፍቷል። በሽቦ ቆንጆ መኪና ሠርቷል፣ ኩሽኔታውንም የሠራው ራሱ ነው። በረባሶ ጫማ ጓኛ በሽልንግ ገዝተን ስናደርግ እሱ ግን ጉማ ቆርጦ የራሱን ጫማ ሠርቷል። ታዲያ በዚህ ሁሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላለፈ ታዳጊ ወጣት ኒውክሌር ቦምብ መሥራት ምን ታቅታለች?

ግርማ ቢፌ አዲስ ፈጠራ በህሊናችን ውስጥ ይፀንስ እንጂ፣ ሃሳቡ ለሁላችንም በጣም ርቆብናል። ጨለማው በፈጠረው ድባብ በመንፈሴ ፍርሃት ተፈጥሯል። "የኒውክሌር ቦምቡ ቁልፍ ማን'ጋ ነው የሚቀመጠው?" አልኩት ግርማን። ቀና ብሎ አየኝ። "በፕሬዚዳንታቸውና በጉሣቸው እጅ ያለ መሰለኝ። ይህ ጉዳይ ትልቅ ምስጢር ነው። ለእንደኔ አይነቱ ተራ ሰው ማን ይነግረዋል? ገምት ካልከኝ ግን ባለሥልጣኖቻቸው እጅ ነው የሚቀመጠው። በምንም ተአምር እነ ጆንሜይ፣ በርትራንድ ካስትር አይደርሱበትም። ሶፊያ ሎሬንም ሆነች ማርሊን ሞርሎ ሺ ጊዜ ቢያባብሏቸውም አያገኙትም። ከተሰረቁም እኔ ኬሬዳሽ! 'ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው' ነው የምለው።"

"ኢትዮጵያ ቦምቡ የላትም?" ባሪቾ ጠየቀ።

"ጉበዝ አትቀልዱ እንጂ!' ዓይናችሁን ገልጣችሁ አልሙ" ሲጋራውን ለኮሰና በረጅሙ ስቦ ጢሱን ሽቅብ ተፋና የምር ወጉን ጀመረ።

"ቴክስ ፊልም አትመኑ። በተለይ የአሜሪካኖቹን! 'ባት ኢዝ ግሬት ክራይም' አሜሪካኖቹ ትልቅ ወንጀል እኮ ነው እየፈፀሙ ያሉት። ሬድ ኢንዲያኖቹን በጠመንጃ፣ በመድፍ ሲፈጁአቸው አይደል የምታጨበጭቡት! አሪፍ መስሏችሁ? ተሳስታችኋል። ሬድ ኢንዲያኖቹ እኮ አሜሪካ አገራቸው ነው። በገዛ አገራቸው በፈልም ጥበብ ስታሮቹ ለዓለም ወንጀለኝነታቸውን ያሳዩታል። አንድ ቀን ሬድ ኢንዲያኑ የባነኑ ዕለት ነጮቹ ይህ ድር ጊታቸው ያሳፍራቸዋል። ስለዚህ እናንተ ማደነቅ ያለባችሁ የተሻለ አስተሳሰብ ያለውን ፈላስፋ አነሽታይንን ነው። እነ ጆንሜይ፣ እነ በርትራንድ ካስትር፣ እነ ክሊንትኢስትውድ ወንጀለኞች ናቸው።"

"አይ ቴልዩ ዘትሩዝ' የሕዝብና የቋንቋ ትንሽ የለውም። አንድ

E=MC² ትክክለኛው የአነሽታይን ቀመር።

ታሪክ ልንገራችሁ። ይህንን ታሪክ ያገኘሁት ስለ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሚተርክ መጽሐፍ አግኝቼ ሳነብ ነው። በዚያ ዘግናኝ ጦርነት ወቅት ዓለም ለሁለት ተከፍላ እየተፋጁ ነበር። ጃፓን፣ ጣሊያንና ጀርመን በአንድ ወገን ሆነው ቡድናቸውን 'አክሲስ' ብለው ሰየሙት። አሜሪካ፣ ግሬት ብሪቴን፣ ሶቭየት ኅብረትና ሌሎቹ አገሮች 'አላይድ ፎርስ' አሉ ቡድናቸውን። ፍጅቱ መጨፋጨፉ ቀጥሎ በከፍተኛ ሁኔታ የሰው ልጆች በመአቱ እንደ ቅጠል ረገፉ።

"በጦርነት ወቅት አንዱ የሌላው ምስጢር ላይ ለመድረስ ልዩ ልዩ ጥበባትን ተጠቀሙ። ይሁን እንጂ አንዱ በሌላው አገር ላይ በሚያ ካሂደው የስለላ ጥበብ ይደርስበታል። ይህን ምስጢርን መመንታተፍ አንዳንዶቹን አገሮች ለከፍተኛ አደጋ አጋለጣቸው። በተለይ አሜሪካና ጃፓን አንዱ ሌላውን መፈናፈኛ አሳጡት።

"አሜሪካኖቹ በፈለጉት መንገድ ምስጢራቸውን እሸገው ቢልኩ ጃፓኖች ይደርሱበታል። በመጨረሻ ግራ ቢገባቸው 'ችግር ብልሃትን ይፈጥራል' እንዲሉ አንድ ድንቅ ሃሳብ ለአሜሪካኖቹ ተከሰተላቸው። ይኸውም ሁለት ዜጐቻቸው የሆኑ ሬድኢንዲያን ወጣቶችን መርጠው መለመሉ። ሁለቱም ወጣቶች እንግሊዘኛም አቀላጥፈው ይናገራሉ። አን ደኛውን ወጣት ጦር ሜዳ ወስደው አስቀመጡት። ሁለተኛውን ወጣት ጠቅላይ መምሪያቸው መደቡት። ከዚህ በኋላ የሚፈለገውን ምስጢር ጠቅላይ መምሪያ ለሚገኘው ወጣት በእንግሊዘኛ ይነግሩታል። ወጣቱም ጦር ሜዳ ላለው ለአገሩ ልጅ ምስጢሩን በሬድኢንዲያን ቋንቋ ይነ ግረዋል። ያም ወጣት የሰማውን ጦር ሜዳ ላለው አዛዥ ተርጉሞ በእን ግሊዘኛ ይነግረዋል። ጀኔራሉም ከአለቆቹ የመጣለትን ምስጢር በተ ግባር ላይ ያውላል። በዚህም በሬድኢንዲያን ቋንቋ ድልድይነት ተግባ ራቸው ተሳክቶ አሜሪካኖቹ በጦርነቱ አሸነፉ።

«ጃፓኖች በሬዲዮ የሚስሙትን ቋንቋ ምንነት በዘመኑ አል ተረዱም። በጣም ተጨነቁ ምስጢሩን በቀላሉ ለደርሱበት ስላልቻሉ ሽንፈታቸውን ሳይወዱ በግድ ተቀብለው የዶግ አመድ ሆኑ። እናም ወንድሞቼ አስተዋላችሁልኝ?» አለ ግርማ የሁላችንንም ገጽታ በአመክሮ እያስተዋለ። እንደፊልም ወለል ብሎ በሚታየን ታሪክ ተመስጠን የቋ ንቋ ምስጢር ባሳረፈብን ምትህት በትኩረት እየተከታተልነው ነው።

«የዚህ ታላቅ ጦርነት ድል ባለውለታ የሆኑት ሬድኢንዲያን 'ወርቅ ሳበደረ ጠጠር፣ እህል ሳበደረ አፈር' እንዲሉት ሆኖ ከገዛ መሬ ታቸው ላይ መፈናቀል፣ እምቢ ብለው ራሳቸውን ለመከላከል ሲያምፁ እንዲገደሉ መደረጉ ተገቢ ነው ትላላችሁ?» ግርማ ጠየቀን።

ብዙ ጊዜ ፊልም ስናይ የምናገዘው ለቴክሱ ነው። ሬድ ኢንዲያኖቹን ቴክሶቹ አሳራቸውን ሲያሳዩአቸው እናጨብጭብላቸዋለን። ድርጊታችን ትክክል እንዳልሆነ ተገለጸልን። ይህ ውስብስብ ምስጢር ከሁላችንም ዕውቀት በላይ ስለሆነ አዘንን።

«ባለፈው ክረምት ቤት አይሠራም' ይላሉ የጥንት ወገኖቻችን። ያለፈው አልፏል። ከአሁን በኋላ ከቁም እንቅልፋችሁ ባንኑ። ትምህርት ከትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከወላጆቻችሁ እቤታችሁ ውስጥ መጀ መር ይኖርባችኋል። 'አይቴል ዩ ዘትሩዝ አይ አም ሲሬስ' ስንቶቻችሁ

ናችሁ የወላጆቻችሁን አፍ መፍቻ ቋንቋ የምታውቁት? በዚህ በኩል ፋንጋይ ጐበዝ ልጅ ነው። የጓሞኛ ቋንቋ ይችላል። አንድ ቀን ከአባቱ ጋር 'ሰሮ አይ መላ' ሲባባል ሰምቼው ደሰ አለኝ» ሲል ግርማ በአድና ቆት ሁላችንም ሳቅን። እኔ ግን ትንሽ እንደማፈር ብዬ ተሸኩረ መምኩ።

«የፋንጋይን መንገድ ተከተሉ እንዳልኳችሁ ትንሽ ቋንቋም ብትሆን አንድ ቀን አገርን ከጥፋት ታድናለች። አሁን ሳጫውታችሁ እንደ ሙቪ ወለል ብሎ አልታያችሁም?»

«ታይቶናል» መለሰን በአንድነት።

«ዓይንን ገልጦ ማለም ማለት አንዱ መንገድ ይህ ነው። ፋንጋይ በልጅነቷ ቀድማ ባናለች። አሁን አማርኛን፣ ጋሞኛን በደንብ ትናገራለች። ትንሽ ቆይታ ደግሞ እንግሊዘኛን ስትጨምርበትና መጻሕፍትን ስታነብ ዓለም ወለል ብላ ትታያታለች።» ሲል ግርማ፣ ጓደኞቹ በአድና ቆት ዓይን አዩኝ።

ደሰ አለኝ። ገና ከማለዳው የአባቴ ጥረትም ድንቅ መሆኑ ገባኝ። ጓደኞቹ ከተለያዩ ዘሮች የተፈጠሩ ቢሆንም አንዳቸውም ከአማርኛ ውጪ የዘሮቻቸውን ቋንቋ አይናገሩም። የትጉ ወላጆች ጥረት ቢኖርም ልጆቻቸው መስማቱን እንጂ መናገሩን ስለማይችሉ የሚመልሱት በአማርኛ መሆኑን አስታወስኩ።

ግርማ ሌላ ሲጋራ ለኮሰ። በረጅሙ ሳበውና ሌላ አስደናቂ ታሪክ ያጫውተን ጀመር «እንደምታውቁት እኔ ውሌዬ ከቱሪስቶች ጋር አይ ደለም? በሥራ አጋጣሚዬ ከበርካታ አገር ተጉዘው ከመጡ ቱሪስቶች ጋር እውላለሁ። በዚያ አጋጣሚም የየአገሩን ቋንቋ እማራለሁ። አንድ ቀን ግን ከአሰደናቂ ገጠመኝ ጋር አምላክ አዋሰኝ። አንድ አሜሪካዊ ፕሮፌሰር በሥራ ተገናኝተን አረፈበት ግዮን ሆቴል ሔድኩኝ በማለዳው አንግዳ መቀበያው አካባቢ እጠብቀዋለሁ። ሙጥቶ ለእግዜሃር ሰላምታ እጹን እየዘረጋልኝ «ሰላም ለከ» አለኝ በግዕዝ ቋንቋችን «ሰላም ለከ» መለስኩለት እየተገረምኩ። ጨዋታችንን በግዕዝ ቋንቋ ሲቀጥል እኔ የማውቀው ቃል አለቀበኝ።» በሳቅ አውካካንና «ፈረንጅ በግዕዝ ቋንቋ?» እያልን ተገረምን።

«በደንብ አቀሳጥፎ ነው የሚናገረው። ይሔንን ሁሉ እንዴት እንዳወቀ ተገርሜ ጠየቅኩት። ቢያጫውተኝ እኩ አገር በመላው ዓለም ይታወቀ ሃርቫርድ የሚባል በጣም ታላቅ ዩኒቨርሲቲ አለ። በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚሰጡት ብዙ የትምህርት አይነቶች መካከል አንዱ የግዕዝ ቋንቋ ነው። ፕሮፌሰር ጆን የኛን የግዕዝ ቋንቋ ተምሮ በመካኩ፣ በአሁኑ ጊዜ ግዕዝ ለሚያጠኑ ተማሪዎች ያስተምራቸዋል። ከተማሪዎቹ መካከል ጥቂቱ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ታዲያ ይህ ፈረንጅ በግዕዝ አንብቦ በአንግሊዘኛ በመተርጉም ለተማሪዎቹ ሲያስረዳቸው የጥንት ወግኖቻችንን ጠሊቅ ዕውቀት በማወቅ ይገረማሉ። ይቆጫሉ።»

እኛ ግዕዝ የምናውቀው የነ አባ ዘለቀ ቋንቋ ብቻ እንደሆነ አበር። ለካ በጊዜው ያልተገነዘብነው ብዙ ዕውቀት የተከማቸበት ታላቅ ምስጢር ውስጡ እንዳለ ግርማ ገለጠልን።

«ታላቁ መጽሐፍ ምን ይላል መሰላችሁ? 'እሱ ታገኛላችሁ። አንኳኩ ይከፈትላችኋል' በለዚህ ይሆን የማንኳኪያና የመሻት ጊዜ በከንቱ አታባክኗት። ጃፓኖች ያ መከራ ከደረሰባቸው በኋላ 'መከራን በመከራነቱ ሳይሆን በመካሪነቱ ተቀብለው' ከማንም አገር ለመማር ፍይናቸውንም ገለጡ። ጆሮአቸውንም ከፈቱ በአሁኑ ጊዜ በጃፓን ዩኒቨርሲቲዎች የሬድኢንዲያን ቋንቋ መማሪያ በርካታ 'ዲፓርትመንት' አሏቸው። 'ለብልህ ይነግሯል እንጂ አይመክሩም' ይላሉ አበው። ትም ህርትን ዛሬ ከአካባቢያችን ጀምረናል ነገ ደግሞ ሁላችንም ከየቤታችን እንቀጥላለን» አለና ፊሊተሯ ብቻ የቀራት ሲጋራውን ልምጥጥ አድርጉ ስቦ መሬት ጣለና በጫማው አወደማት። «እና ጉበዝ እናቶቻችሁ አረብ ቤት ልከዋችሁ ሰኳር ገዝታችሁ ስትመለሱ፣ ስኳሩ የተጠቀለለበትንም ወረቀት አትጣሉት እንብቡት። ከምርቃት ከረሜላው ይልቅ የሚ ጣፍጥ ከረሜላ የምታገኙት እዚያች ወረቀት ውስጥ ነው። አንድ በጣም 'ኢምፖርታንት' ነገር እዚህጋ ሳስታውሳችሁ። መድኃኒትን ሐኪም መጥኖ እንደሚሰጠን ሁሉ፣ ሲኒማንም መጥነንና መርጠን ማየት መቻል አለብን። መድኃኒቱ ሲበዛ ለሞት እንደሚዳርገን ሁሉ ሲኒማ ውም ከምርጥ ምርጡ ላይ አተኩረን ካላየነው የሕይወት ጉዳናችንን ያስተናል። 'ግርም ሲበዛ ይመራል' ይላሉ አበው። አሁን ቅድም አሜሪካኖቹ በሬድኢንዲያኖች ላይ የሠሩትን ፀያፍ ተግባር ትክክል አይደለም አልኩ እንጂ፣ 'አሜሪካንስ በፍሪደም ሩይቲንግ' አገራቸውን ለማቅናት የከፈሉትን መስዋዕትነትና ሌላውን በተመለከተ ድንቅና አሪፍ አሪፍ ፊልሞች አሏቸው። እኩን ግየት ይኖርባችኋል። እንደውም አንድ ቀን እኔ አሪፍ ፊልም መውጣቱን ካየሁ አንድ ባውንድ እመድብና ተሰለፍ!! የቂርቆስ ልጆች ብል?!...» ከአፉ ነጥቀን «እንሰለፋለን!!» አልን በአንድነት።

«አይ ስቄር ' እጋብዛችኋለሁ!» አለንና ሁላችንንም ተራ በተራ ጨበጠን።

ግርማ የምናንኳስሰው እና የምንዘረጥጠው ሳይሆን የምናደ ምጠው ሰው እንደሆነ ብዙዎቻችን እየገባን መጣ። የሚያወራልን ልክ እንደ እኩያ ጓደኞቹ በመሆኑ ሃሳቡ እንደሚጠጥብን ልብ አይልም። እኛ የምናውቀው ታላቅ አገር እንዳለን ነው። ኢትዮጵያ ኒውክሌር ዘምብ የላትም ቢለን ማመን ቸገረን።

ልጁ ዱጥአለ መጣ። አባቱ እግር ላይ ተጠምጥሞ "አንተ ግርማ፣ እኔ አንተን እየጠበቅኩህ እዚህ ታወራለህ?"

"አ! ብርሃኔ እየመጣሁ ነው፣ አልረሳሁህም ልጄ" ልጁን መለ ማመጥ ሲጀምር፣ እኛን እዚያው በዚያው ረሳን። "ይኸው ያል ከኝን እንዱሽዱሽ አምጥቼልሃለሁ" አለና ለዱጥአለ አሹቅ ከኪሱ አውጥቶ ሰጠው።

ብርሃኔ በሕፃንነቱ ፈሱ አመለጠውና "አባ! ዱጥ አለ!" አለ። ይህም ቅፅል ስሙ ሆነ።

ተነሳና ቆመ። ውሃ ልኩ ላይ ተቀምጠ ሱሬው የነካውን አሟራ አራገፈ። አንድ ሲጋራ አወጣና ለኩሶ "ወንድሞቼ ደህና እደሩ ልላችሁ ነው" አለን።

በዚያ የገርነት ዕድሜ እንዲህ አንዳንድ ተራ ሰዎች በሕይወታችን ውስጥ እየተከሰቱ የማናውቀውን ዓለም ምስጢር ይፈነጥቁልንና የስማቸው መዓዛ ሙላውን ዓለም ያወደ ሃሳበ ሰፈ ዘለዓለማዊ ሰዎችን ያስተዋውቁን ነበር።

ቤንዚል በአገራችን አገኘን

«... ገንዘብ ልክ እንደክራር ጨዋታ ነች።
አጨዋወቷን ያላወቀበት ዝብርቅርቅ ጩኸቷን ይሰማል»
ካህሊል ጅብራል

የግንቦት ልደታ ዕለት ሰድስት ጓደኞማቾች በአውሮፕላን ተደብቀን ከአገራችን ለመጥፋት ወሰንን። ይህንን ሐሳብ የፈጠረብን በዚያን ሰሞን የተመለከትነው ፊልም ነበር። አኩዮቻችን የሆኑ አራት ሕፃናት ማንም ሳያያቸው አንድ አውሮፕላን ውስጥ ይገባሉ። የአውሮፕላኑ ነጂ ወደማያውቁት አገር ይሏአቸው በረረ። እውስጡ ሻንጣ ሙሉ የአገራቸውን ብር አግኝተው፣ ባረፉበት አገር ያሰኛቸውን ቆንጆ፣ ቆንጆ ልብስም ሆነ ጫማ ገዝተው እየዘነጡ ይምነሸነሻሉ።

እኛም በአውሮፕላን ብንጠፋ፣ ሻንጣ ሙሉ ብሩን እውሮፕላን ውስጥ ስናገኝ ታየን። ለወላጆቻችን ሺ ሺ ብር እንልክላቸዋለን። በበነ ጋታው ለመጥፋት ቆረጥን። ማለዳ ተገናኝተን ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አየር ማረፊያ ጉዞ ጀመርን።

ለሰንቅ ብለን ሁላችንም የየራሳችንን ቆሎም ሆነ የጤፍ ቂጣ ወይ አሹቅ በኪሳችን ይዘናል። በእግረ መንገዳችን ባጋጠሙን የአትክልት መሸጫ ግሮሰሪዎች አዘናግተን ጎራ እያልን ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ቲማቲም መንትፈናል።

መስቀል እደባባይን አለፍ እንዳልን ቤቶቹ ዘርዘር እያሉ ይሄዳሉ። በአቋራጭ መንገድ በመሔዳችን አውሮፕላን ማረፊያው ደረሰን። እንደገመትነው ሳይሆን አጥር አብረው። መግቢያ ፍለጋ ጥግ ጥጉን መዞር ጀመርን። በአካባቢው ሰው ዝር ሲል አይታይም።

መሹለኪያ ቀዳዳ ለማበጀት ባገኘነው እንጨትም ሆነ ሹል ድንጋይ መቆፈር ጀመርን። ጥቂት ከግሰን በኋላ እየደከመን ይመጣ ጀመር። በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ ልጆች ለሰንቅ ብለው የያዙትን ቆሎም

ሆነ ቂጣ ይቆነጣጥሩለት ጀመር። በዚህ ድርጊታቸው ከማንበላው ልጆች ጋር ንትርክ ተጀመረ።

ሻቃ ተቆጥቶ «ሁልሽም የራስሽን ሰንቅ ጨርሰሽ በኋላ ሌላ አገር ለንደርስ ሰጪኝ ብትይ አምስት ሣንቲም አላቀምስሽም። ፍርፋሪም ቢሆን!» አለ።

«አታይም እንዴ? መቆፈሩ አደከመን እኮ። በልተን ካልጠነከርን ጉልበት ከየት እናመጣለን?» አለ ቀጢሳው፣ አሹቁን ከማገበሩ ፈቃድ ውጪ እየቃመለት።

እኛም በረጃጅሙ ሣር ላይ ተዘርረን የያዝነውን ሰንቅ መብላት ጀመርን። «እነዚያ በአውሮፕላን ሲጠፉ ያየናቸው ልጆች እኮ አውሮፕላኑ ውስጥ ዳቦም፣ ፓስታም ውሃም አግኝተዋል። እኛ ደግሞ ስንጠፋ ዕድለኛ ከሆንን የምንሄድባት አውሮፕላን አባባ ጃንሆይ ፈረንጅ አገር የሚሄዱባት ልትሆን ትችላለች። የምንበላውን አንደ ልብ ልናገኝ እን ችላለን። ሳህንና ማንኪያውም የወርቅ ዕቃ ሲሆን ይችላል» አልኩኝ።

ይህ ሃሳብ ከአንድ ለዓት በላይ የፈጀ ክርክር አስነሳ።

«ጃንሆይ የሚበሉት በወርቅ ማንኪያ አይደለም። በብር ማንኪያ ነው። አባቴ ሲያወራ ሰምቻለሁ። ኃይለሥላሴ ይሙት!! በብር ነው!» አለ ሲሳይ ጎቢጥ።

ስለማለ ሁላችንም ጎቢጥን አመነው።

«እኔ 'ፉድ' ላግኝ አንጂ ማንኪያ አልፈልግም» አለ ኃይሉ ዶሮ። በብዙዎቻችን ቤተሰብ ጤፍ ተሸምቶ ወር ሳይገባ ካለቀ፣ እንደ መዳረሻ ፓስታ ሹታ የአንድ የሁለት ቀናት የቤተሰቦቻችን ምግብ ይሆ ናል። በዚህ ጊዜ በየጠረጴዛው ሥር የተረሳና የዛገ ማንኪያም ሆነ ሹካ ይፈላለግና ወላጆቻችን በእሱ ሲመገቡ እኛ በእጃችን ነበር የምን ወጥቀው።

ወጋችን ደራ። መሹለኪያውን መቆፈሩን ለጊዜው ቸል አልነው። «እዎን» አለ መኩዬ ቀጫጫው «ልብሳችንም ኬፓችንም አንድ አይነት ይሆናል። ሽጉጥም እንታጠቃለን፣ አይደል?»

«የሁላችንም ልብስ ልዩ ልዩ ሆኖ ቆንጆ ከሆነ ደስ ይላል» አለ ኃይሉ ዶሮ «ከፈለግን አየተለዋወጥን መልበስ እንችላለን።»

ተጨቃጨቅን በመጨረሻ ሁላችንም የእሰጎንን ለመልበስ፣ መዋ ዋሱን ግን ለሙተው ተስማማን።

«አንተ ሻቃ፣ ኮትህ ተቀዷል» አለች መኩዬ ቀጫጫው።

«ተይው! በምንጠፋበት አገር ስንደርስ መርፌ ገዝቼ እሰፋ ዋለሁ። አዚያ ሳሙና ሲገዛ መርፌ ላይመረቅ ይችላል» አላትና ቁፋ ሮውን ለመጀመር ተነሳ።

«ቆዩ ልጆች» አልኩ «መቆፈር ከመጀመራችን በፊት አንዴ የቀረንን የአጥር ጎን ተዘዋውረን እንመልከት። ምን እልባት የተሰበረ ያጋጥመን ይሆናል።»

ተስማማን። ሰንዘር መሬቱ እየረጠበ መጣ። ከርቀት እጥሩ በሰፊው ተቀዶ ታየን። መሮጥ ሰንጀምር «ቆይ!» አለ አብነት ባሪያው።

ሁላችንም ቀጥ አልን። አንድ ሞራሮ አነሳና በቀስታ እየተራመደ ወደ ረግረጋማው መሬት ተጠጋ። ጥልቀቱን ለመለካት ሞራሮውን ወደ ረግረጉ ሰደደው። ሞራሮው ሰጠመ። ዞረና አፈጠጠብን።

«ቀዥቃዣዮች! እያንዳንድሽ ቅድም ዝም ብልሽ ይሄኔ ሰጥመሽ ነበር። ወደ እዚያ ሄደን ሴላ መጫለኪያ እንፈልግ»

«እሺ» ብለን ሰንጋዝ በቢንዚን የረጠበ ቦታ ደረስን። ሣር አልበቀለበትም።

«ምንድነው ይሄ?» አለ ሲሳይ ጎቢጥ «እዚህ መሬት ውስጥ ቤንዚን አለ ማለት ነው?»

«ልጆች!» አለ ሴምላል ንፍጡን በእጅጌው እየጠረገ «እውነት ቤንዚን ካለ ትንሽ ብንቆፍረው ሲፈልቅ ማየት እንችላለን።»

በያለንበት መሬቱን መጫር ጀመርን። በማስነው መጠን የበለጠ እየረጠበ ሄደና ነዳጅ አቆረ። በደስታ ሰከርን። ተጫጨቤሽን እየተቃቀፍን ተሳሳምን።

አባባ ጃንሆይ እልፍ ብር ሳያወጡ ቤንዚኑን እዚሁ አውሮፕላን ማረፊያው ሥር አግኝንላቸው። አቤት ይኼንን የምሥራች ስንነግራቸው የሚደስቱት ደስታ! እየሳቁ «አናንተ ጮካዎች እንዴት አገኛችሁት?» ብለው ሲጠይቁን ወለል ብሉ ታየን።ከዚህ ጋር ግን አንዳንድ ስጋቶችም ተፈጠሩብን።

«ለአባባ ጃንሆይ ለራሳቸው ካልሆነ ለማንም አንናገርም። እሳቸውን አግኝተን ከነገርናቸው ግን እኛ እንድንማር፣ ቆንጆ ቆንጆ ልብስና ጫማ እንደልባችን እንድንለብስ ያደርጉናል። ለእያንዳንዳችን ወላጆች ሺ- ሺ ብር እንዲሰጡን እንጠይቃቸዋለን» አለ አብነት ባሪያው።

«ለምን ሺ- ሺ ብር ብቻ? አሥር- አሥር ሺ ብር ለእናትና አባቶቻችን እንዲሰጡአቸው እንጠይቃለን» አልኩ።

«አይሆንም ልጆች፣ እኔ በሬዲዮ የሰማሁት ነገር አለ» አለን ጎቢጥ አባቱ ሬዲዮ ስለገዙ ጎቢጥ ድንቅ ዜና ተከታታይ ሆኗል፣ «አልሰማችሁም? አንድ ሰውዬ ሽማግሌ ናቸው። ሎተሪ ቆርጠው በሚወጣበት ቀን ለሎተሪ ነጋዴው ትኬታቸውን አሳዩት። አሥር ሺ ብር ሎተሪ ወጥቶሎታል ብሎ ሲነግራቸው እ... እእእ! ብለው ዘፍ አሉ። እና ሞቱ። እኔ እናትና አባቴ አንዲሞቱብኝ አልፈልግም። አንድ- አንድ ሺ ብር ከተሰጣቸው ይበቃል።»

በጎቢጥ ሃሳብ ተስማማን። በደስታ እንደሰከርን ነው።

«አሁን ወደ ቤተ መንግሥት ከመሄዳችን በፊት በዚህች በኩል አቋርጠን ፏፏቴ ሄደን አካላችንን እንታጠብ» አለ ሲሳይ ጎቢጥ።

«አይይይይ!» ጮኸ ሴምላል።

ለምን እንደተቃወመ ገብቶናል። ዋና ሄደን ስንመለስ በጣም ይርበናል። ስለዚህ ከተቻለ እዚያው አካባቢ ከሚገኙ ማሳዎች ውስጥ ካሮት እንሰርቅና እንበላለን። ገበሬዎቹ ቀድመውን ነትተው አቀበቱ ላይ ተቀምጠው ይጠብቁናል። አንድ ልጅ ደፍሮ እየተሽለከለከ ማሳው

ውስጥ ሲገባ ከተያዘ ፈሱን እስከሚጨርስ እንደሚወገር ስለምናውቅ ልንጋፈጥ አልፈለግንም።

ከዱላው ረሃቡን መርጠን በመንገዳችን የተሰጣ ከክም ሆነ ሴላ የሚበላ ምግብ ለመመንተፍ እያስተዋልን ወደ ስፈራችን ጉዞ ጀመርን። ከአንድ ግቢ በር አንድ ትንሽ ልጅ እንዳች የሚያክል የድሮ ዳቦ ጉማጅ ይዞ ብቅ አለ። ረሃባችን ተባባሰ። ቀጢሳው እየከመከ ልጁን ተጠጋው። ልጁም ድሮ እንደሚያውቀው ሁሉ እየሳቀ ቀረበው። ቀጢሳው ዳቦውን ሊቀበለው እጁን ሲሰድ ልጁ ጮኸ። ቀጢሳው ቀልጥፎ እጁን ሰበሰበ።

«ምን ታቁለጨልጫናለህ? አትለማመጠው» አለና ተረፈ ገልጆ መንትፎት እግሬ አውጪኝ አለ።

ልጁ እሪታውን አቀለጠው። በሩጫ መስወር ጀመርን። ከኋላችን የልጁን ጩኸት የሰሙት ቤተሰቦቹ ወጥተው ሲረግሙን ይሰማናል። ገልጆ ዳቦውን ሲጨረግደው ከፊት ይታየናል። እኛ ስንደርስበት እሱ ዳቦውን ጨረጋግዶ ሲያጠናቅቅ አንድ ሆነ።

የደብረዘይትን መንገድ እንደተሻገርን መሮጡን እቆምን። በመን ደር ውስጥ ለውስጥ መንገድ ስንሔድ ከፊት ለፊታችን አንድ አነስተኛ ዳቦ ቤት አየን። ውስጡ በዕድሜ ትንሽ የሚበልጠን ልጅ ቆሟል።

ዶጅ ገማጣው ስሙኒ ከኪሱ አውጣና «ለሁሉም የዱንዙሉ፣ ሩርኖ ሁለት ሁለት ስጥልኝ» አለው።

ሩርኖው እጃችን እንደገባ መጨርገድ ጀመርን። ዶጅ በመ ጨረሻ የራሱን ሁለት ሩርኖ ተቀብሎ፣ እንደሚከፍል ስሙኒውን እየሰ ነዘረ «ተበላህ!» አለና ጮኸ። ስሙኒዋን ሳይከፍል መሮጥ ጀመርን።

መጀመሪያውኑ አካኋናችን ያላማረው ዳቦ ነጋዴ ልጅ «ኢዮ! ኢዮ! ኢዮ!» ብሎ እየጮኸና ባንኩኒውን ዘሎ ወጥቶ ተከተለን። ሴም ላል በአራርጠ ደከም ስላለ ደርሶ ተመጥሞበት አብረው ወደቁ። ሴምላል ቢያዝም ዳቦውን በልቶ ጨርሷል። የሁላችንን ዕዳ በወገራ እን ዲያወራርድ ተደርጎ እያነከሰ፣ በግማሽ ሳቅና በግማሽ ልቅሶ ስሜት እየታየበት፣ ከምንጠብቀው ቦታ ደረሰብን። ዛሬ ይህ ትውስታ ስለመጣበት ነብር ዋና መዚዳችንን የተቃወመው።

እዚያው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አየር ማረፊያ መስክ ላይ እንደ ተቀመጥን በሃሳብ ጅው ብዬ ሄጀ ጃንሆይ ግቢ ገብተን ሲቀበሉን፣ ተራ በተራ ጨብጠውን...

ቀጢሳው ጎሸመኝ። ከሃሳቤ ባነንኩኝ። «ዛሬ እኮ የግንቦት ልደታ ነው። ለምን ወደ ስፈራችን ሄደን የአድባር ንፍሮአችንን እየቃ ምን የጠግ ቆለጥ ጠበሰን አንበላም?"

«እንዴ! በአውሮፕላን መደየማችንስ?" ጠየቀ ሻቃ ተቆጥቶ።

«እኔ አልሔድም" መለሰ ቀጢሳው።

«ለምን ቡካታም!» ተናደደ ሻቃ።

«አምን 'ዐክፎለሁ'። በፊልም ያየነው ነገር ሁሉ የእውነት መስላ ችሁ እንዴ?» ተመናቅሮ ቀጢሳው ተነሳ።

«ለምን አይሆንም? ባይሆንማ ፈረንጆቹ ስታሮቹን አንዲት ቀጷቸው። እኛ ነን ጥፋተኛ አንተን ድሮም ና ማለት አልነበረብንም" አለ ዶሮ።

«ኧረ አናንተ 'ደይሙ' አውሮፕላን መንዳት ትችላላችሁ አይ ደል?» ቀጢሳው አሳገጠ።

«ምን መንዳት ያበፈልጋል ንጂው አበከሚመጣ አድፍጠን እንጠ ብቃለን» አለ ሴምላል ንፍጡን በእጅጌው አየጠረገ።

«እኔ መጀመሪያውንም አልቃወምም ብዬ አንጂ ከአገራችን አውሮፕላን ይዘን መጥፋት 'ዛት ኢዝ ሮንግ ቄይ' እንደሆነ ገብቶኛል» አለ ጎቢጥ።

ሁላችንም በሳቅ አውካካን።

በአናታችን ላይ አንዳች የሚያክል አውሮፕላን አኩብኩቦ ማረፊያው መበክ ላይ አረፈ። ከግዘፈቱ የተነሳ ጥላው ሀሐይን ከለለን። ደምፁም አሸበረን።

«ይኼኔ ካፒቴኑ ሾፍን ለዘበኞቹ በበልክ ነግሮአቸው ይሆናል» አለ ጉቢጥ።

«አንተ እውነት ሊሆን ይችላል!» አለ ቀጢሳው

«ከፈለጋችሁ ወይም አሁኑኑ ሂደን ወይም ነገ ለአባባ ጃንሆይ ቤንዚን ማግኘታችንን አንንገራቸው። በአውሮፕላን መጥፋቱን ግን አኔም...» ከማዶ አህል ውሃ የማያለኝ ቆመጥ የያዙ ሁለት ዘበኞች ወደ እኛ አቅጣጫ ሲሮጡ አየሁና ወሬዬን አቆምኩ። አኔ ያፈጠጥኩበት አቅጣጫ ቀጢሳው አየና «ጉሽ ዘበኞች መጡልን። ኑ! ኑ! አውሮፕላን ይዘን ልንጠፋ ነበር የመጣነው። ያዙና አራችንን አብሉን!" አያለ ሮጠ። አኛም ተከተልነው። የቦሌ መበክ ሰንበሌጥ ጥላ ከለላ ሆነን። ዘበኞቹ ንም አጥሩ ገታቸው። ባሉበት የሚያወርዱብን የበድአደግ በድባቸው በርቀት ይሰማን ነበር።

*መደየም፣ መሔድ።
* ሾፈን፣ አየን።

አድባር

አሰይ ሰሉቴ ሰመረ፣ አሰይ ሰሉቴ ሰመረ
አምና ይሺን ገዜ ተሰዬው ነበረ
አሰይ ሰሉቴ ሰመረ፣ አሰይ ሰሉቴ ሰመረ

አናቶቻችን ለግንቦት ልደታ ከማለዳው ለቂጣ መጋገሪያ የሚሆን ዱቄት ያዋጣሉ። ለንፍሮ መቀቀያ በንዴውንም ባቄላ ውንም ከየቤቱ ይሰበስባሉ። ለቡናና ለዕጣን መግዣ ስሙኒም ሆነ ሽልንግ በነፍስ ወከፍ አዋጥተው ይሸምታሉ። እንጨቱም ጉልቻውም እንዳሁ ከያለበት፣ ከየአቅራቢያው ቤት ይሰበሰባል።

አባቶቻችን አንድም ሁለትም ብር አዋጥተው በግ ይገዛሉ። እኔም ሆንኩኝ አብሮ አደጎቼ የምንራኮተው የበጉን ቆለጥ ለማግ ኘት ነው። ከበግ ሥጋ የቆለጥን ያህል የሚጣፍጥ ያለ አይመ ስለኝም።

ማምሻውን እኛ ከጠፋንበት ስንመለስ የበጉም ሽመታ ሰምሮ፣ ከየቤቱ በርጩቄማውም አግዳሚ ወንበሩም ወጥቶ ጨዋ ታው ደርቶ ነው የደረስነው።

"ቱ! ቱ! አበስኩ ገበርኩ! አንድ በግ ሰባት ብር ከሃምሳ?! እግዚአ ደጉን ጊዜ አምጣ!" አለ አባቴ።

"አንተ ሰባት ብር ከሃምሳ መሆኑ ይገርምሃል እንዲ?! ግና አንድ ባውንድ ይገባል! ቱ! ኃይሌ ምን አለ በለኝ!"

"ጉድ እኮ ነው። ኃይሌ ታስታውሳለህ። ድሮ እኛ ልጆች እያለን ጭቃ ረጋጭነት ስንሠራ አንድ በግ ቆዳ መልስ አምስት ብር እንገዛ ነበር።"

"አምስት ብር? እኔ ቆዳ መልስ ሁለት ብርም ገዝቻለሁ። አንተ የትናንቱን ነው የምትሰው" አሉ አባባ አጋፋሪ ያለፈውን ዘመን እያስታወሱ። "በጉን ድፍኑን አምስት ብር ትገዛና፣ አስገ ፍፈህ ቆዳውን መልሰህ ስድስት ሽልንግ ትሸጠዋለህ። በሁለት ብር ድፍን በግ በሳህ ማለት ነው።"

ታዳሚዎቹ ተገረሙ።

አባቴን ጎሸም አደረኩት።

"ምንድነው?"

"የበጉን ቆለጥ..."

"እንጃልህ! ደግሞ የት ውለህ ነው የመጣኸው? ቤት ስንገባ እንጠያየቃለን" አለና ትኩረቱን ወደ ጨዋታው መለሰ።

የሰፈር ልጆች በየመንደራችን ነው አድባር የምናከብረው። እኔ፣ ቀጢሳው፣ ቦቾራ፣ ሳህሉ መቃ፣ አንድ አካባቢ ነን። እነ ዶሮ፣ ሻቃ፣ መኩዬ ቀጫጭው... ሰፈርም አድባር ያከብራሉ። ጨዋታው ደመቅ ባለበት ሂደን የመጫወት፣ አድባር አውጋሩ

ያፈራውን የመቋደስ መብታችን በአዋቂዎቹ ዘንድ ሙሉ በሙሉ የተከበረ ነው።

ጨለማው ለዓይን ያዝ እያደረገ ነው። የክርስትና እናቴ እማማ ቦጋለች ብዙ ስኒ በረከቦት ደርድረው፣ ከስሩ ቁጤማ ጎዝጉዘው እየጓቸው። በማንደጃ ፊይ ቡና ይቆላሉ። እና ታቸውን የሸፈኑብትን የአንገት ልብስ አሁንም- አሁንም እያስ ተካከሉ ይከናነባሉ። ከስታራ ናቸው። ፈቃቸው አይፈታም።

እማዬ የበጉ ሥጋ የሚጠበስበትን ጉልቻ አዘገጃጅታ ምጣድ ጥዳ እሳት ስታቀጣጥል፣ እማማ በለጡ የበጉን ሥጋ በትሪ ይዘው ሲመጡ አየሁ። ሮጬ ሄጀ በዓይኔ ቆለጡን ፈለግሁኝ። ሥጋው መካከል ቆለጡ የለም። ወደ አባቴ ስመለስ፣ ከማዶ መኩዬ ቀጫጫው ስትመጣ አየኋት። አንድ እጇን በኩታ ውስጥ ደብቃለች። ስጠጋት ኮቷን ገለጥ አደረገችና ሁለት ቆለጥ አሳ የችኝ። ደንግጬ ልጮህ ስል "ይሄ እኮ የእናንተ በግ ቆለጥ አይ ደለም። የእኛ ሰፈር ነው። አባባ ዓለሙ ናቸው ስለምናቸው የሰጡኝ። ከፈለክ የእናንተንም እምጣና አንድ ላይ ጠብሰን እንበ ላለን» አለችኝ።

ወደ አባቴ ተመልሼ "ቆለጡስ?" አልኩና ጮዘኩበት።

"ጨዋታ እያቋረጥክ አስቸገርከኝ አይደል? ቆይ በኋላ እንነ ናኛለን። ሂድ እዚያ ጓዳ ትንሽዋ ጠረጴዛ ሥር በንድጓዳ ሳህን ውስጥ አስቀምጨልሃለሁ።"

ይዤ ስወጣ በሩ ላይ መኩዬን አገኘኋት። ወደ ቤቱ ውስጥ እየመለሰችኝ "ቆይ አሁን እማማ አመለወርቅ ኩሽና እንሄዳለን። ብረት ምጣድ ፈልግ፣ ትንሽ ዘይትም ስረቅና በጣም የሚጣፍጥ የቆለጥ ጥብስ እንጠብሳለን።"

እማማ አመለወርቅ እዚህ አድባሩ አካባቢ እየተሳተፉ ነው። ኩሽናቸው ከጓሮ በመሆኑ ከለል ያለ ነው። ዘይቱን ብትንሽ ብልቃጥ ስርቄ መጣሁ። ወደ ኩሽናው ተከተልኳት።

"እየጓቸው!"

"እነማንን?"

"ደምስንና ዓለምነዘን።"

"አዲስ ቤት ሠርተው ከእኛ ሠፈር ሌላ አካባቢ ሄደው የለም እንዴ?"

"ቢሄዱስ? እዚያ የሚሄዱበት ስፈር ማንም አያውቃቸ ውም። ድሮ ሰፈራቸው ቢመጡ ማንም አይከለክላቸውም። ዛሬ ግን ሠራንላቸው። ቆለጡን ይዘን ሽል አልን።"

ዞር ብዬ ሳይ ከሰፈርተኛው ጋር ሰላምታ እየተለዋወጡ ነበር። በእማማ በለጡ ብልጧ ቤት በኩል እጥፍ ብለን፣ በጠባ ብዋ መንገድ አልፈን፣ ኩሽናው አጠገብ ስንደርስ ድምፅ ሰማን።

መኩዬ ፀጥ እንድል ጎሸመችኝና ግርግዳውን ተደገፍን። ሳህሉ መቃ የእናቱን ትልቅ ጋቢ ተከናንቦ እየወጣ ነው። የቤታ ቸውን ጓዳ በር መለስ አድርጎ ሲሄድ አሳለፍነው። በጠባብዋ መንገድ መተላለፊያው ላይ ከአጋጠሙት ልጆች ጋር ወሬ ጀመረ።

"ፉንጋይና መኩዬ ቀጫጫውን አይተሃቸዋል?"

"አላየኋቸውም" መለሰ መቃ።

ጠያቂዎቹ ደምስና ዓለምነህ ናቸው። በጣም ብልጥ ስለሆኑ የበጉን ቆለጥ መውሰዳችንን የጠረጠሩት ከልጆቹ መካከል ስለጠ ፋንባቸው ነው። ሊነጥቁን ነው አመጣጣቸው። ግን አካባቢውን ሲያዩት ጨልሟል። መቃን አምነውት ተመለሱ።

"እኔ ገብቼ እሳት አነዳለሁ። አንተ እዚህጋ ቁምና ሰው ጠብቅ፣ እንካ የእኔን የበግ ቆለጥም ያዝልኝ" አለችና መኩዬ ስጠ ችኝ። ከእኔ የበግ ቆለጥ ጋር አማምሬ ያዝኩት።

መኩዬ እማማ አመለወርቅ ያዳፈኑትን እሳት ቆስቁሳ፣ ማገዶ ጨምራ ስታቀጣጥል ይሰማኛል። "ጎሽ! እዚሁ ብረት ምጣድ አለ። ፉንጋይ፣ አምጣ ዘይቱን?"

ተቀበለቺኝ። በመጋል ላይ በሚገኘው ብረት ምጣድ ላይ ዘይቱን ስትጨምር ተሸሽ ሲል ይሰማኛል።

"አምጣቸው ቆለጣቹን" በሹክሹክታ አዘዘችኝ።

ሰጠኋት።

"ና! ግባ።"

ገባሁና በሩን ዘጋሁ።

የእግር ዳና ተሰማን። ትንፋሻችንን ውጠን የኩሽናውን በር መለስ አደረግነው።

"ማነው እዚህ እሳት የሚያነዳው?"

መቃ ነው።

በሩን ከፍተን ስበን አስገባነው። የምናደርገውን ሲያይ "ምን ሰርቂ ላምጣላችሁ?" አለ።

"ትንሽ ጨው!"

ቆለጦቹ በስለው ፍርክስ አሉ። ጨውን ነሰነስንና ተከፋ ፍለን በላናቸው። እሳቱን መልሰን አዳፈንን። ምንም የተዝረከረከ ነገር ኩሽናው ውስጥ ሳንተው ወጣንና ከአድባር ከአውጋሩ ተቀ ላቀልን።

"እናንተ፣ የት ጠፍታችሁ ነበር? ምንድነው የበላችሁት? ታዲያ አፋችሁ ለምን ዘይት የተቀባ ይመስላል?" ቀጪላው በጥ ያቄ አጣደፈን።

ዝም አልነው።

ማልቀስ ቃጣው።

ቆለጡን ጠብሰን እንደበላን ደርሶብናል። ለአባቱ አቤቱታ ውን እንዳያሰማ ይፈራቸዋል። በብሽቀት እርር ድብን አለ።

ዕጣኑ ይጨሳል። ቡና ለሚጠጡ ታድሏል። ንፍሮው እዚ ያም፣ እዚህም በሳህን እድምተኛው ፊት ተቀምጧል። ካቲካ ላውም፣ ጠጁም ለሚጠጡ ሁሉ ቀርቧል።

"ና ፉንጋይ" ጠሩኝ እማማ ቦጋለች።

ቱር ብዬ አጠገባቸው ደረስኩ

"ሹራብህን ዘርጋ።"

ሹራቤን አጎድጉጄ ቀረብኳቸው። ከንፍሮው በደንብ ዘግነው ሰጡኝ። እማዬ አነባበሮ ጨመረችልኝ። ቤታችን በር ደፍ ላይ ቁጭ ብዬ እየበላሁ አላፊ አግዳሚውን ማየት ጀመርኩ። መኩዬ መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች። እሷም ንፍሮና አነባበሮ በሁለት እጇ ይዛለች። "ለምን የኔታ ዘለቀ ሲመጡ አጠገባቸው ቁጭ ብለን ተረት እንዲያወሩልን አንጠይቃቸውም?"

"ጥሩ ነው፣ እሳቸው እኮ ለምን እንደሆን ባላውቀውም እን ዲህ አይነት አድባር ላይ አይመጡም። ግን አሁን እኮ አስር አለቃ ገመቹ ቶሎሳ ይመጣል። እሱ ስለ ጦር ሜዳ ወሬ ለትልልቅ ሰዎች ሲያወራ ብንሰማ አይሻልም?"

ገመቹ ቶሎሳ የሰፈራችን ልጅ ነው። ስምንተኛ ክፍል እን ደደረሰ ትምህርቱን አቋርጦ ውትድርና ተቀጠረ። ሠልጥኖ ወደ አጋዴን ዘመተ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ፤ በዘመተበት ወታደ ራዊ ጀብዱ ሠርቶ፣ የአስር አለቃ ማዕረግ ተሰጥቶት፣ አባባ ጃን ሆይ ሜዳሊያ ሸልመውት ወደ ሰፈራችን ሰሞኑን መጥቷል። ከአባቴ ጋር በዚያን ሰሞን ሲያወሩ፤ የነበረው ጨዋታቸው ትውስ አለኝ።

"ገመቹ፣ አንተ ላቂታ ነህ። እንደው ከጠላት ጋር ስትዋ ጋም ስትማረክም እየላቅህ ነው?" አባቴ እየላቀ ጠየቀ።

"ታዲያስ፣ ጋሼ ዜራሞ?" እየላቀ መለሰ።

አረንጓዴ ሸሚዝና ቦላሌ ሱሪ ለብሶ፣ ቀይ ቡቲ የቆዳ ጫማው እንደ መስታወት ታብረቀርቃለች። መለዮውን በአንድ ጎን ጋደል አድርጓል። ሮመር ሰዓት አስሯል።

"ሜዳሊያህስ?"

"እሱ እኮ በአዘቦት ቀን አይደረግም። በበዓላት ቀን፣ ለም ሣሌ የዘውድ በዓል ሲከበር፤ አልያም በጃንሆይ ልደት፤ ወይም በድል ቀን ነው።"

"ሰዓትህ ስንት ሆኗል ትላለች?"

"አራት ከሩብ።"

"ወይ ጉድ! ቀይ እኔም እገዛና ታስተምረኛለህ?"

"ደስ ይለኛል። ቀላል እኮ ነው።"

"በልሁ በቀደም ሚስት ሲያገባ ያሠረው የአንተን ተውሶ ነው?"

"ጋሼ ካለ ምን አለበት? አብሮ አደጌ ነው።"

"መዋሱን አይደለም። መቁጠሩን ይችላል ወይ? ትንሽም ቢሆን ትምህርት ይጠይቃል እኮ። አሁንም አሁንም ሠርጉ ላይ ተቀምጦ ሰዓቷን ሲያያት ማሠሩን ካልሆነ መቁጠሩን አይችልም ብዬ ነበር።"

ሁለቱም ሳቁ።

የዕልልታ ድምፅ ተሰማ። እማማ ጫልቱ ናቸው። ሊትሮ የፈረንጅ አረቄ ይዘዋል። ልጃቸው አስር አለቃ ገመቹ ወታደራዊ ልብሱን ለብሶ ከኋላቸው ተከትሏቸዋል። አባባ ቶሎሳ ከእሱ ኋላ ናቸው።

መንደርተኛው ሁሉ ብድግ አለ።

እማማ ጫልቱ አምላክን፣ ከዋክብቱን፣ ሣር ቅጠሉን ሁሉ በአማርኛም በኦሮምኛም እየጠሩ ያመሰግናሉ። መንደረተኛውም ለዚህ ላበቃቸው አምላክ አብሮ ምሥጋናውን ያቀርባል።

የሰፈራችን ትልልቅ ሰዎች ገለል ብለው፣ የአስር አለቃ ገመቹን ምቹ ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ጋበዙት። እሱ ተግደረደረ።

"ተቀመጥ... ተቀመጥ..." እዚያም-እዚህም የአክብሮት ሃሳብ ተሰነዘረ።

"እንዴ?"

"ተቀመጥ ተብለሃል። አሁን እኮ አንተ ትንሽ ልጅ አይደ ለህም።"

ተቀመጠ። አረቄ ቀረበለት። ሥጋው በትሪ፣ በሳህን እየ ሆነ በያለንበት ታደለን። ዘፈን ተጀመረ።

"ማ! ማ!" ግርማ ቢጨቤ ሲጣራ ከርቀት ሰማነው።

"እ ግርሚቲን ይዘን እንምጣና እያላቀ ያጫውተን" አለች መኩዬ ቀጫጫው።

"ትክክል!" አልኩና ዘልዬ ተነሳሁ።

መንገድ እንደጀመርን ሲሳይ ዝቺጥ ከማዶ ወደእኛ ሲመጣ እየነው። ሄድ እንዳልን ግርማንም ከወፍጮ ቤቱ አካባቢ ሲመጣ አገኘነው። ግርማ ቢጨን መልከፍ ትተናል። ልክ እንዳገኘነው በጨዋታና በቀልድ ያዝናናናል። ብዙ ጊዜ ቀልዱ በራሱ ገጠመኝ ላይ ያነጣጠረ ነው። ልክ አጠገቡ እንደደረስን ጨዋታውን ጀመረ።

"ዛሬ ልደታ አይደለችም? የልደታ ማርያም እንላታለን። በጠዋት ይህቺን ቆቤን አድርጌ ጋቢዬን ተከናንቤ ቂርቆስ አካባቢ ደረስኩ። ከቤተክርስቲያኑ ወዲህ ወይዘሮ እልፍነሽ የምሩ ጠጅ ቤት አጠገብ ያለው ቧንቧ ፈንድቷል። አማተብኩና ከቧንቧው ውሃ በእጄ አፈስ አረኩና ጠጥቼ ፊቴን ቾፍ አደረኩኝ። አንዲ ጠጋ አለችና 'አባ እኔንም ይርጨኝ!' አለችኝ።

"እንደፍቃድሽ ይሁን!" አልኩና ቾፍ! አደረኳት። ወዲያው

ቤተ ክርስቲያን ሲሳለም የመጣው ምዕመን ሁሉ ግልብጥ ብሎ መጥቶ እባ ይርጩኝ! አባ ይርጩኝ! ይል ጀመረ:: እኔ የቀልቤሳ ልጅ ለዚህች መች አንሼ! ውሃውን እያነሳሁ ፊት ፊታቸው ላይ ቾፍ! ቾፍ! አደረኩባቸው::"

በጣም ሳቅን:: የአባቱ ስም እንደ ጨዋታው አይነት ይቀ ያየራል:: በቀደም ሲያወራልን የደጃች ድፋባቸው ልጅ ነበር::

"የገረመኝ አንዷን ልጅ ሸግራና በቀኝ ጉንዋ ደግፊው ወደ እኔ አመጣት:: 'አባ እግሬን ይርጩኝ!?' አለች:: ሳያት አሳ ዘነችኝ:: "ውይ! እሱ አንድዬ መድኃኒት ያድርግልሽ! ብዬ እግሯ ላይ ቾፍ! ቾፍ! አደረኩባት:: ተነስታ ድክ ድክ እያለች ሔደች::

"ገርሞኝ አፍጥጬ ቀረሁ:: እምነቷ አዳናት!" አለና እየ ሳቀ፣" እናቴ ፈንጠር ብላ ይኼንን ተአምር ታይ ነበርና 'በል እኔንም እርጪኝ እምላክ በአንተስ አድሮ እንደሆን ማን ያው ቃል? ብላ አጉነበሰች:: እሷንም ቾፍ! አደረኩባትና ምዕመኑን ለነገ ቀጥሬያለሁ:: ሷንሏውን ውሃ ክፍል ካልጠገነው ነገም እሸቅ ልበታለሁ:: ሲል በኃይል በሳቅ አውካካን::

"ጠበል ስረጭ ልብሴ በስብሶ ነበር:: ምዕመኑ ቸር አይ ደል? ስሙኒም ሽልንግም አሰባስበው ቸሩኝ:: ቶሎ እንዲደርቅ ልኝ ካቲካላ ቤት ገባሁ::" ሲለን ተገርመን ተጠቃቀስን::

"ፋራ አትሁኑ እንጂ ሁለቱን መለኪያ ስለጋው አካሌ ጋለ:: ጠላታችሁ ክው ይበል! ልብሴም ክው አለ!" ሳቃችን በመንደራችን አስተጋባ::

ወደ አድባር ዝግጅት እንዲሳተፍ ስንጠይቀው ግርማ ቢጪ እምቢ አለ:: "አዳምጡኝ ከእነዚህ 'የኢኮኖሚ ግሬት ማጂክ' ከማ ይገባቸው መሐይሞች ጋር ተቀምጬ በግ አስር ብር ገባ እያልኩ የማማርር ይመስላችኋል? እኔ ጠጂንም ትሪፓዬንም ጥግብ ብዬ ነው የመጣሁት:: ወደ ቤት ብገባ ይሻለኛል::

"ግን በግ አልተወደደም ማለት ነው? ከድሮውና ከአሁን::" አለችና መኩዬ ቀጫጫ ጠየቀች::

"ፋራ አትሁኑ! ሁሳችሁም ልጆች ስለሆናችሁ በደንብ ልን ገራችሁ:: በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ቁጥር አንድ ሚሊዮን ደርሷል:: እነዚህ ፋራዎች ግን የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ መቶ ሺ በነበረ ጊዜ የገዙትን የአምስት ሽልንግ በግ ዘለ ዓለም ያወጋሉ:: ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ስንት እን ደሆን ታውቃላችሁ?" ግርማ ቢጪ ጠየቀን::

እኔና ነቢጥ ልክ ክፍል ውስጥ እንዳለን ሁሉ እጃችንን አወጣን::

ግርማ እኔ እንድመልስ ጠቀሰኝ::

"25 ሚሊዮን ደርሰናል" አልኩ::

"ብራቮ! አሪፍ 'ማይንድ' አለሽ! ከሃያና ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላስ?" ሲለን ግርማ ቢጪ ማንኛችንም መመለስ አል ቻልንም:: "ልጆች ጋዜጣም፣ መጽሔትም ስታገኙ አንብቡ እንጂ:: 'ቲንክ!' ማድረግ ትማሩበታላችሁ:: አንድ ጥይት ጋዜ ጠኛ አለ:: ስሙ ብርሃኑ ዘሪሁን ይባላል በቅርቡ በጻፈው ድንቅ ጽሑፉ ሲተነብይ ሕዝባችን በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ከ50 እስከ 70 ሚሊዮን እንደምንደርስ ይገመታል::"

ተገርመን ተያየን::ግር መሰኘታችንን ያስተዋለው ግርማ ቢጪ "ገበዝ እመኑ ትድናላችሁ" ሲለን በሳቅ አውካካን::

"በሉ እኔ አድባራችሁጋ እልቀላቀልም:: ቻው!" ሲለን ግርማ ሲሳይ ነቢጥ እጁን ይዞት "እንዴ ጀግና ትውዳለህ አይ ደለም እንዴ? አስር አለቃ ገመቹ መቷል እኮ ሰላም አት ለውም!" አለ እየጐተተው::

"እ! ማይ አኒባል! ማይ ግሬት ሂሮ!' እሱንማ እጅ ልነሳው የግድ ነው! እሱ ካለ አድባር አውጋሩን እቀላቀላለሁ" አለና ወደ አድባሩ ታዳሚ እብሮን ማዝገም ጀመረ:: "እሱና ጓዶቹ እዚያ በረሃ ላይ ዘብ ባይቆሙ እኔም ሽቀላዬን እናንተም የበግ ቆለ ጣችሁን አጥተን ዳሩ መሐል በሆነ ነበር:: የታለ አኒባል! የአስር አለቃ ገመቹ የት ነህ?!" ብሎ ግርማ ቢጪ ጮክ ብሎ ተጣራ::

ገመቹ እየሳቀ ከተቀመጠበት ተነሳ:: ግርማ ቀጥ ብሎ ቆሞ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጠው:: ሰው እውካካ:: ዘሉ ተጠመጠመበት:: ታዳሚው በደስታ በድጋሚ ተሳሳቀ:: "እንዴት ነው:: ብዙ የምና ወራው እለ 'ማይ አኒባል' ስለ አጋዴን ጦር ውስጥ:: ስለ አጋዴን ቤንዚን ቁፋሮ! ሌላም ሌላም" አለ ግርማ አጠገቡ እየተቀመጠ::

የአጋዴን ቤንዚን ፍለጋ ሲል ልጆቹ ተጠቃቀስን:: አን ዳችም ቃል ትንፍሽ አላልን:: ብንናገር የሚመጣብንን መዘዝ እሳምረን እናውቀዋለን:: ስለዚህ ፀጥ ብለን ወሬውን ለመከታመከም ጆሮዎቻችንን ከፈትን::

"ቆይ!" አባባ ቶሎሳ ጮኹ::

ፀጥ ተባለ::

"ይኸው የዚህ የልጅ ጉዳይ እንቅልፍ ነስቶኝ፤ ሌት ተቀን ለአምላክ ስለምን ነበር:: አድባሩም አውጋሩም ረድቶኝ በዓይነ ሥጋ ለመተያየት አበቃን:: ስለዚህ፣ የተሳልኩት እንድ ሊትር ነጭ አረቄ ይኸው!" አሉና ከማማ ጫልቱ እጅ ተቀብለው ለዕ ድምተኛው አቀረቡ:: እልልታው ቀለጠ:: ሁሉም የተሳለውን አቅ ርቦ ዘፈኑ ተጀመረ::

እሰይ! ሰለቱ ሰመረ፣ እሰይ! ሰለቱ ሰመረ...
ዓለምነሽ ማውረድ ጀመረች::
ተቀብልናት "እሰይ ሰለቱ ሰመረ፣ እሰይ! ሰለቱ ሰመረ"
አምና ይኼን ጊዜ ተሰዶው ነበረ
እሰይ! ሰለቱ ሰመረ፣ እሰይ! ሰለቱ ሰመረ

ኪስ አበደች

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰላለፍ፣
አንድ ጌታቸው አበበ (ዱላ) ሁለት አለማየሁ ፊኖ..."
ሰለሞን ተሰማ

"የቡድንና የቡድን አባቶች::"
"ከምንና ከምን?!"
"ከሰማይ በራሪ ከምድር ተሽከርካሪ!"

ከቡድን አባቶች አንዱ "የሰማይ በራሪ" ሲል የተመረጠው ተጫዳኝ ወደ መረጠው የቡድን አባት ይሄዳል:: ሌላኛው ወደ ተቃራኒው የቡድን አባት ሄዶ ይቀላቀላል::

"ከቦንብና ከመድፍ::"
"መድፍ" አለ የቡድን አባት እየሳቀ::

የቡድን አባቶቻችን የሚሆኑት ልጆች ታላላቆቻችን ናቸው:: ጉርምስናው በጀማመራቸው ወቅት ላይ ነው የሚገኙት:: ከተጣሉ በመደባደቡ አይሸናነፉም:: ገሃድ ወጥቶ አይነገር እንጂ እርስ በእርስ ውስጥ ውስጡን ይፈራራሉ:: የመፈራራታቸውን ያህል፣ የተጣሉ እንደሆን ፀቡ በቀላሉ የሚበርድ አይደለም::

ዛሬ የቡድን አባቶቻችን ቦቸራና ዶጅ ገማጣው ናቸው:: ሁለቱም ኃይለኞች ናቸው:: ቦቸራ በባሕርዩው አትንኩኝ ባይ የሠይጣን ቁራጭ ሲሆን፣ ዶጅ ገር መልአክ ነው::

ቦቸራ በጥቁርና ጠንካራ አካሉ ላይ የድል አድራጊነት ስሜት ይታይበታል:: የእሱ ቡድን ከተሸነፈ ሰይጣኑ ይነሳበታል:: በዚህ ጊዜ መጀመሪያ ምንም ያህል ያልተጫወትንባትን አዲሷን ኪስ ያፈነዳታል:: ከዚያም ለቡድኑ መሸነፍ ምክንያት የሆነውን ልጅ አሳዶ የገባበት ገብቶ ይወገረዋል:: ልጁ ካመለጠው ሲያገኘው ነፍስ ከሥጋው እስከሚለይ አሳሩን እንደ ሚያሳየው እየጮኸ ይዝታል:: ከአሸናፊዎቹ ልጆች ጋር ለመ ጣላት 'ፀብ ያለሽ በዳቦ' የሆነ ባሕርዩውን ያሳያል:: ተቃራኒው ቡድን ሲያሸንፍ በደስታ ያጨበጨበውን ልጅ በአጠገቡ ሲያልፍ በጠረባ ይዘረጋዋል::

ተመቺው ልጅ "ተው! እንጂ እኔ ምን አደረኩህ? በጥ ልበትህ አምላክ! ወንድ ከሆንክ ዶጅን አትመታውም?" ይላል ከዳግም ምት ለመከላከል እየሸሸ፣ አቧራውን እያራገፈ::

"ይምጣ!" ይላል ቦቸራ ወደ ዶጅ ገማጣው እያፈጠጠ:: ዶጅ ሳይወድ በድንገት ለፍልሚያ ራሱን ያዘጋጃል:: የስፖርት ሜዳው ወደ ጦር ሜዳነት ይቀየራል:: እንደ እኔ አይነቱ ደቃቃ ከዚህ አካባቢ የሚሸወረው በዚህ ሰዓት ነበር::

ይህ አይነቱ ሽብር በተለያየ ወቅት የሚያጋጥም ቢሆንም፣ በሚቀጥለው ቀን የትናንትና ፀባችንን ረስተነው በአዲስ መንፈስ ተጫዳኝን፣ በአዲስ ስሜት መጫወታችንን እንቀጥላለን::

ሁላችንም፣ ችሎታችንንና የጓደኞቻችንንም ብቃት አሳም ረን እናውቀዋለን:: ገና መጫደን ስንጀምር አረፍቱን ልጆች የራስ ቡድን አባል ለማድረግ ኃይለኛ ሽኩቻ ይጀመራል:: የቡድን አባቶች ቀደም ብለው ከአሪፉ ልጅ ጋር በምስጢር ተስማምተው የራሳቸው አባል ሲያደርጉት ቀድሞ የነቃው የተቃራኒ የቡድን አባት ባለመስማማት አንጃ ግራንጃ ይገጥማል::

ይህ አይነቱ ንትርክ የሚነሳው በተለይ አሸናፊ ፔሌን ለመ ምረጥ ነው:: ቦቸራ የማጥቃቱን ተግባር ለፔሌ ሰጥቶ መከላ ከሉን ራሱ መያዝ ይፈልጋል:: ዶጅ ገማጣውም በእጨዋወት ስለሚግባቡ የእሱ ቡድን አጥቂ እንድትሆን ፔሌን ይመርጣል::

ፔሌ ሁለገብ ተጫዋች ነች:: ከፍተኛ የግብ ዕድል አላት:: ሲያሰኛትም ግብ ስር ደርሳ *ሞሳ ትሠራለች:: *ፍጥር ማንም አይችላትም:: ፔሌ በእግር ኳስ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ስፖርት አሪፍ ነበረች:: በማራቶን ከቂርቆስ ተነስቶ ጎተራ ነክቶ በመ መለስ 'አኅንስ' ሰጥታን ተሽቀዳድማ ብዙ ጊዜ የሰፈራችን ሻም ፒዮን ሆናለች:: በአከሮባት፣ በዋና... ኮከባችን ነች:: በድብ ድብም ከአውራዎቹ በቀር ሌሎቻችንን ታስገብራለች::

ጢቢ ጢቢ በምትጫወትበት ጊዜ ሺ ቤት አይጠቅማትም:: ጨዋታው ጠዋት ቢጀመር አብሯት የሚጫወተው ልጅ ለምሳው ቤቱ ደርሶ ቢመጣም ፔሌ ሳትፎርሽ ያገኛታል::

ከእኛ መካከል እሷን ማሸነፍ የሚችለው ኮሚኩ ቀጢሳው ብቻ ነው:: ጢቢጢቢውን መምታት ስትጀምር ቀጢሳው መቀለድ ይጀምራል:: እሷም በፈጣን ስልት የምትመታውን እየቆጠረች "እሪፍ! አርባ! ባ አንድ፣ ባ ሁለት... ትቆጣለች" በቁጣዋ ውስጥ የሳቅ ድባብ አለ::

ቀጢሳው ቁጣዋን ሰምቶ እንዳልሰማ ኩምከናውን ይቀጥ ልበታል:: ፔሌ ዘርዛራ ጥርሷ መታየት ይጀምራል:: እግሯ ቅል ጥፍናው እየከዳው ዝግ ማለት ትጀምራለች:: መቁጠሩን ትሳ ሳታለች፣ ትፎርሻለች::

መጫደኑ እንደቀጠለ ነው:: ፑሉቶና ዲዲ ተጫዳኙው መጡ:: ሁለቱም ልጆች ጥልቅ የኪስ ፍቅር አላቸው:: ፑሉቶ የአራተኛ ክፍለ ጦር ጨረቃ በር ቡድን ደጋፊ ነው:: ዲዲ የክብር ዘበኛው ቡድን አፍቃሪ በተለይ 'ኪስ ፊደሉ' የተባለውን ተጫዋች አድናቂ ነው:: ሁለቱም በአዘቦቱ ቀን እንኳን የሚ ለብሱት ወደ ኪስ ሜዳ እንደሚሄድ ተጫዋች ነው:: የትምህርት ቤት ዩኒፎርም ለመልበስ ቢገደዱ ገንባሌ ማጥለቁን አይረሱትም::

*ሞሳ እና ፍጥር፣ በኪስ ጥበብ የግል ችሎታ የሚታይበት ነው::

ሁለቱም የቡድን አባቶች ሳይነታረኩ አንድ አንድ ልጅ ወሰዱ። ቀጢሳው ፀጉሩን ተሳጭቶ የአባቱን ነጭ መለዮ አድርጎ ነው የታደመው። ዛሬ የፊለገው መጫወት ሳይሆን ተመልካች መሆን ነው። ከተጫወተ የአባቱ መለዮ ይቆሽሻል። መለዮውን በአደራ ለመስጠት ማንኛችንንም ያንን የመሰለ ንፁህ መለዮ ንፅህናውን ጠብቀን ለማቆየት አ☺መጥንም። የቡድን አባቶች የመከላከል ብቃቱን ስለሚያውቁ እንዲቧደንና እንዲሳተፍ ገፋፉት። ከአበረ ሻቃ ጋር ተቧድኖ ቀረበ። ቀጢሳው ለቦቸራ ቡድን ተሰለፈ። ቀጢሳው ፈሪ ስለሆነ ኳስ ሳያባክን በጥንቃቄ መጫወቱን ይችልበታል። ምርጥ ተከላካይ ቢሆንም ሁለገብ ተጫዋች ነው። በእሱ ስህተት ከዶጅ ገማጣው ጋር የተወራረደው ቦቸራ ስሙኒው ከተበላ ወየውለት!

ዳዊት ምች፣ አመዶ፣ ተረፈ ገልጆ፣ ጎቢጥ እየተቧደኑ ቀር ብው በተመረጡበት ቡድን ተሰለፉ። ምችና ገልጆ ጎበዝ ጎልኪፐሮች ናቸው። ሁለቱም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በረኛ ጌታቸው ዱላን መብለጥና በዓለም አንደኛ ደረጃ በረኛ መሆን ታላቁ ሕልማቸው ነው። አይደለም ራስ ብሩ ሜዳ ሣር ላይ አስፖልትም ላይ ቢሆን ተፈጥፍጠው ኳስ ይቀልባሉ።

ዳኛው አለማየሁ ነው። ከቡድን አባቶቹ ጋር ይከባበራሉ። የሚፈርደውም ስለደንብ ብሎ መሆኑን ሁለቱም የቡድን አባቶች ያምኑበታል። ገራጅ አየሠራ ፍራንክ እንደልቡ ስለሚያገኝ ለገን ዘብ አይንገበገብም። ዲናሬ ከኪሱ አወጣና የጎል አቅጣጫ ለማ ስመረጥ "ከዘውድ፣ ከጎፈር?!" አሳቸው።

"ጎፈር!!" አለ ቦቸራ።

አለማየሁ ሣንቲሚን ሽቅብ በአውራ ጣቱ ለጋት። ተቃጭላ መሬት ወደቀች። ዘውድ ታየ። ዶጅ ገማጣው የጎል አቅጣጫ መረጠ። ውሮና ሴምላል፣ የመስመር ዳኛ ሆኑ። ጨዋታው ተጀመረ። እኔና መኩዬ ቀጫጫው፣ ኮት ጠባቂዎች ሆንን። ብዙ ኮት ደራርቤ ለብሼ መፃጉ መስያለሁ።

ተጨዋቾቹም ሸራ ጫማቸውን ማጠባበቅ፣ በረባሶአቸውን ለጨዋታው ያመጥናል አይመጥንም እያሉ መመዛዘን ይዘዋል። አንዳንዶቹ ማንነቻቸውን ቆጣጥረው ቦታ ቦታቸውን ይዘው የጨዋታውን መጀመር አካላቸውን እያፍታቱ ይጠባበቃሉ።

አሸናፊ ፔሌ በረባሶዋን አውልቃ ወደእኔ እየወረወረች "ጎንጌ ጠብቅልኝ!" ስትለኝ፣ እንደ ጎልኪፐር እየተወረወርኩ ቀለ ብኳቸው። የራሴን ችሎታ ስገምተው ጎበዝ በረኛ ይወጣኛል። ኳስ ጨዋታ ብወድም፣ኳሷ እግሬ ስትገባ፣ የእኔ ቡድን አባል "አቀብለኝ!" እያለ ሲጠራኝ የተቃራኒው አባል ሊነጥቀኝ ሲንደረደር፣ እኔ ኳሷን ምን ሳድርጋት እያልኩ ስጨነቅ እነጠቃለሁ። ከቡድኔ አባላት ወቀሳ ይደርስብኛል። ተቧድኜ የቡድኑ አባቶችን ጋ ስቀርብ እኔን ላለመምረጥ ሲጠቃቀሱብኝ አያለሁ። ተጨዋች

ከጠፋ እኔን የሚመርጡኝ ለበረኝነት ብቻ ነው። ልጆች ከተት ረፈረፉ ግን የኔ ፋንታ ኮት ጠባቂ መሆን ነው።

እኔ ደግሞ ለራሴ አስደሳች የሆነ የጨዋታ ሥልጣን እሰጠውና እንደ ስለሞን ተስማ ወይም ነጋ ወልደ ሥላሴ የጨዋታውን ጥበብና ስልት ለሬዲዮ አድማጮች አስተላልፋለሁ።

ጀርባዬን ለራስ ብሩ ቤት ሰጥቼ ጉብታ ላይ ተቀመጥኩ። አንዱን የኮት ጫፍ እንደማይከራርን አፈ ላይ ደገንኩ። "አድማጮቻችን፣ የጨዋታውን አካሔድ በጊዜያዊ ስቱዲዮዋችን የምና ስተላልፍላችሁ! እኔ ስለሞን ተሰማና ነጋ ወልደሥላሴ ነን" ስል፣ መኩዬ ቀጫጫው ጭኑን እየፎከተ "እኔ ሰለሞንን ልሁን፣ አንተ እንደነጋ ሆነህ ጀምር።"

"እሺ!" አልኳት። ተጨዋቾቹን እያየሁ "ጨዋታው ሊጀመር ነው። የመሐል ዳኛ አለማየሁ ገራጅ ናቸው። የመቻሉ አምበል ዶጅ ገማጣውና የጊዮርጊሱ አምበል ቦቸራ ተሰማ አርማ እየተለዋወጡ ነው።

"በመጀመሪያ የተጨዋቾቹን አሰላለፍ እንገልጻለን። የመቻል አንድ ዳዊት ምች፣ ሁለት ኃይሉ ዶሮ፣ ሦስት ተስፋዬ ገበሎ፣ አራት ቁጥር ለብሶ በስምንት ቦታ እሚጫወተው ፑሉቶ ሲሆኑ..." ስል፣ ፑሉቶ ተደስቶ እያፏጨ አካላቱን አፍታታ። መኩዬ ቀጫጫው ጣልቃ ገባና "ዶጅ ገማጣው ለምን ገማጣው እንደተባለ ግለጽ።"

"አድማጮቻችን፣ የመቻሉ አምበል ዶጅ ለምን ገማጣው እንደተባለ እንድገልጽ ሰለሞን ተሰማ አስታውሶኛል። ዶጅ ድሮ በልጅነቱ ጠቅላይ ግዛት እያለ በግ ሲያግድ ጅብ መጥቶ በጎቹን ሊበላበት ሲል፣ ለመከላከል በግራ እጁ በጦር ሊወጋው ወረወረ። ጅቡም ተናዶ ግንባሩን ግምጥ አደረገው! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ገማጣው ባባቱ መጠራቱ ቀረ..." ይሆንን ስል ሁሉም ልጆች ሳቁ።

ራሱ ዶጅ ገማጣው እየሳቀ "ስደባደብ ተፈንክቼ ነው እንጂ ጅብ ገምጦኝ አይደለም" አለ።

"አስተያየቱን ተቀብለናል" ዳኛው ፊሽካ ነፍተዋል። ጨዋታው ተጀምሯል። የጊዮርጊስን ተሰላፊዎች በቆይታ እናስተዋውቃለን። ለማንኛውም፣ አጥቂ- አሸናፊ ፔሌ፣ ሁለገቡ አምበል ቦቸራ ይገኛሉ።"

ገልጆ "ጎንጌ፣ እኔንስ ጌታቸው ዱላን እሚበልጠው ተረፈ ገልጆ አለ አትልም?"

"አድማጮቻችን፣ ታዋቂ ጎልኪፐሮቻችን እናስተዋውቃለን" ስል ገልጆ ከደስታው ብዛት ስሙን ሳልጠራው ሜሩ ላይ እየተገለባበጠ ይፈነጥዝ ጀመር። "የወደፊቱ የአገራችን የኢትዮጵያ ተስፋ ተረፈ ገልጆ ገልጃጃው! በዚህ ጨዋታ ተሰላፊ ነው። አሁን ደግሞ ጨዋታውን ሰለሞን ተሰማ ያስተላልፍላችኋል" አልኩና ለመኩዬ ቀጫጫው ቦታ ለቀቅኩ።

"ጎጋ እንዳለው ጨዋታው ተጀምሯል። ኪስ ወደ ሰማይ ሄዳለች። ቦቸራ ዘለለ። በቴስታ የመታት ኪስ ለአሹዬ ፔሌ ደርሳለች። ፔሌ በደረቷ ተቀብላ እግሯ ላይ አበረደቸ። ፔሌ! እያታለለች ነው። ገማጣውን አስፈች። አመዶን *በላይነን ሸመ ደች። አደጋ ነው! አደጋ ነው! መታች። አ! ዳዊት ምች ተወር ውሮ በቀላሉ ኪሷን ጎረሳት።

"የመቻሉ አምበል ቡጅኑ እንዲረጋጋ እያበረታታ ኪስ ከምች ተቀብሏል። ኪስ ሰጋ። ለቀጢሳው ደርሶታል። ኪሷን በረጅም ቅልጥሞቹ እያንከባለለ ተጨዋቾቹን ያማትራል። ዶጅ ተጠጋ። ነጠቀው። አሸናፊ ፔሌ ተሚሙታ ነጠቀችው። ፔሌ እያታለለች ነው። አ! እያጣጠፈች ነው። ሰቦቸራ አቀበለችው። ቦቸራ ዶጅን አልፎ ለፔሌ መለሰላት። ፔሌ ኪስ ይዛለች። አመዶ እግሩን ደነቀረ። አለፈችው። መታች። ጎል!"

እኔ በአድናቆት ሜዳው ላይ ተገለባበጥኩ።

"የጊዮርጊስ ቡድን አንድ መቻል ዜሮ። አሁን ደግሞ ጨዋታውን ጎጋ ያስተላልፍልናል!" አለችና መኩዬ ቀጫጯው እኔ እንድዘግብ ተራውን ለቀቀልኝ። ጨዋታውን በራዲዮ ስናስተላልፍ በወቅቱ ዝነኛ በነበሩት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ስምም ልጆቹን እንጠራቸዋለን። ይህ በጣም ያስደስታቸዋል።

"ጨዋታው እየተፋፋመ ነው። የጊዮርጊስ ደጋፊዎች ችቦ ለኩሰዋል። ጭፈራው ጦፏል። የመቻል ደጋፊዎች ማታ ነው ድሌ' እያሉ ነው። ገማጣው ለጎቢጥ፣ ጎቢጥ ለፑሉቶ፣ ፑሉቶ መልሶ አቀበለው። ጎቢጥ ለገማጣው ሰጋ። ገማጣው እያንከባለለ ለአብነት ባሪያው፣ አያየ! ለጎቢጥ። ጎቢጥ ሰጋ ጎል!

"አስኪ ቆይ፣ የጊዮርጊስ አምበል ጎል አይደለም ብሎ እየ ተከራከረ ነው። የመሐል ዳኛው የመስመር ዳኛ የሆኑትን አቶ ሴምላልን ጠየቋቸው። ሴምላልም ንፍጣቸውን ሽቅብ ሳቡና ጎል ነው ብለው መለከሩ። ቦቸራ እየተሳደበና እየጮኸ ተጨዋቾቹ ነቅተው እንዲጫወቱ አዘዘ። ጋዜጠኞቹንም አንዴ ነረመመን። ዳኛው አለማየሁ ብርሃኑ ጎልዋን አፀደቋት።"

ቦቸራም ሴምላልን በነብር ዓይን አየው። ሴምላል ዓይኖቿ ወደ ፍየል ዓይን ተቀይረው የሚገቡበት አጡ።

የቦቸራ ቡድን ከተሸነፈ ሰይጣኑ ይነሳበትና መጀመሪያ ለመስዋዕትነት የሚቀርበው ሴምላል ይሆናል። ሴምላል ነቄ ከሆነ ጨዋታው ከመጠናቀቁ በፊት ከራስ ብሩ ሜዳ መሰወር ይኖርበታል።

ቦቸራ ወደእኛ አካባቢ እያፈጠጠ "አንት ቀጫጭ! የአኔን

*ላይነን፡ በተቃራኒ ቡድን ተጫዋች በእግርና በእግሩ መሐከል ኳስ ማሳለፍ።

ቡድን ለመሸቀብ ነው ግራ ቆሰጥህን ይዘህ የተቀመጥከው?" ብሎ መኩዬ ላይ ጮኸባት።

በእኛ እምነት መሸቀብ የፈለገ ልጅ ቆለጡን ይይዛል። እንዲሸነፍ የፈለገው ቡድን በግራ ጎል በኩል ከተሰለፈ ግራ ቆለጡን ይይዛል። በቀኝ ጎል በኩል ከተሰለፈ ቀኝ ቆለጡን ይይዛል።

እኔ ቶሎ ብዬ እጆቼን ከጭኖቼ አካባቢ አራቅሁ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ እጆቼን የማደርግበት አጣሁ። መሬቱን ብመረኮዝ "እኔ በመሸነፌ ደስ ብሎህ ነው የምትዝናናው?" ብሎ ይመታኛል።

"አረ እኔ አንተን ለመሸቀብ አይደለም" አለች መኩዬ በተጨነቀ ድምፅ። "ቆለጤን ደግሞ አልያዝኩም። መሬት በቂጤ ተቀምጬ ሽንቴን እየሸናሁ ነው። ከፈለክ ፉንጌ ምስክሬ ነው። ናና ሽንቴን እየው!"

እኔም ጭንቅላቴን በመወዝወዝ መሰከርኩ። ግን ማን አምኖኝ? ሁለታችንም በሬዲዮን ለአድማጮቻችን የምናስተላልፈውን ጨዋታ አቆምን።

ጨዋታው ተጀመረ። ፔሌ የሰጋት ኳስ በቀጥታ ለቀጢሳው አናት ለቴስታ ተመቻችታ ደረሰች። ቀጢሳው በቅልጥፍና የአባቴን ነጭ መለዮ ከአናቱ ላይ አወለቀና በቴስታ ኳሷን መታና ጐል አግብቶ መለዮውን በዚያው ፍጥነት መልሶ አናቱ ላይ አደረገ።

ቅልጥፍናው ሁላችንንም አሳቀን። ሜዳው ውስጥ ሰፍኖ የነበረው አሰፈሪ ውጥረት ረገበ። እየሳቅሁ ዞር ብዬ አያለሁ፣ መኩዬ ቀጫጯው ከአካባቢው ተሰውራለች። መሬት ተሰንጥቆ ይዋጣት፣ ወይም ሰማይ በርራ ጥልቅ ትበል አላወኩም።

ፔሌ በቀጢሳው ኩምክና ተማርካ፣ ኳስ እግሯ በገባ ጊዜ ደጋግማ በቴስታ እንዲመታ ትልክለታለች። ቀጢሳው እንዳስ ለመደን እየኮመከ በቴስታ ይሊጋና መለዮውን ጭብጥ በማትሞላ አናቱ ላይ ያደርጋል።

ይህ ሳቅ የተሞላበት የአጨዋወት ስልት ቦቸራን አልጣመውም "ስሚ ፔሌ! ስሙኒዬን ልበላና ሰጋሽን ነው የምበላው!"

ከደቂቃዎች በፊት የተገላገልነው አሰፈሪ ድባብ እንደገና ሜዳው ላይ ሰፈነ። እልህ በተሞላበት ስልት ጨዋታው ቀጠለ። አንዱ ሌላውን ጠልፎ ይጥላል። ተጠላፊው እየተንጫነጨ ዳኛው እንዲያስተውል ይከሳል። ዳኛው በቆራጥነት እየመራ ነው። ጨዋታችንን እንዲህ አሰፈሪ ድባብ ሲውጠው ድባቡን ለነገ የማስ ተላለፍ ኃይል ያላት ዐሐይ ብቻ ነች። ዐሐይ ስትጠልቅና በተራው ጨለማ ሲነግስ ኳስ የሄደችበት አቅጣጫ ሲጠፋ በይደር ጨዋታውን ማስተላለፉ የግድ ይሆናል።

የዛሬውን ጨዋታ ግን ማስተላለፍ አንችልም። ሰዓቱ ገና ዘጠኝ ሰዓት ቢሆነው ነው። ምሳ አልበላንም። ጨዋታችንን ሰዓት አይገድበውም፣ ድል እንጂ። የገማጣው ቡድን እንደ አንድ ሰው ተባብረው እየሠሩ ነው። ስማቸውን በልቤ እየጠራሁ እከ ታተላለሁ። በቃል መጥራትና ለአድማጭ ማስተላለፉ አደጋ አለው።

ከአስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አቅጣጫ መኩዬ ቀጫጭው እየሮጠች ስትመጣ አየኋት። የጀሥራች እንደምትናገር ሁሉ ፊቷ ጥርስ ሆኖዋል። አካባቢያችን እንደደረሰች "ልጆች!" አለች ጮክ ብላ። ማንም የለማት የለም።

"ልጆች፣ አባባ ጃንሆይ አስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን በር ላይ ለሰዎች ብር እየሰጡ ነው!" ብላ ታላቁን ዜና አብስራን በመ ጣችበት ፍጥነት ወደ ቤተክርስቲያኑ አቅጣጫ ሮጠች።

እኔ የሰማሁትን የምስራች ጮክ ብዬ ለፈፍኩ። ጨዋታው ተቋረጠ። እኔም መኩዬን እየተከተልኩ ኮት ለሰጠኝ ኩቱን፣ በረ ባሶውን አደራ ላለኝ በረባሶውን እየመለስኩ እሮጣለሁ። በእንዲህ መልኩ የአባባ ጃንሆይ መልካም መንፈስ አስፈራውን የኳስ ጨዋ ታችንን ደባብ አስወገደልንና ወደ ሰላም የሕይወት ትዕይንት ተሸጋገርን። ኳሷም ከማበድም ከመፈንዳትም ዳነች። ሙሉ ትኩ ረታችንን የጃንሆይ ብር ማደል ስለገዛው ኳሳችንን እዚያው ራስ ብሩ ሜዳ ረስተናት ነበር።...

አባባ ጃንሆይ

አባባ ጃንሆይ! አባባ ጃንሆይ! የእኛ እናት አባት!
አሳድገውናል አሳድገውናል በማር በወተት!
ልጆች ሆንን ከዘመርነው

አስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ከአፍ እስከ ገደፉ በሰዎች ጢም ብሏል። የሰማይ ሰባሪ የሚያካክሉት የክብር ዘበኞች ትርምሱን ተቆጣጥረውታል። ሕዝቡ ፀጥ ብሎ ባለበት መሬት ላይ ተቀምጠ በቅደም ተከተል አባባ ጃንሆይ ዙፋን ድረስ በመቅረብ አንድ ብር ይሸለማል።

ጃንሆይ ወታደራዊ ልብስ ለብሰዋል፣ ልዑላን፣ ልዕልታት፣ መሣፍንትና መኳንንት በግራና በቀኝ መድረኩ ላይ ከበዋቸዋል።

መስኩ ላይ እንደ ቴያትር ተመልካች እኔና አብሮ አደ ጎቼ፣ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ሰዎች ተቀምጠን ሽቅብ እናያቸዋ

ለን። ከጃንሆይ በስተቀኝ አንድ መኳንንት በኮሮጆ ብዙ ብሮች ይዘው አንድዋን ብር ነጥለው ለንጉሡ ይሰጧቸዋል። ጃንሆይም ተቀብለው ከፊታቸው ለሚገኝ ትልቅ ሰው ወይ ልጅ ይሰጣሉ።

ድርሻውን እንደተቀበለ ለዋ ብሎ እጅ ነስቶ ከግቢው ይወ ጣል። የሚቀጥለው ዜጋ መድረክ ላይ ሲወጣ ያችው አንድ ብር ትደርሰዋለች። አንዳንዱም ወረፋው እስኪደርሰው ተሽቀዳድሞ የጃንሆይን ጫማ ይስማል። ጫማቸው ቀይ ሆኖ በጣም ትልቅ ነው፤ ሳይሰፋባቸው አይቀርም።

ግፊያው፣ ፍትጊያው፣ እንዱ በሌላው እግር ላይ መቆሙ፣ ጫጫታው አካባቢውን ገበያ ቢያስመስለውም፣ ከክብር ዘበኞቹ ቁጥጥር በላይ አልሆነም። ይሁን እንጂ የተሳካለት አጭበርባሪም አልጠፋም። የቁልጭ እናት ነጠላ እየተከናነበችና እያገለደመች ሦስቴ ተቀብላለች። ለአራተኛ ጊዜ ስትመጣ ክብር ዘበኞቹ ደር ሰውባት ወደ ቅጥሩ ድጋሚ እንዳትገባ አገዷት። እሷ ግን "ንጉሠ ነገሥቱ ለሰጡት የእናንተ መመቅኘት ምን ይባላል?" ብላ ድጋሚ ለማጭበርበር እየጣረች ነው።

ከአጠገባችን አንድ ፀጉረ ሸበቶ ሰው ነጭ በነጭ ለብሰው ቁጭ ብለዋል። ጃንሆይን ትኩር ብለው እያዩ የዘለዓለም ሕይ ወት ይመኙላቸዋል።

"አሁን እርሶ ምን አጥተው ነው ከሕፃናቱ ጋር የሚ ጋፉት?" አላቸው በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ የክብር ዘበኛው።

"እንዴ! ከንጉሤ እጅ የምቀበለው በረከትስ? የብሩ መብ ዛትና ማነስ አይደለም ቁም ነገሩ ልጄ። ትልቁ ነገር ከጠቅል እጅ የምቀበለው በረከት ነው። ለብሩማ የተፈረን ዕድሜ ያር ዝመው ሞልቶኛል" ሲሉ፣ በአመላለሳቸው የረካው የክብር ዘበኛ ከበረከቱ እንዲቋደሱ ቅድሚያ ሰጣቸው።

የእኔም ብር ሲኒማ የማልገባባት እንደሆነች የገባኝ እዚያው ሆኜ ነው። ወሬውን ቤተሰቦቼ ቀድመው ስለሚሰሙ ብሯ ለበረ ከት ትፈለጋለች። በምትኩ ሌላ ብር ይሰጡኛል።

በኳስ ጨዋታ ላይ የነበርነው ልጆች ጠረን ይተነፍጋል። አሷራ አሷሯ እንሸታለን። እንዳንነሳ ክብር ዘበኛው በእርጩሜ ስለሚዠልጠን ተፋፍገን ተቀምጠናል። ከግዶ ልዑላን ልጆች ቁልቁል አፍጠው ያዩናል። ንፍጥ በአፍንጫቸው ላይ የለም። በልካቸው የተሰፋላቸው ልብስ የአካላቸውን ውበት የበለጠ አጉል ቶታል። በነጭ ካልሲ፣ ቆዳ መጫሚያ አድርገዋል። ፀጉራቸው ላይ ቅባቱ ያብለጨልጫል። ፎሮፎር፣ ቂቁቻ፣ ቆረቆር፣... ሲያ ልፍም አልነካቸውም።

እኛ ፀጉሯችን ነጫጭባ፣ አካላችን ለዓመት በዓል ብቻ የሚታጠብ፣ ቀጭ፣ ሙጃሌ፣ ችፌ መለያችን ነበሩ። ብዙዎቻ ችን በባዶ እግራችን ነው የምንኳትነው "እቤት ልብሳቸው ሲያ ምር" አልኩ ለራሴ ያህል።

"ጫማቸውስ?" ሲል ቀጪላው ጠየቀኝ።

"ደሞ ቆንጆዎች ናቸው!"
"የአባባ ጃንሆይ ልጆች ለለሆኑ እኮ ነው::"
እንድ ቀን እኔ አባቴና እናቴ እንዴት እንደተነናነንን ለቀጢላው አጫወትኩትና "እነሱንም ልውሳኑን አባባ ጃንሆይ ከቅዱ ሳኑ ላይ በብዙ ብር ገዝተዋቸው ነው ማለት ነው" ብዬ ለቀጢላው ላወራለት እሱም ተገርሞ ሲያዳምጠኝ ወረፋችን ደረሰ::
ጃንሆይ አካባቢ በጣም ቅረብኩ:: ቅንድቤ ግጥም መሆኑ ትውስ አለኝ:: እማማ ረታሽ አንዳንድ ቀን ሲያስፈራሩኝ "እይ ፋንጋይ! ጃንሆይ ቢያገኙህ ለሆረው ቆሪጥ ሽክ! አርገው ይገብሩህ ነበር!" ያሉኝ ትውስ አለኝ:: ግን ወደ ኋላ መመለስ አይቻልም:: በግራም በቀኝም በልጆች ተከብቤያለሁ:: ክብር ዘበኞቹ አፍጠው እያዩን ነው:: ግን ደሞ አዲሷ ብር አማለለችኝ:: ጃንሆይን በጣም በጣም ቀረብኳቸው:: ተራዬ ደረሰ:: አንድ ብሩን ሲሰጡኝ ተቀበልኩ:: ፊት ለፊት ተያየን:: ጃንሆይን ሲያዩዋቸው ደስ ይላሉ:: ይህች ዕለት ከታላቁ ንጉሠ ነገሥት ጋር ፊት ለፊት የተያየንባት የመጀመሪያዋም የመጨረሻውም ዕለት ሆነች::

አባባ ጃንሆይ አባባ ጃንሆይ ዮኛ እናት አባት
አሳድገውናል አሳድገውናል በማር በውተት ...

ድንገተኛው ክስተት

"ክትልቅ ወይም ክትንሽ መወለድ ሙያ አይደለም፣
ራስን ለትልቅ ታሪክ መውለዱ ግን ሙያ ነው"
ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሐውልት ላይ የተጻፈ::

በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የጦር ኃይሎች ቀን ይከበር ነበር:: በመላ አገራቱ የሚገኙ ከሠራዊቱ አባሎች የተውጣጡ ምርጥ ስፖርተኞች በእግር ኳስ፣ በዘክስ፣ በዋና፣ በገላይ፣ በአ ጭር ርቀት ሩጫና በግራቶን ይወዳደራሉ:: ሙግቢያ ዋጋ ያጎንም ፍራንክ ሳይከፈል በብላሽ በመሆኑ ለእኛ ለልጆቹ 'ሠርግና ምላ ሻችን' ነበር::
አበበ ቢቂላን፣ ማሞ ወልዴን፣ ሌሎቹንም ምርጥ የኦሎ ምፒክ ጀግኖች ሩጫ እንመለከታለን:: በኳሱ መስክ ኳስ ፊደ ሉን፣ ሞሪስንና ሌሎቹን ተወዳጅ ተጨዋቾች የግል ችሎታቸ ውንና የቡድን ቅንብራቸውን አስተውለን እንደሰታለን:: በግል የምንደግፋቸው ተጨዋቾች ሲያሸንፉ በደስታ እንሰክራለን:: የተሸነፉብን እንደሆን እስክማልቀስ እንደርሳለን::

ፑሉቶ በጣም የሚወደው ቦክሰኛ ባዩ አየለ በእንግዳ ወርቅ ባቡር ክፉኛ ተደብድቦ ተሸነፈ:: ባቡር ረጅምና ግዙፍ አካል ያለው ቦክሰኛ ነበር:: ሲጫወት ግራ እጁን ገትሮ ሳያስጠጋው በቀኝ እጁ እያፈራረቀ ባዩን ደበደበው:: ባዩ አጭርና ፍርጥም ያለ አቋም ቢኖረውም በቅልጥፍና የባቡርን ግራ እጅ ሾልክ መደ ብደብ ባለመቻሉ ጨዋታው ፈታኝ ሆነበት:: ባቡር ባዩን ሳያስ ጠጋው የቡጢ መአት አወረደበት:: ባዩ ባይዘረርም ሁለተኛው ዙር በባቡር የበላይነት ተካሂዶ የመጨረሻው ዙር ተጠናቀቀ:: በወቅቱ ፑሉቶን ማየት አሳዛኝ ነበር:: "እረ ገደለው! ምን ማለታቸው ነው? ፎጣ ጥለው ጨዋታውን ለምን በዘቻኝ አያቋ ርጡም?" እያለ እንባው ጣምራ ጣምራ በጉንጩ እየወረደ ይጮኻል::
ባዩ ከእረፍት በኋላ ቴክኒኩን እየቀያየረ ለማጥቃት ሞክረ:: ግን ባቡር የሚቀመስ አልሆነም:: ይህ የኦሎምፒክ ተሰላፊ፣ የመ ላው አፍሪካ ውጤታማ ተጨዋች የሆነው ባዩ በባቡር ክፉኛ ተደ ብድቦ ከመድረኩ ወረደ:: አድናቂውና አፍቃሪውን ፑሉቶን እያፅናናን ወደሚቀጥለው ጨዋታ ተሸጋገርን::
እንዲህ ባለ የስፖርት ውድድር ላይ ትልልቅ ሰዎች ዓለምአቀፍ የስፖርት ክለቦችን እያነሱ ሲወያዩ፣ እኛ በወቅቱ የሚካሄደውን ጨዋታ ብቻ የምንመለከት መስለን የሚያወሩትን እናደምጣለን:: አንደኛው ሲጃራ የሚጠጣ ጥርሰ ወላቃ ሰውዬ በጎርናና ድምፁ ስለመሐመድ ዓሊና ስለ ሶኒ ሲስተን ግጥሚያ ማውራት ጀመረ::
«መሐመድ ዓሊ እኮ የተባለው በቅርብ ነው:: የድሮው ሰሙ ካሽል ክሌ ነው:: ታዋቂ የሆነው በሮም ኦሎምፒክ በቦክስ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ከሆነ በኋላ ነው:: በፕሮፌሽናል ቦክስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋጠመው ከሶኒ ሊስተን ጋር ነው:: መሐመድ ዓሊ አጭር ወፍራም ነው፣ እንደ ባዩ አየለ:: ሶኒ ደግሞ ረጅም ነው ልክ እንደ ባቡር:: እጁን ገትሮ ባዩን አሳስጠጋም እንዳለው፣ ሶኒ መሐመድን እንደእዚያ ገትሮ ሊይዘው አልቻለም:: ምክንያቱም መሐመድ እጁን ቀየገነጠለ እየገባ 'ዳቦ ቤቱን' ይፈተፍተው ነበር:: ሶኒ በጣም ተናዶ ቁጥታ ቀኝ ቡጋይል ሰነዘረ፣ መሐመድን ሳተውና እጁ ተገነጠለ:: ከዚያ በኋላ ሶኒ የመሐመድ ዓሊ መጫወቻ ሆኖ ተዘረረ::"
ትልልቆቹ ሰዎች ተሳሳቁ:: እኛ ደግሞ በዚች በሰማናት ዓለም አቀፍ ዜና ጨዋታውን እንዳየነው ያህል ለእኩዮቻችን ማውራት ነበር ልማዳችን ነው::
የቀላል ሚዛን በክሰኞቹ የአየለ መሐመድ፣ የግርማዬ ገብሬ፣ የኢብራሂም ሰዒድ፣... ጨዋታ ዳንስ ይመስል ነበረ:: ጨዋታው ፈጣንና በስልት የሚካሔድ በመሆኑ ደጋፊውንም ሆነ ነቃፊውን፣ ሁሉንም ያረካ ነበር::

የዋና ውድድር የሚካሄደው በግቦን ሆቴል የመዋኛ ገንዳ ውስጥ ነበር:: መግቢያ በነፃ ቢሆንም እንደኛ አይነት ውሪዎችን

ዘበኞች ማስገባት አይፈልጉም። በዚህ ምክንያት የማየት ዕድላችን በዚህ ስፖርት ላይ የታቀበ ነበር።

አልፎ አልፎ መሽለኩለኩ የሚሳካልን ጊዜ ነበር። ግን አንዳችን የተጠቀምንበት ብልሃት ለሌላው ልጅ አይሠራም። አንድ አንድ ንፁህ የለበሱ ጎልማሳ ወይም ወጣት ተመልካቾችን "በናትዎት ጋሼ ልጄ ነው ብለው አስገቡኝ?" ብለን እንማፀናለን።

ሰዎቹ ይስማማሉ።የተማፀንናቸው ንፁህና ሽቅርቅር ሲሆኑ፣ እኛ ግን አመድ የነፋብን ነው የምንመስለው። ይህ የኑሮ ልዩነት እኛን እደባባይ ያሰጣናል። ዘበኞቹ ነጥለው ቀብ ያደርጉንና ያስቀሩናል። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ዘበኞች እና እኛ አንዋ ደድም። ሁልጊዜ እንደ አይጥና ድመት እንደተሳደድን ነበር።

ይህ ለ15 ቀን በተከታታይ የሚካሄድ ውድድር እሁድ ዕለት ሲያበቃ ስፖርተኞቹ የየክፍል አርማቸውን አንግበው፣ በየክፍለ ጦራቸው ተሰልፈው በማርሽ ባንድ መሪነት በክቡር ትሪቡኑ በአባባ ጃንሆይ ዙፋን ፊት የሚያልፉበት ሰዓት ደረሰ። ይህ ተወዳጅ የሆነ ትዕይንት ሊከናወን ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው አንድ ተአምር ተፈጠረ።

አንድ ጎስቋላ ታዳጊ ወጣት መሐል ሜዳው ውስጥ ታየ። ሚንገቻውን በቅጡ አጠባበቀ። እኔ ካታንጋ አካባቢ ስለሆንኩ ወጣቱ ከጀርባው ይታየኛል። ለጃንሆይ ለጥ ብሎ እጅ ነሳ። ተመልካቾች በኃይል አጨበጨቡለት። ትዕይንቱን ማትረብ ጀመረ። በአየር ላይ ተገለባበጠ። በእጁ ሄደ፣ በአገጩ ቆመ። ተመልካቾች በፉጨት በጭብጨባ አደመቁለት። ታዳጊው ወጣ ትም በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ትዕይንቱን አጠናቆ ለጥ ብሎ እጅ ነሳ። አሁንም ከቅድሙ በበለጠ ጭብጨባው ጎረፈለት፡ አባባ ጃንሆይም አጨበጨቡለት። ባለበት ቀጥ ብሎ ቆመ። አንድ ወጣት መኮንን በሶምሶማ ሩጫ ወደ ታዳጊው ወጣት ቀርቦ እናቱን እየደባበሰው ወደ አባባ ጃንሆይ አቀረበው። ደጋግሞ ምኞቱን ሲነግረን የኖረው ተረፈ ገልጆ አባባ ጃንሆይን በአካል አግኝቶ አነጋገራቸው።

በኋላ እንዳጫወተኝ ጃንሆይም ውብ ፈታቸውን ፈገግ አድ ርገው "ምን እንድናደርግልህ ትፈልጋለህ?"

"የደሃ ልጅ ስለሆንኩ አሳድጉኝ" አላቸው።

ጃንሆይ አጠገባቸው ወዳለው መኮንን ዞር ብለው "እገሌ ይህ ወጣት የናንተ ክፍል ባልደረባ እንዲሆን ፈቅደናል"! ብለው አባባ ጃንሆይ ተረፈ ገልጆን ለዘለዓለም ሲያልመው የነበረውን ድል አጎናፀፉት።

በሃሳቤ ወደ ሰፈራችን ቁርቆስ ተመለስኩ። የገልጆ አባት በልጃቸው ተረፈ ላይ ባወረዱበት አሳር በጣም ያዘንን የሰፈር

ልጆች በለከፋ መቆሚያ መቀመጫ ስላሳጣናቸው ሠፈራችንን ለቀው ሔደዋል።

ገልጆ መኖሪያው ካምቦሎጆ ይሁን እንጂ ከእኛ ጋር ለመ ጫወት ወደ ሰፈራችን ይመጣል። ሆዱ አሁንም ቋሚ ጠላቱ ነበር። አንዳንዴ ረሃብ በጣም ሲጠናበት የሚይዘው የሚለቀው ይጠፋዋል፡

አንዴ ሰፈራችን ርቦት መጣ። ጓደኞቹ የምናበሳው አጣን። እኔን እናቴ በኩሊ ያስፈለጠችውን እንጨት ጓሮ እንድ ከምር አዛኝ እየከመርኩ ነው። በቆይታም ከጉልት ከሃያ በቀሉ ቅቤ ገዝቼሳት እመጣለሁ። ስመለስ የምትሰጠኝን ለገልጆ ለመስ ጠት ወስኛለሁ። የታዘዝኩትን በትጋት ሳከናውን በዚህ መካከል ተአምር ተፈጠረ። የጨኔ እናት እማማ ቅመም እደጅ ድንች አጥበው ወከከ ባለ የከሰል ምድጃ ላይ በድስት አድርገው ጣዱት። ከሰሉን ማራገብ ጀመሩ። ከገልጆ ጋር ተጠቃቀስን። እማማ ቅመም ከሰሉን አራግበው ውሃው እየተንተከተከ መክደ ኛውን ከድስቱ ላይ ሲገፈትረው እየበሰለ እንደሆነ ገባን። መኩዬ ቀጫጫው በእማማ ቅመም ቤት ጓሮ ሔዶ ኩሽናውን አንኮ ሻኮሸው።

"አብ!! ይሔንን ድመት ምንድነው የሚገላግለኝ" እያሉ ወደ ቤታቸው ገቡ።

ገልጆ ቱር ብሎ ሔደና የሹራቡን እጅጌ ቁልቁል እንዳ ያቃጥለው ስቦ ድስቱን አፈፍ አድርጎ አነሳና ከእኛ ቤት ጓሮ ገባ። ቶሎ ብዬ የተፈለጠውን እንጨት እየከመርኩ ጋረድኩት። መኩዬም ዞራ መጥታ አገዘችኝ።

በፍጥነት ከመኩዬ ጋር ወደ ሃደ በቀሉ መደብ ሔድን። ትንሽ ራቅ እንዳልን "ወይኔ ድስቴ! ድስቴስ! ድስቴን ጉድ ሠሩኝ! ወይኔ የኮርያ ማስታወሻዬ" እያሉ እማማ ቅመም ሲጮኹ ይሰማናል።

ባለቤታቸው አባባ ወርቁ አህመድ ናቸው ከክንዱ ዘመቻ መልስ ይህንን 'ኦርጂናል' ድስት ገዝተውላቸው የመጡት። እናቶ ቻችን በመሶብ፣ በድስት፣ በጋን፣ በጭልፋ፣... ላይ ነው ትዝታ ቸውን የሚከትቡት። ዕቃው ቢሰበር ወይም ቢሸነቆር እንኳን እይ ጥሉትም።

እኔና መኩዬ ከሃደ በቀሉ መደብ ስንመለስ ጨኔ ወደ እኛ ሮጣ መጥታ "ድንቹ ይበላ ግድየለንም ድስቷን ግን ገልጆ እን ዲመልስላት" እሷ ነቁ ነች።

"እትጨቅጭቂኝ!" አለቻት መኩዬ።

"መኩዬ የምሬን ነው። ድስቱ ለእናቴ ማበታወሻዋ ነው" አለች ጨኔ እርግጠኛ ነች ገልጆን በላየችው ይህንን ሌብነት ያከናወነው እሱ እንደሆነ ገምታለች። እኛ ግን ዓይናችንን ግንባር ያድርገው ብለን ካድን።

ፀጥ ብለን ቅቤውን ቤት ይዘን ገብተን ለእናቴ ሰጠናት። በኪሳችን የባቄላ አሹቅ ለሁለታችንም አጨቀቸልን።

ይሔኔ ገልጆ ያንን የተንገረገበ ድንች ወጥቆ አጠናቋል። መኩዬና እኔ አሹቃችንን እየጠረጠርን ወደነሽፈራው በጉ ሰፈር ሔድን። እንደገመትነው ገልጆ ድንቹን ልክ አግብቶት በቤቶቹ ጓሮ ተሹለክልኮ በመንደሩ ውስጥ ለውስጥ መንገድ አድርጌ ዋናው መንገድ ላይ ሲወጣ አገኘነው።

ደስ ብሎት ምላሱን አፍንጫው ድረስ እያወጣ አፉን ዙሪያውን ያብሳል። ሆዱን በደስታ ይዳብሳል። ሁለታችንንም እቅፍ አደረገንና "ድንቹ በስሉ ነበር በደንብ አድርጌ ወጠቅኩት። ማታ ወደ ካምቦሎጆ ላድር ከመሔዴ በፊት በጠጠር በራቸውን ኪ! ሳደርጋት እማማ ቅመም በሩን ሲከፍቱ ድስታቸውን ደጃፋቸው ላይ ያገኙታል" አለንና የሁለታችንንም ጉንጭ ሳመን። ከዚያም እንደ ሽርሽር ወደ ታች ሰፈር ወደ ሲሳይ ሜዳ ሔድን።

በጉልምስና ዕድሜዬ በሆድ ላይ የተተረቱ አያሌ ዘይቤያዊ አባባል ባነበብኩ ወይ በሰማሁ ቁጥር ምንጊዜም የማስታውሰው አብሮ አደግ ጓደኛዬን ተረፈ ገልጆን ነበር።

"ሆድ የሌትም የቀንም ጅብ ነው። ከፊት መሆኑ በጀ እንጂ ከጀርባ ቢሆን ገፍትሮ ገደል ይከተን ነበር።" ይላል ሰው።

"ሆድ ጭራቅ ነው" አለ ዓይነ ስውሩ ነዳይ።

"ውሻ ምነው አረጀሀ? ቢሉት፣

"ሲቢሉ ሳይ" አለ።

"ማሸነፍ ማለት ሆድን ነው" አለ ባለሞያ አሳማ።

ገልጆ ሰውንም ውሻንም ሁሉንም ሆኖ በልጅነቱ ሕይወትን ኖራት። በመደምደሚያው እንዳለመው አባባ ጃንሆይን በአካል አግኝቶ ላንዲም ለመጨረሻ ጊዜ ሆዱን ድል መታ። እኔም የዓይን ምስክር ሆንኩ።

ከሃሳቤ ተመልሰኩ። ወደ ማዶ ስመለከት ተረፈ ገልጆ በክብር ትሪቡኑ ጃንሆይ አካባቢ ተቀምጠ የስፖርት ውድድሩን ይከታተላል።

...ከወራት በኋላ ተረፈ ገልጆ በጣም አምሮበት ወደ ቂርቆስ መጣ። አፈርማ ካኪ ሸሚዝና ሱሬ ለብሷል። ከላይ ቆንጆ ሹራብ ደርቧል። ሸራ ጫማ ተጫምቷል። መንደርተኛው ሁሉ በመደነቅ ከያለበት ተሰብስቦ እየሳመ በጥያቄ ያጣድፈው ጀመር። ገልጆም እንደ ድሮው ዝግ ብሎ ይመልሳል።

መንደርተኛው እነ ኃይሉ ዶሮ ቤት ጢም ብሎ እሱ አግዳሚው ላይ ተቀምጠ ወጉ በሰፈው ቀጠለ። ለእንግድነቱ እማማ ሸጊቱ አረንቻታ ገዙለት። ገልጆ የአደይ ዝግምን ድምፅ ከውጪ ሲሰማ ነዮሮ ተነሳ። ወደ ቤቱ ውስጥ ሲዘልቁ እግራቸው ላይ ድፍት አለ። ቀና አድርገው እገላብጠው ሳሙትና «የአንበሻ ሂሳብ አለብህ

ወይስ ተቀማጭ አለህ?» ቢሉት እደይ ቤተኛው ተሳሳቀ። እሱም አብሮ ሳቀ።

አለሚቱ አንነሳ እየሳቁ "ወታደር ቤት ብሩ ነው እንጂ መቅኖ ቢስ! እህሉስ በረከት አለው? አንተ ደግሞ የማይበገር ሆድ አለህ፣ ተገናኛችሁ። ተረፈ መቼም ድፍኑ እንጀራ አያቅትህም። ካልጠገብክ ጨምሩልኝ ማለት ትችላለህ?" ይሉታል... እየሳቁ። ገልጆ ይመልሳል።

እማማ ረታሽ "የቂርቆስ አድባር አረፈች፣ አንድ ጭልፊት ተገላገልን። ተመስገን ነው። ክካችንን ያለምንም ሥጋት እናሰጣለን" ይላሉ።

"ጃንሆይ እንዲህ እጅ ሰፊ ናቸው። አሳቸው አሳድገውህ እንዳትከዳቸው። እህዚያ ነውረኞች የጣዝ እንጀራቸውን በልተው ነው ሊገለብጧቸው የነበረው" አሉ አባባ አጋፋሪ በአንድ ዓይናቸው አፍጠው እያዩት። ቀጠሉና "ተረፈ፣ ለመሆኑ ታስታውሳለህ? ያችን የመከራህን ቀን? ያአሻሮ ሲከካ አጥንት ሲቆረጥም ተአምረኛ የሆነው ጥርስህ ደህና ነው?" ሲሉ ሁሳችንም ሳቅን።

ገልጆ የጥርሱን ደህንነት ፈገግ ብሎ አሳያቸው። ድሮ ጭቃ የተሟቸው የሚመስሉት ጥርሶቹ አሁን በረዶ መስለዋል። ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ "የንጉሥ ነገሥቱ የፖሊስ ሠራዊት..." ይል ነበር።

ይህ አመላለሱ ያላስደሰታቸው አባባ አጋፋሪ "ተራ ወታደር ተረፈ፣ ስለ ንጉሥ ነገሥቱ የፖሊስ ሠራዊት አንተ አትነግረን ም። አንተ መለዮውን ከማድረግህ በፊት እናውቀዋለን። እኛ ያልፈሳንበት ዳገት የለም አለች አሀያ" ብለው ተርተውበት፣ "ብቻ ሥልጠናህን ጨርሰህ ስትመረቅ ጉበኛ ሆነህ የበቀልክበትን ሕዝብ እንዳታሳዝን" ብለው ምክራቸውን አከሉበት።

"ለመሆኑ ገልጆ፣ ጃንሆይ ምግባችሁን ምሳ ላይ ነው በራት ሰዓት የሚቀምሱላችሁ?" አሉና እማማ ወርቅውሃ ጠየቁት።

ሰፈርተኛው ሲሰቅ አባባ አጋፋሪ በመሐል ገብተው "ድን ገት ነው የሚደርሱት። አሳቸው መቼ ሞልቶላቸው በየዕለቱ ይጎበኟቸዋል? ድንገት ግን ከተፍ ይላሉ! አይደል!?" አሉና ተረፈን እውነት መሆኑን እንዲያረጋግጥ ጠየቁት። በትክክል እንዳሉት በድንገት ደርሰው እንደሚጎበኙዋቸውና በዚህም ሥጋት ምንጊዜም ምግብ ቤቱ፣ መኝታ ቤቶቹና ግቢው በንፅህና እንደሚጠበቅ ተናገረ።

ተረፈ ገልጆ አመሻሽ ላይ ሰፈረተኛውን ሁሉ ተሰናብቶ ወደ ካምቦ ለመንገ ተነሳ። አረንቻታዋን ግማሽ ብቻ ነበር የተጎጨላት። ዶሮ አነሳና ጨለጣት። ለእኔም ትንሽ አቀመሰኝ።

የሰፈር ልጆች አጅበን ሸኘነው። ከረሜላ ገዝቶ ለአብሮ አደጎቹ እኩል አካለን። እሱ ግን ምንም አልበላም። አኳኋኑ ሁሉ የእኩያ ሳይሆን የታላቅ መንድም ይመስል ነበር። የሰጠኝን ከረሜላ እየመጠጭኩ በሃሳብ ልብሶቹን ለካኋቸው፤ ልኬ ትሆና

ለች። አባባ ዘውዴ ግቢ ሠንሠለቱ አጠገብ ስንደርስ ገልጆ ሽን ቱን መሽናት ጀመረ፤ ሳየው ተገርሟል። "አባባ ጃንሆይ ናቸው፤ አንትን እ ያደረጉልህ" አልኩት።

"አዎን ጃንሆይ ናቸው ያስገረዙኝ" አለና ተረፈ ያሳፈረኝን ቃል ፊት ለፊት ጠርቶ ተናቂረና ግርማቱ በፖሊስ ሆስፒታል ውስጥ መካሔዱን አስረዳን።

"ግን ካምቦሎጆ እንዲት ፦ ገብተህ ጃንሆይን ፊት ለፊት ልታገኛቸው ቻልክ?" አልኩት እጁን እየደባበስኩ።

"ጉምሩክ መሥሪያ ቤት አጠገብ ያለች ሚዳጋ አንድ በሣር የተ ሸፈነች ቱቦ አለች። በእሱ ቱቦ ውስጥ ለውስጥ ሔጀ ከክቡር ትሪቡኑ በስተግራ ባለው ጉል'ጋ ወጣሁ። ልክ የምፈልጋት ሰዓት እስክምትደርስ እዚያው ቱቦ ውስጥ አደፈጥኩኝ። ልክ ባሰብኩበት ሰዓት ወጥቼ ለጃንሆይ እጅ ነበቼ ትርዒቴን አቀረብኩ። እግዚአብሔርም ረዳኝ" አለና ገልጆ አናቴን እየደባበሰ ምስጢሩን ይፋ አደረገልኝ።

"ሲኒማስ እንደ ልብህ ትገባለህ?" አልኩት። ፈገግ ብሎ በፍቅር አናቴን እየደባበሰ "ፋንታዬ አሁንም ቂል ነህ?" አለኝ፤ እንደ መሽኮርመም አደረገኝ። እያወራን እስከለገሀር ድረስ ሸኝነው። በእው ቶቡስ ተሳፍሮ ሔደ። ተለያየን። እነሆ ከዚያን ዕለት በኋላ ዳግም ከገልጆ ጋር አልተገናኘንም።

...ብዙ ዓመታት አልፈው በቅርብ የኢትዮጵያን ቴሌቪዥን የስፖርት ፕሮግራም ስከታተል ተረፈ ገልጆ ማረፉን ተረዳሁ። በአካል ከተለያየን ከአርባ ዓመት በላይ ቢሆንም በቴሌቪዥን ውስጥ ፎቶውን እንዳየሁ ለየሁት። እሱ ራሱ ተረፈ ገልጆ ነበር። ያ የጦር ኃይሎች ቀን ድንጉጥኛ ኮከብ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ተመልሶ ጠለቀ...

የታሠረው ጋኔን

"የልጅነቴን ዘመን በአንድ ቀፎ ልመሰለው እችላለሁ። ንቦች ማራቸውን እያመጡ በቀፎ እንደሚያከማቹ ሁሉ ብዙ ልዩ ተራ ሰዎች የዕውቀትና የኑሮ አስተያየታቸውን ማር እያመጡ እያንዳን ዳቸው ጠባዬን ለማነፅ ሰፊ መዋጮ አድርገዋል። ብዙውን ጊዜ ማሩ ቆሻሻና መራር ነበር፤ ነገር ግን የእውቀት ማር በመሆኑ ያው ማር ነው።"

ማክሲም ጎርኪ

አባቴ ሬዲዮ መግዛት ይወዳል። ወደ ጋምጎፋ ቢሔድ እዚያ ለሚኖሩ ባላገሮች በትርፍ ይሸጥላቸዋል። ስንበትበት ያልና ሀጥያው

ሲያስፈራው፤ አሊያም ሬዲዮኑን ይዞ ነጭ በነጩን ለብሶ መዘነጥ ሲያ ምረው እንደገና ይገዛል። አሁንም ትውስ ይለኛል በድጋሚ ሬዲዮ ከአንድ ኮርያ ዘምቶ ከመጣ ወታደር ላይ በመቶ ብር ገዛውና እኛ ቤት ውስን ተዋውለው ተፈራረሙ። አባቴም ገንዘቡን ቆጥሮ ሲያ ስረክበው እዚያው ነበርኩ። የኮርያው ዘማችም ሬዲዮኑን ለአባቴ አስረክቦ "ይህ የሬዲዮኑ ፋክቱር ነው። ያለ እዚህ ፋክቱር ይህ ሬዲዮን ምንም ዋጋ የለው። እንዳይጠፋብህ ደህና ቦታ አስቀም ጠው። ዕቃው ያንተ መሆኑን ማረጋገጫ ነው" አለና የተጣጠፈ ወረቀት ለአባቴ ሰጠው።

"ያለፋክቱርማ ወርቅም ዋጋ የለው። ልክ ነው ያለው ይኼ ወታደር። አንድ ምቀኛ ቢነሳብህ ፊርማቶሪ መጥቶ ዕቃው ያንተ መሆኑን ለማረጋገጥ መጀመሪያ የሚጠይቀው ፋክቱር ነው። ከእጅህ ከጠፋ ቀለጥክ ዜራም" አሉ ቀለም ቀቢው አባባ ታዴ፤ የፋክቱርን አስፈላጊነት በአካላቸው እንቅስቃሴ ጭምር እያስረዱ።

"ፋክቱር የሌለው ዕቃማ ይዞ መገኘት በንጉሠ ነገሥት ግዛት ወንጀል ነው፤ ያስቀጣል። በል ዜራም፤ የፍንጥር በለና" አሉ እማማ በለጡ እየሳቁ።

"ገጠ ተልኳል። ሣሬ አስክሬ ወደ ባልሽ እልክሻለሁ።"

"ዜራም የዋዛ ዶርዜ መሰላችሁ? በፋክቱሩም ላይ ወታደሩ የራሱ ንብረት መሆኑን ማረጋገጫ አስጽፎ አስፈርሞታል" አባባ ኃይሌ አከሉ።

የፍንጥሩ ሊትሮ ካቲካላና ማንቆርቆሪያ ሙሉ ጠጅ መጣ። ጨዋታው ደራ። ስፈረተኛው የፋክቱር አስፈላጊነት አስጨንቋቸው ብዙ አወሩ።

እኔ በሆዴ 'ሬዲዮኑ ፋክቱር ባይኖረውስ? በመቶ ብራችን የገዛነው የእኛ ሬዲዮ ነው። በቃ የእኛ ነው' ብዬ አሰብኩ።

ዶጅ ገማጣው የውል ወረቀቱን ሲያነብ ከአንድ ጥግ ተቀ ምጬ አደምጣለሁ። እማዬ ቡና ታፈላለች። አባ ዘለቀ፤ በለጡ ገጠ፤ አባባ አጋፋሪ፤ የክርስት አባቴ ኃይሌ፤ ቀለም ቀቢው ታዴ፤ ግንበኛው አባባ ቱሉ፤ ምክትል የአሥር አለቃ አበበ እን ዲሁም፤ አናጢው አባባ በየነ ግስላቸውን እያጤሱ ካቲካላቸውን በመለኪያ ፉት እያሉ ያወጋሉ። የሚነጋገሩት ስለ ሬዲዮ አሠራ ርና ጥበብ ነው። ሁሉም የሚያውቀውን በእርግጠኝነት ይወያያሉ።

"ጠቅል! ምን ይሳነዋል?" አለ የኮሪያው ዘማች፤ ቀጠል አድርጉ "ትልቁን ጋኔን አቡነ ጴጥሮስ ሃውልት'ጋ አስሮ እንደ ፈለገ ያስለፈልፈዋል። በስለሞን ጥበብ የተቀባው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋኔንንም ለዜና መዋዕል በጥበብ አዋለው።"

"ሬዲዮ እሚሠራው በኮረንቲ ተደርጎ ከነፋስ ለልክ ሲለቀቅ ማንም ወሬ እሚያደምጥ ይመስለኝ ነበር" አሉ ክርስትና አባቴ

በጥርጣሬና በትህትና። የአሳቸው አባባል ትክክል እንደሆነ አኳኋናቸው ይገልጻል።

"አይደለም!" አለ የኮርያው ዘማች በእርግጠኝነት። ጉልበቱ ላይ ያኖራትን መሰቦ እየደባበሰ "ከንፋስ ስልክ ሠፈር በንፋስ እሚላከው ስልክ ነው። ይህ ሬዲዮ በየቤታችን የምንሰማው ግን በንፋስ እሚላከው ተአቡነ ጴጥሮስ ሃውልት አካባቢ ነው። 'ይህ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ነው' ይልና 'ከአቡነ ጴጥሮስ አካባቢ የምናስ ተላልፈውን ፕሮግራም አሁን "እንጀምራለን" ብሎ ያበሥራል። አሁን ስንት ሰዓት ሆነ?" አለና በግራ እጁ ላይ ያሠራትን ሮመር ሰዓት በቁንጥ አየ። 'አ! አምስት ጉዳይ... ደርሷል። አሁን ይጀምራል።"

በእኛ መንደር ውስጥ ጋሼ ደገፉ ብቻ ናቸው ሮመር ሰዓት ያላቸው። ይሁን እንጂ ለማንም የጊዜውን ልክ ሲጠየቁ ብዙ ጊዜ ተናግረው አያውቁም። ችላልቅ ሰዎች ሲጠይቋቸው፣ ዕድሉ ሰንበት ከሆነ «የዕድሩ አልፏል የዕቁቡ አየደረሰ ነው» ይሏቸዋል። በአዘዐት ቀን ከሆነም የሚሉትን አያጡም።

ልጆች ስለሚወዱ ያጫውቱናል፤ ይተርቡናል። 'እጅ ወርቁ' ጓደኞችን ባሪኾ ሞቶ ተደናግጠን አዩንና ጠየቁን። የሆነውን ነገርናቸው። ምንም ሳይመስላቸው «ድሮስ መች ኖረ? ልጆች!» ብለው ነገር አሰኙን።

በጨዋታ አዘናግተን ሰዓት ስንጠይቃቸው «እኔ አንድ ሚስማር አሮጌ ጫማ ውስጥ ጥልቅ የማደርገዝትን ጊዜ ለእናንተ ብዬ ከእጁ ፈትቼ ኪሴ ያስቀመጥኩትን ሰዓት ልይ?» ይሉንና በአፋቸው ከያዙት አንዲን ሚስማር ያወጡና በእፍጢሙ በደፋት ጫማ ላይ ይመታሉ።

ወደነበርንበት ተመለስኩ።

"ነንዘቡ ይገኝ እንጂ ዋናው ቅርስ መያዝ ነው። አላቂ ጌጥ ምን ዋጋ አለው? ፍሪዳም አርደው ቢበሉት ሆድ አየሁ አይል" ሲባባሉ ብዙ ጊዜ ሰምቾቸዋለሁ።

"እስኪ ስለ ኮሪያ ዘመቻ አጫውተን?" አሉ ምክትል የአስር አለቃ አበበ።

"የኮርያን ታሪክ እዚህ ከጀመርኩ አደርኂት።"

"አጠር አድርገህ!"

"አየጥርማ! ጀግንነታችንን፣ ጀብዱአችንን፣ ስንቱን አንስቼ እዘልቀዋለሁ? አሳጥረው ካሉኝ፣ የአስር አለቃ፣ አንድዋን ጣል ላድርግ" አለና አፉን አብሶ "እንደሚታወቀው እኛ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበርተኛ ስለሆንን ሰላም ለማስከበር ነው ንጉሠ ነገሥታችን ያዘመቱን። ታዲያ ከዕለታት በአንድ ቀን ከጠላት ጦር ጋር ስንፋለም አንዳንድ ታክቲክ መጠቀም ነበረብን።"

"ታክቲክ" አልኩ ሳላስበው ጮክ ብዬ።

"ታክቲክ ብልሃት ማለት ነው።" ብሎ ተረጎመልኝና "ከካምፕ ሙዳ ሙዳ ሥጋ በኪሳችን ይዘን ወጣን። በአጋጣሚ

ውጊያ ተነሳ። የኢትዮጵያ መታደር ቆራው እየተንደረደረ ገባ በት። ሬሳው ተረፈረፈ። ከዚያም አንዳንድ ሬሳ ላይ ጉብ ብለን በሳንጃ ቁርጣችንን እየመተርን ስንከመኩም፣ ጠላት ይሆንን ዓይቶ ሰው የሚበሉ መአተኞች አዘመቱብን ብሎ በሽሽት ገደል ገባ።"

መገረምና አድናቆት ጉረፈለት።

የኮርያው ዘማች እየተጫወተ ሰዓቱን አየ። ስድስት ሰዓት ሆነ። ሬዲዮኑን ከፈተ። የሚያደርጋትን ሁሉ በጥንቃቄ አያለሁ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ በመሣሪያ የተቀነባበረ መዝሙር መሳይ ድምፅ ተሰማ። ከዚያም ዘማቹ እንዳለው *"ይህ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ነው። የኢትዮጵያ ሬዲዮን ከቀኑ ሰድስት ሰዓት አስከ ሰባት ሰዓት ተኩል እሚያሰማውን ፕሮግራም አሁን ይጀምራል"*

ጎረቤቶቻችን ሁሉም አፍጠው ትንሽዋ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠችውን ሬዲዮ ያስተውላሉ።

"እንደምን ዋላችሁ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን" ብለው በንብረት መለሱለት።

"ዜና እናሰማለን። ዜናውን የማሰማችሁ ታደሰ መሉህ ነኝ። በመጀመሪያ አርዕስተ ዜና" አለ ጋዜጠኛው። የጋዜጠኛው ድምፅ ሰላም አብላሪ ነው። የአነባብ አርጋታው አንዲያደምጡት ይጋብዛል።

"ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከመስኮብ የመጡ ልዑካንን ተቀብለው አነጋገሩ..."

"ከሞስኮብ...!" አለ የኮርያው ዘማች በመደነቅ። አንድ ስለሞስኮብ የሚያውቀው ትልቅ ምሥጢር እንዳለ ከገጹ ያስ ታውቃል።

"የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ክቶማ ይፍሩ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን መልእክት ይዘው ወደ ተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት ሄዱ።"

"በክፋ ጠቅላይ ግዛት የልማት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አገረ ገዥው ፀሐይ ዕንቁሥላሴ ገለጹ" አለና ዝርዝር ያሰማ ጀመር።

ወላጆቼም ሆኑ ጎረቤቶቻችን የተቀዳላቸውን ካቲካላና ጠጅ እየተጎነጩ በአንከሮ ያደምጣሉ። አንዳንዴ ፈገግ፣ እንደገናም ኮስተር እያሉ ይከታተላሉ።

"የአሰራኤልዋ ጠቅላይ ሚኒስትር ጎልዳሜር አረቦች ሙሉ ናክሳቸውን ካላቆሙ አሰራኤል የራሷን ሕልውና ለማስከበር ሰትል ጦር መምዘዟ አማይቀር መሆኑን ገለጹ።"

"ትክክል ከአሰራኤል ፊት ሊቆም?" አለ የኮሪያው ዘማች "የክርስቲያን ደሴት ነች። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት እየሩሳሌም አገር" አለና አከለበት።

"እውነት ብለሃል! ከዓመት አስከ ዓመት ይፀለያል። ገበሬው በዓመት አንዴ ብቻ ነው የሚያርሰው። ምንም ችግር የለባቸው፣ ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው" አሉ አባ ዘስቀ።

የእውቀቱ ብዛት ሁሉንም አስደነቃቸው። ደሞ ሁሉን ነገር መተቸትና መተንተን ይችላል።

"የግብፁ ጠቅላይ ሚኒስትር ገማል አብደል ናስር የጎልዳ ሜርን ዘጅ ሰምተው ለሚጨጣው ጥቃት ሁሉ አረቡ ዓለም እጅጉን አስተባብሮ እንዳነሳ ጥሪያቸውን በዘረው ዕለት አሰምተዋል..." በማለት ጋዜጠኛው ዜናውን አበቃ::

"ኤዲያ! የማይመስል ነገር:: 'ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ!' አረቦች እኮ እልፍ ናቸው:: ተራራ ላይ ቆመው ሽንታቸውን ቢሸኑ እስራኤልን በጎፍፍ ሊያጥለቀልቋት ይችላሉ:: ግን በብልሃት አልቻሏትም" ሲል የአረቦችን አቋም ተቸ የኮሪያው ዘማች::

ምክትል የአስር አለቃ አበበ "ትክክል ብለሃል፣ የሃምሳ አለቃ ደምሰው" አሉት "እኔ አጋዴን በረሃ እያለሁ በአዛዦችን ኮረኔል ገመዳ ባዩ ሬዲዮ ጉዳዩን ስንከታተል፣ እሥራኤሎች ትንሽ ወታደር ያዘምቱና በሺ እሚቆጠረውን አረብ እምሽክ ያደርጉታል:: ይኼ የወታደራዊ ጥበብ መብለጥን ነው የሚያሳየው:: የአምላክም ትእዛዝ አለበት..."

አባ ዘለቀ በግዕዝ ቋንቋ አንድ ቃል አነበነቡና "ይላል መጽሐፉ:: ማንም ከእሥራኤልና ከኢትዮጵያ ፊት አይቆምም::"

ምክትል የአስር አለቃ አበበና የኮርያው ዘማች ደረታቸውን ነፉ:: እኔም የኃያልነት ስሜት ወረረኝ:: እማማ በለጡና እማማ የወርቅውሃ እልልታቸውን አቀለጡት::

ቀጢላው፣ ኳቢጥ፣ ዲዲ፣ መኩዬ ቀጫጫው አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ የበቀሉ ይመስል በራችን ላይ ተደራርበው ተገሸረው የሬዲዮኑን ወሬ ይሰማሉ:: በጥቅሻ እንዲገቡ ነገርኳቸው:: ማንም ሳይገስፃቸው ተራ በተራ ወደ ቤት ውስጥ ገቡ:: ሁላችንም ፀጥ ብለን ጓዳ በር ላይ ተሰባሰበን የአዋቂዎቹን አስተያየት እናደ ምጣለን::

የኮርያው ዘማች ሞቅ እያለው ፈሌደ:: ልክ ዜናው እንደ ተጠናቀቀ በሰፈራችን ሕይወት ያልተለመዱና እኛ ከምንኖርበት ዓለም ውጪ የሆኑ ደስ የሚሉ ጨዋታዎችን እያነሳ አወጋ::

"ቅድም ሞስኮብ ስንል አልነበረም?" አለና አፉን እያበሰ ጠይቆ፣ "መስኮብ ውስጥ ድሃና ሀብታም የለም:: ሁሉም እኩል ነው እሚኖረው:: ለምሣሌ አንዱ መኪናውን ያስነሳና እፈለገበት ቦታ ሲደርስ መክፈቻ ቁልፉን እዚያው ትቶ ይሄዳል:: ሌላው ሰው ደግሞ ከዚያ ያስነሳና ልቡ እሻበት ቦታ ይዞት ይሄዳል:: በአጠቃላይ ኑሮአቸው እንዲህ ነው:: እሚበሱት፣ እሚጠጡት፣ እሚለብሱት እሚኖሩበት ቤት፣ አንድ አይነት ነው:: እኩል ይከፈላቸዋል፣ እኩል ይሠራሉ፣ እኩል ይታከማሉ:: በአጠቃላይ ሁሉም ሰው እኩል ነው::"

"ባላባትና ሹሰኛም የለበት?" አለ አባቴ በጣም ተገርሞ::

"ኤዲያ! የምን ባላባትና ሹሰኛ? እንኳን ሹሰኛ... እናንተ ሰዎች ፖለቲካ እንዳታናግሩኝ::በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ' አሉ!"

ምክትል የአስር አለቃ አበበ ከአፉ ነጥቀውት "አትፍራ የሃምሳ አለቃ ሁላችንም የገባር ልጆች ነን::"

"ቢሆንም 'ዝም አይነቅዝም' 'መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች' 'አሳርፍ ያለች ጣት...' እንደሚሉት ሆንኩ::"

"አኼ! 'ካለመናገር ደኃዝማችነት ይቀራል' አሜውተን እባክህ እኛ መካከል ፌርማቶሪ የለ:: ምን ያስፈራሃል?" አሉ ምክትል የአስር አለቃ አበበ::

"ሰዎች በስመ አብ በሉ" አሉ አባ ዘለቀ::

"በስመአብ ብለናል አባታችን::... ብቻ መስኮብ ጥሩ ጥሩ ነገር አለው ያልኩትን ያክል የዚያኑ ያህል መጥፎም ባህል አለው:: ለመጥቀስ ቢያስፈልግ ሃይማኖት የላቸውም:: እግዚአ ብሔርን አያውቁም:: የጭንቅ አማላጇን አያመልኩም::"

"ቱ! ማኅተብም የላቸውም? ያገኙትን ነዋ እሚውጡት" አሉ እማማ የወርቅውሃ::

"ታዲያስ! ፈረሱንም አሳማውንም ያነክቱታል!"

"ስብሃት ለአብ እንበል" አሉና አባ ዘለቀ ተነሱ:: ቤተኛው ሁሉ ተነስቶ ቆመ::

እኔና ጓደኞቼ ብናገኘው አያሌ ጥያቄ እምንጠይቀው አዋቂ ወታደር ከወላጆቻችን በእጅጉ የላቀ አስተሳሰብ ነበረው:: የሰው ልጆች እንደልባቸው የሚኖሩበት ዓለም እንዳለ ብልጭ አድርጎ አሳየን::

መደምደሚያው አባባ ጃንሆይ እንዲሆኑ አባ ዘለቀ ቤተኛውን አስገደዱት:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለዘላለም እንዲኖሩ ፀለዩን...

"እ! ጥሳሁን ገሠሠ መዝፈን ጀመረ ልጆች ደንሱ" አለን የኮርያው ዘማች ርዕሰ ለመቀየር በፈለገ ስሜት 'የኔ ፍቅር' እሚለውን ዘፈን ማዜም ጀመረ:: እማማ ወርቅውሃ አብረውት እያዜሙ "ውሮ ተነስ ደንስ" ሲሉ ልጃቸውን ጋበዙት::

ውሮ እንደ መሽኮርመምም፣ እንደማፈርም፣ አንደ መጀመርም እያደረገው ወደ መሐል መድረክ ገባ:: ዶቃ የታሰረባቸው ሦስት ቁንጮዎቹ እንደ ጉልቻ አናቱ ላይ ተጊጠዋል:: ዶቃዎቹ እርስ በርስ እየተጋጩ ለዳንሱ ድምቀት የራሳቸውን ድምፅ አዋጡ:: አንገቱ ላይ የተደረገለት የቡዳ መድኃኒት ከካኔቴራው ላይ እፈትልኮ ደረቱ ላይ ይዘላል::

ውሮ በጥቅሻ ለእናቱ ወደእኔ አመለከታቸው:: እማማ የወርቅውሃ ትንንሽ ዓይኖቻቸውን ወደእኔ አጮልቀው "ፉንጋዬ ኑ ደንሱ" ብለው ጋበዙኝ::

ለደንቡ ያህል ተግደረደርኩ፣ እንጂ ባለሁበት ልቤ መደነሷን ጀምራለች:: ጥሳሁን አዝማቹን ጨርሶ ወደ ግጥሙ ዘልቋል::

"አትመልከቺ ሱፍ፣ አትይ መኪና
እኔም እገዛለሁ ዕድሌ ሲቃና

በጀት እንሔዳለን እንኳን በመኪና
ብትታገሺ ዕድሌ እሰኪቃና"

ሲል፣ እኒህ ድህነት እንደ ወስከምባይ የተደፋባቸው ጎስቋ ሎች፣ እኒህ አንድ ቀን የተሻለውን ሕይወት እንኖራለን የሚሉ ተስፈኞች ዳንሱን በሳቅ አጀቢት።።

እኔና ውሮም ዳንሱን አስነካነው።። ሰዉ ሁሉ ያጨበጭብ ጀመር።። ውሮ ከፍ ዝቅ እያሌ ይደንሳል።። እኔ በቆምኩበት እግ ሬን እያንቀጠቀጥኩ ጣቶቼን እያፏጨሁ፣ ዓይኔን ገርበብ አድርጌ አካሌን በማንቀጥቀጥ ዳንሱን አስነካዋለሁ።።

ጥሳሁን ዜማውን ሲጨርስ ሁሉም ሰው አጨበጨበልን።። ሲስቁ ዓይቼ እማሳውቃቸው የክርስትና አባቴ እንኳ ፈገግ ብለው የሲጋራ ጢስ የመታው ጥርሳቸውን እያሳዩኝ፣ ጠቀሱኝ።።

እማማ ረታሽ እኔና ውሮን ሳብ አድርገው እየሳሙን "እን ትፍ! እንትፍ!" አሉና ምራቃቸውን አርከፈከፉብን።። "ከዓይን ያው ጣችሁ!" ሲሉ መረቁን።። ስለአደናነሳችን የተለያየ አስተያየት ተሰጠ።።

አዋቂው ወታደር ሮመር ሰዓቱን እያየ "መሄጃዬ ደርሷል" አለና፣ ለአባቴ "እንግዲህ እንዴት እንደምትዘጋና እንደምትከፈት ሳሳይህ" አለው።።

ሬዲዮኑ ወሬውን ሳይጨርስ ከፈቱ ካሉ ብሎን መሰል ነገሮች አንዱን ጠመዘዘና ዘጋው።። ሬዲዮኑ ዝም አለ።። ሲያስ ረዳም "ይኼው ነው አጠቃቀሙ።። ጣቢያ መፈለጊያውም ይኼው።። በርግጥ እናንተ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ብቻ ስለምትሰሙ ጣቢያውን መነካካት አያስፈልጋችሁም።። ይኼ ኮርት ይባላል" አለና ከሬዲዮው ጀርባ ያለውን ክፍል አሳየ።። ከዚያም ከጎንና ከጎን ሁለት ቡሎኖች ፊታና የጀርባውን ሽፋን ነለጸው።።

አያሌ ሽቦዎች ተጠላልፈው ታዩኝ።። አባቴ ጭን ላይ ጋደም ብዬ እሚናገረውንም በፈጣን ጣቶቹ እሚከውነውንም በጥ ንቃቄ እከታተላለሁ።።

"ይህ ድንጋይ የሚጎርስበት ነው።። ድንጋዩ ሲያልቅ እንዲህ ታወጣውና ሌላ አዲስ ገዝተህ ትጨምርበታለህ" ድንጋዮቹን ቆጠ ርኩ።። መልሶ ከትቶ ሬዲዮኑን ሲከፍተው አንዲት ደምፃዊት ክራ ሯን እየከረከረች በማንጎራጎር ላይ ነበረች።።

"ዛሬ ደግሞ ሬዲዮ ጣቢያው ድንቅ ድንቅ ዘፋኞቻችንን ነው በአየር ላይ የናኘልን።። ይህች ደምፃዊት ሜሪ አርምዴ ትባ ላለች" አለን የኮርያው ዘማች።።

ሁሉን ነገር ማወቁ በጣም አስገረመኝ።።

ሃምሳ አለቃ ደምሰው ለፍንጥር አምስት ብር ቆጥሮ ጠረጴዛ ላይ አኑሮ ሁላችንንም ተሰነባበተና ሽቅብ ወደ ብረት ጋራጅ ተጓዘ።። እማማ ረታሽ በዓይናቸው እየገረመሙ ሸኑት።። ቤተኛው ወዲ

ያውኑ ወጣ እንዳለ ስለ ኮርያው ዘማች ይወራ ጀመር።። "አዋቂ ወታደር ነበር፣ ሃሳቡ ግን ዘውዱን የሚሃረር መሰለኝ" አሉ አባ ዘለቀ፣ በጥርጣሬ ዓይን ተቀምጠ የነበረበትን ወንበር እያስተዋሉ።።

"በጣም እያስተዋሉ እያወቁ ሲመጡ፣ ንጉሡ ነገሥቱን እሚ ያስጠላ በሽታ ይጠናወታቸዋል "አሉ ምክትል የአሥር አለቃ አበበ።።

አባቴ "እኛ ንጉሡን እሚያስወድደን መሐይሞች መሆ ናችን ሳይሆን ይቀራል?" ሲል፣

"ዝጋ! አንተ ዶርዜ! አርፊህ ዲቃላህን አሳድግ" አሉ እማማ ረታሽ ቱግ ብለው።።

"በገዛ ዘመዶቼና ጎረቤቶቼ ፊት እንደፈለኩ ሳላወራ ነው?"

"አሀሆ! 'ጎመን በጤና' ልጄ!" አሉ አባ ዘለቀ በጥርጣሬ፣ "አርፊህ ሸማህን ሽምን።። ቦለቲካ የንጉሡ ጉዳይ ነው! ይኼ ግን ኮሌጅ ገብተው ከወጡት ተማሮች መካከል አንዱ ሳይሆን አይ ቀርም።።"

"እነርሱ እዚያ ኮሌጅ ውስጥ አስለፍልፍ ሳይቀምሱ አይ ቀሩም" አሉ አባባ ቱሉ ዝም ብለው ቆይተው።።

"ይህ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ነው ምናምን ምናምን በደህና ዋሉ" አለና ጋዜጠኛው ተሰናበተን።። አባቴም አዋቂው ወታደር እን ዳሳየው ሬዲዮኑን ዘጋው።።

"አሜን እናንተም ደህና ዋሉ!" አሉ እማማ ረታሽ ወደ ሬዲዮኑ እጅ እየነሱ።።

ከዚያ በኋላ አዋቂዎቹ የሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ ተማሪ ዎችን የተመለከተ ስለነበር እዚያ የነበርን ሕፃናት ፀጥ ብለን ስና ደምጥ እማማ ረታሽ አዩንና "ፈሳም ሁሉ! ውጡ ከዚህ!" አሉን።። ግር ብለን ወደ ውጪ ስንወጣ 'ጫፌቴት ፊት ፈንግል አይወራም' ሲሉ ሰዉ በሳቅ አውካካ።።

« እስኪ ፋክቱሩን አሳየኝ» አሉ እማማ ረታሽ።።

መለስ ብዬ በሩ ላይ ቆምኩኝ።።

«ምነው?» አለ አባቱ ፋክቱሩን ሳይሰጣቸው።።

«ይህ ሁሉ አዋቂ ባለበት አያታልልም ብዬ እንጂ እኔና ሬዲዮን ሻጭህ እንተዋወቃለን።።»

«አንዳችሁ የሌላውን ዓይን ሰትሸሹ እኔም ልብ ብያለሁ» አለች እማዬ።።

«የአስር አለቃ አበበ፣ የሃምሳ አለቃ ደምሰውን ቀደም ብሎ ታውቀው ነበር?» ጠየቁ እማማ ረታሽ።።

«እንዲያውም!» መለሱ የአስር አለቃ አበበ።።

«በቅፅል ስሙ ደምሰው አቅልጥ ይባላል...» ብለው እማማ ረታሽ የጀመሩትን ሃሳብ ሳይጨርሱ የአስር አለቃ አበበ ከአፋቸው ነጥቀው «ደምሰው አቅልጥን? አሳምሬ በዝና አውቀዋለሁ።። በድፍን የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ውስጥ ይታወቃል።። ይኼ እሱ ነው እንዴ?»

«በጀብዱና በጀግንነቱ እንዳይሆን የሚታወቀው?» ጠየቀ አባቴ ጣልቃ ገብቶ።

«ጓሳስ! ኧረ እሱ አቴ! ወንዶች በዋሉበት ውሎም አያውቅም። በኡጋዴን ጠላት መጣ ሲባል ቀድሞ ታሟል። ጠላት በጀግኖቹ ከንድ ተመክቶ ሲመለስ ይድናል።» ሲሉ እማማ ረታሽ፤ ቤተኛው አጀብ ብሎ የከረኩሩትን ያህል በሣቅ አውካካ። «ቦሚቀጥለው ቀን ዞር ዞር ብሎ ወሬውን ይቃርማል» አሉ እማማ ረታሽ ሲቀጥሉ «ሃምሳ አለቃ አቅልጥ ጠርነቱን ከመሩት ጀግኖች በላይ ሲንደቀደቅ ይደመጣል።

«ያም ይኼም ይጋብዘዋል። አቅልጥ ወግ አዋቂ ነው። ያገኙትን ይወሽማል። አዚያም እዚህም ዘሩን ይተዋል። ይቅር ይበሉኝ አባ ነውር ተናገርኩ?!» አሉ እማማ ረታሽ እጅ እንደመንሳት ብለው።

«እንዲያውም ሰው ምን እንደሚመስል አያሳዩን ነው እመት ረታሽ» አሉ አባ ዘለቀ ስልል ባለ ድምፅ።

እማማ ረታሽ ፈጥን ብለው ሲቀጥሉ «ከልብስ እንኳን ከጦር ሠራዊት የደንብ ልብስ ውጪ የሲቪል ሸሚዝ ትከሻውን ነክቶት አያውቅም ነበር። አንዴ ጃንሆይ ...» ብለው ሲቀጥሉ ቢሉ፤ የአስር አለቃ አበበ ከአፋቸው ነጥቀው «ጃንሆይ በሰንበት ቀን ለዕረፍት ወደ ቢሾፍቱ ሲሔዱ ሃምሳ አለቃ ደምስውን መንገድ ላይ ያገኙታል። ደምስው መቼም ያልሞተ ይገናኛል የሚሉት አውነት ነው። ለመጪረሻ ጊዜ የተገናኘው ውጋዴን በረሃ ነበር? ለመሆኑ ደህና ነህ? ብለው ጉንጩን ደባበሱት የሚባለውስ?»

«ይኼ ቆርጦ ቀጥል ምን የማያስወራው አለ? ይኼ ወሬ ተዛምቶ ንጉሠ ነገሥቱ ጆሮ ደረሰ ይባላል። አስጠሩት፤ አለቃው ተገርመው ተዘጋጅ አሉት። የደንብ ልብስ አልቆብኛል አለ። በአስቸኳይ ከግምጃ ቤት ከምጥሌት የደንብ ልብስ ወጥቶ እንዲሰጠው አዘዙ።

«አቅልጥ ቂቅ ብሎ ቤተ መንግሥት ሔደ። በአለቃውና በባልደረባው ታጅቦ ወደ ውስጥ ሲገባ አሳበኝ አለና መፀዳጃ ቤት ገባ። ሲወጣ ከንዱ ላይ የሃምሳ አለቃ ማዕረግ ለጥፏል። ማን ይናገረው? አለቃው ተገርመው ፀጥ አሉ። ጥድፊያ ላይ ናቸው። ጃንሆይ እየጠ በቁት ነው።»

«ጉድ! ጉድ!» አሉ አባባ ታደሰ ተገርመው። መንደርተኛው ጨዋታው ከማርና ወተትም በላይ ጥሟቸዋል። በፍንጥሯ አምስት ብር ካቲካላውም ጠጁም ተልከ መጥቶ ወጉ ደራ። አንዴ አውካኩና የመጪረሻውን ለማወቅ አቆበቆቡ። «ጃንሆይ እንዳዩት ተራ ወጥቶ አደር መስለኸን ነበር። ሃምሳ አለቃ ነህ እንዴ? ሲሉት ጌታዬ ፊት እንዴት ሌጣዬን አቀርባለሁ ጠቅል መርቅልኝ! አላቸው። ጃንሆይም መርቀንልሃል አሉት።» ሲሉ እማማ ረታሽ ቤታችን ውስጥ ሳቅ ሆነ።

« እንዲህ ነው ሃምሳ አለቅነቱን ያገኙት» ብለው ከቤተኛው ጋር እየሳቁ የነበሩት እማማ ረታሽ ፊታቸውን በነጠላቸው ጫፍ እያበሱት «አጅሬ መቼ በዚህ አቆመ። መቼም ያውቅበታል። ጉደኛ ሰው ነው። አንዴ ምን ያደርጋል? ሙሉ ሱፍ ከትና ሱሬ ገዛ። በሕይወቱ ለመ ጀመሪያ ጊዜ የሲቪል ልብስ ለበሰ። ጠዋት ይነሳና ይወጣል። የት

እንደሚሔድ ማን ያውቃል? በጓሳ ሲጣራ ማለዳ ማለዳ የሚሔደው ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ለመንሳት ነው።»

«ጉድ! ጉድ! አያችሁ?» እዚያም እዚህም የተሰማ ድምፅ ነበረ። እማማ ረታሽ ሲቀጥሉ «እንደሚታወቀው መሣፍንቱና መኳንንቱ ማለዳ ቤተመንግሥት እየሔዱ ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ይነሳሉ። ደንብ ነው። ይኼ አጭልግም በዓደባባይ ከመኳንንቱ ጋር መዋል ጀመረ።

«ጃንሆይ አንዴ ያዩትን ሰው አይረሱም ይባላል። ሃምሳ አለቃ ደምሰውን ከመኳንንቱ ጋር ደጋግመው አዩት። አንዴ በጥቅሻ ጠሩትና፣ 'ሃምሳ አለቃ ምን እንድናደርግህ ፈልገህ ነው? አዘውትረህ ዓደባባያችን ላይ የምትታየው?' አሉት።

«አምላክ ጌታዬን እንዴት አውሎ እንዳሳደረው ለማየትና ምሥጋናዬን ለማቅረብ እንጂ፣ እኔስ ምንም ፈልጌ አልመጣሁም። እግዚአብሔር ምሥጋና ይድረሰው ፀሎቴን በምቶኛል።»

«ምንም የምናግዝህ ነገር የለም ማለት ነው?» አሉ ጃንሆይ ፈጥነ ብለው።

«ኃይለሥላሴ ይሙት! ይኼ ጉልቆ መሣፍንት ሁሉ የሚያስቸግርህ መቼ አነሰና ነው አኔ የምጨመርበት። ግን ጌታዬ መልካም ፈቃድህ ከሆነ ይህቺን ዓደባባይ እየተጨዋወትን አንዴ እንዙራት።»

«ምን አይነቱ ጮሌ ነው? በል ተከተለኝ» አሉና ጃንሆይ አስከተሉት። እሱ እንደሆን ጨዋታ ይችልበታል። እኚህ ሃሳብ ያደቀቃቸውን ንጉሠ ነገሥት በሣቅ አንከተከታቸው። ከዚያማ በኋላ ምን ይጠየቃል? መሬት ይዞታ ይሔዳል ይፈቀድለታል። ባንክ ቤት ይሔዳል ብድር እጅ ተነሰቶ ይሰጠዋል።...» ሲሉ እማማ ረታሽ ቤተኛውን ሳቅ አሸነፈው።

«ሃምሳ አለቃ አቅልጥ መዝናኛቱንም ይችልበታል። ለአለቆቹ ሐረርጌ ዕረፍት ሔጃለሁ ብሎ እሱ ምዕዋ ቀይ ባህር ላይ በመርከብ ሊዝናና ሔደ። አንዷን የመኳንንት ልጅ አስኮብልሏል። የመርከቦኞቹ አዛዥ ከጃንሆይ ጋር ስላየው መድፍ እያስተኮስ ተቀበለው ይባላል» አሉ እማማ ረታሽ።

«አገሪቱ ፊርማቶሪ የላትም እንዴ?» አሉ አባባ ኃይሌ አብረው ሲስቁ ቆይተው።

«ፊርማቶሪ? ፊርማቶሪ እኮ ሰው ነው። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተ ሳሳቀውን ስንት እንጀራ ቢበላ ነው ቀና ብሎ የሚያየው? የትኛውስ ወንድ ነው እንዲህ አይነት ሰው ልከውብናል ወይ ብሎ ንጉሡን የሚጠ ይቀው?» ሲሉ ረታሽ መለሱ።

አባቴ በጣም ሰንቶ በድጋሚ ፋክቱሩን በእኔና በአባ ዘለቀ አስነበበ። ሁላችንም ሕጋዊነቱን አረጋገጥን።

«ኮሪያ አልዘመተም እያልሽን ነው ረታሽ?» አሉ አባባ ታደሰ በጣም ተገርመው።

«ኧረ እሱ አቴ ጀግኖቹ ኮሪያም፣ ኮንጐም ይዘምታሉ አይደል? ከነሱ ጋር በጨዋታ ወሬዋን ልቅም አድርጉ ያጠናል። በሚቀጥለው ቀን የራሱን ሳንቲካ አክሉበት ዋናው አዋጊ እሱ ሆኖ ቁጭ ይላል» አሉ እማማ ረታሽ።

አባ ዘለቀ ከቤተኛው ጋር እየሳቁ «ቀልቤ አልወደደውም ነበር። ከልክ በላይ ቀደም ቀደም ያለው ጌቶች ፊት ቢያሳዩት ይሆን?» አሉ የተቀመጠበትን ወንበር እያስተዋሉ።

«አቅልጥ ከመኳንንቱና ከመሳፍንቱ ጋር መቀናጣት የሚችለውን ያህል ከድሃም ጋር አብሮ ቆርሶ መብላት ያውቅበታል። ቡና በስኳር ነው የሚጠጣው ጨው ቤቱ በስኒው ጠብ ሊያደርግበት ሲል የኔን ባዶውን ስጡኝ ይልና ከኪሱ ስኳር አውጥቶ ይጨምራል። ለቡና ቁርስ ደረቅ እንጀራ ከቀረበ ከኪሱ ቆልማማ የማሪቆ ቃሪያ አይጠፋም። ቁርጥ ሥጋ በቀረበበት ሲደርስ ሴንጢውን ከጉኑ፣ እዋዜውን ካኖረበት ያወጣና መሙተሩን ይያያዘዋል። እመብርሃንን ነው የምላችሁ አቅልጥ የትም፣ ምንጊዜም ዝግጁ ነው» አሉ እማማ ረታሽ ወሬያቸውን ሲያሳርጉ።

«አንቺ ይሼን ሁሉ ከየት አጠናሽው?» አለች እማዬ ተገርማ ሲኒዋን እያነሳች።

«የእልፍነሽ ውሽማ አልነበረ»

«እልፍነሽ የኛ»

«ጓሳስ!»

«ይሼ እያሳቀ ይተኛታል የሚባለው ነው እንዴ? »

«እወቅሽው።»

ተገረሙ ተደነቁ አጀብ ጉድ ተባለ።

ከስማይ የወረደ ይመስል ሃምሳ አለቃ ደምሰው ተመልሶ መጣ። ልክ ጃንሆይ ሳይታሰብ የደረሱ ያህል ቤተኛው ተደናግጦ በአንድ ላይ ነዎር አለው።

«ኧረ በወላዲት አምላክ! አትነሱ። አሁን ከእዚህ ወጣ እንዳልኩ መምሬ ከበደ ቤት ስልክ ተደውሎ ጌቶች እንደሚፈልጉኝ መልዕክት ደረሰኝ።

«ጌቶች!?» ቤተኛው በድንጋጤ አንድ ላይ አስተጋባ። የእባባ ጃንሆይ ኃያል መንፈስ የታዳሚውን ቀልብ ጨምዶ ያዘው።

«እዎን ጌቶች እዚህ እናንተጋ ለጉዳዬ ስመጣ የምገኝበትን አካባቢ ካምፕ አስታውቄ ነበር፣ መምሬ ከበደ ቤት ስልክ የተደወለልኝም ለዚሁ ነው። አንድ ገስጋሽ አሽከር ወደ እኒ ሲመጣ መንገድ ተገናኝንና መልዕክቱን ነገረኝ። መምሬም ጌቶች መጥተው የቂርቆስን ደብር እንዲጉበኙላቸው ጠየቁኝ። ምንም ችግር እንደሌለ አሳስብኳቸው። አሁን በሴቼንቶ በፍጥነት ጊቢ መድረስ ይኖርብኛል። ኪሴ የያዝኩት ድፍን መቶ ብር ስለሆነ እስኪ አንድ አራት ብር ካለህ ስጠኝ?» አለ አባቴን እያየ።

ሁሉም ሰው ኪሱ ገባ። አባ ዘለቀ ወደ ደረት ኪሳቸው እጃቸውን ሰደዱ። «የደብራችን አለቃ ያሉት ልክ ነው። ጌቶች ደብራችንን ቢጉበኙልን ታላቅ ሞገስ እናገኛለን።» አሉ ኪሳቸው ውስጥ ብር እየፈለጉ።

አባቴ በሁለት ኪሶቹ እጆቹን አስገባ። እማማ እረታሽ መሐረባቸውን ከጉያቸው አወጡ። የአስር አለቃ አበበ ኪሶቻቸው ገብተው ገበሮቹን በፍጥነት ገለበጡ። እኔም እጆቼን ኪሶቼ ውስጥ አገኘኋቸው። አባቴ ከሁሉም ቀልጥፎ ድፍን እምስት ብር አወጣና «ሮጬ ሴሼንቶውን ይገፍ ልምጣ?» አለ እንደ ታዛዥ ንቁ ልጅ።

«ግዴለም ራሴው እደርሳለሁ።» አለና እምስት ብሩን ተቀብሎ እመስግኖ ሔደ። 'እላዲን ኤንድ ዘላምፕ' ታሪክ ውስጥ የእሮጌው ኩራዝ ጂኒ ሁሉን እንደሚያፈዝ፣ ሃምሳ አለቃ ደምሰውም በታላቁ ሰው መንፈስ ሁላችንንም አፈዘዘን። አባ ዘለቀ ቀድመው ነቅተው «ፉንጋይ ሩጥና አካሔዱን አይተህ መጥተህ ንገረን» አሉኝ በለሆሳስ። ትእዛዛቸውን ተቀብዬ እናቴን ዞሬ እየጓት። በጥቅሻ ሐድ አለችኝ። ፈትለክ ብዬ ወጣሁ።

ትልልቅ ሰዎችን ሳስተውላቸው ልክ እንደሽንኩርት ተመስለው ይታዩኛል። ሽንኩርት እንደኛውን ግልፋፊ ሲላጡት ሌላኛው ቀጥሎ ብቅ ይላል። ሰዎችም እንደኛው ባህርያቸውን አንዱ ወገን ሲያውቀው፣ ሌላኛው በፍጡም ሳያውቀው እስከ ህልፈት ይኖራል።

እኛ ልጆች ግን ከግለጻው እስተዋይ፣ ፈሪ፣ ደፋር፣ አቃጣሪና ሌባ መሆናችንን እርስ በራሳችን አሳምረን እንተዋወቃለን። «ልጅ እግሩ እየረዘመ ሲሔድ ክንፉ እያጠረ ይሔዳል» እንዲሉት ሊቃውንቱ በሒደት እኛ ልጆቹ የምንበረሰባችን አካል እንሆናለን።

ከተሳከብት ተመለስኩ። ሃምሳ አለቃ ደምሰው በሴቼንቶ ተሳፍሮ መሔዱን ማየቴን ነገርኳቸው። ነገርግን ከመምሬ ከበደ ጋር መንገድ ሲተላለፉ የእግዜር ሰላምታ እንኳን አለመዋወጣቸውን ትንፍሽ አላልኩም። እጀብ ተባለ። ሁሉም የመሰላቸውን ሃሳብ ሰነዘሩ። አባ ዘለቀ ተነሱና አሳረጉ። ጐረቤቶቻችን እየተገረሙና እየተደነቁ የዓለም የሲሳይ እንዲያደርገው እየመረቁ ወደየመጡበት ሔዱ። አባቴም ለሦስተኛ ጊዜ ፋክቱሩን አበንበኝ። በሕይወቱ በለመማሩ የተቆጨው የዚያን ዕለት ነበር። እኔ ግን አሪፍ ፊልም እንዳየ ደስ ብሎኝ ስለ ሃምሳ አለቃ አቅልጥ ለንደኞቹ ላወራ ወደ ውጪ ወጣሁ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮም ጎረቤቶቻችን አዘውተረው እኛ ቤት ማምሸት ጀመሩ። አባቴ ለሬዲዮኗ ልብስ አሰፋላት። ጠላ የጠመቁ ጎረቤቶቻችንም አባቴ መጥቶ ገድ እንዲላቸው ይጋብዙታል። ሬዲዮኑን ይዞ ይሄድና እየጠጣ ይከፍታታል። የተጠመቀው ጠላ እጅግም የማይጥም ቢሆን እንኳ፣ ስለሬዲዮ ወሬ ሲሉ አላፊ አግዳሚው ገብቶ ጠላውን እየጠጣ በዘመኑ ጥበብ እየተወያየ ዜናዎቹን ያደምጣል፣ ይወያያል፣ ይከራከራል። በጨዋታው መካከል ከመካከላቸው አንዱ እኔን ያስተውልና "ዜራሞ ይሼ ልጅህ ነው?" ሲል አባቴን ይጠይቀዋል።

"እዎን!"

"ስንት ዓመትህ ነው?"

"አስራ ሁለት።"

"ስንተኛ ክፍል ነህ?"

"ስድስተኛ።" ሁሌም ስመልስ አንድ ክፍል እጨምራለሁ። አባቴ የሃፍረት ፈገግታውን ያሳያል።

እኔ እቁነጠነጣለሁ።።

ጠያቂዬም በአድናቆት "ፐ! ጨርሰሃል እኮ! ምን ቀረህ? ጎበዝ! ዋናው ስድስተኛ ክፍል መድረሱ ነው።። ሌላው ቀላል ነው" ሲል ያበረታታኛል።።

አንድ ቀን ሬዲዮኑን እከፍታለሁ ብዬ ጣቢያ በመቀየሬ እየ ተንኮራኮረ ፀጥ አለ።። በዚህ ጥፋቴ ልቤ እስከሚጠፋ ተገረ ፍኩኝ።። ሬዲዮኑም ጣቢያው ሳይስማሰተካከል ለዕለታት አልተከ ፈተም።። በዚህም ሬዲዮ ሊያጌምጥ የመጣው ሁሉ እኔን ብቻ ሳይሆን ትውልዱን ክልፍልፎች ሲል ረገመን።። "ምን አለ አርፈህ ብትቀመጥ?" እያሉ በጥያቄ አፋጠው ዳግም ምንም ነገር እን ዳልሞክር ገደቡኝ።። ጉረቤታችን ያሉት መምህር ተጠርተው አስተ ካክለት ርቀን የሰነበተውን ደስታ መለሱልን።።

በሰፈራችን አንዳንድ የምንወዳቸው የሬዲዮ ፕሮግራሞች እየተፈጠሩ መጡ።። ትልልቆቹ ሰዎች እነአሳምነው ገብረወልድ እሚያዘጋጇቸውንና የመምሬ አብራራውን ፕሮግራሞች ሲወዱ፤ እኔና ጓደኞቼ ሰለሞን ተሰማና ነጋ ወልደሥላሴ የሚያዘጋጁትን የስፖርት ፕሮግራም ማፍቀር ጀመርን።። የዘፈን ምርጫው የጋራ መደሰቻችን ሆነ።።

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዘቦት ቀን ምሽት የሚተላለፍ ፕሮግራም ሴቶቹን ያበሳጫቸዋል።።

"...ጣፋጭ ቮርባ ለማዘጋጀት በመጀመሪያ ብረትድስት ይታ ጠብና በምድጃ ላይ ይጣዳል።። ከዚያ ሽንኩርቱ ተክትፎ ይጨ መራል...

"ፎቃቃ የሰው ፎቃቃ! አምጪውና አሠራሩን ከእኛው ትማ ሪዋለሽ!" እማዬ ሬዲዮኑ ላይ አፍጣ በቁጣ ትመልሳለች።።

"የጥርስን ጤንነት ለመጠበቅ አዘውትሮ ውተት መጠጣት ጠቃሚ ነው"

'የአይጥ መቅረዝ ድመት ሲያየው ይጠፋል' ይላል የአገሬ ሰው መች አጣነው? አምጪው እስኪ በማንቆርቆሪያ ስጪልጠው አሳይሽ ነበር።።"

"አካላችን የተመጣጠነ ፕሮቲን እንዲያገኝ ቀይ ሥጋ..."

እማዬ ከትክት ብላ ትስቃለች "ዜራሞ፣ ዝጋልኝ ይህንን ሬዲዮ።። 'መብሰሉ የማይቀርለት ጭንቅላት የሰው ማገዶ ያስ ጨርሳል' አሉ።።

አባቴ እየሳቀ ሬዲዮኑን ዘጋው።።

እሱንም የሚያበሳጨው ፕሮግራም ነበር።። አንድ አይነት ክብረ በዓል በአገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር በሬዲዮ ስለ ዕለቱ አለባ በስ ይለፈፋል።። በዕለቱም መኪንንቱና ወይዛዝርቱ በሬዲዮ የታዘዘውን ዓይነት ልብስ ለብሰው ወደ ቤተመንግሥት ይሔዳሉ።።

"የወንዶች አለባበስ ሱፍ ዝርዴን ቡ..." ብሎ ሬዲዮው ለፋፊ ተናግሮ ሳይጨርስ አባቴ በንዴት ቱግ ይልና "እነዚህ ስምች የእውነት እያበዱ ነው።። የእኛንም እንጀራ ዘግተው የአገር ባህልን እያጠፉ እንደሆን አይገባቸውም? እሺ ምን ሠርተን እንኑር?" ብሎ በቁጣ መወርወሪያውን አርቡ ላይ ይጥላል።።

"የወይዛዝርት አለባበስ..." ይልና የሬዲዮ ለፋፊው የፈረንጅ ጨርቅ በያይነቱ ሲጠራ፤ አባቴ ሸማ መጠቅለያውን ያነሳና አርቡ ላይ ጥሎ ከጉድጓዱ ይወጣል።።

"ጉድ እኮ ነው ማነው የብር ዋንጫውን ጥበብ? ጥልፉን? ኩታና ቀሚሱን ድሮ የሚለብሰው? ወይዛዝርቱ አልነበሩም? አሁ ንስ? ይኼ ሱቲ ምን ይረባቸዋል? ባሎቴ የት እንሒድ? በአገ ራችን መሬታችንን ባላባት ወሰደው፤ በከተማ ደግሞ ሥራችንን ሱፍ ገበርዲን፤ ሱቲና ሻማ ጨርቅ እየነጠቀን እኮ ነው" ይልና ሬዲዮኗን ተንደርድሮ ይዘጋዋል።።

ዕለታት አልፈው በቴሌቪዥን አበባ ጃንሆይን ነጭ በነጭ የአገር ባህል ልብስ ለብሰው ካያቸው ደስ ይለውና "የእኛ ዋና መለያችን ድፍን ዓለም የሚያውቀን በዚህ ቆንጆ አለባበሳችን ነው።። ታያቸዋለህ ጃንሆይን እሱ ራሱ መድኃኒዓለምን አልመሰ ሉም? መኪንንቱስ ቢሆን ነጭ በነጫቸውን ለብሰው ከበዋቸው ሲሰተዋሉ መልአክ ይመስላሉ።። ቤተክርስቲያናችን በዚህ በኩል ቁም ነገረኛ ነች ተአምር ቢመጣ ውሏን አትስትም።። ይሀንን ነው መማር ያለብን።። ለእኔ ሽመናዬ ይጐዳል እይደለም ስጋቴ።። የእኔ ስጋት ባህላችን እንዳይጠፋ ነው።። ቆይ አንተም ትንሽ ከፍ ስትል ነጭ በነጭ አሰፋልሃለሁ" ይለኛል በፍቅር ዓይን እያስተዋለኝ።። "ባህላችን መጥፋት የለበትም።። ጃንሆይ ልጆቻቸውን ያስተምሩ፤ እኔም አንተን ማሳወቅ ግዴታዬ ነው።። ጋሼ! ብርዝ መድኃም ትፈልጋለህ?"

አስነጠሰኝ።።

"ይኸው ሆዴ ንፁህ እኮ ነው፤ እውነቱን እናገረኝ።። አንተ ለልጄ ብርዝ ቅዳለት።።"

በሌላ ቀን መንደርተኛው እኛ ቤት ቡና ሲጠጡ ሬዲዮኑ ተከፍቶ ወጋቸውን ያደምቃል።። አንድ አስተዋዋቂ ድምፅ *"ምግብ አልበላ ይሉታል? ወይንስ ከተመዝቡ በኋላ በሆድ ዕቃዎት ውስጥ ያለመፈጨት ችግር አለብዎት? አይሰጉ አንዱሩስ የተበት ጨው አለልዎት...*

መንደርተኞቹ ሁሉ ደማቸው በቁጣ ፈልቶ "አዬ ግፍ! አዬ ጡር! አሁን እኛ አገር እህል አልበላለት ብሎ የእንግሊዝ ጨው የሚያስፈልገው አለ?" ይላሉ።።

እማማ ደስታ የተረት ያህል ደስ የሚለውን ትዝታቸውን ያወጋሉ።። "ደጃች ውቤ እህል አይበላላቸውም ነበር።። ስለዚህ አስ ጎምጂ ቀጠሩ።። አሰጎምጃቸው የተዋጣለት፣ እኔ ነኝ ያለ ሆዳም

ነው። ደጃች ውቤ ትንሽ እህል መቅመስ ሲፈልጉ 'እስኪ ያንን አስጎምጂዬን ጥሩልኝ' ይላሉ።

"ተጠርቶ ይመጣል። ቡሩንዶ የሆነ ጮማ ሁለት ጎበዝ በት ከሻቸው ተሸክመው እፊቱ ይቆማሉ። አጅሬም ቢላውን ያፏ ጭና ከቡሩንዶው ላይ ይመትራል። አዋዜውን ያጠቅስና ዋጥ ስል ቅጥ ሲያደርግ፣ ደጃች ውቤ አፋቸው ምራቅ ይሞላል። አስጎ ምጂው አሁንም ሙዳ ሙዳውን እየቆረጠ ይውጣል። ይኼኔ ደጃች ውቤ 'በቃህ!' ይሉናል አሳቸውም ቢላቸውን ያነሳሉ። ይህ እንግዲህ አስጎምጃቸው የሳቸው አንዱሩስ የጉበት ጨው መሆኑ ነው።"

ሬዲዮ ለእኛ ሠፈር ሰዎች ሌላው የዓለም መመልከቻ መነ ፅር ነበር። ከምንኖርበት አካባቢ ውጪ ያሉትን ሕዝቦችና አገ ሮች አቅርቦ ያሳየናል። በዚህም እኔን ያስደንቀኝና ያስገርመኝ ስለነበር እኔም ሳድግ ሬዲዮ ውስጥ ቁጭ ብዬ ለማውራት እመ ኖለሁ።

"ዜራሞ፣ ሬዲዮኑን የገዛኸው ለታ የኮሪያው ዘማች ጋኔኑን እው ስጡ አስረውት ነው የሚያስለፈልፉት አለ አይደል? ጋኔን ምንድ ነው?" አልኩት አባቴን።

"ጋኔንማ ጋንጪር ነው።"

"ጋንጪርስ?"

"ጋንጪርማ ጂኒ ነው።"

"ጂኒ ደግሞ ምንድነው?"

"ጂኒማ ሰይጣን ነው።"

"ሰይጣንስ?" አልኩት፤ የበለጠ በጠየኩ ቁጥር መልሶቹ እየጠጠሩብኝ።

"እኔም ሰይጣንን አይቼው አላውቅም። አባ ዘለቀ ናቸው ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሰብኩ የሰማሁት። እሳቸውም እንዲሁ ማስፈራሪያ ያደርጉታል እንጂ ሰይጣንን ያዩት አይመስ ልኝም። ጃንሆይ ግን ምን ይሳናቸዋል?" ሲል በራሱ ሃሳብ ሳቀ።

ባልታሰበ ቀን አባቴ ሬዲዮናችንን ሸጠው። ምክንያቱም አንድ ቀን ሠርቶ የቆረጠውን ጋቢ ይዞ ሬዲዮኑን አንግቶ ወደ ለገሃር ደርሶ ሲመጣ አንድ ነጭ ለባሽ ያዘው።

"ከየት አመጣኸው? ዘርፈህ ነው" አለ ነጭ ለባሹ።

"አልዘረፍኩም። የራሴ ነው። እቁብ ጥዋቼ ባገኘሁት ገንዘብ ነው የገዛሁት"

"ፋክቱርህን አሳየኝ?"

"እቤት ነው ያለው"

"እሺ፣ ከቤትህ እስክምታመጣ ጣቢያ እንሂድና አስመዝ ግበህ ሄደህ ፋክቱርህን ይዘህ ትመለሳለህ።"

ነጭ ለባሹ እየመራው ማይጨው አደባባይ ወደሚገኘው አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ። ዕቃውን ካስመዘገበ በኋላ አባቴ

ታሰረ። የሰፈር ሰው ፈልጎ መልዕክት ወደ ቤት ላከ። እናቴ የሬዲዮኑን ፋክቱር ይዛ አባቴን ለማስፈታት የክርስትና አባቴን ጨምራ ሄደች። ለጣቢያው አዛዥ ፋኩትሩን አሳይታ፣ አባቴ ዋስ የመጥራት መብቱ ተጠብቆለት ተፈታ።

አባቴ "ድሃ በመሆኔ ነው በጣዝ ንብረቴ የታሰርኩት። በንጉሥ እኅር ሰው በጣዝ ንብረቱ ይታሠራል?" እሰና አማርሮ ሬዲዮኑንም ሸጠው።

አንዳንድ ቀን ከጎረቤቶቻችን መካከል "ዜራሞ፣ ያችን ሬዲ ዮንህን ለምን ሸጥካት?"

"ተናድጄ!"

"ምን ያናድድሃል?"

"እኔ ገዝቼው ይዘ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ነው ሲል እያና ድድም?"

ሬዲዮው የፈጠረልን አዲስ ዓለም ቀረ። እንደገና ወደ ድሮው ዓለማችን መመለስ ጀመርን። ሬዲዮው የፈጠረልን ጣፋጭ ማር ተረስቶ ወደ ለመድነው መራር ማር ተመለስን። ጎርኪ እንዳለው '...የዕውቀት ማር በመሆኑ ያው ማር ነው'

እኔ ግን አይቆጨኝም። ሬዲዮናችን ከመሸጡ በፊት እኔ አባቴና እናቴ ሬዲዮናችንን መሐል አስቀምጠን የብርድ ልብስ ከጀርባችን ተጋርደ ፎቶ ተነስተናል። ይህ ፍቶግራፍ በመስ ታወት ተደርጎ ቤታችን ግርግዳ ላይ አሁንም ተሰቅሎ የዘመኑን ትዝታውን ይመሰክራል።

ፋኖ ተሰማራ

ፋኖ ተሰማራ፣ ፋኖ ተሰማራ፣
እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ
(ከድሮ ተማሪዎች መዝሙር)

ዛሬም ልክ እንዳለፈው ቅዳሜ አቆራርጠን ፈረንሣይ ለጋ ሲዮን በመሄድ ከአሸናፊ ፔሌ ጋር ስንጫወት ለመዋል የድሮ ሰፈሯ ልጆች ጉዞ ጀመርን። ፈረንሣይ ለጋሲዮን ስንደርስ ፔሌ በለመደ እግሯ እየመራችን ጫካው ውስጥ ገብተን እንሽሎኮስ ካለን። ወይም ሜዳ ላይ ወጥተን ኪስ ተባድነን ስንጫወት አሸናፊ ፔሌ 'ሞሳ አትሠራብኝም። በችሎታችን ዝቅ ያልነውን ልጆች ቶሎ ቶሎ ኪስ እያቀበለችን ጥሩ ተሳታፊ እንድንሆን ታደርገናለች። ጎል የማግባት ዕድሉንም ስትሰጠን ራሳችንን በቡ ድናችን ውስጥ ተፈላጊ ልጅ አድርገን እናስባለን።

አረፍ ብለን ስለ አዲሱ ሰፈሯ ጉሮ ታወጋናለች። አረን ጓዴው መስክ ላይ ተኝተን እንሰማታለን። ታሳቅ እህትዋ ቤተልሔም ምሳ መድረሱን መጥታ ትነግረናለች። እማማ አወጣሽ አቅርበውልን ዞር ሲሉ የትሪውን እንጀራ በአንዴ ጥርግ አናደርገዋለን። ፍራንክ ካለን በሰሙኒ አንድ ጠርሙስ ወተት ገዝተን ተከፋፍለን እንጠጣለን።

ሁሌም ወደ ፈረንሚይ ለጋሲዮን ስንሔድ እግረ መንገዳችንን ሌሎቹንም ሰፈሮች እየጎበኘን ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴያትር ደረስን። ቴቲያትር ቤቱ አጠገብ ያለው ሱቅ ውስጥ ደስ የሚል ልብስ የለበሰ አሻንጉሊት ወደውጭ በመስታወት ውስጥ አፍጦ ይታያል።

ቀጢሳው አሻንጉሊቱን "ጤና ይስጥልኝ ሚስተር ስሚዝ!" ሁላችንም መሳቅ ጀመርን።

"እባኮትን ልብስ እንለዋወጥ!" አለና የነተበ ኮቴን ጎትቶ ለአሻንጉሊቱ አሳየው።

አሻንጉሊቱ እንደተገሸረ ነው።

"እረ አይዘንጡብኝ።"

እኛ በሳቅ እንንከተከታለን።

"አትጠፉም ከዚህ!" አለ አንድ አስደንጋጭ ድምፅ። ዞረን ስናይ በጠራራ ፀሐይ ካፖርት የለበሰ ዘበኛ ነው። ብትን አልን። ራቅ ብለን ተሰባሰብንና ጉዞአችንን ወደ ፒያሳ አቀናን።

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ" አለ ቀጢሳው፣ ባንኩ ላይ የተፃፉትን ፊደላት ቆጥሮ እያነበበ።

"አይ ቀጢሳው! ብትማር እኮ አንጎል ነበረህ!" አለ ጎቢጥ።

"መማር እፈልጋለሁ። ግን አስተማሪዎቹ ከፉዎች ስለሆኑ ይጋረፋሉ" አለ በቅሬታ።

እኔ ስለዚህ ትልቅ ፎቅ ያለኝን እውቀት ለጓደኞቼ ላካፍ ሳቸው ፈለግኩ። "ይኼ ፎቅ እኮ በጣም ትልቅ ሰለሆነ አንድ ቀን ይናድ ይሆናል። እኔና አባቴ በዚህ መንገድ ወደ መርካቶ ስንሄድ እዚህጋ ስንደርስ አባቴ ቶሎ ነው እሚያልፈው።"

ሲሳይ ጎቢጥ በመገረም አንድ ዓይና መነፅሩን አወለቀና "አንዴት ይናዳል? ይኼኮ በሲሚንቶ፣ በብረት፣ ደግሞ በውሃና ድንጋይ ተደርጎ ነው የተሠራው።"

"ይሠራ! ቢሠራስ? አንተ ደግሞ ከትልቅ ሰው ትበልጣለህ? እንዴት እኔ አባቴ የነገረኝ ነው እያልኩህ ውሸቴን ነው ትለኛለህ?"

ቀጢሳው "ልጆች! ልጆች" አለና ተጣራ እንዳንጋጠጠ ሁላችንም እንደርሱ ወደ ሰማይ አንጋጠጥን።

"ከጉሙ ጀምራችሁ ወደታች ወደፎቁ ተመልከቱ አይታ ያችሁም? ፎቁ ይነቃነቃል።"

ሲምላል ንፍጡን በኮቴ እጅጌ ሞዠቅ አደረገና አፈጠጠ። "እውነትም!" አለና ፈትለክ አለ። እኛም በፍጥነት ተከተልነው።

"ይኼውልህ ጎቢጥ፣ አየህ አይደል? አንተ ከትልቅ ሰው አትበልጥም። ፎቁ ይነቃነቃል" አልኩት። ቀጥዬም "ይኼ በሩ ላይ እንደ ትልቅ ኪስ የተቀመጠው ወርቅ እኮ አይደለም" አል ኳቸው፣ ፎቁ ሲናድ እንዳይጎዳን ራቅ ብለን በቆምንበት።

"እሪ ወርቅ ነው" አለ አብነት ባሪያው።

"አይደለም። እማዬ እንደነገረችኝ፣ በታኅሣሥ ግርግር የተተኮሰውን የመዳብ ቀለሃ አባባ ጃንሆይ አሰብስበው ተቀለጠና ድቡልቡሉ ድንጋይ ተቀባ!"

"አንተ ከአባትህና ከእናትህ ጋር ስለምታወራ እንደፈለክ እየጠየክ ይነግሩሃል። እኛ ግን ማን ይነግረናል? ልክ ነህ። ሊሆን ይችላል" አለ ቀጢሳው።

ከወላጆቼ ያገኘሁትን ዕውቀት ቀጢሳው ስላመነልኝ ወደ ድኩት። ሲሳይ ጉቢጥ ስለተከራከረኝ ጠመድኩት። አባቴ የክቡር ዘበኛ መሥሪያ ቤት ባልደረባ ስለሆኑ ስለመሣሪያ ከተነሳ እኔን ብቻ አድምጡኝ የሚል አባዜ አለበት። እኔ ግን አኮረፍኩት።

የሽቦ መኪናችንን እየነዳን ቸርቸር ጎዳናን ወጣን። ፒያሳ ደስ እሚሉ ቆንጆ ልብሶች ያለባቸውን ብዙ ሱቆች አየን። አንደኛዋ ሱቅ ስንደርስ ጎቢጥ "ልጆች! ልጆች"! ብሎ ጠራን። እጅብ አልንና አፈጠጥን።

ደስ የምትል ነጭ የስፖርት ጫማ ተረከዝዋን ሚስማር ላይ ሰቅላ ትታያለች።

"ለእኔ አረፍ ነች" አለ ጎቢጥ በበረባሶ የተከረከረውን እግሩን እያስተዋለ።

"ለእኔ ነው አረፍ የምትሆነው" አለ አብነት ባሪያው።

"ውይ! እኔ ባገኛት!" አለ ውሮ ቁንጮውን እያከከ።

"እባካችሁ ይኼ እኮ የሀብታሞች ሱቅ ነው።"

"ተው ባክህ፣ ስናድግ ትምህርታችንን ሰንጨርስና ሥራ ሰንገባ እንዛዋለን..." አለ ጎቢጥ በርግጠኝነት።

አንድ አሞር እንደ እንጨት በርሜል የተድበለበለ ሰውዬ ተቆጥቶ ከሱቁ ብቅ አለና "ጥፋ ከዚህ! የስሙኒ ልጅ..." አለ።

ተበተንን።

ሲሳይ ጎቢጥ ግን እንደተቆጣ ቆሚል። "ማነው የስሙኒ ልጅ?" አለው የስድቡ ነውረኝነት ገብቶታል።

"አትሄዱም!" አለና ብትር ሊያመጣ ወደ ሱቁ ተመለሰ።

"ማንን ነው የስሙኒ ልጅ ያልከው?!" አለ ጎቢጥ እንደ ተናደደ።

ሰውዬው በጠርሙስ ውሃ ይዞ መጣና ይረጨን ጀመረ። ሁላችንም ሳቅንበት።

ጉዞአችን ፒያሳን መሐል ለመሐል አቋርጠን ወደ አራት ኪሎ ሆነ። ሐውልቱ አካባቢ እንደደረስን "ይህችን ሐውልት አቤ አይዘላትም?" አልኩት ሲሳይ ጎቢጥን።

"ይህችን? አይደለም አቤ፤ ማሞ ወልዴም ይዘላታል። አበበ ቢቂላ የቱን ይዘላል መሰለህ? የዋቢ ሸበሌን ሆቴል ፎቅ ታውቀዋለህ? ማይጨው ዓደባባይ ጋ ያለውን?

"አዎን።"

"እርሱን ፎቅ በደንብ ይሻላል!" አለኝ በእርግጠኝነት።

"የዋቢ ሸበሌ ፎቅ እኮ በጣም ትልቅ ነው።"

"ይሁና! አቤም እኮ ዓለም ላይ የሚገኙ ሰዎችን ሁሉ ተሰብስበው ሁሉንም በማራቶን ቀድሞዋቸው አንደኛ የወጣ ጀግና ነው።"

"ልክ ነው" አለች መኩዬ ቀጫጫው፣ ፎሮፎራም ጭንቅላቷን እየፎከተች።

አበበ ቢቂላን እኔ በአካል ዓይቼው ስለማላውቅ፣ እነጎቢጥ ስለአካሉ እርዝመትና አንድ ወጥነት እያወጉኝ ወደ ስድስት ኪሎ ወጣን። ጎቢጥ አንድ ቀን አበበ ቢቂላ ካምቦሎጆ ተለማምዶ ሲወጣ አግኝቶት ጨብጦት እንደነገረኝ፣ ጎቢጥ ቁመቱ አበበ ወገብ አካባቢ ደርሷል።

ከርቀት የክሌጅ ተማሪዎች ጭፈራ ይሰማናል።

ፋኖ ተሰማራ፣ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼጉቬራ

መጨፈሩን ያቆሙትና በየመሃከሉ በአንዱ ባይነት በሌሎቹ ተቀባይነት ቢጎይል ጮኸው ይናገራሉ።

መሬት ላራሹ!
መሬት ላራሹ!
ፊውዳሊዝም ይውደም!
ይውደም!

እሚሉት ባይገባንም፣ በካርቶን ላይ የጻፉት መልእክት ባይ ነበብልንም ደስ ብለውን ቆም አልን። በአካባቢው የነበሩ ትልልቅ ሰዎች ግን ከቦታው በፍጥነት ይሰወራሉ።

"ይህ ነገር ጭፈራ አይደለም! ታዲያ ምንድነው?" አለ ቀጪሳው

"ሰላማዊ ሰልፍ ነው፣ ከዚህ አካባቢ እንጥፋ" አለና አብነት ባሪያው ፈትለክ አለ። እኛም ፍርሐት ተጋባብንና አብረን ተፈተለክን።

አብነት የአዲስ አበባን ጓዳ ጎድጓዳ አሳምሮ ያውቀዋል። በዚያ የገርነት ዕድሜ የከተማዋን መውጫ መግቢያ እንድንለይ የካፒቴናችን ብቃት በእጅጉ እንደረዳን በደንብ አስታውሳለሁ። በተለይም፤ ያችን የጭንቀት ቀን በውስጥ ለውስጥ መንገድ አቆራርጠን እሪ በከንቱ ደረስን። ጉራንጉሩን ዘልቀን አሮጌውን ቄራ አልፈን

ተረት ሰፈር፣ ከዚያም ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ በሰላም ደረስን። ሰፈራችንን ቁልቁለ አየናት።

የለገሀር ባቡር ጣቢያ ከማዶ ታየኝ። ከባቡር ጣቢያው በሰተ ጀርባ ሰፈራችን ቂርቆስ ነው። እናቱ ጉያ እንደሚገባ ሕፃን ቧረቅን። እዚህ ቸርችል ጉዳና አካባቢ ሕይወት እንደድሮዋ በፀጥታና በሰላም እንደቀጠለች ነው። አላፊ አግዳሚው በሰላም ያልፋል ያገድማል። ቁልቁል ወደ ሰፈራችን ሳንጣደፍ እያዘገምን ስንሔድ የተማሪዎቹ መዝሙር ትውስ አለኝ።

ፋኖ ተሰማራ፣ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆችሚኒ እንደ ቼጉቬራ! ምን ማለት ነው?" አልኩኝ።

ቀጪሳው ከአፌ ነጥቆኝ "ቼ! አታውቅም? ቼ ፈረሴ ቁና ገብሴ ነዋ!"

«ምትሃተ መስከት»

'ሰለ ይህም ሰዎች ሲመረምሩ አይፈልጉም።
አሰምርመሬ ከአባቶቻቸው የሰሙትን ሲያምኑ ይመርጣሉ።"
ፈላስፋው ዘርአያዕቆብ

ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት አባባ ጃንሆይ የነገሡበት 30ኛው ዓመት የዘውድ በዓል ሲከበር የቴሌቪዥን ጥበብ ከባህር ማዶ ወደ አገራችን ገባ። ዜናው እኛ ሰፈር የደረሰው ዘግይቶ ነበር። አንድ ቀን ማታ ተሰባስበን ስንጫወት ከመካከላችን ሲሳይ ጎቢጥ አልነበረም። በበነጋታው ቅዳሜ ጠዋት ፀሐይ እየሞቅን ፌታችንን ስንታጠብ ሲሳይ መጣ።

"ልጆች!" አለ በተደነቀ ድምፅ"ትናንትና ቴሌቪዥን አየሁ። ብታዩ...!" ብሎ የነገረን የወሬ ዝርዝር ለማመን የሚያስቸግር ነበር።

"ልክ እንደ ሬዲዮ ፕሮግራም ምን እንደሚያቀርቡ ሴት ዮዋ በቴሌቪዥኑ ውስጥ መጣችና ተናገረች። አምን በአማርኛ! ከዚያም ዜና ተነበበ። ከዚያም አባባ ጃንሆይ ታዩ! በመቀጠል ዳንስ፤ እንጥላሁን ሲዘፍኑ አይተን ከአባቴ ጋር ወደ ቤት መጣን። ሰው ሁሉ ፀጥ ብሎ ነበር የሚከታተለው። አቤት ደስ ሲል! ቴሌቪዥን ያየነው ርግብ ጠጅ ቤት ነው።" በማለት ሲሳይ ጎቢጥ በመደነቅ ዝርዝሩን አጫወተን።

ርግብ ጠጅ ቤት ለሰፈራችን በጣም ቅርብ ነው።

"አሁኑኑ ሄደን እንየው?!" አለ ቀጢሳው።
"የሚከፈተው ማታ ማታ እኮ ነው" ሲሳይ ነቢጥ አረመው።

ዕለቱ እስኪመሽ በጣም ረጅም ቀን ሆነብን። የአረንቻታ መጠጫ ያላቸው ልጆች ማታ ርግብ ጠጅ ቤት ስመገናኘት ቀጠሮ ተያያዙ። እኔ ወደ ቤት ሄጄ ስለአባቴ ስለ ሰማሁት አዲስ ዜና ስነግረው ምንም ሳይደነቅ "ምን ችግር አለው? አንድ ቱባ ማግ አዳውርልኝና ማታ ርግብ ጠጅ ቤት ወስጀ አሳይሃለሁ።"

እናቴም እንደ እኔው ጓጓችና "አንተ ትናንትና አይተሃል ማለት ነው?"

"ሊጋሼ! ወሬው ወደ ጆሮ የደረሰው ዘግይቶ ነው!" አለ አባቴ እኔን እያስተዋለ።

"ወይኔ! እኔን ሳትወስደኝ ብቻህን ሄደህ ታያለህ?!" አልኩና እየተቆጨሁ ማዳወሪያውን አዘገጃጅቼ ማዳወር ጀመርኩ።

"ጋሼ! አንተ የሞላልህ ነህ። እኔ ቴሌቪዥን እያየሁ ልገ ናና ብል ያንተንና የእኔን ሆድ ማን ይሞላልናል? ስማንኛውም ማታ ርግብ ጠጅ ቤት ነን!" አለና ሥራውን ቀጠለ።

የተናፈቀው ምሽት ደረሰ። ተያይዘን ርግብ ጠጅ ቤት ሄድን። ሁለት ሰዓት ላይ ቴሌቪዥኑ ተከፈተ። ፕሮግራም አስተዋዋቂዋ ብቅ ብላ በዕለቱ ምን እንደሚቀርብ ነገረችን። ተከ ትሎም ዜና አቅራቢው ብቅ አለ።

"ይኼውልህ አሳምነው ገብረወልድ ማለት ይህ ነው" አለኝ አባቴ በሹክሹክታ።

"እንደምን አመሻችሁ፣ ዜና እናሰማስን። ዜናውን የማሰ ማችሁ አሳምነው ገብረወልድ ነኝ። በመጀመሪያ ርዕሰ ዜና!"

"ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በዋሽንግተን ዲሲ የሚያ ደርጉትን ጉብኝት ለጠናቀው ወደ መናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ ገብተዋል..."

አስር አለቃ ወልዴ "ጠቅል!" ብለው አቅራሩና ተነስተው በተጠንቀቅ በቴሌቪዥን ለሚታዩት ንጉሠ ነገሥት ሰላምታ ሰጡ።

ጠጅ ቤቱን የሞላው ተመልካች "ቁጭ በል! ቁጭ በል!" በማለት ጮኸባቸው።

አስር አለቃ ግን ማንንም አልከሰሱም፣ ጀርባቸውን ለግ ርግዳ እንደሰጡ ነበር። ጃንሆይ የክብር ዘቡን እየፈተሹ ጠርዙ አካባቢ ሲደርሱ ሰላምታ ሰጡ። ያጀቡአቸውን ትልልቅ ሰዎች እጅ አስነስተው ውብ መኪናቸው ውስጥ ገብተው ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተጓዙ።

አስር አለቃ ወልዴ ሰላምታቸውን አውርደው ቁጭ አሉ። ብርሌውን ጠጅ ከጠረጴዛው ላይ ብድግ አድርገው አንደቀ ደቁት።

አሳምነው ሌሎች ዋና ዋና ዜናዎችን አነበበ። ተመልካቾቹ ግን ዓብይ ብለው በናፍቆት የሚጠብቁት የጃንሆይ ዜና በመ ጠናቀቁ ማውጋት ጀምረዋል። የቴሌቪዥን አሠራር እኛን ልጆ ቹን ብቻ ሳይሆን አዋቂዎቹንም አስገርሟል። "ራዲዮ በጋኔን እንደሚሠራ ሁሉ ቴሌቪዥንም ጋኔን ይኖርበት ይሆን?" ይላሉ። "አባ ጠቅል ምን ይሳነዋል? ረብጣ ባውንዱን ሲቆጥርላቸው ፈረ ንጆቹ እምጥተው ተከሉስት፣ በረከቱ ለእኛም ደረሰ" ብለው ይህ ንን ሳሳያቸው አምላክ ምሥጋናቸውን አቀረቡ።

'ቴሌቪዥን በጋኔን አይሠራም ማለት ነው?' አልኩኝ በሆዴ።

ጓደኞቼን ማየት ጀመርኩ። ሴምላል ንፍጡን በእጅጌው እየጠረገ ቴሌቪዥኑን ያያል። ሲሳይ ነቢጥ ያባቱን ካፖርት ደርቦ፣ ትልቅ ዱላቸውን ተመርኩዞ፣ አፉን በሰፈው ከፍቶ ቴሌ ቪዥኑ ላይ አፍጧል። ቀጢሳውና አብነት ባሪያው በአባታቸው ግራና ቀኝ ተቀምጠዋል።

"ፉንጌ!" አለኝ ቀጢሳው።

ዞርኩኝ።

"አሁን ዘፈን አለ እኮ።"

በጥቅሻ አዎን አልኩት።

"እስኪ ከአረንቻታህ አቅምሰኝ። እኔ የምጠጣው ብርዝ ነው። ከፈለክ አቀምስሃለሁ።"

አባቴ "ወሬ ታወራለህ እንዴ? የሚያነበውን እንድታይ አይ ደል ያመጣሁህ?!" አለኝ።

ቀጢሳውን ትቼ አረንቻታዬን ተጎነጨሁና ቴሌቪዥኑ ላይ አፈጠጥኩ።

ዜና ተፈጸመ። ሙዚቃ ተጀመረ። አንድ ወጣት ዘፋኝ የአገር ባህል ልብሱን ለብሶ ፍንጭት ጥርሱን ብልጭ እያደረገ አኮርዲዮን መጫወት ጀመረ። በዜማም፣

በየቦታው ዞሬ እኔ እንዳየኋቸው
የኢትዮጵያ ምዶች የተዋቡ ናቸው

"ትክክል!" አሉ አስር አለቃ ወልዴ።

"ምን ይጠየቃል፣ እውነቱን ነው!" አሉ አባባ በየነ፣ ግስላ ሲጋራቸውን ቡን እያደረጉ። "ይኼኮ የአገር ፍቅር ቴያትር ኮከብ ድምፃዊ ፍሬው ኃይሉ ነው።"

በራዲዮ በድምፅ የምናውቃቸውን ጋዜጠኞችና ዘፋኞች እን ዲህ እንዲህ እያልን በምስል መተዋወቅ ጀመርን። መልካቸውም ለዘለዓለሙ ሀሊናችን ውስጥ ምስሉን አኖረ።

የፍሬው ሙዚቃ እንደተጠናቀቀ አንዲት ዘፋኝ ተተካች።

"...ሶሚ ብወረውር
አሃ አሃሃ

ደረቱን መታሁት
ኦሃ ኦሃሃ...
ኦወይ ኩላሊቱን
ኦሃ ኦሃሃ..
ልቡን ባገኘሁት
ኦሃ ኦሃሃሃ... እያለች በመዝፈን ዳንሱን ስታስነካው ሞቅ ያለ ሁካታ ጠጅ ቤቱን ሞላው::

"ማነች?" አባቴን ጠየቁት::

"እኔንጃ"

"ዘነበች ትባላለች:: ጃንሆይ ዳንሷን አይተው ሙራ ቀረሽ ኣሏት" አሉ አባባ በየነ::

ፕሮግራሙ ሲለዋወጥ ቆይቶ ወደ እንግሊዘኛ ዝግጅት ተሸጋገረ:: አንድ ወጣት ጋዜጠኛ የዕለቱን ዝርዝር ዜና በእንግሊዘኛ አሰምቶ እልባቱ ላይ ደረሰን:: የአነጋገሩ ቅልጥፍናና ብቃት ሁላችንንም አስገረመን::

"ይህንን ትሰሙታላችሁ? መቼም ጃንሆይ ባሕር ማዶ ልከውት የፈረንጅ አፍ ተምሮ ነው እንጂ፣ እንዴት እንዲህ አቀላጥፎ መናገር ይቻላል?" አለ አባቴ ሲያደንቀው::

ሁሉም አባቴን አመኑት::

"ልዑልሰገድ ኩምሳ ይባላል:: በእርግጥ ባሀር ማዶ ተልኮ የፈረንጅ አፍ ተምሯል" አሉ አባባ በየነ::

እነ ጥላሁን ገሠሠን፣ እነ ብዙነሽ በቀለን ጠብቀን በመቅረታቸው ቅር አለኝ::

"ጋሼ፣ በሥራው ከተግባባን ነገም እዚሁ አመጣሃለሁ::" አለኝ አባቴ::

ፊታችንን ወደ ሰፈራችን መለስን:: በዚያን ጊዜ የመንገድ ላይ መብራት በመንደራችን እከባቢ አልተተከለም:: ድንገት የሚከፈቱና ክፍታቸውን ያሉ በሮች የሚሠሩት የብርሃን እርከን አልፎ አልፎ ይታያል:: የአረብ ቤቶች መብራት በየተንጠለጠለበት ይንጨለጨላል::የአባቴን እጅ ጨብጬ እናዘግማለን:: እማዬ "ይኼስ ቴሌቪዥን እንኳን ያልኖረኝ! ቢኖረኝ ድስቴ ያር ነበር:: አንዱ ወሬ ሲያልቅ ሌላ፣ ሌላው ሲያልቅ፣ ሌላው እያለ በጨዋታ ላይ ጨዋታ ሲደራረብብን ፈዞ መቅረት አይደለም እንዴ?! ሁለተኛ ከእናንተ ጋር አልሄድም" ብላ ወሰነች:: እንዳ ለችውም ሆነ::

እኔና አብሮ አደጎቼን ግን ቴሌቪዥን የማየት ኃይለኛ ሱስ ተጠናወተን:: በነጋታው ማታ ስለ ቴሌቪዥን ምትሃት ሞቅ ያለ ወሬ ይዘን ያየነውን ላላዩ ጓደኞቻችን ስናወራ ዋልን:: ማምሻው ላይ ቦቾራ መጣና "ከፈለጋችሁ በብላሽ ማየት የምትችለብት ቦታ ለገሃር እንሂድ" አለን::

ተከተልነው:: እንዳለውም ለገሃር ባቡር ጣቢያው ፊት ለፊት፣ በሚገኝ አደባባይ ከአንድ ጥግ አባባ ጃንሆይ ሕዝቡ እን ዲያየው ያስቀመጡት ቴሌቪዥን አገኘን::

ቴሌቪዥኑ በብረት በተሠራ ሳጥን ውስጥ ሆኖ በብረት ማማ ላይ ተቀምጧል:: ሕዝቡ ቴሌቪዥኑን ከፍቶ እስከሚጨርስ ይዝናናበትና ዘግቶት ይሄዳል::

እየቆየ ሕዝቡ እቅሙ ያለው ቁሳቁሱን እያፈራ በየቤቱ መመ ልከት ሲጀምር:: እዚህ አደባባዩጋ የሚገኘውን ቴሌቪዥን የሚመ ለከተው ቁጥሩ እየቀነሰ መጣ:: የሚከፍቱትና የሚዘጉት በረንዳ አዳሪ ልጆች ሆኑ:: ጎማ አንድደው እየሞቁ ፕሮግራሙ እስከሚ ጠናቀቅ ይከታተላሉ:: የሚበሉትም የሚጠጡትንም ይዘው ይመ ጣሉ:: ሲጃራም ያጤሳሉ:: የቴለቪዥኑ ትዕይንት ካለቀ በኋላም ዘግተውት እዚያው ድሪቶአቸውን ለብሰው ይተኛሉ:: በእነዚህ ልጆች በጊዜው በጣም ቀናሁባቸው:: 'እኔም እኮ እናትና አባት ባይኖረኝ ኖሮ እዚህ ማታ ማታ ቴሌቪዥኑን እንደ ልቤ አይቼ ከእነዚህ ልጆች ጋር እተኛ ነበር' ብዬ በሆዴ ተቆጨሁኝ::

እንደ መታደል ሰፈራችን ውስጥ ከእኛ ቤት ፊትለፊት ጠጅ ቤት ተከፈተ:: ባለጠጅ ቤቷ ጎደቴ የሚባሉ የወላይታ ሰው ናቸው:: ጠጅ በስሙኒ ሁለት ብርሌ፣ ብርዝ 15 ሚንቲም ሲሆን፣ ትልቁ ለስላሳ መጠጥ በስሙኒ፣ ትንሹ በ15 ሚንቲም ይሸጣል:: ጎደቴ ጠጅ ቤት ቴሌቪዥን ስለነበረው የእኛ ደን በኝነት እየጠነከረ ሄደ:: ፍራንክ ስናጣ ደጅ ላይ ቆመን እን መለከታለን:: አንዳንዴ ዞር እንድንል ተነግሮን ችክ ስንል አንቡላ ይደፉብናል:: ይሁን እንጂ ተመልሰን እዚያው ነን::

የጎደቴ ቴሌቪዥን ባሕርይ ይገርመኝ ነበር:: የዜና አን ባቢው የጌታቸው ኃይለማርያም ድምፅ እየተሰማ ምስሉ ይጠ ፋል:: ጎደቴ ልጃቸውን ይጠሩታል:: ጦና ይመጣና ከጀርባው ቴሌቪዥኑን ጎርጉሮት አንዴ በጥፊ ጎኑ ላይ ሲለው ጌታቸው ኃይለ ማርያም በቅምጡ እንደመደነስ እያለ ብቅ ይላል:: ከዚያ ለረጅም ሰዓታት ያለምንም ብልሽት ግልጋሎቱን ይቀጥላል::

ሰኞ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ላይ ቻርሊ ቻፕሊን 'ዘ ማድ ሙቪ' የተባለውን ፊልም ያቀርባል:: አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው የሚኮምከው:: ያ'ለሚምንት የሚሆነን ሳቅ ያሸምተን ነበር:: እኛም ቻርሊን እየሆንን እንተውነዋለን::

ማክሰኞ 'ስታር ትሬክ' ስታሮቹ እነስፓክ ምትሃት የተሞላ ጥበባቸውን በማሳየት ሕሊናችን ባላሰበበት በኩል እንድናስተውል እያደረጉን በማድነቅና በመገረም የመሰለንን በመናገር ጉንጭ አልፋ ክርክር ውስጥ እንድንገባ ያድርጉን ነበር::

በዚያው ምሽት ከዜና አንባቢ በኋላ ስለሞን ተሰማ ተወዳጅ የሆነውን የስፖርት ፕሮግራም ይዞ ብቅ ይላል:: የራሳችንን አገር የእግር ኳስ ፈርጦችን ጨምሮ፣ የብራዚልን ፔሌ ጋራቺንና የስፖ

ርቱን ዓለም ከከቦች ውሎ ያወጋናል። ወደ አሜሪካን በምናብ ይዞን ሄዶ በዘመናችን ዝነኛና ተወዳጅ የሆነውን ቦክሰኛ መሐመድ ዓሊ ምንነትና ውጤት እነሆ ይለናል። ቦክሰኛው መሐመድ ዓሊ ታሳላቆቻችን ሲያውሩ እንደሰማነው አጭርና ወፍራም ሳይሆን፣ ቆንጆና ተፈጥሮ ዘንካታ ቁመና የቸረችው ወጣት ሆኖ እግኝነው።

ረቡዕ 'ሲሲሚስ ስትሪት' ላይ አከተሮቹ አሻንጉሊቶች ናቸው። ስማቸውን ባናውቀውም እኛ የራሳችንን ስም አውጥተ ንላቸው እንመለከታለን።

ሐሙስ ለእኛም የቀን ቅዱስ ነበር። 'ማይኤክ' በሚል ርዕስ አጭርና በድርጊት የተሞላ ፊልም ይተላለፍልናል። ማይኤክስ እንደልብ ከትክት ስላለበት በጣም እንወደዋለን። ልከ እንደ ጀምበ ቦንድ አሪፍ ሽዋጅ ነው።

አርብ "ቮናዛ' አራት ወይም አምስት ቴክሶች የዕለቱን ትዕ ይንት አቅርበውልን ከጥበብ ምትሃት ያቋድሱናል።

ቅዳሜ 11 ሰዓት አካባቢ አባባ ተስፋዬ ውብ እገርኛ ተረቶቻቸውን ያቀርቡልናል። ልጆች ብቻ ሳንሆን አዋቂዎቹም እነዚያን ተረቶች ይወዱት ነበር። ማታ የሚመንቱ ታሳቅ ፊልም ይተላለ ፉል። የሚጀምረው ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ በመሆኑ ቤቱ አምሽቼ መግባቱ የግድ ነው። በዚህም ችግር ሁሌም ከተት ያልታወጀበት ጦርነት ከአባቴ ጋር እናካሂዳለን። አንዳንዴ ግን የጠጣው ጠጅ በዝቶ፣ የእኔም በዘዴ በር ሳላንኳኳ የመግባት ልምምዴ ሰምሮ፣ በሰላም ወደ አሁድ እንሸጋገራለን። እንዲህ መስዋዕትነት የምከፍልለት ፊልም አንዳንዴ ከድርጊት ይልቅ ወሬ ይበዛበትና በተቀመጠኩበት ቴሌቪዥኑ ላይ አፍጥጬ ማዛጋት እጀምራለሁ። ውሎዬ ጨዋታ የበዛበት ሆኖ አካሌ ድቅቅ ብሎ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ የሚልበት ጊዜም አለ። ጓደኞቼ ቀስቅሰውኝ ነቃ አልና ትንሽ ቆይቼ እንቅልፉ አይለሎ እንደገና ይዞኝ አልም ይላል። በዚህ ወቅት እኔ ወይም ጓደኛዬ ፈላችንን 'ቁቅ!' ስናደርጋት እነቃና "እኔ አይደለሁም፣ እሱ ነው!" እያልኩ በአንዱ ላይ አላክካለሁ።

በዚህ አይነት አያልቅበት የቴሌቪዥኑ ውስጥ ምትሃት እን ዳነሆለለን የሕይወት ሂደቱ ቀጠለ። ፈላስፋው ዘርአያዕቆብ እን ዳለው፣ ከአባቶቻችን የሰማነውን ከማመን ይልቅ የራሳችንን ጨቅላ ግንዛቤ በምትህተ መስክት አጋዥነት እየፈጠርን መሄዳችንን ገፋንበት።

ንባብን በጥበብ

"ዕውቀትን ከአንቀልባ እስከ መቃብር ባለው ዘመን ፈልንት"
ነቢዩ መሐመድ (ሰ.አ.ወ)

አባባ ጃጋማ አናጢ ናቸው። አባቴ ጠየቃቸውና አንዲት ትንሽ መጻሕፍት መደርደሪያ ሠሩልኝ። ትዝ እንደሚለኝ ታሪክና ምሣሌ፣ ክልታማዋ እህቴ፣ የዕንባ ደብዳቤዎች፣ ጉድና ታሪኩ፣ ፀሐይ መስፍን... እና መጽሐፍ ቅዱስ ደረደርኩባት።

ሌላ ቀን አባቴ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቶልን መጣ እጁ ላይ እንዳየሁ "ተታለህ ያለኝን መጽሐፍ በድጋሚ ገዛኸልኝ!" አልኩት።

ትንሽ ፈገግ ብሎ "አይ የልጅ ነገር! መጽሐፍ ቅዱሱን አይደለም የምትለው?" አለኝ "አውቄ ነው ያደረኩት። የእግዜር ቃል አይደለም? አንድ ሁለት አይደለም፣ ሦስት ቢኖርህ ምን አለበት? አንድ ብቻ ከሆነ ግን ሊቀደድ ይችላል። ልብ በል፣ እህትህ ነፍስ አታውቅም፣ ድክ ድክ ማለት ጀምራለች። ያገኘ ችውን ሁሉ አምጡ ነው የምትለው። ብትቀዳድደውስ የማን ያለህ ይባላል? ወይም አንድ ቀጣፊ ቤታችን ገብቶ ሊሰረቅ ይችላል። ይህንን አስቤ አውቄ ያደረግኩት ነው።"

ዛሬም ሽማውን እየሸመነ እኔ ፈንጠር ብዬ የማደርገውን እንቅስቃሴ ያስተውላል። ትንሽ ቆይቶ "አንብብልኝ ማታ ቴሌ ቪዥን እንድጋብዝህ" ይለኛል። ለግብኖው ስል ሁልቀን የተለያዩ ታሪኮች አነብለታለሁ። በዚህ መሐል ሲላይ ጎቢጥ መጣ። 'መጽ ሐፍ መደርደሪያ እንደተሠራልኝ ሰምቷል። ፍንድቅ እያለ "እኔም አባቴ እንዲያሠራልኝ አለምነዋለሁ። አባቴ በጣም ብልሃ ተኛ ነው። ማታ ማታ መጽሐፍ እንዳነብለት ሲፈልግ ምን ያደ ርጋል መሰለህ? ውሃ በመወዘቻ ያስሞቅና፣ እግርህን በሙቅ ውሃ መታጠብ ከፈለክ መጽሐፍ አንብብልኝ፣ እንቢ ካልክ ግን ደጅ ወጥተህ ድንጋይ ላይ ተቀምጠህ በቀዝቃዛ ውሃ ታጠብ" ይለኛል።

"አንተ የትኛውን ትመርጣለህ?"

"እንዴ! ሞኝ ነኝ እንዴ? በሙቅ ውሃዬ ትጥብ አልና አነብለታለኋ! ምን ቸገረኝ?"

"አንተ!" አለ አባቴ በመደነቅ። የምንጨዋወተውን ሰም ቶናል። "አኘህ ጋሼ ታደለ እንዴት ብልህ ናቸው እባክህ?!" ብሎ ተገርሞ ወደ ጓዳ እየተመለከተ "ባሎቴ! ከዛሬ ጀምሮ ቤት ውስጥ እኔና ፉንጋይ እግራችንን የምንታጠብበት ሙቅ ውሃ እንድታ ፈይልን!"

"ይቻላል። ማገዶውስ?"

"እኔ ለከሰል ሁልቀን አራት አራት ፍራንክ እመድባለሁ::"

"ተስማምቻለሁ" ብላ ማሚቱን አስተኝታ ወደ ሥራዋ ሄደች::

ከዚያን ዕለት ጀምሮ በሙቅ ውሃ ለመታጠብ ብዬ በተ ከታታይ ለአባቴ መጻሕፍትን ማንበብ ጀመርኩ:: ይህን ምስጢር በማውጣቱ ሲሳይ ጎቢጥን ጠላሁት:: በትምህርት ጎበዝ ስለሆነ አባቴ ይወደዋል:: እንዴት ጎበዝ እንደሆነ ስጠይቀው "ታላቅ እህቴን ሂሩትን ታውቃት ኖሯለ? ከእኛ ጋር አንድ ክፍል ነን:: ከትምህርት ቤት ስትቀር የእኔንም ፋንታ ተማርልኝ ትለኛለች:: እሺ እላታለሁ:: አንዳንድ ቀን ከጓደኛዋ ፍቅርተ ጋር ስትቀር የሁለታችንንም ፋንታ በደንብ ተማርልን ይሉኛል፤ እሺ ብዬ በደንብ ነው የምከታተለው:: ማታ ክትምህርት ቤት ስመለስ በጥያቄ እያጣደፉኝ ሁሉንም የተማርኩትን ሁሉ ያናዝዙኛል:: እኔም ደስ እያለኝ እንዳስተማሪ አስረዳቸዋለሁ:: በቃ በዚህ ነው ጎበዝ ተማሪ የሆንኩት::" አለና ሲሳይ ጎቢጥ በትሁት ድምፅ "እኔኮ 'ቀለሜዋ ሆኜ' አይደለም ጎበዝ የሆንኩት:: የእህቴንም የጓደኛዋንም ፋንታ ስለ ምማር ነው::"

"ዋ! እኔም እንዳንተ ትልቅ እህት ቢኖረኝ ኖሮ እሷ ከትምህርት ቤት ስትቀር የእሷንም ፋንታ እማር ነበር" ብዬ እቆጫለሁ::

ትዝ እንደሚለኝ አባቴ ጋዜጣም የመግዛት ልምድ ነበ ረው:: በተለይ በሣምንት አንዴ ይወጣ የነበረው ፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ በአባቴ ተወዳጅ ነበር::

አንድ ቀን ጋዜጣውን ገዝቶ ሲመጣ እኔን እቤታችን ውስጥ አጣኝ:: በአጋጣሚ ጩኔን አገኛት:: እንድታነብለት ጠየቃት:: ትእዛዙን እሺ ብላ ፈፀመች:: በጣም ተገርሞ ሲጮህ እኔ ደረ ሰኩ:: ጩኔም ጋዜጣውን ሰጥታኝ ከቤት ወጣች:: አባቴ በጣም ደንግጧል:: እጅግ በጣም አዝኗል:: ይህንን ስሜት የፈጠረበትን ዜና በጋዜጣው ውስጥ ፈለኩ:: ምንም አላገኘሁም:: የተለመደው ፖሊሳዊ ተግባርና የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸውን ለመከላከል የተደረገውን ጥረት የሚያወሳ ነው::

"በል ደግመህ አንብብልኝ?"

"ምኑን?"

"ይህ በኤሌ ገብርኤል የሚገኙ ቀሳውስት እርስ በርስ በፈ ጠሩት አለመግባባት ሁለት ሰው ሞተ፤ ሦስት ቆሰለ የሚለውን::"

"ጩኔ ይህንን ዜና ከዚህ ጋዜጣ ውስጥ አንብባልሃለች?"

"አዎን!"

ከፊት ገጹ ጀምሬ ዜናዎቹን አንድ በአንድ ርዕሳቸውን ማንበብ ጀመርኩ:: አባቴ ክርስትና የተነሳበትን ኤሌ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ የተዘገበ ዜና አለመኖሩን ስነግረው አላመነኝም::

"እንዴ! በደንብ እየው:: መምሬ ሰንቡቆ ሰሎ እና መምሬ አታርቃ ዶሪ በፈጠሩት አለመግባባት በመሣሪያ ተጠፋፉ የሚል ምንም ወሬ የለም ነው የምትለኝ?"

"እውን የለም!"

"ሂድ! አንተ ማንበብ አትችልም::"

"ለምን አልችልም? ሁሌ በደምብ የማነብልህ እኔ አይደ ለሁ እንዴ? ጩኔ ከክፍል ወደ ክፍል እየተዛወረች አምስተኛ ክፍል ደረሰች እንጂ እሷ ነች ማንበብ የማትችለው:: ጋዜጣ ማን በብ ቀርቶ ስሚንም በደምብ መጻፍ አትችልም::"

"ታዲያ ከየት አምጥታ አነበበች?!"

"አንተ ስለአገርህ አውርተህ ስለማትጠግብ እዚህ ስትገባ ስትወጣ ያዳመጠችውን በወሬ በሃሳቧ ይዛ አንብባልህ ነዋ!"

"ወይ ጉድ! ጩኔ!" አለና እየተጣራ ዘሎ ወጣ::

ከአካባቢው ተስውራለች:: አባቴ በእኔ ማንበብ ችሎታ አልተማመነም:: እርግጠኛ ለመሆን ጋዜጣውን ይዞ ጎረቤታችን ቤት ሄደ:: እማማ ኩሪባቸው ቤት እንድ መምህር በደባልነት አብረዋቸው ይኖራሉ:: በአጋጣሚ እቤት ውስጥ መምህሩ ተገኙ:: ጋዜጣው ተሰጥቷቸው የተባለው ዜና ተፈለገ:: መምህሩ ለጥቂት ደቂቃዎች አገላብጠው ካዩ በኋላ እኔ ትክክል መሆኔን መሰ ከሩልኝ::

ወደ ቤታችን እንደተመለስን፤ አባቴ በንዴትም በመገረምም ከትከት ብሎ ሰቆ በወዳጅነት ያወጋኝ ጀመር:: "አንተ! ያጋደለቻ ቸው ሰዎች ሁለቱም ዘመዶቼ ናቸውኮ:: የሚገርም ነው! ባለመ ማሬ አላገጠችብኝ:: ደግነቱ እሷም ከእኔ አትሻልም" አለና እንደ ሷው ኮስተር ብሎ "በጋሞጎፋ ጠቅላይ ግዛት የኤሌ ገብርኤል ቀሳውስት እርስ በርስ መጋደላቸው ተገለጸ:: ችግሩ እንዲከሰት ያደረጉት ግለሰቦች በፖሊስ ተይዘው በመመርመር ላይ ይገኛሉ" አለችና ኮስተር ብላ አየችኝ:: 'ወይኔ ወገኖቼ!' ብዬ ሰጮህ ኮስተር ብላ ንባብዋን ቀጠለች::

"ከ600 ዓመታት በላይ ዕድሜ እንዳለው የሚነገርለት የኤሌ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ካህናት በሰላምና በፍቅር ምዕመናኑን ቢያ ገለግሉም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፈጠሩት አለመግባባት የሰው ደም እንዲፈስ ሆነ" ብሎ ኮስተር አለ:: "ልክ እንደ አሳምነው ገብረ ወልድ እሷም ኮራ አለች! እኔ እጮኻለሁ፣ ላብድ ትንሽ ቀርቶኛል፤ እሷ ችላ ብላኝ ንባብዋን ቀጠለች::

"መምሬ ሰንቡቆ ሰሎና መምሬ አታርቃ ዶሬ በፈጠሩት አለመግባባት፤ በመጀመሪያ ድምፅ በሌለው መሣሪያ አንዱ ሌላ ውን ጎድተው፤ የሁለቱም ደም በከፍተኛ ሁኔታ ስለፈሰሰ ሕይወ ታቸው አልፏል::

"ኡ! ኡ! ማበድ ጀመርኩ:: ይኼኔ አንተ መጣህ!" አለና አባቴ በራሱ ስቃይ እየቀለደ አሳቀን::

"ቆጨኝ!" አለ።

"ምንድነው የቆጨህ?"

"እፍፍ በሉልኝ ያለችውን ረሳህ?"

አስታወስኩ።

የእናቷ እማማ ቅመም፣ በርበሬያቸው እንደ ስማቸው ነው። ትልልቅ ሰዎች እንጂሚሉት፣ የቅመም በርበሬ ወደ ሆድ ሲገባም ያቃጥላል። ሲወጣም ያቃጥላል።

አንድ ቀን ሽንት ቤት ገብታ ከተጠናቀቀች በኋላ እናቷ ሚጥሚጣ ቋጥረውበት ወለል ላይ በጣሉት ወረቀት ልብ ሳትል፣ በወረቀቱ ተጠቀመች። ከጥቂት ደቂቃ በፊት ጤናማ የነበረችው ልጅ አበደች። መሬት ተዘርራ እግሯን እንደባላ ከፍታ "ተቃጠልኩ! እፍ እፍ ፍፍ በሉልኝ!" ብላ ጮኸች።

በአካባቢው ያለን ልጆች ግር ብሎን ደረስን። እናቷ አል ነበሩም። የኔ አባት ጨኸቷ አሸብሮት ከሁላችንም ቀድሞ ነው የደረሰው። 'ሲኒማ በነፃ'ውን አጥርተን ሳናይ አባረረንና በሩን ዘጋ። በባልዲ ውስጥ ያለ ውሃ በእግር መታጠቢያ ገቡቴ ላይ ገልብጦ ብድግ አደረጋትና ውሃው ላይ ዘፈዘፋት። "ቾፍ! ቾፍ! እያደረግሽ በውሃው የሚያቃጥልሽ ላይ ምቺው" ሲላት ይሰማ ናል።

ነፍሷ መለሰ አለ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ ጨኒ ቅፅል ስሟ እፍፍ በሉልኝ ሆነ...

አባቴ የዕለት ሥራውን ጀመረ። እኔ ጋዜጣውን አነሳ ብጣለሁ። ከውጪ ድምፅ ሰማሁ። የጨኒ ነው። ሳሙላት ቶሎ ብዬ ወጣሁ። ይህች እንደጠጣ ብልጥ የሆነች ፍጥረት ቱር ብላ እጄን አንቅ አድርጋኝ፣ በጣም ዝግ ባለ ድምፅ "አባትህ ሁሌም አንብብልኝ እያለ ሲያስጨንቅህ ስለምሰማ በጣም ነው ፆምና ደ ደው። ስለዚህ ዛሬ ላንተ ስል ነው የቀጣሁት!" አለችኝ።

እውነቷን መሰለኝ። ዓይኖቿ እየተማጠኑኝ ነበር። እጆቼ ዛሉ።

"እንደምታውቀው እኔ ማንበብ አልችልም። ዛሬ ግን ሳባትህ ሠራሁለት። ልክ እንደ አሳምነው ገብረወልድ ነው ኮለተር ብዬ ያነበብኩለት።"

አብረን ሳቅን።

"ጋሼ" አለ አባቴ እቤት ውስጥ ሆኖ።

"እቤት!" አልኩ በሳቅ መካከል።

"ያልኩህን አልሰማሽኝም መሰለኝ። ማታ በሙቅ ውሃ እግርህን መታጠብ አትፈልግም?!"

በአሁኑ ዕድሜዬ ሳነብ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.አ.ወ) *"እውቀትን ከአንቀልባ እስከ መቃብር ባለ ዘመን ፈልጓት"* እንዳሉት፣ የጥበብን ሀሁ በአባቴ ሐዋርያነት ልፈልጋት ወደ ቤት ገባሁ።

ምስጢር

"ለንፁሃን ሁሉም ነገር ንፁህ ነው"
የአረብኛ ምሣሌ

በትምህርት ቤታችን ሕግ የከሰዓት በኋላው ትምህርት እንደተጠናቀቀ ክፍል ውስጥ የምንቀረው ተረኛ ቤት ጠራጊ ተማሪዎች ብቻ ነበርን። ማክሰኞ ዕለት እኔና ዘምዘም ሁሴን ተረኞች ሆንን። ወደ ሰፈሬ ለመሄድ ቸኩያለሁ። ስለዚህ ዘምዘም እስክምትከተለኝ ሳልጠብቅ በፍጥነት ወደ ቧንቧው ሄጄ በተሸነቆረ ታኒካ ውሃ መቅዳት ጀመርኩኝ። የታኒካውን ቀዳዳ በእጄ ደፍኜ ውሃው ሞላልኝ። ተሸክሜ እየተንገዳገድኩ ወደ ክፍል ሰገባ ዘምዘም ቁጭ እንዳለች ነበር።

"አንቺ ተነሺና ክፍላችንን እንጥረገው እንጂ?!"

ፀጥ እንዳለች ተቀምጣለች። ውሃው በቀዳዳው እየተንዠ ቀዠቀ አሏራማ ክፍላችንን ማራስ ጀምሯል፣ ሳያጨቀየው በፍጥ ነት ከእንዱ ጥግ ወደ ሌላው እየተራመድኩ አርከፈከፍኩትና "ዘምዘም!" አልኩ ጮኬ።መሐል እጄን በላኝ። የእማዬ ምክር ትዝ አለኝ 'መሐል እጅህን ከበላህ ገንዘብ ታገኛለህ። ለማንም እንዳትናገር። የበላህን ቦታ እከከውና ሳመው። ለአንዱ ልጅ ትንፍሽ ካልክ ግን ይረክሳል።' ያለቺኝን አስታወስኩና ምክሯን ተግባራዊ አደረግኩት።

በቀስታ ድምፅ "ተስፍሽ ና!"

የማውቃት ዘምዘም አልሆነችም። በትምህርቷ ንብ፣ ስት ጫወትም ልክ እንደ ቢራቢሮ የነበረች ልጅ ደመ ቀዝቃዛ ሆና ሳያት አስደነገጠኝ። ቀልጠፍ ብዬ ከአጠገቧ ተቀመጥኩኝ።

"በእናትህ ተስፍሽ፣ የማሳይህ ነገር አለኝ፣ ለማንም እንዳት ነግርብኝ!"

ተጨንቃለች።

"ምንድነው የምትነግሪኝ!"

"ምን እንደሆንኩኝ እኔም አላውቅም። እኔና አንተ ተጋ ግዘን እናፀዳውና በምሥጢር ከጠበክልኝ የፈለከውን ነገር አደርግ ልሃለሁ፣ የጠየከኝን ሁሉ እሰጥሃለሁ።"

አባቷ የአስመጪና ላኪ ድርጅት እንዳላቸው አጫውታ ኛለች። ከረሜላ፣ ብስኩት፣ ፍራንክ እንደልሏ ነው። ክፍል ውስጥ ተወራርደን "አለይዝ! አለይዝ!" ተባብለን ከሌሎቹ የክፍል ጓደኞቻችን ጋር በእስክሪቢቶ፣ በእርሳስ ወይም በኩርኩም ሰንወራ ረድ፣ ዘምዘም ብቻ ከፈለገች ፍራንክ ወይም ደስታ ከረሜላ ታስ ይዛለች። እቤት እሷን መርታት ደስ ሲል! ምክንያቱም ፍራንክ የበላ ፓለቴውን ይነጫል፣ ከረሜላ የበላም ይደሰትበታል። በቀ ላሉ የምትበለጥ ባለመሆንዋ ፉክክሩ የምር ይሆናል። ይህች ንቁ ልጅ ዛሬ የእኔን ዕርዳታ ፈልጋለች።

መቸኮሌን ተውኩት። "ለማንም አልናገርም። ምንድነው የሆንሽው?"

"መጀመሪያ ማልልኝ! እናቴ ትሙት በል!"

"እናቴ ትሙት! ለማንም አልናገርም!"

በዚህ ወቅት ዕድሜአችን ከ13 እስከ 14 ዓመታት እየተጠጋ ነበር።

"ተስፍሽ ምለሃል! ዋ! ለልጆች ብታወራ እናትህ ሙትት ነው የሚሉብህ። አሳይቼህ አብረን ጠራርገን እናፀዳዋለን። ከዚያም ወደ ሰፈሬ ትሸኘኛለህ፥ ነገ የፈለከውን ስጪኝ ብትለኝ እስ ጥሃለሁ!"

"አላወራም። ለምን መለለሽ የማላወራው? መሐላዬን አፍርሼ እናቴ ሙትት እንዳትልብኝ። እማዬን እኮ በጣም ነው የምወዳት።"

"ጎሽ!"

ቀስ ብላ ብድግ ስትል የተቀመጠችበት ቦታ በደም ርሷል። ደነገጥኩኝ። "ምን ሆነሻል?"

"እሽ! ሽ! ሽ!" አለቺኝ ከጐን ክፍል ያሉ ልጆች እንዳይሰሙን። ያለንበትን ክፍል በር ሮጬ ዘጋሁት "ቂጥሽን የወጋሽ ነገር አለ?" እየተመለስኩ በለሆሳስ ጠየኳት።

"አይደለም" ምን መሰለህ... ሂድና ውሃ በታኒካው ቅዳልኝና ና!"

ሽንቁሩን ታኒካ ይገር ወጣሁ። በፍጥነት ቀድቼ እየተመለስኩ በሹክሹክታ "ቀይ ስር ላይ ተቀምጠሽ እንዳይሆን?"

"አዎን ተስፍሽ! ይህቺ ፎዚያ ነች ጉድ የሠራችኝ። በል ወንበሬ ላይ እርጪው።"

ረጪሁት። በቆሻሻ ወረቀት ዘምዘም ጠረግ ጠረግ አደረገችው። እኔ ውሃ እያፈሰስኩላት ወንበሩ ፀዳ። ጉርድ ቀሚሷን ሳታወልቀው ወደፊት አዘረችው። ደም የነካውን ቦታ ሰብስባ ይዛ "ጨምርልኝ" ስትለኝ ውሃው አልቆ ነበር። ቀድቼ መጣሁ። እግረ መንገዴንም መምህራኖቻችን የሚታጠቡበትን ሳሙና መነ ተፍኩላት። እጥባ ስትጨርስ፣ "ተስፍሽ፣ ንበዝ ልጅ ነህ። ወላሂ ቆንጆ አንጎል አለህ። ቀይ ስር ላይ መቀመጤን ስትነግረኝ ችግሩ ገባኝ። ምሳ የበላነው ወጥ በቀይ ስር የተሠራ ነው። አህመድ የሚባል ትንሽ ወንድም አለኝ። እሱ የጠረጴዛውን ልብስ ሲስበው ወጡ ዝርግፍ አለ ወምበር ላይ ፈሠሠ እኔ ደግሞ ሳላ ውቅ ወጥ የተደፋበት ወንበር ላይ ተቀምጬ ምሳዬን ብልት አድርጌ መጣሁ።"

ስታወራ ንቃትዋ ከመመለሱ በተጨማሪ አለብላቢት ሆነች ብኝ። ጠረጠርኳት። ቅድም ፎዚያ ብላ ታላቅ እህቷን ማንሳቷን ረስታ አሁን ለምን አህመድ ላይ አላከከችበት? ማጣራቱን አልፈለኩም። ምሥጢረኛዋ እንዳደረገችኝ ገብቶኛል። ይህንን ምሥ

ጢር እስከወዲያኛው ለማዳፈን ተማምለናል። ቀሚሷ ጠቆር ያለ በመሆኑ እርጥበቱ ገኖ አይታይም። ለጥንቃቄ ብላ ከላይ የደረብኩትን ጃኬት ተውሳኝ ወገቧ ላይ ሸብ አደረገችው።

"በል ቶሎ ቶሎ ወረቀት ወረቀቱን እንልቀም!"

አፅድተን ልንወጣ ስንል በሩጋ አቁማኝ ዓይን ዓይኔን እያየቺኝ "ተስፍሽ ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ? ምን ልስጥህ። የፈለከውን ጠይቀኝ?"

አስቤ አውጥቼ አውርጄ ወስኛለሁ። "ሙቪ መግቢያ ስጪኝ?"

ሳቋ መጣ። አመቀችው። ወደ ፈገግታ ተቀየረ። "ስንት ልስጥህ?"

"ሁለት ብር?"

"የትኛው ሲኒማ ቤት ነው መግባት የምትፈልገው?"

"ሁሉም ሲኒማ ቤት የወጡት ፊልሞች አረፍ ናቸው።"

"ሁሉም'ጋ ነው መግባት የምትፈልገው?"

"አዎን"

"በጠቅላላው ስንት ፍራንክ ይበቃሃል?"

"ሁለት ብር" አልኩና ደገምኩላት። ሲኒማ አዲስ ከተማ፣ ራስ፣ ዓድዋና ሀገር ፍቅር በልቤ ቆጥሬ፣ የምሣ ጉዳይ እዚህ ስሌት ውስጥ አይካተትም። ከተገኘ ይበላል ከጠፋም አይር በኝም።

ኪሷ ገባች። ብሮች አወጣች። ቆጠረቻቸው አምስት ብሮች ናቸው። "እንካ በሁለቱ ብር ሲኒማ መግባት ትችላለህ። ሦስት ብሩ ለምሣህ ይሆንሃል" እንድቀበላት እጇን ዘረጋች።

አልተቀበልኳትም። የማየውንና የምሰማውን ማመን ተሳነኝ። የቤተሰቤ ቁጥጥር በጣም ጥብቅ ነው። ይህንን ያህል ገንዘብ በኪሴ ይዤ መገኘት ያስወግራል። ምርመራውም አሣር ነው። ብቀበላትም እንኳን እምስት ብርን ያክል ብዙ ብር ቀርቶ እንድ ብር ኪሴ ካለ እንቅልፍ ወስዶኝ እያውቅም። ለዛሬው ግን ሁለት ብር ተቀብያት እላሬንም ባይ፣ አምሮቴን ለመቁረጥ ወሰኜ ነበር። እሷ ግን እምስት ብር ጭናብኝ ቀልቤን ገፈፈችው። እሷስ ይህን ያህል ገንዘብ ከየት አመጣች? ስል ራሴን ጠየቅኩ። እንዳልጠረጥራት ጭቦ ይሆንብኛል። ዘምዘም ጨዋ ልጅ እንደሆነች አውቃለሁ።

"ሁሉንም አንድ ላይ መቀበል ካልፈለክ ተወው። ስትፈልግ ግን ሁሌም ገንዘብ ጠይቀኝ" አለችኝና ዘምዘም ገንዘቡን ወደ ኪሷ መለሰች።

ሁለታችንም ደብተሮቻችንን አንስተን ከክፍል ወጥተን እያ ወራን ወደ ሰፈራችን መሔድ ጀመርን። አሁን ምስጢረኛዋ ስለሆንኩ ፈራ ተባ እያልኩ "ዘምዘም እንቺ ይህንን ሁሉ ብር ከየት አመጣሽው?"

"እኛ ቤተሰብ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በወር በወር አምስት አምስት ብር ይለጠዋል። ሁለተኛ ደረጃ ስንገባ 10 ብር

ይሆናል የሚሰጠን። የኒቨርሲቲ የገቡት ወንድምና እህቶቼ እንደዚሁ የሚሰጣቸው አለ። እናቴ ወይም አባቴ ለምን እንደተጠቀምንበት ይጠይቁናል። እውነቱን እንነግራቸዋለን። ስለዚህ አሁን ልሰጥህ የነበረው ገንዘብ የራሴ የኪስ ገንዘብ ነው። ያጋጠመኝን ሁኔታና እንተ ያገዝከኝን በገርገር ኔግሬአቸው በጣም ተደስተው እንቲን ቤታችን አስጠርተው በደንብ ይጋብዙሃል" አለቺኝ በእርግ ጠኝነት።

ምን እንዳደረኩላት እስካሁን አልገባኝም። ከአነጋገሯ እንደ ተረዳሁት ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቿም ባለውለታ ሆኛለሁ። ስላስማለችኝ ምሥጢሯን ሕይወት በምደርስበት ምዕራፍ እስከምት ገልፅልኝ ለማንም ትንፍሽ አልልም።

"በአምስት ብሩ ምን እንድታደርጊበት ነው በየወሩ የሚሰ ጡሽ?" ጠየቅኩ። በጣም የማረክኝና ማመን ያስቸገረኝ የቤተሰብ ልማድ ሆኖብኛል።

"እስኪሪቢቶዬ ቢገኝልብኝ፣ እርሳስ ወይም ደብተር ቢያል ቅብኝ እዝበታለሁ። አረንቻታ መጠጣት ቢያምረኝ ገዝቼ እጠጣ ለሁ። ነፃ ጊዜ ካለኝ ሲኒማ እገባበታለሁ። አባታችን ወይም እና ታችን በአስራ አምስት ቀን አንድ ቀን ከልጆቻቸው ጋር በሚያ ደርጉት ስብሰባ ላይ ገንዘቡን በምን በምን ጉዳይ እንዳዋልን እና ስረዳለን። ከአግባብ ውጪ የተጠቀመ ልጅ ይወቀሳል።" በማለት ዘምዘም ታወራልኛለች። እኔ ደስ ብሎኝ በፀጥታ እያደመጥኩኝ ነው።

"የወላጆቻችን ዋናው ዓላማ ምን መሰለህ? የገንዘብ አጠ ቃቀም እንድናውቅ አድርገው ነው ልጆቻቸውን የሚያሳድጉን። ቤታችን ውስጥ ያለነው ልጆች በሙሉ በሳምንት ያለን ፕሮግራም ታውቆ የሚሰጠን ሥራ አለ። አትክልት ውሃ ማጠጣት፣ መኪና ችንን ማጠብ፣ የውሻ ቤት ማፅዳት፣ የቤታችንን ንፅህና በጋራ መጠበቅ፣ ይጠበቅብናል። ለምሣሌ በዚህ ሣምንት እኔ ከተሰጠኝ ሥራ ውጪ አትክልቶቹን አርሜ በመኮትኮቴና የውሻውን ቤት ስላፀዳሁ እሸለማለሁ። በሚሰጠኝ ገንዘብ ከፊለኩ ሲኒማ እገባ በታለሁ፣ ወይም ግሮን ሆቴል ሔጀ ዋና እዋኝበታለሁ። በትምህ ርታችን አንደኛ ከወጣንም አንደዚሁ ይሸልሙናል።"

የልጅ ልብ በሚያማልል ትረካዋ ተመስጬ ብዙ ሐሴን። እኔ ከምኖረው ልማድ ውጪ በመሆኑ ተደንቄአለሁ። ፀጥ ብዬ ሳስተውላት ዘምዘም ምሥጢረኛዋ አድርጋኛለችና ምክሯንም አከለ ችበት "አንተ፣ ሲሳይ፣ መኩዬና ሌሎች ልጆች ሲኒማ የምትገቡት ከትምህርት ቤት ፎርፋችሁ እንደሆነ አውቃለሁ። ይህ ልክ አይደ ለም። ከትምህርት ቤትህ በምንም ተአምር አትቅር።" ስትለኝ ከአፍዋ ላይ ነጥቄ "ቅዳሜ እኮ ሲኒማ ቤቶቹ መግቢያቸው አንድ

ብር ነው። እኛ ደግሞ በአንድ ብሩ አንድ ጊዜ ከምንገባበት፣ አንድ ቀን ፎርፌን በሽልንግ ብንገባ አይሻልም?"

"አይሻልም! ትምህርት የወደፊት ኑሮ ማቃኛ ነው። ለተማሪ ትምህርት ሥራው ነው። ሲኒማ ጥቂት አስተምሮህ፣ ብዙ ቢያዝናና ነው..." ስትለኝ ዘምዘም ትልቅ ሰው መሰለችኝ፣ ፀጥ ብዬ አደም ጣታለሁ፣ "ስለዚህ የወደፊት ሕይወት ለማቃናት ትምህርትን መከ ታተል ነው ያለብህ ወይስ መዝናናትን?!" አባባልዋ ተወሳሰ በብኝ። በፀጥታ አስተውላታለሁ ቀጠለች "ለማንኛውም ቀስ በቀስ እንዲገባህ አደርጋለሁ። ምክንያቱ ምን መሰለህ? አንተ አሁን በጣም የምወድህ ጓደኛዬ ሆነሃል" አለችና ያሸረጠችውን ጃኬቴን ከጭንዋ ላይ ፈትታ ሰጠችኝ። ተቀብዬ ለበስኩ። ደስ የሚል ምክሯን ቀጠለችበት "ስለዚህ ጉብዝ ተማሪ እንድትሆን መጥፎ የሆነውን ተግባር ሁሉ መተው አለብህ። ተምሪህ ትልቅ ሰው መሆን ከፈለግክ በአሁኑ ዕድሜህ ጉብዝ ተማሪ ለመሆን የሚያ ታልሉ ጨዋታዎችን መተው ይገባሃል። እኔ ጉብዝ ተማሪ የሆን ኩት በነገርኩህ መሠረት በትጋት ስለምማር ነው። አሁን ጉብቼ የቤት ሥራዬን ሳልሠራ አልጫወትም።"

ሁለታችንም የየመጣንበት ማኅበረሰብ ውጤቶች ነን። ማኅ በረሰቡ ዘምዘምን እጅግ በጣም ሩቅ ተመልካች አድርጉ ሲፈ ጥራት እኔና አብሮ አደጉቼን ግን ሩቅ አይደለም ቅርቡንም አጥ ርተን እንድናውቅ አልታደልንም። ስለዚህ እንደዘምዘም አይነት አስተዋይ ልጅ ሲገጥመኝ ከትልቅ ሰው ጋር የማወራ ይመ ስለኛል። የባቡር ሃዲድ አካባቢ ደርስናል። ትንሽ ከተጓዘች ቤቷ ትደርሳለች። ሳላስበው ብዙ ሸኝቼአታለሁ። ከመሰነባበታችን በፊት የሚያጓጓኝን ጥያቄ ሰነዘርኩ። "ቴሌቪዥን ስላላችሁ የም ታይው እንደልብሽ ነው?"

"የእኛ ቤተሰብ ቴሌቪዥን የምንመለከተው በፕሮግራም ነው። በእኛ ቤት ሕግ ተማሪዎች እንድናመሽ የሚፈቀድልን እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ብቻ ነው። የቤት ሥራችንን ሠርተን የጨረስን ልጆች ዜና መከታተል፣ ዘፈንም ካለ ማየት እንች ላለን። ሦስት ሰዓት ከደረሰ በኋላ ግን ማንም ሳያላስበን ወደ መኝታ ቤታችን መሔድ እንዳለብን እናውቃለን። ከሦስት ሰዓት በኋላ አባባና እማማ አብረው ያመሻሉ። ስለኛም ሆነ ስለሌሎች ጉዳዮች ይመካከራሉ።

"እኛ እንደልብ እንድናመሽ የሚፈቀደው ቅዳሜ ማታ ብቻ ነው። የዚያን ዕለት ሁሉንም የቴሌቪዥን ፕሮግራም እንከታተላ ለን። ከፈለግንም አምሽተን ታላቅ ፊልም እናያለን። በተረፈ ከእሁድ ጀምሮ በጊዜ መተኛትና በጠዋት የመንቃት ፕሮግራማ ችን እንደነበረው ይቀጥላል" አለችኝ።

ከብረት የጠነከረው የቤተሰቡ ዲስፕሊን አስገረመኝ፣ ነገር ግን እኔ ካደግኩበትና ከኖርኩበት ልማድ ውጪ ስለሆነ መቀበሉ

በጣም ከበደኝ። ተስናብቼአት ወደቤቴ ለመመለስ እጄን ለስንብት ዘረጋሁላት። በአንድ ብር ጨበጠችኝ። "ሻይ ጠጣበት አብሬህ እንዳ ልሆን አሁን መቀየት አልችልም። ሙቪ ማየት የምትወድ ከሆነ፣ የሚመጣው ቅዳሜ መውሲድ ነው። ለምን እኔ ሲኒማ ኢትዮጵያ አልጋብዝህም?" ከደስታዬ ብዛት ልቤ ትርክክ ያለ መሰለኝ። አልተግደረደርኩም ተቀበልኳት። በቀጣዩ ቀንም በህይወቴ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ድፍን አንድ ብር እሚከፈልበት ሲኒማ ቤት ልገባ ነው! "እሺ!" አልኳት ፍንድቅ እንዳልኩኝ "እንኳንም ቀይ ስር ላይ ተቀመጠች!" አልኩ በሆዴ።

መውሊድ

ኣላህ መሶሌ ኣላህ መሐመዴ ሰይዲ
ሰይዲ ሰይዲ የዓለሙ ዘውዲ
ኣልሀምዱሊላሂ ረቢል ኣላሚን
ኡመት ያደረገው ለመሐመድ ኣሚን
ምሥጋና ይድረሰው ፍትህ በራህ ቤት
ያደረሰኝ ጌታ ለመውሊዱ ዕለት
ኣሁንም ወደፊት ሳይለየን በሞት
በደህና ያድርሰን ለዚያኛው ዓመት
የመንዙማው ሊቅ መሐመድ አወል

ዛሬ የመውሊድ በዓል ነው። እኔና ዘምዘም ሁሴን 'ላቭ ኢን ቶኪዮ' የተባለውን የሕንድ ፊልም በሲኒማ ኢትዮጵያ ለማ የት ተቀጣጥረናል።

ዕለታቱ ይረዝሙብኝ ጀመር። የዛሬዋ ቅዳሜ ላይ ለመድ ረስ ምን ያህል እንዳማጥኩ ምንጊዜም አልረሳውም። ማክሰኞ ዘምዘምን ሸኝቼ ወደ ቤቴ እየተመለስኩ ሳለ ፓስቴ መብላት አማረኝ። በቀጥታ ወደ መላ ሻይ ቤት ጉራ አልኩኝ። የመላ ሻይ ቤት አሪፍ አሪፍ ሙዚቃዎች ስለሚከፍት ሻዩ ዋጋው ውድ ነው። እንድ ብርጭቆ ሻይ ዲናሬ ነው። ከአራት ፓስቴ ጋር ገጨሁ። ብሬን መዥረጥ አድርጌ ስከፍል ያዩኝ የበፊር ልጆች ክው ብለው ቀሩ።

በሩ ስር ቁጭ ብሎ ጥቁር ፊቴን የበሩ ጥላ ጋርዶኝ እየሳቀ ያፈጠጠ ልጅ ታየኝ። ጥርሶቹ እንደሩፍስ የሚያበሩት አሻሮ እንደሆን አወቅኩ። «ፉንጋይ ጋብዘን እንጂ? አበላልሀን ላየ ባንክ የዘረፍክ ትመስላለህ» አለኝ። ሻይ ጋብዝኩት። መልሴን ተቀብዬ፣ አምሮቴን ቆርጬ ወደ ቤቴ ሔድኩ። የቤት ሥራዬን ሠራሁ ስተኛ ግን እንቅልፍ አልወሰደኝም። ረቡዕ ናፍቃኝ ረጅሙን ሌሊት ሳብሰ

ለስል ውድቅት ላይ ተኛሁ። ማለዳ በእናቴ ውትወታ ተቀሰቀ ስኩኝ። ትምህርት ቤት ስሄድ ዘምዘም ያለወትሮዋ አርፍዳ መጣች። በቀለማ ቀለም ያሸበረቀ ቀሚስዋን ለብሳ፣ ነጠላ ጫማዋን ተጫምታ፣ አናትዋን በውብ ሻሽ ሸፈን አድርጋ ስትራመድ ትልልቆቹ ልጃገረዶች እንደሚያደርጉት ሰበር ሰካ ትላለች። እንዳፈጠጥኩባት ነኝ። ክፍል የምንገባበት ሰዓት ደርሶ ስለነበር በአንገትዋ ሰላም ብላኝ ከሴቶቹ ጋር ተለለፈች።

ክፍል ገብተን ቁጭ እንዳልኩኝ ቁር ብላ እኔ ወንበር አጠ ገብ መጥታ አንድ ሜንታ ከረሜላ ኪሴ ከተተችልኝ። ሜንታ ከረሜላ በዱንቡሉ ሁለት ነው የሚሸጠው። በጣም የሚዋደዱ ተፋቃ ሪዎች ብቻ ግዝተው እንደሚበሏት አምነታችን ነው። ይህ ከረሜላ ጣዕሙ ብቻ ሳይሆን የዘምዘምን ፍቅር ልክ አመላከተኝ። ማንም አላያትም። በምስጢር የመነናኘቱ ጥበብ እንዲህ ተጀመረ። ሜንታ ከረሜላዬን መጠጥኩኝ። ማምሻውን ወደ ቤታችን ስንሄድ እንድሸኛት ጠየቀችኝ። ተስማማሁ።

"ለእሁቴ ለፎዚ ስላንተ ነግሬያት በጣም አመሰገነችህ። ልታይህ በጣም! ጓጉታለች። ቅዳሜ በአራት ሰዓት እቤታችን ትመጣና ምሳ አብረን በልተን ወደ ሲኒማ እንሄዳለን።"

እኔ ሲኒማ ለመግባት ለሄድ ያለብኝን ጭንቀት ስለማውቅ "ወላጆችሽ አይቆጡሽም ሲኒማ መግባትሽን ካወቁ?" አልኳት በመገረም።

"ለምን ይቆጣሉ? አይቆጡም። የአንተ አባት ከሲኒማ ብዙ ትምህርት እንዳለው ስለማያውቁ ነው የሚቆጡት። የእኔ እናትና አባት ግን በሲኒማ ጥሩ ጥሩ ትምህርት እንዳለው ስለሚያውቁ ብፈልግ ብቻዬን አንዳንዴ ደግሞ ወላጆቻችንን ልጆቻቸውን ይዘ ውን ሲኒማ ይገባሉ እኮ።"

ወላጆቼ ሲኒማ የዱርዬ ሥራ ነው ብለው በሕሲናዬ ውስጥ የጠቀጠቁትን መጥፎ ሃሳብ ስለዘችልኝ። ለካ ሳላውቀው ከሌላው ዓለም እየተማርኩኝ ኖሯል?!

ሐሙስና አርብ እየተጎተቱ አልፈውልኝ፣ በዛሬው ቅዳሜ ላይ ደረስኩ። የክት ሱሪና ጃኬቴን ለብሼ ሽራ ጫማዬን አጥልቄ ቁርሴን እየበላሁኝ "ዛሬ አክስቴ'ጋ ሽሮሜዳ እሄዳለሁ!" አልኳት እማዬን።

"በእግርህ ነው የምትሄደው? እኔ ዛሬ ስሙኒ የለኝም።"

"ለአውቶቡስ ደርሶ መልስ ትኬት መቁረጫ ስሙኒ አለኝ!"

ለአባቴም ሆነ ለጎረቤቶቻችን ሽማኔዎች አንድ ቁባ ማግ ካዳወርኩ ዲናሬ ይከፍሉኛል። በከርክ በገዛሁት ባንክ ውስጥ እከ ትና እናቴ በሣጥኗ ውስጥ እንድትጠብቅልኝ በአደራ አስጣታ ለሁ። እማዬ አማካሪዬ ተመስላ በስልት ትቆጣጠረኛለች። ለደብተር ወይም ለእርሳስና ለስኪሪቢቶ መግዣ የራሴን ወጪ እችላለሁ።

ከቤት እንደወጣሁ መኩዬ ቀጫጫው አገኘችኝና "ፉንጌ ወዴት ነው የምትሔደው? ዛሬ እኮ ግጥሚያ አለን።"

ተጠግቼአት "እማዬ ልካኝ ሰንጋ ተራ መሄዴ ነው። ቶሎ እመጣለሁ። የምንጫወተው ካምቦሎጆ ነው ወይስ ራስ ብሩ ሜዳ?"

"አሸዋ ሜዳ ነው።"

ብልጥ እየሆንኩ እንደመጣሁ ተሰማኝ። እናቴ ሳትለማኝ መኩዬን ሸውጃታለሁ። ይህች ቆቅ የሆነች ፍጥረት አኳኋኗን አይታ እየተጠራጠረች ተለያየን።

ወደ ተናፋቂው ቀጠሮ ጉዞ ጀመርኩ። ፈጠን ማለት አለ ብኝ። አባቴ ከመጣ ለአንድ ላልታሰበ ጉዳይ ይፈልገኝና ከፕሮ ግራሜ እንዳልስተጓጎል ፈርቻለሁ። እንደስጋሁት ሳይሆን ምንም ችግር ሳይገጥመኝ፣ እነዘምዘም ሰፈር ደረስኩ። ደጅ ወጥታ ትጠ ብቀኝ ነበር። እንዳየችኝ እየሮጠች መጣች። ተጨባበጥን። ብዙም ሳንሔድ ትልቅ ቀይ የብረት በር ከፍታ ገባች። ግቢው ውስጥ አፔል መኪና ልብስ ለብሳ ቆማለች። ግቢውን ጥላ ያለ በሰው የወይን ተክል ከዳር እስከዳር ተዘናፍሏል።

ዘምዘም እህቶቿን ተጣራች። ወጥተው እንደመሽኮርመም እያሉ ተዋወቁኝ። ፊታቸው በደስታ እያበራ ያስተውሉኛል።

ፎዝያ እንዳየችኝ "እ! አንተ አላህ የባረከህ ልጅ!" እያለች ጉንጩን ሳም አደረገችኝና እጇን ይዛ እየመራችኝ ወደ አንድ ክፍል ይዛኝ ገባን። ወንበር የለም። ወለሉ ላይ በልዩ ልዩ ቀለ ማት ያሸበረቀ ምንጣፍ ከዳር እስከ ዳር ተነጥፎበታል። በወለሉ ጥግ ጥግ ላይ ትራሶች አኑረውበታል። ጥቅሶች በአረብኛና በአማ ርኛ የተጻፉባቸው ሥጋጃዎች ግድግዳው ላይ ተሰቅለዋል። አን ደኛው ላይ ከንፍ ያላት ነጭ ፈረስ ስትበር ይታየኛል። ሸራ ጫማዬን አወለቅኩና ጥግ ቁጭ አልኩኝ። ከጎን ካለው ክፍል መንዙማ ይሰማል።

ሰኔ አሥራሁለት
የዓለሙ ንጉሥ የተወለደበት
ሲበራ ይኖራል የድሉ መብራት
ተወለደ የድሉ ባለአልጋ
ይከበራል ቀኑ ክረምት ሆነ ቢጋ
እንኳን የነቢዩ ሰው ሌላም አይዘንጋ

ሴቶቹ አንድ የተከበረ እንግዳ እንደመጣባቸው ሁሉ ከወ ዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። ሁሉም በቀለማት ያሸበረቁትን ቀሚሶቻ ቸውን ለብሰዋል። ዘምዘም ትልቁን ኮካኮላ አምጥታ ከፍታ በብርጭቆ ቀድታ ሰጠችኝ። ፎዝያ ብስኩት፣ ከረሜላና ቴምር ያለበት ሳህን አምጥታ ከፊቴ አኖረችና "አንተ ቅዱስ ልጅ አላህ የባረከህ ብላ!" አለችኝ።

ዘምዘም እንድበላ እየጋበዘችኝ አንዷን ብስኩት አንስታ ትገምጣት ጀመር። መንዙማው ልብ በሚነካ ድምፅ ቀጠለ፦

በእግሬም በእጇም በቆላ በደጋ
ጠረፍ እስከ ጠረፍ ምድርን የዘረጋ
የጌታ ውለታ አያልቅም ተቆጥሮ
እኛን ፈለገና ዘይኖ ቀምሞ
ዓይንም እየሰጠን መስሚያም ደማሞ ጆሮ
ይህንን ማየት ነው ገምግሞና አዙሮ
በአማን በሊማን በእስልምና ኑሮ
ሰጠታው ደረሰ ታምናው ለዘንድሮ
ደሞ አገናኘን ደሞ አገናኘን በመውሊድ ቀጠሮ
መለየት ነው ደጉ ሐቄን ተመካክሮ

"አንተ አህመድ፣ ምነው ወጤን እያጠቀስካት ብትበላት? እንዲያ አላምሬ ሠርቼአት ትጠጣት?" የፎዝያ ድምፅ ነበር።

"ምን ልዩነት አለው? ተጠቀሰም ተጠጣ ያው በሆድ መዋሃ ዳቸው አይቀር" አለ አህመድ ወደ አለንበት ክፍል እየገባ። እን ዳየኝ ፈገግ ብሎ "አንተ ነህ የዘምዘም ጓደኛ? ጥሩ ልጅ! አላህ ይባርክህ" አለና እጁን ለሰላምታ ዘረጋልኝ።

በፍጥነት ብድግ ብዬ በሁለቱም እጄ ጨብጬው እጅ ነሳሁት።

"ተቀመጥ አይገባም። በአላህ በነቢይ! በሉ አስተናግ ዱት።" አለና ከእንዱ ጥግ ተቀምጦ ጋዜጣውን ገለጠ። "እነ አባባስ?" ካለ በኋላ "አ ለካ መስጊድ ሄደዋል" አለና ለራሱ መለሰ። አኳኋኑ ፈጣን ነው። ጋዜጣውን እያስተዋለ "እ! ይኼ የእስራኤልና የአረብ ፍጥጫ መቼ ይሆን ረግቦ በሰላም ሕዝቡ የሚኖረው?" አለ አሁንም ለራሱ።

የሰፈራችን ትልልቅ ሰዎች ይህ ዜና የሚመስጣቸውና ዋነ ኛው ወግ መሆኑ ትዝ አለኝ። አብዛኛውን ጊዜ ከርከር ውስጥ ሲከታቸው አስተውያለሁ። የከርከራቸውን ፍሬ ነገር አብጠርጥሬ ባላውቅም፣ እስራኤል አንዲት ትንሽ አገር ስትሆን አረቦቹ ብዙ አገሮች ናቸው። ምድራቸው ቤንዚን እንደምንጭ ስለሚፈልቅበት ያንን እየሸጡ በሚያገኙት ገንዘብ ጠመንጃ እንደልብ እንዳላቸው ሰምቻለሁ።

ሁሌም ለእስራኤል የሚያዳሉት አባ ዘለቀ "የጌታን አገር ማን ይችላል? እሱ ባርኪታል!" ብለው በተጨማሪ በግዕዝ ያነ በንቡና "እስራኤል እኮ እሱ ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለባረካት በዓመት አንድ ቀን ብቻ ነው የሚታ ረሰው። ምድረ እስራኤልን ለሕዝቧ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ

አድርጎ ፈጥሯታል" የመንደርተኛው የነብስ አባት በመሆናቸው ተሳስተዋል የሚሳቸው አልነበረም።

"እውነታቸውን ነው! እውነታቸውን ነው!" ይላል።

መንደርተኛው ወደየቤቱ ከሄደ በኋላ አባቴን "አንተ ዜራሞ፣ እናንተ አገር ጋሞጎፋ ሁልቀን እናርሳለን ትላለህ። እስራኤል ግን በዓመት አንድ ቀን ብቻ አርሰው እንዴት ሁልቀን ጠግበው ይኖራሉ?"

"ጫማ ሰፊውን ደጉ ምን ይላል መሰለህ?"

"ምን አሉ?"

"ደንበኞች ጫማቸውን አሰፍተው ክፍያው ላይ ይከራከሩታል። አስተያየት እንዲያደርግላቸው፣ በደንበኝነቱ እንዲቀንስላቸው ሲወተውቱት ምን ይላል መሰለህ? 'ትክክል ናችሁ፣ ለደንበኞቼ አስተያየት ማድረግ አለብኝ። ለናንተ አስተያየት እንዳላደርግ ችግር አለብኝ። ይሽውም ሆዴ ለእኔ የ45 ዓመታት ደንበኛዬ ነው። በቀን ሦስት ጊዜ የሚበላውንም፣ የሚጠጣውንም አቀር ብለታለሁ። አንድም ቀን ከደንበኝነቱ የሚፈለግብኝን አጓድቤበት አላውቅም። ሆዴም ደንበኝነቴን አውቆ አንድም ቀን ምሮኝ አያውቅም። እናንተም በደንበኝነታችሁ መሠረት ጫማችሁን አሳምሬ እሰፋላችኋለሁ፣ ተገቢውን ክፍያ ክፈሉኝ' ብሎ ያስቃቸዋል።"

"ፋንጋይ አባ ዘሰቀ የተናገሩት ልክ አይመስለኝም። ሆድን ያክል ቋሚ ደንበኛ ሁላችንም አለን። ስለዚህ ያለማቋረጥ መሥራትና የደንቡን ማድረስ የእኛም የእስራኤሎችም ግዴታ ነው። እንዲያውም እስራኤል አገር ሌት ተቀን የሚያርሱ ነው የሚመስለኝ። ቀን በፀሐይ፣ ማታ በመብራት። ትራክተርም አላቸው እኮ። አባ የመጽሐፍ ጉዳይ ብዙ ቢያውቁም አንዳንዴ በወሬ የሰሙትን እውነት አድርገው ያወራሉ። እኛ እንግዲህ አዋቂ አይደለን፣ አልተ ማርን። ምን ማስረጃ ጠቅሰን እንከራከራቸዋለን? ያሉንን መስማትና ማመዛዘን ይኖርብናል። እሳቸው የተከራከራቸውን ይገዝ ታሉ።" ያለኝን አስታወሰኩ።

ዘምዘም ግብፅ አገር ካይሮ ዩኒቨርሲቲ የሚማር ወንድም እንዳላት ነግራኛለች። ትንሽ አሞት ወደ አዲስ አበባ መምጣቱንና ብዙ ጨዋታ እንደሚያጫውታቸው፣ ተረትና ታሪክ እንደሚያውቅ ያወጋችኝ እሱ እንደሆነ ገመትኩኝ። አህመድ የሚያውቀውን ሲያወጋ እንደ እኩያ ባልንጀራው እቅርቧት ስለሆነ ብዙ እንድታውቅ አግዟታል። በትምህርት ቤታችን ክርክር በሚካሄድበት ወቅት ብዙ ጊዜ ዘምዘም ሁሴን የተሰለፈችበት ቡድን አሸናፊ የሚሆነው ከእርሱ ባገኘችው እውቀት ነበር። አንዳንዴ በክርክሩ ወቅት የምታነሳቸው ጭብጦች የዕድሜ እኩዮቿን ግር ሲያሰኘን መምህራኖቻችንን ያስገርማቸው እንደነበር አስታወሰኩ።

በአንድ ወቅት በዘመናዊና በባሕላዊ አለባበስ ሁለት ቡድን በክፍላችን ተፈጥሮ ክርክሩ ሲካሔድ ዘምዘም ባህላዊውን አለባበስ ነበር የምትደግፈው። "እንደምትመለክቱኝ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሴት ልጆች አዘውትረው የሚለብሱትን መቅለሚያ እና ኢጃብ ለብሼ የቀረብኩበት ያለ ምክንያት አይደለም። አንደኛው ምክንያቴ ባህላዊ አለባበሳችንን በጣም እወደዋለሁ። ዘመናዊ አለባበሳችንን ግን እነቅፈዋለሁ" እያለች ቀጠለች። በድፍረቷ፣ በቋንቋዋ ቀላልነት ዳኞቹን የማረከችው ዘምዘም ሁሴን ቡድንዋን ለድል አበቃችው። ከዚያን ዕለት ጀምሮ በትምህርት ቤታችን ዘምዘም ዝነኛ ሆነች።

"የሚገርም ነው!" አለ አህመድ።

ክሃሳቤ አባነነኝ።

"ምን የሚገርም ነገር ተፈጠረ?" አለች ፎዝያ ኪክ በሣህን ይዛልን ከውጭ እኛ ወዳለንበት ክፍል እየገባች። ለሁላችንም ድርሻ ድርሻችንን አደለችን። ዘምዘም ኬክ እንዴት ተቆርሶ እንደሚበላ አሳየችኝ። እንደሷ በሹካ ቆርሼ እየበላሁ ጆሮዎቼን ከፈትኩኝ።

"የሰው ልጅ ክመፋቀር ፍጅትን፣ ክመተባበር መጫረስን የፈለገበት ዓለም። ምናለ አላህ ሰውዬውን ልኮት ሁላችንም ፍርዳችንን ባገኘን።"

አላህ እግዚአብሔር እንደሆነ ዘምዘም ነግራኛለች። የሚላ ከው ሰውዬው ማን እንደሆነ ግር አለኝ። ሲቀጥሉም የወሬያቸው ፍሬ ነገር ተወሳሰበብኝ። ዘምዘም ጣልቃ ገብታ የተናገረችው ታሪክ ብቻ አስደሰተኝ፦

"ነብያችንማ የመዲና ከንቲባ በነበሩ ጊዜ ከተለያዬ ሃይማኖት መልዕክተኞች ጋር ተሰብስበው ይነጋገራሉ። በዚህ ጊዜ አይሁድ መልዕክተኞች የፀሎት ሰዓታቸው ስለደረሰ...

"እሺ የእኛ ጠቢብ" አለች ፎዝያ ትንሽ ፈርጠም ብላ እንደ መቀለድ እያለች። ቀጥይ በሚል ስሜት አህመድ ጠቀሳት።

"ሄደን ፀልየን እንድንመለስ ይፈቀድልን አሉ። ነብዩም እኔ የምፀልይበት ክፍል አለ። እዚያ ግቡና ፀልዩ ስትመለሱ መወያየታችንን እንቀጥላለን፣ ብለው ፀሎት ቤታቸው እንዲዘጋጅላቸው አዘዙ" አለቺና ዘምዘም ወጉዋን ቋጨች።

"ድንቅ ልጅ!" አለ አህመድ "እንዲህ ብሩህ ሕሊና ያለው ትውልድ እየተካን ነው። ተስፋ አደርጋለሁ፣ በናንተ ሕይወት መሠረት እንኪ" ድፍን አንድ ባውንድ አወጣና ሰጣት።

ፍንድቅ ብላ ተቀበለችው። እኔም ዓይኖቼን ማመን አልቻልኩም። "አስር ብር?!" ምን ታደርግበታለች? ትንሽ ተጨዋውተን ተሰናብተን ወጣን። ስመጣ በደስታ ተቀብለውኝ የነበሩት ልጆች እንደገና ከበቡኝና ተሰናበቱኝ። የማፈር የመሽኮርመም ባሕርይ ይታይባቸዋል። ፎዝያ አናቴን እየደባበሰችኝ፣ እንዴት መሄድ እንዳለብን ምክሯን እየለገሰችን ከግቢው ወጣን።

ከዚህ በኋላ የሆነው ሁሉ በአየር ላይ በአበባች መካከል እንደመብረር ሆኖ ነበር የሚታየኝ። ዘምዘም ፍንድቅ ብላለች። ታወራለች ትስቃለች። "ወደድካቸው?" ደጋግማ ትጠይቀኛለች። አውቶቡስ ማቆሚያ አጠገብ ደርሰናል።

"አራት ሰሙኒ ያለው!" ስላላ ድምፅ።

"የአውቶቡስ ትኬት የሚፈልግ!" ጉርናና ድምፅ።

ተዘውትሮ አውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ የሚሰማ ልፈፋ ነው።

"ለምን በአውቶቡስ አንሄድም?!" አልኳት።

"በሴቼንቶ ነው የምንሄደው"

ሴቼንቶ ስንጠብቅ "ያንን ያልከኝን የፍቅር ደብዳቤ ታሪክ አሁን ንገረኛ?"

"እ? የፒፖንና የትዕግሥትን የፍቅር ደብዳቤ?"

"አዎን። ስማቸውን አትጥራ። ዝም ብለህ ደብዳቤውን እን ዴት እየጻፍክ እንደምታገናኛቸው አውራልኝ።"

"አንድ ቀን ለታ ፈረንጁ ወፍጮ ቤት አካባቢ የሚኖሩ ዘመ ዶቼን ልጠይቅ ሔድኩ። ከጐረቤት ሦስት ወንድ ልጆች ያለው ጣሊያን ሰውዬ አለ። እናታቸው አበሻ ነች። ታላቃቸው ፒፖ ይባላል። ወንድሞቹ እንቶንዮና ማሪዮ ይባላሉ። ሁለቱንም አሸንፋቸዋለሁ።"

"ተደባድባችኋል?"

"አዎን።"

"መደባደብ ጥሩ አይደለም"

"እኔ ኮ መጣላት ፈልጌ አይደለም። ልጆቹ የምፈራ መስ ሏቸው ይዋጣልን አሉኝ። እሺ አልኩ። አንቶኒዮ በቦክስ ሲለኝ መሬት ወደቅኩኝ። ከዚያም አሻሮ የሚባለው ጓደኛዬ "እንደገና ይዋጣላችሁ" አለና ቀድሟ እንድመታው መከረኝ። እንዳለኝ አደረኩ። አንቶኒዮ ቲማቲም መስሎ ተዘረረ። ትንሹን እንቅ አደረግኩና በቴስታ መረግኩበት። ሁለቱም ጮኸው አለቀሱ። ከዚያ በኋላ ተከባበርን። በአሁኑ ጊዜ ዘመዶቼን ልጠይቅ ስሔድ ወንድማቾቹ ማርማላታ የተቀባ ዳቦ ይገብሩልኛል። እኔ ግን ማር ማላታ በልቼ ስለማላውቅ ዳቦውን ብቻ ቀፍፌ እበላለሁ።"

አየላቀች "ማርማዳ የመሰለን የጤፍ ቂጣ ከመግመጥ ተገላገልክ!" አለቺኝ።

አብረን ሳቅን።

"የፍቅር ደብዳቤውን ለትልቁ ወንድማቸው መጻፍ እንዴት ጀመርክ?" አለችኝ። ወደ ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት አቅጣጫ በእግር እያዘገምን ነው። ጓደኞቼን አስታወስኩ። አሁን የሚጫ ወቱት አሸዋ ሜዳ ሆነ እንጂ ራስ ብሩ ሜዳ ቢሆን ኖሮ ከዘምዘም ጋር ያዩኝ ነበር። ቢያዩኝ ደግሞ አይምሩኝም ይለክ ፉኛል። ዕድለኛ ስለሆንኩ ማንም ሳያየኝ ወደ ግዮን ሆቴል የሚወስደውን አቅጣጫ ያዝን።

"ፒፖ የተማረው ጣሊያን ትምህርት ቤት ነው። የሚወዳት ልጅ ደብዳቤ በማሊያንኛ ቢጽፍላት አታነበውም። ስለዚህ የእኔን እጅ ጽሕፈት አየና ወደደው። ከዚያም የምጽፍለትን እየነገረኝ ያጽፈኛል። ከጨረስን በኋላ ያስነብበኛል።

"ምን ምን ብሎ ነው የሚያስጽፍህ? በአላህ! ስማቸውን የእ ሷንም የእሱንም ሳትጠራ አውራልኝ"

ፒፖ የሚያስጀምረኝ በስሟ ስለነበር እንዴት እንደምጀምር ግራ ገባኝ። ዘምዘም ልክ እንደ ትልልቅ ፍቅረኞች ግራ እጅዋን ከቀኝ እጁ ጋር አቆላልፋ አቅፋ አፍዋንና ዓይኖቿን ከፍታ ታየኛለች።

"በጣም ለምወድሽና ለማፈቅርሽ ውድ ፍቅረኛዬ..."

ዘምዘም በረጅሙ ተነፈሰች። የጎንዮሽ ሰረቅ አድርጌ አየ ኋትና ቀጠልኩ።

"እንዴት ነሽ? ፍቅርሽ ከሰማይ ርቀቱ፣ ከከዋክብት ድም ቀቱ፣ ከባሕር ጥልቀቱ፣ ሁሉ ጠልቆ እየታየኝ አንቺን ሁሌም እንዳብሰለስልሽ ያደርገኛል"

ዘምዘም ሙዚቃዊ ሳቅዋን ለቀቀችው። ሳቅዋ ተጋባብኝ።

"ስበላም ስጠጣም፣ ስተኛም ሁሌም አንቺን አስብሻለሁ። ፍቅሬ፣ እኔና አንቺ በነፃነት ሙዚቃ እየሰማን፣ ሲኒማ እያየን፣ ሃሳብ ሰሃሳብ እየተለዋወጥን የምንጨዋወትበት ቀን እንደዘለዓለም ርቆኝ ያብከነክነኛል።"

ዘምዘም ዓይኖቿን አስለመለመችና በእጅዋ ጥብቅ አድርጋ ያዘችኝ። ቀጥል በሚል ስሜት ትንሽ ጎኔን ጎሸም አደረገችኝ። እንደ መሽኮርመም እያደረገኝ ተእዛዝዋን ተቀበልኩኝ።

"ውዴ፣ አንቺስ ስለእኔ ምን ይሰማሻል? መልስሽን በፍጥ ነት ላኪልኝ። ያንቺን ደብዳቤ ካላገኘሁ ምግብም አይበላልኝ፣ እንቅልፍም አይወስደኝ፣ አንሳሌም ሰላም አያገኝም።"

"እሱ እንዲህ እያለ ሊነግርህ አንተ ስትጽፍ ምንም አይሰ ማህም?" ብላኝ፣ ፊቷን ወደ እኔ አዙሯ በረጅሙ ስትተነፍስ፣ የትንፋሽዋ ወላፈን ቀያይ ጢሞቼን ፈጅቶ ያረገፋቸው መስሎኝ። ምን እንደነካኝ ላላውቅ ደስ በሚል ስሜት ውስጥ ገብቼ ፍንድቅ አደልኩ ነበር።

"አንዳንዴ ቃላቶቹ ያሳፍሩኝና እሽኮረመማለሁ" ስላት ሳቅዋን መቆጣጠር አልቻለችም።

"ለልጅቱ እንዴት ነው የምትሰጣት?"

"ከእሷ ቤት ጓሮ የምንጫወትበት ክትፎ ሜዳ የሚባል ቦታ አለ። የእኛን ካስ ጨዋታ በአጥር አሾልካ የምታይ መስላ ዳንቴል እየሠራች ትጠብቀኛለች። ቀኑ እሁድ ከሆነ የኪስ ሬዲዮናን ከፍታ የዘፈን ምርጫ ፕሮግራም ከአንድ ከሁለት ጓደ ኞቿ ጋር ታደምጣለች። እሁድ እሁድ ሁሌ ፒፖ ዘፈን በሬዲዮ ይመርጥላታል። ስሙን ግን በእንግሊዘኛ ፊደል አሳጥሮ ነው የሚጽፈው። የእሷንም እንዲሁ ይጽፍና ለሬዲዮ መሥሪያ ቤት

ያሳውቃል። እሷም ስትሰማ ደስ ይላትና ፈገግ ብላ ዓይኖቿን ገርበብ አድርጋ ታደምጣለች። ቀስ ብዬ በእጥሩ ቀዳዳ ደብዳቤውን ሳቀብላት በፍጥነት ተቀብላ ታነብና መልሷን ጽፋ እስከ ምትመጣ እየተጫወትኩ እቆያታለሁ። አንዳንዴም ደብዳቤ ከፒፖ ሳይመጣላትም ጽፋ ትጠብቀኛለች።"

"የእሷንም ደብዳቤ ለእሱ የምታነብለት አንተ ነህ?"

"አዎን፣ የእሷ ደብዳቤ ሽቶ ሽቶ ይሸታል። የእጅ ጽሕፈ ትዋ ግን ሳነበው ያስቸግረኛል።"

"አዎን ፍቅርዬ ማለቷ ነው። በጣም ነው የምትወደኝ። ቀጥል እሺ ፍቅርዬ" ይለኝና ያደምጠኛል። "እምወድህ፣ የእኔን ስቃይና መከራ ባየኸው! አንተን ከማለም ከማሰብ፣ በፀሎቴም አምላክን ከመለመን አላጓድልም።"

'እየተሸከረመምኩ አንብቤ እጨርስለታለሁ።"

"ይህንን ሁሉ ስታደርግለት ምን ይሰጥሃል?"

"ሁልጊዜ ከርክ ከርክ ይለጠኛል።"

"እንተም ጮርናቄህን ትነጭበታለህ?"

"በደንብ!"

ዘምዘም በሰማችው ታሪክ ረክታ ደስ አላት። ሴቼንቶ አስቱመን የጓለኛውን በር ከፍተን ገብተን ጎን ለጎን ተቀመጥን።

"ተስፍሽ፣ አንድ ነገር ልለምንህ?" አለቺኝ በሹክሹክታ።

"ምን?"

"በፍራንክ ቁማር እንዳትጫወት። ሌቦች የሆኑ የሰፈራችሁ ልጆች አሉ፣ ከእነሱ ጋር እንዳትገጥም፣ ከትምህርት ላይ ላለመፎረፍ ቃል ግባልኝ።"

ዱብ ዕዳ ነበር የሆነብኝ፤ ስለእኔ ብዙ ታውቃለች።

"እሺ ቃል እገባልሻለሁ። ግን?"

"ግን ምን?"

"እነዚህ 'ቲፍ' የሆኑት ጓደኞቼ እኮ መጻሕፍት ማንበብ ይወዳሉ። አብሬያቸው ስሆን ብዙ መጻሕፍት ያስነበቡኛል። ከእነሱ ጋር ካልሆንኩ መጽሐፍ ከየት አመጣለሁ? ከማንስ ጋር እጫወታለሁ?!"

"መጽሐፍ እኛ ቤት አለ፣ አመጣልሃለሁ። ካስፈለገም አባቴን እንዲገዛልኝ አደርጋለሁ። ካስ ጨዋታውን ግን አታቁም።"

"እሺ!" አልኩኝ። ጓደኞቼን መለየት ግን መሪር ሐዘን በውስጤ ፈጥሮ ስለነበረ በካስ ጨዋታ ስበብ እንዳገኛቸው በመፍቀዷ ደስ አለኝ። ከእነዚህ ልጆች ጋር ያለኝን ግንኙነት አባቴ ለማስቆም ብዙ ሞክሮ አቅቶት ነበር። ዛሬ ግን እነሆ፣ በሄዋን ዘር በጥቂት ቃላት ትእዛዝ አካሄዴን ማስተካከሉ የግድ ሆነ።

"እናቴ ትሙት በለኝ።"

ማልኩላት፤

"እንዴት ነው አኳኋናችሁ? ወንድምና እህት ናችሁ?" አለን ባለታክሲው።

"አዎን!" አለች ዘምዘም።

"ጥሩ! ግን አይመስልም። በጣም ትዋደዳላችሁ።"

"ወንድምና እህት እንደሚዋደዱው?" አለችና ዘምዘም ብር አውጥታ ሰጠችው። ሽልንግ መለሰላት። ሲኒማ ኢትዮጵያ ደጅ ወረድን። ግርግር አልነበረም። ደብዘዝ ያለ ብርሃን በሲኒማ ቤቱ ውስጥ አለ። ለእኔ አልታየኝም። ዘምዘም በለመደ እግሯ እጄን ይዛ እየመራችኝ ወንበር አግኝተን ተቀመጥን። ሲኒማ ቤቱ ለእኔ አዲስ ስለነበር ዙሪያ ገባውን በደብዛዛው ብርሃንም ቢሆን በፍጥነት ለማስተዋል ሞከርኩ። ለስላሳ መጠጥ ጋበዘችኝ። ዘና ብዬ መጎንጨት ጀመርኩ። ሁሉም ነገር ብርቅ ሆኖብኛል።

"ያ ልጅ እንዴት ነው የሚያደህየ?" አለችኝ ዘምዘም።

"የቱ?" ብዬ ሳጮልቅ መብራት ጠፋና ሲኒማው ተጀመረ። ልጁን አላየሁትም። ዘምዘም እጅዋን አመጣችና እጄ ላይ ጫነች። ጭብጥ ስታደርገኝ ሙቀቷ በፍጥነት ተጋባብኝ። የማይበት አይኖቼ ተደፍነው ውስጣዊ ዓይኖቼ ተገለጡ...

የቴያትር ሀሁ

"ልጅ ሆይ፣ መልካም ነውና ማር ብላ፣
የማር ወለላ ጣዕም ይጣፍጥሃል።
ጥበብም ለነፍስህ እንደዚሁ ጣፋጭ እንደሆነች እወቅ፣
ብታገኛት ለነገ አለኝታ ይኖርሃል፣
ተስፋህም ከንቱ አይሆንም።
መጽሐፈ ምሣሌ 24:13-14

መምህራኖቻችን ከለኞ እስከ ሐሙስ ከሂሳብ ጮራው፣ ከሣይንሱ፣ ከቋንቋ፣... መጻሕፍት እያጣቀሱ ያስተምሩናል። አርብ ከሰዓት በኋላ የተለያዩ ኪነጥበባዊ እውቀት እምንቀስምበት ዕለት ነበር። ከትምህርት ቤት በመቅረት የታወቁት እነ ጋንች፣ ቁልጭ፣ ቾምቤና ሌሎችም ልጆች ዕለተ አርብ ከሆነ አይዘነጉትም። እይቀሩም።

ቲቸር መስፍን 'ቱሲ' ክፍል ውስጥ 'ትምህርት ቤቴ ማርና ወተቴ' የተባለውን መዝሙር ያስዘምራሉ። የነገዋ የኢትዮጵያ ተስፋዎች በክፍተኛ ድምፅ ሲዘምሩ አድማስን ሰንጥቆ ይሰማል። ቲቸር መስፍንም የድምፁን አወጣጥ እንደ ድንቅ የኦርኬስትራ መሪ በጣቶቻቸው ምልክት እየመሩ እየዘመሩ ያስዘምራሉ።

ቲቸር ጥበበ በ'ስራ ሲ' ውቢቷ አገሬ' የሚባለውን መዝሙር እያስዘመሩ ከ'ቱ ሲ' ልቆ እንዲሰማ የልጆቹን ስሜት ከፍ እንዲል እያበረታቱ እርሳቸውም አብረው ይዘምራሉ::

ቲቸር አባብያ ጥቁር መነፅራቸውን ሽቅብ ከፍ እያደረጉ 'ሰንደቅ ዓላማችን' የተባለውን መዝሙር የ'ፎር ቢ' ተማሪዎችን ያዘምሩናል:: ሌሎችንም ክፍሎች የተለያዩ መምህራን ተከፋፍለው አገራችንን፣ ውበታችንን፣ ነፃነታችንን፣ ፍቅራችንን፣ ጀግንነታችንን፣... የሚገልጹ በርካታ መዝሙሮች እንዘምራለን::

እርስ በራሳችን ተመራርጠን ቴያትር የምንተውንበት ጊዜም አለ:: ብዙ ጊዜ እንደ ምንጭ የምንጠቀመው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚተላለፉትን ድራማዎችን ነበር:: በገፀ ባሕርያት ድልድል ወቅት ሁሉም ልጆች የሚፈልጉት ዋና ዋናዎቹን ገፀ ባሕርያት መስለው መጫወት ነበር:: ችሎታው አለኝ የለኝም ብሎ ራስን የመመዘን ልማዱ አልነበረንም:: ለአብዛኛው ተማሪዎች ባሕርያቱ ከገሃዱ ዓለም ጉሮ ጋር የሚጋጭባቸው ጊዜ ነበር::

"ገረድ ሆኜ ብጫወት ለእኔ ምንም አያመለለኝም፤ እናቴ ግን ብታየኝ አስተምሬ፣ አስተምሬ ገረድ!? ብላ ትገድለኛለች!" አለች ኑኑሽ እንደ ማልቀስ እየቃጣት::

"እንዴት ዘበኛ ሁን ትለኛለህ? ይዋጣልናል! ሰኔ 30 ጠብቀኝ!" አለኝ ተሰማ ብልጭ ደሙ ፈልቶ "አንተ እንደወጋየሁንጋቱ እየዘነጥክ ልትኮምክን፣ ጓደኛህ ሲሳይ ጎቢጥ እንደ ደበበ እሸቱ ሊጫወት! ሽርክህ ዘምዘም እንደ ዓለምፀሐይ ወዳጆ ትጫወታለች! እኔ ግን ዘበኛ! ብሞት ይሻለኛል! አባቴ ዘበኛ ነው፣ እኔም ዘበኛ ልሆን!? አንላቀቃትም:: ሰኔ 30 ትድረስ::"

ጥበቡን በገባን መንገድ እንደመሰለን ተረጎምነው:: የቴያትር ሀሁን እንዲህ ፋና ብንወጋም በመካከላችን በቀላሉ ተግባብተን ልንፈታው የማንችለው ችግር ተከሰተ:: ዓለምፀሐይ ወዳጆን የወከለ ችሎን ገፀ ባሕሪ ሆና የምትጫወተው ዘምዘም የተሰጣትን የፍቅረኛ ሚና ወዳዋለች:: ዓይኖቿን እያስለመለመች "ምንድነው? የእውነት እኮ አይደለም:: ጨዋታ አይደለም እንዴ?!" እያለች እንድን ጀምር ታግባባናለች:: አስናቀች ወርቁ የእናትነት ባህርይን ተላብሳ ስትጫወት አይተናታል:: ይህችን ባህርይ ፀሐይ በቴሌቪዥን አይታት ወዳታለች:: ልክ እንደ አስናቀች ለመጫወት ስለቋመጠች «እውነትም እኮ ጨዋታ ነው:: በቃ ልጆች በእናታችሁ ልምምዱን እንጀምር::» እያለች ትወተውታለች::

በዚያን ወቅት በርካታ ሕፃናት ቴሌቪዥን የማየት ዕድል አልነበራቸውም:: እኔ፣ ሲሳይ ጎቢጥ፣ መኩዬ ቀጫጫው ቴሌቪዥን የማየት ዕድል ስለነበረን የደራሲውንና የአዘጋጁን ሚና ከዋና ባሕርያቱ ጋር አጣምረን በመያዝ ቡድኑን በግድም በውድም

እንመራለን:: እንዳለ መታደል ተመልካቾቻችን እኛን የሚያዩን እንደ ተዋጣልን ተዋንያን ሳይሆን እንደ ዱርዬ ተማሪ ነበር::

አንዳንዴ መምህራኖቻችን ራሳቸው ፀሐፊም፣ ተዋናይም ሆነው እኛን በተመልካችነት እንድንታደም ይጋብዙናል:: ቃለ ተውኔቱ ሲፅፉት ለእኛ በሚገባን ቀላል ቋንቋ ይሆንና፣ ጭብጡም በእኛው ሕይወት ዙሪያ ላይ ያተኮረ ስለሚሆን ታሪኩ የሚኖረው ቅርበት ያስደስተን ነበር::

ቲቸር ጥበበ የሰነፍ ተማሪ ባሕርይ ተላብሰው፣ ቲቸር አባብያ አስተማሪ ሆነው በጥያቄ ያፋጥጧቸዋል::

"ካት፣"
"ድመት::"
"ዶግ?"
"ውሻ"
"ቴብል?"
"ጠረጴዛ::"
"ቸርች?"
"እውራ ዶሮ::"

በዚህን ጊዜ በሳቅ እናውካካለን::

ቲቸር ጥበበ መልሷን ለማግኘት ዓይናቸውን ሲያስለመልሙ፣ ሲቅለሰለሱ፣ ሲንቆራጠጡ የባስ በሳቅ ሆዳችን ይቆስላል:: ቲቸር አባብያ የእውነት ተናደው አፍጠው ይቁነጠነጣሉ:: ቲቸር ጥበበ ጣራውን መሬቱን እያዩ የ'ቸርችን' መልስ ያብሰለስላሉ::...

ቴያትር ሲባል አስቂኝ ብቻ አለመሆኑን ልባችን ውስጥ ጭፍጉን ትዕይንት ለመቅረፅ የተጠቀሙበት ስልት አሁን ሳስበው ያስደንቀኛል::

ቲቸር መስፍን አንድ ቀን ሲተውኑ የወታደር የደንብ ልብስ ለብሰው፣ ጠመንጃ አንግተው፣ በሰፊ ቀበቶ ኮዳ ታጥቀው መድረክ ላይ ወጡ:: ወታደራዊ ሰላምታ ሰጡን:: በአድናቆት አጨበጨብንላቸው::

ቃላቱን ሲያነበንቡ በቀጥታ ከእኛ ጋር እሚያገናኝ ሆነ "ልጆች፣ ደህና ሁኑ:: ታላቅ ወንድሜ ለአገራችን ኢትዮጵያ ፍቅርና ክብር ሲል በውጋዴን በረሃ ከጠላት ሠርጎ ገቦች ጋር ሲዋጋ ሞተ!" ሲሉ ተማሪው በንዴት አጉተመተሙ::

"ስለዚህ በወንድሜ ምትክ እንድዘምት ታዝዣለሁ:: ከሰኞ ጀምሮ ከእናንተ ጋር አንገናኝም:: ዘመቻ መሄዴ ነውና ደህና ሁኑ" ብለው በወታደራዊ ሥርዓት በቀኝ እግራቸው መድረኩን በክስክስ ጫማቸው ደቁትና ሰላምታ ሰጡን::

አዳራሹ በሐዘን ተውጦ ፀጥ አለ:: ቲቸር ጥበበ ተከዝው መድረክ ላይ ወጡ "ይቅናህ፣ ወታደር መስፍን:: ጠላትን ድል አድርጋችሁ ስትመለሱ እንደገና ልጆቻችንን እንደምናስተምር እርግጠኛ ነኝ" ብለው በመሳሳም አሰናበቷቸው::

ሆደ ቡቡዋ እታለም እረታዋን አቀለጠችው፣ ኑኑሽ እዬ ዬዋን አስነካችው፣ ዘምዘም ተንሰቀሰቀች። ልቅሶው ካንዱ ወደ ሌላው እየተጋባ አዳራሹ የልቅሰ መናኸሪያ ሆነ። ጨካኙ ቾምቤ እንኳ ንፍጡን እያዝረከረከ ኡኡታውን ለቀቀው። ዝምተኛዋ ወይንሸት እንባዋ በጉንጮቿ ላጭ ወረደ።

ወታደር መሰፍን ቀኝ ጓሳ ዞረው ወደ በሩ ተራመዱ። የት ምህርት ቤታችን የእግር ኳስ ቡድን በረኛ ሁሴን ጂቦ ተወረወረና እግራቸውን ጥርቅም አድርጎ ይዞ እየጮኸ አለቀሰ።

ቲቸር ጥበበ በጥልቅ ሐዘናችን ልባቸው ተነካ። ቲቸር "ፀጥታ!" አሉና በአስገምጋሚ ድምፅ አዘውን "መምህር መሰፍን እንዲቀር ትፈልጋላችሁ?!" ሲሉን አንድ ላይ "አልን!" አልን።

"በጣም ጥሩ! መሰፍን እንዲቀር የፈለጋችሁ ከሆነ እናንተ ንበዝ ተማሪ ሰመሆን ጣሩ። ንበዝ ተማሪዎች ሆናችሁ ፈተና ችሁን በአኩሪ ውጤት ካለፋችሁ፣ በአስቸኳይ ሰጃንሆይ ደብዳቤ ጽፌ መምህር መሰፍን ከውትድርናው ይልቅ ቢያስተምር ለሀገር የበለጠ እንደሚጠቅም አሳሰባለሁ። ሰለዚህ ንበዝ ተማሪ ለመሆን ቃል ግቡልኝ" ሲሉን ሁላችንም ቃል ገባን።

ቲቸር መሰፍን ያነጉቱትን ጠመንጃ እወረዱ። ሁሴን ጂቦም እግራቸውን ለቀቃቸው። ፈተና እየወደቀ ሁሌም ክፍል የሚደግመው አለሙ ጅሎ በለሆሳስ "እውን እናጠናለን፣ ንበዝ ተማሪ እንሆናለን" ሲል ሰማሁት።

ውዝዋዜ

"የማታውቁ ብትሆኑ የእውቀት ባለቤቶችን ጠይቁ"
ቅዱስ ቁርአን

ወንድ ልጆች ምን እንደነካን እንጃ ስለ ልጃገረዶች ማውራት ጀምረናል። ከእነዚህ ቆነጃጂት ጋር የአካባቢውን እየር በጋራ የምን ተነፍስበት ቦታ አንዱ ጥምቀተ ባሕር ነበር። በዛ ሬው ጥምቀት እየደነሰን ጀምበር ስትጠልቅ የሚመጣው ጥምቀት ይናፍቀናል። የሕፃኑ ቂርቆስ ንግሥ ጥር 15 ቀን ሰለሆነ ተጨ ማሪ የዳንስ ቀን አለን። በማግሥቱ ጥር 16 ቀን የሕፃኑ ቂርቆስ እናት የእየሉጣ ንግሥ ነው፣ ሌላ ተጨማሪ የደስታ ቀን ይዛልን ትመጣለች።

ጥምቀት ለእኛ ለቂርቆስ ልጆች ከሰፈራችን ታቦት በተ ጨማሪ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንም ሔደን እንጫወታለን።

እዚያ ከቦሌ፣ ከፊት በር፣ ከፍልውሃ፣ ከሠንጋ ተራ፣ ከመር ካቶ፣... ከሚመጡ ልጆች ጋር እንደንሳለን።

የእኛ ሰፈር አርሞኒካ ተጨዋች ጎሣዬ አበበ ነው። ንቁና ቁንጠኛ ወጣት ነው፣ ሲራመድ ይነጥራል። አፍሮ ፀጉሩን ነስንሶ በንፁህ አለባበሱ ብቅ ይላል። ሀርሞኒካውን ይቃኛታል። እንክ በዋለን። "ሞቅ አርጉታ!"

አጨብጨቡ ማለቱ ነው። ችክችክ ባንባ በአርሞኒካው መዝፈን ይጀምራል። ነሸጥ ያደረጋቸው ልጆች ተገባብዘው ዳን ኪራውን ያስነኩታል። የመደነሻው መድረክ እንዳይጠብ አንዱ ጭራሮ ይዞ ታዳቼሚዎችን ወደኋላ እየገፋ ያሰፋዋል። ታዳሚው ግን ዳንኪራውን ለማየት ሲንጠራራ ሲጋፋ መድረኩ ተመልሶ መጥበቡ የግድ ነው።

የባህል ዘፈን ሞቅ ይላል። አሮምኛው፣ አማርኛው፣ ትግር ኛው፣ ጉራጌኛው፣ ጋሞው፣... እዚያም፣ እዚህም ክብ ሠርተው ያዜማሉ። በጨጠቆረ (ዳርት)፣ ለስላሳ ጠርሙስ ላይ ቀለበት ወርውሮ ማስገባት የሚያጫውቱ ከበዓሉ አካል ናቸው። ከረሜላ፣ ማስቲካ፣ ሽምብራ እሸት፣ ሸንኮራ አገዳ፣ ሽልምልም ዘንግ ሻጮች በልፈፋቸው በዓሉን ያደምቁታል። የጥምቀተ ባሕሩ ሞቅታ እየበዛ ሲመጣ፣ ጀምበርም ለመጥለቅ ስታዘቀዝቅ ፀብ እን ዳይደፈርስ በመስጋት ፖሊስ ጨዋታውን መበተን ይጀምራል።

ቀጢሳውን ድርቅ ብሎ ቆሞ አገኘሁት።

"ምን ሆንክ?" አልኩት ጠጋ ብዬ።

ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ "አሰገደች አሁን ስታልፍ ነካ ችኝና የሆነ ነገር ድርርርር አደረጎኝ" ከሚክ ስለሆነ ጭብጥ የማትሞላ አናቱን እየነቀነቀ በዓይኑ፣ በእጁ፣ በእግሩ፣ በሁለን ተናው ነው የሚያወራው።

ይህ የቀጢሳው አኳኋን መኩዬ ቀጫጫዋም ባልተለመደ መልክ አምለሰትን ብቻዋን ስታገኛት እንዴት እንደምትለማ መጣት አስታወሰኝ።

እሷ እየተሽኮረመመች "እምቢ"

ምን እንደምትለምናት ጠይቄአት "አልነግርህም" ብላኛለች።

እከታተላቸዋለሁ። ይህቺ መኩዬ አምለሰትን ወደ ማስ ገደዱ ቃጣት። ይኼኔ አምለሰት ፊትዋን በእጅዋ ሸፍና እያለ ቀሰች "አደይ!" ስትል፤

"ወይ!" አሉ እናቷ ቤት ውስጥ እንዳሉ።

"ይኼ መኩዬ 'ባለጌ ሥራ' እንሥራ ይለኛል!" አለች አምለሰት የምር እያለቀሰች።

መኩዬ ቀጫጫው እንደጥይት ቱር ብላ ተሰወረች። ድር ጊቷ ስላሳፈራት ለዕለታት ከሰፈራችን ጠፋች። ይህ ቀጢሳውን ድርርር! ያደረገው ስሜት፣ የመኩዬ አይነት ነው? ስል አብ

ሰለሰልኩት:: (ለዘምዘም ያለኝን ስሜትም ልስልስ ባለ ደስታ አስታወስኩ!)

ከሀሳቤ ተመለስኩ አሰገደች ከማዶ ቀሚስና ሱሪ ለብሳ ትታየናለች፣ መቅደስ ከጎንዋ አለች:: እቴቴና ዓለማየሁ እየደነሱ ነው:: እቴቴ ድርብ ጥርሷን ለመሸፈን ከንፈሯን ስባ አፍዋን ገጥማለች:: ይታወቅኛል እየሳቀች ነው:: አሌክስ ዓይኑን ገርበብ አድርጎ በስልት ተከትሏታል:: እሷ ፀጉሯን ተተኩሳለች፣ የቆዳ ፓሪሞድ ለብሳለች፣ ባለቡሽ ታች ጫማ አድርጋለች:: ጎሣዬ ሀር ሞኒካውን ያስነካዋል:: ከቀጢሳው ጋር ስለ ልጃገረድ ጓደኞቻችን እየተጨዋወትን ነው::

"እኔ ሳድግ የማገባው አሰገደችን ነው:: አንተ ደግሞ መቅደስን ማግባት ትችላለህ:: እሷ እኮ ያንተ ሚስት ነች::"

"እኔ ሳድግ የማገባው ዘምዘምን ነው::"

"እንዴ! እሷ እስላም፣ አንተ ክርስቲያን ስለሆንክ አይቻልም!"

"ይቻላል! ከፈለክ ልንገርህ አንድ ቀንለታ" አልኩት "ከእማዬ ጋር መርካቶ ሄደን በራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ስናልፍ፣ አንድ ሰውዬ በማይክሮፎን ሲዘምር ሰማሁና እማዬን ምንድነው? አልኳት:: ይኼ የእስላሞች ፀሎት ቤት ነው አሰችኝ:: 'ሁሰት ልጆች በጣም ተዋደው እስላምና ክርስቲያን ቢሆኑ መጋባት ይችላሉ ወይ?' ብዬ ጠይቄአት፣ 'ይችላሉ ሁለቱም የአንድ እግዚአብሔር ፍጥረት ናቸው' ብላኛለች:: ስለዚህ ትምህርታችንን እንደጨረስን የማገባው ዘምዘምን ነው::"

መቅደስ ወደ እኛ እያየች ነው:: ድሮ ዕቃ ዕቃ ስንጫወት ሚስቴ ነበረች:: የሷ ፍላጉት በዚያው አድጉ አሁንም ትወደኛለች:: የኔ ቀልብ ግን ዘምዘም ሁሌን ላይ ካረፈ ቆየ:: ዝም አልኳት:: ቀጢሳው ከአሰገደች ጋር ሊደንስ ወደ መድረኩ ገባ:: ዓይኔን ሳማትር ዘምዘምን ወደእኔ ስትመጣ አየኋት:: ተጠግታኝ በግራ እጇ ሜንታ ከረሜላ አስጨበጠችኝ:: አንዱን ለራሷ በላችና "አንተ፣ በሰፈራችሁ ላልፍ ኃይሉን አየሁት:: በራቸው'ጋ ቆሟል:: ግድ ግዳ ላይ የተሰጠፈውን የክበባችሁን አርማ በጣቱ ጠቁሞ አሳየኝ:: የሕፃናት ፍሬ የሰውነት ማዳበሪያ ክበብ ይላል:: ልክ አይደላች ሁም:: አሁንም ሕፃን ናችሁ? መሆን ያለበት የወጣቶች ፍሬ የሰውነት ማዳበሪያ ክበብ ነው::"

በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ አባባ ቱሉ አጠናና ቆርቆሮ ሰጥተውን ከጓሮአቸው ያለው መሬት ላይ ቤት ሠራንበት:: ከምድር ባቡር በሰረቅነው የባቡር ፍሬን ሰውነታችንን የምናዳብርበትን የስፖርት ቁሳቁስ አዘጋጀን:: ከየቤታችን ያለንን መጻሕፍት አዋጣን:: መደርደሪያ አዘጋጅተን በወጉ ደረደርናቸው:: በወር ስሙኒ ስሙኒ ለክበባችን እናዋጣለን:: መጽሐፍ ተውሰን እናነባለን:: በቻልናቸው ቀናት ጠዋትና ማታ ክብደት በማንሳት አካላችንን ማዳበር ጀምረናል:: ለማኅበራችን እኔ ፀሐፊ፣ አብነት

ባሪያውን ዳኛ አድርገን መርጠን አብሮ አደጎቹ በመልካም እንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን::

"ለኃይሉ ነገርሺው?" አልኳት ዘምዘምን::

"በደንብ ነዋ! በዚህ ዕድሜ six grade student ሆነህ ሕፃን ትባላለህ:: አሁን ሁላችሁም ወጣቶች ናችሁ::" ይሀንን ስነግረው ኃይሉ መሰላል አመጣና ሕፃናት የሚለውን ቃል ሰርዞ ወጣቶች ብሎ ጻፈበት::"

"ዘምዘምዬ አንጎልሽ ክፍት ነው አሪፍ ልጅ!" አልኩና ሳብ አድርጌ ጉንጭዋ ላይ ሣም አደረኳት:: ሁለታችንም ደነገጥን:: በለሆሳስ ድምፅ እንድንደንስ ጋበዘችኝ:: ወደ መድረኩ ገባን:: ፓምፕ የሚባለውን ዳንስ እናስነካው ጀመር::

"*ጭራሮ! ጭራሮ!" አሰ ክቡን እንዲያሰፉ የሚያዘው ፍፁም፣ አርጩሜ ይዟል:: መሬቱን እየመታ ተመልካቾች ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ አደረገና ዓለምፀሐይን አብራው እንድትደንስ ጋበዛት:: ባቴንድራስ የሚባል ጃኬት ለብሶ፣ ቤልባተም ሱሪ ታጥቆ፣ የወታደር ክስክስ ጫማ አድርጓል:: ገንባሌውን ተልት ሎታል:: የጎረምሳ ፋሽን አሰባበስ ነው::

ጭብጨባው ሞቅ አለ:: ጎሣዬ ላብ አጥምቆት አሁንም ሀርሞኒካውን በፍቅር እየነፋ ነው:: አሏራው ጨስ!

አጠገባችን ባቴንድራስ የሰበሰ አፍሮ ወጣት ዝንጉርጉር ቀሚስ ከሰበሰች ልጅ ጋር ይደንሳል:: እየደነሱ ማንነቷን ለማወቅ በርካታ ጥያቄዎች ይጠይቃታል:: የሚያወሩት ጥርት ብሎ ይሰማናል:: ጣፋጭ ከረሜላችንን እየመጠጥን አካላችንን ለዳንስ፣ ጆሮአችንን ለጎረምሳው ውትወታ አስገዝተን እንጫወታለን::

"ሰፈርሽ የት ነው?"

"ዝም ብለህ ደንስ፣ ምን ያደርግልሃል?"

"እንድንገናኝ ነዋ!"

"ተገናኝተንስ?"

"እንጨዋወታለን::"

"እና!?"

"የት ነው የምትማሪው?"

"ሽመልስ ሀብቴ አንደኛ ደረጃ::"

"ስንተኛ ክፍል ነሽ?"

"4ሲ!"

"አ ለትንሽ በለጥኩሽ:: እኔ 5ኤ ነኝ::"

ዘምዘም እየሳቀች "ሁለቱንም እንበልጣቸዋለን:: እኛኮ 6ኤ ነን!" አለችኝ::

አቀፍኳት:: ጡቶቿ ደረቴን ሲነኩት ልክ እንደ ቀጢሳው ድርርርር! አደረገኝ::

*ጭራሮ! ጭራሮ!፣ አጨብጭቡ እንደማለት ነው::

ምሕረት

"ሰው በዚህ ዓለም ላይ በሚኖርበት ዘመን ሁሉ
ለሕይወቱ እንጀራ፣ ውሃ፣ ልብስ ካገኘ ይበቃው ነበር።..."
ፍ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ

ከቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ጀርባ የሚገኘው ሰፈር ዲተልበር ይባላል። ጥቂት ሴተኛ አዳሪዎች ይኖሩበታል። በጣም ትንንሽ ልጆች እያለን መጫወቻ የሚሆነን ቆርኪ የምንለቅመው ከዚህ አካባቢ ነበር።

በዚሁ መንደር ከሚገኙት ቤቶች እንደኛው የጆቢራው ዳንስ ቤት ነው። ጆቢራው የአራተኛ ክፍለ ጦር ከባድ ሚዛን ክብደት አሸኒ ነው። ይህንን ዳንስ ቤቱን ከባለቤቱ ጋር በመተ ባበር ያካሂዳል።

መጎርመስ እንደጀመርን ማታ ማታ ታዳሚዎቹ ሲደንሱ ለማየትና ከጥበቡ ለመቅሰም እኔና ጓደኞቼ እንሄዳለን። ሁሌ ቀድመውን ደርሰው በር ላይ የምናገኛቸው ጓደኞቻችንን አወቀ ዱዱና ጉይቶም አሻሮን ነበር። ቀይ መብራት በርቷል። በጀምስ ብራውን ዘፈን ቆነጃጂቱ ከጎበዛዝቱ ጋር ጃርኩን፣ ቡጊውንና ፓንፑን ሲያስነኩት እንመለከታለን።

ፊዘን ስንመለከት የብርጭቆ እጣቢ በድንገት ይረጭ ብናል። ብትን እንላለን። ተመልሰን የምናፈጥ የመኖራችንን ያዘል በደረሰብን ድንገተኛ መበስበስ እየተሳደብን ወደ ሰፈራችን የምንሄድም ነበርን።

በዚህ ዳንስ ቤት ውስጥ የሚሠሩ ሴቶች ምሽት ባለሽንሽን ቀሚስ ወይም ፓሪሞዱን ለብሰው፣ ሰፊ ቀበቶ በወገባቸው ሸብ አድርገው፣ ተኳኩለው፣ ፀጉራቸውን 'አፖሎ ስታይል' ተሠርተው ይሽቀረቀራሉ።

ብዙ ጊዜ ወደ ዳንስ ቤቱ የሚመጡት ወንዶች የአራተኛ ክፍለ ጦር ወታደሮች ናቸው። ታዋቂ የሆኑ ስፖርተኞችም ይገ ኙባቸዋል። የዘመኑን 'ፋሽን' ለብሰው በቴንጥ እየነጠሩ ሲገቡ እና ያቸዋለን። ከቆነጃጂቱ ጋር ሲተላለፉ ጡታቸውን ጨበጥ፣ ዳሌ ያቸውን ቸብ! ማድረግ የተለመደ ነው። አንዳንዷ ሴት በሳቅ እየተፍለቀለቀች "ኡ! የቂጤን አደጋ ይስጥህ!" ብላ ትሽኮረመምና ቸብ ያደረጋት ጎረምሳ ጭን ላይ ተቀመጣለች። ድንገት ዞራ ካየ ችን "አትፈሯም እናንት ውሪዎች!?"

ቅድም አንድዋ የብርጭቆ እጣቢ ረጨችብን፣ አህን ሌላዋ ሰደበችን። እናቄማለን። በዘኋለኛው ሕይወቴ እንደተገዘብኩት

ሴቶቹ ማታ የሚያገኙት ገቢ ለመተዳደሪያ አይበቃቸውም። ስለ ዚህ ቀን በቡና ማበጠሪያ ድርጅት ውስጥ ቡና ለቀማ ይሠራሉ። ማታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የሚያልፉት በእኛ ሰፈር ነው። በዚህ ጊዜ በሰፈራችን የታወቁ ለካፊ ልጆች እንደተርብ ይቀበ ሏቸዋል። ሴቶቹ በቁጣ ቱግ ብለው የስድብ መአት ያወርዱ ብናል። ብትን እንላለን። ትተውን ወደ ሰፈራቸው ሲያዘግሙ "እፍ እፍ ኮሌጅ!" ይላል በቅጭን ድምፅ አበራ ጥይቴ። የኤሌ ክትሪሻን ረዳት ሆኖ ነው የሚሠራው። ማታ ወደ ቤቱ ከመግባቱ በፊት አንድ አራት አምስት ለወች ይለክፋል። ስለዚህ አበራ አጠገብ ካለ ማንኛውም ልጅ መጠንቀቅ ይኖርበታል።

አበራ ጥይቴ ሴቶቹን ለክር አበሳጭቶ ከሸኘ በኋላ፣ በለከ ፋው እየሳቀ ወደ ጎደቴ ጠጅ ቤት አሾለቀና ተመለከተ። አንድ ሽጉጥ ሰርቀው ከውትድርና የተባረሩ አዛውንት ሰው አየ። "ሽጉጡን ቁጭ አርግ!" ብሎ ጮኽ ፈትለከ አለ።

አዛውንቱ በረገጡና ከጠጅ ቤቱ ተወርውረው ወጡ። ሁላ ችንም ወደ አቅራቢያችን መሸሸጊያ ቱር አልን። አበራ ጥይቴ ቁልቁል እየሮጠ ሲስቅ ይሰማናል። ሰውየው አውላላ ሜዳ ላይ ቆመው ባለጌ ስድብና የርግማን መዓት ያወርዱብናል። እኛም የባለ እንስቃለን። ይህ ሆታ የተሞላበት ሳቅ አንጀታቸውን እርር ድብን ያደረጋቸው ሰውዬ ከኪሳቸው የፖሊስ ፊሽካ አወጡና በኃይል ነፉ።

አስቂኙን ትዕይንት በፍጥነት ተቀይሮ አስፈሪ ሆነ። እነ ባሻ ሐረሩ፣ ሃምሳ አለቃ ታደሰ፣ ምክትል አስር አለቃ አበበ ገሰግሰው ደረሱ። እኛ በየስርቻው ተወትፈን ሁኔታውን እንከታ ተላለን።

"ምን ተፈጠረ?!"

"በንጉሥ አገር ወሮ በላ አስቸገረኝ።"

"የታል?"

"ሳትይዘው! ፈለጉን ላታውቅ ነው የድረሱልኝ ፊሽካ ያሰማኸው?"

"አሸባሪው አንተ ነህ!"

አበራ ጥይቴ በዚህ ጊዜ በጨነቀው ሱቅ በኩል አድርጎ ሲያልፍ ያገኘውን እየለከፈ፣ ተለካፊው ሲያባርረው እየሮጠ በማ ርገኛ አድርጎ ወደ ሰፈር ይመለሳል። ወይም ወደ ዲተልበር ብቅ ብሎ ጆቢራው ዳንስ ቤት ደጅ ላይ ቆሞ የዳንሱን ጨዋታ ያያል።

እኛ በነጋታው የሰፈራችን ታዛቦ ንግሥ ላይ ለምንጨ ፍረው ዳንስ የመጨረሻ ዝግጅት ለማድረግ ወደ ጆቢራው ዳንስ ቤት ሄድን። ሴቶቹ አድፍጠው ጠብቀውን ነበርና፣ ፍቅረኛ ቻቸው የሆኑ ጦር ሠራዊቶች በክበባ ይዘውን በኩርኩም ቆጥን። አስፈራሩን፣ አስጠነቀቁንና ለቀቁን። በዚህ ድንገተኛ ወገራ ተበሳ ጭተን አበራ ጥይቴን ጠመድነው።

በበነጋታው ታቦቱ ነግሦ ቀሳውስቱ ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው መቋሚያቸውን ይዘው ጸናጽላቸውን እያቅጨለጨሉ ክበሮ እየመቱ ያሬዳዊ ዜማ ሲያዜሙ ምዕመናን በእልልታ ያደም ቁታል። ይኼ መንፈሳዊ ትዕይንት ልብን በሐሴት ይሞላል።

ጨዋታው እዚያም፣ እዚህም ተጀመረ። ከዘምዘም ጋር ዳንስ ልንጀምር ስንል ጉይቶ አሻሮ በጥቅሻ ጠራኝ።

"ምንድነው?"

"አወቀን አበበች 'አትደንስም፣ ክደነስክ ግን ለወንድሜ ለቸርነት ነግሬ አስወግርሃለሁ' ብላው እያለቀሰ ነው።"

ቦዲው ቸርነት በዓይኑ ቂጥ አላፊ አግዳሚውን እያየ ደረቱን የማንቀጥቀጥ ልማድ አለው። አወቀ ዱዱ ደግሞ ሲያቀ ብጠው ከዚህ ቦዲ ቢልደር አህት ጋር ጓደኝነት ጀምሯል። በተጣሱ ቁጥር ማስፈራሪያዋ ያው ቦዲ ወንድሟ ነው። አሁን ደግሞ የጥጋቧ ጥጋብ ከእሷ ፈቃድ ውጪ ከሆነ ጥምቀተ ባሕሩ ላይ እንዳይደንስ አገደችው።

ጉይቶም አሻሮ ይሀንን የሚነግረኝ የሰፈር ልጆች እንድና ግዝለት ነው። እኔ ግን አወቀን በዕዳ አፈልገዋለሁ። ባለፈው ሆያ ሆዬ ከመድረሱ በፊት ክረምቱ ላይ "ብይ አስቆጥረኝ ለሆያ ሆዬ እከፍልሃለሁ" አለኝና ተስማማሁ። የስሙኒ ብይ ተበድሮ ተጫውቶ ተበላ። ሆያሆዬ ጪፍሮ በደንብ ሸቀለ። ነገርግን የኔን ፍራንክ ላለመክፈል መንገድ እየቀየረ እየሸወደኝ በጣም ተቸግሬ ዛሬ አገኘሁት።

"ቸርነት ዓይኑን ቢያጠፋው እኔ የለሁብትም። ክርኬን ብቻ ይክፈለኝ! የታለ?" ብዬ ሳዘግም ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በሩ ላይ አየሁት።

"ስማ!" አለኝ አወቀ ዱዱ እንዳየኝ። ሲያወራ ምንጊዜም ጮክ ብሎ ነው። "ሲኒማ ኢትዮጵያ ያላየሁህ እንዳይመስልህ!"

ልቤ ድው፣ ድው አለ። ወደ ዘምዘም ዞርኩኝና በጥቅሻ ጠየኳት። የዚያን ዕለት "ያ ልጅ ዝም ብሎ እየተቁለጨለጨ የሚያይህ ለምንድነው?" ብላኝ ስታመላክተኝ ላየው ስንጠራራ የሲኒማ ቤቱ መብራት ጠፋ። የዚያን ዕለት አይቶኛል ማለት ነው። ምሥጢሬን እንዲደብቅ ጠጋ አልኩኝና "አይዞሽ አውሽክን፣ አግዝልሻለሁ። ስሙኒውንም ምሬሻለሁ" ለአፌ እንጂ እንኳን እኔ ቸርነትን እነ ግርማ ቸሩም አይችሉትም።

"ስማ የጎልቤው አህት አትደንሳትም። ሞቼ ነው ቆሜ አለ ችኝ።" ሲለኝ አወቀ ዱዱ አበበችን ጠጋ አልኳትና "ምንድነው?"

"ፋንጋይ በዓመት በዓል ምድር ከልጆች ጋር ትጣላለህ እንዴ!" ከኋላዬ ስጠራ ሰማሁ። የጠራኝ ጋሼ ጋንጨር ነው።

"እልተጣላሁም። ስሜ ተስፋዬ ነው!" አልኩ በዝግታ እየተ ጠጋሁት። እኔም ጋሼ ቀስቱን ጋንጨር ብዬ መተራት ጀምሬያለሁ።

"ተውንጂ ፋንጋይ? እኔኮ አንተን የማውቅህ ከሕፃንነትህ ጀምሮ ነው። በዚህ ላይ ዘመዳማቾች ነን። ለማንኛውም ፀቡ ውስጥ ከሌለህበት ጥሩ ነው። በል የገንዘብ አጠቃቀም እወቅ። ጓደኛ አታብዛ እንካ አረንቻታ በዳቦ ብላ" ብሎ ዲናሬ አወጣና ሊሰጠኝ እጁን ዘረጋ።

"ይኼ ፍራንክ እኮ የሚገዛው አረንቻታ ብቻ ነው።" አልኩ ሳልቀበለው።

ነቅቼበታለሁ። ድሮ በልጅነቴ ዱምቡሎ ከኪሱ ያወጣና 'ሻይ በዳቦ ብላ' ብሎ ይሰጠኛል። ወቅቱ ሐምሌና ነሐሴ ሊሆን ይችላል። ሁለቱም አምሮኝ እጨነቃለሁ። ረስቶት ይመስለኝ ነበር። ዛሬ ግን ነቃሁበት ተፈጥሮው ነው።

"ውይ አራት ፍራንክ ነው እንዴ? የሰጠሁህ ስሙኒ መስሎኝ" ብሎ ኪሱ ተጨማሪ ፍራንክ ፍለጋ ሲገባ "እኔ ፍራንክ ከማንም ላይ እንዳልቀበል አባቴ አስጠንቅቆኛል። አልቀበልም!" አልኩት።

ደም በጐረሱ ዓይኖቹ ገላመጠኝ፣ አልወደውም። ለጥላቻዬ በቂ ምክንያት አለኝ። አንድ ወንድሙ እንደሆነ የሚነገርለት የደረሰ ጉረምሳ አብሮት ይኖራል። ስሙ ገሠሠ ነው። እኛም በገጣጣነቱ ገሠሠ ጥርሶ እንለዋለን። ከንፈሩ አጥሮ ጥርሱ በዝቶ፣ እንዳለ ጥርሶቹ ደጅ ናቸው። በአንድ እርጉም ቀን ገሠሠ ጥርሶ ተጣልተው ጋሼ ጋንጨር ሲደበድበው የፊት ጥርሱ ረገፈ። በወቅቱ በቁማር ሃያራው ጦፎለት ስለነበር ወጣቱን አሳክሞ ጥርሱን ወርቅ በወርቅ አደረገለት። በልጅ ልብ የሰፈር ልጆች በወርቅ ጥርሱ ቀናንበት።

ጋሼ ጋንጨር ሰንበትበት እንዳለ ከጥርሶ ጋር ተጣሉ። ትልልቅ ስዎች ሲያወሩ እንደሰማሁት ጋንጨር ጥርሶን ጠልፎ ጥሎ ሌንጨቻጨን ሽቅብ ስቦ በጉጠት ያስተከለለትን ወርቅ ጥርስ ሁሉ ነቅሎ ወስዶ ሸጦበታል። ገሠሠ ጥርሶ ድድ ብቻ እያልን ስናበሽቀው ተናዶ አገር ጥሎ ጠፋ።

የዚያን ጊዜ በዘሀ በጋሼ ጋንጨር ድርጊት መኩዬ ቀጫጫው ተናዳ እንፈንክተው ብላኝ ነበር። ቆይ አሁን አይደለም ብዬ አረጋጋኋት።

ጋሼ ጋንጨር አልገባውም እንደድሮው ችስታ መስዬዋለሁ፣ ማንም ፍራንክ ቢሰጠኝ የምቀበል መስሎታል። ያ'ድሮ ቀረ ከጥምቀት መልካም ስሜት ጋር ፊቴን ወደ ጓደኞቼ ስመልስ ወደ ደስታዬ ተመለስኩ።

"አስጠናሻለሁ ብሎ ሳመኝ ይሄ ባለጌ! አስወግረዋለሁ!" አለቺን አበበች በለሆላስ እንደማፈር አያለች።

"ውይ! እንቺ?፣ እንዴት ባለጌ ነው? ቱ! አፈር ያስበላው! አስወግሪው።" አልኳትና ጉይቶም አሻሮን ጠጋ ብዬ ጠየኩት።

"አስጠናሻለሁ ብሎ እየሳማት ቆየ። እሷም ተስማማች። በድንገት መሳሳሙን አቁሞት ወደ ጥናት ማተኮሩ አስኮረፋት።"

ተሳሳቅን። ባስታርቃቸው እርቀ ሰላም ወርዶ ጨዋታው እንደሚደራ ገመትኩ። አወቀ ዱዱ ዘምዘምን፣ እኔ አበበችን ይዘን ወደ መድረኩ እንድንገባ አደረኩኝ። በቀይታ እንለዋወጥና ከራሳችን ጓደኞች ጋር እንሆናለን።

ጉይቶም አሻሮ ደስ ብሎት ፊቱ ሁሉ ጥርስ ሆኖ እያጨበጨበ ያስተውሰናል። የነሳዬ አርሞኒካ ታዘምራለች። የታዳሚው እጆች በማጨብጨብ ያደምቃሉ። እኛም በቅርቡ የተማርነውን ጃርከ እናስነካው ጀመር። ልሕይወታችን እንጀራን፣ ልብስን በወላጆቻችን ጥረት እያገኘን ሴቷ ከወንዱ፣ ወንዱም ከሴቷ የሚገኘውን ደስታ ለመገብየት እንዳሀ ነበር የጀመርነው።

ፍተሻ

"ሳገራ ለእኔ ምን ትሠራልኛለች ሣይሆን፣
እኔ ለሀገሬ ምን እሠራላታለሁ እንበል።"
ጆን ኢፍ ኬኔዲ

መምህራችን በሚተርኩልን ጭብጥ መንፈሳችን ተሰማሮ በሁሉም ነገር አንደኛ የመውጣት ስሜት አያሌዎቻችንን የተጠና ወተን በዚያው በጨቅላነት ዕድሚያችን ነበር። በግብርና፣ በማራቶን፣ በትምህርትም፣ በኪነጥበብም፣... በሁሉም መስክ እንደኛ መሆን።

ቲቸር መስፍን፣ ቲቸር ጥበበ ከዜሮ ከፍል ጀምሮ የገጠሙኝ መምህራኖች ነበሩ። ለማ በገበያን፣ ለማና ዘመዶቹን አስተማሩን። መጻሕፍቱ በሥዕል የተደገፉ፣ ብዙ ጽሑፍ የሌላቸው፣ ደስ የሚሉ ነበሩ።

ቱ ኤ በገባን ጊዜ ታረክና ምሳሌ፣ ተንኮለኛው ከበደ፣ ላሜ በራ፣ እና ሌሎች አያሌ መጻሕፍት ውስጥ ያገኙአቸውን ተረቶች ይተርኩልናል።

ቲቸር መጽሐፉን ገለጥ ሲያደርጉ በወረፌ ይተራመስ የነበረው ከፍላችን ቀስ በቀስ ፀጥ ይላል። አጠገቤ የተቀመጠው ሲሳይ ነቢጥ አፉንም፣ ዓይኑንም በሰፊው ከፍቶ መምህራችንን በተመስጦ ያስተውሏል። ከስቶኪንግ የተሠራ ትልቅ የጨርቅ ኳስ ከእግሩ ስር የማይጠፋው አበረ ሻቃ ከፍል ውስጥ ከገባንም በኋላ ከደስክ ስር ምትሮሽ እንጫወት ይል ነበረ። የዚያን ዕለት በትረካው ይመሰጥና ጨርቅ ኳሱን የት እንዳስቀመጠ ይረሳል።

ለእኔ ብቻ በሚሰማ ሰዋሰስ ድምፅ "መጽሐፍ ማንበብ ጥሩ ነገር ነው!"

"እምን!" እለዋለሁ ከሚመስጠው ከቲቸር ትረካ መንፈሳዊ ሂደት ላይ ሳልወርድ። "እኛ ቤት እንቅልፍ ለምኔ የሚባል መጽሐፍ አለን። እማዬ ሣጥን ውስጥ ቆልፋዋለች፣ ስናድግ ስለም ትሰጠኝ አብረን እናነበዋለን"

"እሺ" በሹክሹክታ እመልሳለሁ።

ከከበደ ሚካኤል ግጥሞች የብረት ድስትና የሸክላ ድስት፣ ሁለት አፍ ያለው ወፍ፣ አዝማሪና የውሃ ሙላት፣... ይነበብልናል። ሲያስቁን ሲፈልጉ 'የዝንጀሮ ሠርግ'ን ይተርኩልናል።

...ነይ ትንቡሽ ገላ፣ ነይ ትንቡሽ ገላ
ለኛ ልጅ ሚስት ሁኚ፣ ትዳር እንዲሞላ
አትፈጪ፣ አትጋግሪ፣ አይጠፋ የሚበላ
ቆርጦ ይሰጥሻል የሰንዴውን ዛላ
የማሩን መለሳ...

"ታዩታላችሁ ይኼንን ቀጣፊ? አያጭድ፣ አይነስጉል!" ሲሉ ቲቸር በሳቅ እናውካለን።

3ሲ እና 4ሲ ስንደርስ የእንግሊዘኛን ሥነ ጽሑፍ በስነ ቃል ያስተዋወቁን መምህራችን ቲቸር ጥበበ ናቸው። 'በረደር ዋን' ውስጥ የነበሩት ታረኮች 'አሲባባ ኤንድ ዘ ፎርቲ ቲቭ'፣ "አላዲን ኤንድ ዘ ላንፕ"፣ 'ዲክ ኤንድ ሂዝ ካት'... የመሳሰሉት ተረቶች እጅግ በጣም ተወዳጆች ነበሩ። በእነዚህ ትረካዎች በሕይወታችን ለመጀመሪያ ጊዜ በምናብ ከአገራችን ውጪ ባሕር ማዶ የሄድንባቸው የጥበብ ውጤቶች ናቸው።

'ALADDIN AND THE LAMP' በማለት ቲቸር ጥበበ ወፍራምና ጆሮ ገብ በሆነ ድምፅ አንብበው 'አላዲንና ፋኖሱ' በማለት ይተረጉሙልናል። ማንኮሻኮሹ- ጫጫታው ፀጥ ይላል። ቲቸርም ፊገግ ብለው 'Once there was a wizard, He lived in Africa, He went to China to get the lamp" በማለት ሲተረጉሙልን "እንድ በአፍሪካ ውስጥ የሚኖር ጠንቋይ ነበር። ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ፋኖሱን ለማግኘት ወደ ቻይና ተጓዘ።

The wizard knew that the lamp was hidden in a hole in a field. It was a very little hole. The wizard was a big man, He could not go into the hole... እያሉ ወደ ተረቱ ዓለም እያጓጉን ይዘውን ይጓዛሉ።

ቲቸር ጥበበ አልባቱ ላይ ደርሰው ከከፍላችን ይወጣሉ። ወዲያውኑ በኩርኩም እየተወዳደርን የእንግሊዘኛ ቃላት መጠየየቅ እንጀምራለን።

"ዊዛርድ!" ሲሳይ ነቢጥ ጠየቀኝ።

"በሦስት በሦስት ኩርኩም" አልኩት።

"እሺ!" ብሎ ሳይጨርስ "ጠንቋይ!" አልኩት።

አጎነበሰልኝ:: የበላሁ የጠጣሁትን ያህል ቆጋሁት::

"ትጣፍጣለች!" አለ አንድ ዓይኑ እንባ አቅሮ በሕመም በተንገበገበ ድምፅ::

ስላሳዘነኝ ሁለቱን ማርኩት::

'አሁን የምጠይቅህን አትመልስም?' አለኝ ጎቢጥ::

"ጠይቀኝ' አልኩት::"

"ላምጥ?"

"ኩራዝ" አልኩ በፍጥነት::

"ፋኖስ" ሲል አበረ ሻቃ አሮመኝ::

አጎነበስኩ:: ሊኮረኩመኝ እየቃጣ አውቆ ዘገየ:: ተሸማ ቅቄ ዓይኔን ጨፍኜ ጠበኩት:: ጎቢጥም ምራቁን ጣቱ ላይ ተፋና ቆጋኝ::ሁለተኛውን አሸማቀቅኝና ማረኝ::

እኔም "ልጠይቅህ ሪንግ?"

"ጂኒ"

"ቀለበት" ሲል መኩዬ ቀጫጫው ጭንቅላቱን እየፎከተ አረመው:: ሲሳይ ጎቢጥ ግን እኔ ነኝ ትክክል ሲል ተሟገተ:: በዚሁ መካከል ቲቸር አባቢያ ጥቁር መነፅራቸውን ሽቅብ ከፍ እያደረጉ ወደ ክፍል ገቡ:: ክፍተኛ ትርምስ ተፈጠረ:: መኩዬ ቀጫጫው ወደ ኋለኛው ቦታው ለመመለስ ስትወረወር፣ ኋላ የነበረው ሁሴን ጂቦ ወደ ፊት ሲወነጨፍ መካከል ላይ ባለመ ተያየታቸው ተጋጩ:: ስፖርተኛው ጂቦ ባለበት እንደ ብረት ቀጥ ብሎ ሲቆም መኩዬ ቀጫጫው ግን እንደ ጨርቅ ኪስ ቱር ብላ ቲቸር እግር ስር ጥቅልል አለች:: ቲቸርም ቁልቁል እያ ዩዋት ደረትዋ ላይ የጫማቸውን መዳፍ በእርጋታ አቆሙት::

በተወለጋገደ የእጅ ጽሑፍ 'My name is...' ብላ ጥቁር ሠሌዳው ላይ መጻፍ የጀመረችው ዘምዘም በጥድፊያ ማጥፋት ጀመረች:: እንደ ቲቸር ልተርክላችሁ እያለ የሚንተባተበው ዓለሙ ሰማይ ተገትሮ ቀረ::

ቲቸርም ያን ሲካሄድ የነበረውን ትርምስ በደንብ ዓይተ ውት ስለነበር በስም እየጠሩ አንበረከኳቸው:: የተቀረነው ለአክብሮት ተነስተን ስለነበር እንድንቀመጥ ፈቀዱ::

ቲቸር አባብያ ታላቅ መምህራችን ናቸው:: እስከ ስድስ ተኛ ክፍል ሲያስተምሩን የዓለማችንን ካርታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳዩንና ያስነበቡን ተወዳጅ መምህራችን ናቸው::

እንግሊዘኛን፣ ጎብረትን፣ ሂሣብን አስተምረውናል:: በር ካታ ልቦለድ መጻሕፍትን ያስተዋወቁን፣ የገሃዱንና የመጻሕፍትን ዓለም ትዕይንት የቀረፁብን ናቸው:: ካነበቡልን መጻሕፍት <u>"ፀሐይ መስፍን፣ አርሙኝ፣ አቴሎ፣ ተረት ተረት የመሠረት፣ ይእምባ ደብዳቤዎችና</u> ሌሎችም ነበሩ::

ከቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ሥራ <u>አርሙኝ</u> ከተባለው መድብል ውስጥ 'የዓይኔ አበባ፣ 'አልሞትኩም ብዬ አልዋ

ሸም' የተባሉትን በጣም እንወዳቸው ነበር:: በተለይ የ'አልሞ ትኩም ብዬ አልዋሽም' ዋና ገፀ ባሕርይ አቶ ተሚቹ የሀገር ፍቅርን ስሜት አሳድረውብናል::

አቶ ተሚቹ ልጆቻቸውን ክንዴንና ጋሻዬነህን አስከትለው ሲዘምቱ ይታዩናል:: ረሃባቸው፣ ጥማቸው፣ ፍልሚያቸው፣ የመ ጨረሻው አወዳደቃቸው መራርነት ያስለቅሰናል:: በገዛ ቤታቸው ደጅ ለማኝ ሆነው ሲመጡ ስናይ፣ በመጨረሻ ሕይወታቸውን በስቅላት ሲገላገሏት የክፍሉ ልጅ በሙሉ በእንባ እንታጠባለን::

በዚህ ወቅት ጉርምስና ቀስ በቀስ ነፍሳችን ውስጥ ማቆጥ ቆጥ ጀምራለች:: ልብሳችንን እንደልብ እየቀያየርን ፋሽን ባንከ ተልም በራሳችን ስልት ፋሽን እንፈጥር ነበር:: በዚያኑ ጊዜ እንድ ፊልም አይቼ ወደድኩት:: አክተሩ ጀርባው ላይ "Love and Peace!" የሚል ጽሑፍ ለጥፏል:: አክተሩ ስላማዊ ሆኖ መልዕክቷ ስለመሰጠችኝ እኔም አብነት ባሪያው ሰደሪያዬ ጃኬት ላይ እንዲጽፍልኝ አደረኩት:: ለተስፋዬ ገበሎም "Love is blind!" ብሎ ጻፈለት:: ትምህርት ቤት ማክሰኞ ዕለት ለብስነው ሄድን:: የተማ ሪዎቹን ቀልብ ሳብን:: መነጋገሪያ ሆንን:: ይህ ያልተለመደ ትኩ ረት የመሳብ ነገር ስላልጣመኝ ከሰዓት በኋላ ለምሣ ቤቴ ሔጄ ስመለስ ሰደርያዋን አውልቄያት ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩኝ:: ከሰዓት በኋላ ክፍላችን ውስጥ ትምህርት መሰጠቱ ቀረ:: ቲቸር ጥበበ እያነከሱ ወደ ክፍላችን ገቡ:: በጣም ተኩሳትረዋል:: "Love and Peace!" አሉ ቲቸር::

ዝም አልኩኝ:: ደንግጫለሁ::

"ተስፋዬ ዜራሞ"

"አቤት!"

"ና ውጣ!"

"Love is blind!"

የክፍል ጓደኞቻችን እየሳቁ ሞክሼዬ ላይ አፈጠጡበት::

"ተስፋዬ ሮባ!"

ደንግጦ ፀጥ አለ::

"አንት ገበሎ፣ ና! ውጣ!" አሉ ቲቸር ጥበበ::

ተስፋዬ ሮባ ክዚያን ዕለት ጀምሮ 'ገበሎ' የቅፅል ስሙ ሆነ::

ቲቸር አባብያ ወደ ቲቸር ጥበበ ተጠግተው በለሆሳስ እኔን ገሯቸው:: ተግባቡ:: መድረኩን ቲቸር አባብያ ተረከቡ:: በእንዲህ አይነት ወቅት ቀደም ብለው ቢሆን "አይ ዊል ጊቭ ዩ ዩር ኩዌንሲኩዌንስ!' ብለው ማስመሪያ ወይም ልምጭ ለማምጣት ክክፍል ይወጡ ነበር:: ዛሬ ግን ጉርምስናው እየተፈታተነን ልምጩንም፣ ማስመሪያውንም ችላ እያልነው እንደምን ገረፍ አስተውለዋል::

"ጥሩ ነው በእካል የገዘፍክ መሆን" አሉንና ቲቸር አባብያ ሲቀጥሉ "ጥሩ ነው ከሳምሶን የእጥፍ እጥፍ አድገህ መገኘት::

ይሁን እንጂ፣ የአካልን ግዝፈት በማንበብ፣ በመማር ገርተህ ሕሊናህን ከአእምሮህ ጋር አዋህደኸው ተሰዋኦና ዝንባሌህን አውቀህ መጓዝ ካልቻልክ ግን እጣህ የዳይኖሰር ይሆናል::

"ዳይኖሰር ከሚሊዮናት ዓመታት በፊት በዓለማችን ላይ የነበረ ግዙፍ እንስሳ ነበር:: የአካሉን ግዝፈት፣ ከሕሊናው ብስለት ጋር አዋህዶ መምራት ባለመቻሉ ከምድረ ገጽ ጠፋ:: እና ንቲም እንደሱ እንዳትጠፋ ማንነታችሁን ፈትሹ...!"

ቲቸር በኑሮአቸው ሃዘንተኛ ነበሩ:: አንድ ዓይና ናቸው:: እኝህን በጣም የምንወዳቸውንና የምናከብራቸውን አስተማሪያችንን ማነው ዓይናቸውን ያጠፋው? እንዲህ አይነቱን ነገር ለማጣራት የጊዜው ልማድ አይፈቅድልንም:: አስተዋይ ተማሪዎቻቸው፣ ጥያቄውን እያነሳን ከማብሰልሰል በስተቀር:: የቤትም ሆነ የክፍል ሥራ ሲያርሙልን አልኮል አልኮል ይሸቱን ነበር:: ሽታውን ለማጥፋት ማስቲካ ቢያኝኩም ሁሌ በመጎንጨታቸው ጠረኑን ለም ደነዋል:: እድም ያጥራቸው ስለነበረ ተጨማሪ ዝቢ ለማግኘት ከትምህርት ቤታችን ፊት ለፊት በሚገኝ ሀብታም ሰውዬ ቤት ልጆች ያስተምሩ ነበር::

ከብዙ ዓመታት በኋላ ጆን ኤፍ ኬኔዲ "አገሬ ለእኔ ምን ታደርግልኛለች? ሳይሆን፣ እኔ ለአገሬ ምን አደርግላታለሁ እንበል!" ያለውን ሳነብ "ልክ እንደ ቲቸር አባብያ!" ነበር ያልኩት::

ጥናት

"አንዱን ከሌላው አናበላልጥም"
ቅዱስ ቁርአን

ዘምዘም በቃልዋ መሰረት የሐዲስ ዓለማየሁን *ቲረት ቲረት የመሠረት*፣ የሻንበል አፈወርቅ ዮሐንስን *ቾግረኞች*፣ *ዛዲግ ወይም ዕድል* የተባሉ ትርጉም መጻሕፍት እና የብላቴን ጌታ ኅሩይን *ማህደረ ብርሃን ሀገረ ጀጋንን* አምጥታልኝ በትጋት ማንበብ ጀምሬያለሁ:: በሆድ ማንበብ ስለማልችልበት እየተለማመድኩ ነው:: ቲቸር መስፍን ናቸው ይህን ችግሬን አይተው ዘዴውን ያስተማሩኝ:: ይህንኑ ልምምዴን ቤታችን ውስጥ ሳካሂድ አባቴ፣ "ጋሼ! ለእኛም አንብብልን፣ እንስማህ?"

"በሆዴ ማንበብ እየተለማመድኩ ነው::"

አንድ ነውር ነገር እንደሰማ ግር ብሎት "እንዴ? ሆድ መቼ ሥራ ፈታና ማንበብ ይማራል? መጽሐፍ የታተመው የሚ

ያወቁት ለማያውቁ እንዲያነቡ ነው:: በሆድ ማንበብ ብሎ ነገር ከየት መጣ?" ሲለኝ፣ ከተለያየ አቅጣጫ ጎረቤቶቻችን ወደ እኛ ቤት መግባት ጀመሩ:: እማማ አመለወርቅ የዚያን ዕለት ያስፈፀቱን በርበሬና ሽሮ እማዬ እንድትቀምስላቸው በሳህንና በኩባያ ይዘው ወደ ቤት ገቡ:: "እትዬ እንኩ እስኪ::"

እማዬ ተተበለቻቸው::

"እንደምን ዋላችሁ?" እማማ ዱምቡሎ ናቸው::

"ዛሬር ይመስገን" መለሰ ቤተኛው::

የእኔና የአባቴ ጨዋታ እዚህ ላይ ቆመ::

"ዱምቡልዬ፣ መጣሽ?" አባቴ እማማ ዱምቡሎን በማየቱ ተደሰቷል::

"መጣሁልህ አንት ጋንድያ ዶርዜ፣ መቼም እንዳላጥከብኝ እትቀር!"

"ምን ላርግ? ወድጄ አይደለም:: አንቺን ሳይሽ አንድ ሐሙስ ብቻ የቀረሽ ትመስይኛለሽ::"

"ተው እባክህን! እግሬ ሰላሳ ይሞታል ሲባል እግሬ ደንዳና ይሞታል::"

"ተረቱንማ ታውቂበታለሽ::"

"ሽማ ተበድሬህ ለለባሹ ሸጬ ለአንድ ልጂ ቆሎ መሸመቻ እንዳነኝ ብሯሯጥ አንተ በቅጥነቴ ታሚርትብኛለህ?"

"ምን ላርግ? ተበድረሽ ወስደሽ ሳትከፍይ ሙትት ብትይ የማን ያለህ እላለሁ?"

"አንተ አጋሰስ ዶርዜ አትተወኝም?" ሲሉ እማማ ዱምቡሎ እኔ ተናደድኩኝ:: እሳቸው ፊት እንዳልናገር ትልቅ ለው ስለ ምፈራ ነው እንጂ ዶርዜ ብለው ደጋግመው መሳደባቸው አበሳጭቶኛል::

"በል እንካ ገንዘብህን:: ሌላ ሽማ ስጠኝና ሽጬ አንድ ልጂን አጉርሼ ልደር:: አሁን ኮምፕሌት ቀማስና ነጠላ ስጠኝ" አሉና በመጀመሪያ የወሰዱትን ጋቢ ሂሳብ ስድስት ብር ቆጥረው ሰጡት::

እየተቀበለ "እሺ እሰጥሻለሁ:: ግን መኪና መንገድ ስትሻገሪ ዝም ብለሽ ደፋ ደፋ አትበይ፣ ግራና ቀኝ እይ" እያላቸው አባቴ ከተቀመጠበት ሳጥን ውስጥ ካሉት አንዱን ኮምፕሌት ልብስ አውጥቶ ሰጣቸው::

እማማ ዱምቡሎ ቸኩለው ስለነበር የሰጣቸውን በፍጥነት ተቀብለው አገላብጠው እይተው ዋጋ ተስማምተው ከቤታችን ወጥተው ሄዱ::

እማማ ዱምቡሎ ቀጭን ረጅም ናቸው:: ዘሩ የሚባል አንድ ልጅ አሳቸው:: መሳርመስ ስንጀምር ልጃቸው ዘሩ በውትድርና ዘምቶ እንደወጣ ቀረ:: በልጃቸው ሐዘንም፣ በኑሮም ጫና ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ታመው መሞታቸው ተሰማ:: አባቴ

አዘኑ። ተከዝ ብሎ አብሰለሰለና "ነብሷን ይማረው፤ ምንም ዕዳ የለባትም።"

"ለምን ዶርዜ ሲሉህ ዝም ትላቸዋለህ?" አልኩት ቆጣ ብዬ። እማማ ዱምቡሎ የዚያን ዕለት ከቤታችን ወጣ እንዳሉ አባቴም ከትከት ብሎ ሰቆ "ምን አለበት ዶርዜ ቢሉኝ? አለ፤ ከጋሞ ዘሮች ዶርዜ አንዱ እንጂ ስድብ እኮ አይደለም። እኒህ እትዬ አመለወርቅ የሸዋ አማራ ናቸው። አንቺ አማራ ብላቸው ሰደብሏቸው ማለት ነው?"

እማማ አመለወርቅም እማዬም ሳቁ።

"ተመልከት አንድ ፊደል ሳንቆጥር የምንሠራውን ጥበብ፤ የምንሸምነውን ሸማ። ይህ ችሎታ በብዛት ለእኛ ዘር ተመርጦ የተሰጠ እውቀት ነው። ጃንሆይ ድፍን የአፍሪካ መሪዎችን አዲስ አበባ ሲጋብዙ የእኛን ሸማ መልበስ አማራቸው። ድፍን የጋሞን ልጅ ሰብስበው 'የእኔን መልክ በጥበብ አንሱልኝ፤ የአፍሪካ ካርታንም ጨምሩበት' አሉ። እኛም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሚል ጽሑፍ ጨምረን በጥበብ ለቀምንላቸው። ማነው የሠራው ቢባል፤ እኛ ዶርዜዎች ነን።

"ድፍን ኢትዮጵያ ሁሉም እንደየቸሎታው በመሥራት እንግዶቹን ደስ አሰኘን። አገራችንን በድፍን ዓለም አስጠራን። መቼም የመሪዎቹ ሚስቶች ጉትቻም ቀለበትም ሃብልም መፈለጋቸው አይቀርም። ያንን የሠራው ማነው? ከትግሬ አገር የመጡ የአክሱም ልጆች..." አለና ቀና ሲል ባሻ ሐረሩን በመሰከት ሲያልፉ አያቸው። "እነሱም!" አለ በከንፈሩ ወደ ባሻ ሐረሩ እየጠቆመኝ። ኃይለኛ ስለሆኑ አፍ አውጥቶ አይናገር እንጂ እንደ ሚፈራቸው አውቃለሁ። "እነሱም ወታደሮቹ ፀጥታውን ያስከብራሉ። አምባጓሮ የሚፈጥረውን አያንቆራጠጡ ልክ እያዝቡትና ሰላም ያሰፍናሉ። አገር የቆመው በሁሉም ዘር ድጋፍና የጋራ ጥረት ነው። ንጉሡ ትዕዛዝ መስጠት ብቻ ነው ሥራቸው። አድርገናል! ፈቅደናል! ይላሉ ጃንሆይ።"

"በቀደም ጠጅ ቤት በግጥም የሰደበህ ሰውዬስ?" አልኩት እየተቆጨሁ።

"እ! 'አሁን ኦሮ ነው ወይ የሸማኔ ኦሮ?
ግማሽ አካላቱ በጉርጓድ ተቀብሮ?' ያለኝን? ታዲያ አንዱ ልባም አንነል ያለው ሰውዬ የመለሱትን ለካ አልነገርኩህም።

'ሸማኔማ ሸማኔማ ሸማኔ ባይኖር
ይህ ጋንድያ ቁጥህን ማን ያለብሰው ነበር?'

አለ። ጠጪው ሁሉ በዚያኛው ሳቀበት። እኔም ስሙኒ አውጥቼ ሁለት ብርሌ ጠጅ ጋበዝኩት። እንዲህ አይነት አውደ ልዳይ ሥራ ፈቶችን ስትሰማ ጆሮህን አትክፈትላቸው።"

"እውነት እኮ ነው! ሸማኔ ባይኖር የአዳምም ሆነ የሔዋን ዘር እርቃኑን በኖረ ነበር!" አሉ እማማ አመለወርቅ ተገርመው።

"አገራችን ከሁሉም ብልጫ ያለው ወታደር ነው ትላለች እንጂ ጃንሆይ ማክበር የነበረባቸው ሸማኔን፣ አስተማሪንና ገበሬን ነበር። ሸማኔ አገር ያለብሳል፣ አስተማሪ ያስተምራል፣ ገበሬ ባይኖር ግን ምን እንበላ ነበር? ይህ አፈኛ ሁሉ ጉዱ ይፈላ ነበር! ፈረንጅም ፋብሪካ ሠርቶ ካኪውን፣ ሱፉን ምናምኑን መሸመን የጀመረው ከእኛ ከሸማኔዎቹ በጋኔን ስቦ በወሰደው ብልሃት ነው።"

"እንዴት ጋኔንን?" ጠየኩኝ።

"አዬ ጋሽዬ፣ የጋኔንን፣ የጋንጨርን፣ የጂኒን ጥበብ ለመ ረዳት አይቻልም። ይህንን የሚያውቁት አላ ዘለቀ ናቸው" ሲል ቤተኛው በሳቅ አውካካ።

አባቴ ነሸጥ አድርጎታል። በአደገበት ባህል መሠረት ሮክ ብሎ ያወጋን ጀመር። በባህሉ ድምፅን ዝቅ አድርጉ ማውራት ከመዋሸት ጋር ሰለሚያያዝ ምን ጊዜም የጋሞ ማኅበረሰብ አባል ሲያወራ ሮክ ብሎ ነው። አሁንም አባቴ አርቡን ስብስብ አድርጉ ያመነበትን እውነት ያጫውተኝ ጀመር። «ይሔ የሚሆነው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ነው። በአሁኑ ጊዜ በሥልጣኔ በድፍን ዓለም የታወቁት እንግሊዝና አሜሪካን የሚባሉ አገሮች አይደሉ? አሜሪካ የሰው ልጅን ለመጀመሪያ ጊዜ በእየር ጨረቃ ላይ ልካለች። ከነምልከቱ ከጨረቃ ላይ ያመ ጡትን ድንጋይ ለጃንሆይ አሳይተዋል። አሜሪካኖቹና እንግሊዞቹ እዚህ ብልህት ላይ ለመድረስ በየአገሩ እየዞሩ የተለዩ ጥበቦችን ይማራሉ። ቱሪስት ይባላሉ እነዚህ ፈረንጆች።

«ቱሪስት» አልኩ በሆዴ።

«እነዚህ ቱሪስኮች እኛ አገር መጥተው አክሱምና ላሊበላን ሲመ ለከቱ የሕንፃዎቹ አሠራሮች፣ ጥበባችን ሲያዩ ልክ ጠጅ እንደጠጣ ሁሉ አስክራቸው። ከዚያም በምስጢር እሺ ያለውን በውድ፣ እጅ መንሻ እየሰጡ ዳጉሰ ያለ ቀለብ እየቀረጡ ባዘር ማዶ አሻገሩት። እምቢ ያለውን ደሞ ባስከተሉት ፈንጋይ ጠልፈው ጥለው በጉማሬ እየለበለቡ በአንገቱም ሠንሰለት አስገብተው አጋዙት። በዚህም መዘዝ እኛ አዋ ቂዎቻችንን አጥተን ጉጆ ቤት ውሰጥ ቀረን። እነሱ በሕንፃ ላይ ሕንፃ ገነቡ።»

«ጋንጨር ነው ይኼን የሚያደርገው?» አልኩ።

«ጋሼ አትሞኝ አንጂ ጋንጨር ሲሉህ ቀንዱሙ ሰይጣን ነው የሚታይህ? ፀሐይ የመሰለ ነጭ ይሆናል። ብሩን በቦርሳው አሞቀ ነው የሚመጣው። ለሆዱ ያደረ ጥቁር ሁሉ ይከተለዋል። በዚህም በድፍን ዓለም የፈለጓቸውን ሰዎች ሰብስበው ወደ አገራቸው በመውሰድ በሕንፃ ላይ ሕንፃ ይገነባሉ።»

«ለአንተ ማን ነገረህ?» ተገርሜ ጠየቅኩት።

«አንድ አዋቂ ቁም ነገረኛ እንድ ቀን ጠጅ እየጠጣን ስናወጋ አጫውቶኛል» ሲል አባቴ ቤቱ ሙሰጥ ሳቁ ከስሞ ቁጭት ተቀላጠለ።

«አባባ ጃንሆይ ዝም አሉ?» አልኩ እንደተቆጨሁ።

«እናቴ ጃንሆይ ሺ ጦር ነው የሚቀልቡት። የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ አለ። በዚያ ላይ ጡረተኛው። ለዚህ ሁሉ ቁና ሙሉ ብር አሜሪካኖቹ ሲቆጥሩላቸው ጭጭ ምጭሎ ይላሉ እንጂ ትንፍሽም አይሉ። ምንስ አፍ አላቸው? ልጄ ንኑሥ መሆን ፍርጃ ነው። ዕዳ ነው» አለ አባቴ በዘዴት።

የቁጭት ድባብ ቤቱን ቸላው።

«ወይ ጉድ ለካ እንዲህ ነው?» ይባባሉ ጀመር።

«ስውዬው ክሌጅ የተማረ ነው?» ጠየኩት። እንዲሁ አይነት ምስጢር የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብዙ ያውቃሉ።

«ዘደንብ ሣይንስና ሕይወት በቅሙ ያጠናቀቀ። አራቱን መደብ ሂሳብ አሳምሮ የሚችል ነው። የሚያሳዝነው ጓደኞቹ ተመቅኝተውት በሚሰሳበት ውስጥ ምናምን ብን አደረጉበት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እህል አስጠላው መጠጣት ወደደ። አሁን ጋደም በሚልበት እንኪን ብርሌ ጨብጠ ነው»

እማማ አመለወርቅና እማዬ «አፈር ልሁን! አፈር ልሁን!» እያሉ ደረታቸውን ደቁ።

እኔም ቆዘምኩ።

ሳይንቲስቱ ጎቢጥ ኒውክሌር ቦንቡን የመሥራቱን ጉዳይ እውን ለማድረግ ቆርጠ ተነስቶአል። ይህን ሃሳብ በውስጡ ስር እንዲሰድ ያደረገው መጀመሪያ ግርማ ቢጨ ነው። ዘመቀጠል አባቴ ናቸው። የክብር ዘበኛ መሣሪያ ግምጃ ቤት በለደረባ ስለሆኑ፣ ግምጃ ቤት ውስጥ ያሉትን መሣሪያዎች ስንቀ ሊያደርስላቸው ሲሔድ ጉበኝቷቸዋል። በዚያ አጋጣሚ ሲጨዋወቱ ጣሊያን የወረረን እነዚህ መሣሪያዎች ስላልነበሩን ነው። ስለኒውክሌር ቦንቡ አንስቶባቸው «እናንተ ትምህር ታችሁን ስትጨርሱ ትደርሱብታላችሁ» ብለውታል። እሱ ግን ጥናትና ምርምሩን ከወዲሁ ጀምሯል። መንገድ ላይ ያገኘውን ቆርቆሮ ብረታ ብረት ወይም ሽቦ እያመጣ እኛ ጓሮ ያጠራቅማል። አንዳንዴ ችስታ ሆኖ ሲኒማ መግቢያ ሲያጣና ቆርቆሮ ያለው እኛ ስፈር ሲመጣ ጉቢጥን አየዋለሁ። ሃሳቤ ከዕይታዬ ጉብቶት «በምንም ተአምር አልሸጠ ውም» ይለኛል።

ትምህርቱን በአግባቡ ያጠናል። እኔም አማካሪው ስለሆንኩኝ አብሬው በትጋት ማጥናት ጀምሬአለሁ። በሕይወቱም ለመጀመሪያ ጊዜ በክፍል ውስጥ ቱስት አስር ከአስር አግኝቼ ተጨብጭቦልኛል። ስለኒውክሌር ቦምብ ምስጢር ባቅሙ ለመረዳት ሌላው አጋራችን ያደረ ግነው ግርማ ቢጨን ነው። ሁሌም የቤት ሥራችንን ሠርተን እንዳጠ ናቀቅን ጨለማው ዓይን ያዝ ሲያደርግ 'ገደል ግቡ' ጠጅ ቤት እየሔ ድን ግርማን እንቀበለዋለን። ግርማም ልዩ ልዩ ደስ የሚሉ ጨዋታዎች እያጫወተን ወደ ስፈር እንመለሳለን።

ግርማን ተቀብለን ወደ ስፈር ስንመለስ «ወንድሞቼ ጉንዳንና ስካራም መንገዱን በምንም ተአምር መሳት የለበትም። ስካራምም ወደ

ቤቱ ሲሔድ ምን ያህል ጉድጓዶች እንደሚያጋጥሙት፣ ምን መሰናክል እንደሚገጥመው ካሳወቀ መሰበር ይመጣል። አሁን ግን እናንተ ከኔ ጋር ስለሆናችሁ መሬት መሬቱን ማየቱን ትቼ ከዋክብቱን ላድንቃቸው እስቲ።» አለና ቆም ብሉ ሲጋራውን ለኮስ ሆጨጭ ብለው በሰማዩ ላይ የወጡ ከዋክብት ላይ አፈጠጠ። ጥቂት ከጠበቅነው በኋላ ወደምንፈ ልገው ወግ መራነው።

ስለ ኒውክሌር ቦምብ አፈጣጠር አንስተንበት፣ «ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ስትሆኑ ሁሉም ነገር ቀለሉ ይታያችኋል። ሁሉንም ትምህርት በእንግሊዘኛ ስለምትማሩ የኬሚስትሪና ፊዚክስ ዕውቀታችሁ ጉልብቶ በሒሳብ ትምህርት ረቀቅ ስትሉ ምስጢሩ ላይ ልትደርስበት ትችላላችሁ። አሁን ግን የሣይንስ 'ኖሌጃችሁን ዴቨሎፕ' ለማድረግ የሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስን የሬዲዮ ፕሮግራም ተከታተሉ። አሪፍ 'ኖሌጅ' ስለ ሣይንስና ሕይወት ይስጡአችኋል» ሲል በየጊዜው የቤት ሥራችንን ያበሩዋል። እኛም ሳንታክት ጥረታችንን እንቀጥላለን።

ይህ ፍተሻችን በዚያ የጨቅላነት ጊዜ አንዱን የዓለም ምስጢር ጫፍ ያዝን ስንል እየተጉረጉረ ወደሌላው ምስጢር ይዞን ጅው እያለ ሁሉም ነገር ይወሳሰብብን ነበር። ዛሬም አባቴ የነገረኝን ታላቅ ምስጢር ግርማን ጠይቄ ለመረዳት ወስኛለሁ። ይኼን ሃሳብ ሳውጠነጥን አባቴ የወጉን ማሳረጊያ አከለበት።

«የሚገርመው» አለ አባቴ፣ ከቁዘማችን ነቃ ብለን ማድመጥ ጀመርን። «አሁን አሜሪካንና እንግሊዝ አገር የሚኖሩት ከየአሩ ተግዘው ባሪያ የሆኑት ወገኖቻችን ብቻ ሳይሆን ከሌላው ዓለም የተሰባሰቡት የራሳቸውን ቋንቋ ረስተውት የሚነጋገሩት በፈረንጅ አፍ ነው አሉ። የሚገርመው ግን የኛዎቹ አበሾች ግን ዕቁብ መጠጣቱንና ዕድር መሳሱን አሁንም አልረሱትም» ሲለን በሳቅ አውካካን።

«የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ' እንደሚባለው መሆኑ ነዋ። እውነ ታቸውን ነው» አሉ እማማ አመለወርቅ።

ከትንሽ ወጥታ በኋላ፣ "ለሁላችንም አንብብልን እስኪ?" አለኝ አባቴ።

የሚሉኝን እየሰማሁ ትምህርት ቤት ከህብረት ትምህርት መጽሐፌ ላይ ስዬ ያመጣሁትን የኢትዮጵያን ካርታ ከደብተሬ ውስጥ አወጣሁ። ግርግዳ ላይ ከመለጠፌ በፊት ለአባቴ "ይኸ ውልህ የኢትዮጵያ ካርታ።"

ተቀበለኝና ተመለከተው። በአድናቆት ፊዞ አየና "ስማ ቸውን ጽፈህበታል የጠቅላይ ግዛቶቹን?"

"አዎን!"

"ይኼ ማነው?"

"ከፋ ጂማ።"

"ይኼስ?"

"ኢሊባቡር ጎሬ።"

"ይህችስ?"

"አሩሲ አሰላ።"

እየተደነቀ ፍክክ ብሎ "ይኼስ?"

"በጌምድር ጎንደር::"
እንደገና በጣቱ ጠቆመኝ::
"ኤርትራ አሥመራ::"
"ጋሞጎፋ የታለ?"
"ይኼ አረንጓዴው ነዋ:: የህብረት ትምህርት መምህራችን ቲቸር አባብያ ላይ ምን ይላል መሰለህ? በአሁኑ ጊዜ በደን ከተ ሸፈኑት የአገራችን ጠቅላይ ግዛቶች መካከል አንደኛው ጋሞጎፋ ነው:: ለዚህ ነው አረንጓዴ የቀባሁት::"
በጣም አዘንና "አየህ፣ ስላላስተማሩን ማይሞች ስለሆንን ነው በደን የተከበብነው:: ያ ደን ለስንት ታላላቅ ጥበቦች በሆነ ነበር:: ያሳዝናል:: ብቻ በርትተህ ተማር፣ ሄደን ልማት የምን ጀምረው እኔና አንተ ነን!"
"እሺ::"
የኢትዮጵያን ካርታ በፍቅር አያትና "ነሽ! እዘህ ፊት ለፊቴ ስቀለው:: እንዲት ደስ ይላል! ሁልቀን እየጠየኩህ እኔም አጠናዋለሁ:: አሁን ገና እውነት አስተማሩህ!"
ይህ ካርታ በቤተሰቡ ዘንድ በጣም ተውዳጅ ሆነ:: ከአባቴ ጋር በሌላ ቀን ተጣላንና ላናድደው ከግርግዳው ላይ ካርታውን አነሳሁት:: አባቴም ተገነንቶ ከውጪ ሲመጣ ካርታውን ከግርግዳ ላይ አጣውና ቤቱ ውስጥ ከፍተኛ ፀብ ተነሳ:: በብዙ ድርድር ከደበቅኩበት አምጥቼ እንበረበት መለስኩና እርቀ ሰላም ወረደ::
የዚያን ዕለት በትምህርት ላይ የተባባልነው አሁንም ትውስ ይለኛል::
"እረ ሁልቀንም እውነት ነው እሚያስተምሩን::"
"አንተ እመናቸው እንጂ እኔ ግን አላምናቸውም::"
"ለምን? ምን ውሸት አገኘህበት?"
"አንድ ጊዜ ስንጨዋወት መሬት ድብልብል ነች አላል ከኝም? ሌላ ጊዜ ደሞ የዓለም ሦስቱ እጅ ውሃ ነው፣ አንዱ እጅ ደግሞ በመሬት የተሸፈነ ነው አላልከኝም?"
"ብዬሃለሁ:: እውነት እኮ ነው!"
"እኔ ግን አላምናቸውም:: የሚያስተምሩህ የሚፈትኑህ እነርሱ ስለሆኑ አስተማሪዎችን እመናቸው:: በሆድህ ግን ብትጠረጥራቸው ጥሩ ነው::"
"ለምን?"
"ምን ለምን ትላለህ? መሬት ድብልብል ከሆነች እኔ እንደ ምገምተው ስንሄድ ተንጋደን መሆን ነበረበት:: እኔ ወዳንተ ስመጣ ዳገት ሲሆንብኝ ሲገባ፣ አንተ ወደእኔ ስትመጣ ቁልቁለት መሆን አለበት:: እንደምታየው ሁሉም ነገር ጠፍጣፋ ነው:: በርግጥ አንተ ብዙ ቦታ ሄደህ አታውቅም፣ ነገር ግን ሄደህ ብታየው ብዙ ቦታ ጠፍጣፋ ነው:: ለምላሌ መርካቶ ሄደሃል:: መርካቶ ጠፍጣፋ አይደለም?"

"ነው::"
"እኔ ደግሞ ከዚህ እስከ ጋሞጎፋ ተጉዣለሁ:: እኛ አገር አካባቢ ትንሽ ዳገታማ ይሆናል:: ታዲያ ከየት አምጥተው ነው? እነዚህ አስተማሪዎች ዓለም ክብ ነች እሚሉት::"
እኔም ተጠራጠርኩ:: አስተማሪዎቼን መጠርጠሩን ግን ኩነኔ እንደመግባት ቆጠርኩት:: "የውሃውስ?" አልኩት::
"እርሱም ውሸት እንደሆነ በመሐላ ላረጋግጥልህ እችላለሁ:: ድፍን አዲስ አበባን በደንብ አውቀዋለሁ:: ከአባ ኮራን ሰፈር እስከ ደጃች ውቤ፣ ከእንጦጦ ተራራ እስከ ገፈርሳ፣ እረ በከንቱ ብትል፣ ዶሮ ማነቂያ ብትል፣ በጠቅላላው ልጅ ሆኜ የቦረቅኩብት ነው:: አንድም ባሕር የለም:: ጋሞጎፋ ድረስ ስንገዝ ከሰማይ የገጠመ ባሕር አላየሁም:: ታዲያ ከየት መጥቶ ነው ዓለም ሦስት እጁ ውሃ እሚሆነው::"
"ወደ ኤርትራ እኮ ቀይ ባሕር አለ" አልኩት:: እኔም እየተ ጠራጠርኩ ካርታው ላይ ጠቆምኩት::
"በርግጥ ባሕሩ አለ:: ካርታው ላይ አየዋለሁ:: እሱኮ ከዚህ ብትዘል ማዶ የምትሻገረው መሬት ይሆናል" አለ፣ ከኢትዮጵያ ድንበር ሳይዳ አረብያ በዝላይ መሻገር እንደሚችል ሲያስረዳኝ::
ስለቀይ ባህር መምህሮቼ የነገሩን ምንም ነገር ስለሌለ፣ ከማዶም ያለውን አገር ስለማላውቀው፣ ያባቴን ጥርጣሬና እምነት ወደመቀበሉ አደላሁ::
"ግን! ግን!" አለ ትንሽ በተመስጦ ሲተክዝ ቆይቶ "እኔ እን ድንጨዋወት እንጂ የምነግርህ ሁሉ የመሰለኝን ነው:: አስተማሪዎችህ ግን የመረመሩትን ከመጽሐፍ ያጠኑትን ነው:: አንተ እምትጓዘው በአንርሱ ጎዳና ስለሆነ የእኔን አስተሳሰብ ተወው:: ግን አስተውለው አዙረህ ለማየትም ሞክር:: ከዚያማ ፍርዱን ላንተ እተዋለሁ:: በቆይታ ምራቅህን ስትውጥ ከሁለት አንዳችን ላይ ትበይናለህ:: የእኔን ዋና ጭንቀት ልንገርህ:: እኔ አሁን ገን ዘብ አጠራቅሜአለሁ:: አንዳንድ ሰዎች ሲመክሩኝ እዚህ ጎፋ ሰፈር መሬት አንድ ካሬ ሜትሩን ሃምሳ ሣንቲም ገዝቼ ቤት እንድሠራ ይፈልጋሉ:: እኔ ግን ምኔ ሞኝ ነው? ጎፋ ሠፈር መሬት ገዝቼ ከጅብ ጋር የምጋፋው! አንተ ብቻ ተምረህ እወቅልኝ:: አገራችን ጋሞጎፋ ሄደን አብረን እናለማለን::"
መሬት ፀሐይን እንደምትሠርና ቀንና ሌሊትም የሚፈጠረው በዚህ ፍርርቆሽ እንደሆነ ሳወራላቸው መጀመሪያ ተገረሙ:: ከዚያም ሁሉም የኮረኮሩአቸውን ያህል ሳቁብኝ::
ቴማ "እንደምን አደራችሁ?" እያለ ወደቤት ገባ::
ቴማ መጽሐፍ እንጠልጥዬ ባየኝ ቁጥር አንብብልኝ ከማሉኝ ደንበኞቼ አንዱ ነው:: ዛሬም እንዳነብለት እንደ ሚጠይቀኝ ገምቼአለሁ:: ሞት ሁሉንም እኩል ያደርጋል' በሚል ርዕስ የተጻፈው የከበደ ሚካኤል ግጥም በጣም ይመስጠዋል:: ግጥሞቹን

ከታሪክና ምሳሌ ውስጥ ደጋግሜ በማንበቤ ብቃሌ እምወጣበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። ለደንቡ ያክል መጽሐፍዋን መግለጤ ግን የማይቀር ነው።

ዛሬ ግን ሌላ ትኩረቱን የሳበ ጉዳይ ስለገጠመው "እረ ጋሼ፣ ዛሬ ጉድ አይቼ መጣሁ" አለ ቱማ።

"ምን ተፈጠረ?" አባቴ ተገርሞ መሸመኑን ገታ አድርጎ ጠየቀ።

"ተማሪዎቼ ጉድ አፍልተዋል! መሬት ለአራሹ! እያሉ እየ ጨፈሩ ሲወጡ ፊጥኖ ደራሽ ፖሊስ ደረሰና ምድራቱን ቁና አደ ረጋት። እኔም እግሬ አውጪኝ ብዬ እየሮጥኩ እዚህ ደረስኩ።"

"መረበሽ ጀመሩ?" አሉ እማማ አመለወርቅ።

"አንድ የሚያውቁት እውነት አለ ማለት ነው። እውነታቸ ውን ነው መሬት ያራሹ መሆን አለበት" አለ አባቴ።

ጨዋታቸው ርስት፣ ጉልት፣ አፅመርስት፣ ጭሰኛ፣ ባላባት ነቀሉን እያሉ በማይገቡኝ ቃላት ማውጋት ጀመሩ። አትክልት ተተክሎ ሲነቀል አይቻለሁ። ሰው ግን እንዴት ከተተከለበት ይነ ቀላል? ብዬ አሰብኩ። "ዜራሞ፣ ሰው እናንተ አገር ይተከላል እንዴ?"

ሁሉም በሳቅ ፈነዱ። ነገሩ የበለጠ ጠጠረብኝ። "ምን እሚያስቅ ነገር አለ?" ጠየቅኩኝ።

አባቴም ሳቁን እንደጨረሰ "የኔ ውረ፣ እንዲህ አይነት ጉዳይ ላንተ ወገግ ብሎ የሚታይህ ስታድግ ነው። ምናአልባትም ልባም ክሆንክ አስራሁለት ክፍልን ስትጨርስ። ለማንኛውም አት ጨነቅ። ይህ ለጊዜው ያንተ ጉዳይ አይደለም። አንተ ብቻ በር ትተህ ትምህርትህን ተማር። ትምህርት ብርሃን ነው። የማታ ውቀውን ነገር ለማወቅ ከፈለክ ሁሌም መጻሕፍት ማንበብ እንዳለ ብዙ በቀደም ዕለት ቲቸር ጥበበ ነገሩኝ ብለኸኝ አልነበር? እኔም ዓለምን ሁሉ እንድታውቅ መጽሐፍ እየገዛሁ እመጣልሃለሁ። ታነ ብልኛለህ። ሁሉም ነገር መጻሕፍት ውስጥ አለ።"

"የፉንጋዬ ድምፅ ግን ትንሽ አልቀጠነም?" አለ ቱማ።

"ምንም አይደለም፣ ሲያድግ ይወፍራል። ማታ ደግሞ ርግብ ጠጅ ቤት ይገዘ ሄጀ አሳምነው ገብረወልድ እንዴት እንደሚያነብ በቴሌቪዥን አሳይሃለሁ። ጎበዝ ጋዜጠኛ ነው። በዓለም እሚወዳደረው የለም። አንድ ጊዜ ግርማዊ ጃንሆይ ልደታቸውን ሲያከብሩ ሲጠይቃቸው 'ግርማዊ ጃንሆይ፣ እርሶ የነገሥታት ዘር የለብዎትም እንዴት ንጉሠ ነገሥት ሊሆኑ ቻሉ?' አላቸው።"

"አሄሄ! 'አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች' ማለት ይኼኔ ነው" አሉ እማማ አመለወርቅ።

"የተማረ በድፍረት ሳይሆን በጥበብ ነው መርታት ያለበት" አለች እማዬ።

"አይ ወንድሜን! ተቀጭ ሲለው ነው" አለ ቱማ።

"ከዚያ ወዲህ ንጉሡ ጠሉት። ገሰጡት። የወደፊቱን አምላክ ያሳምርለት።"

"ቆይ! ቆይ! ሌላም ያላቸው አለ፤ ላጫውትህ። መቼም የአሳምነው ድምጥ ማማር! 'ግርማዊ ሆይ፣ እዘውትረው እሚ መገቡት ምንድነው?' ቢላቸው አጅሬ ብልጥ አይደሉ 'ጥራጥሬ እንወዳለን' አሉታ!"

"ወዴት? ወዴት? ጮማና ጠጁን ማን ከልክሏቸው?" አለ ቱማ እየሳቀ "ጥራጥሬውን ለእኛ ይተውልን።"

"ፉንጋዬ፣ በል ብርር ብለህ እነረታሽን ቡና ጥራልኝ" አለ ችኝ እማዬ።

እንደ ወፍ ቱር አልኩ።

ከሰሞኑ ለሰፈር ልጆች ባሕርዬ ተለውጠባቸዋል። ለምን እግሬን ሰብሰብ እንዳደረኩ ምሥጢሩ ስላልተገለፀላቸው እማዬ ልካኝ ቡና ልጠራ ስወጣ *"ገርጋጅ! ገርጋጅ!" ብለው ለከፉኝ።

ፀጥ ብያቸው አልፌ፣ ቡናውን ጎረቤት ጠርቼ ተመለ ስኩኝ። አሁንም ደገሙኝ። 'እጀወርቅ' ጓደኞቼን መርካቶ ውስጥ የሚያሸቅሉት አብነት ባሪያውና ደረጀ ናቸው። መርካቶ ውስጥ አንዱ ሻይ ቤት ቁጭ ብለው እየበሉና እየጠጡ መጽሐፍ ሆነ መጽ ሔት እያነበቡ ይጠብቁአቸዋል። 'እጀወርቆቹ' ከአንድ *ገርጋጅ ጋር ገበያው ውስጥ ይሰማራሉ። አንድ ሱቅ ውስጥ ሰዎች ሲገበያዩ ዘው ብለው ይገባሉ። 'እጀ ወርቁ' የአንዱን ተገበያይ ኪስ ሲፈትሽ ገርጋጁ ከኋላ ማንም አልፎ ሂያጅ እንዳያየው ይከልለውና ከፊት ባለሱቁን ልዩ ልዩ ዕቃ በመጠየቅ በመከራከር ትኩረቱን እሱ ላይ እንዲያደርግ ያደርጋል። የሚሰረቀው ሰው በዚህ መካከል ካልባነነ፣ 'እጀ ወርቁ'ና ገርጋጁ ተግባራቸውን ለማከናወን የደቂቃዎች ጊዜ ይበቃቸዋል።

ሰሞኑን እኔም ዘነጥ ብዬ የፀባይ ለውጥ የማሳየቴ ምሥ ጢር ግር ስላላቸው ገርጋጅ ሆነህ ነው የዘነጥክብን እንጂ ምን እግኝተህ ነው የተወጣጠርክብን?' ማለታቸው እንደሆን ገብቶ ኛል። ምንም ሳልል ወደ ቤት ተመለስኩኝ።

ጉረቤቶቻችንን ቡና ጠርቼ ስመለስ ሁለት በሸማ ሥራ ለመ ቀጠር የመጡ ሸማኔዎች ከእባቴ ጋር ያወጋሉ። ለጥቂት ደቂቃ በጋሞኛ ቋንቋ ሲያነጋግራቸው ቆየና "አንተ ስምህ ማነው?" ሲል አባቴ ጠየቀ።

"ሚላሁን ዝሞሣ"

"ምን?" አባቴ ደነገጠ።

ሰውዬው በእርግጠኝነት ስሙ ጥላሁን ገሠሠ መሆኑን ተናገረ። አባቴ እሱን ችላ ብሎ ሁለተኛውን "እሺ አንተስ?" አለው።

*ገርጋጅ፣ ዕጩ ሌባ።

ሁለተኛው ሰውዬ "መስፍን ስለሺ::"

"እንዴ? ባለሙቴ፣ ከድፍን አዲስ አበባ ነዋሪ ከጋሞጎፋ ቀድመን መጥተን ስማችንን ያልቀየርን እኔና አንቺ ብቻ ልንሆን እኮ ነው" አሰ በማላገጥ "አዳሜ ንፋስ ስልክን ሲሻገር ስሙን ጥላሁን ገሠሠ ካሰው፣ አንጫ ይመጣና መስፍን ስለሺ ነኝ ካለ፣ እኔም ስሜን ከዛሬ ጀምሮ አቀይራለሁ" አሰ በማሾፍ:: ወደ እንግዶቹ ዞረና "ጋሞጎፋ ውስጥ ዜራሞ እሚባል ሰው አለ:: ሰምን? አገሩ ነው:: አንተ ግን፣ ገሠሠ እሚባል የአገሩ ተወላጅ ሰው አለ?"

"አዎን አለ::"

"ገሠሠ እሚባል ጋሞ ነው? ወይስ ዘሩ አማራ ነው?"

"ጋሞ ነው"!

"ከጋሞዎች በዘርህ አመሬ ነህ?"

"አይደለሁም"

"ይኸውልህ፣ ከጋሞ ምናልባት ዘርህ አመሬ ቢሆን ጲላሁን ገሠሠነትህን አቀበል ነበር:: ጋሞው ዘር ውስጥ ግን በዚህ ስያሜ የሚጠራ ሰው እንደሌለ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ:: ወይስ ክርስትና ያነሱህና ያሳደጉህ ከመሐል አገር የሔዱ አማሮች ናቸው?"

"አይደሉም::"

"ታዲያ አንተ ከጋሞ ተነስተህ ገፈርሳን ስትሻገር ነዋ ጲላሁን ገሠሠ የሆንከው:: በእርግጥ ከሺ ዓመት በፊት ክርስትናን ይዘው ወደአገራችን የገቡት አማራዎች ናቸው:: እነዚያ ዘሮች አሁን አመሬ በመባል ይታወቃሉ:: አመሬ ሰእኛ ለጋሞዎች የአምላክ መልእክተኞች ናቸው:: ታቦቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ይዘው ወደአገራችን መጥተው የአምላክንም ቃል የሰበኩን አመሬ ዎች ናቸው:: ስለሆነም አመሬን አሁን ስንጠራ 'ካዎ' ነው የምን ላቸው፤ ይኸውም ንጉሥ ማለት ነው:: በሕዝባችን በጣም የተከ በሩ በጣም የተወደዱ ናቸው:: ተጋብተናል ተዋልደናል:: እናም ወንድሜ አንተ ዘርህ አመሬ ነው?"

"አይደለም:: ጋዎማላ ነኝ::"

"ጋዎማላማ ከሆንክ ወንድሜ ነህ:: እኛ ዘር ውስጥ ጲላሁን ገሠሠ የሚባል ሰው የለም:: አንዱ ከእኛ ዘር ስሙ ጎጆ ነው:: በባህላችን መሠረት ልጅ በተወለደ ቁጥር ከእናቱ ወይም ከአባቱ ስም ስያሜ አንድ ፊደል መውሰድ አለባቸው:: ቢያስብ ቢያስብ በጎ የሚገጥም ስም አጣ:: የወሬ ወሬ ሲሰማ ጎንደሬ የሚል ስም አንዳለ ሰማ:: የልጁን ስም ጎንደሬ አለው:: ሴት ልጅም ወለደ:: የሴት ልጁም ስያሜ ከስሙ አንዲገጥም ቢያስብ ቢያውጠነጥን በጎ የሚጀምር በጎ የሚጨርስ አጣ:: በቆይታ ሲያጣራ ጎጃሜ የሚባል ስም እንዳለ ደረሰበት:: የሴት ልጁንም ስም ጎጃሜ አላት::

ጎጃም ድረስ መሄድ አላስፈለገውም፣ ጎጃምን ጋሞጎፋ ድረስ አመጣው አንጂ:: እንተ ግን ገፈርሳን ስትሻገር ጲላሁን ገሠሠ ሆነህ ጋሞጎፋ ልትመለስ ነው:: ስምህን ካላስተካከልክ ሥራ የለኝም::"

«እውነት ጋሼ የኔ ቲኪሊኛ ሰም ጲላሁን ገሠሠ ነው:: ገብርኤል አይለመኔኝ!::»

"እሪ ተው? በእኛ ዘር ጲላሁን ገሠሠ የሚባል ስም የለም:: እንዲህ አይነት ስም የሚኖራቸው ባላባት ሆነው በንጉሡ የተሾሙ ወይም መጫዎች እንጂ ተወላጆቹ እናንተ ነን እምትሉት አይነት አሰያየም የለንም:: ለምሳሌ እኔን ውሰድ፤ ዜራሞ ኢንቻ ነው ስሜ:: አያቴን ብትጠራ ጋልጎ ነው:: ቅድመ አያቴ ኡማ ነው:: እያልን እያልን ብንሄድ አንድም እናንተ በተሰየማችሁበት የሚጠራ በዘሬ የለም:: ስማንኛውም እኔም ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ስሜን ቀይሬአለሁ:: ማንም ተነስቶ ዜራሞ ቢሰኝ አቤት አል ልም:: ዕዳ አለብኝ እንዴ? እኔ ከሰው ቀድሜ አዲስ አበባ ገብቼ ስምንድነው ዘላለም ዜራሞ ኢንቻ እምባለው?"

"ማን እንበልህ የኛ ጋንድያ?" አሉ እማማ ረታሽ ቡና ሊጠጡ ወደ ቤት እየገቡ::

ቱር ብዬ ጓዳ ገባሁና ጆሮዬን አቆምኩ::

"ልዑል አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን እባላለሁ::"

"እሪግ! እሪግ! ይኼ ዶርዜ እንዴት ጠግቧል! በንጉሡ ስም ታላግጣለህ?"

"አዳሜ ታዲያ ትናንትና አዲስ አበባ መጥቶ በታዋቂ አዝማሪ ስም ጲላሁን ገሠሠ ሲባል፤ ከዚህ ቤተ መንግሥት ድረስ ሳይሮጥ ስሙ አበበ ቢቂላ ሲሆን፤ የትም ሳይዘምት መስፍን ስለሺ ሲሆን፤ እኔ ታዲያ ዕዳ አለብኝ፣ ዘላለም ዜራሞ ኢንቻ እየ ተባልኩ የምጠራው?"

"አሁን ቆረጥክ፣ ተፈሪ መኮንን እንበልህ?"

"ልዑል አልጋ ወራሽ የሚሰውን ማዕረጌን ለማን አስቀር ተሽ?"

"እንካ ቡና ዜራሞ!" ስትለው እማዬ ፀጥ አላት:: "እንተ ዜራሞ፣ ተቀበለኝ እንጂ፣ ተቃጠልኩ!" ምንም አይነት መልስ አልሰጣትም:: "እሪ የፉንጋዬ አባት!"

ዝም!

"ውይ በሞትኩት እረስቼው፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን፣ ቡና ይቀበሉኛ!"

"እሺ ልዕልት!"

ኩረጃ

ተማሪ ነኝ ያልገባኝ
የምታውቁ አስረዱኝ...
ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ::
ግጥም የሃምሳ አለቃ ገዛኸኝ ደስታ::
ዜማ አቡዘከር አሸኔ::

በወላጆቼ መሀል ከውጪ በሚመጣ አለመግባባት በከፍተኛ ሁኔታ አለመጣጣም ተፈጠረ:: ጎረቤታችን የሃምሳ አለቃ ተንኮሉ ከአባቴ ጋር ተጣሉ:: ቤተሰቦቼና መንደርተኛው የምናልፍ የምና ገድመው በሃምሳ አለቃ ተንኮሉ ደጅ ላይ ነው:: መሬቱ የሃምሳ አለቃ ተንኮሉ ነው:: መንገዷ አህያና ጅብ የተገናኙባት ጠባብ ሰርጥ ነች::

ሃምሳ አለቃ ተንኮሉ አባቴን "አንት ምናምንቴ በመሬቴ ላይ አታልፍም!" አሉና ስድስት ጥይት ጎራሽ ሽጉጣቸውን መዘዙ::

ሃምሳ አለቃ ተንኮሉ ጡረታ ወጥተው ስለነበር ጀንበር ወጥታ እስከምትጠልቅ የሚውሉት ሰፈር ውስጥ ነበር:: በዚህ ሰፊ ጊዜያቸው አባቴን ሊከታተሉት፣ ሲወጣ ሲገባ ሊቆጣጠሩት ቻሉ:: ለአባቴ ከቤት ወጥቶ ዋናው መንገድ መድረስ ራሱን የቻለ ጭንቀት ይፈጥር ጀመር:: አባቴ የሃምሳ አለቃን መሬት ሳይረግጥ ለማለፍ የሚያደርገው ጥረት አስቂኝ ትዕይንት ነበር:: ከውጪ ወደቤት ለመግባት በአባባ ይመር ውሃ ልክ ላይ በጥ ንቃቄ መሬቱን ሳይረግጥ ይራመድና እማማ ማሚቴ ደጅ ይደ ርሳል:: ከዚያ በቀጭን ገመድ ላይ ሚዛኑን ጠብቆ እንደሚረ ማመድ የሰርከስ ተጨዋች ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ በዝግታ ግርግዳውን እየታከከ እነአለምነህ በረንዳ ላይ አርፎ፣ በነበላቸው እናት ቤት ላሉን አጭርጦ በጓዳ ይወጣና አጥር ሾልኮ የከርሰትና አባቴ መሬት ላይ ይደርሳል:: ከዚህ ሁሉ ጣር በኋላ ወደቤት ይገባል:: ቢለካ 50 ሜትር የማይሞላ አጭር መንገድ የረጅም ደቂቃዎች ጉዞ ነበር:: እኔ ቢያንገዳግደው የሃምሳ አለቃ ተንኮሉን መሬት እንዳይረግጥ ልደግፈው አብሬው በዝግታ አዘግማለሁ::

ሃምሳ አለቃ ለሽንት ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ቤታቸው ከገቡ አባቴ በልጅ እግሩ ፈትለክ ይልና የተከለከለውን መንገድ በመሮጥ ያቋርጣል:: ሃምሳ አለቃ ደጅ አለመኖራቸውን የሰለባ ተግባር የማ ከናውነው እኔ ነኝ:: ድንገት ከነቁ ከቱት ያልታወጀበትን ጦርነት በመ ንደሩ ውስጥ ያስነሳሉ::

ሃምሳ አለቃ ተንኮሉ እኔንና እናቴን በመንገዱ እንዳን ጠቀም አላገዱንም:: በዚህ ቸርነታቸው ብደሰትም እሳቸው ግን ጭንቀቴን ባለማየት ወይም እስከመፈጠሬ ረሰተውኝ ትኩረታ

ቸው ሙሉ በሙሉ አባቴ ላይ ነው:: ሳት ቢለው በስድስት ጎራሽ ኮልታቸው ሊቆነድዱት ዓይናቸውን ሳያረግቡ አፍጠው ይከተ ሉታል:: ይህ ፍርሃትና ጭንቀት እኔን ብቻ ሳይሆን እናቴንም ያስጨንቃል:: እንደ አማራጭ በጓሮ በኩል በክርስትና አባቴ መሬት ጠርዝ ላይ እየተራመደ በባሻ ሐረሩ ደጅ ያልፍና የአባባ አጋርን አጥር ቀዶ በማለፍ ዋናው መንገድ ይደርሳል::

ይህም ዘላቂ መፍትሔ አልሰጠም:: መንደርተኛውም ፍርሃ ታችን ተጋብቶበት ስለነበረ፣ ሽምግልናም ቢሞክሩ አልሳካ ብሎአ ቸው ቤተሰቤ ሰፈሩን ለቆ ቢሄድ ማለፊያ መሆኑን መከሩ::

እኛም ከመሞት መሰንበት ብሰን ቤት ለቀቅን:: ጎረ ቤቶቻችን እያገዙን እኔና እናቴ የቤተሰቡን አነሰተኛ ቅራቅንቦ አግዘን አዲሱ ሰፈራችን ኩራዝ ሰፈር ገባን::

ከድሮ ሰፈሬ ብዙም የራቀ አይደለም:: ከአዲሱ ሰፈር ልጆች ጋር ወዲያውኑ ወዳጅነት መሠረትኩኝ:: መሸሻና ወርቁ ሽርክ አደረጉኝ:: የመሸሻ ታናሽ ሂሩት እናቷ እማማ አፀነት ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ስለሚሠሩ በብላሽ አዳሪ ትምህርት ቤት አለገብተዋታል:: ቅዳሜና እሁድ ለእረፍት ስለምትመጣ በእንግሊዘኛ ቃላት ችሎታችን እንወዳደራለን:: አወዳዳሪያችን በወቅቱ ዘጠነኛ ክፍል የነበረው ወርቁ ነበር:: ሁሌም እንዳ ትበልጠኝ የእንግሊዘኛ ቃላት በማጥናት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ::

የሃምሳ አለቃ ተንኮሉን እገዳ ቤት ቀይረን ከተገላገልን በኋላ የለሳም ሕይወት መኖር ጀመርን:: ያኔ ለእኔ በልጅነት መንፈስ ሕይወት ሙሉ ሆና ትሰማኝ እንጂ፣ ቤተሰቦቼ ግን ከውጪ በመጣ ሌላ ነገር ሰላማቸው የደፈረሰ ነበር:: አባቴ ከጋንጩር ጋር ተጣላ:: ሁለቱ በጣም ተማረሩ:: ሰውዬው አደገኛ ቂመኛ ስለሆነ አድፍጦ ይጠብቀዋል:: አባቴ ደግሞ በጊዜ በመግባት ደህንነቱን ይጠብ ቃል:: እናቴ ሰላም ለማውረድ ጋንጩርን ትለማመጣለች:: ይህ የሰላም ጥረቷ ስላልገባው አባቴ እናቴን ጠላት::

ይህ ጭንቀትዋ እኔም ላይ ተጋባ:: ውጪ በትምህርቴም ሆነ ከጓደኞቼ ጋር ባለኝ ስላም ደስ ብሎኝ ብመጣም፣ እቤት የሚጠብቀኝ ፍቅር አልባ ኑሮ ነብሴን ሰቅዞ ያዛት:: ሕይወት ምንጊዜም ማርም ሬትም መሆንዋ ይታየኝ የጀመረው በዚያው የጨቅላነት ዕድሜዬ ነበር... ችግሩን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገል በማሰብ አዲስ አበባን ትተን ወደ ጋሞጐፋ ጠቅላይ ግዛት እንድንሔድ አባቴን ጠየቅኩት:: «አልሔድም:: አንደኛ አንተ ትምህርትህን አልጨረስክም፣ ሁለተኛ እኔ ዜራም ነኝ ጋንጩርን ፈርቼ አገር የምለቀለት?» አሰና በኃይለ ቃል መልሶልኝ ሃላቤን ውድቅ አደረገው::

ዛሬም ተዘናግቶ አምሽቷል::

ጋንጬር አባቴን የአገራችሁ ልጅ ነኝ ይበል እንጂ ውሸቱን እንደሆን አጣርቻለሁ። አንዴ በሰላሙ ወቅት ከአባቴ ጋር ጠጅ ቤት ቁጭ ብለን ቴሌቪዥን እንመለከታለን። ፊንጠር ብሎ ጋንጬር አንድ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት ከመጡ አዛውንት'ጋ ያወጋል። ደን ጠበቅ እያደረገ ሲያወራ እንዳለ ወሎዬ ሆነ። ዘርም አካባቢም ሲቆጣጠሩ የአዛውንቱ እናት አገር ሰው ሆነና ቁጭ አለ።

ገርሞኝ የዚያን ዕለት ወደ ቤት ሰንሔድ አባቴን ስጠይቀው "እሱ እቴ፣ ጉራጌ ካገኘ ቸራጌ ነው። ጉጃሜም ካገኘ ጉጃሜ... ምንም የማይሆነው ዘር የለም። ድፍን ኢትዮጵያን ከጃንሆይ በላይ ያውቃል። ሰይጣን በዕድሜው እንጂ በብልሃት አይበል ጠውም" ብሎኛል።

አባቴ በሃሳቤ መጣ። «አሌ ጋሼ» አለኝ በጋም ቋንቋ፣ ሲያላግጥብኝ። ኖር ጋሼ አያለኝ ነው።

«ታና ወዳኔ?!» አልኩት። 'ልትገለኝ ነው እንዴ?' ማለቴ ነው። በጋሞዎች ባህል ሽማግሌ የእግዚአብሔር ኃይል አለው ተብሎ ይታመናል። ሽማግሌ የተናገረው ቃል እንደ ቅዱስ ቃል በማነብረበቡ ይከበራል። ከዚህ ባህል ያፈነገጠ ከማነብረበቡ አባልነት ይገለላል። በዚህም መገለል ቢታመም የሚጠይቀው፣ ልጁን ቢድር የሚያደምቅለት፣ ቢሞት የሚቀብረው አይኖርም።... በዚህ ጠንካራ ጎብረት ሽማግሌዎች ታላቅ ኃይል ስላላቸው የገደለን ይቅር ለእግዜር የማሰኘት ሥልጣን በባህሉ ተሰጥቷቸዋል። ሰለዚህ ከምድር ከሰማይ የከበዱ አዛውንት ወጣትን ኖር ካሉት ቁጣን ያወርዳል ተብሎ ይታመናል።

አባቴ ይህን ባህሉን በቅጡ እያወቅኩት በመሔዴ ደስታው ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ ሔዷል። መቀራረባችን ጥልቅና ጥብቅ ሆኖ፣ «አንተ ልጅ ነህ» ማለቴን ትቶኝ የሆድ የሆዳችንን የምንጫ ወትበት ደረጃ ላይ እየደረስን ነው። ተዝናንቶ ሞቅ ብሎት ሲመጣ «እኔና ተሰፋዬ ትንሽ ነው የምንበላለጠው እኩዮች ነን» ይለኛል።

አባቴ አልገባውም። እኔ የመሐል አገር ተወላጅ ነኝ። ለእኔ አንድን ባህል ማወቅና መቀበል የተለያዩ ናቸው። እኔ በዘር የርሱ ደም ቅጂ ልሁን እንጂ በአመለካከት ከተፈጠርኩበት ጎብረተሰብ አኳያ የደፈረኝ ሁሉ ተገቢውን ቅጣት ልሰጠው እንደሚገባ አምና ለሁ። 'የሰው ሆዱን የወፍ ወንዱን እንዲሉ' የተመለከትኳቸው አያሌ ፊልሞችም ያስተማሩኝ ይህንኑ ስለሆነ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው" የሚለውን የቸር ልቦናን ሰበካ በአንዱ ጆሮዬ ሰምቼ በሌላው አፍስሼዋለሁ።

ከፀቡ በኋላ አባቴን በምን እንደተጣሉ ጠይቄው ሲያጫውተኝ "አክመልን አታውቀውም? አዎን! መኪና ሰፈው። አንድ ዓይና ነው። በታጎሣሥ ግርግር ጊዜ የቦንብ ፍንጣሪ ዓይኑን ያፈሰሰው። ጃንሆይ ይህንን ዓይተው አሳከሙት። አርተፈሻል ዓይን አስተከሉለት። አሱም አይረባም ሱስ ቢጤ አለችበት። ሲቸግረው በአስራ

አምስት ብር ይህንን አርተፈሻል ዓይኑን ለጋንጬር ያሲይዛል። ሲወልድ ሲወልድ 100 ብር ደረሰ። እክመል ከየት ያምጣ? 100 ብር ኖሮት አይደለም፣ ሞልቶለት ባንክ ቤት ሄዶ 100 ብር አይቶ አያውቅም። አክመል ጋሼ! አለኝና ጠጅ እየጋበዘ አዋየኝ። በጣም ስላዘንኩ ጋባዡ እኔ ሆኜ በእማላጅ የሰጠኝን 50 ብር ይዤ ጋንጬር ቤት ሔድኩ። ዓይኔ ጉድ አየ። ሰካ አንተዋወቅም።» አለና ተከዘ። እንዲህ አይነት ጉዳይ እንደሚያሰጨንቀው አውቃለሁ። የእክመል አርተፈሻል ዓይን እጁ እስከምትገባ ድረስ አባቴ በመንፈስ ዕረፍት አልባ እንደሚሆን አገምታለሁ። ሁሌም ከተበደሉና ከተገፉ ሰዎች ጋር መቆም ተፈጥሮው ነው።

«አንድ አራጣ አበዳሪ ሲያደርግ እማውቀው ሰው ሲቸግረው ወርቅም፣ ጨርቅም ሲያሲይዝ ነው። በእክመል አርቲፈሻል ዓይን ጉድ ስል። ለካ አርተፈሻል እጅና እግር ሁሉ ይይዛል። ባለ ዕቃው ምን እማራጭ አለው ያንን አካሉን የመለደውን ያህል ወልዶ ዕዳው ቢከመርበትም ይቅለጥ ብሎ አይቀራትም። ተበድሮም ተለቅቶም ይከፍላታል። ይኼንን ጋንጬር አሳምሮ ያውቃል። የአክመል አርቲ ፊሻል ዓይንም ውሃ በተሞላ ብርጭቆ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብላ እየጓት። የአገር ቅራቅንቦ ቤቱን ጠም አድርጐታል። ኮንትሮባንድ ጦር መሣሪያም እንደሚነግድ መንግሥት ያውቃል። ሰለዚህ የእሱ ጠላ ትነት እያሰፈራኝም። በዚህ ተናድጄ ሽምግልናው ቀረና ኃይለ ቃል ተናገርኩት። ሰይጣን በዕድሜ እንጂ በብልሃት አይበልጠውም ያልኩት የዚያን ዕለት ነው። ይህ የማይረባ ጋንጬር!!" አለ አባቴ በጣም አምርሮ።

የምሬት ሳቅ እየሳቀ "የሚገርመው ጋንጬርን በፀሎት ማንም አይበልጠውም። ለምሳሌ ሌሊት ቤተክርስቲያን ብትሔድ ዳቆናቱ ደርሰው ደጀሰላሙን ከመክፈታቸው በፊት እሱ ዛፉ ስር ቆሞ ያነበንባል። ቀሳውስቱን እንዳየ ብቅ ብሎ እባ አሳልሙኝ ሲል ብታይ ከቄሱ ጋር አብረህ ትደነግጥ ነበር።" ትንሽ ሲተክዝ ቆየና «በእገራችን እምላክን ሰንማፀን፣ ሴይጣንም እንዳይደርስብን የምንሰጠው ምሰ አለን። ከእሁሉ እንበትንለታለን፣ ከማሩ እንረጭለታለን። ሰለዚህ የዚያን ዕለት ጋንጬርንም እንደዚያው መናገር አልነበረብኝም። ልክ እንደ ሰይጣን ምሱን ሰጥቼው መሰናበት ነበረብኝ። ይህንን የአገራችንን ደንብ መጣሴ ጋንጬር በርኩስ ጥበቡ ቤተሰቤን ፍርሰርሱን አውጥቶት ነበር» ሲል ዜራሞ ወቅቱ ትውሰ አለኝና የሚመር ምራቅ አፌን ሞላው።

ከሃሳቤ ተመለስኩ። እንደገና ደሰ በሚለኝ ሃሳብ ላይ ተሳፈርኩ።

...ከዘምዘም ሁሴን ጋር ያለኝ ግንኙነት እንደቀልድ ተጀምሮ፣ ቀስ በቀስ የምር ጥልቅ ፍቅር ውስጥ ስላስገባኝ፣ ከሰሞኑ በግቶም ለዘምዘም የፍቅር ደብዳቤ ጽፌላታለሁ። በደብተር ሱስ በሠራሁት ፖስታ ውስጥ ደብዳቤውን ጨመርኩት። ፖስታው ላይ በቀስት የተበሳ ልብ ሥዬበታለሁ። ደብዳቤውን ራሴው አድራሽ ሆኜ፣ በተዋሰኩት የጎብረት ትምህርት ደብተሯ ውስጥ በሽፋኑና በመለበጃው መካከል አኖርኩት። እንደተሰመደው ክፍል ስንገናኝ

ደብተሩን ስሰጣት ዝግ ባለ ድምፅ "ዕቃ አለበት!" አልኳት። ምን እንደሆነ ጠርጥራለች። በጥንቃቄ ተቀበለችኝ። ልክ ሰዓት ቆጥሮ የሚፈነዳ ቦምብ ውስጡ የተጠመደበት ይመስል ዝግ ብዬ ነው ያቀበልኳት። ይህንን ማድረጌ ታላቅ የመንፈስ እረፍትን ሰጥቶኛል። የአረፋ በዓል ነገ ይከበራል። እሁድ ሲኒማ አብረን ልንገባ ወስነናል። ከሲኒማው በላይ ምላሽዋን በበነጋታው ለመስማት እየናፈቅሁ ነው።

ጀንበር ጠለቀች። ኩራዝ ለኮስኩ። እናቴም ብዙ ሳትቆይ ገበያው ቀንቷት መጣች። የሚበስለውን ጎመንም ሆነ ድንች ሸማ ምታ መጥታለች። ታናሽ እህቴን ከጀርባዋ አውርዳ ሰጥታኝ ጉድ ጉድ ትል ጀመር።

"አባትህ አልመጣም?"

"ይመጣል" አልኳት፣ ይህ ሰዓት በመጣ ቁጥር አንቆ የሚ ይዘኝ ፍርሃት እየተጠናወተኝ ነው። ኮሽ ባለ ቁጥር አባቴ የመጣ እየመሰለኝ ወደ በሩ እንጉቴን አሰግጋለሁ። ትንሽ እህቴ እማዬ ለመቆያ የሰጠችኝን አምባሻ ካልሰጠሽኝ ብላ አለቀሰች። ቆርሼ ሰጠኋት፣ ተቀብላኝ መግመጥ ጀመረች።

ፀጥታው በመንደሩ ነግሦአል። ከርቀት የውሾች ጩኸት ይሰማል። እማዬ የጎመን ወጡን ማያቤት ሠርታ ገባች። ቡናዋን ለማፍላት ሲኒዋን ማቀራረብ ጀመረች። መፀለይ አሰኘኝ። እህቴ እንቅልፍ እያንጎላጀት ስለነበር አቅፌ አንስቼ ወላጆቼ አልጋ ላይ አስተኛኋት። መጽሐፍ ቅዱሴን አነሳሁና ወደ ኩራዝዋ ተጠጋሁ። መጽሐፉን አልገለጥኩትም። እንደያዝኩት ወደ ደጅ ወጣሁ። ሙሉ ጨረቃ ደም የነከሯት መስላ ወጥታለች፤ ልብ ብዬ ሳስተውላት ፍርሐቴን አባባሰችው፤ በፍጥነት ወደ ቤት ውስጥ ገባሁ።

ዘምዘምን አሰብኳት። ይሼኔ ደብዳቤዬን አንብባዋለች። በደስታ ስትቅበጠበጥና ምላሹን ምን ብላ እንደምትጽፍልኝ ስታብሰለስል ታየችኝ። ፍርሃቴን ፍቅር አሸነፈልኝና ልቤ በድፍረት ተሞላ። ጋንጬር አባቴን አንድ ነገር እንደሚያደርገው ጠርጥሬአለሁ። በቀሌ ከማንም ከምንም የከፋ እንደሚሆን ከራሴ ጋር ተማማልኩ... ያለምንም ጥርጥር በማዘር ኢንዲያ ፊልም ላይ እንዳየሁት እንደ አክተሩ ፒቹ ሸፍታ እሆናለሁ። መጀመሪያ የአባባ ተንኩሉን ሽጉጥ ስርቄ ጋንጬርን ገድዬ ጉፋ ሰፈር ጫካ ውስጥ እሸፍታለሁ። እየተደበቅኩ ልክ እንደ ፒቹ ፊቴን በጨርቅ ሸፍኜ ሽማግሌ ወይም ለማኝ እየተመሰልኩ ሰፈራችን ቂርቆስ መጥቼ እማዬንና ዘምዘምን አጠይቃቸዋለሁ።

...አባቴ በጨለማው ውስጥ ከውጪ "ጅብ ስሪያ እጠግባለሁ ብሎ ሔዶ እራሱ ተበርሮ ይመጣል' ይላል ያገሬ ሰው!" ሲል

ተሰማኝ፤ ዘልዬ ወደ ደጅ ወጣሁ። ክኋላው ሁለት ሰዎች ተከት ለውታል። ደህና ነው።

"ማንም በማንም ላይ እየተጫወተ የኖረ የለም። ሁላችንም ከሕግ በላይ አይደለንም" አለ ሰሩሞ። በድምፅ ለይቼዋለሁ። ሌላኛውን ሰው አላወቅኩትም።

"አንተ እያለህ ነው እኛ የምንሸኘው?"

ደርሰሃል ሊለኝ ፈልጎ ነው።

"እሱ ለምን ያመሻል?"

"ዝም በል!" አለና አባቴ ገሰጠኝ፣ ፀጥ አልኩኝ።

እየተጨዋወቱ ቡናውን ጠጡ። ወሬው ሁሉ ስለ ጋንጬር ነው። ፍርሐቴን እንደገና ቀሰቀሱት። እማዬ በፀጥታ ታዳምጣ ለች። ዝምታውን የመረጠችበት አሳማኝ ምክንያት አላት። ባለፈው ስሞን ጋንጬር ሰኞ ጠዋት አባቴ በሌለበት እቤታችን መጣና ለእናቴ የአያቴን መሞት አረዳት። እናቴም በጣም ደንግጣ «የልጆቼ አያት ለኔም አባቴ ናቸው እባክህን ቀስቴዬ ለአንድ ሣምንት ታገሰኝና ቤቴን ላስተካክል» ብላ ተማፀነችው። የጆሮ ጉትቻዋንም አስይዛው ሃምሳ ብር ተበደረችው።

የፊታችን እሁድ አባቴን ሊያረዱት ተስማሙ። እህል ሸምታ በትልቅ ጋን ጠላ ጠመቀች፣ የቆሸሹ ልብሶች አጣጠበች፣ ቤቱን በቅጡ የጐደለውን አሟልታ አስተካከለች። እንዲህ ከወዲያ ወዲህ ቱር ቱር ስትል ቅዳሜ ደረሰ። ይሼንን ያልተለመደ ሁኔታዋን አይቼ በብዙ ውትወታ ምስጢር እንድጠብቅ አስምላ ነገረችኝ። አባቴ ግን የጉዳዩን ምንነት አልተረዳም።

ቅዳሜ ዕለት አባቴ ከውሎው ጠጁን ጥጉብ ብሎ ነው የመጣው። እንደገባ ረጋ ባለ አንደበት «የአባቴን ሞት ልታረጂኝ ዝግጅት ላይ ነሽ አሉ!...» አለ። ክው ብላ ቀረች። ይዛው የነበረው ውሃ የሞላ መወዘቻ ከእጇ አምልጦ መሬት ተደፋ። ፀጥ ብላ ተክዛ ከቤት ወጣች። አባቴ እግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጦ በረጅሙ ተነፈሰ። ትንሽ ፀጥ ብዬ ቆየሁና «አሁን ከማን ጋር ቆይተህ እንደመጣህ ልንገርህ?»

አፍጥጦ አየኝና «እ?» አለኝ።

«ከጋንጬር ጋር ነው። እሱ ነው የአባትህን በሕይወት መኖር ያበሰረህ፤ እዚህም መጥቶ ደግሞ ለእማዬ ሞተዋል ብሎ ያረዳት እርሱ እራሱ ነው።»

ጉርንን ባለ ድምፅ «እውቃለሁ፣ እኔም እኩ እልተሸነፍኩለትም። እያበባ እያጠጣ ነው ተቆርቋሪ መስሎ የነገር መርዙን የዘራብኝ። መጀመሪያ ስሰማ ደነገጥኩ። የአባቴን መኖር በቅርቡ ከገጠር በመጡ ሰዎች ወሬ ስለሰማሁ ተዕናናሁ። ጋንጬርን እኔ አውቀዋለሁ። ይህቺ ቂል እናትህ ግን ተታለለችለት።» አለና ትንሽ ተከዝ ብሎ «እኔ ግን ደጋግሜ እሸንፈው ነው የመጣሁት።»

«እንዴት?» የምሥራቹ ናፈቀኝ።

ከኪሱ ሚጢጢ የፕላስቲክ ሣጥን አወጣ። የእናቴ የጆሮ ጉትቻ የሚቀመጥባት ሣጥን ነች። ተቀብዬው ስከፍተው የወርቅ ጉትቻዋ

በጥጥ ተጠቅልሎ አየሁት። መልሼ ከደንኩት፣ በጣም ደስ አለኝ። «ሙዳይዋ ውስጥ አስቀምጥሳት።» አለና ቀጣዩን ሲያበስረኝ «ሁለተኛው ድል የአከመልን አርተፊሻል ዓይን ገንዘብ ጨምሬ አስለቅቄለታለሁ። ለእኛ አርተፊሻል ይሁን እንጂ ለእሱ ያው ዓይኑ አይደል? ስነብስ ይሆነኛል ብዬ ነው ይኼን ያደረግኩት። ሦስተኛው ድል በጠጅ ፈረስ ገስግሰህ ድረስ ብሎ ሲልከኝ ቆም ብዬ አሰብኩና ብልህ ሆንኩበት እንጂ ገስግሼ ደርሼ ቤቴን እንዳፈርስ ነበር የላከኝ። አንተ እኔን ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?» ልል አባቴ ድንገት ጠየቀኝ።

የሚመር ምራቅ እንደገና አፌን ሞላው፣ ተቁነጠነጥኩና ፀጉሬን ነጨሁ። ሁኔታዬን እየና «አንድ የአገራችንን ተረት ልንገርህ?» ሲል አባቴ ወጉን ጀመረ። በባህርይው በውሳቹ መሐከል የሚመጡለትን ዘይቤያዊ አባባሎችም ሆነ፣ ተረት እንደ ጨዋታው አመጣጥ አስገብቶ ማውጋት ልማዱ ነው። ይህ አይነቱ ተረት እምነቱንና እመለካከቱን ስብሰብ እድርጉ የማሳየት ኃይል አለው። በድንገት ተረት አውራልኝ ስለው ግን ይጠፋብታል።

«በድሮ ጊዜ እኛ አገር ጋሞጉፋ ውስጥ እባትና ልጅ እየተ ጨዋወቱ መንገድ ይሔዳሉ። በመንገድ ዳር ሞቶ የተጣለ አባብ አዩና አባትየው ልጁን ልጄ እኔ ላንተ ያለኝን እውነተኛ ሃሳብ ብናገርና እንተም ስለኔ ያለህን ምኞት ብትነግረኝ ይህ አባብ ከሞት ይነሳል አለው። አባትና ልጅ ተስማምተው ሲጨዋወቱ አንተ ልጄ እድገህ ለውግ ለማዕረግ አብቅቼህ ማየቴ ታላቅ ምኞቴ ነው ይላል አባት፣ ልጅም፣ እኔ ደግሞ አባቴ ሲያረጅ በአግባቡ ጠሬው ደስ አስኝቼው ሲሞት በውግ በማዕረግ አልቅሼ አስለቅሼ እቀብረዋለሁ አለ።

«እቡብን ሲያዩት ከሞት አልተነሳም። አባትም ይሔን አየና ከሁለት እንዳችን እውነት አልተናገርንም። ልጄ እመነኝ እኔ ቀደም ብዬ ያጫወትኩህ ሃሳብ ከአንጀቴና እውነቴን ነው አለው።»

ልጅም፣ «አባቴ እኔ ነኝ የዋሸሁት። በአሁኑ ጊዜ የማስበው አባቴ ሞቶልኝ፣ ይሔንን እንደልብ የሚታረስ መሬት ወርሼ፣ በንጋ ፈረሶን ጋልቤ፣ ጋሻ ጦሩን አንግቼ... እያልኩ አስባለሁ» ሲል ልጅ፣ አባቡ ነፍስ ዘራና ወደ ጥሻው ገባ።

አባቴ ውስጤን ያየ መስሎ አስደነገጠኝ። ይሔንኑ ችግር በሌላ ቤተሰብ የደረሰ አስመስዬ ለዘምዘም አንድ ቀንለታ አውርቼላት ነበር። ምላሽዋን ስታጫውተኝ «አንድ የአረቦች ተረት አለ 'አላህንም እመን ግመልህንም እስር' ይላሉ። እንዲህ አይነት ችግር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሲፈጠር አዋቂ ሰዎች ችግሩን ለመፍታት ትእግስትና ብልሃቱን አላህ ያመላክታቸዋል። ልጆች ግን ከእነሱ ብልሃቱን መማር አለብን ብላኛለች። ይህ እባባሷ የአባቴን አስተዋይነትም አመላክቶኝ።

«ችኩል በሬ ያልባል' ይላል የአገሬ ሰው፣ ጐረምሳም እንደ ችኩሉ ሰው ነው። እንተ አሁን የሚገባህ አርፈህ ትምህርትህን ተምረህ ትልቅ ቦታ መድረስ ነው እንጂ በእኛ ጣጣ ውስጥ እንድትገባ አልፈልግም። የጋንጩርን ነገር እርሳው። ጉዳዩ የእኛ የድሆቹ ብቻ ሳይሆን የመንግሥትም ሆኗል። ኮንትሮባንድ ጠብመንጃ ይነግዳል። በዚህ ወንጀል መንግሥት ፈርማቶሪውን ልክ እየተከታተለው ነው። ጠላ

ትነቱ የእኛ ብቻ ሳይሆን የንጉሠ ነገሥቱም ነው» ያለኝን አስታወስኩ። እንዲህ ስንመካከር አመሸን። እናቴ ግን እንዳከረፈች ነው። አባቴ ከእኔ'ጋ በፈጠረው ሰላም ደስ ብሎት «እሷን ተዋት እንደጉደታ 'ዱቢን ሃቡሉ' እንባባል።» ብሎ በሰላም ወደመኝታው እየሔደ «ቤታችን ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ሰሞኑን እንዲት ጠቦት ገዝተን እናርዳስን» አለኝ።

«እኔም አንድ ብር አዋጣለሁ» አልኩት።

«እምጣ! ጉራጌዎች ሲተርቱ 'ለሚጥሚጣም ያዋጣ ለበሬም ያዋጣ እኩል ነው» ይላሉ።

አንድ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት።

እየሳቀ «አንተም ስታድግ ለልጆችህ ይኼን ማድረግ እንዳትረሳ» ብሎኝ ልብሱን አውልቆ ተኛ።

ጋሼ ጉደታን አስታወስኳቸው። ጋሼ ጉደታ በመንደራችን በነገር አዋቂነታቸው የተከበሩ ሽማግሌ ናቸው። ትልልቅ ሰዎች ሲናገሩ እንደምሰማው ሲፈጠሩም ዳኛ ሆነው ነው የተወለዱት። አንዳንዴ የዕርቅ ሥርዓት ይዘው በሚመሩበት ጊዜ በሁለቱም አቅጣጫ ተበደልኩ ባሮች ነገሩን ሲያከሩት ጉዳዩን በይደር ለማየት 'ዱቢን ሃቡሉ' ይላሉ። ነገሩን በይደር እንያዘው እንደማለት ነው።

ራሳቸው ጋሼ ጉደታ ሲናገሩ እንደሰማሁት በአሮሞ ባህል ዕልባት ያልተገኘለት ጉዳይ በይደር እንዲታይ ይሆናል። ዐበኞቹም ሌሊቱን ሲያብሳሉ ሲያወጠነጥኑት ያድራሉ። ዳኛውም ግራ ቀኙን ለማስተዋል ፋታ ይኖረዋል። ትናንትና አስፊሪ የነበረው ነገር ማለፊያ መፍትሔም ይገኝለታል። ጋሼ ጉደታም ከዘር ማንዘራቸው በወሰዱት ቱባ ባህል ላይ የከተሚውም አስተሳሰብ በቅጡ የገባቸው በመሆናቸው፣ መንደራችን ውስጥ አንድ ችግር ተፈጥሮ በአካል ከተገኙ ሰላም እንደሚያወርዱ የታወቀ ነው። በዚህም 'ዱቢን ሃቡሉ' በስፈራችን ታዋቂ ቃል ናት።

ውድቅት ላይ የጠላው ጋን ጳ ብሎ ፈነዳ። «ተመስገን ጦሴን ይዞ ይሂድ!» ስትል እማዬን ሰማኋት። ከሃሳቤ ተመለስኩ።

ዛሬም ሰሩም «ሁላችንም ከሕግ በላይ አይደለንም» ያለው ትዝ አለኝና ጋንጩር የእጁን ማግኘቱ እንደማይቀር ገባኝ። ለዚህ ነው እማዬ ዝምታውን የመረጠችው። እንደተለመደው የቀረበው ቡና ተፈልቶ ተጨዋውተው ዘመዶቻችን ወደየቤታቸው ሔዱ።

ነገ ምን ይዛ እንደምትመጣ እያብሰለሰልኩ ወደ መኝታዬ ሄድኩ። ዘምዘም በሃሳቤ እንደገና መጣች። ልቤን ሞቅ አድር ጋው ዛሬን ድል መትተን ነገ በአረፋ በዓል እንደምንገናኝ ተስፋ እያደረግኩ፣ ፍርሐትና ፍቅር እየተፈራረቁብኝ ለመተኛት ሞከ ርኩ። እንቅልፌ ቶሎ አልመጣም። ከፉውንም ደጉንም እያሰ ብኩ፣ እንቅልፍም ትንሽ ሸለብ እያደረገኝ፣ አስፈሪው ሌሊት አልፎ ንጋት ተተካ።

ዛሬ የአረፋ በዓል ነው። እዚያው አልጋዬ ላይ ተንጋልዬ አብሰ ለሰላለሁ። አባቴ በሌሊት የሠራውን ሸማ ለደንበኞቹ ለማድረስ ሔዷል። እናቴ የዕለት ሥራዋን ታከናውናለች። ማሚቴ ዕንቅልፏን አልጨረሰችም። እንዲተኮስልኝ በጥንቃቄ አጣጥፌ ከካሊሙ ስር

የተኛሁበትን ሱሪዬንና ሸሚዜን ለበስኩ፡ ጀኬቴን ደረብኩ፡ እማዬ በእስር ብር የገዛችልኝን ዳርማር የቆዳ ጫማዬን ተጫማሁ፡፡ ቁርሴን ስበላ ውጭ የነበረችው እማዬ ወደ ቤት እየገባች ግርግዳ ላይ የሰቀ ልኩትን የኢትዮጵያ ካርታ አስተዋለች፡፡ ከዚህ በፊት ስትመለከተው አይቼአት አላውቅም፡፡ ፊቷን ወደእኔ ሳትመልስ «ከፋ ጅማ የትኛው ነው?» አለች፡፡ እገሯ እዚጂ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነው፡፡ አሁንም እንዳ መረረች እንደሆነ ገባኝ፡፡ ፍርሐቴም ተቀስቀሰ፡፡ ቀደም ብሎ በቤተ ሰባችን ውስጥ መኳረፍ ሲፈጠር ሽማግሌ መሐከላቸው ሳይገባ ለዕለታት ተኳርፎ መታረቅ የተለመደ ነበር፡፡ አሁን ግን በእናቴ ማምረር ጉዳዩን ለአባ ዘለቀና ለጋሼ ጉደታ መንገር እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡ ከሲኒማ እንደተመለስኩ ይሔን ውጥኔን ተግባራዊ አደርገዋለሁ፡፡ ወደ ካርታው ጠጋ ብዬ በጣቴ ጠቆምኳት፡፡ ገባኝ በማለት ስሜት ጭንቅላቷን ወዘወ ዘች፡፡ ካርታው ላይ አፍጣ በትክዜ ስሜት ውስጥ እንዳለች "አንዲት ልጅ ውጪ ትፈልግሃለች" በማለት መልእክት ነገረችኝ፡፡

ደነገጥኩኝ፡፡ ዘልዬ ወጣሁ፡፡ ዘምዘም ነች፡፡ እንደ ወርቅ በሚያብረቀርቅ ውብ ልብስ ተሽቀርቅራለች፡፡ ፊቷ ሳቅ በሳቅ ሆኗል፡፡ እጅዋን ለሰላምታ ዘረጋችልኝ፡፡ ስለተደናገጥኩኝ እልጨበ ጥኳትም፡፡ ከመንደሩ እንድንወጣ ከንፈን ይገፍ በፍጥነት መራመድ ጀመርኩ፡፡

ሳቋ ሳይከስም "አንተ ስታደግ በጣም ጎበዝ ደራሲ ነው የምትሆነው» አለችኝ፤ የወፍ ዝማሬ በመሰለ ድምፅዋ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ፊቴ ፏ! ብሎ ሲፈካ ይሰማኛል፡፡

ሳብሰለሰል አውነት አላት፡፡ እናቴ የምትነግረኝን አንዳንድ ታሪኮችና በሃሳቤ የሚመላለሰውን ርዕስ ጉዳዮች መጻፍ ጀምሬ ያለሁ፡፡ ይህ ታዲያ ደራሲ ያደርጋል? ራሴን የጠየኩት ጥያቄ ነው፡፡ ደራሲ ለመሆን እንዴት እንደሚጀመርም አውቀቱ የለ ኝም፡፡ መምህራኖቻችንም የሚወዱትን ታሪክ ከማንበብ ውጪ አንድ ደራሲ በወጣትነቱ ወቅት እንዴት መጻፍ እንደሚጀምር ምንም የሰጡን ፍንጭ አልነበረም፡፡

እሷ ግን በጻፍኩላት የፍቅር ደብዳቤ ሃሳብ ድል ተመትታ የወደፊቱን እኔነት ተንብያለች፡፡ ዘምዘም በጅምር ፍቅር ታውራ ልብ አላለችም እንጂ፣ የጻፍኩላት የግጥም ደብዳቤ ውስጥ ግን አንዳም ሃሳብ የኔ አይደለም፤ እሷን እያሰብኩ ከከበደ ሚካኤል ትርጉም ሥራ ከሮሚዮና ጁሊዬት፣ ከሚባለው መጻሕፍና ከሌሎች ደራሲያን ፈጠራ ውስጥ በርካታ ሃሳቦችን ወስጃለሁ፡፡ ሮሚዮ ሮሚዮ የሚለውን ቃል እየገደፍኩ ዘምዘም፣ ዘምዘም ብዬ ጻፍ ኩኝ፡፡ ከዚያም፣ ከዚህም መጻሕፍት የኮረጅኩት ሃሳብ ደብዳ ቤዬን የተሟላ አደረገልኝ፡፡ ሃሳቡ ለባለመብቷ ደርሶ ስታነበው ሙሉ ስሜት ፈጥሮላታል፡፡ በዚህም እኔ ሳድግ ጎበዝ ደራሲ እንደ ምሆን አምናለች፡፡

ለራሴ ታማኝ ለመሆን በማለት "ዘምዘም እውነቱን ልን ገርሽ፣ እኔ ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩልሽ ከከበደ ሚካኤል ድርሰት ውስጥ ..." ብዬ ሃሳቤን ሳልጨርስ፡ ከአፌ ነጥቃኝ "ይሁና! የም ታነበው ለምንድነው? አውቀህ ጥሩ ልጅ ለመሆን ቆንጆ ቆንጆውን ትወስዳለህ፡፡ አንተ ደግሞ እኔን ስለምትወደኝ ደስ ያለህን ሃሳብ ጽፈህልኛል፡፡ እሳቸውስ ለእኛ የጻፉልን ከሼክሲፒር ድርሰት ወስደው አይደለም? አሁን እኛ እንግሊዘኛ በደንብ ስለማናነብ ነው እንጂ፣ አድገን በእንግሊዘኛ ስናነብ ሺክስፒርም ከማን እንደወሰደ እናውቀዋለን፡፡"

አከመችኝ፡፡ ነፍሴ በፍቅር ጀልባ መንሳፈፍ ጀመረች፡፡ በእግር እየተንሸራሸርን የማያልቅ ወሬያችንን ጀመርን፡፡ ሜንታ ከረሜላ ሰጠችኝና እየመጠጥኩ "ስለ ደብዳቤው ከአህመድ ጋር አውርተሻል?"

"ጠይቄዋለሁ፣ በብልሃት፡፡ 'ሰዎች ከሰዎች ነው የሚማ ሩት፡፡ ለምሳሌ የእኛን አገር ቀደምት ዘመናዊ ዘፋኞች ብትወስጂ በርካታ ዜማዎቻቸው ከሱዳን ዘፋኞች የተወሰዱ ናቸው፡፡ የድር ሰትም ሃሳብ አንዱ ደራሲ ከሌላው እየተማረ ነው የራሱን ችሎታ የሚያዳብረው፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላም ወደ ራሱ ችሎታ ይመለሳል' ብሎኛል፡፡ በዚህ ነው ያንተን ስታድግ ደራሲ መሆን የኅ መትኩት፡፡"

'ወይኔ! እኔም ታላቅ ወንድም ቢኖረኝ እንዳንቺ ያስረዳኝ ነበር!' አልኩ በልቤ፡፡

"በእግራችን እንሂድ ወይስ በሴቼንቶ?"

"እኔ ከአንቺ ጋር ስሄድ የትም ቢሆን አይደክመኝም፡፡ ከፈለግሽ በእግራችን እንሂድ፡፡"

"እኔም ከአንተ ጋር ስሆን የትም ብሄድ አይደክመኝም፡፡ ግን ግጥሙን ስትጽፈው ለምንድነው?

ዘምዘሜ ዘምዘሜ የልቤ ወለላ

እባክሽ ስምሽን ለውጭው በሌላ ያልከው? ዘምዘም ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆን ታውቃለህ?"

"አላውቅም፡፡"

"የኅኑት ውሃ ማለት ነው፡፡ ልክ እንደጠበል፣ እ? ስለዚህ 'ዘምዘሜ፡ ዘምዘሜ የልቤ ወለላ' ያልከው እንዳልከው ይሁን፡፡ አባ ክሽ ስምሽን ለውጪው በሌላ' ያልከውን ግን አስተካክልልኝ፡፡"

መደምደሚያውን ማግኘ ጀመርኩ፡፡ ሳብሰለሰል፣ እኔን ከሷ ባቆራኘ መልኩ የሚቋጭ ስንኝ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ በሃሳቤ ምጤን ቀጠልኩ፡፡

ግራ እጇን በቀኝ እጅዋ አቅፋ ይዛለች፡፡ ቀደም ብሎ ግር ይለኝና ያሳፍረኝ የነበረው ስሜት ለምጂው ሐፍረቱ ከተወኝ ሰነባብቷል፡፡

"ለምን ዝም አልክ? አታወራም እንዴ?"

"እያሰብኩኝ ነው?!"

"ስለምን?"

"ስላንቺ፡፡"

ለሃሳቤ ተወችኝ፡፡ እሷም ደስ ብሏት ስለእኔ ማሰብ የጀመረች መሰለኝ፡፡ መንታዎቹን ሱቆች አልፈን ሽቅብ የሚያወጣውን አስፋልት መንገድ ያዝነው፡፡ እንደለመደችው ክንዴን ከክንዷ ጋር አቆላልፋ ይዛለች፡፡ ሽቅብ ወጣን 'አይ ክራይ' የተባለው ሙዚቃ ከመላ ሻይ ቤት ይሰማል፡፡ አረማመዳችን ከሙዚቃው ጋር አንድ ሰልት ያዘ፡፡

መኩዬ ቀጫጫው መላ ሻይ ቤት በር ላይ ቆማ ጥርሷን ትፍቃለች፡፡ እንዳየችን ጥርሷን መፋቅ አቆመች፡፡ አንድ አስገራሚ ትዕይንት ድንገት ያየች ይመስል ጥቂት ፈዘዘ፣ ወዲያው ነቃች፡፡ ሻይ ቤት ገብታ ሲባይ ንቢጥንና ኃይሉ ዶሮን እስክትላ ወጣች፡፡ ሁሉም በመደነቅ አፈጠጡብን፡፡

ዘምዘም "ተመልከት" አለች በሹክሹክታ፡፡

ደስ አለኝ 'ገርጋጅ' አለመሆኔ ዛሬ ለተወሰኑት ጓደኞቼ ተገ ለጠላቸው፡፡ እንዳይለክፉኝ "ሕፃን አትሁን" መባባል ስለጀመርን ክብራቸውን እንደጠበቁ ፀጥ ብለው አሳለፉን፡፡ ሙዚቃው እንደ ቀጠለ ነው፡፡ 'አይ ክራይ...' እኛም በሰልት፣ የሙዚቃውን ምት ተከትለን በቄንጥ እየነጠርን ሽቅብ አዘገምን፡፡

ዞሬ ላይ ሦስቱም ጓደኞቼ እያንሾካሾኩ በርቀት የመጨረሻችንን ለማየት ይከተሉናል፡፡ የጉቢጥ የኒውክሌር ዐምብ የመሥራት ዕቅድ ትውስ አለኝ፡፡ ይሔን ምስጢር የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፡፡ በምስጢር መጠበቅ የዘምዘምን ታላቅ ፍቅር እንዳፈራሁበት ሁሉ ለግዩንቲስቱ ጉቢጥም ምስጢረኛነቴ እንደቀጠለ ነው፡፡ ዛሬ ግን ከዘምዘም ጋር መታየቴ ለጓደኞቼ አጓጊና ከሁሉም የላቀ ምስጢር ነው፡፡ እርግጠኛ ነኝ ግታ ከሲኒማ ስመለስ ሦስቱም ጓደኞቼ እዋዋሌን ለመስማት እቤቴ ይጠብቁኛል፡፡ እንዲህ አይነቱን ከቆንጆዎች ጋር የምናሳልፈውን ጊዜ ማውራት ከሚያስደስቱን ጉዳዮች መካከል እንዱ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ ይህ አይነቱ የባህርይ ለውጥ በሁለቱም ዓለማቶች መካከል የሚታይ እንደሆነ እየተገነዘብኩ መጥቻለሁ፡፡ እሁን ግን ዘግተናቸው አለፍን፡፡

ሪቼ መዝናኛ አካባቢ ለንደርስ በሯ ከፊት ወደኋላ የምት ከፊት ሴቼንቶ መጣች፡፡ አስቁመን ከኋላ ተሳፈርን፡፡ ሁለታችንም ተጠጋግተን ተቀመጥን፤ አልተነጋገርንም፡፡ እኔ የግጥሜን ማሳረጊያ አብሰለሰል ጀመር፡፡

ዘምዘሜ ዘምዘሜ የልቤ ወለላ
ፍቅርሽን ጠብቂው እባክሽ በትጋት

ቤት አልመታልኝም፡፡ ከፊት ወንበር ላይ አንድ የጦር ሠራዊት መኮንን ተቀምጧል፡፡ ጢሙን የጎንዮሽ እየቋጨ ሰረቅ አድርጎ ያየናል፡፡ ወደ ዘምዘም ዞሬ አየሁ፡፡ "የትኛው ሲኒማ ቤት ነው የምንገባው?" አለችኝ፡፡

"አሪፍ ፊልም ያለው ሲኒማ አምፕር አይደል? ናይት ኢን ለንደን ደስ የሚል የሕንድ ፊልም ነው፡፡ በዚያ ላይ አሪፍ ቴክስ ጌሪኩፐር ነው ስታሩ፣ በተጨማሪም ቆንጆ ዲቴክቲቭ እንዳለ ከጓደኞቼ ጠይቂ ነግሬሽ የለ?"

"አዎን፣ ረስቼው ነው፡፡"

"ሲኒማ ልትገቡ ነው?" አለ ጥልቅ ብዬው መኮንኑ፡፡

"አዎን" አለችና አፈጠጠችበት፡፡ ማንም በእኔና በእሷ መካከል ሲገባ አትወድም፡፡

"ለልባም ልጅ ሲኒማ ማስተዋልን ይጨምርለታል፡፡"

ዝም አልነው፡፡ በፀጥታ መንገዶቹን በሴቼንቶ አቆራርጠን ፒያሳ ሲኒማ ኢትዮጵያ ደጅ ላይ ወረድን፡፡ ሽልንጉን ለባለ ሴቼንቶው ዘምዘም ከፍላ "ና ኬክም ባቅላባም እጋብዝሃለሁ፡፡ ባቅላባው በጣም ጣፋጭ ስለሆነ አንዱንም አትጨርሰም፡፡"

"እረ? እኔ እኮ ስፖርተኛ ነኝ፡፡ ሁለት ሶስትም ብትገዢልኝ እጨርሳለሁ" አልኳት፡፡ ባቅላባ ዝናውን ሰምቻለሁ እንጂ በልቼው አላውቅም፡፡ ገብረተንሣይ ኬክ ቤት ይዛኝ ገባች፡፡ ሁለት ባቅላባና ቡና በወተት፣ አዘዘች፡፡

'ፍቅርሽን ጠብቂው እባክሽ ዘላለም' አልኩ በሃሳቤ ቡና በወተቱን ፉት እያልኩኝ ደገምኩት፡፡ ስሜት ሰጠኝ 'ፍቅራችንን ጠብቂው እባክሽ ዘላለም' ብለው የተሻለ እንደሆነ ገባኝ፡፡ አሁንም ቤቱን ሰቻለሁ፡፡

"ባቅላባው ቀርቧል"

ባነንኩኝ፡፡

"አበላሉን አሳይኝ?"

ባቅላባውን በቢላ ቆራረሰችውና በሹካ ወጋ አድርጋ አሳረሰችኝ፡፡ አበላሉን እኔም ከእሷ ኮረጅኩ፡፡ የባቅላባውን አኮራረጅ ያህል ለምን ግጥሙ አልሰመረልኝም?

"ይህንን የጥላሁን ገሠሠን ዘፈን እወደዋለሁ፣ ስማው" እለቺኝ ዘምዘም፡፡ ጆሮዎቼ ተክፈቱ፡፡

ተማሪ ነኝ ያልገባኝ
የምታውቂ አስረዱኝ!!

ተ ፈ ጸ መ

የፀሐፊው ቀደምት ሥራዎች

1. ሕይወት በባህር ውስጥ ጥር 1985 ዓ.ም
   * የባህሩንና የውቅያኖሱን ሕይወት የሚያስቃኝ::
2. ማስታወሻ መጋቢት 1993 ዓ.ም
   * በደራሲ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ግለ ታሪክና ኪነጥበባዊ ክህሎት ላይ የተጻፈ::

ማስታወሻ

